

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች ቅጽ-17

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# ሰበር ችሎት ውሣኔዎች



ቅጽ-17

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት

# የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ-17


የኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሲ ሪፐፐሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ጥቅምት 13, 2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ



<u>የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

የሰበር ውሳኔዎችን ለሕዝብ ለማዳረስ እየተደረገ ያለው ጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች እየታዩበት ነው፡፡ ከሰበር ውሳኔዎች አስገዳጅነት አንጻር ውሳኔዎቹ እንደተሰጡ ወዲያውኑ ለሥር ፍ/ቤቶች ሆነ ለሌሎች አካላት መድረስ ይኖርባቸዋል፡፡ አትሞ ማሰራጨት የቱንም ያህል ለማፋጠን ቢሞከር ጊዜ መውሰዱ አይቀርም ፡፡በአሁኑ ጊዜ የኢንተርኔት አገልግሎት እስከ ወረዳ ድረስም ስለደረሰ ውሳኔዎቹ በተሰጡ ጥቂት ቀናት ውስጥ በፍ/ቤታችን ድረ ገጽ በመጫን ተደራሽ ለማድረግ እየሰራን ነው፤የዚህን እትም ውሳኔዎችና የበፊቶቹንም በድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል፡፡ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ አገልግሎታችንን ለማሻሻል የሚረዱ አስተያየቶችን ለመቀበል ዝግጁ ነን፡፡

**ተገኔ ጌታነህ**

**የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት**

## 2007 ዓ.ም. የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች

## ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | | 1 |
| 1. | ቤትና ይዞታን በሚመለከት በሚደረግ ክርክር አንድ ጣልቃ ገብ አመልካች ክርክር በሚደረግበትቤትና ይዞታ ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር መብት አለኝ በማለት መብቱን የሚያሳዩ ሰነዶችን አቅርቦ እያለ የባለይዞታነት ወይም የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አላቀረብክም ተብሎ ከወዲሁ ጣልቃ ገብተህ ልትከራከር አትችልም ተብሎ አቤቱታውን ውድቅ ማድረግ አግባብነት የሌለው ሥለመሆኑ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41 | 90713 | ወ/ሮ አሚና ሰይድ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ወለላ ንጋቱ -/ሁለት ሰዎች/ | መስከረም 29 ቀን 2007 | 2 |
| 2. | ተከራካሪ ወገኖች ለፍ/ቤት የሒሳብ አጣሪ ይሾምልን የሚል አቤቱታ ሲያቀርቡ በሒሳብ አጣሪዎች ሪፖርት አለመስማማት ቢኖር እንኳ ጉዳዩ የንግድ ህጉንና የፍትሐብሔር ሥነ-ስርዓቱን መሠረት በማድረግ ውሣኔ በዛው በኩል እንደሚሠጥ በግልጽ ከተስማሙ ይህ ግልጽ ስምምነት ባለበት ሁኔታ የሒሳብ አጣሪዎች የስራ ክንውን ግድፈት አለበት በማለት ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት የሚያቀርቡበት ህጋዊ | 93239 | የአቶ አበበ ክብረት ሚስትና ወራሾች<br>እና<br>አቶ ነጋ ቦንገር (አስር ሰዎች) | ጥቅምት 25/2007 | 5 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ምክንያት የሌለ ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 277(1)(2) ፣የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3312 | | | | |
| 3. | በህግና በሚመለከተው መንግስት አካል እውቅና የተቋቋሙ ማህበራት የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማሳካት፣የአባላታቸውን መብትና ጥቅም ለማስከበርፍ/ቤት፣ለግልግል ተቋም ወይም ለሌሎች የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት የዳኝነት ጥያቄ የማቅረብ መብት ያላቸው ስለመሆኑ፣<br><br>የፍትሐ ብሔር ህግ ቁጥር 454(1)<br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 35<br>አዋጅ ቁጥር 62/2001 አንቀፅ 55፣110 | 100631 | ሮፓክ ነዋሪዎች ማህበር<br>እና<br><br>ሮፓክ ኢ/ኃ/የ/የግ/ማህበር | ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም | 9 |
| 4. | በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 74(2) መሰረት ፍ/ቤቱ የተዘጋን የይግባኝ አቤቱታን እንደገና ስለሚያይበት አግባብ፣ | 94511 | እነ ወ/ሮ ብዙ ሰንበታ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ታደሰ ሰንበታ | 30/01/2007 ዓ.ም. | 13 |
| 5. | የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የፍትሐብሔር ሥነ- ስርዓት ህጉ በሚያዘው መሰረት ሥርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ ከሆነ ዳኝነት ሊሰጥበት የማይችል ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 234(1)፣(2) | 94713 | እነ ህፃን ሰኢድ ዘውዱ(ሦስት ሰዎች) እና<br><br>እነ ወ/ሮ ጥሩ ሰው ሞሳ<br><br>(ዘጠኝ ሰዎች) | መጋቢት 16 ቀን 2007 | 16 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 6. | አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት (ሰበር ሰሚ ችሎት )የሥር ፍ/ቤት ጉዳዮን አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች ሁሉ አጣርቶ እንዲወስን ብሎ አንድን ጉዳይ ሲመልስ ስለማስረጃ አቀራረብ በህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ሁሉ ባላገናዘበ መልኩ ማስረጃ ይቅረብ ማለት ስላለመሆኑ፡-<br><br>ለአንድ ጉዳይ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች መቅረብ ያለባቸው ለህጉ የተዘረጋውን ሥርዓት ጠብቀው ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑና ተገቢውን የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ሳይጠብቅ የሚቀርብ ማስረጃ ግን ዋጋ ሊሰጠው የማይገባና ውድቅ ሊደረግ የሚገባ ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 137(3) እና 256 | 97217 | አቶ ባካፋ አንለይ<br><br>እና<br><br>አቶ ቴዎድሮስ አንለይ | መጋቢት 16 ቀን 2007 ዓ.ም | 21 |
| 7. | በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ መብት አለን ብለው ተቃውሞ የሚያቀርቡ ሠዎች በንብረቱ ላይ ያላቸውን የቀዳሚነት መብት ወይም ባለይዞታነት ለማረጋገጥ በጽሁፍ ማስረጃ ብቻ ሳይወሠኑ ሌላ ማስረጃም ሊያቀርቡ የሚችሉ ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.418/3/ እና የፍ/ህ/ቁ 1193/1//2/ | 97094 | ወ/ሮ አስቴር አምባው<br><br>እና<br><br>እነ አቶ አበባው ክፍሌ/ሁለት ሰዎች/ | ሕዳር 08/2009 | 28 |
| 8. | በሞተ ሰው ስም ቀደም ብሎ የተሰጠን ውክልና በመያዝ የሚቀርብ ክስ ፣የሚደረግ ክርክር እና የሚሰጥ ውሣኔ እንዳልቀረበ እና ውሣኔም እንዳልተሰጠ የሚቆጠር ስለመሆኑ፣ | 95587 | ወ/ሮ ሀዋ በከር እና<br><br>እነአቶቶፊቅመሐመድ(ሁለትሰዎች ) | ጥቅምት 28/2007 | 31 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2232(1)<br><br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 57 | | | | |
| 9. | የፍርድ ባለዕዳ ንብረት የሆነ ለፍርድ ማስፈፀሚያ ተብሎ በጨረታ ከተሸጠ በኂላ በሐራጅ ላይ ጉድለት አለ፣የጨረታ ሽያጩ ይሰረዝ የሚል አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ ሽያጩ ሊሰረዝ ይገባዋል? ወይስ አይገባውም? በሚለው ላይ መከራከር ያለባቸው የፍርድ ባለዕዳና ባለገንዘብ ብቻ ሳይሆኑ ንብረቱን በሐራጅ አሸንፎ የገዛው 3ኛ ወገንም ጭምር ስለመሆኑ፡<br><br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 32፣39፣40፣79 እና 370(3) | 97332 | አቶ ከይምር በላይ<br><br>እና<br><br>እነ አንዱአለም አሻግሬ | መጋቢት 30 ቀን 2007ዓ.ም | 34 |
| 10. | ሌሎች ሰዎች በሚከራከሩበት መዝገብ ለክርክሩ መነሻ ከሆነው ንብረት ውስጥ በአንደኛው ወገን ጠያቂነት የታገደን ንብረት ሌላ ሶስተኛ ወገን ለሌላ እዳ አፈፃፀም ንብረቱን ሥለምንፈልገው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 158 መሰረት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ይነሳልኝ ብሎ አቤቱታ አቅርቦ ዕግዱ ሊነሳ አይገባም ተብሎበሚሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ በሚጠየቅበት ወቅት ከስረ ነገር ውሳኔ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም ሊባልየማይቻል ስለመሆኑ፡-<br><br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320(3) | 101632 | አቢሲኒያ ባንክ<br><br>እና<br><br>ወ/ሮ ዘይቱ ከማል | መጋቢት 4 ቀን 2007 | 38 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 11. | በፍርድ የተከለከለ ሰው የፍቺ ጥያቄ ስለሚያቀርብበት አግባብ | 103781 | ወ/ሮ አስካለ አሸኔ<br>እና<br>አቶ ታምራት ተስፋዬ | መጋቢት 17/2007 ዓ.ም | 41 |
| አሠሪና ሠራተኛ | | | | | 43 |
| 12. | በስራ ክርክር የተከራካሪ ወገኖች ማንነት የፍርድ ቤቶችን ስልጣን (የክልል ወይም የፌዴራል)ብሎ ለመወሰን እንደወሳኝ መለኪያ ሊወሰድ የማይገባ ስለመሆኑ፤<br>የአሰሪው እርምጃ ህገ ወጥነት የተረጋገጠ እንደሆነ የክፍያ መጠኑ ሊሰላ የሚገባው አዋጁ ባስቀመጠው ስሌትና በማስረጃ በተረጋገጠ የደመወዝ መጠን መሆን ያለበት ስለመሆኑ፣<br>አዋጅቁጥር377/1996አንቀፅ 35(1(ለ))፣39(1(ለ))፣40(1)(2)፣43(4(ሀ)፣68፣71 | 95638 | ኢስት ሲሜንት አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>አቶ ዘላለም ታደሰ | መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ/ም | 44 |
| 13. | በሠራተኛው የሚጠየቅ የውዝፍ ደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በአሠሪው የይርጋ መቃወሚያ ካልቀረበበት በስተቀር ተከፋይ ስለመሆኑ::- | 101020 | አቶ ዳዊት ገ/ማርያም<br>እና<br>አቶ ሣህለማርያም ደግፌ | መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ.ም | 52 |
| 14. | አንድ ባለሙያ በአሠሪው ቁጥጥር ሳይሆን በራሱ የሙያ ኃላፊነት የሙያ አገልግሎት ለመስጠት ከአንድ አሠሪ ጋር ውል ሲኖረው ጉዳዩ የሚገዛው በአሠሪና ሠራተኛ ህግ ስላለመሆኑ፣ | 101396 | አዲስ አጠቃላይ ሆስፒታል<br>እና<br>ዶ/ር ምስራቅ ጥላሁን | ታህሳስ 21/2007 | 55 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | -ከአንድ ባለሙያ ጋር የሙያ ግልጋሎት ውል ያለው አሠሪ ውሉን በማናቸውም ጊዜ ማፍረስ ሥለመቻሉ፣<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀስ /1//2/<br>የፍ/ህ/ቁ. 2140፣2646/1/፣ 2638/1/ | | | | |
| 15. | ከአሠሪና ሠራተኛ ክርክር ጋር በተነሳ ማንኛውም የሠራተኛ ክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የዕዳ ጥያቄ ቅድሚያ የሚኖረው ለሠራተኛ እንጂ ለስራ መሪዎች ስላለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 2(2)(ሐ) (3)፣167 | 101913 | አቶ መላኩ ሙሉጌታ<br><br>እና<br><br>አቶ አበበ አቡራ | የካቲት 17 ቀን 2007ዓ.ም | 59 |
| 16. | አንድ ተማሪ በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ ህገመንግስታዊ መብት ያለው ስለመሆኑ፡-<br><br>አንድ አስተማሪ የሚያስተምራቸውን ተማሪዎች በአግባቡ የመቆጣጠርና የመከታተል ህጋዊ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑና ይህንን ግዴታውን ተላልፎ ተማሪን ቢደበድብ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል በቂ ምክንያት ስለመሆኑ፡<br><br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በአንቀፅ 16<br><br>የፍ/ሕ/ቁ 2124 እና 2125<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27(1)(ቀ) ፣አንቀፅ 14(2)(ሀ) | 103209 | አትላስ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ት/ቤትእና<br><br>ወ/ሪት መስታወት ስመኝ | የካቲት 16 ቀን 2007ዓ.ም | 62 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 17. | የዓመት ዕረፍት ክፍያ አስፈላጊው የገቢ ግብር ተቀንሶ ለሠራተኛው ሊከፈለውየሚገባ ስለመሆኑ:-አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 27(ሐ)፣36፣37<br><br>የገቢ ግብር አዋጅ 286/94 እና ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀፅ 3 | 101040 | አቶ አየለ መንግሥቱ<br>እና<br><br>የኢትዮጲያ እህል ንግድ ድርጅት | መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም. | 66 |
| 18. | አንድ አሠሪ ለሙከራ የቀጠረውን ሠራተኛ በቀጠረው በ46ኛው ቀን ለስራው ብቁ አይደለም ብሎ የስንብት ደብዳቤ ቢጽፍለት ድርጊቱ ህገ ወጥ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(2)፣(3) | 101890 | የኢትዮጵያ አየር መነገድ እና<br><br>ወ/ት ፍፁም ሀይሉ | ጥቅምት 24/2007 | 69 |
| 19. | "ስለሠራተኛ ዕድገት አሰጣጥ ስርዓት" በሚል በአዋጁ የተገለፀው ሀረግ ሊተረጎም የሚገባው ከአንድ የሠራተኛ የስራ መደብ ወደ ሌላ የሠራተኛ የስራ መደብ የሚፈፀም የዕድገት አሰጣጥ ስርዓት በሚል መልኩ ስለመሆኑ፣<br><br>በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 142(1)(ሠ) | 101795 | የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት<br><br>እና<br><br>አቶ አድማሱ አበበ | መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም. | 72 |
| 20. | የአንድ ድርጅት የበላይ ኃላፊ ለሠራተኞች ለጡረተኞች የክፍያ ጭማሪን በተመለከተ በስሩ ለሚገኙ እንደየገቢያቸው መጠን እያስወሠኑና እያስፀደቁ የጭማሪ ክፍያ እንዲያደረጉ ያስተላለፈው ውሣኔ በሙሉ በስር በሚገኙት ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ሥለመሆኑ፣ | 101579 | እነ አቶ ገ/መድህን አስፋው<br>እና<br><br>ትንሳኤ ጉባኤ ማተሚያ ቤት | ሕዳር 24/2007 | 76 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 21. | የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የወሰነውን ጉዳይ በይግባኝ ሲያይ የህግ ስህተት መኖሩን እና አለመኖሩን ከማረጋገጥ ባለፈ የፍሬ ጉዳይ እና የማስረጃ ምዘናን በተመለከተ የማየት እና የማረም ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ፣<br><br>አንድ አሠሪ የሠራተኛ ቅነሳ በሚል ምክንያት ሠራተኞችን ከሥራ ሲያሰናብት በአዋጁ የሠራተኛን ቅነሳ በተመለከተ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች መሠረት ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28(2)(ሐ) ፣29፣140 | 102512 | እነ ብርሀኑ ቢኒ (ሰላሳ አራት ሰዎች)<br><br>እና<br><br>የአርባ ምንጭ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ | ታህሳስ 10/2007 | 81 |
| 22. | አንድ ሠራተኛ የስራ ግዴታውን በአግባቡ ባለመወጣት በአሰሪው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሰ ከሆነ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ በቂ ምክንያት ሥለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/96 (1)(ሸ)፣ 12(2)(7) | 104294 | ሀግቤስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br><br>እና<br><br>አቶ በላይ ገ/ማሪያም | መጋቢት 29 ቀን 2007ዓ.ም | 85 |
| 23. | ከስራ በቅነሳ ምክንያት ለሚሰናበት ሠራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የሚከፈል ስለመሆኑ፡-<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 39(1)(ሐ)፣40(1)(3)፣28(2)(ሀ)(3) | 105620 | እነ አቶ ሀብቴ ብርሃኔ (ስድስት ሰዎች) እና<br><br>አቶ ሙሉነህ ቡና ላኪ ትራንስፖርትና ትሬንቢት አገልግሎት | ሚያዚያ 13 ቀን 2007 | 88 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 24. | አንድን ሰው ሠራተኛ ነው ለማለት በቅጥር ላይ የተመሰረተ የሥራ ግንኙነት መኖር፣ሠራተኛው አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑ፣ ሊሰጥ የሚገባውን አገልግሎትመቼ ሊያከናውን እንደሚገባና እንዴት ማከናወን እንደሚኖርበት አሰሪው የመቆጣጠር ስልጣን ያለው ስለመሆኑ መረጋገጥ ያለባቸው ስለመሆኑ፣<br><br>አንድን አደጋ በስራ ላይ የደረሰ ነው ለማለት ሠራተኛው ስራውን በማከናወን ላይ እያለ ወይም ከስራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሱ ውጪ በሆነ ምክንያት ወይም በአካሉ በማንኛውም ክፍል ተፈጥሯዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት የደረሰበት ጉዳት ስለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 2.4፣58.96፣97፣107፣110 | 105555 | እነ መፍትሄ ሙሜ<br><br>(ሶስት ሰዎች)<br><br>እና<br><br>አቶ ዑስማን አሲ | መጋቢት 18 ቀን 2007ዓ.ም | 91 |
| 25. | አንድ ሠራተኛ በህግ የተቀመጠው የጡረታ መዉጫ ዕድሜው ደርሶ በስራው ገበታ ላይ ቢቆይና በኋላ የስራ ውሉ ቢቋረጥ በአሰሪው ላይ የተለየ ግዴታ የሚጥል ስላለመሆኑና የማስጠንቀቂያ ጊዜ አልሰጠህም ተብሎ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ክፈል ተብሎ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 24(3)<br><br>አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀፅ 17(1) | 101736 | ግዮንኢንዱስትሪያል ኮሜርሻልኃ/የተ/የግል/ማህበር<br><br>እና<br><br>አቶ አዲስ ዓለም | መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ.ም | 97 |
| **ውል** | | | | | **100** |
| 26. | አንድ ቤት የተከራየ ሠው የኪራይ ዘመኑ ሲያልቅ አከራዩ ኪራዮን | 96858 | ወ/ሮ አብቢልክሽ ገለታ | ህዳር 26/2007 | 101 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መጨመሩን ማስጠንቀቂያ ከሠጠውና ተከራዩም ዝም ብሎ ቤቱን መጠቀም ከቀጠለአዲሱን የኪራይ ተመን ተከራዩ እንደተቀበለው የሚቆጠር ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ህ/ቁ. 1684፣ 2952/2/ | | እና<br><br>ዶ/ር ትግስት ቦርጋ | | |
| 27. | -ከአስተዳደር ውሎች አለመፈፀም ጋር ተያይዞ የወለድ ጥያቄ ሊቀርብ የሚችለው የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ በውሉ በተመለከተው መሠረት ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ለተዋዋዩ ስለ ገንዘቡ አከፋፈል የሚያስፈልገውን የማረጋገጥ ሥራ ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ወይም የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ የሚፈለግበትን ገንዘብ የማረጋገጥ ሥራ በተፈፀመ በ3 ወር ውስጥ ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ ስለመሆኑ፣<br><br>-ተቃራኒ የውል ቃል ቢኖርም እንኳን ከአስተዳደር መስሪያ ቤት ጋር የተዋዋለው ሰው መስሪያ ቤቱ ሳይከፍል ለቆየበት ገንዘብ ወለድ ወይም ኪሣራ ለመጠየቅ የሚችለው ሳይከፈል የቆየበት ጊዜ ከ6 ወር በላይ ሲሆን ወይም ውሉን ያደረገው የአስተዳደር መስሪያ ቤት ተዋዋዩን ለመጉዳት ብሎ ያደረገው ወይም ከባድ በሆነ ቸልተኝነትና ወይም ጥፋት ያደረገ ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ህ/ቁ. 3196፣3197 | 95797 | ደበበ ደረሠ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭእና<br><br>የፈንታሌ ወረዳ ውሃ መአድን ኢነርጂ ጽ/ቤት | ጥር 20 ቀን 2007 ዓ.ም | 104 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 28. | አንድ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆነ ሰው ከመንግስት የተከራየውን ቤት ለሌላ ሰው አከራይቶ መጠቀምየሚችለው በመመሪያው የተመለከቱት ምክንያቶች ተጣምረው የተገኙ እንደሆነ ስለመሆኑ፡- <br><br> መመሪያ ቁጥር 3/2004 አንቀጽ 6 <br><br> መመሪያ ቁጥር 4/2004 አንቀጽ 12 | 103704 | | ጥር 20/2007 | 107 |
| 29. | የባህር ላይ የእቃ ማጓጓዝ ውልን በተመለከተ የዕቃው ርክክብ ከተፈፀመበት ወይም የማስረከቡ ጉዳይ ሳይፈፀም ቀርቶ እንደሆነ እቃውን ማስረከብ ከሚገባበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ውስጥ ክስካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ፡- <br><br> የባህር ህግ ቁጥር 203፤180፤162 | 98358 | አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ እና <br><br> የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት ሎጂስቲክ አገልግሎት | ጥር 5 ቀን 2007ዓ.ም | 110 |
| 30. | አንድ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃ ለገዥ የሸጠ ሻጭ የገባው ውል እቃው ቢበላሽ ጥገና ለማድረግ እያለ ሆኖ እያለና ለድብቅ ጉድለቶች ኃላፊነት ሳይኖርበት ከውላቸው ውጭ እና ከህግ ውጭ እቃው ስላልሰራ እቃውን እንዲቀይር ወይም ገንዘቡን እንዲመልስ ሊደረግ የማይችል ስለመሆኑ፡- የፍ/ህ/ቁ 1731፣2266፣2288-2293፣2300 | 95072 | ግሎርየስ ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና <br><br> ሜሮን ጌትነት | ጥር 7 ቀን 2007 ዓ.ም | 114 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 31. | -የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ ውልን በተመለከተ እዳው እንዲከፈል በተወሠነ ጊዜ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂው የመያዣ መብት ያገኘበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይወስዳል በሚል የተደረገ ውል ፈራሽ ስለመሆኑ፣<br><br>-የብድር ውልን በተመለከተ ተዋዋዬች ወለዱ በወር እንዲታሠብ የሚዋዋሉት ውል ፈራሽ ስለመሆኑና በህጉ መሠረት ወለድ ሊታሠብ የሚችለው በዓመት ሥለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ህ/ቁ. 3060/1/፣ 1711 እና 2479/1/ | 102711 | ፈንታዮ ፍስሀ<br><br>እና<br><br>አቶ ደጀኔ ማርየ | ሕዳር 10/2007 ዓ.ም | 117 |
| 32. | በግልፅ የሰፈረ የውል ቃል ባይኖርም ስጦታ ሰጪው በድህነት ላይ ወድቆ ሲገኝ ስጦታ ተቀባይ የመጦር ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ፣ ሥጦታ ተቀባይ ይህን ግዴታውን ካልፈፀመ ደግሞ ስጦታ ሰጪ ውሉ እንዲሻር መጠየቅ ስለመቻሉ፣<br><br>የፍ/ሕ/ቁ. 2458(1)፣ 2464(1) | 107990 | እማሆይ ወ/ገብርኤል<br><br>እና<br><br>ደረጀ ደስአለኝ | መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ.ም | 121 |
| **ወንጀል** | | | | | **124** |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 33. | አንድ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ወንጀል የሰራው አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ሲሆንና ቅጣቱ በሚወሰንበት ጊዜ ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን ማንዋል ይልቅ አዲሱ የቅጣት አወሳሰን ማንዋል(መመሪያ) ቅጣቱን የሚያቀልለት ሲሆን ተፈፃሚ መደረግ የሚገባው አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ስለመሆኑ፡- <br>የወ/ሕ/ቁ. አንቀፅ 88(4)፣6 | 95440 | አቶ ሰሚር ኢብራሂም ሂቡ <br>እና <br>የፌዴራል ዐ/ሕግ | ሰኔ 4 ቀን 2006 ዓ.ም. | 125 |
| 34. | በማስረጃ በተረጋገጠ የወንጀል ፍሬ ነገር መፈፀሙ የተረጋገጠው የወንጀል ተጠያቂነትን በሚያስከትለው የህግ ድንጋጌ መሰረት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሠጠት ያለበት ስለመሆኑ፡- <br><br>የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 አንቀጽ 98(2)(ሀ) | 96607 | እነ አቶ ኤርሚያስ ካጢሶ (ሁለት ሰዎች)እና <br>የከምባታ ጠምባሮ ዞን ገቢዎች ባለስልጣን ዋና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት | መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ.ም. | 129 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 35. | በወንጀል ክስ ክርክር የክስ ይሻሻል ጥያቄ ቀርቦ ጥያቄው ውድቅ ከተደረገ ጥያቄው ውድቅ የተደረገበት ትእዛዝ በድጋሚ ለክርክር ሊቀርብ የሚችልበት ዕድል የሌለ በመሆኑና ትእዛዙ የመጨረሻ እንጂ ጊዜያዊ አገልግሎት እንዳለው ተቆጥሮ በስረ ነገሩ ከሚሰጠው ፍርድ ጋር ተጠቃሎ ይግባኝ የሚባልበት ነው ሊባል የሚችል ስላለመሆኑና በተሠጠው ትእዛዝ ላይ በስረ ነገሩ ከሚሰጠው ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ስለመሆኑ፡- <br><br> የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 118፣184፣ | 93234 | የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ሕግ <br><br> እና <br><br> አቶ ኃይለኪሮስ ወልደብርሃን ካሕሳይ | መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም. | 134 |
| 36. | የወንጀል አድራጊው በአንድ ድርጊት ከአንድ ጊዜ በላይ አደራርቦ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የአካባቢ ሁኔታዎችን ሲመረምር በተለይም ወንጀለኛው አስቦና አቅዶ ህግ መጣሱን ወይም ግልጽ የሆነ መጥፎፀባይ ማሣየቱን ባመነ ጊዜ ቅጣቱን አክብዶ መወሠን ሥለመቻሉ፣ <br><br> ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የድምር ውጤት የቅጣት አወሣሠን መርህን ተፈጻሚ ማድረግ ያለባቸው ሥለመሆኑ፣ <br><br> በተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሠነው ቅጣት ድምር ውጤት ከሃያ አምስት አመት ጽኑ እስራት ሊበልጥ የማይችል ሥለመሆኑ፣ <br><br> የወ/ህ/ቁ. አንቀጽ 184/1/ለ/፣ 108/1/፣ 187/1/፣65 | 92296 | እነ አንዷለም አራጌ/ሶስት ሰዎች/ <br><br> እና <br><br> የፌዴራል ዐ/ህግ | ሕዳር 22/2007 | 137 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 37. | ከአንድ በላይ ሰዎች በወንጀል ተሳታፊ በሚሆኑበት ጊዜ ለወንጀሉ ድርጊት ኃላፊ ናቸው የተባሉት ወንጀለኞች የእያንዳንዳቸውን ተሳትፎ ህጉ ባስቀመጠው የማስረጃ መለኪያ መሰረት መለየት ያለበት ስለመሆኑ-<br>የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 141፣ የወ/ህ/ቁ. 40 | 97203 | እነ አቶ ታምራት ደምሴ<br>(ሦስት ሰዎች) እና<br>የቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ሕግ | መስከረም 30 ቀን 2007 | 147 |
| 38. | ከዳኝነት ስራ ጋር ያልተያያዙ እና የአስተዳደር ስራ ሲያከናውኑ የሚፈፀሙ የወንጀል ጥፋቶች ዳኛውን ከተጠያቂነት የማያስቀሩ ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/ቁ. 402(1) እና (2)<br>በትግራይ ክልል ዳኞች እና ሬጂስትራሮችን ለማስተዳደር ተሻሽሎ የወጣው ደንብ ቁጥር 1/2003 | 98283 | አቶ ሐጐስ ገ/ብሄር መኮንን<br>እና<br>የትግራይ ክልል የስነ/ፀ/ሙ/ኮ | መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም | 155 |
| 39. | የወንጀል ህጉ አንቀጽ 420 ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረው የመወሰን ስልጣን በሌላቸው እና የሙያ አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት ያለባቸው በመንግስት ስራ ተመድበው ባሉበት ሁኔታ በመንግስት ንብረት ላይ የሥራ ኃላፊነት ወይም ግዴታቸውን ባልተወጡት ላይ ስለመሆኑ፣<br>የወ/ህ/አንቀጽ 420/1/ | 92826 | የደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት<br>እና<br>ወ/ሮ ፀሐይ ነጫሎ | ጥር 05/2007 | 158 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 40. | የማስረጃ ምዘና መሰረታዊ መርሆችን መሰረት ያላደረገ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለመሆኑ | 89676 | የፌደራል ዓቃቤ ህግ እና አቶ ሳሙኤል ፈቃዱ | ጥር 22 ቀን 2007 ዓ.ም | 162 |
| 41. | አንድ በወንጀል ተጠርጥሮ የተከሰሰ ሰው ቅጣት በሚያከብድ የህግ ድንጋጌ ስለተከሰስኩ ክሱ ይሻሻልልኝ በማለት ተቃውሞ ካቀረበ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ፍ/ቤቱ የሚወስነው እንጂ ከጅምሩ ማስረጃ ሳይሰማ አቋም የሚወሰድበት እና ክሱ ይሻሻል ተብሎ የሚታዘዝ ስላለመሆኑ፣ | 103452 | አቶ ጥዑም ተኬ ገብራይ<br><br>እና<br><br>የፌዴራል ሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዓቃቤ ሕግ | ጥር 19/2007 | 170 |
| 42. | በወንጀል የቅጣት አወሳሰን ጊዜ የቅጣት መነሻ ለማግኘት ቀላል የእስራት ቅጣትን ወደ ፅኑ እስራት መለወጥ የሚያሥፈልገው ወንጀለኛው ጥፋተኛ የተባለው በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ወንጀሎች ሲሆንና አንዱ ወንጀል በቀላል እስራት ሌላው ደግሞ በፅኑ እስራት የሚያስቀጣ በሆነ ጊዜ ብቻ ስለመሆኑ፡-<br><br>የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁ.2/2006<br><br>የወ/ሕ/አንቀፅ 184(1(ለ)) | 103448 | አቶ አገኘሁ አስፋው<br><br>እና<br><br>የፌደራል ዓቃቤ ህግ | የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም | 174 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 43. | በአንድ ተከሳሽ ላይ ከቀረቡት ከአንድ በላይ ከሆኑት ክሶች መካከል ከፊሎች የሚወድቁት በፌዴራል ፍ/ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር ከፊሎቹ ደግሞ በክልል ፍርድ ቤት የስረ- ነገር ስልጣን ስር በሆነ ጊዜናበወንጀል ህግ ሥነ-ስርዓቱ የክስ አቀራረብ መርህ መሰረት በቀጥታም ሆነ በውክልና በፌደራል ፍ/ቤት ቀርበው እንዲታዩ ከተደረገ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የይግባኝ እና የሰበር ሥርዓታቸው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲቀርቡ እንደተደረገው ሁሉየፌደራል ፍ/ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ሥርዓት ተከትለውና ተጠቃለው መታየትያለባቸው ስለመሆኑ::- ወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 109(3)፣116(2)<br><br>አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 4(4)፣15(1) | 99883 | አቶ ገ/ስላሴ ገብሩ<br><br>እና<br><br>የትግራይ ብ/ክ/መንግስት ፍትህ ቢሮ | ጥር 19/2007 | 178 |
| 44. | አንድ ወንጀል ከመስራት ሃሳብ የሚመነጩ የተለያዩ ድርጊቶች አንድ ወንጀል ከመስራት ሃሳብ የሚመነጩ ናቸው በማለት ተጠቃለው እንደ አንድ ወንጀል እንዲተገበሩ ማድረግ የህጉን አግባብ የተከተለ ስላለመሆኑ፡-<br><br>በፅኑ እስራትና በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው ሲገኙ የቀላል እስራት ወደ ፅኑ እስራት እንደሚለወጥ፤ስሌቱም የሁለት ዓመት ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ፅኑ እስራት የሚቆጠር ስለመሆኑ፡-<br><br>የወ/ሕ/ቁ/ 184 (1)(ለ) | 104715 | እንደሻው ይልማ ዳዲ<br><br>እና<br><br>የፌደራል አቃቤ ህግ | መጋቢት 02 ቀን 2007ዓ.ም | 188 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 45. | አንድ የትራፊክ ባለሙያ የሚሰጠው ሙያዊ አስተያየት የማስረጃ ዋጋ የማይሰጠው አስተያየቱ ተገቢውን የሙያ ደንብ ተከትሎ ያልተሰጠና ያልቀረበ፣በጊዜውና በቦታው ከነበሩት የአይን ምስክሮች ቃል ጋር ተነፃፅሮ ሲታይ በመሰረታዊ ነጥቦች ላይ ልዩነት ያለበት መሆኑ ሲረጋገጥ እንጂ በጭፍጫፊ ነጥቦች ላይ ልዩነት ተከስቷል ተብሎ ሊሆን እንደማይገባ፣<br><br>የልዩ አዋቂዎች ምስክሮች ቃላቸውን ገለልተኛ ሆነው መስጠት እንደ አለባቸውና ቃላቸው ያለበቂ ምክንያት ልዩ አዋቂ ያልሆኑ ሰዎች በሚሰጡት የምስክሮች ቃል ውድቅ መሆን የሌለበት መሆኑን ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ህግ ደንቦች የሚያስገነዝቡ ስለመሆኑ<br><br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141፣142፣194<br><br>የወንጀል ህግ ቁጥር 24፣59፣239(2)፣57፣543(2) | 92141 | የደ/ብ/ብ/ህ/ክልል ዓቃቤ ህግ<br><br>እና<br><br>አቶ አለማየሁ አስፋው | መስከረም 30 ቀን 2007ዓ.ም | 191 |
| 46. | በወንጀል የተከሰሰ ሰው ጉዳዩን በሌለበት ለማየት ፍ/ቤቱ በመጀመሪያ ለተከሣሹ ህጉ ያስቀመጠውን ጥብቅ መስፈርት በተከተለ መልኩ በአግባቡ ጥሪ ሊያደርግለት የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 161(1)(2) እና 162 | 93577 | አቶ ዘውዴ ተስፋዬ ስመኝ<br>እና<br>የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐ/ህግ | ህዳር 22/2007 | 198 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 47. | አንድ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በምርመራ ሒደትም ሆነ ክሱን ለሚሠማው ፍ/ቤት የሚሠጠው የእምነት ቃል ውጤት በራሱ በቃል ሠጪው ላይ ተወስኖ የሚቀር ከመሆኑ ውጪ ወንጀሉን አልፈፀምኩም ብሎ በሚከራከር ሌላ ተከሣሽ ላይ ህጋዊ ውጤት ሊያስከትል የማይችል ሥለመሆኑ፣<br>የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ-ሥርዓት ቁጥር 27፣35 እና 134 | 96310 | አቶ ጉደና ለማ ገዛኸኝ<br>እና<br>የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልል መንግስት የስ/ፀረሙስና ኮሚሽን | ህዳር 26/2007 | 203 |
| 48. | ከስር ተከሳሾች መካከል ፍ/ቤት የሠጠው ውሣኔ ለአንዱየሚጠቅም በሆነ ጊዜና ይግባኝ ባዩ ጋር ተከሠውጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ ሠዎች ይግባኝ ቢያቀርቡ ኖሮ በይግባኝ ሠሚው ፍቤት ውሣኔ ሊጠቅሙ ይችሉ የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ ይግባኝ ሠሚዉ ፍ/ቤት የሠጠው ውሣኔ ይግባኝ ላላቀረቡት ተከሳሾች ጭምር ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚገባ ሥለመሆኑ፤<br>የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁጥር 196/1/ /ሀ/ /ለ/ | 96378 | ሀቡብ ጀማል<br>እና<br>የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ዐ/ህግ | ህዳር 25/2007 | 209 |
| 49. | የRTD ችሎት መከላከያ የማቅረብ መብትን የማያስነፍግ ስለመሆኑ | 100712 | አቶ ሽብሩ ጌቱ ሴንጫ<br>እና<br>የፌዴራል አቃቤ ሕግ | መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ/ም | 213 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ጉምሩክ/ታክስ/** | | | | | 216 |
| 50. | በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ የተባለ ሠው በቅጣት ማቅለያነት እንዲያዝለት ያቀረበውን ምክንያት በማስረጃ ማስደገፍ እንዲችል በቂ ጊዜ ባልተሠጠበት ሁኔታ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በሚል የማቅለያ ምክንያቱን ውድቅ በማድረግ የሚሠጥ የቅጣት ውሣኔ በወንጀል ህጉ እና በቅጣት አወሳሠን መመሪያው ሥለ ቅጣት አወሣሠን የተቀመጡትን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ስላለመሆኑ፣<br>የወ/መ/ሥ/ሥርዓት 149/3//4/ | 96168 | አቶ አርአያ ኪዳኔ<br>እና<br>የኢትዮጵያገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን | ህዳር 9/2007 | 217 |
| 51. | የህግ ሰውነት ያለው የንግድ ድርጅት በህግ በግልፅ በተደነገገ ጊዜ በዋና ወንጀል አድራጊነት ፣በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሊቀጣ የሚችል መሆኑ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ህጉ በወንጀል የሚጠየቁ እንደሆነ በልዩ ሁኔታና በግልፅ ባልደነገገባቸው ወንጀሎች የወንጀል ተጠያቂነት እንደማይኖርባቸው በወንጀል ህጉ የተደነገገ ስለመሆኑ፡-<br><br>ህጋዊ ህልውና ያለው ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በኃላፊዎቹ ወይም ከሰራተኞቹ አንዱ ከድርጅቱ ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት አለአግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት በአነሳሽነትና በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ መሆኑ በወንጀል ህጉ | 100079 | አቶ እቁባይ በረሃ ገ/እግዚአብሄር እና<br><br>የኢትዮጲያ ገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ዓ/ህግ | መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ/ም | 221 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በግልፅ የተደነገገ መርህ ስለመሆኑ፡፡-<br><br>አንድ የንግድ ድርጅት የወንጀል ተግባር ከፈፀመና ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ከተረጋገጠ ለወንጀሉ አድራጎት ኃላፊ የሚሆኑት ሠራተኞችና ኃላፊዎች በወንጀል ከመጠየቅ ነፃ የማይሆኑ ሥለመሆኑ፡-<br><br>የወንጀል ህግ አንቀፅ 34 | | | | |
| **ከውል ውጪ ኃላፊነት** | | | | | 231 |
| 52. | ሁለት የሞተር ተሽከርካሪዎች ሲጋጩ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየራሱ አንዱ ከአንዱ ላይ ጉዳት እንዳደረሱ የሚቆጠረውና የእያንዳንዱ መኪና ባለሀብት ለአደጋው ኃላፊ የሚሆነው አደጋው የደረሠው ከአንደኛው መኪና አሽከርካሪ ስህተት መሆኑ በማስረጃ ያልተረጋገጠ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፡- *የፍ/ሕ/ቁ 2084* | 95267 | ናይል ኢንሹራንስ<br><br>እነ<br><br>ካሳሁን ወንድሙ (ሶስት ሰዎች) | ጥቅምት 28/2007 | 232 |
| 53. | የአንድ ግንባታ ባለቤት ግንባታውን ለሚያከናውነው የስራ ተቋራጭ ግንባታው ሲከናወን ለሚደርሱ ከውል ውጪ ኃላፊነቶች ወይም በህጉ የተጣለበትን ፍትሐ ብሄራዊ ግዴታዎች ለስራ ተቋራጩ በማስተላለፍ የሚያደርገው ስምምነት በህግ ጥበቃ የሚደረግለት ስለመሆኑ፡-<br><br>የፍ/ሕ/ቁ.2027(1)፣2130፣2132(1)፣2131(1)፣2035(1)፣2141 | 93772 | አቶ ሁሴን አምዴ<br><br>እና<br><br>እነ ኢትዮ ቴሌኮም<br><br>(ሁለት ሰዎች) | የካቲት 30 ቀን 2007ዓ.ም | 235 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የፍ/ሕ/ቁ. 1675፣1716፣1731<br><br>አዋጅ ቁጥር 464/97 አንቀፅ 3(3) | | | | |
| 54. | አንድ ኢንሹራንስ ኩባንያ በውል የመነጨውን ግዴታውን በወቅቱባለመወጣቱ ለተከሰተው ተጨማሪ ወጪ ተጠያቂ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>የን/ሕ/ቁ 665 | 95751 | ወ/ሮ እመቤት መኰንን<br><br>እና<br><br>እነ ወ/ሮ መሰረት አስናቀ (ሁለት ሰዎች) | መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ.ም. | 241 |
| 55. | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ያልተወረሰ ቤትን በህገወጥ መንገድ በመያዝ የተጠቀመበት ከሆነ የኪራይ ገንዘብና ያለአግባብ የበለፀገበትን ያህል ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ፡-<br><br>ያለአግባብ በመንግስት ተይዞ ለቆየ ቤት የታጣ ጥቅም አይከፈልም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፡-<br><br>የፍ/ሕ/ቁ 2162<br><br>አዋጅ ቁጥር 193/92 አንቀፅ 7(3)<br><br>አዋጅ ቁጥር 192/92 አንቀፅ 3 | 97683 | አክበር አሊ ካምሩዲን ኩባንያ<br><br>እና<br><br>የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | መጋቢት 18 ቀን 2007ዓ.ም | 243 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ባንክ እና ኢንሹራንስ** 247 | | | | | |
| 56. | አንድ የባንክ ደንበኛ ከባንኩ ጋር በገባው ውል መሰረት የቁጠባ ሂሳቡን በኤ.ቲ.ኤ.ም ካርድ ሲያንቀሳቅስ ቆይቶ ነገር ግን በአጋጣሚ ካርዱ ቢጠፋ እና ይሄንኑ በፅሁፍ ለባንኩ ካሳወቀ ከዚያ በኋላ በሂሳቡ ላይ ለሚደርስ ጉድለት ባንኩ ኃላፊ ስለመሆኑ፡- | 96309 | ዳሽን ባንክ አክስዮን ማህበር<br>እና<br>አቶ አበባየሁ ግርማ | መስከረም 27/2007 ዓ.ም | 248 |
| **የዳኝነት ስልጣን** 251 | | | | | |
| 57. | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ጋብቻን በተመለከተ የባልነት ወይም የሚስትነት የምስክር ወረቀት ከመስጠት ባለፈ በማስረጃው ላይ ክርክር ከተነሳበት ወይም የጋብቻ መኖር አለመኖርን ለመወሠን የስረ ነገር ሥልጣን ያልተሠጣቸው ሥለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀፅ 2<br>አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41/1/ /ሽ/ | 75560 | ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማርያም<br>እና<br>አቶ ገብረስላሴ ኃይሌ | ሐምሌ 26/2004 | 252 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 58. | የዲፕሎማቲክ ግንኙነቶችን ስምምነት ልምድን ለማክበር ሲባል የውጭ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችና ኢትዮጲያዊያን ሠራተኞቻቸው የሚያደርጉት የቅጥር ግንኙነት ላይ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ ተፈፃሚ የማይሆን ስለመሆኑ፡-<br><br>የተባበሩት መንግስታት አካል የሆነ ድርጅት የተባበሩት መንግስታት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ በተደነገገ ሥምምነት በማንኛውም የመንግስት ፍ/ቤቶች ተከሶ መቅረብ የሌለበት ሥለመሆኑ፡-<br><br>አፈፃፀም በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ትርጉም እንዲኖረው በማድረግ ውጤት ያለውና በተገቢው መንገድ መፈፀም ያለበት መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም ለማንኛውም ጉዳዮች ይሰራል ተብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስ የማይቻል ስለመሆኑ፡-<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 3/3(ሀ)<br><br>የተባበሩት መንግስታት ቻርተር አንቀፅ 105<br><br>ከተባበሩት መንግስት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ የተደነገገው ሥምምነት አንቀፅ 2/2/ እና 3<br><br>የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 212 | 98541 | አቶ አለማየሁ ኦላና<br><br>እና<br><br>የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት/UNDP/ | ህዳር 10 ቀን2007 ዓ.ም | 258 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 59. | የከፍተኛ ትምህርት ተቋም መምህራን ትምህርት ለመማር ከአሰሪያቸው ተቋም ጋር የሚያደርጉትን ውል አፈፃፀምና ከውሉ ጋር ተያያዥ ባላቸው ጉዳዮች ላይ የሚነሱ ክርክሮችን ለማየት ስልጣኑ ያላቸው የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስለመሆናቸው፣<br><br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 79(1)<br><br>የፌድራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515//1919 አንቀፅ 75(5)(6) | 99717 | አቶ ሲሳይ ይማነ<br><br>እና<br><br>አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ | ጥር 20 ቀን 2007ዓ.ም | 262 |
| 60. | በክልል በተነሳ ግምት በሌለው የመንገድ ይከፈትልኝ ጥያቄ ላይ ከተከራካሪ ወገኖች መሃል አንደኛው በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ ማህበር ከሆነ ጉዳዩ በፌዴራል የፍ/ቤቶች ስልጣን ስር፣በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስረ ነገርሥልጣን ስር የሚወድቅ ሲሆን የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በውክልና ስልጣኑ ጉዳዩን የሚመለከት ስለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 5(2) እና 5(6)፣ አንቀፅ 14<br><br>በኦሮሚያ ክልል ህገ መንግስት አንቀጽ 64(3) እንዲሁም በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 27(4) | 105962 | እነ ቢ.ኤም.ጂ ኃ.የተ.የግል ማህበር (ሁለት ሰዎች)<br><br>እና<br><br>ፕሮፌሰር በደግ በቀለ | የካቲት 19/2007ዓ.ም | 266 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 61. | የአዲስ አበባ መስተዳደር አስፈፃሚ አካላት በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል ካሳ ይክፈሉ ተብሎ የሚቀርብ ክስን በተመለከተ የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ያላቸውየፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆናቸው፡- አዋጅ ቁጥር 361/1995፣ አዋጅ ቁጥር 408/1996<br><br>አዋጅ ቁጥር 25/88 | 99375 | አቶ አምባቸው አለሙ<br><br>እና<br><br>እነየካ/ክ/ከተማ/ወ/01 አስተዳደር( አራት ሰዎች) | መጋቢት 15 ቀን 2007ዓ.ም | 270 |
| 62. | የክርክሩ አጠቃላይ ይዘት የዕቁብ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄን መሰረት አድርጐ የቀረበ በንግድ ህጉየተመለከቱትን አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎችን አተገባበር ለመመርመር የሚያስችልና ቼክ እንደተራ ማስረጃነት ሆኖ በክርክር ወቅት በቀረበበት ጊዜ ጉዳዩ የፌደራል ነው ተብሎ የማይወሰድ ሥለመሆኑ፡-<br><br>አዋጅ ቁጥር 25/1988 | 104511 | እነ አቶ ዳኜ ሃይሉ( ሁለት ሰዎች)<br><br>እና<br><br>እነ አለም ሰገድ ሃብታሙ<br><br>( ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም | 273 |
| **ቤተሰብ** | | | | | **276** |
| 63. | ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ ስም የነበረን የግል ንብረት በጋብቻ ወቅት በንብረቱ ላይ መሰረታዊ መሻሻል ቢደረግበትና ይሄው መሻሻል የተደረገው የባለንብረቱ የግል ገንዘብ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ህጉ ንብረቱ የጋራ ነው የሚል ግምት የሚወስድ ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀፅ 63(1) | 94952 | ወ/ሮ ዙሪያሽ ተገኝ<br><br>እና<br><br>ወ/ሮ የሺ ውድዬ | መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም. | 277 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 64. | በኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ መሠረት ባልና ሚስቱ በየግል ያገኟቸውን ንብረትም ሆነ ገንዘብ በግል ይዘው መቀጠል እንደሚችሉ ሲደነገግ ይህ የግል የተባለው ንብረት የግል ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው የግል ይባልልኝ ተብሎ በፍ/ቤት ሲፀድቅ ስለመሆኑ፣<br>የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ህግ ቁ.69/1995 አንቀፅ 7410፣አንቀፅ 74/2/ | 95680 | ወ/ሮ የሺ ተሾመ<br>እና<br>አቶ መስፍን ኃይሉ | መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ/ም | 281 |
| 65. | የባልና ሚስት ጋብቻ ፈርሶ የጋራ የሆነ ንብረት ክፍፍል በሚፈፀምበት ጊዜ በፍ/ሕጉ ላይ የተቀመጡት በቅድሚያ የመግዛት መብት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሌላቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ.ቁ. 1386፣1388፣1391፣1392፣1393፣(1)፣1397 | 88275 | አቶ ኃይለሚካኤል ልኬ ሉሱ<br>እና<br>እነ አቶ መኮንን በለጠ /ሁለት ሰዎች/ | ጥር 19/2007 | 284 |
| 66. | የDNA ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ መሰጠቱ አንደኛው ወገን አሉኝ የሚላቸውን የመከላከያ ማስረጃዎች የማሰማት መብት የማይከለክል ስለመሆኑ፣<br>የDNA ምርመራ እንዲረግ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ስለሚሠጥበት አግባብ፣ | 90121 | | መስከረም 28/2007 ዓ/ም | 289 |
| 67. | ሚች በህይወት እያለ ከይዞታ ቦታው ላይ ለሌላ ሠው ቤት እንዲሠራፈቅዶ ቢሰጠው ሚች በሚሞትበት ጊዜ በሚች ፈቃድ ቤት የሠራው የቤቱ ባለቤት እንደሚሆንና ከሌላው ቦታ ጋር ሆኖ የውርስ ክፍል የሚሆን ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ህ/ቁ. 826/2/፣1179/1/ | 96628 | እነ አሳምነው ከበደ /አምስት ሰዎች/ እና<br>አቶ ዳንኤል ከበደ | ሕዳር 08/2007 | 293 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 68. | አንድ ተናዛዥ ኑዛዜውን መሻር ሲፈልግ ሀሳቡን በማያሻማ አኳኋን በመግለጽ ከሻረ ኑዛዜዎች ዋጋ ያላቸው እንደሆኑ በሚያስፈልገው ፎርም አይነት ግልጽ አድርጐአልሻረውም ሊባል የማይችል ስለመሆኑ፣<br>የፍ/ህ/ቁ. 898(1)፣ 899(1) | 96364 | እልፍነሽ ወርቁ<br>እና<br>ኤልሳቤጥ አስራት | ጥቅምት 10/2007 | 298 |
| 69. | አንድ የቀበሌ ቤትን ተከራይቶ የነበረ ሠው ከዚህ አለም በሞት ሲለይ ወራሾቹ ወይም ቤተሠቦቹ የተከራይነት መብቱ ይተላለፍልን ብለው በሚጠይቁበት ጊዜ ከሕግ አኳያ ዳኝነት የሚሠጥበት እንጂ በፍርድ ቤት የሚያልቅ ጉዳይ አይደለም ብሎ ጥያቄውን አለመቀበል አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 37<br>የፍ/ህ/ቁ. 826/2/ እህ 2928 | 97948 | ወ/ሪት ሔለን ተክሌ<br>እና<br>ወ/ሮ ዘይድ አብርሃ | ታህሳስ 21/2007 | 301 |
| 70. | በጋብቻ ጊዜ የተፈራ የባልና ሚስት የጋራ የሆነ የአክስዮን ድርሻ በፍቺ ጊዜ በአይነት ሊከፋፈል የሚችል ስለመሆኑ፣<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 91 እና 92 | 102652 | ወ/ሮ ሃቢባ መካ<br>እና<br>እነ ደሊል ሁሴን(ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 16 ቀን 2007 | 304 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 71. | አንድ ሰው ከህግ ውጪ የገጠር እርሻ መሬት ለመውረስ የሚያስችል የወራሽነት ማስረጃ ስላወጣ ይሰረዝበት የሚል አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ ፍ/ቤት ጭብጥ ይዞ ውሳኔ የሚሰጥበት ጉዳይ እንጂ የመሬት ክርክር ሲነሳ የሚታይ ነው ተብሎ ክሱን ውድቅ ማድረግ አግባብነት የሌለው ሥለመሆኑ፣<br><br>የአ/ብ/ክ/መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98<br><br>እና ደንብ ቁጥር 51/99 | 108539 | አቶ አበባው አጥናፍ<br><br>እና<br><br>እነ ወ/ሮ የካባ ግዛው (ሶስትሰዎች) | መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም | 307 |
| **ንብረት** | | | | | **310** |
| 72. | በገጠር የእርሻ መሬት ላይ በተሠጠ ፍርድ የፍርድ መቃወሚያ ሲቀርብ ፍርድ ተፈፅሟል ሊባል የሚችለው የፍርድ ባለመብቱ በይዞታው ላይ ህጋዊ ማረጋገጫ ሲያገኝ ስለመሆኑ፣ | 101079 | የይልማና ዴንሳ ወረዳ አከባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ፅ/ቤት እና<br><br>አቶ ውበት ገ/መድህን | ጥር 22 ቀን 2007 ዓ.ም | 311 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 73. | በአንድ ተቋም ውስጥ ተቀጥሮ ለሚሰራ ሠራተኛ አሰሪው ተቋም ለሰራተኛው ለመኖሪያ የሚሆን ክፍል ከሰጠው እና ሰራተኛው በአሰሪው ተቋም ፍቃድ ተጨማሪ ግንባታ በራሱ ወጪ ከገነባ እና አሰሪው ሰራተኛው እንዲወጣ ካስገደደው አሰሪው ተቋም ሰራተኛው ለተጨማሪ ግንባታ ያወጣውን ወጪ መክፈል ያለበት ወይም ሰራተኛው ተጨማሪውን ግንባታ አፍርሶ የመውሰድ መብት ያለው ስለመሆኑ፡- <br>የፍ/ሕ/ቁ. 1446፣1454፣1455 | 96495 | የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት <br>እና <br>አቶ ኃይሌ ብሩ | የካቲት 5 ቀን 2007ዓ.ም | 315 |
| 74. | ለክርክሩ መነሻ የሆነ ሽጉጥ (የጦር መሳሪያ) የንምራ ቁጥር አከራካሪ በሆነበት ወይም የመጀመሪያው ንምራ ቁጥር በሌላ ተተክቷል የሚል ክርክር በተነሳ ጊዜ በመሳሪያው ላይ ያለው ንምራ ቁጥር ኦሪጅናል ነው? ወይስ በሂደት የተተካ ቁጥር ነው? የሚለውን አግባብነት ባለው አካል ሞያዊ አስተያየት/expert opinion/ አጣርቶ መወሰን አስፈላጊ ስለመሆኑ፣ | 97132 | አቶ መሃመድ ከማል <br>እና <br>የከሚሴ ወረዳ ሚሉሻ ፅ/ቤት | መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም | 318 |
| **ንግድ** | | | | | **321** |
| 75. | ክሱ የቀረበው በአንድ ተለይቶ በታወቀ ጊዜ ወይም ቀን የተፈጠረ ክስተትን መሠረት በማድረግ ሳይሆን በተለያየ ጊዜ ተከስተዋል የተባሉ የተለያዩ ችግሮችን መሠረት አድርጉ ሲሆን የማህበር ይፍረስልኝ ጥያቄ ወይም ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚባልበት ምክንያት | 94278 | አቶ ሐሠን መሀመድ <br>እና <br>ማጅ አግሮ ፎረስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል | ሕዳር 11/2007 | 322 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሥላለመኖሩ፣<br><br>የን/ሕ/ቁ 218(1)፣541(1)<br><br>የፍ/ሕ/ቁ 1835፣1845 | | ማህበር | | |
| 76. | ከውጪ አገር በዶላር የተላከ የውጭ ምንዛሬ ለተላከለት አላማ አልዋለም በሚል ገንዘቡ እንዲመለስ ክርክር ሲነሳ ገንዘቡ ሊመለስ የሚገባውዶላር በተላከበት ጊዜ በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ በተሠጠው ተመን መሠረት ስለመሆኑ፣<br><br>የፍ/ሕ/ቁ 1705፣1749፣1750፣1771 | 95069 | እነ ስፍሜት አግሮ ቢዝነስ ኃ/የተ/ማህበር /ሁለት ሰዎች/<br>እና<br>ወ/ሮ ኤልሳቤት ብረቱ | ሕዳር 23/2007 | 325 |
| **አፈፃፀም** | | | | | **332** |
| 77. | በፍርድ ባለዕዳው ሥም የሚታወቅ ቤት ቤቱ በህጋዊ መንገድ የተገነባና የፍርድ ባለዕዳው እስከሆነ ድረስ ካርታና ፕላን የሌለው መሆኑ እና ለሌላ ሶስተኛ ወገን ተሠጥቷል መባሉ ስጠታው ህጋዊ በሆነ መንገድ እስካልተከናወነ ድረስ ቤቱ ለፍርድ አፈፃፀም እንዳይውል ሊያደረግው የሚችል ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ሕ/ቁ 276፣277 | 90722 | ወ/ሮ መዓዛ መዝገቡ<br><br>እና<br><br>አቶ መሠለ ገላው | ጥቅምት 11/2007 | 333 |
| 78. | በፍርድ ውሣኔ በተሰጠበት ጉዳይ አፈፃፀምን ለማስቀረት በፍርድ ባለመብት እና በፍርድ ባለ ዕዳ የሚደረግ የእርቅ ውል በፍርድ ቤት ቀርቦ ካልፀደቀ በቀር አፈፃፀምን ሊያስቀር የሚችል ስላለመሆኑ፣<br>የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 276፣277 | 98263 | ወ/ሮ እናናይቱ ኢሳ<br>እና<br>ወ/ሮ አሲና ሁሴን | ጥር 06/2007 | 336 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 79. | የፍርድ ባለመብት ፍርዱን እንዲፈፀምለት ሲጠይቅ የፍርድ ባለዕዳው የፍርድ ባለመብቱ ተነፃፃሪ የሆነ ግዴታውን እንዲወጣ ትዕዛዝ ይሠጥልኝ በማለት ጥያቄ ለማቅረብ የሚችለው በአንድ ፍርድ ቤት ውስጥ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች የፍርድ ባለመብት መሆናቸው ተረጋግጦ ውሳኔ ተሰጥቶበት እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ፡- <br><br> አንድ የፍርድ ባለእዳ እንደ ፍርዱ እንዲፈጽም ሲጠየቅ ፍርድ ያላረፈበትን ቅድመ ሁኔታ በማቅረብ በአፈፃፀም ሊከራከር ሥላለመቻሉ፣ <br><br> የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 398፣ 378 | 99743 | ንብ ኢንሹራንስ <br><br> እና <br><br> ራዲካል ኢንጅነሪንግ | መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም | 341 |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | **344** |
| 80. | አንድ የመንግስት ሠራተኛ የጡረታ ዕድሜው ከደረሠ በኋላ አሠሪው መ/ቤት ፈቃድና ከየትኛውም አካል ተቃውሞ ሣይቀርብ የጡረታ ጊዜው ከተራዘመ ለተራዘመበት ጊዜ የሠራበት ለጡረታ ሊያዝ የሚገባው ሥለመሆኑ፣ <br> አዋጅ ቁጥር 714/2003፣ አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 85፣89 | 96833 | የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ <br> እና <br> አሥፋው ደነቀ | ታህሳስ 8/2007 | 345 |
| 81. | በአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም ውስጥ አንድን ጉዳይ በግልግል እንዲያይ የተቀመጠ የግልግል ዳኛ ከተከራካሪ ወገኖች በአንዱ እንዲነሳ አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ ይነሳ የተባለው ዳኛ ልነሳ | 99679 | የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት <br> እና | ታህሳስ 24/2007 | 348 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | አይገባም ብሎ ጥያቄውን ካነሳው ወገን ጋር ሊከራከር የማይገባው ሥለመሆኑና ልነሳ አይገባም እያለ በሚከራከርበት ሆኔታም ጉዳዩን ገለልተኛ ሆኖ ያየዋል ተብሎ ሥለማይገመት መነሳት ያለበት ሥለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 9 እና 10<br>የፍ/ህ/ቁ.3342/ 3340/2/<br>የግልግል ተቋሙ የተሻሻለ ደንብ አንቀጽ 13 እና 15 | | አቶ በየነ ወልደገብርኤል | | |
| 82. | አንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ላስተማራቸው ተማሪዎች ጊዜያዊ ዲፕሎማ ከሠጠ በኋላ ዋናው ዲፕሎማ ሳይሠጣቸው የማስተማር ፈቃዱ ቢነጠቅ እንኳ ፈቃዱን ተነጥቂያለሁ፣ ዋናውን ዲፕሎማ ልሰጥ አልችልም የማለት መብት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>አዋጅ ቁጥር 650/2001፣ ደንብ ቁጥር 199/2003 | 99689 | የአዲስ አበባ ዴንታል ባይንስ ኮሌጅ<br>እና<br>እነ መንግስቱ ጋሞ<br>(ሰባት ሰዎች) | ታህሳስ 24/2007 | 351 |
| 83. | አንድ የንግድ ድርጅት ሲከስር የዕዳ ክፍያን በተመለከተ የድርጅቱን ንብረቶች በመያዣነት ከያዛቸው ባንክ ይልቅ የከሰረው ድርጅት ሰራተኞች የቀዳሚነት መብት ያላቸው ስለመሆኑ፣<br><br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 167<br>አዋጅ ቁጥር 97/1990 እንደተሻሻለ | 102061 | የከሰረው ሆላንድካር ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br><br>እና<br>ዘመን ባንክ | የካቲት 6 ቀን 2007 ዓ.ም | 354 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 84. | በአንድ መተዳደሪያ ደንብ በማህበር አባላትና በድርጅቱ መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች በመጀመሪያ በእርቅ መፈታት አለባቸው የሚል ድንጋጌ ሲኖር ይኸው ሥርዓት ሳይፈፀም ወደ ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ አግባብነትየሌለው ስለመሆኑ<br><br>ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የሚነሳ አለመግባባትን በተመለከተ ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሽምግልና እንዲታይ ሊሰማሙ ሥለመቻላቸው፣<br><br>የፍ/ሕ/ቁ. 1731(1)፣1732፣1736፣1738 | 106286 | ቦሮ ትራቪል የግንባታ ሥራዎች የተ.የግ.ማህበር<br><br>እና<br><br>አቶ ኤፍሬም ሽብሩ | መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም | 358 |

# ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

የሰ/መ/ቁ. 90713

መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ አሚና ሰይድ ጠበቃ ይርሳው ጌትነት ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1 ወ/ሮ ወሰላ ንጋቱ - ጠበቃ ዘርፉ ካብትይመር ቀረቡ

2. የዲላ ከተማ ማዘጋጃ ቤት - ነ/ፈጅ ማዴቦ ዋንጐ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሰረት ያቀረቡትን የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡
የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ በዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ላይ ክስ መመስረታቸውን፣ የክሳቸው ይዘትም ከሳሽ ለኢንቨስትመንት ዓላማ ለማዋል በጨረታ ተወዳድረው እና አሸንፈው የገዙትን 602 ካሬ ሜትር የቦታ ይዞታ ተከሳሽ የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር ሊያስረክባቸው ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን የሚገልጽ ሆኖ ይህንኑ ቦታ ነጻ አድርጎ እንዲያስረክባቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት መሆኑን፣ተከሳሹም ርክክቡ የዘገየው የአሁኗ አመልካች በፈጠሩት ችግር ምክንያት መሆኑን እና በክሱ መሰረት ቦታውን ለማስረከብ ፈቃደኛ መሆኑን ገልጾ መልስ መስጠቱን፣አመልካች የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ያቀረቡትም ጉዳዩ በዚህ ደረጃ ላይ እያለ መሆኑን፣ፍርድ ቤቱም የጣልቃ ገብነት ማመልከቻውን እና አባሪ ሰነዶችን ከመረመረ በኃላ አመልካች በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር የሚያስችላቸውን በቂ ምክንያት አላቀረቡም በማለት የጣልቃ ገብነት ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉን እና አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም ለክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት በማጣቱ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡
የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በተጠሪዎች መካከል ክርክር የተነሳበት ንብረት በሟች ባለቤታቸው ሐጅ መሐመድ ዑመር ስም ተመዝግቦ የሚታወቅ መሆኑን እና የአመልካች ሚስትነት እና የልጆች ወራሽነት በፍርድ የተረጋገጠ መሆኑን የሚያሳዩ የተለያዩ ሰነዶችን አመልካች ከአቤቱታቸውጋር አያይዘው አቅርበው እያለ በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር የሚያስችላቸውን በቂ ምክንያት አላቀረቡም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት ከፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 ድንጋጌ አንጻር

ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአንድ ክስ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች በክርክር ላይ ባሉበት ጊዜ ማናቸውም ሶስተኛ ወገን በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ሲሆን ከፍርድ ውሳኔ በፊት ጣልቃ ገብ ሆኖ ለመከራከር እንደሚችል እና የጣልቃ ገብነት ማመልከቻው በክሱ ውስጥ ያገባኛል የሚልበትን ምክንያት የሚዘረዝርና በተለይም የመብቱን ሁኔታ የሚገልጽ መሆን እንዳለበት፣እንዲሁም የጣልቃ ገብነት ጥያቄ አቅራቢው በጉዳዩ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚያስችል መብት ያለው መሆን አለመሆኑ በቅድሚያ ሊወሰን እንደሚገባው፣ጣልቃ ለመግባት የሚያስችል መብት የለውም በተባለ ጊዜ መሰናበት እንደሚገባው እና መብት አለው በተባለ ጊዜ ግን የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ከተደረገ በኃላ ከጣልቃ ገቡ መብት አንፃር ጭምር አጠቃላይ ክርክሩ ተመርምሮ ተገቢ ነው የሚባል ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 (1)፣ (2) እና (3) ድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከቤተሰቦቻቸውጋር የሚኖሩበት በሟች ባለቤታቸው ስም እንደሚታወቅ እና 189 ካሬ ሜትር ይዞታ እንዳለው የተገለጸው ቤት የሚገኘው 1ኛ ተጠሪ በጨረታ ከ2ኛ ተጠሪ ገዝቸዋለሁ በሚሉት 602 ካሬ ሜትር የቦታ ይዞታ ውስጥመሆኑ በተጠሪዎቹም ያልተካደ ጉዳይ ሲሆን የጣልቃ ገብነት ማመልከቻው የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበል የቀረው አመልካች ከግብር ደረሰኞች በስተቀር ባለይዞታ ወይም ባለቤት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የባለቤትነት ሰነድ አላቀረቡም፣ደረሰኞቹም የሚታወቁት በአመልካች ስም አይደለም፣ሰነዶቹ የሚያመለክቱት ክስ ያስነሳውን ይዞታ ስለመሆኑም የቀረበ ማረጋገጫ የለም በማለት መሆኑን የብይኑ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ይሁን እንጂ አመልካች ለጣልቃ ገብነት ማመልከቻው ምክንያት ያደረጉት ቤትና ይዞታ በግብር ደረሰኞች የሚታወቀው በሟች ባለቤት ስም ቢሆንም አመልካች ሚስትነታቸውን እና የልጆችን ወራሽነት በፍርድ ቤት ያረጋገጡ መሆኑ በተረጋገጠበት እና የባለይዞታነት ወይም የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ማቅረብ ያልቻለ ተከራካሪ ወገን ክርክር ባስነሳው ቤት እና ይዞታ ላይ አለኝ የሚለውን መብት የባለይዞታነት ወይም የቤት ባለቤትነት ማረጋጫ ሰነድ በማቅረብ ካልሆነ በስተቀር በሌላ ማስረጃ ማስረዳት የማይችል ስለመሆኑ ግልጽ የሆነ የሕግ ክልከላ በሌለበት ሁኔታ የጣልቃ ገብነት ጥያቄው የቀረበለት ፍርድ ቤት አመልካች በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ለመከራከር የሚያስችላቸውን በቂ ምክንያት አላቀረቡም በማለት የሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ብይን ከላይ ከተጠቀሰው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 ድንጋጌ ይዘት እና መንፈስ አንጻር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ የአመልካች የጣልቃ ገብነት ጥያቄ መሰረት የሚያደርገው የካሳ እና የምትክ ቦታ መብትን ብቻ ሳይሆን የኢንቨስትመንት የቅድሚያ መብትን ጭምር ስለመሆኑ ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለ ሲሆን አመልካች በጣልቃ ገብነት ሊያቀርቡ የሚችሉትን ክርክር ይዘት እና አድማስ በተሟላ ሁኔታ መገንዘብ የሚቻለው ጥያቄአቸው ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ጉዳዩ እንዲገቡ ሲደረግ ነው፡፡

በሌላ በኩል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር  41 መሰረት በጣልቃ ገብነት መከራከር የሚቻለው ከፍርድ ውሳኔ በፊት መሆኑ በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (1) የተመለከተ ሲሆን ጉዳዩ የፍርድ ውሳኔ ካገኘ በኃላ በሆነ ጊዜ ግን በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባውና ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቴን ይነካል የሚል ሰው ተነክቶብኛል የሚለውን መብት

ማስከበር የሚችለው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ መሰረት ነው፡፡በመሆኑም አመልካች የጣልቃ ገብነት አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ በተጠሪዎች መካከል ክርክሩ ቀጥሎ ውሳኔ ተሰጥቶበት ከሆነ የአመልካች አቤቱታ ሊስተናገድ የሚገባው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል የአመልካችን የጣልቃ ገብነት ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአመልካችን የጣልቃ ገብነት ማመልከቻ ውድቅ በማድረግ በዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09114 በ05/03/2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 06769 በ05/06/2005 ዓ.ም. በውሳኔ እና በመዝገብ ቁጥር 58897 በ13/07/2005 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 በተደነገገው መሰረት በጉዳዩ በጣልቃ ገብነት ለመከራከር የሚያስችል መብት ነበራቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች የጣልቃ ገብነት ማመልከቻ ያቀረቡበት ተጠሪዎች ከሳሽ እና ተከሳሽ በመሆን የሚከራከሩበት ጉዳይ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚደርስበት ቀን ውሳኔ ያላገኘ ከሆነ አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 41 ድንጋጌ መሰረት የተሟላ ክርክር እንዲያቀርቡ በማድረግ፤ጉዳዩ ውሳኔ አግኝቶ ከሆነ ደግሞ አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 358 ድንጋጌ በተዘረጋው ስርዓት መሰረትየመቃወም አቤቱታቸውን አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ በማድረግ የሶስቱንም ተከራካሪ ወገኖች አጠቃላይ ክርክር መርምሮ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት ወስነናል፡፡
4. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ለዲላ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፤እንዲያውቁት ደግሞ ለጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁጥር 93239

ጥቅምት 25 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካቾች ፡- የአቶ አበበ ክብረት ሚስትና ወራሾች እነ ወ/ሮ ብርሃኔ መኰንን 10 ሰዎች

ጠበቃ አቶ አምሳሉ ባየ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ነጋ ቦንገር ዶ/ር ሸዋረጋ አስራት ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው በሥር የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ባቀረቡት አቤቱታ በኮ/መ/ቁ 06187 በ 13/07/2005ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ ነው፡፡አመልካቾች እና ተጠሪ የነበራቸውን ክርክር በስምምነት ለመጨረስ ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.277 መሠረት በፍ/ቤት የተመዘገበ መሆኑ መዝገቡ መዘጋቱን በሥር ፍ/ቤት መዝገብ የተገለጸ ሲሆን በስምምነቱ መሠረት የተሾሙት የሂሳብ አጣሪዎች ሪፖርት ፍ/ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ በአሁኑ አመልካቾች ግንቦት 09 ቀን 2004ዓ.ም አቤቱታ ቀርቧል፡፡

የሥር ፍርድ ቤቱም የግራቀኙ የስምምነት ይዘት አጠር ባለመልኩ ከጠቀሰ በኃላ የግራ ቀኙ ጥያቄ ወይም ዳኝነት የተጠየቀበት ጉዳይ ሂሣብ አጣሪ ይሾምልን የሚል እንደነበር፤የሂሳብ አጣሪዎች ከተመረጡ በኃላ ሂሳቡ በምን መንገድ ተሠራ ወደ ሚለው ፍሬ ጉዳይ በመግባት የሂሣብ ሪፖርቱ የሚመረመርበት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ፤የፍ/ቤቱ ሥልጣን የሂሳብ አጣሪ ኮመሽም የዘለለ አለመሆኑና ሥልጣኑ አጣሪ ከመሾም የዘለለ ነው የሚባልቢሆን እንኳ ግራቀኙ በስምምነታቸው መሠረት የሂሣብ አጣሪው ውሳኔ እንደሚቀበሉ በስምምነታቸው ተራ ቁጥር 4(3)መመልከቱን ፣የሂሳብ አጣሪ በፍ/ቤት ትዕዛዝ መነሻነት ከሂሳብ አጣሪነት ሊነሳ እንደሚችል ፤ይሁንና በተያዘው ጉዳይ ሂሣብ ከተጣራ በኃላ የሂሣብ አጣሪዎች ሪፖርት ይፅደቅ ወይም አይፅደቅ ወደ ሚል ክርክር ውስጥ መግባት ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚሰጡበት አግባብ አለመኖሩን በመጥቀስ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ በትዕዛዝ ክፍሉ ግራቀኙ በስምምነቱ መሠረት ያልፈፀመ ወገን ካለ የአፈፃፀም ጥያቄ ማቅረብ እንደሚቻል አስፍሯል፡፡

አመልካች የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በመቃወም ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል ፡፡ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱም ግራቀኙ ያደረጉት ስምምነት ህግና ሞራል የማይቃረን

መሆኑ ተረጋግጦ የተመዘገበ እና በይግባኝ ያልተሻረ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት የአመልካቾች ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ በአግባቡ ነው በማለት በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካቾች በሥር የመጀመሪያ እና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ተፈጽሟል ያሉትን ስሕተት በመዘርዘር የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታቸው መሠረታዊ ይዘት በሂሣብ አጣሪዎች ተፈጽሟል ያሏቸውን ግድፈቶች ከዘረዘሩ በኃላ በግራቀኙ የተደረገው እና በፍ/ቤት የተመዘገበው ስምምነት ይዘት የሂሳብ አጣሪዎችን ምርጫ ብቻ እንደሚመለከት የሁለቱም ወገኖች መብትም ሆነ ግዴታ የሚመለከት ጉዳይ በስምምነቱ ሰነድ አለመካተቱን ፤የሂሳብ አጣሪዎች የሚያቀርቡት ሪፖርትም የስምምነቱ አካል አለመሆኑን፤የሥር ፍ/ቤቶች ጉዳዩ አስቀድሞ በስምምነት አልቋል ሲሉ የደረሱበት ድምዳሜ ትክክል ባለመሆኑ እንዲሻር እና በሂሣብ አጣሪዎች የቀረበው ሪፖርት ፍ/ቤቱ አሻሽሎ እንዲያፀድቀው ጠይቋል፡፡ተጠሪ በበኩላቸው መልስ ሰጥተዋል፡፡ ዋና ፍሬ ነገሩ በአመልካቾች የቀረበው አቤቱታ የግራቀኙ ስምምነት አለማገናዘቡን ፤የሂሳብ አጣሪዎችም ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ ግዴታቸውን የተወጡ ስለመሆናቸው የግራቀኙ ስምምነት በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 3312 መሠረት ሊነካ የማይችል እና ይግባኝ አልባ ውሳኔ መሆኑ ተረጋግጦ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ በውሳኔ እንዲፀና አመልክቷል፡፡ በአመልካቾች የቀረበው የመልስ መልስ አቤቱታቸውን የሚያጠናክር ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል ፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ግራቀኙ ጉዳያቸው በግልግል ስምምነት ለመጨረስ ይችሉ ዘንድ ሂሳብ አጣሪዎች በመሾም ስልጣን እና ተግባራቸውን በመወሰን ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረጋቸው ነው፡፡ በሥር ፍ/ቤት ግራቀኙ ያቀረቡትን የእርቅ ስምምነት ህግና ሞራልን የማይቃወም በመሆኑ ተቀብሎ ማፅደቁ ከመዝገቡ ጋር የተያያዘው ማስረጃ ያሳያል በዚህ ጉዳይ ለክርክሩ መሠረት የሆነው በግራቀኙ የተደረገው የግልግል ስምምነት የሂሣብ አጣሪዎች ሪፖርት በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች በፍርድ ቤት እየታዩ መፅደቅ አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚል ነው ፡፡አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት በሂሳብ አጣሪዎች ተፈጸመ የተባለው ግድፈት በፍርድ ቤት ስሕተቱ እንዲታረም ማድረግ እንደሚችሉ ሲገለጽ ተጠሪ በበኩላቸው የሂሣብ አጣሪዎች ውሳኔ የመጨረሻ እና ይግባኝ የማይጠየቅበት መሆኑን ነው፡፡

የግራቀኙ መሠረታዊ የልዩነት ነጥብ ለክርክሩ መሠረት የሆነውን የሂሣብ አጣሪዎች ሪፖርት ተገቢነት በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ የሚችል ነው ወይስ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህንን መሠረታዊ የክርክር ነጥብ ይዘት በአግባቡ ለመረዳት በግራቀኙ የተደረገው ስምምነት ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው የስምምነቱ ክፍል ማየቱ ተገቢ ይሆናል ፡፡ ግራ ቀኙ ሰኔ 17 ቀን 2000 ዓ.ም ተስማምተው የተፈራረሙት ሰነድ እንደሚያመለክተው በጋራ ማህበር ያቋቋሙት የናዝሬት የምግብ ዘይትና ሳሙና ኢንዱስትሪና የእህል ንግድ ማህበር ስለፈረሰ ሂሳቡን በአጣሪዎች ለማጣራት መስማማታቸውን ፤የሂሳብ አጣሪዎች በተሰጣቸው ኃላፊነት መሠረት ከ1990 ዓ.ም ወዲህ ያለውን ሂሣብ አጣርተው ዕዳ ጠያቂዎች የሚያቀርቡት ማስረጃ መርምረው ዕዳውን በመቀበል ወይም ስላለመቀበል ውሳኔ እየሰጡ በመጨረሻም የማህበሩ ንብረት በመሸጥ እዳውን ከከፈሉ በኃላ ቀሪው ለተገልጋይ ወገኖች እንደ አክስዮን መጠን እንዲያከፋፍሉ መስማማታቸው፤ሂሣብ አጣሪዎች የሂሳብ መጣራቱን በሚያካሂዱበት ወቅት ከተገልጋይ ወገኖች

የሚቀርቡ ሂሳቦች ቢኖሩ እንደሚቀበሉ፣ጉዳዩም በስምምነት ለመጨረስ ጥረት እንደሚያደርጉ፣ ጥረቱ ፍሬያማ ካልሆነ ግን በንግድ እና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጎች መሠረት የራሳቸውን ውሳኔ በማድረግ ሥራቸውን በትክክል አከናውነው ከፍጻሜ እንደሚደርስ መስማማታቸውን በስምምነቱ ተራ ቁጥር 4.2 እና 4.3 በግልጽ ተመልክቷል፡፡

ግራ ቀኙ ካደረጉት የግልግል ስምምነት መገንዘብ እንደተቻለው የሂሳብ አጣሪዎች ጉዳዩን በስምምነት ለመጨረስ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ይሁንና በስምምነት መቋጨት ካልተቻለ ግን የበኩላቸውን ውሳኔ እንዲሰጡ ነው፡፡አመልካቾች የሂሳብ አጣሪዎች የሥራ ክንውን ግድፈት አለበት በማለት ይከራከራሉ፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ የሂሳብ አጣሪዎች ሪፖርት ግራቀኙን የሚያስገድድ ይግባኝ የሌለበት ውሳኔ መሆኑን ይገልፃሉ ፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ስምምነት አፅድቆታል ፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሰፈረው የአመልካቾች ጥያቄ በፍ/ቤት ትዕዛዝ የተሾሙ የሂሳብ አጣሪዎች ከኃላፊነት ይነሱልን ጥያቄ አይደለም ፡፡ የሂሳብ አጣሪዎች ተገቢ ነው ያሉትን ተግባር አከናውነው ለግራቀኙ አቅርበዋል ፡፡ ግራቀኙ ከመጀመሪያውኑ ጉዳዩ ከፍርድ ቤት ውጭ በስምምነት ለመጨረስ ተስማምተዋል ፡፡ በግራቀኙ ስምምነት መሠረትም የሂሳብ አጣሪዎች ሥራቸውን አከናውነው ውጤቱ ለሚመለከታቸው ባለ ጉዳዬች ማቅረባቸው በሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ተመልክቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ስምምነት ከመዘገበ በኃላ መዝገቡን ዘግቶታል ስምምነቱ ህግና ሞራልን የማይቃረን መሆኑ በፍ/ቤት ታምኖበት ከተመዘገበ በኃላ ያለው ሕጋዊ ውጤት እንደማንኛውም ፍርድ እንዲፈጸም አቤቱታ ሊቀርብበት የሚችል መሆኑን ከፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.277(1)እና(2) እንዲሁም ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3312 ይዘትና የሕጉ መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ክርክራቸው የሂሣብ አጣሪዎች የግራ ቀኙ ስምምነት የጣሱ ስለመሆናቸው ወይም ከስምምነቱ ውጭ መሠረታዊ እና የሥነ ሥርዓት ሕጎች በሚቃወም አግባብ ስለመሥራታቸው የቀረበ ነገር የለም ፡፡ በአንፃሩ የሂሣብ አጣሪዎች ጉዳዩን በስምምነት መቋጨት ካልተቻለ የንግድ ህግና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህጐች ተፈፃሚ በማድረግ የመጨረሻ ውሳኔ እንደሚሰጡ በግራቀኙ ስምምነት አንቀፅ 4.3 ተመልክቷል ፡፡ ይህ ግልፅ ስምምነት ባለበት ሁኔታ የሂሳብ አጣሪዎች የሥራ ክንውን ግድፈት አለበት በማለት ጉዳዩን በድጋሚ ወደ ፍርድ ቤት የሚያቀርቡበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ አመልካቾች የሂሳብ አጣሪዎችን የመጨረሻ ውሳኔ መሠረት በማድረግ ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ ይግባኝ ከሚጠይቁ በስተቀር የግራቀኙ ክርክር በሥር ፍርድ ቤት በተገለጸበት ሁኔታ የሂሳብ አጣሪዎች የሥራ ክንውን ሪፖርት በፍርድ ቤት እንዲሻሻል ያቀረቡት አቤቱታ ከግራቀኙ ስምምነት ውጭ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቾች የሂሳብ አጣሪዎች ሪፖርት ተገቢነት በፍርድ ቤት ይታይልን በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው ብለናል ፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ የግራቀኙ አስገዳጅ ስምምነት ይዘትና መንፈስ ያልተከተለ ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍ/ቤቶች የአመልካቾች የሂሳብ አጣሪዎች ሪፖርት ተገቢነት ተመርምሮ ይሻሻልልን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የህግ ስሕተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም ፡፡ በዚህ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል ፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ.መ.ቁ.06187 በ 13/07/2005 ዓ.ም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ.መ.ቁ 137138 በ 5/10/2005 ዓ.ም የሰጡት ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. አመልካቾች የሂሳብ አጣሪዎች ሪፖርት ተገቢነት በፍ/ቤት ተመርምሮ ይሻሻልልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለናል ፡፡ ይሁንና አመልካቾች በስምምነቱ መሠረት ያልፈፀመ ወገን ካለ የአፈፃፀም ጥያቄ የማቅረብ መብት የተጠበቀ ነው ፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

**ት/ጌ** **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ. 100631

ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ሮፓክ ነዋሪዎች ልማት ማህበር - ጠበቃ አቶ ማርሻል ፍቅረ ማርቆስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሮፓክ ኢንተርናሽናል ኃላፊነቱ የተወ.የግል ማህበር -ጠበቃ አቶ ያለለት ተሾመ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 128626 ጥር 30 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መዝገብ ቁጥር 98701 ሚያዝያ 22 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 197501 ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የግልገል ዳኛ እንዲሰየም ትእዛዝ ይስጥልኝ በሚል መንገድ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ለስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ማመልከቻ ነው፡፡ ከሳሽ (አመልካች) ተከሳሽ(ተጠሪ) ከአባላቱ ጋር በተለያየ ጊዜ በተዋዋለው የመኖሪያ ቤት ግንባታ ውል ቤቶቹ ለሚሰሩበት መንደር የመሰረተ ልማት ግንባታና ልማት ስራ ለማከናወን ለነዋሪዎቹ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግየውል ግዴታ ገብቷል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ (ተጠሪ) በውሉ በገባው ግዴታ መሠረት የመሠረተ ልማት ግንባታ እንዲያከናውን ሲጠየቅ፤የግንባታ ስራውን ለመስራት ፍቃደኛ አልሆነም፡፡ተከሳሽ ከከሳሽ አባላት ጋር ባደረገው ውል በአፈፃፀም ሂደት የሚፈጠር አለመግባባት ለግልግል ዳኛ የሚቀርብ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ የግልግል ዳኛ እንድንሰይም ባቀረባቸው ጥያቄ መሰረት የግልግል ዳኛ ለመሰየም ፍቃደኛ ባለመሆኑ ፍርድ ቤት ተከሳሽ የግልግል ዳኛ እንዲሰይምና ስብሳቢ ዳኛ ሊሰየም በሚችልበት ሁኔታ ትእዛዝ እንዲሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡
2. ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ፤ ከከሳሽ (አመልካች) ጋር ያደረኩት የውል ግንኙነት የለም፡፡ ከሳሽ አባላቱን ለመወከል በግልግል ጉባኤ ለመከራከር የሚያስችለው ልዩ ውክልና በአባላቱ አልተሰጠውም፡፡ ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው መብትና ጥቅም ወይም የውክልና ስልጣን የለውም፡፡ ስለዚህ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተኝ

በማለት ተከራክሯል። የስር ፍርድ ቤት የተከሳሽን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግና ከሳሽ የተቋቋመበት አላማ በተከሳሽ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው በመሆኑ ተከሳሽ የግልግል ዳኛ እንዲሰይም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል።

3. ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል። የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኃላ መልስ ሰጭ(አመልካች) አባላቶችን በመወከል ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው የውክልና ማስረጃ ያላቀረበ በመሆኑ፤ ይግባኝ ባይ (ተጠሪ) የግልግል ዳኛ እንዲሰይም ጥያቄ ለማቅረብ አይችልም በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል። አመልካች ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል። ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካች ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 377 መሰረት ሰርዞታል።
4. አመልካች ግንቦት 5 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ አመልካች የአባላቱን መብትና ጥቅም ለማስከበር የተቋቋመ ማህበር መሆኑን ተጠሪ አምኖ የተለያዩ ደብዳቤዎችን ሲፃፃፍ ቆይቷል። ተጠሪ ከተጠያቂነት ለማምለጥ ያቀረበውን ክርክርና መቃወሚያ በመቀበል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲሻርልኝ የሚል ይዘት ያለው የሰበር አቤቱታ አቅርቧል። ተጠሪ በበኩሉ አመልካች በተጠሪ ላይ የግልግል ዳኛ እንዲሰየምለት ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችለው ውክልና ወይም ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ መብትና ጥቅም የሌለው በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚል ይዘት ያለው መልስ ሐምሌ 22 ቀን 2006 ዓ/ም በፅሁፍ አቅርቧል። አመልካች ነሐሴ 13 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል።
5. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ችሎት ያቀረቡትን የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ለተጠሪ የግልግል ዳኛ እንዲሰይም ክስ ለማቅረብና ለመጠየቅ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት የሰጡት ብይን (ውሳኔ) የህግ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።
6. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካች ህጋዊ ህልውና ሲያገኝ ሊያሳካቸው የሚችላቸው መሰረታዊ ዓላማዎችና አመልካች አላማዎቹን ለማሳካት ሊፈፅማቸው ስለሚችላቸው ህጋዊ ተግባራት መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል። ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በኦሮሚያ ክልል በፊንፍኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ ሮፓክ ቀበሌ ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች የተመሰረተና የአካባቢ ብክለትና የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል፤ጎርፍለመከላከል፤ የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ስራ ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር፤ የልማት ስራ የመስራትና የመሰረተ ልማትና የማህበሩ የአገልግሎት ተቋማት በፕላን መሰረት መገንባታቸውን በአባላቶቹ ስም ለመከታተልና ይህ ግዴታ ያለበት ሶስተኛ ወገን በሕጉ መሰረት ግዴታውን እንዲወጣ ለማድረግ በአባላቱ ስም አስፈላጊውን ለመፈጸም ለማስፈፀምና ሌሎች አላማዎችን ለማሳካት የተቋቋመ ማህበር መሆኑን ከማህበሩ መመስረቻ ፅሑፍ አንቀጽ 5 የተዘረዘረ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ከሰጡት ውሳኔና ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር ይዘት ለመረዳት ችለናል።
7. ይህም ከተጠሪ ጋር በተናጠል የቤት ግንባታና የማዘዋወር ውል የተዋዋሉ ግለሰቦች፣ተጠሪ በተናጠል በገባላቸው የውል ግዴታ በአንቀጽ 1 በተደነገገው መሠረት የመሠረተ ልማት ተቋማትን የመገንባትና የአገልግሎት ሰጭ ማዕከላትን የመገንባት ግዴታውን ያልተወጣ

በመሆኑ፣ ተጠሪን ከውል ወይም በሕግ ስልጣን ለተሰጠው አካል በማቅረብ የውል ግዴታውን እንዲወጣ ክስ የማቅረብና ተከታትሎ የማስፈፀም ዓላማና ሌሎች አላማዎችን የሚያሳካ ማህበር በመፍጠር፣ የፈጠሩት ማህበር፣ የማህበሩ አባላት በተናጠል ከውል የመነጨ መብታቸውን፣ለማስከበር ቢንቀሳቀሱ፣ የሚያወጡትን ወጭዎችና ጊዜ በሚቆጥብ ሁኔታ በተደራጀ መንገድ ማህበሩ ጥያቄ እንዲያቀርብላቸው ሙሉ ፈቃድና ስምምነታቸውን ሥልጣን ባለው የመንግስት አካል ፊት በመቅረብና የማህበሩን መመስረቻ ፅሑፍ በፊርማቸው በማፅደቅ የሰጡ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች በውሣኔያቸው ካሰፈሩትና ከደረሱበት የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ ለመረዳት ይቻላል፡፡

8. አመልካች የተቋቋመበት አንደኛው መሰረታዊ ጉዳይ የማህበሩ አባላት አመልካችን ከማቋቋማቸው በፊት በተናጠል ከተጠሪ ጋር ባደረጉት የመኖሪያ ቤት ግንባታና የማዘዋወር ስምምነት መሰረት ተጠሪ ግዴታውን እንዲወጣ አባላቱን በመወከል አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ክስና ሌሎች የዳኝነት ጥያቄዎችን በማቅረብ ኃላፊነት ያለበት ሶስተኛ ወገን /ተጠሪ/ ግዴታውን እንዲፈጽም ለማድረግ መሆኑ በአመልካች መመስረቻ ጽሁፍ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 11 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ አመልካች ይህንንና ሌሎች ዓላማዎችን ለማሳካት እንዲንቀሳቀስ ዕውቅና ፈቃድ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተሰጥቶታል፡፡ይህም አመልካች በአላማነት ይዟቸው የተነሱ ተግባሮች ለመፈጸም የሚያስችልን ህጋዊ ተግባራት እንዲፈጽም አባላቱ ማህበሩን ሲመሰርቱ በሰጡት ፍቃድና ስምምነት መሰረት የመንቀሳቀስ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ከአዋጁ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 55 ድንጋጌዎችና ከአዋጅ ድንጋጌ ጋር የሚቃረን ይዘትና ውጤት ያላቸው የሌሎች ህጎች ተፈጻሚነት የሌላቸው መሆኑን ከሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 110 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘት ህጋዊ ውጤት በማገናዘብ ለመረዳት ይችላል፡፡

9. ለዚህም ምክንያቱ የአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 110 ድንጋጌ፣ ከአዋጅ ጋር የማይቃረኑ የፍትሐብሔር ሕጉና የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሚከለክል ይዘትም ሆነ ሕጋዊ ውጤት የሌለው መሆኑ ነው፡፡ ይህም ስለ ማህበራት "ችሎታ" የሚደነግገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 454 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንድናገናዝብ የሚጠይቅ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለማህበራት ችሎታ የሚደነግገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 454 ንዑስ አንቀጽ 1 "ማህበሩ ከዓይነቱ ጋር የሚያስማማበትን ብሔራዊ የኑሮ ተግባሮች ሁሉ ለመፈፀም ይቻላል" የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ከዚል አንፃር ሲታይ፣ አመልካች የተቋቋመበትን መሠረታዊ ዓላማ ለማሳካት የሚያስችለውን የዳኝነት ጥያቄ የአባላቱን መብትና ጥቅም ለማስከበር በሚያስችለው አግባብ ለመጠየቅ ከአዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 55፣አንቀጽ 110 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 454 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች የሚፈቅድለት መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

10. ከዚህ በተጨማሪ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 35 ድንጋጌ፣ ከአንድ ሰው አንድ አይነት መብትና ጥቅም የሚጠይቁ ካሉ ከሳሾች፣ መብትና ጥቅማቸውን እነሡን በመወከል የሚጠይቅ በህግ ዕውቅና የተሰጠውና ህጋዊ ህልውና ያለው ማህበር በማቋቋም፣ በማህበሩ መብታቸውን እንዲጠይቅላቸው በማህበሩ መመሥረቻ ፅሑፍ በሙሉ ፈቃድና ስምምነት በማፅደቅ የሚሰጡትን ስምምነት ዋጋ በሚያሳጣ ሁኔታ መተርጐም ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአንፃሩ የህግ ህልውና ያገኙ የሲቪል ማህበራት ፣የተቋቋሙለትን ዓላማ ለማሣካትና፣ ሲያከራክሩት የሚፈልጉትን የአባላታቸውን መብትና ጥቅም ለማስከበር፣ ለፍርድ ቤት ለግልግል ተቋም ወይም ለሌሎች የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት ጥያቄዎችን ለማቅረብ በሚያስችል መንገድ የሕጉን ድንጋጌዎች መተርጐም በግልና

በተናጠል እንዲሁም በራሳቸው ችሎታ ተከራክረው መብትና ጥቅማቸውን ለማስከበር ከፍተኛ ወጭና ጊዜ የሚጠይቃቸው ግለሰቦች፣ ለዚህ ዓላማ በመሠረቱት ማህበር በኩል መብትና ጥቅማቸውን በቀላሉ ለማስከበር የሚችሉበትን ዕድል በሚያሰፋና የሰዎችን ፍትህ የማግኘት መብት የሚያረጋግጥ አግባብ መተርጐም ያለበት ሆኖ አገኝተነዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ በሕግና በሚመለከተው የመንግስት አካል ዕውቅና የተቋቋሙ ማህበራት፣ የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት፣ የሚያስችላቸው የዳኝነት ጥያቄ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ያቀረበው መቃወሚያ ከላይ በዝርዝር የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ይዘትና ተግባራዊ ተፈፃሚነት ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

11. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸውን ድንጋጌዎች ይዘትና ተግባራዊ ውጤት ሣያገናዝቡ አመልካች የግልግል ዳኛ እንዲሰየምለት ለማቅረብ አይችልም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ውሣኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 197501 ታህሳስ 1 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ. 94511

30/01/2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካቾች፡-

1. ወ/ሮ ብዙ ሰንበታ } ቀረቡ
2. ወ/ሮ ባይሴ ሰንበታ

ተጠሪ፡- አቶ ታደሰ ሰንበታ - መብታቸው ታልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይግባኙ ሊሰማ በተቀጠረበት ዕለት በቀጠሮው ሰዓት ለመድረስ ያልቻሉት ለጠበቃቸው የሰጡት የውክልና ስልጣን ማስረጃ በእጃቸው በመቅረቱ እና የሚመጡትም ከርቀት አካባቢ በመሆኑ ምክንያት መንገድ በመዘጋጋቱ በመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 73 መሰረት የተዘጋው የይግባኝ መዝገብ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 74(2) መሰረት ተከፍቶ እንዲታይላቸው ያቀረቡት አቤቱታ በበቂ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በውሳኔ የጸናው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካቾቹ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በነበራቸው ክርክር መዝገቡ በ4፡00 ሰዓት ተዘግቶ አመልካቾቹ በዚያኑ ቀን በ4፡30 ሰዓት በፍርድ ቤቱ የደረሱ መሆናቸውን እና በሰዓቱ ለመድረስ ያልቻሉትም በመንገድ ስራ ምክንያት መንገድ በመዘጋጋቱ መሆኑን ገልጸው በሚከራከሩበት ሁኔታ አመልካቾቹ ያቀረቡት ምክንያት በቂ ምክንያት የሚባል አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾቹን አቤቱታ ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት "በቀዳሚው ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረው በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተረዳው እንደሆነ" በሚል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 74(2) ስር ከተመለከተው ሐረግ ይዘት እና ተፈጻሚነት አንጻር ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ የተላከላቸውን መጥሪያ ፈርመው ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸው በስርዓቱ መሰረት በመረጋገጡ የመከራከር መብታቸው እንዲታለፍ ተደርጓል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ

የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የአሁኖቹ አመልካቾች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የግራ ቀኙን የይግባኝ ክርክር ለመስማት ለ18/03/2005 ዓ.ም. ከጠዋቱ በ3፡00 ሰዓት ተይዞ በነበረው ቀጠሮ በይግባኝ ባዮቹ በኩል የቀረበ ሰው ባለመኖሩ ተጠሪው ያቀረቡትን ክርክር በመቀበል ፍርድ ቤቱ መዝገቡን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 73 መሰረት የዘጋው መሆኑ፣አመልካቾቹ በዚሁ ዕለት ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ላይ ቀርበው በሰዓቱ በቀጠሮ ሊገኙ ያልቻሉት ለጠበቃቸው የሰጡት የውክልና ስልጣን ማስረጃ በእጃቸው በመቅረቱ፣የሚመጡትም ራቅ ካለ አካባቢ በመሆኑ እና አዲስ አበባ ከተማ ከገቡ በኃላም ፍርድ ቤቱ የሚገኝበትን አካባቢ እና የታክሲ መያዣ ቦታውን በትክክል ባለማወቃቸው መሆኑንበመግለጽ መዝገቡ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 74(2) መሰረት ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ትዕዛዝ እንዲሰጥላቸው በጽሁፍ የጠየቁ መሆኑ በክርክሩ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ሲሆኑ ፍርድ ቤቱ በአቤቱታቸው ላይ የሌላኛውን ተከራካሪ ወገን አስተያየት ከተቀበለ በኃላ መዝገቡ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል አመልካቾቹ ያቀረቡትን ጥያቄ ሳይቀበል የቀረው ይዘቱ ከላይ የተመለከተው በአመልካቾቹ በኩል የቀረበው ምክንያት በቂ ሊባል የሚችል አይደለም በማለት ነው፡፡

በመሰረቱ በአንድ ነገር ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ እና ተከሳሹ ቀርቦ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉም ሆነ በከፊል ያመነ እንደሆነ ከሳሹ በሌለበትም ቢሆን ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በሙሉ ወይም በከፊል ላመነው ጉዳይ የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት እንደሚችል እና ከሳሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን በመዝጋት እንደሚያሰናብተው በፍትሐብሄር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 73 ላይ የተመለከተ ሲሆን ይህ ድንጋጌ በይግባኝ ክርክር ጉዳዮች ላይ ጭምር ተፈፃሚነት ያለው መሆኑም በቁጥር 32(2) ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ በሌላ በኩል በቀነ ቀጠሮው ሳይቀርብ የቀረበትን ምክንያት በመግለጽ ይግባኝ ባዩ መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መዝገቡ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ጥያቄውን ለፍርድ ቤቱ ሊያቀርብ የሚችል ስለመሆኑ እና ይግባኝ ባዩ በቀዳሚው ቀነ ቀጠሮ ሳይቀርብ የቀረው በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ የተረዳው እንደሆነ ስለኪሳራው እና ስለ ማናቸውም ወጪ አከፋፈል ተስማሚ መስሎ የታየውን ውሳኔ ከሰጠ በኃላ የተዘጋው መዝገብ እንደገና ተከፍቶ ነገሩ እንዲቀጥል ትዕዛዝ መስጠት የሚችል ስለመሆኑ በቁጥር 74(2) ተደንግጓል፡፡እንደሚታየው ይህ ድንጋጌ ይግባኝ ባዩ በቀነ ቀጠሮው ሳይቀርብ የቀረበት ምክንያት በቂ ሆኖ የሚገመት እክል መሆን እንደሚገባው ከመግለጽ ውጪ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ውስጥ የሚካተቱት ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ የሚጠቁመው ነገር የለም፡፡ይህም በዚህ ረገድ የሚቀርብላቸውን አቤቱታ ከድንጋጌው ይዘት እና ዓላማ አንጻር መርምሮ ተገቢውን ዳኝነት የመስጠት ኃላፊነት የፍርድ ቤቶች መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾቹ ጉዳዩ እንዲንቀሳቀስላቸው አቤቱታ ያቀረቡት መዝገቡ በተዘጋ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መሆኑ እና ለጠበቃቸው የውክልና ስልጣን የሰጡትም ቀጠሮው ከመድረሱ ከስምንት ቀናት በፊት በ10/03/2005 ዓ.ም. በወልመራ ወረዳ ፍትሕ ጽ/ቤት በኩል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡አመልካቾቹ ለጠበቃቸው የሰጡት የውክልና ስልጣን ማስረጃም በእጃቸው የቀረ መሆኑን በመግለጽ የተከራከሩ ሲሆን በአንጻሩ የውክልና ስልጣን ማስረጃው አስቀድሞ ለጠበቃቸው ተሰጥቶ የነበረ ስለመሆኑ በተጠሪው በኩል የቀረበ ክርክር እና ማስረጃ የለም፡፡የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቾቹ ያቀረቡት ምክንያት በቂ ሊባል የሚችል አይደለም ከማለት ውጪ በቂ ተደርጎ ሊወሰድ ያልቻለው በምን ምክንያት እንደሆነ በውሳኔአቸው ላይ በግልጽ አላሰፈሩም፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚሰጥ ውሳኔ ደግሞ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 182(1) ስር

በአስገዳጅነት የተቀመጠውን የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት የተከተለ ባለመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡ ይልቁንም አመልካቾቹ ጉዳዩ እንዲንቀሳቀስላቸው አቤቱታ ያቀረቡት መዝገቡ በተዘጋ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መሆኑ ሲታይ ጉዳያቸውን በአግባቡ በመከታተል ላይ የነበሩ መሆኑን እና በሰዓቱ በቀጠሮው ሳይገኙ የቀሩትም በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል በመሆኑ አመልካቾቹ መዝገቡ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ያቀረቡት አቤቱታ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 74(2) መሰረት ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው ይገባ እንደነበረ ከክርክሩ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ሲጠቃለል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 73 መሰረት የተዘጋው የይግባኝ መዝገብ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 74(2) መሰረት ተከፍቶ እንዲታይላቸው አመልካቾቹ ያቀረቡት አቤቱታ በበቂ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በውሳኔ የጸናው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የተዘጋው የይግባኝ መዝገብ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል አመልካቾቹ ያቀረቡት አቤቱታ በበቂ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 141122 በ09/04/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 158692 በ13/01/2006 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾቹ በሰዓቱ በቀጠሮው ሳይገኙ የቀሩት በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ መዝገቡ ተከፍቶ ክርክሩ እንዲቀጥል ያቀረቡት አቤቱታ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 74(2) መሰረት ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. መዝገቡን አንቀሳቅሶ ክርክሩን ቀጥሎ በመስማት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት ወስነናል፡፡
4. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
5. ቁጥሩ 141122 የሆነው መዝገብ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይመለስ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ አመልካቾች የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::**

**ሃ/ወ**

የሰ/መ/ቁጥር 94713

መጋቢት 16 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካቾች፡- 1. ህጻን ሲኢድ ዘውዴ
2. ህጻን ኑሩ ሁሴን ዘውዴ
3. ህጻን አዲሱ ዘውዴ
} ሞግዚት ወ/ሮ ሙሉ ሞሳ - ጠበቃ ሆነልኝ ዋለ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1.ወ/ሮ ጥሩሰው ሞሳ
2. ሶፊያ አግማስ
3. ፋንታ አግማስ
4. አስጋርጅ አግማስ
5.ብርቄአግማስ
6. ሞሚና አግማስ
7. ጥጋቡ አግማስ
8. በላይ አግማስ
} የ1ኛ፣2ኛ፣3ኛ፣5ኛ-8ኛ ጠበቃ አዲስ መንግስት ቀረቡ፡፡
9. አለሚቱ ታደሰ ⟶ ታልፏል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከውርስ ንብረት ግምት ክፍያ ጋር ተያይዞ የቀረበ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው ያሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት ላይ በአማራ ብሔራዊ ክልልዊ መንግስት በደብረ ታቦር ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻነት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት ተከሳሽ፣ አሁን ከተራ ቁጥር አንድ እስከ ስምንት የተጠቀሱት ተጠሪዎች ከሳሾች፣9ኛ ተጠሪ ደግሞ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡

የክሱ ይዘትም፡-ከተጠሪዎች መካከል ከተራ ቁጥር ሁለት ጀምሮ ያሉት ከወላጅ አባታቸው ከሟች አቶ አግማስ አምባው ላይ በውርስ ያገኙትንና አዋሳኙ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን በ369 ካ/ሜትር ያረፈውን ቤት ከሟች ባለቤት ከወ/ሮ ጥሩሰው ሞሳ ጋር እኩል ተካፍለው ከይዞታው ውስጥ 184.57 ካ/ሜ ከወ/ሮ ጥሩሰው ሞሳ ድርሻ ውጪ ያለው ግማሹን በወ/ሮ ሙሉ ሞሳ ተይዞ እንደሚገኝ፣ይህንኑ ቤትና ቦታ የወ/ሮ ሙሉ ሞሳ ባለቤት አቶ ዘውዱ አግማስ እንደስር ከሳሾችና ሌሎች የሟች ወራሾች ሁሉ የሟቹ ልጅ በመሆናቸው በቤቱ ላይ ወርሃዊ ኪራይ ክፍያ

እየከፈሉ ይዘው ቆይተው አቶ ዘውዱ አግማስ በመስከረም ወር 2001 ዓ/ም ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ በኋላ ወ/ሮ ሙሉ ሞሳ ቤቱን ያለ ክፍያ ይዘው የተቀመጡ መሆኑን ዘርዝረው ከጥቅምት ወር 2001 ዓ/ም ጀምሮ የቤቱን ጥቅም በተመሳሳይ ቤት በአካባቢው ያሉ ቤቶች በሚያስገኙት ዋጋ መጠን እንዲከፍሉና ቤቱንም እንዲለቁ ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስም ጉዳዩ ቀድሞ በፍርድ ማለቁንና ጥያቄው ውርስ ሳይጣራ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚሉ ነጥቦችን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተው በፍሬ ነገሩ ደግሞ አውራሹ ሳይሞቱ የነበረው ሙሉ ቤትና ቦታ በአንድ በኩል ከሞቱ በኋላ ለሁለት የተከፈለው ቤትና ቦታ ተይዞ ሁለቱ ቤትና ቦታዎች በገንዘብ እያንዳንዳቸው ያለመገመታቸውን፣ የቤት ኪራይ ውል በጽሑፍ ሳይኖር የክፍያ ጥያቄ መቅረቡ ያላግባብ መሆኑን፣ ቤቱን የያዙትም ባለቤታቸው አቶ ዘውዱ አግማስ የአውራሹ ልጅና ወራሽ በመሆናቸውና የአሁኑ አመልካቾችን የወለዱላቸው በመሆኑ አመልካቾች በተተኪ ወራሽነት በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን፣ ስለቤቱ ከአውራሹ ሞት በኋላ የተሰጡ የምስክር ወረቀቶችን በተመለከተ መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ/ም የተሰጠውን የሚስማሙበት ሆኖ የካቲት 15 ቀን 2001 ዓ/ም የተሰሩትን ግን ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላ የተሰሩ፣ ነገር ግን የእርሱ ስም የተጠቀሰባቸው የተተኪዎችን ጥቅምና መብት የማያስከብሩ በመሆናቸው ተቀባይነት ሊሰጣቸው እንደማይገባና ሊሰረዙ የሚገባቸው መሆኑን፣ የውርሱ ጉዳይ ስለቤቱ ብቻ ሳይሆን ስለሌሎች ተንቀሳቃሽ ንብረቶችም ጭምር በመሆኑ በአጣሪ ሊጣራ እንደሚገባ፣ የእርቁ ጉዳይን ለማረጋገጥ የቀረበው ሰነድም ባለቤታቸው ተስማሚ ያልሆኑበት ሰነድ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ፣ ክሱ የቀረበበት ቤት ሟች ባለቤታቸው ከአባታቸው ከአቶ አግማስ አምባው ለጎጆ መውጫ እንዲሆናቸው የተሠጣቸው መሆኑን፣ የውርስ ሃብት ክፍፍል ይደረግ ከተባለውም ተከሳሽ እና ሌሎች ወራሾች እየተጠቀሙበት ያለው የአቶ አግማስ አምባው ንብረቶች በአጣሪ ተጣርተው ሊካፈሉ ይገባል እንጂ ተከሳሽ የያዙትን ቤት ብቻ የሚያካፍሉበት አግባብ ያለመኖሩን ዘርዝረውና በውርሱ ሊካተቱ ይገባል ያሏቸውን የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን አይነታቸውና ግምታቸውን ጠቅሰው ክፍፍሉ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ በተከሳሽ የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ውድቅ አድርጎ ከአለፈ በኋላ ፍሬ ነገሩ ላይም ግራ ቀኙን በቃል ከአከራከረና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ ከአጣራ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ክርክር የተነሳበትን ቤት ተከሳሽ ይልቀቁ፣ ከአስሩ የሟች አቶ አግማስ ልጆች ጋር የተከሳሽ ልጆችበአባታቸው አቶ ዘውዱ እግር ተተክተው ተጠቃሚ ይሁኑ፣ ከጥቅምት 01 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ታህሳስ ወር 2002 ዓ/ም ድረስ ያለውንተከሳሽ ቤቱን ይዘው የተጠቀሙ በመሆኑበወር አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር ቤቱ እንደሚከራይ በአካባቢው ግምት መነሻ ተረጋግጧል ብሎ ይህንኑ ስሌት መሰረት አድርጎ እስከ ታህሳስ ወር 2002 ዓ/ም ድረስ ያለውን የኪራይ ገንዘብ ብር 21,000.00 አንድ አስረኛ ድርሻ ትተው ተከሳሽ ለከሳሾች እንዲከፍሉ፣ጧልቃ ገብም አንድ አስረኛ ከቤቱም ሆነ ከኪራዩ ገንዘብ እንዲያገኙ፣ የዳኝነት ገንዘቡን በተመለከተም ተከሳሽ ለከሳሾች  እንዲተኩ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁኑ አመልካቾችም በተሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸውን ለደቡብ ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ያልተከፋፈለ የሟች አግማስ አምባው ንብረት በመሆኑ ወራሾች ባሉበት ሁኔታ ለመካፈል ካልተስማሙ በጨረታ ተሸጦ አንድ አስረኛ ድርሻ ለአሁኑ አመልካቾች ሁኖ ቀሪውን ተጠሪዎች በድርሻቸው እንዲከፋፈሉ፣ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስን

በተመለከተም ተጠሪዎች አመልካች የዳኝነት አልከፈሉም ከማለት በስተቀር ሌላ ክርክር አላቀረቡም፣ በይግባኝ ሰሚው ችሎት ያቀረቡት የይርጋ ክርክርም ተቀባይነት የሌለው ነው በሚል ምክንያት አርባ ሺህ የተገመተ አይነታቸው ሃያ የሆኑ ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን ተጠሪዎች ለአመልካቾች በድርሻቸው እንዲከፍሉ በማለት በአብላጫ ድምጽ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካቾች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በአመልካች መከላከያ መልስ ጋር በአማራጭ መልስነት የቀረበና ዳኝነት የተከፈለበት ስለመሆኑ የማያሳይ እና ክሱ ስርዓቱን ጠብቆ ያልቀረበ ሁኖ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስን ራሱ ከይግባኝ ክርክር ጋር ተቀብሎ ተጠሪዎች የሚንቀሳቀሱ ንብረቶቹን ግምት ለአመልካቾች ድርሻቸውን እንዲከፍል በማለት የሰጠው ውሳኔ ስነ ስርዓታዊ አይደለም፣ የቤት ኪራዩንም አመልካች የሚከፍሉበት የሕግ አግባብ የለም በሚል ምክንያት በዚህ ረገድ የተሰጡትን የውሳኔ ክፍሎች የሻራቸው ሲሆን በአመልካቾች ሞግዚት ተያዘ የተባለውን ቤት በተመለከተ ግን እንዲለቀቅና ለወራሽ ልጆች እንዲያስረክቡና አከፋፈሉን በተመለከተም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1272 እና ተከታዩቹ መሰረት የሚፈጸም ሁኖ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት አጽንቶታል፡፡የዳኝነት ገንዘቡን በተመለከተ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍልንም አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት በዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው የውሳኔ ክፍል ቅር በመሰኘት የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-- አከራካሪውን ቤት እንዲለቁ መወሰኑ ከህፃናት መብትና ጥቅም አንፃር ተገቢ ያለመሆኑን፣ በጉዳዩ ላይ ያነሱት ይርጋ መታለፉም ያላግባብ መሆኑን፣ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስም ስርዓቱን ጠብቆ ስልጣን ላለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበ ሁኖ እያለ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ መሆኑን፣ ባልተከፋፈለ የጋራ ሃብት ላይ በቀረበ ክስ ረቺና ተረቺ በሌለበት ሁኔታ የዳኝነት ገንዘብ እንዲከፍሉ መደረጉም ከህግ ውጪ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ሊለወጥ ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ አይደለም ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ዳኝነት ሳይከፈል ክሱ ቀርቦ ከታየ በኋላ ፍርድ ቤቱ ሊከተለው ስለሚገባው ስርዓት ይህ ችሎት ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንፃር ለመመርመር ተብሎ ለዚህ ችሎት የቀረበ ሲሆን ከ9ኛ ተጠሪ በስተቀር ሌሎች ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና ይዘት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሣኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡ በዚህም መሰረት በጭብጥነት የተያዘው ጉዳይ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት የሚመለከት በመሆኑ የአመልካቾች ሞግዚት ቤቱን እንዲለቁ፣ በቤቱ ላይ ያነሱት የይርጋ መቃወሚያ፣ እንዲሁም የዳኝነት ገንዘብ እንዲከፍሉ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ያቀረቡት የሰበር ቅሬታ በዚህ ችሎት እንዲታይ ያልተደረገ ከመሆኑም በላይ አመልካቾች በወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ ታልፎ ቤቱን እንዲለቁ፣ የዳኝነት ገንዘቡንም እንዲከፍሉ ተወስኖባቸው ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት የይግባኝ ክርክርም በዚህ ረገድ በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ፀንቶባቸው ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረቡት የአሁኑ ተጠሪዎች መሆናቸውን የክርክሩ ሂደት

ስለሚያሳይ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ደግሞ አመልካች በዚህ ረገድ መስቀለኛ ይግባኝ ወይም የመቃወሚያ ክርክር ያቀረቡ ስለመሆኑ ውሳኔው ስለማያሳይ በዚህ ችሎት በእነዚህ ነጥቦች ላይ የሚያቀርቧቸው ክርክሮች ተቀባይነት የሚያገኙበት የስነ ስርዓት ሕግ አግባብ የለም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረቡትን የአመልካቾችን የክርክር ነጥቦች ስርዓቱን ጠብቀው ያልቀረቡ በመሆኑ አልፈናቸዋል፡፡

ስለተከሳሽ ከሳሽነት የቀረበውን ቅሬታ በተመለከተ ከክርክር ሂደቱ መገንዘብ እንደሚቻለው ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካቾች ሞግዚት ከፍ ሲል እንደተገለፀው ዳኝነት ጠይቀው እየተከራከሩ ያለው አከራካሪ ከሆነው ቤት ጭምር ሌሎች የሚንቀሳቀሱ የውርስ ንብረቶች መኖራቸውን ገልጸውና የንብረቶችን አይነት፣ብዛትና ግምታቸውን ዘርዝረው እነዚህ ንብረቶች የውርሱ አካል ተደርገው ክፍፍሉ ሊፈፀም ይገባል በማለት ሲሆን ይህን የዳኝነት ጥያቄ በወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት ግን ተጠሪዎች ባቀረቡባቸው ክስ የመከላከያ መልስ ሲያቀርቡ በአማራጭ መልስነት ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን የመራበት ሁኔታም ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት ግራ ቀኙን በስር የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ያስገነዝባል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቀራረብ ስርዓት በሕጉ የተቀመጠውን አግባብ ያለመከተሉን በአቢይ ምክንያትነት ጠቅሶ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔውን መሻሩን ከውሳኔው ተገንዝበናል፡፡አመልካቾች በዚህ የሰበር ክርክር ደረጃ አጥብቀው የሚከራከሩት ደግሞ በወረዳው ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ ነበር ሳይሉ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩ እንዲቀጥል ተደርጎ የንብረቱ ግምትም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን እንዲኖረው የሚያደርግ በመሆኑ ክርክሩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከይግባኝ ክርክር ጋር እንዲታይ ተደርጓል በሚል ነው፡፡ ሆኖም አመልካቾች በስር ፍ/ቤት ተከሳሾች እንደመሆናቸውና እነሱም በበኩላቸው ከተጠሪዎች የሚጠይቁት መብት ካላቸው በህጉ አግባብና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 234/1/ /ረ/ መሰረት ከመከላከያ መልሳቸው ጋር የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 215/2/ ስር እንደተመለከተው በመፈፀም በተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የተጠቀሱት የሚንቀሳቀሱት ንብረቶች ግምት እንዲከፈላቸው በሚል የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ የለም፡፡ በዚህ አግባብ ተሟልቶ የቀረበ የዳኝነት ጥያቄ በሌለበት ደግሞ ዳኝነቱ ሊሰጥ አይችልም፡፡ አመልካቾች በተከሳሽነታቸው በተሰጣባቸው ውሳኔ ይግባኝ ብለው በሄዱት ክርክር ላይ በስር ፍርድ ቤት በሕጉ አግባብ ያልቀረበ የተካሳሽ ከሳሽነት ክስ እንዲቀርብ ተደርጎ ከይግባኙ ጋር የሚወሰንበት አግባብ የለም፡፡ እንዲህ አይነት የክርክር አመራር የተከራካሪ ወገኖችን የመሰማት መብትም የሚጎዳ በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 17352 የሠጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚመለከተው ተገቢው ዳኝነት ክፍያ ሳይፈፀም በፍርድ ቤት በቀጠለ ክርክር ስለሚፈፀም ስርዓት እንጂ ከመነሻው የክስ አቀራረብ ስርዓትን ሳይከተል የቀጠለውን ክርክር ሁኖ የሚመለከት አይደለም፡፡

ሲጠቃለል ከፍ ሲል በተገለፁት ምክንያቶች የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካቾች የዳኝነት አገልግሎት ፈፅመው የተከሳሽ ከሳሽ ዳኝነቱንም በስርዓቱ ባላቀረቡበት ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ግምት በተመለከተ ተጠሪዎች የአመልካቾችን ድርሻ እንዲከፍሉ ሊገደዱ አይገባም፣ አመልካቾች በሕጉ አግባብ ክስ ሊያቀርቡ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመፅናቱ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መ/ቁ 31215 ሰኔ 05 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁ 33634 ጥቅምት 15 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካቾች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ አይደለም ተብሎ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በተሰጠውና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፀናው የውሳኔ ክፍል የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ በሌሎች ነጥቦች ላይ የተሰጠው ውሳኔም አልተነካም፡፡
3. ለዚህ የሰበር ክርክር ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

## ትዕዛዝ

በዚህ መዝገብ ህዳር 04 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡*

የ/ማ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ ቁጥር 97217

መጋቢት 16 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ባካፋ አንለይ -- ራሳቸው ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ቴዎድሮስ አንለይ - ጠበቃ ጌትነት አየለ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ያለአግባብ የተያዘ የመኖሪያ ቤት ይለቀቅልኝ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ በመሠረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 08 ክልል ውስጥ የሚገኘውን፣ በካርታ ቁጥር 10/00/93 የሚታወቀውንና በ660 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ሰፍሮ በስማቸው ተመዝግቦ ያለውን መኖሪያ ቤት ተከሳሽ ምንም መብት ሳይኖራቸው ከህዳር ወር 1998 ዓ.ም ጀምሮ በመያዝ እየተጠቀሙበት እንደሚገኙ ገልፀው ቤቱ እንዲለቀቅላቸውና ያላግባብ ቤቱን ለተጠቀሙበት ጊዜ ደግሞ በወር ብር 2000.00(ሁለት ሺህ) ኪራይ ታስቦ እንዲከፈላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተከሳሽ የሰጡት የመከላከያ መልስም፡- ከሳሽ ቦታውን የተመሩበት ካርኒ አላቀረበም፡፡ ቤቱ በ1963 ዓ.ም የተሠራ ሲሆን ውሃና መብራት የገባው በወላጅ አባታችን በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም በመሆኑ ቤቱ የአባታችን ቤት ነው፡፡ በአባታችን ስም የተከፈተው የማህደር ቁጥር 1224 የአባታችን ቤት መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ማህደሩ በሙሉ ተዘርፏል፡፡ ግብርበአባታችን ስም የተገበረ ለመሆኑ የባህር መዝገብ ቁጥር 202 ስለሚያስረዳ ቀርቦ መታየት ይችላል፡፡ ቤቱ ከአባታችን ሞት በኋላ ከእናታችን ጋር የምንገለገልበት እንጅ ተከራይቶ አያውቅም፡፡ ከሳሽ ከአከራካሪው ቤት ጐን በሊዝ የተመራውን ቦታ አንድ ላይ በማድረግ የሟች አባታችንን ቤትና ቦታ አጠቃሎ ካርታ እና ፕላን አወጣበት እንጅ የእሱ አይደለም፡፡ ስለዚህ የወራሽነት ድርሻውን ከሚጠይቅ ውጪ የግሌ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ሐሰት ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አከራካሪው ቤት የከሳሽ ለመሆኑ ከተከሳሽ በተሻለ አስረድተዋል በማለት በአብላጫ ድምጽ ተከሳሹ ቤቱን ለከሳሽ ሊያስረክብ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣የሰበር

አቤቱታቸውን ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ሲያጡ ጉዳዩን ለዚህ ችሎት አቅርበው ይህ ችሎትም ግራ ቀኙን በመ/ቁጥር 55907 አከራክሮ የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡትን ውሳኔ በመሻር ጉዳዩ በአግባቡ ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል ሲል ሊጣሩ የሚገባቸውን ነጥቦች ለይቶና ሊቀርቡ የሚችሉትን ማስረጃዎችን ጭምር ጠቁሞ ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት መልሶ ልኮለታል፡፡

ጉዳዩ የተመለሰለት የምዕራብ ጐጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም እንደገና ግራ ቀኙን በመጥራት አለኝ የሚሉትን የሰውና የሰነድ ማስረጃ አስቀርቦ በመስማትና ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው ያላቸውን የሰነድ ማስረጃዎችን ከሚመለከታቸው አካለት እንዲቀርቡና ማብራሪያም እንዲሰጥበት ጭምር ከአደረገ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ ከ660 ካ/ሜትር ቤትና ቦታ ውስጥ በ440 ካ/ሜትር ክልል ውስጥ ያለው ቤት የአሁኑ ተጠሪ አይደለም፣ 220 ካ/ሜትር ቦታ ግን ተጠሪ በሊዝ የገዙት በመሆኑ የአሁኑ አመልካች ለቀው ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ጉዳዩን በይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ 440 ካ/ሜትር ቤትና ቦታ የአሁን ተጠሪ ስለመሆኑ በሰውም ሆነ በሰነድ ማስረጃ ከአሁኑ አመልካች ክርክርና ማስረጃ በተሻለ መልኩ ተረጋግጧል የሚል ድምዳሜ ይዞ የአሁን አመልካች ቤትና ቦታውን ሙሉ በሙሉ ለቀው ለተጠሪው ሊያስረክቡ ይገባል፣ ያላግባብ ለተጠቀመበት የቤት ኪራይም በወር 2000.00 ታስቦ በድምሩ ብር 62,000 /ስልሳ ሁለት ሺህ ብር/አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኂላ የአሁኑ አመልካች ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸውን አቅርበው ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ አመልካች 440 ካ/ሜትር ቤትና ቦታ ጭምር እንዲለቁ መወሰኑ ባግባቡ ነው፣ የኪራይ ገንዘቡን በተመለከተ ግን ለተጠሪ ቀድሞ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያልወሰነው እና ጉዳዩ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሲመለስም እንዲጣራ ያልታዘዘ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍሉ የሚወስንበት የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የለም ብሎ በጉዳዩ ላይ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አከራካሪው ቤትና ቦታ የሟች አባታችን ለመሆኑ በተገቢው መንገድና ማስረጃ ተረጋግጦ እያለ የተጠሪው ነው ተብሎ እንዳስረክብ የተወሰነው ያለአግባብ ነው፣ተጠሪው አለኝ ያሉት የኑዛዜ ሰነድም የማስረጃ አቀራረብ ስርዓትን ተከትሎ ያልቀረበና ሕጋዊ አይደለም፣በጉዳዩ ላይ ዳኝነት የተሠጠው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲጣሩ የተለዩት ነጥቦችንና ጉዳዩ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተመለሰ በኂላ ከሚመለከታቸው አካላት የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎችን ባለገናዘበ መልኩ ነው የሚል ሁኖ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከለተው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች 440 ካ/ሜትር

ቤትና ቦታ ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡

በቅድሚያ ተጠሪ ጉዳዩ የፍሬ ነገር ክርክር ነው በማለት ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተመልክተናል፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለው ክርክር ከማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ጋር የተያየዘ ሲሆን በዚህ ችሎት ጉዳዩ የቀረበው ጉዳዩ በሕጉ አግባብ ተጣርቶ የተወሰነ መሆን ያለመሆኑንና የማስረጃ አቀራረብ ስርዓትን እንዲሁም የምዝና መርሁን ባገናዘበ መልኩ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጭብጥ የፍሬ ነገር ማጣራት ወይም የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ባለመሆኑ በዚህ ችሎት የማይታይበት አግባብ ስላላገኘን በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪን ተቃውሞ አልተቀበልነውም፡፡

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመለስም፡- ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ይህ ችሎት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ሲመልስ ሊጣሩ የሚገባቸውን ነጥቦችን የለየ መሆኑን ነው፡፡ይህ ችሎት ጉዳዩን ወደ ታች ሲመልሰው ለክርክሩ መነሻ የነበረውን ይዞታ ማነው የተመራው ፣ ቤቱን ማነው የሰራው፣በማን ገንዘብ ተሰራ የፅሁፍ ማስረጃዎችን በተመለከተ ካርታ በከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ስም የተሰጠ መሆኑ ከማስረዳት ባለፈ የከተማው አስተዳደርየቤቱንና የይዞታውን አመጣጥ በአግባቡ ያውቃል ተብሎ ስለሚገመት በስር ፍርድ ቤቱ በኩል ታዞ ተጨማሪ ማብራሪያዎችንእንዲሰጥበት ሊደረግ እንደሚገባ፣ ማብራሪያ ከሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች መካከልም በከተማ አስተዳደሩ የነበረውን የማህደር ቁጥሩ 1224 የሆነውና በደጃዝማች አንለይ ሃይል ስም የነበረው/ የተከፈተው ለየትኛው ይዞታና ቤት ነበር የውሃና መብራት ውል በስማቸው ሊዋዋሉ የቻሉበትን አግባብ እንዴት እንደነበር፣ ከማህደሩ ውስጥ ጠፍቷል የተባሉት ገፆች እንዴት ሊጠፉ እንደቻሉ ፣ጠፍተውም ከሆነ መጥፋታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጠፉት ገፆች ይዘታቸው ምን እንደነበር ያሁን ተጠሪ ካርታ 660 ካሬ ሜትር ላይ የወጣላቸው በአንድ ጊዜ ነው ወይስ አሁን ክርክር ካስነሳው ይዞታ ጎን የነበረውን 220ካሬ ሜትር ከተመሩ በኋላ ነው፣ አሁን ክርክር የተነሳበት ይዞታ ከ220 ካሬ ሜትር ጋር ተጠቃሎ የተሰራ ነው ወይስ አይደለም፣ ሒደቱስ እንዴት ነበር የሚሉት ነጥቦች ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ናቸው በማለት ዘርዝሯል እንዲሁም ሰበር ችሎቱ የግብር አከፋፈል ሂደቱ በተካራካሪዎች አባት ሲከፈል የነበረበትና በተጠሪም ሲከፈልበት የነበረበት አግባብ ሊጣራ የሚገባው ነጥብ መሆኑን በመግለፅ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በባህርዳር ከተማ ገቢ ፅ/ቤት የባህር መዝገብ ተራ ቁጥር 202 በአባታቸው ስም ይገበር የነበረ በመሆኑ ቀርቦ ይታይልኝ በሚል ጥያቄ ቀርቦ ፍ/ቤቱ ስለማየቱ በፍርዱ ውስጥ የተባለ ነገር ባለመኖሩ ማስረጃው ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባ ለስር ፍርድ ቤት መመሪያ ሰጥቷል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ቤቱ ተሰራ ከተባለበት ከ1963 ዓ.ም ጀምሮ ግራ ቀኙም ሆኑ ሌሎች የቤተሰብ አባላት በተለይም እናትና አባት ከቤቱ ጋር ያላቸውና የነበራቸው ቁርኝት መታየትና መጣራት እንዳለበትም በውሳኔው ላይ አስፍሮ ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት የመለሰለት መሆኑን ተረድተናል፡፡

ከላይ የተመለከቱት ነጥቦች ይህ ችሎት በስር ፍርድ ቤት እንዲጣሩ የለያቸው ሲሆን የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ከተመለሰለት በኋላ ፍሬ ነገሩን ያጣራበትን መንገድ መመልከቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ምስክሮች የሰማ ሲሆን በሥር ፍ/ቤት የተሠሙት የተጠሪ ምስክሮች ቤቱን ከ1961 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1965 ድረስ ባለው ጊዜ ተመርቶ የሠራው ተጠሪ መሆኑን፣ ቤቱን ሲሰራም ከተለያዩ ሰዎች ገንዘቡን ተበድሮ መስራቱን የሚያውቁ መሆኑን አስረድተው ቤቱን ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲሄድ አባቱ እንዲኖሩበት ፈቅዶላቸው

ይኖሩበት እንደነበር፣ በዚሁ ሁኔታ ውሀና መብራት በእሳቸው ስም መግባቱን መስክረዋል፡፡ ባንቺ ዓለም አንለይ የተባለችው የግራ ቀኙ እህት በሰጠችው ምስክርነትም ቤቱ የታላቅ ወንድማችን የቴዎድሮስ አንለይ ነው፣ አባታችን በሕይወት እያሉ ሁሉን ነገር ያንቀሳቅሱ የነበሩ እሳቸው ናቸው፣ በኑዛዜያቸውም ቤቱን የተጠሪ መሆኑን ገልፀዋል፣ እሳቸው በ1990 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ ቤቱ በብር 2000 ተከራይቶ ነበር፣ከ1998 ዓ.ም. ጀምሮ ቤቱ በአሁኑ አመልካች ይዞታ ስር መቆየቱንም ሁሉም ምስክሮች አስረድተዋል፡፡ የአመልካች ምስክሮች በበኩላቸው ቤቱን የሠሩት የግራ ቀኙ አባት ደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ናቸው፣ ቦታውን የተመሩት ደግሞ በተጠሪው ስም ነው፣ ግብር ይከፈል የነበረው ደግሞ በደጃዝማች አንለይ ስም ነበር በማለት መመስከራቸውን የውሳኔው ግልባጭ ያሳያል፡፡

ከክፍሉ ማዘጋጃ ቤት የቀረበው የሙያ ምስክር የሰጠው ምስክርነትም የደጃዝማች አንለይ በልጃቸው ቴዎድሮስ አንለይ ስም ቦታ ተመርተው በራሳቸው ስም ሲገብሩ ቢኖሩም በኋላ ግን ቦታው በስሙ በተመራው ልጃቸው /በተጠሪ ስም/ ግብሩ ተስተካክሎ ሲገበር መቆየቱን፣ በፊት የነበረው ቦታ 440 ካሬ ሜትር ሲሆን በኋላ 220 ካሬ ሜትር ቦታ ሊዝ ገዝቶ ጨምሮበት 660 ካሬ ሜትር ቦታ በተጠሪ ስም ተጠቃሎ መስጠቱን መግለጹን የስር ፍርድ ቤት መዝግቧል፡፡

የስር ፍርድ ቤት በሰነድ ማስረጃነት ያስቀረበው የባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት ጥቅምት 11 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ቁጥር አዘል ደብዳቤ በባህር መዝገብ ቁጥር 202 በሆነ ግብር በተጠሪው ስም የማይገበር መሆኑንና መዝገቡ በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም መሆኑን የሚያሳየውን ሰነድ፣ በባህር ዳር ከተማ ውሀና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ጥቅምት 10 ቀን 2004 ዓ.ም. በተፃፈ ቁጥር የያዘ ደብዳቤ ውሀ የገባው በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም መሆኑንና በመሥሪያ ቤቱ አሠራር ውሀ በስም ለማስገባት የሚቻለው ባለይዞታ መሆኑን ገልፆ በወቅቱ ደጃዝማች አንለይ ባለይዞታ ስለሆኑ ውሃው የገባላቸው መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠው ሰነድ፣በባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ጥቅምት 10 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የማህደር ቁጥር 1224 የሆነውን በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም የነበረው ቦታ የሚያሳየው የተለያዩ ቦታዎችን ከሰዎች መግዛታቸውን፣ ይሁን እንጂ እነዚህ ቦታዎች የተወረሱባቸውና በተለያየ ምክንያት የፈረሱ መሆኑን፣ ህዳር 19 ቀን 1984 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ቦታ እንዳሌላቸውና በልጃቸው በቴዎድሮስ አንለይ ቤት በጢሰኝነት እንደሚኖሩና ቦታ እንዲሰጣቸው ያመለከቱበት ማመልከቻ መኖሩንና አቶ ቴዎድሮስ ፋይል ላይ ደግሞ ግንቦት 11 ቀን 1992 ዓ.ም በተዘጋጀ ሳይት ፕላን ባህር ዳር ከተማ 08 ቀበሌ የ440 ካሬ ሜትር ቦታ እንደነበራቸውና 220 ካሬ ሜትር ቦታ በሊዝ ጠይቀው ከሚያዚያ 24 ቀን 1993 እስከ ግንቦት 02 ቀን 1993 ዓ.ም እንዲወስዱ ተወስኖላቸው የ660 ካሬ ሜትር ቦታ ካርታ መውሰዳቸውን የሚገልፅ ሰነድ ፣ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በባህር ዳር ዲስትሪክት ቁጥር 2 አገልግሎት ማዕከል ጥቅምት 06 ቀን 2004 ዓ.ም የተፃፈ ደብዳቤ መብራት በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም መግባቱን የሚያሳይ ሰነድ፣ የባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤ በደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ስም ይገበርበት የነበረ ምንም ዓይነት ካርታና ፕላን የለም ሲል የገለጸበት ሰነድ፣የባህር ዳር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት ጥቅምት 07 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አከራካሪው ቤትና ቦታ በአቶ ቴዎድሮስ አንለይ ስም በካርታ ቁጥር 10100/93 በፋይል ቁጥር 291 ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን እንደሚያሳይ የገለፀበት ሰነድ ናቸው፡፡ ከእነዚህ የሰነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት በማስረጃነት የያዘው ሰነድ የአሁኑ ተጠሪ ጉዳዩ ወደ ስር ፍርድ ቤት ከተመለሰ በኋላ አገኘሁ ብለው በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲታይላቸው ያቀረቡት

ሰነድ ሲሆን ይህም ሚች ደጃዝማች አንለይ ኃይሌ መስከረም 06 ቀን 1984 ዓ.ም. አደረጉ የተባለው ኑዛዜ ሁኖ ለጉዳዩ አግባብነት አለው የተባለው የኑዛዜው ክፍል ሚቹ ".....አሁን ያለንበት መኖሪያ ቤት በልጄ በቴዎድሮስ አንለይ ስም የተሠራ ነው፣ቤቱም የተሠራበት ቦታ በራሱ ስም የተገኘና የተያዘ ሥለሆነ ቤቱን ከነቦታው መረከብ ይችላል...." በማለት ማስፈራቸውን ያሳያል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች ተመዝግቧል፡፡ ከዚህ የሰውና ሰነድ ማስረጃ መገንዘብ የሚቻለው በአከራካሪው ቤትና ቦታ ውህና መብራት በደጃዝማት አንለይ ኃይሌ ስም መግባቱንና በቤቱም ውስጥ እየኖሩ ግብር በህይወት እስከነበሩ ድረስ በእሳቸው ስም ይገበሩ የነበረ መሆኑን ሲሆን የቤቱን ካርታ እና ፕላን ግን በእሳቸው ስም የተመዘገበ አለመሆኑንና በተጠሪው ስም የተመዘገበ መሆኑን ነው፡፡በተጠሪው ስም የተመዘገበበት ጊዜ በ1993 ዓ/ም ስለመሆኑ ክርክር የቀረበበት የፍሬ ነገር ነጥብ አይደለም፡፡ይህ ምዝገባ  የተከናወነው ቦታው በተጠሪው ስም የተመራ ነው በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ማዘጋጃ ቤቱ የሚከተለውን አሰራርን መሰረት በማድረግ ለስር ፍርድ ቤቱ ማብራሪያ እንደሰጠ የቀረቡት ሰራተኞች ከሰጡት የምስክርነት ቃል መገንዘብ የሚቻል ቢሆንም በቤቱ ማህደር ውስጥ ሰነዶች እንደነበሩ ሳይካድ ሰነዶቹ የጠፉት ህጋዊ ምክንያት ግን በማስረጃ ያለመረጋገጡን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ ማዘጋጃ ቤት ያለው የቤቱ ማህደር የአመልካችን አባት ስም የማይጠቀስ ነው የተባለ ቢሆንም ተመሳሳዩን ቤትና ቦታ በተመለከተ በግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ይገኛል የተባለው ማህደር ደግሞ የአሁኑን ተጠሪ ስም የማይገልፅ፣ይልቁንም የሚች ደጃዝማች አንለይ ኃይሌን ስም የሚገልፅ መሆኑን የሚመለከተው አካል ለፍርድ ቤቱ አረጋግጦ ልኳል፡፡ይህ ማህደር ሰነዶቹ የጠፉት ስለመሆኑ በተጠሪ ክርክር ያልቀረበበትና ሕጋዊ  ተቀባይነቱም ጥያቄ ውስጥ ያልገባ  የሰነድ ማስረጃ መሆኑን ክርክሩ በግልጽ ያሳያል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው በፍ/ብ/ህ/ቁ 1195 ድንጋጌ መሰረት የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሃብትነትን በማወቅ በአስተዳደር ክፍልየምስክር ወረቀት ሲሰጥ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሰው የማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለሃብት ሁኖ ሊገመት እንደሚገባ ተመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ በግልጽ የሚያሳየው በአስተዳደር አካሉ የሚሰጥ ማስረጃ የመብቱ ባለቤት የሆነውን ሰው ለመለየት ግምት የሚወስድበት እንጂ አሳሪ ወይም ድምዳሜ ማስረጃ /conclusive evidence/ ያለመሆኑን ይልቁንም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 ስር በተመለከቱት ውስን ምክንያቶች አግባብ ሊስተባበል የሚችል ሕጋዊ ግምት /rebuttable legal presumption/ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ህ/ቁ 1195 ስር የተመለከተው የህግ ግምት ፍጹም የሆነ ወይም ድምዳሜ ማስረጃ ሳይሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 ስር የተመለከቱት ሁኔታዎች ስለመኖራቸው በማናቸውም ማስረጃ በማረጋገጥ ሊስተባበል የሚችል የሕግ ግምት ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው በአስተዳደር አካል የተሰጠ ካርታ በመያዙ ብቻ በካርታው የተጠቀሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ህጋዊ ባለሃብት እንደሆነ ህጉ ግምት ቢወስድለትም ይህ ግምት ግን ካርታው የተሰጠበትን አግባብ ከደንቡ ከአስራሩና ከሰልጣኑ ውጪ እንዲሁም በማይረጋ የምስክር ወረቀት መሰረት ማስረጃው ተሰጥቶ ከሆነ ይህንኑ በማናቸውም ማስረጃ በማረጋገጥ የህጉን ሕሊናዊ ግምት ማፍረስ እንደሚቻል ፍ/ብ/ሕ/ቁ 1196 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ ይህንኑ የህጉን ይዘትና መንፈስ ካርታው ከመሰረዝ ጋር አስተሳስረን ስንመለከተውም አንድ የአስተዳደር አካል በሕጉ አግባብ የተሰጠን የባለቤትነት ማስረጃ በሕጉ የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ዋጋ አልባ የሚያደርገው ሕጋዊ አግባብ የሌለ መሆኑን በቀላሉ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ አንድ ሰው በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የባለቤትን መብት አቋቁሟል ለማለት የሚቻለው  በህግ አግባብ የተገኘውን ማስረጃ መሰረት አድርጎ የመፋለም ክስ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት አቅርቦ በጉዳዩ የሚቀርቡት ማስረጃዎች በሕጉ

የተዘረጋውን የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት ተከትለው ሲቀርቡና ማስረጃዎቹ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ባለው የማስረጃ ምዘና መርህ መሰረት ክሱን ማስረዳታቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በ1993 ዓ/ም ከአስተዳደር አካሉ የባለቤትን ማረጋገጫ ደብተር አግኝተዋል ተብሎ ማስረጃው መቅረቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 መሰረት ማስረጃው የተሰጠበትን ንብረት ባለሃብት ናቸው ተብሎ የሚገመቱት ተጠሪ ናቸው ተብሎ ግምት ለመውሰድ የሚያስችል ቢሆንም የክርክሩ ልዩ ባህርይ ሲታይ በተለይም የአከራካሪው ቤት ማህደር ውስጥ ነበሩ የተባሉ ሰነዶች ከጠፉ በኋላ ማስረጃው ለተጠሪ መሰጠቱ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪ አለኝ በማለት ያቀረቡት ይኼው የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ሕጋዊ ተቀባይነት እንዲሰጠው የማያደርገው ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ይህንን ለማስተባበል በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1196 በተደነገገው አግባብ ለተጠሪውየተሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከደንብ ውጪ በሆነ አሠራር ወይም ሥልጣን በሌለው አስተዳዳር ክፍል ስለመሆኑ በሰውም ሆነ በሰነድ ማስረጃው ያስረዱት ነገር የለም በማለት መደምደማቸው በክርክሩ ሂደት የቀረቡትን ሁሉንም ማስረጃዎች ያገናዘበ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሟች ደጃዝማች አንለይ ኃይሌ ግብር በስማቸው መገበራቸው ወይም ውሃና መብራት በስም ማስገባታቸው ከሚመለከታቸው አካላት በቀረቡት ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን እነዚህ ማስረጃዎች በአመልካችና በተጠሪ መካከል አይነት በተነሳው ክርክር የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን ለማረጋገጥ አይችሉም ተብሎ ማስረጃዎቹ ውድቅ የሚሆኑበት የማስረጃ ምዝና መርህ የለም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶች የባህር ዳር ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ውሃ በስም ሊገባ የሚችለው የይዞታ ባለቤትነት ሲረጋገጥ ነው በማለት የሰጠውን የሰነድ ማስረጃም በደፈናው በምን እንዳረጋገጠው የገለፀው ነገር ባለመኖሩ የሰጠው ማረጋገጫ ተቀባይነት አለው ብሎ ለመውሰድ የሚቻል አይደለም በማለት ከማለፋቸው በስተቀር የመስሪያ ቤቱ የተለመደ አሰራር አለመሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲቀርብ ያላደረጉ በመሆኑ ማስረጃው ተቀባይነት ያጣበት አግባብ ሕጋዊ ምክንያትን መሰረት አድርጎ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ቤትና ቦታው የሟች አባታችን ነው በማለት ሲሆን ሟች አባታቸው መስከረም 06 ቀን 1984 ዓ.ም ባላደረጉትና ስርዓቱን ጠብቆ ባልቀረበው የኑዛዜ ሰነድ ክርክር ያስነሳው ቤት የተጠሪ ነው መባሉ ያላግባብ ነው በሚል ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ይህ የኑዛዜ ሰነድ ለማስረጃነት የቀረበበትን አግባብ በውሳኔውአቸው ላይ በግልጽ ባያሰፍሩም የአሁኑ ተጠሪ በዚህ የሰበር ደረጃ በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር ሰነዱ ቀድሞ ሊገኝ ባለመቻሉ የቀረበና ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለስር ፍርድ ቤት ሲመልስም ጉዳዩ አግባብነት ባላቸው ሌሎች ማስረጃዎች ጭምር እንዲጣራ ብሎ ስለአዘዘ ማስረጃው መቅረቡ ተገቢ ነው በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ችሎት የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን አግባብነት ባላቸው ማስረጃዎች ሁሉ አጣርቶ እንዲወስን በማለት የሰጠው ውሳኔ ስለማስረጃ አቀራረብ በህጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ሁሉ ባላገናዘበ መልኩ ማስረጃው እንዲቀርብ በማሰብ ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚገባ አይደለም፡፡ በመሆኑም ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች መቅረብ ያለባቸው በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት ጠብቀው ሊሆን ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር ተጠሪ አለኝ የሚሉትን የኑዛዜ ሰነድ በተመለከተ ለማስረጃነት ያቀረቡት ጉዳዩ ከዚህ ችሎት ከተመለሰ በኋላ ሲሆን ሰነዱ በማስረጃነት እንዲቀርብ የጠየቁበት አግባብም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 137(3) እና 256 ድንጋጌዎች ይዘት ጋር የተገናዘበ መሆኑን ያረጋገጡት ነገር የሌለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ የተጠሪ ምስክር የሆኑት እህታቸው ቀድሞ ክርክሩ ላይ የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ

ሲሆን በዚህ ጊዜ ስለኑዛዜ ሰነዱ የሰጡት የምስክርነት ቃል ሳይኖር ጉዳዩ ወደ ዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲመለስ ቤቱ የተጠሪ መሆኑን ሟች ደጃዝማች በኑዛዜ አረጋግጠውላቸዋል የሚለው ምስክርነታቸው ቀድሞውንም ኑዛዜ መኖሩ ይታወቅ የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ምስክርነት ነው ሊባል የሚችልና ተጠሪ ሰነዱን በጊዜው ተገቢውን ጥረት አድርገው ማቅረብ ይችሉ የነበረ፣ ማቅረብ የማይችሉበት ምክንያት ካለውም ይህንኑ ለፍርድ ቤቱ ማሳወቅና በሌላ አግባብ ማስረዳት ይችሉ የነበረ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው። በመሆኑም የኑዛዜው ሰነድ ለማስረጃነት የቀረበበት አግባብ ከተጨማሪ ማስረጃ አቀራረብ ስርዓት ውጪ ነው። በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ሰነዱን ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው ሟቹ በኑዛዜው ላይ ቤቱ የልጅ ቴዎድሮስ አንለይ በስሙ ቦታ ተመርቶ የሠራው ስለሆነ ቤቱ ከነቦታው መረከብ ይችላልብለው ማስፈራቸውን፣የኑዛዜው ቃል ይዘት ቤቱ የሟች ነው ተብሎ አሁን የተከሰተው ዓይነት ክርክር እንዳይፈጠር አስቀድመው አስበው ያደረጉት መሆኑን ነው በሚል ምክንያት ሰነዱ የማስረጃነት ዋጋ መስጠታቸው ተገቢነት የሌለውን የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት ተፈጻሚ በማድረግ የደረሱበት ድምዳሜ በመሆኑ በሕግ ተቀባይነት ሊሰጠው የማይገባ ሁኖ አግኝተናል።

ሲጠቃለልም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አከራካሪው 440 ካ/ሜትር ቤትና ቦታ የተጠሪ ሃብት ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ ጉዳዩ እንዲጣራ ሲመለስ በክርክሩ ላይ በህግ አግባብ የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎችን ይዘት ከክርክሩ ልዩ ባህሪና ተገቢነት ካለው የማስረጃ ምዘና መርህ ጋር ባለማገናዘብ ሁኖ ስለአገኘው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 34051 የካቲት 20 ቀን 2005 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 88365 ታህሳስ 02 ቀን 2006 ዓ/ም ተሻሽሎ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል።
2. የምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 25679 ግንቦት 30 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል።
3. አመልካች 440 ካ/ሜትር ቤትና ቦታ ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል የተባለው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል። አመልካች ብር 62,000 /ስልሳ ሁለት ሺህ ብር/ የቤት ኪራይ ለተጠሪ ሊከፍሉ አይገባም፣ 220 ካ/ሜትር ቦታ ሊለቁ ይገባል ተብሎ የተሠጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል።
4. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል።
5. ተጠሪ በውርስ አግባብ አለኝ የሚሉትን መብት ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል።

***<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>***

በዚህ ችሎት መጋቢት 08 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የአፈፃፀም ዕግድ ተነስቷል። ይፃፍ። መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ 97094

ቀን 08/03/2007 ዓ.ም

ዳኞች:- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች:- ወ/ሮ አስቴር አምባው - ቀረቡ

ተጠሪዎች:- 1. አቶ አበባው ክፍሌ የቀረበ የለም

2. ያሬድ አለማየሁ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በከፋ ዞን የቦንጋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በስር ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 418 በአፈፃፀሙ ጉዳይ ጣልቃ የገቡ ሲሆኑ 1ኛ ተጠሪ የአፈፃፀም ከሳሽ 2ኛ ተጠሪ የአፈፃፀም ተከሳሽ ነበሩ የአፈፃፀም ከሳሽ /የአሁንተጠሪ/ ለአፈፃፀም ይውሉ ዘንድ 1. የልብስስፌት ማሽን፣ ኮንትሮል ብሬ፣ የሴቶች ፀጉር ቤት ካስክ፣ ስሶት የፀጉር ማሽን፣ የፀጉር ቤት መስታወት፣ የመቀመጫ ወንበር፣ ባለ 21 ኢንች ቴሌቪዥን እና አራት የሶፋ ወንበሮች ተሽጦ እዳው ይከፈለኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የተጠቀሱት ንብረቶች ተገመተው እንዲቀርቡለት ትዕዛዝ በመስጠቱ ምክንያት የአሁን አመልካች ንብረቶች የግሌ ናቸው በማለት ሊፈፀም አይገባም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 418 መሰረት በመቅረቧ ፍ/ቤቱም አመልካች ተጠቃሹ ንብረቶች የራሳቸው ለመሆኑ ያቀረቡት የፅሁፍ ሰነድ የለም፣ በሰው ምስክር አስረዳለሁ ያሉትን ክርክር በስነ ስርዓት ህጉ 418/3/ መሰረት ተቀባይነት የለውም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በየደረጃው ያሉትም የክፍሉ ፍ/ቤቶችም ይህንኑ ተቀብለውታል፡፡

የአመልካች አቤቱታም የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልፁ 2ኛ ተጠሪ በእኔ ድርጅት ተቀጥሮ የሚሠራ ነው፤ ተጠቃሾቹ ንብረቶች የግሌ እና መጠቀሚያዎቼ ናቸው ብዩ ብቀርብምበሰው ምስክር ማስረዳት አይቻልም፤የፅሑፍ ሰነድ ካልሆነ በቀር በማለት ላቀርብ እችላለሁ ያልኩትን ሰነድ ሳይቀበለኝ ጥያቄየን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረምልኝ ይገባዋል ሲሉ አመልክተዋል፡፡

በዚህም መሰረት እኛም አመልካች በሰውና በሰነድ ንብረቶቹ የእኔ መሆናቸውን ላስረዳ እያሉ በሰው ማስረጃ ብቻ ማስረዳት አይቻልም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ

የግራ ቀኙ በቀረበው አቤቱታ ላይ መልስና የመልስ መልስ በፅሑፍ እንዲቀባበሉ ተደርጐ ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ የሚሉት 2ኛ ተጠሪ የአመልካች ባል ናቸው በአካሌ ላይ ጉዳት አድርሶብኝ እንዲፈፀምልኝ ያቀረብኩትን ንብረቶች አመልካች ለማስቀረት በማሰብ ነው የእኔ ንብረቶች ናቸው የሚሉት የራሳቸው ለመሆኑ በሰነድ ማቅረብ ባለመቻላቸው እና በሰው ማስረጃ አስረዳለሁ ማለታቸው ውድቅ መደረጉ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ነው፡፡የሚከራከሩት አመልካች በበኩላቸው በ2ኛ ተጠሪ ፍቃድ እኔ ንብረቶቹን አቀርቤ ቀጥሬያቸው ነው የሚሰሩት እንጂ የጋብቻ ግንኙነት የለኝም በስር ፍ/ቤት በሰነድና በሰው ማስረጃ ላስረዳ ብዬ እያመለከትኩ ይህ ታልፎ በሰው ማስረጃ ማስረዳት አይቻልም ተብሎ መወሰኑ ንብረቴን የሚያሳጣኝ ውሳኔ በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል ሲሉ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሱትን ይመስላል፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አኳያ መርምሯል፡፡

እንግዲህ አመልካች ተጠቃሾቹ ንብረቶች የእኔ ለመሆናቸው “ሰነድ” ማቅረብም እችላለሁ ስል እንዳቀርብ ከተፈቀደልኝ በኂላ ነው፡፡ ይህ ታልፎ በፅሁፍ ማስረጃ ብቻ ነው እንጂ በሰው ማስረጃ ማስረዳት አትችይም የተባልኩት ነው የሚሉት፡፡ በመሰረቱ የፍ/ብ/ህ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 ድንጋጌ አስፈላጊነት የክርክሩ አካል ያልሆኑና ፍርድ ያላረፈባቸው የ3ኛ ወገን ንብረት ሳይረጋገጥ የፍርዱ ማስፈፀሚያነት እንዳይውሉ ለመከላከልና ባንጻሩ ፍርዱን የመፈፀም ለማስተጓጉል (እንዳይፈፀም ለሚቀርቡት በቂ ላልሆኑ አቤቱታዎችም (መቃወሚያ) እልባት የሚሰጥ ነው፡፡ በመሆኑም በተያዙት ንብረቶች ላይ መብት አለኝ የሚል ወገን የሚያቀርበውን መቃወሚያና አቤቱታ ተቀብሎ መመርመር እንዳለበት የተጠቀሰው ድንጋጌም በግልፅ ያስፈረውነው፡፡ ይህ ከሆነ የዚሁ አንቀጽ 418(3) የአራተኛው ቅጂ ባለይዞታነትን ለማስረዳት የፅሁፍ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበትየሚደነግግ ቢሆንም የእንግሊዘኛው ቅጂ የስነ- ስርዓት ህጉደግሞ ይህንኑ አንቀጽ ሲገልጽ The Claimant or 0bjector Shall adduce evidence to Show that and the date of the attachment he had Some interest in or was possessed of the property attached ይላል፡፡ እንግዲህ ከዚህኛው የእንግሊዘኛ ቅጂ የምንረዳው “ማስረጃ በማቅረብ ለአፈጻጸም የቀረበውን ንብረት ማስረዳት እንደሚቻል የሚገልጽ ነው፡፡ የአማርኛው ቅጂም ቢሆን ከፍ/ህ/ቁ/1193 (1) እና (2) ድንጋጌዎች ጋር ተደምሮ ሲታይ ሌላውን የማስረጃ አይነት በግልጽ እንዳይቀርብ የከለከለው ሆኖ አይታይም፡፡በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች አመልካች አካራካሪውን የሚንቀሳቀስ ንብረት በሰው ማስረጃ ሊያስረዱ አይችሉም ሲሉ ያደረሱበትን ድምዳሜ የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 418 ድንጋጌ መሰረታዊ አላማና የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ሀብቶችን ባለ ሃብትነት ለማስረዳት የሚጠቅሰውን የማስረጃ ዓይነት ያገናዘበ ሁኖ አልተገኘም በመጨረሻ በስር ፍ/ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሰው ማስረጃ ከወዲሁ ሳይሰማ ሰነድ አልቀረበም በማለት ጥያቄያቸውን ውድቅ በማድረጉ የማስረጃ አቀራረብ ስርዓትን ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የከፋ ዞን ቦንጋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 06403 በቀን 11/04/2006 ዓ.ም የሰጠው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 10082 በ30/04/2006 ዓ.ም እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 01555 በቀን 09/05/2006 ዓ.ም የተሰጡት ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የቦንጋ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በጉዳዩ የቀረበውን የሰው ማስረጃ በመስማት አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች በመመርመር ተገቢነት ያለውን ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት መዝገቡን መልሰን ልከናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የወጪ ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::**

ሰ/መ/ቁ. 95587

ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ወ/ሮ ሐዋ በከር አቶ ጀማል የሱፍ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. አቶ ቶፊቅ መሀመድ
2. አቶ አብዱሰላም መሀመድ
} ጠበቃ አቶ ፋይሶ ከድር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በሐዋ በከር የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 164559 ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይወሰንልኝ በማለት የሐዋ በከር ጠበቃ ነኝ በማለት አቶ ራጅ ገመቹ በአመልካች ስም ፅፈውና ፈርመው ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በሐሮማያ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአውዳይ ፍርድ ቤት ጥር 30 ቀን 2004 ዓ.ም በሀዋ በከር ስም የቀረበለት ክስ ላይ የተከሳሾችን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተከሳሾች በከሳሽ የይዞታ ቦታ ላይ ግንባታ በማከናወን ሁከቱ የፈጠሩበት ስለሆነ ሁከቱ እንዲወገድ በማለት በመዝገብ ቁጥር 24494 ታህሣሥ 15 ቀን 2005 ዓ.ም. ውሣኔ ሰጥቷል፡፡
2. ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለምስራቅ ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችን (ሀዋ በከርን) በመልስ ሰጭነት በመሰየምና መልስ ሰጭ በወኪሏ በኩል መልሷንና ክርክሯን እንዳቀረበች በማስፈር የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመዝገብ ቁጥር 34942 ግንቦት 19 ቀን 2005 ዓ.ም. በሰጠው ውሣኔ አፅንቶታል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ሀዋ በከርን በተጠሪነት በመሰየምና ተጠሪ በወኪል በኩል እንደተከራከረች በውሣኔው ውስጥ በማስፈር የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡
3. ይህንን ውሣኔ በማስለወጥ በሀዋ በከር ስም ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ.ም. የተፃፈ የሰበር አቤቱታና መጋቢት 15 ቀን 2006 ዓ.ም. የተፃፈ የመልስ መልስ ለዚህ ሰበር ችሎት ጠበቃው ራጅ ገመቹ ያቀረቡ ሲሆን ሐምሌ 15 ቀን 2006 ዓ.ም ሀዋ በከር በህይወት

የሌለች መሆኑ ለፍርድ ቤቱ በመግለፅ፣የሀዋ በከር ወራሽ የወራሽነት ማስረጃውን እንዲያያይዙ ትዕዛዝ ተሰጥቷል። በዚህ ትዕዛዝ መሰረት አቶ ጀማል ዮሱፍ ጥቅምት 12 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሃረሚያ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 25234 መጋቢት 6 ቀን 2004 በተፃፈ መሸኛ ሀዋ በከር ህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየች መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠውን ፍርድና የወራሽነት ማስረጃ ቀርቧል። ተጠሪዎች በበኩላቸው ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ የቀረበውና እስካሁን ክርክሩ በሀዋ በከር ስም የቀጠለው ሚች ከሞተች በኋላ በመሆኑ ጉዳዩ ሊሰረዝልን ይገባል በማለት ጥቅምት 18 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቀዋል።

4. ይህችሎትሀዋበከር ህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም በሞት ከተለየች በኋላ በሀዋ በከር ስም ከወረዳ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ ሰበር እንዴት ክርክር እንደ ቀረበ ለማጣራት ግራ ቀኙን በቃል እንዲከራከሩ በማድረግ አጣርቷል። ጠበቃው አቶ ራጅ ገመቹ በመጀመሪያ ፋይሉን የከፈተው ጀማል ዮሱፍ ነው። እኔ ክርክሩ ከተጀመረ በኋላ ነው ጉዳዩን የያዝኩት በማለት መልስ የሰጠ ሲሆን አቶ ጀማል ዮሱፍ በሚች ስም ለወረዳው ፍርድ ቤት ክስ ያቀረብኩት እኔ ነኝ። ባለማወቅ ነው ክሱን ያቀረብኩት በማለት መልስ ሰጥቷል።
5. አጠቃላይ የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀ ሲሆን፤ እኛም ጉዳዩን እንደመረመርነው በሀዋ በከር ስም ከወረዳ ፍርድ ቤት ጀምሮ እስከ እዚህ ሰበር ችሎት ክርክር ሲደረግ የነበረው ሀዋ በክር ከዚህ አለም በሞት ከተለየች ከህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም በኋላ ነው። ሀዋ በከር በህይወት እያለች ለአቶ ጀማል ዮሱፍ የሰጡት ውክልና ሀዋ በከር ህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ ውጤት እንደማይኖረውበፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2232(1) ተደንግጓል። ከዚህ አንፃር ጀማል ዮሱፍ ሚች ሀዋ በከር በሕይወት እያለች የሰጠችውን ውክልና በመጠቀም ጠበቃ ወክሎ ሚች በህይወት እንዳለች በማስመሰል ለወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስና ክፍያ ከዚያም በኋላ በይግባኝና በሰበር ያቀረበው ክርክር የሞተችው ሀዋ በክር በህይወት እያለች ሆኖ የቀረበ፣እስከ ሐምሌ 15 ቀን 2006 ድረስ ለሌሎች ፍርድቤቶችም ሆነ ለዚህ ችሎት ያልተገለፀና፣ ሀዋ በክር በህይወት እንዳለች ጀማል ዮሱፍ ወኪሏ እንደሆነና ወኪሏ ደግሞ ጠበቃ እንደወከለ ተደርጐ የቀረበ መሆኑን በመዝገቡ የቀረቡ ውሳኔዎችንና ሌሎች ክርክሮችን በመመርመር ተገንዝበናል።
6. በአንድ ሰው ስም ፍርድ ቤት ቀርቦ ክስ ለማቅረብና ለመከራከር የሚችለው ዋናውባለጉዳይ ወይም ለዋናው ባለጉዳይ የወኪልነት፣የጠበቃነት ወይም የነገረ ፈጅነት ሥልጣን ያለው ሰው እንደሆነ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 57 ይደነግጋል።በያዝነው ጉዳይ ጀማል የሱፍ የሚች ወራሽ መሆኑን ገልዖ በወራሽነቱ ያቀረበው ክስና ክርክር የለም።ጀማል የሱፍ ሀዋ በከር በህይወት እያለች የሰጠችውን የውክልና ሰነድ በመጠቀም የሀዋ በከር ወኪል በመሆንና ጠበቃ በመቅጠር በሀዋ በከር ሥም ሚች ከሞተች በኃላ ክስ አቅርቧል።ይህም ጀማል የሱፍ ሀዋ በከር በመሞቷ ምክንያት የተሰጠው የውክልና ሥልጣን ቀሪ ከሆነ በኃላ በወኪልነት ሥልጣኑ በመጠቀም ጠበቃ ያቆመ በመሆኑና ጠበቃውም ሀዋ በከርን በመወከል ጠበቃ ለመወከል ሥልጣን በሌለው ሰው ተወክሎ ክርክሩ ያቀረበ በመሆኑ ከወረዳው ፍርድ ቤት ጀምሮ በሀዋ በከር ስም እስከዚህ ችሎት ያቀረቡት ክርክር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2232/1/ እና የፍታሐብሔር ሥነ -ሥርዓት ሕግ ቁጥር 57 ድንጋጌዎችን የሚጥስና ህጋዊ ዕውቅናና ውጤት ሊሰጠው የማይገባው ነው።

7. በመሆኑም ህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በተለየችው ሀዋ በከር ስም ለሥር ፍርድ ቤት የቀረበ ክስና ከዚያም በኃላ ፍርድ ቤቶቹ ሀዋ በከር በህይወት እንዳለች በመገመትና በውሣኔያቸው በማገለፅ የሰጡት ውሣኔና ህጋዊ ዕውቅና ውጤት ሊሰጠው የማይገባ በመሆኑ በአመልካች ስም የቀረበውን ክርክርና የተሰጠውን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሠርዘናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. ክሱ የተጀመረውና እስከዚህ ሰበር ችሎት ክርክሩ የተደረገው ሀዋ በከር ህዳር 15 ቀን 2004 ዓ.ም በሞት ከተለየች በኃላ በሀዋ በከር ስም በመሆኑ ይህም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2232/1 እና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 57 ድንጋጌን የሚጥስ በመሆኑ በሟች ሀዋ በከር ስም የቀረበውን ክርክርና በየደረጃው ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ተሰርዟል፡፡
2. ሀዋ በከር በሞት ከተለየች በኃላ በስሟ የቀረበው ክስ፣ክርክር እንዳልቀረበና በየደረጃው የተሰጡት ፍርዶች ሁሉ እንዳልተሠጡ ይቆጠራሉ ብለናል፡፡
3. በሞት በተለየችው ሃዋ በከር ሥም ክርክር በማቅረብ በተጠሪዎች ላይ ለደረሰው መጉላላትና ኪሣራ አቶ ጀማል የሱፍ ብር 2000/ሁለት ሺ ብር/ ኪሣራ ተጠሪዎች ይክፈል በማለት ወስነናል፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::**
**እ/ኢ**

የሰ/መ/ቁጥር 97332

መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ አይመረ በላይ - ጠበቃ ሙሉአለም ዘውዴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. መሪጌታ ኮነ ንጋቱ - ጠበቃ ተሾመ መኮንን ቀረቡ

2. አቶ አንዷለም አሻግሬ - ታልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አንድ በፍርድ ቤት የተደረገ የጨረታ ሽያጭ ውድቅ የሚሆንበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 14450 በሆነው ህዳር 4 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲነሳላቸው አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት በማጣቱ ነው፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ሲታይም የአሁን1ኛ ተጠሪ ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በነበረባቸውና በወረዳው ፍርድ ቤት በተወሰነው የብር 15,000.00 ዋና ገንዘብ፣ የዚሁ ገንዘብ ወለድና የተለያዩ ወጪዎች ዕዳ መክፈያ እንዲሆን በአሁን አመልካች ስም ይታወቅ የነበረው በአዴት ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቤት በምስራቅ መንገድ፣ በምእራብ 16 ቁጥር፣ በሰሜን 15 ቁጥር፣ በደቡብ 19 ቁጥር በሚያዋስኑት መካከል የሚገኝ ቤት ባለሙያ ተገምቶ በአከባቢ ማስታወቂያ ጨረታ እንዲወጣ ተደርጎ የአሁኑ አመልካች የሃራጁ አሸናፊ ሁነው ከተሸጠ በኋላ የ1ኛ ተጠሪ እዳ ለ2ኛ ተጠሪ እንዲከፈል፣ የተረፈው ገንዘብ ደግሞ ለአሁኑ 1ኛ ተጠሪ እንዲቀመጥላቸው የወረዳው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲሰጥ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ በሐራጅ ሽያጩ ጉድለት እንደአለ ገልጸው አቤቱታ ቢያቀርቡም የወረዳው ፍርድ ቤት ጥያቄአቸውን ባለመቀበል መዝገቡን የዘጋባቸው ሲሆን በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነት ስለአጡ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበው ችሎቱ በ1ኛ ተጠሪ አመልካችነት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ (የስር የፍርድ ባለመብትን) ብቻ ተጠሪ አድርጎ ክርክሩን ከመራ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ለፍርድ ማስፈፀሚያነት የዋለው የ1ኛ ተጠሪ ንብረት የጨረሻ መነሻ ግምቱ ብር 76,354.30 ሁኖ

በጨረታ የተሸጠው ግን በብር 76,358.60 መሆኑ ቤቱ በአከባቢ ማስታወቂያ ለሰላሳ ቀናት ማስታወቂያው አየር ላይ ሳይውል መሸጡ በሽያጭ አካሄዱ ላይ ጉድለት መኖሩን የሚያሳይ ነው የሚል ምክንያት ይዞ በወረዳው ፍርድ ቤት ትእዛዝ የተካሄደውንና የፀደቀውን የጨረታ ሽያጭን እንዲሰረዝ በማለት ወስኖታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የጨረታው አሸናፊ የሆኑትን አመልካች ሳይጠራና የሐራጅ ሽያጩም ጉልህ ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ በሌለበት ሁኔታ አመልካች በግልጽ ተወዳድረው አሸናፊ የሆኑበትን የጨረታ ውጤት መሰረዙ ያላግባብ ነው፣ንብረቱም በሕግ አግባብ ለሶስተኛ ወገን ተሸጦ የሀራጅ ሽያጩ ወደ ነበረበት ቦታ ሊመለስ በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ይገኛል የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ 2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ሊቀርቡ ባለመቻላቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው የታለፈ ሲሆን1ኛ ተጠሪ ግን በመቅረባቸው ከአመልካች ጋር በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁኑን አመልካች ወደ ክርክሩ ሳያስገባ ክርክሩን መርቶ ዳኝነት መስጠቱና አመልካች ጉዳዩ ባሉበት እንዲታይላቸው ያቀረቡትን አቤቱታ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ነው በማለት ያለመቀበሉ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች በጨረታው አሸናፊ መሆናቸው የተረጋገጠ ሲሆን ሽያጩ የሽያጭ ስነ ስርዓት ጉድለት አለበት ተብሎ እንዲፈርስ ጥያቄ የቀረበው የፍርድ ባለእዳ በሆኑትና ለእዳው ማስፈጸሚያ ተብሎ የተሸጠው ቤት ባለንብረት የሆኑት የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ መሆናቸውን፣ይኼው ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት የሽያጭ ይፍረስልኝ ጥያቄ ተቀባይነት ሲያጣ ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲያቀርቡ ተጠሪ ያደረጉት የአሁኑን 2ኛ ተጠሪ ወይም የስር የፍርድ ባለመብት መሆኑን፣በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው የ1ኛ ተጠሪ ይግባኝ የተሰረዘው ተጠሪዎች ክርክር ሳያደርጉበት መሆኑን፣ከዚህ በኋላ 1ኛ ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲያቀርቡ ተጠሪ ያደረጉት የአሁኑን 2ኛ ተጠሪ ሁኖ የሰበር ችሎቱ ጉዳዩን አከራክሮ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ የሰጠው የጨረታውን አሸናፊ የሆነውን የአሁኑን አመልካች ወደ ክርክሩ ሳያስገባ መሆኑን ነው፡፡

በመስረቱ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ለ)) እና እና በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 67(2(ሐ)) ተለይቶ የተሰጠው ስልጣን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ማረም እንጂ ፍሬ ነገርን ማጣራት ወይም ማስረጃን መመዘን ያለመሆኑ ተጠቃሽ የሕግጋተ መንግስታት ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡ ሲሆን የክልሉን ፍርድ ቤቶችን ያደራጀው የክልሉ አዋጅ ቁጥር 153/2000 በአዋጅ ቁጥር 169/2002 እንደተሻሻለ በአንቀጽ 8 ስር ሰበር ችሎቱ ያለው ስልጣን መስረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የማረም ስልጣን እንጂ ፍሬ ነገርን ማጣራትና ማስረጃን መመዘን ስልጣን ያለመሆኑን ያስረዳል፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚመራው ከላይ በተጠቀሰው የክልሉ የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅና በ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት መሰረት መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

በመሆኑም ችሎቱ የተለየ የክርክር አመራር ስርዓት የሌለው እስከ ሆነ በ1958ቱ የፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሰረት አድርጎ ክርክሩን መምራትና ዳኝነት መስጠት ያለበት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በ1958ቱ የፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ከተካተቱት ጉዳዮች መካከል ደግሞ የአፈፃፈም ክርክር የሚመራባቸው ድንጋጌዎች በግልጽ ተቀምጠዋል፡፡ እንዲሁም ይኼው ሕግ በአንቀጽ 32 እና 79 ድንጋጌዎች ስር የፍትሃ ብሔር ድንጋጌዎች በሕጉ በተመለከቱት ሁሉም ጉዳዮች ተፈጻሚነት ያላቸው መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን እነዚህ ድንጌጌዎች የቀጥታ ክስና የይግባኝ ክርክሮች ላይ በስነ ስርኣቱ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ያላቸው መሆኑን፣ የይግባኝ መብት ደግሞ በፍርድ አፈፃጸም ፍርድ ቤቱ በሚሰጣቸው ትዕዛዛት ላይ በፍርድ አፈፃፀም ደንብ መሰረት ሌሎቹ ትዕዛዞች ይግባኝ እንደሚባልባቸው ሁሉ ስለ አፈጻጸሙ በሚሰጠው ትዕዛዝ ይግባኝ ማለት የሚቻል መሆኑን በአንቀጽ 370(3) ስር ደንግጓል፡፡ የቀጥታ ክስ ወይም ይግባኝ ክርክር ሲመራ ተግባራዊ መሆን ከአላባቸው የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መካከል ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39 እና 40 ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረታዊ አላማ በአንድ ጉዳይ ላይ ክስ ሲቀርብና የክሱም ምክንያት የብዙ ሰዎችን መብትና ጥቅም የሚነካ ሆኖ ከእነሱ አንዱ ወይም ከፊሉ ክስ በቀረበ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጉዳዩ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ መብትና ጥቅም የሚነካ ሲሆን በክሱ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ በማድረግ መብታቸውን ለማስጠበቅ ነው፡፡ በመሆኑም ይኼው በሕጉ የተቀመጠው መመዘኛ መሟላቱ ከተረጋገጠ በክሱ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39/1/ እና 40/2/ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡

እነዚህ ወገኖች ተካፋይ ሳይሆኑ የሚሰጠው ውሣኔ ወይም ፍርድ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑም የተጠቃሽ ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም በክሱ መግባት ያለበት ተከሣሽ የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የክርክር ተካፋይ እንዲሆንና በቀረበው ክስና መልስ መከላከያውን እንዲያቀርብ ሊያዘው የግድ የሚል ስለመሆኑ ሥነ ሥርአቱ ያሳያል፡፡ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች ማለት ደግሞ ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ ጥቅማቸው፣መብታቸው ወይም ግዴታቸው የሚነካ፣በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች ስለመሆናቸውም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በይግባኝ ደረጃ በሚደረገው ክርክርም ይግባኝ በቀረበበት የበታች ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ውስጥ ተካፋይ የነበረ ማናቸውም ሰው በይግባኝ ክርክሩ ላይ ተካፋይ ሳይሆን የቀረበ እንደሆነ የይግባኝ ውጤት የሚመለከተው መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ሲረዳው የይግባኝ ክርክር መስሚያ ቀነ ቀጠሮ በማስተላለፍ ተካፋይ ያልሆነውን ሰው በመልስ ሰጪነት አባሪ ሆኖ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት ያለበት መሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 40(5) በግልጽ የተመለከተ ሲሆን የሰበር ችሎት የሚመራው በዚሁ በይግባኝ ስርዓት የክርክር አመራር በመሆኑና በዚህ ድንጋጌ የተቀመጠው መመዘኛ ደግሞ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 447(4) ድንጋጌ ይዘት ጋር ሲታይ በጨረታ አሸናፊ የሆነ ሰውን ወደ ክርክሩ እንዲገባ ሳያደርግ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በፍርድ ቤት የሚደረግ ጨረታ በሕግ አግባብ የሚቋቋም ውል በመሆኑ የጨረታ አሸናፊ የሆነ ሰው የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን ውሉ ፈራሽ የሚሆንበት አግባብ ከውል አመሰራረት መሰረታዊ መርሆዎችም ሆነ ከፍርድ አፈጻጸም ስርዓት ጋር የማይሄድ ከመሆኑም በላይ የፍርድ ቤት ክርክሮች በግልጽ ታይተው መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ ሕገ መንግስቱ ስል

ገልፅነትና ተጠያቂነት ከተደነገገው መርህ ጋርም አብሮ የማይሄድ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት አይደለም፡፡ በሕጉ አግባብ የተቋቋመ ውል መኖሩ በፍርድ ቤት የጸደቀለት ሰው ይኼው ውል በሕግ አግባብ ያልተደረገ ነው ተብሎ ፈራሽ ነው የሚል ውሳኔ ሲሰጥበት በዚሁ ላይ የሚያቀርበው ክርክር የማስረጃ ምዘና ብቻ ነው ተብሎ አቤቱታዋው በሰበር ሰበር ስርዓት የማይስተናገድበት አግባብ የለም፡፡ችሎቱ የጨረታ አሸናፊ የሰበር ክርክር የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን የማያሟላ ነው የሚለውን ዳኝነት መስጠት ያለበትም ክርክሩን በሕጉ አግባብ ከመራ በኋላ ሊሆን ይገባል እንጂ አቤቱታ አቅራቢው ወደ ክርክሩ ገብቶ ተገቢውን ክርክር ሳያሰማ ሊሆን አይችልም፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አምስት ዳኞች ተሰይመው የሰጡት ዳኝነት የጨረታውን አሸናፊ የክርክሩ ተካፋይ ያላደረገ ነው የሚለውን የአመልካችን ክርክር የማስረጃ ምዝና ነው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የአመልካችን የመሰማት መብትንም የጎዳ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካች የሰበር አቤቱታ የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ምዘና ቅሬታዎችን መሰረት ያደረገ እንጂ የመሰረታዊ ህግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ አይደለም በማለት ትዕዛዝ መስጠቱ ከመነሻውም ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት ተከትሎ ባልተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሳኔም ሆነ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 14450 ህዳር 04 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ እና በዚሁ መዝገብ ቀኑ ሳይጠቀስ የአመልካች አቤቱታ ማስረጃን መስማትን የሚጠየቅ ነው ተብሎ የተሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽርዋል፡፡
2. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአሁኑን አመልካች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ አድርጎ በ1ኛ ተጠሪ በቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ ግራ ቀኙ በሕጉ አግባብ እንዲከራከሩ በማድረግ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1) መሰረት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ብ/ይ**

የሰ/መ/ቁ.101632

መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- መድሕን ኪሮስ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቢሲኒያ ባንክ አ.ማ. - ነገረ ፈጅ ብርሃኑ አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ዘይቱ ከማል - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ተጠሪ እና የተጠሪ ባለቤት ናቸው የተባሉት አቶ ኑሪ ከማል እንደቅደም ተከተላቸው ከሳሽ እና ተከሳሽ በመሆን ከፍቺ ጋር ተያይዞ ክርክር እያካሄዱ በነበረበት መዝገብ የአሁኑ አመልካች በተከሳሹ ግለሰብ ላይ በሌላ መዝገብ ላስፈረደው የብድር ዕዳ በንብረቱ ላይ አፈጻጸሙን መቀጠል ያስችለው ዘንድ ከፍቺ ክርክር ጋር ተያይዞ በተከሳሹ ስም ተመዝግቦ በሚታወቀው ቤት ላይ በከሳሽ ጠያቂነት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ እንዲነሳለት በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 158 መሰረት ያቀረበውን አቤቱታ እና በአቤቱታው ላይ የተሰጠውን መልስ የመረመረው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዕግዱ ሊነሳ አይገባም በማለት የሰጠው ብይን እና ብይኑ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው በመሆኑ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸው በመሆኑ ሊታረሙ ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ጉዳዩን በተመሳሳይ ጉዳይ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አስቀድሞ በመዝገብ ቁጥር 86400 በ21/09/2005 ዓ.ም. ከተሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም አንጻር ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባው ዕግዱ ሊነሳ አይገባም በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይንጊዜያዊ አገልግሎት ያለው በመሆኑ ከስረ ነገሩ በፍርድ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ትዕዛዝ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ነጥብ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአንድ ፍርድ ቤት በተሰጠ የማገጃ ትዕዛዝ ላይ ቅሬታ የተሰማው ወይም አላግባብ ነው የሚል ወገን ለፍርድ ቤቱ አቤቱታውን ያቀረበ እንደሆነ እና የቀረበውም አቤቱታ በቂ ምክንያት የሚያስገኝ መሆኑን የተረዳው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ሰጥቶት የነበረውን የማገጃ ትዕዛዝ እንዲሻሻል፣እንዲነሳ ወይም ጨርሶ እንዲሰረዝ ለማድረግ እንደሚችል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 158 ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን የማገጃ ትዕዛዝ ይነሳልኝ ጥያቄው በመዝገቡ ተከራካሪ በሆነ ወገን ወይም የክርክሩ አካል ባልሆነ 3ኛ ወገን ጭምር ሊቀርብ የሚችል ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ የዕግድ ይነሳልኝ ጥያቄው የቀረበው በአመልካች ባንክ ሲሆን ተጠሪዋ ባለቤቴ ናቸው ከሚሏቸው ግለሰብ ጋር በሚከራከሩበት መዝገብ ባንኩ ተከራካሪ ወገን አይደለም፡፡ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዙ ላይ እንደገለጸው በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (4) ስር በተጠቀሱት ትዕዛዞች ላይ ካልሆነ በቀር ማናቸውም ፍርድ ቤት ክርክሩን በሚሰማበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ሲሰጥ፣ቀነ ቀጠሮ ሲወስን፣በመጀመሪያ ደረጃ በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ሲሰጥ በእንደእነዚህ ዓይነቶቹ ትዕዛዞች ላይ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ማለት የማይቻል ስለመሆኑ እና ነገር ግን ለክርክሩ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ከዚህ በላይ በተገለጹት ትዕዛዞች ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን በስረነገሩ ፍርድ ላይ ከሚያቀርበው ቅሬታ ጋር አጠቃሎ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 320(3) ስር ተደንጓል፡፡

ከድንጋጌው አነጋገር በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው ድንጋጌው ጊዜያዊ አገልግሎት ባላቸው ትዕዛዞች ላይ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ማቅረብን የከለከለው የስረ ነገሩ ጉዳይ ውሳኔ ባገኘ ጊዜ በስረ ነገሩ ፍርድ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን  በስረ ነገሩ ፍርድ ላይ ብቻ ሳይሆን አስቀድሞ በተሰጠበት ጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትዕዛዝ ላይም ቅሬታውን አጠቃሎ የማቅረብ መብት ስለተጠበቀለት ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ባንክ የስረ ነገሩ ጉዳይ ተከራካሪ ወገን ስላልሆነ የስረ ነገሩ ክርክርም ሆነ በክርክሩ መጨረሻ የሚሰጠው ውሳኔ አይመለከተውም፡፡ የዕግድ ትዕዛዙ ሊነሳ ይገባል ወይስ አይገባም? በሚለው ጭብጥ ላይ የሚሰጠው ትዕዛዝ ከአመልካች አንጻር እንደመጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር እንጂ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ነው የሚባል አይደለም፡፡በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከዚህ አንጻር በመገንዘብ የቀረበለትን የይግባኝ ቅሬታ መርምሮ ተገቢ ነው የሚለውን ትዕዛዝ ሊሰጥበት ሲገባ ብይኑ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው በመሆኑ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት መዝገቡን ዘግቶ መመለሱ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 320(3) ድንጋጌን እና ዓላማ እና ይዘት ያገናዘበ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የእግድ ትዕዛዙ ሊነሳ አይገባም በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው በመሆኑ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ  መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የዕግድ ትዛዙ ሊነሳ አይገባም በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 206422 በ03/07/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ብይን ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ስለሆነ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ

ቤት በመዝገብ ቁጥር 150681 በ15/08/2006 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሮአል፡፡

2. የዕግድ ትዛዙ ሊነሳ አይገባም በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 206422 በ03/07/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ብይን ከአመልካች ባንክ አንጻር የመጨረሻ እንጂ ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ይህንኑ ተገንዝቦ የቀረበለትን ይግባኝ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት ወስነናል፡፡በዚሁ መሰረት ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::**

**ብ/ይ**

የሰ/መ/ቁ. 103781

ቀን መጋቢት 17/2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች ፡- ወ/ሮ አስካለ አሸኔ - ጠበቃ በርታ በቀለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ታምራት ተስፋዬ - ጠበቃ አሸናፊ ቦሻ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በመዝገብ ቁጥር 197469 ጥር 12 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 150493 ግንቦት 5 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የፍች ውሳኔን በመቃወም የቀረበ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ የአባቱ የአቶ ተስፋዬ ጉልማ አሳዳሪና ሞግዚት መሆኑን ገልፆ፣የአቶ ተስፋዬ ጉልማና አመልካች 1964 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ ተሣስረው ኖረዋል፡፡በትዳራቸው ልጆች አላፈሩም ፡፡ አባቴና ሞግዚት አድራጊና በእድሜ በመግፋታቸው ምክንያት የአእምሮና የጤና መታወክ አጋጥሟቸዋል፡፡ ተጠሪ ባላቸውን ሊንከባከቡዋቸው አልቻለም በዚህ ምክንያት ሁለቱ ተለያይተው መኖር ከጀመሩ ረዥም ጊዜ ሆኗቸዋል ፡፡ ስለዚህ ሞግዚት አድራጊዬ ከተጠሪ /አመልካች /ጋር ያላቸው ጋብቻ በፍች እንዲፈርስ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ የአሁን አመልካች /በሥር ተጠሪ/ለፍች የሚያበቃ ምክንያት የለንም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አቶ ተስፋዬ ጉልማ በአካል በተደጋጋሚ እያስቀረበ ካነጋገረ በኃላ በአቶ ተስፋዬ ጉልማና በአመልካች መካከል በፍች እንዲፈርስ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡
2. አመልካች ተጠሪ ፍች እንዲወሰን የማመልከት ስልጣን የለውም ፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው የፍች ውሣኔ ህግን መሠረት ያደረገ አይደለም በማለት ነሐሴ 5 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርበዋል ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ከሞግዚት አድራጊዬ ጋር የባልና የሚስት ግዴታ እየተወጡ አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠው ሞግዚት አድራጊዬን በተደጋጋሚ አስቀርቦ ሁኔታውን ከተረዳ በኃላና በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ መሠረት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል ፡፡

3. የሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የተጠሪን የፍች ጥያቄ በመቀበል የሰጡት የፍች ውሳኔ ሕግን መሠረት ደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳይን መርምረናል፡፡
4. በመርህ ደረጃ የፍች ጥያቄ ለማቅረብ የሚችሉት ባል ወይም ሚስት ወይም ሁለቱም በጋራ ጥያቄ በማቅረብ እንደሚሆን በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/992 አንቀፅ 81 ተደንግጓል ፡፡ ሆኖም አንድ ሰው ጋብቻ ፈፅሞና በጋብቻ ተሣሥሮ ከኖረ በኃላ በፍርድ ክልከላ የተደረገበት በሆነ ጊዜ የፍች ጥያቄ የሚያቀርበው በምን ሁኔታና እንዴት ነው የሚለው ጥያቄ ሲነሳ በፍታብሔር ሕግ በፍርድ ስለሚደረግ ክልከላና ክልከላው ስለሚያስከትለው ውጤት ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 351 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 389 የተደረጉትን ድንጋጌዎች መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይም የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 370 ንዑስ አንቀፅ 1 ፍች ወይም ከሕግ ውጭ የሚያደርገው የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲቀር ጥያቄ ለማቅረብ የተከለከለው ሰው ፈቃድ የግድ አስፈላጊ እንደሆነ የአሳዳሪውም ፈቃድ የግድ አስፈላጊ ነው በማለት ይደነግጋል ፡፡
5. ከዚህ አንፃር የአቶ ተስፋዬ ጉልማ አሳዳሪና ሞግዚት ሆኖ የተሾመው ተጠሪ ሞግዚት ሆኖ የሚያስተዳድራቸው ወላጅ አባቱ ፤በእድሜ በመግፋታቸው ምክንያት ራሳቸውን ችለው ህጋዊ ተግባራት መፈፀም እንደማይችሉ በፍርድ ተረጋግጦ ክልከላ የተደረገባቸው መሆኑንና አመልካችና አቶ ተስፋዬ ጉልማ ተለያይተው ለረጅም ጊዜ መኖራቸውን በመግለፅ ፍች እንዲወሰን ጠይቋል፡፡ ይህም ተጠሪ የፍታብሔት ህግ ቁጥር 370 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ጋብቻው በፍች እንዲፈርስ ጥያቄ ያቀረበ መሆኑን ያሳያል ፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ፤አቶ ተስፋዬ ጉልማ በተደጋጋሚ ቸሎት በማስቀረብና ካናገረ በኃላ አመልካችና አቶ ተስፋዬ ጉልማ በቤተሠብ ህጉ በባልና ሚስት ላይ የተጣለውን እርስ በእርስ የመተጋገዝ የመረዳዳት ፣የመደጋገፍና የመተሳሰብ ግዴታ እየተወጡ አለመሆኑን በማረጋገጥ ጋብቻው በፍች እንዲፈርስ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይህ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ አመልካችና አቶ ተስፋዬ ጉልማ በሕግ ፊት ባልና ሚስት ናቸው ቢባልም በዕውኑ ግን በባልና ሚስትነት የመፈፀማቸውን ተግባራትን ግዴታዎች እየፈፀሙ የማይኖሩ መሆኑንና የጋብቻው በፍች መፍረስ በፍርድ ክልከላ የተደረገባቸውን አቶ ተስፋዬ ጉልማ መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ መሆኑን በማረጋገጥ የሰጠው ውሳኔ መሆኑን በውሣኔ ተረድተናል ፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል ፡፡
2. ይህ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 103781 ህዳር 17 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስትዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

# አሠሪና ሠራተኛ

የሰ/መ/ቁጥር 95638

መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካች፡-ኢስት ሲሜንት አክሲዮን ማህበር - ጠበቃ ዓለሙ ደነቀው - ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ዘላለም ታደሰ - ጠበቃ ገናናው ተሾመ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የቀረበውን የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረበት ፍርድ ቤት የሂደቡ አቦቴ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡በዚህ ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ሁኖ የክሱ ይዘትም፡-በተጠሪ ድርጅት በአስተዳደር ኃላፊነት እና ጉዳይ አስፈፃሚነት አምስት አመት ከዘጠኝ ወር ብር 6,410.90 በወር እየተከፈላቸው ማገልገላቸውንና የስራ ውሉ ከሕግ ውጪ መቋረጡን ገልጸው ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ የነበረ ቢሆንም መጥሪያ ደርሶታል፣ግን አልቀረበም ተብሎ በሌለበት ጉዳዩእንዲታይ ተደርጓል፡፡የሥር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑ አመልካች ለክሱ ኃላፊ ነው ተብሎ ለከሳሽ ብር 277,294.00 ( ሁለት መቶ ሰባ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና አራት) ብር እንዲከፈል ወሰኗል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሌለሁበት ታይቶ የተወሰነው ውሳኔ ተነስቶ ባለሁበት ይታይልኝ በማለት ጥያቄ ያቀረበ ሲሆን ከዚሁ ጋር በተጨማሪ ከሳሹ የአሰሪ ወገን ስለሆነ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ሊዳኝ አይገባም፣በአዋጁ መሰረት ሊዳኝ ይገባል ከተባለም የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጋዊ መንገድ ስለሆነ ሊፈጸም የሚገባ ክፍያ የለም፣ክፍያ ሊፈፀም ይገባል ከተባለም ከሳሽ ደሞዜ ነው ብሎ ያቀረበው መጠን ትክክል አይደለም፣በትክክል ደመወዙ ላይ ተመስርቶ ሊከፈል የሚገባውም የደመወዙን $\frac{1}{10}$ ኛውን ያህል ብቻ ነው ብሎ ተከራክሯል፡፡የስር ፍርድ ቤት በአመልካች በሌለሁበት ታይቶ የተወሰነው ውሳኔ ይነሳልኝ ጥያቄ ላይ የአሁኑ ተጠሪ (የስር ከሳሽ) አስተያየት እንዲሰጡበት ያደረገ ሲሆን ተጠሪው በሰጡት አስተያየትም ለአመልካች መጥሪያውን ባቀረቡት የቃለ መሐላ አቤቱታ የተዘረዘሩ ምስክሮች የሚያረጋገጡ መሆኑን እና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው የተወሰነውም በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ጉዳዩ ባለሁበት ይታይልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፣በቃለ መሐላ ተረጋግጧል በማለት ውሳኔ ሰጠ ፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ

ፍርድ ቤት አቅርቦ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ከዚህም በኋላ አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ መጥሪያው በሕጉ መሰረት ለአሁኑ አመልካች የደረሰው መሆንያለመሆኑን የግራ ቀኙን ምስክሮችእንዲሰሙና ተገቢው እንዲወሰን በማለት ጉዳዩን ለወረዳው ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡ በዚህ አግባብ ጉዳዩ የተመለሰለት የወረዳው ፍርድ ቤትም በ18/03/2004 ዓ/ም የአሁኑ ተጠሪ ለወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረቡት ቃለ መሃላ ላይ ያሉትን ምስክሮችን ከሰማ በኋላ የአሁኑ አመልካች ደግሞ የቀረቡት ምስክሮች ይበቁናል ስላለ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ መጥሪያው ለአመልካች መድረሱ ተረጋግጧል በማለት በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሳኔ አይነሳም ሲል በ24/05/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ ላይ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ይግባኙን አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ መሰማት የሚገባቸው ምስክሮች በ18/03/2004 ዓ/ም በተጻፈ የተጠሪ ቃለ መሃላ ላይ ያሉት ምስክሮች ሳይሆኑ በ26/03/2004 ዓ/ም በተጻፈ ቃለ መሃላ ላይ ያሉት ምስክሮች ናቸው በማለት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መመሪያ መሰረት የወረዳው ፍርድ ቤት አልፈጸመም ሲል በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ በ28/06/2005 ዓ/ም በዋለው ችሎት ሽሮ በ26/03/2004 ዓ/ም በተጻፈ ቃለ መሃላ ላይ ያሉት ምስክሮች እንዲሰሙ ሲል ጉዳዩን ለወረዳው ፍርድ ቤት መልሶ ልኮለታል፡፡.የአሁኑ ተጠሪ በዚህ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ችሎቱ መሰማት የሚገባቸው በ18/03/2004 ዓ/ም በተፃፈ ቃለ መሃላ ላይ የተዘረዘሩት ምስክሮች ናቸው? ወይስ በ26/03/2004 ዓ/ም በተጻፈ ቃለ መሃላ ላይ የተገለፁት ምስክሮች ናቸው? የሚለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በመመርመር የወረዳው ፍርድ ቤት በ12/03/2004 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ የተከሳሽን መልስ ለመቀበል ብሎ ለ18/03/2004 ዓ/ም መቅጠሩን፣በዚህ ቀን ከሳሽ ለተከሳሽ መጥሪያ ማድረሱን በመግለፅ በቃለ መሃላ የተከሳሽ መልስ የመስጠት መብት መታለፉን፣በ26/03/2004 ዓ/ም ደግሞ ከሳሽ ደመወዝ ሲበላበት የነበረ ፔሮል ለተከሳሽ ድርጅት እንዲያቀርብ የታዘዘ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳቱን ጠቅሶ መሰማት ያለባቸው ምስክሮች በ18/03/2004 ዓ/ም በተፃፈው ቃለ መሃላ ያሉት ምስክሮች እንጂ በ26/04/2004 ዓ/ም በተጻፈ ቃለ መሃላ የተገለፁ ምስክሮች አይደሉም በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ በ20/01/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የተሠጠውን ውሳኔ ሽሮ የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲሆን የአመልካች የሠበር አቤቱታ ቅሬታ መሰረታዊ ነጥቦችም፡-የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለወረዳው ፍርድ ቤት የመለሰው በ26/03/2004 ዓ/ም በተፃፈ ቃለ መሃላ የተገለፁትን ምስክሮች እንዲሰሙ ሁኖ እያለ መልሶ መሰማት ያለባቸው በ18/03/2004 ዓ/ም በተጻፈ ቃለ መሃላ የተገለፁትን ምስክሮች ናቸው ማለቱ ተገቢነት የለውም፣የተጠሪው ደመወዝ ተጠሪው እንደገለፀው ብር 6,410.00 ሳይሆን ብር 3,230.70 ብቻ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የስራ ስንብት ክፍያ ብር 47,383.60 እንዲሆን መወሰኑ ያላግባብ ሲሆን የስራ ስንብት ክፍያው ብር 8,348.00 ብቻ ነው፣የካሳ ክፍያ ብር 19,384.00 መሆን ሲገባው ብር 25,849.60 መሆኑ ያላግባብ ነው፣የሳምንት የእረፍት ክፍያ ሊተመን በማይችል ስሌት ብር 188,784.57 ሁኗል፣የአምስት አመት በዓል በማለት ብር 16,357.00 እንዲከፍል መወሰኑ ያላግባብ ነው፣የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው የሚባል ከሆነም ሊከፈሉ የሚገባቸው ክፍያዎች፤-የአገልግሎት ክፍያ ብር 8,384.30፣የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ ብር 6,461.40፣የካሳ ክፍያ ብር 19,384.20 በድምሩ ብር 34,229.90 እንጂ ብር 277,294.00 እንዲከፈል መወሰኑ ያለአግባብ ነው በማለት በዚህ ችሎት እንዲወሰን የጠየቀው ዳኝነትም የአመልካች የመከራከር መብቱ እንዲጠበቅለት፣ይህ የሚታለፍ ከሆነ በአዋጁ መሰረት ክፍያዎቹ መወሰን አለባቸው የሚል

ነው፡፡የሠበር አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት ጉዳዩ እንዲታይ የተደረገው ከአመልካች ማንነት አንፃር ይህንኑ ጉዳይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀብሎ ማየቱ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ሲሆን ተጠሪ ቀርበው በሰጡት መልስም ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ስለሆነ አዋጁ ከወጣበት ጊዜ አንጻር በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የማይታይበት ምክንያት የለም፣ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ስለሆነ በዚህ ችሎት የሚታይ አይደለም፣በሌለበት በታየ ጉዳይ በስንብቱ እና በደመወዝ መጠኑ ሊከራከርአይችልም፣ተጠሪ የአሰሪ የአስተዳደር አካል ያለመሆናቸው በማስረጃ ተረጋግጧል፣በቃለ መሃላ ጉዳይ ላይ ማስተባበያ ማስረጃ አላቀረበም፣የተጠሪ ምስክሮች የእኔም ምስክሮች ናቸው በማለት መግለፁን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል፣የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ራሱ የሰጠውን ውሳኔ አልሻረም፣በ26/03/04 በተጻፈ ቃለ መሃላ የተገለጹት ምስክሮች የሚሰሙበት ምክንያት የለም፣በዚህ ቀን የቀረበው ቃለ መሃላ የስር ተከሳሽ ከሳሽ የሚበላውን ደመወዝ መዝገቡን እንዲያቀርብ በ22/03/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ፍርድ ቤቱ አዞት ስለነበር ተከሳሹ የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ አልፈፀመም፣የፍርድ ቤቱን መጥሪያአልወሰድም ማለቱን ለማረጋጋጥ ነው፣ በማለት ዘርዝሮ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 163369 በ20/01/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲፀናላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካችም ያስቀርባል የተባለበትን ነጥብ በመደገፍና በሰበር አቤቱታው ላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦችን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

ከዚህም በኂላ ይህ ችሎት ጉዳዩን መርምሮ አመልካች መጀመሪያ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳለት ለወረዳው ፍርድ ቤት አመልክቶ ተቀባይነት ካጣ በኂላ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ሲያቀርብ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ስርዓቱን ጠብቆ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መከራከሩን ለማወቅ ይረዳ ዘንድ የወረዳው ፍርድ ቤት መጀመሪያ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ ግልባጭ፣አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የይግባኝ እና የሰበር አቤቱታ ግልባጮችን እንዲያያይዝ ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካችአሉኝ ያላቸውን ውሳኔዎችን አያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክርና ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩመርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ነጥቦች፡-

1. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለው ወይስ የለም?
2. የአመልካች የመከራከር መብት የታለፈው በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?
3. የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተለያዩ ክፍያዎችን ለተጠሪ እንዲከፍል በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም?

<u>**የመጀመሪያውን ጭብጥ** በተመለከተ</u>፡-በመሰረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግስትና በክልሎች መዋቀሩን መሰረት በማድረግ የዳኝነቱም ሥልጣን በፌዴራል መንግስቱ እና በክልል መንግስታት መካከል እንደተከፋፈለ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 50 እና 51 ሥር ተመለክቷል፡፡በኢ.ፌ.ዲ.ሪሕገ መንግስት በአንቀጽ 80 “የፍ/ቤቶች ጣምራነትና ሥልጣን” በሚል ርዕስ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻየዳኝነት ሥልጣኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት፤በክልል ጉዳዮች ላይ በክልሉ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሥልጣኑ የተደነገገ ሲሆን የክልል ፍ/ቤቶች በህገ-መንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት ካልሆነ በቀር የፌዴራልን ጉዳይ ለማየት፤እንዲሁም የፌዴራል ፍ/ቤቶች የክልልን ጉዳይ ለማስተናገድ የሚያስችል ሥልጣን የሌላቸው መሆኑን በዚሁ ድንጋጌ ስር የተቀመጡት ንዑስ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ

ያሳያል።አንድ ጉዳይ የፌዴራል ነው? ወይስ የክልል? የሚለውን ለመለየትም መሰረቱ የአዋጅ ቁጥር 25/88 ሲሆን፤በዚሁ ህግ አንቀጽ 5 ሥር በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የክልል ፍ/ቤቶችስልጣን የሚኖራቸው በህገመንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን አግባብ ብቻ ነው።ይህ በግልፅ የሚያሳየው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 መሰረት የፍርድ ቤቶች ስልጣን በጉዳዩ ባለቤትነት (Subject matter) የሥልጣን ክፍፍል እንደተጠበቀ ሆኖ ክሱም መቅረብ ያለበት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሥረ-ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ስለመሆኑ ነው።የፌደራል ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 8፣11፣14 እና 15 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ደግሞ አንዳንድ ጉዳዮች ሊያስነሱ በሚችሉት የክርክር ባህርይ ምክንያት ለተወሰኑ ፍ/ቤቶች እንዲቀርቡ በህግ ተለይተው ከተመለከቱት በቀር የሥረ-ነገር ሥልጣን የተደለደለው በክሱ በተመለከተው የገንዘብ ወይም የንብረት ግምት መነሻ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 14 እና 15 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌች ጣምራ ንባብ እና የክልል መንግስታት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ሕጎች ያስረዳሉ።ይህ በእንዲህ እንዳለ ግን አዋጅ ቁጥር 25/1988"ን" ያወጣው የፌዴራል መንግስት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የስራ ክርክሮች የሚመሩበትን ስርኣት የዘረጋውን አዋጅ ቁጥር 377/1996 ከየካቲት 18 ቀን 1996 ዓ/ም ስራ ላይ ያዋለ ሲሆን በዚህ አዋጅ የስራ ክርክር ስልጣን ድልድል የተደረገው የግል የስራ ክርክርና የወል የስራ ክርክር የሚሉትን ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ ሲሆን የተከራካሪ ወገንን ማንነትን ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መልኩ አይደለም።በመሆኑም ክርክሮቹ ክልል የተነሱ ቢሆንም ጉዳዩን የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም አግባብነት ያላቸው የቋሚ ወይም ጊዜአዊ ቦርዶች ሊመለከቱ እንደሚችሉ አድርጎ ሕጉን ሕግ አውጪው አውጥቷል።ይህ አዋጅ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 በኋላ ከመውጣቱም በላይ ለስራ ክርክሮች ልዩ ሕግ ነው።እንዲህ ከሆነ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ለስራ ክርክሮች ከሕገ መንግስቱ በመለስ ባሉት ማናቸውም ሕጎች የበላይ ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያስረዱን ጉዳይ ነው።በመሆኑም በስራ ክርክር ተከራካሪ ወገኖች ማንነት የፍርድ ቤቶችን ስልጣን (የክልል ወይም የፌዴራል) ብሎ ለመወሰን እንደወሳኝ መለኪያ ሊወሰድ የሚገባው አይደለም።ከዚህ አንጻር ሲታይ ደግሞ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ ማየቱ ከላይ የተመለከተውን የህጉን ማዕቀፍ እና በዚህ ረገድ ይህ ችሎት በመ/ቁጥር 95298 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) መሰረት በአከራካሪው የህግ ነጥብ ላይ ከሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጋር የተጣጣመ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበትን አግባብ አላገኘንም።

__ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ__:- በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር94 ስር እንደተመለከተው መጥሪያ በቅድሚያ መድረስ ያለበት ለተከሰሰው ሰው ሲሆን የተከሰሰው ሰው የንግድ ድርጅት ከሆነ ደግሞ ከድርጅቱ ጸሃፊ ወይም ለድርጅቱ ኃላፊ መስጠት ያለበት መሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 97(1) ስር ተመልክቷል።ሕጉ መጥሪያ አሰጣጥ ዘዴና ቅደም ተከተሉ እንዲሁም መጥሪያው ለማን እንደሚሰጥ የሚመለከተው የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ክፍል ዓይነተኛ ዓላማ ከሆኑት መካከል አንዱ ተካራካሪ ወገኖችን እኩል የመከራከር መብት እንዲኖራቸው በማድረግ ጉዳዩን ፍትሐዊ በሆነ አኳኋን ለመወሰንማስቻል መሆኑን ይታወቃል።በመሆኑም ፍርድ ቤቱ መጥሪያ የሚደርስበትን ተገቢ መንገድና ለማን መድረስ እንዳለበት ማረጋገጥ ይገባዋል።

መጥሪያ በተገቢው መንገድ ደርሶት ተከራካሪ ወገን ካልቀረበ ወይም መጥሪያን አልቀበልም ካለ ፍርድ ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ስርዓትም በሕጉ በግልጽ ተመልክቷል። ከእነዚህም ድንጋጌዎች መካከል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 70(ሀ)፣103፣104፣105፣ 106 እና 107 ስር የተመለከተው ሊጠቀሱ

የሚችሉ ሲሆን በእነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት ተከሳሽ በሌለበት ክርክሩ ታይቶ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው መጥሪያው በአግባቡ የደረሰው መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም መጥሪያውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑ ወይም ሊገኝ ያልቻለ መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ድንጋጌዎቹ መጥሪያው በትክክል ያልደረሰው መሆኑ ከተረጋገጠ ጉዳዩ ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ የማይታዘዝ ስለመሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 70(ሀ) ድንጋጌ ስር ላይ **"መጥሪያው በትክክል መድረሱ"** የሚለው ሐረግ መኖሩም የሚያሳየው ስለመጥሪያ አሰጣጥና አደራረስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 94 እስከ 110 ድረስ የተመለከቱት ሁኔታዎች በአግባቡ መሟላታቸውን የሚያስገነዝብ ነው፡፡አንድ ተከሳሽ በሌለበት ጉዳዩ ታይቶ ውሳኔ ከተሰጠውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 78 መሰረት መፍትሔ መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት መፍትሔ ሊጠየቅ የሚችለው አቤቱታ አቅራቢው በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ የጥሪው ትዕዛዝ "በሚገባ ያልደረሰው" መሆኑን በመጥቀስ ይህንኑ ማረጋገጥ ሲችል ነው፡፡ከእነዚህ ሁሉ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው አንድ ሰው የመከራከር መብቱን እንደተወው የሚቆጠረው መጥሪያው በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓትና ቅደም ተከተል መሰረት ደርሶት ክርክር ያለው መሆኑን እያወቀሳይቀርብ ሲቀር ብቻ መሆኑን ነው፡፡ፍርድ ቤቱ በሕጉ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትሎ አማራጭ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት ከፈጸመ መጥሪያው ለተከሳሹ እንደደረሰ እንደሚቆጠርና በቂና ሕጋዊ ምንክያት ካለው ብቻወደ ክርክሩ እንዲገባ የሚፈቀድ መሆኑን ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ስለሆነም ማንኛውም ውሳኔ መሰጠት ያለበትም በሕጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሰረት መጥሪያው መድረሱ በሚገባ የተረጋገጠና የተከሳሽ የመከራከር መብት የተጠበቀ መሆኑ ሲታወቅ ሊሆን ይገባል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም በወረዳው ፍርድ ቤት በነበረው ክስ ተጠሪ ለአመልካች ድርጅት መጥሪያውን እንዲያደርሱ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ መጥሪያውን ይዘው "ለድርጅቱ ኃላፊ ልሰጥ ስል ኃላፊው አልቀበልም ብለውኛል" በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 103 መሰረት በቃለ መሃላ አረጋግጠው መጥሪያውን የመለሱ ሲሆን ለዚህም ምስክሮች ያላቸው መሆኑን ጭምር ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት በ18/03/2004 ዓ/ም እና በ26/03/2004 ዓ/ም የተጻፉ ሁለት ቃላ መሃላዎችን ያቀረቡ ሲሆን አሁን በዚህ ረገድ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው በየትኛው ቀን የተዘረዘሩት ምስክሮች ናቸው ስለመጥሪያው አደራረስ ሊመሰክሩ የሚገባቸው? የሚል ነጥብ ነው፡፡ከላይ እንደተገለጸው የተጠሪ የመጥሪያ አደራረስ በቃለ መሃላ ተደግፎ የቀረበ ቢሆንም መጥሪያውን ለአመልካች ድርጅት ያደረሱ መሆን ያለመሆኑን በተመለከተ ምስክሮች እንዲሰሙ በማለት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 148159 ጥቅምት 26 ቀን 2005 ዓ/ም ተወስኖ ጉዳዩ የተመለሰለት የወረዳው ፍርድ ቤትም በ18/03/2006 ዓ/ም በተፃፈው ቃለ መሃላ የተጠቀሱትን ምስክሮች የሠማና ምስክሮቹ መጥሪያውን ተጠሪ ለአመልካች ድርጅት ማድረሳቸውንና የአመልካች ድርጅት ኃላፊ አልቀበልም ማለታቸውን ማረጋገጣቸውን ምክንያት አድርጎ የአመልካችን በሌለሁበት ታይቶ የተወሰነ ውሳኔ ይነሳልኝ ጥያቄን ሳይቀበለው የቀረ ሲሆን ይኼው የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ በክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ እንግዲህ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 148159 በ26/02/2005 ዓ/ም በተሰጠው ውሳኔ ስለመጥሪያው አደራረስ የግራ ቀኙ ምስክሮች እንዲሰሙ ተብሎ ለወረዳው ፍርድ ቤት ከመመለሱ ውጪ በ26/03/2004 ዓ/ም በተጠሪ ለወረዳው ፍርድ ቤት በቀረበው ቃለ መሃላ የተጠቀሱት ምስክሮች እንዲሰሙ በግልጽ የተሰጠ ውሳኔ የለም፡፡በ26/03/2004 ዓ/ም ቀረበ በተባለው ቃለ መሃላ ያሉት ምስክሮችም አመልካች የተጠሪን ደመወዝ መጠን ለማወቅ ይቻል ዘንድ መዝገቡን እንዲያቀርብ የወረዳው ፍርድ ቤት በ22/03/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቶ ስለነበር አመልካች  የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ አልፈፀምም፣የፍርድ ቤቱን መጥሪያአልወሰድም ማለቱን ለማረጋጋጥ የቀረቡ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ ሁኖ

አግኝተናል፡፡እንዲህ ከሆነ በ26/03/2004 ዓ/ም በቀረበው ቃለ መሃላ የተጠቀሱት የተጠሪ ምስክሮች ስለመጥሪያ አደራረስ የሚሰሙበት የሕግ አግባብ የለም፡፡አንድ ማስረጃ መሰማት የሚገባው ለጉዳዩ አግባብነት ሲኖረው ስለመሆኑ ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ሕግ ደንቦች የሚሳዩት ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነምአመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡በ18/03/2004 ዓ/ም በተጻፈ የተጠሪ ቃለ መሃላ የተጠቀሱት ምስክሮች መሰማታቸው ተገቢ ነው ከተባለ እነዚህ ምስክሮች አመልካች መጥሪያ ደርሶት አልቀበልምበማለት ተጠሪን የመለሳቸው መሆኑን ያረጋገጡት የፍሬ ነገር ጉዳይ በመሆኑ የተጠሪ የመከራከር መብቱ መታለፉ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 97(1)፣103፣70(ሀ) እና 78 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ተገቢ እንጂ የሚነቀፍበት አግባብ የለም፡፡

<u>ሦስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>አመልካች ተጠሪን ያሰናበተበትን ሕጋዊ ምክንያት በዋናው ክርክር ያለበቂ ምክንያት ባለመቅረቡ አላስረዳም፡፡ይልቁንም ተጠሪ አመልካች ከህግ ውጪ ያሰናበታቸው መሆኑን በወረዳው ፍርድ ቤት ባቀረቡት ማስረጃ ያረጋገጡት ጉዳይ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡በመሆኑም የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በዚህ ችሎት የሚለወጥበት አግባብ የለም፡፡በመሰረቱ አንድ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ በተሰጠው በዋናው ጉዳይ ላይ ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ የይግባኝ አቀራረብ አድማሱ በተወሰኑት ነጥቦች ላይ ብቻ መሆን እንዳለበት የይግባኝ አቀራረብን በተመለከተ የተደነገጉት ድንጋጌዎች መንፈስ እንደሚያስረዳና ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተወሰነበት ተከሣሽ ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ በስር ፍ/ቤት በተከራካሪነት ቀርቦ ያላነሣውን ነጥብ ማንሳት እንደማይችል፣እንደዚህ ዓይነት ተከራካሪ በፍ/ቤቱ የውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ክሱን፣የማስረጃዎችን አግባብነት ተቀባይነት እና ጥንካሬ ባግባቡ ያላገናዘበ ሁኔታ አለ የሚል ከሆነ ይግባኝ ሊያቀርብ እንደሚችል ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 36412 በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤትን የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም ፍ/ቤት ከሣሹ ያቀረበው ክስ አባሪ ሆነው ከቀረቡት ማስረጃዎች አግባብነት፣ተቀባይነትና ጥንካሬ አኳያ በመመርመር ተገቢውን ዳኝነት አልሰጠም በሚል ይግባኝ የማቅረብና ወደ ቀጣዩ የሰበር ደረጃም ቅሬታውን ማድረስ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ ውሳኔ ለተሰጠበት ወገን በሕግ የተጠበቀለት መብት መሆኑ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የወረዳው ፍርድ ቤት በ29/03/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ብሎ ሲወሰን በዚህ ውሳኔ ተጠሪ የሚከፈለኝ ገንዘብ በግልጽ አልተቀመጠልኝም በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን አይቶ ለስር የተጠሪ ደመወዝ ተጣርቶ ሊታወቅ ይገባል፣ከዚህ በኋላ የማስጠንቀቂያ፣የስራ ስንብት ክፍያ እና ካሳ፣የሳምንት፣የአመት እና የበዓል ቀናት ክፍያዎች እንዲሁም ያልተከፈለው ደመወዝ ታስቦ በግልጽ መቀመጥ አለበት በማለት በመ/ቁጥር 33824 በ17/05/2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ለወረዳው ፍርድ ቤት መልሶለት የወረዳው ፍርድ ቤትም ተከሳሽ ግብር ሲከፍልበት የቆየበት ቦታ በደገም ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት እና በተከሳሽ ድርጅት እንዲቀርብ አዝዞ ደመወዝንና የትርፍ ሰዓት ክፍያ በጠቅላላው ብር 6410.92 መሆኑ በድጋሚ እንደቀረበለት ጠቅሶ እንዲሁም ከደገም ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ከሳሽ ደመወዝ ሲበላበት የነበረው እና ወሩ ያልታወቀ ፔሮል ቀርቦ በሁለቱም ወገኖች ስምምነት መደረሱን ገልፆ ውሳኔውን ወደ ገንዘብ ለውጦ ማስቀመጥ የአፈፀጸም ክስ ቡድን እንጂ የፍርድ ቤት ተግባር አይደለም፣ግን የይግባኝ ሰሚውን ፍርድ ቤት ትዕዛዝ መከተል ተገቢ ነው ብሎ ተጠሪ በሰዓት የሚያገኘው ደመወዝ ብር 13.46.00፣በቀን ደግሞ 107.69 መሆኑን ማረጋገጡን ጠቅሶ የወር

ደመወዙን ብር 3230.70 ይዞ ክፍያዎችን አስልቶ በጠቅላላው ብር 277,294.04 እንዲከፈለው ሲል በመ/ቁጥር 03756 የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት ወስኗል፡፡አመልካች በሌለበት ጉዳዩ በመታየቱ ላይ የይግባኝ ቅሬታና የሰበር አቤቱታ ለክልል ፍርድ ቤቶች ሲያቀርብ ለተጠሪ እንዲከፈሉ በተወሰኑ ክፍያዎች መጠን ላይም በሕግ አግባብ ያልተሰሉ መሆኑን ጭምር በመጥቀስ ቅሬታ ሲያቀርብ የነበረ መሆኑን የክርክር ሂደት የሚያሳይ ሲሆን ተጠሪ በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር አመልካች በሌለበት በታየው ውሳኔ ላይ ይግባኝና የሰበር ክርክር ማቅረብ አይችልም የሚል መሆኑን ተረድተናል፡፡ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለጸው አመልካች በሌለበት ጉዳዩ ቢታይም ተጠሪ ያቀረቡት ክስ አባሪ ሆነው ከቀረቡት ማስረጃዎች አግባብነት፣ተቀባይነትና ጥንካሬ ያለመመርመሩንና እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 377/1996 ከአስቀመጠው የክፍያ ስሌት ውጪ መሆኑን በሚያሳዩት ነጥቦች ላይ በዚህ ችሎት ክርክር ከማቅረብ የሚያግደው የሥነ ስርዓት ህግ የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር የምንቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የሥራ ውል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል ሁኔታ ሣያጋጥመው ካቋረጠ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 39(1/ለ) መሠረት በአንቀፅ 40 ንዑስ አንቀፅ 2፣ በአንቀፅ 44 እና በአንቀፅ 43 ንዑስ አንቀፅ 4(ለ) የተደነገጉትን ክፍያዎች ለተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ከዚህ አንጻር የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል በማለት የዘረዘራቸው የክፍያ አይነቶች የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ካሳ፣የስራ ስንብት ክፍያ፣የሳምንት እረፍት ክፍያ፣የአምስት አመት በዓላት ክፍያ ናቸው፡፡የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣የስራ ስንብት ክፍያና የካሳ ክፍያዎች የሚሰሉበት አግባብ በሕጉ ተለይቶ የተቀመጠ ሲሆን ይህንኑ በሕጉ የተቀመጠውን ስሌት ተግባራዊ ለማድረግ ሰራተኛው በወር ሲከፈለው የነበረው ደመወዝ በሕጋዊ ማስረጃ መረጋግጥ የግድ ይላል፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪ የወር ደመወዝ ብር 3230.70(ሶስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ብር ከሰባ ሳንቲም) መሆኑን በመ/ቁጥር 03756 የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ አረጋግጧል፡፡በመሆኑም የተጠሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣የስራ ስንብትና የካሳ ክፍያዎች መሰላት ያለባቸው በዚሁ የተጠሪ ወርሃዊ ደመወዝ የተባለው መጠን መሰረት ተደርጎ በሕጉ የተቀመጠው ስሌት ባገናዘበ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡

ይህንኑ መሰረት አድርገን እያንዳንዱን የክፍያ መጠን ስንመለከትም ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ያላቸው የአገልግሎት ዘመን አምስት አመት ከዘጠኝ ወርበመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 35(1)(ለ)) መሰረት ሊከፈላቸው የሚገባው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የሁለት ወር ደመወዝ ብር 6,461.40 (ስድስት ሺህ አራት መቶ ስልሳ አንድ ብር ከአርባ ሳንቲም) ሁኖ አግኝተናል፡፡የስራ ስንብት ክፍያን በተመለከተም በአዋጁ አንቀጽ 39(1(ለ)) እና 40(1)(2) ድንጋጌዎች መሰረት የሚመጣው ውጤት ብር 8,384.30 (ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ሰማንያ አራት ከሰላሳ ሳንቲም) እንጂ ብር 47,383.60 ያለመሆኑን ተረድተናል፡፡እንዲሁም የካሳ መጠኑ በአዋጁ አንቀጽ 43(4(ሀ)) መሰረት ሲሰላ የወረዳ ፍርድ ቤት የተጠሪን አማካይ የቀን ደመወዝ ብር 107.69 ያደረገው በመሆኑ ይኼው የቀን አማካይ ደመወዝ በመቶ ሰማንያ ሲባዛ የሚመጣው ውጤት ብር 19,384.20(አስራ ዘጠኝ ሺህ ሶስትመቶ ሰማንያ አራት ብር ከሃያ ሳንቲም) እንጂ ብር 25,849.60 ያለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ሌላው የስር ፍርድ ቤት በአዋጁ አንቀጽ 71 እና 68 መሰረት የሳምንት እረፍት ክፍያ በማለት ያስቀመጠው ብር 188,784.57(አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ አራት ብር ከሃምሳ ሳንቲም) የስሌቱ መነሻ እና የመብቱ አድማስ ለጉዳዩ አግባብነትና ጥንካሬ ያላቸውን ማስረጃዎችን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡በመሆኑም በዚህ ረገድ የተሰጠው

የውሳኔ ክፍል ሕግና ማስረጃን መሰረት ያደረገ ሁኖ አላገኘነውም፡፡የአምስት አመት በዓል ክፍያን በተመለከተ ግን አመልካች በስር ፍርድ ቤት በሌለበት የታየ በመሆኑና የይርጋ ክርክር ተነስቷል ለማለት ስለማይቻል እንዲሁም ፍርድ ቤቱ ደግሞ ይርጋውን በራሱ ሊያነሳ የሚችልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ የገንዘቡ መጠን ብር 16,357.00(አስራ ስድስት ሽህ ሶስት መቶ ሃምሳ ሰባት ብር) ተብሎ በስር ፍርድ ቤት መቀመጡን የማንቀበልበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>***ው ሳ ኔ***</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 163369 በ20/01/2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. በሂደቡ አቦቴ ወረዳ በመ/ቁጥር 03756 የካቲት 12 ቀን 2004 ዓ/ም በዋለው ችሎት የአመልካች የስንብት እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የፀና ሲሆን ውጤቱን በተመለከተ የሰጠው የውሳኔ ክፍል ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
3. የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው፣የአመልካች የመከራከር መብት የታለፈው ባግባቡ ነው፣የአመልካች እርምጃ ህገ ወጥ ነው በማለት መወሰኑም ተገቢ ነው በማለት ውጤቱን ግን አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 በተቀመጠው ስሌትና በማስረጃ በተረጋገጠው የደመወዝ መጠን በመሆኑ፡-
    - 3.1 የስራ ስንብት ክፍያ ብር 8,384.30፣
    - 3.2 የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ብር 6,461.40፣
    - 3.3 የካሳ ክፍያ ብር 19,384.20 እና
    - 3.4 የአምስት አመት የበዓል ቀናት ክፍያ ብር 16,357.00 ሁኖ በድምሩ ብር 50,586.90(ሃምሳ ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር ከዘጠና ሳንቲም) ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. የሳምንት ዕረፍት ቀናት ክፍያ ብር 188,784.57 በተመለከተ ግን በሕግ እና በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

የሰ/መ/ቁ. 101020

መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

መኰንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ዳዊት ገ/ማርያም - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ሣህለማርያም ደግፌ - የቀረበ የለም፡፡

**መዝገቡ ተመርምሯል፡፡**

**ፍ ር ድ**

የሰበር አቤቱታው የሶማሌ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.05-0-60/06 መጋቢት 19 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል ይታረምልን የሚል ሲሆን፤ይግባኝ ባይ በጠበቃቸው በኩል ግንቦት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ሦስት ገጽ ቅሬታ፡-

በሥር ፍርድ ቤት ከሳሽ የአሁኑ የሰበር አመልካች በተጠሪ ላይ በ17/10/2005 ዓ.ም በተፃፈ ክስ ከተጠሪ ጋር በ30/09/2004 ዓ.ም በተዋዋሉት የሥራ ቅጥር ውል መሠረት አመልካች ሲሰሩ የቆዩ ቢሆንም ተጠሪ ክፍያ ባለመፈፀማቸው እና አመልካችን ከሥራ አላግባብ በማሰናበታቸው ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ፣ ካሣ እና ሌሎች ጥቅማ ጥቅም ለአመልካች እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ለቀረበባቸው ክስ ከአመልካች ጋር የሥራ ቅጥር ውል የለንም ከማለት አልፈው በፍሬ ነገር ክርክሩ መልስ ባለመስጠታቸው ክሱ የቀረበለት የጅጅጋ ወረዳ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መካከል የሥራ ቅጥር ውል አለ ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ብር 42,000 /አርባ ሁለት ሺህ/ አመልካች ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በውሣኔው ቅር በመሰኘት ለፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ የጠየቁት ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ አከራክሮና ማስረጃ ሰምቶ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማፅናት ጥር 26 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበው ግራ ቀኙን ያከራከረ ቢሆንም በሥር ፍርድ ቤት ያልቀረበ የይርጋ ክርክር በማንሳት የአመልካች ክስ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/3 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ በመሻር መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የፈፀመ በመሆኑ ችሎቱ የሥር ሰበር ችሎት ስህተት በማረም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲያፀናልኝ እና ወጪና ኪሣራዬን ይተካልኝ ዘንድ በመወሰን ያስናብተኝ የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ አጣሪ ችሎቱ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ሰኔ 20 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት መርምሮ፡፡

"የሱማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በይርጋ ላይ ተመርኩዞ የሰጠው ዳኝነት አግባብነት ከፍ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 244/3 አንፃር ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ" ሲል አዟል።

ተጠሪ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ደርሷቸው በጠበቃቸው በኩል ሐምሌ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት መልስ፤ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት የቀረበባቸው ክስ ችግር የተሞላበት የነበር ቢሆንም በይግባኝ ደረጃ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ህገወጥነት ከመግለጽ አልፎ በቃል ክርክር ስለይርጋ በማንሳት ተከራክረዋል። ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ቢያጸናውም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት መወሰኑ የሚነቀፍ ባለመሆኑ ውሳኔው ስህተት የለበትም ተብሎ ችሎቱ ከበቂ ወጪና ኪሣራ ጋር ያሰናብተን የሚል ነው።

አመልካች ሀምሌ 25 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ ያቀረቡ ሲሆን የሰበር አቤቱታውን በሚያጠናክር መልክ የቀረበ ነው።

እኛም በሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ መሠረት በማድረግ የግራ ቀኙ ክርክር አግባብ ካላቸው ህጐች አንፃር መርምረናል ።

አመልካች ለሰበር አቤቱታቸው ምክንያት ያደረጉት በሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ ላይ ያቀረብኩት ክስ በይርጋ ቀሪ አይሆንም፣ በሥር ፍርድ ቤትም ያልቀረበ መቃወሚያ በሰበር ደረጃ ሊቀርብ አይገባም በሚል ሲሆን ተጠሪ መቃወሚያ በቃል ክርክር አቅርቤያለሁ ውሳኔው አግባብ ነው ባይ ናቸው።

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 244/3 መሠረት መቅረብ ከሚገባቸው መቃወሚያዎች ውስጥ ተጠቃለው ካልቀረቡ ያልቀረበው መቃወሚያ ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያሰናክል ከሆነ ባለጉዳዩ ራሱ ሆነ ብሎ ለማቅረብ ባለመፈለግ እንደተወው የሚቆጠር ለመሆኑ ተመልክቷል። ተጠሪ መቃወሚያ በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ አጠቃለው አለማቅረባቸው አሁን በሰበር ክርክር ያመኑ ሲሆን በሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ውሳኔም ስለመቅረቡም አልተመዘገበም። መቃወሚያ ካልቀረበም ተከሳሹ ሆነ ብሎ እንደተወው የሚቆጠር ከመሆኑም በላይ በሥር ፍርድ ቤት ያልተነሳ ክርክር ኋላ በማንሣት ለውሣኔ መሠረት ማድረግ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 329/1 የሚፃረር ነው።

የክልሉ ሰበር በሥር ፍርድ ቤት ያልቀረበውን መቃወሚያ በማንሳት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ሲል መወሰኑ የህግ ስህተት ሲሆን፤ አመልካች ሥራ ከተቀጠርኩ ጊዜ ጀምሮ ደመወዝ አልተከፈለኝም ውዝፍ ደመወዜ ይከፈለኝ በሚል ነው። አመልካች አስራ ሦስት ወር ለተጠሪ መስራታቸው ተረጋግጧል። አመልካች የጠየቁት የውዝፍ ደመወዝ ክፍያ የይርጋ መቃወም በተጠሪ ካልቀረበበት የማይከፈልበት ምክንያት የለም።

የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአሁኑ ተጠሪ የተነሳ የይርጋ ጥያቄ ሳይኖር የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ማድረጉ የሕግ ስህተት ስለሆነ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል።

## ው ሣ ኔ

1. በሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቁጥር 05/1/60/06 ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 348/1 መሠረት ተሽሯል።
2. የሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፈፉን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.19-05-06 ጥር 29 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ እና የጅጅጋ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.M/D/J746/05

ሐምሌ 04 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕግ ቁጥር 348/1 መሠረት ፀንቷል፡፡

3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራቸው ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ግ**

የሰ/መ/ቁ. 101396

ታህሳስ 21 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አዲስ አጠቃላይ ሆስፒታል ጠበቃ አብደላ ዓሊ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዶ/ር ምስራቅ ጥላሁን ጠበቃ አቶ ስመኘው አራጌ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 42275 ሐምሌ 9 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 135997 ግንቦት 18 ቀን 2006ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሥራ ውል ከሕግ ውጭ በአሠሪው ተቋርጣል በማለት ያቀረቡትን ጥያቄየሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በወር ብር 8000,/ስምንት ሺ. ብር/ እየተከፈለው በራዲያሎጅስት ሙያ ከጥር 1 ቀን 2000ዓ.ም ጀምሮ ሲያገለግሉ የቆዩ መሆኑን ገልፀው፣አሰሪው አመልካች ከሕግ አግባብ ውጭ ያቋረጠ ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡
   አመልካች ተከሣሽ ሆኖ ቀርቦ ከከሳሽ/ተጠሪ/ጋር የሥራ ቅጥር ውል ግንኙነት የለንም፡፡ከሳሽ ጋር ያለን ግንኙነት፣ከሳሽ በትርፍ ሠዓታቸው የሙያ ግልጋሎት እየሰጡ ክፍያ የሚያገኙበት የውል ግንኙነት ነው፡፡ተከሳሽ ይህንን በትርፍ ሠዓት የሚሰጥ የሙያ ግልጋሎት ውል አላቋረጠም፡፡ ከሳሽ የሙያ ፈቃዳቸውን ከጤና ጥበቃ ሚኒስትር ያላሳደሱ በመሆኑ ፈቃዳቸውን አድሰው ሲቀርቡ ሥራ የሚጀምሩ ፣መሆኑን ተገልፆላቸዋል ከሳሽ በድርጅታችን ውስጥ በቀን ሁለት ሰዓት የሚሠራ ሲሆን በጡረታ የተገለሉ በመሆኑ ከከሳሽ ጋር ቋሚ የሆነ የአሠሪና የሠራተኛ ግንኙነት የላቸውም በማለት ተከራክረዋል፡፡
2. የሥር ፍ/ቤት ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር ከመረመረ በኃላ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የከሳሽን ስም በመጥቀስ ጥቅምት 5 ቀን 2002 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤና ሌሎች የፅሑፍ ሰነዶች በማስረጃነት ያቀረቡለት መሆኑን ጠቅሶ በከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል የአሠሪና ሰራተኛ ግንኙነት አለ ከሳሽ የተከሳሽን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጭ ነው

በማለት ከሳሽ ለተከሳሽ የሥራ ስንብት ክፍያ የማስጠንቀቂያ ክፍያ የካሣ ክፍያና ክፍያ ለዘገየበት ክፍያና የፅሁፍ ክፍያ እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አፅንቶታል፡፡

3. አመልካች ግንቦት 28 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው ከአመልካች ዘንድ በቀን ሁለት ሠዓት ብቻ የሚያገለግሉ ራዲዮሎጂስት ናቸው፡፡ ይህ ፍሬ ጉዳይ በተጠሪ አልተካደም ይህም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀጽ 2(1) የሚሸፈንና በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የአሠራና እና ሠራተኛ ግንኙነት የሌለ መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የሥራ ውል አላግባብ ተቋርጧል በማለት የተለያዩ ክፍያዎች እንድከፍል መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ሐምሌ 17 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ መልስ እኔ በራሴ ኃላፊነት ሳይሆን በአመልካች ኃላፊነትና ቁጥጥር ሥር ሆኜ ሥራ የምሠራ ሠራተኛ ነኝ፡፡ ሬዲዮሎጅስት አገልግሎት የሚሰጥበት የሙያ ዘርፍ ነው፡፡ አመልካች ከሚገኘው ደመወዝ በየወሩ የሥራ ግብር 2,433.65(ሁለት ሺ አራት መቶ ሰላሣ ሶስት ብር ከስልሣ አምስት ሣንቲም ) እየቀነሰ ያስቀራል እንጅ በቀን ሁለት ሰዓት መስራት የአመልካችና የእኔን የስራ ውል ስምምነት የሚያሳይ እንጂ የአመልካች ሰራተኛ አለመሆኔን የሚያሳይ አይደለም፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ይጽናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካችና በተጠሪ መካከል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የሚሸፈን የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት አለ፣ አመልካች ከሕግ አግባብ ውጭ የሥራ ውሉን አቋርጧል በማለት የተለያዩ ክፍያዎች አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የሰጠው የሕግ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ "በሬድዮሎጂ" የሕክምና ሙያ የስልጠና በቂ ዕውቀትና ክህሎት ያለውና የደንብ ቁጥር 76/1994 አንቀፅ 20 በሚደነግገው መሠረት በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል በሙያው የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለሙያ መሆኑ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ ከጥር 1 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በአመልካች ድርጅት በቀን ለሁለት ሠዓት ያህል በመገኘት ከአመልካች ጋር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2641 በሚደነግገው መሠረት የሆስፒታል ውል ከተዋዋሉ የአመልካች ደንበኞች የሙያ አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ መሆኑና ተጠሪ ለሚሰጠው አገልግሎት አመልካች በየወሩ ብር 8000 /ስምንት ሺ ብር/ክፍያ ሲከፍለው የኖረ መሆኑ በግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡

6. አመልካች እና ተጠሪ ከላይ የተገለፀው አይነት የውል ግንኙነት የነበራቸው መሆኑ አያከራክርም፡፡ አከራካሪው ጉዳይ ይኸ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ፀንቶ የኖረው ግንኙነት የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ነው ወይስ የዕውቀትና የሙያ ሥራ ለማከራየት የተደረገ የውል ግንኙነት ነው? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ይህንን ጭብጥ ለመወሰን በአመልካች ተጠሪና የሕክምና አገልግሎት በሚሰጣቸው ህሙማን /የአመልካች ደንበኞች

መካከል የሚኖረውን ግንኙነት መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ከላይ እንደተገለፀው አመልካች በደንብ ቁጥር 76/94 አንቀጽ 20 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት በሙያው የሕክምና ግልጋሎት ለመስጠት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ያለው ባለሙያ ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2140 በሕክምና ባለሙያዎች ላይ የሚጥለው ግዴታና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2646(1) መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት የአመልካች ደንበኛ ከሚከፍለው ክፍያ ተጠሪ ምን ያህል ገንዘብ በወር ሊከፈለው እንደሚችል በውል በመስማማት፣ሙሉ በሙሉ በአመልካች ተቆጣጣሪነትና አሠሪነት እየተመደበ ሳይሆን ፣በቀን ለሁለት ሠዓቶች ሙያዊ አገልግሎትየሚሰጥ ባለሙያ መሆኑን የግራ ቀኙ ክርክርና በበታች ፍርድ ቤቶች የተረጋገጡት ፍሬ ጉዳዮች ያሳያሉ፡፡

7. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የተፈፃሚነት ወሰን በዝርዝር የሚደነግገው በአዋጅ ቁጥር 397/96 አንቀፅ 3 ፣ንዑስ አንቀፅ (1) አዋጅ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን በመርህ ደረጃ ደንግጓል፡፡ አዋጅ በዚህ ጠቅላላ መርህ የማይካተቱና የቅጥር ላይ የተመሰረቱ የሥራ ግንኙነቶች በአዋጅ ቁጥር 377 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 በልዩ ሁኔታና በዝርዝር ደንግጓል፡፡ የአዋጅ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ ‹‹ይህ አዋጅ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት በቅጥር ላይ በተመሠረቱ የሥራ ግንኙነቶች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም ›› የሚል ይዘት ያለው ሲሆን በአዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2 በዝርዝር ከተደነገጉ አዋጅ ተፈፃሚነት ከማይሆንባቸው ግንኙነቶች ውስጥ፤አንድ ተዋዋይ ወገን ዋጋ እየተከፈለው በራሱ የንግድ ሥራ ወይም በራሱ የሙያ ኃላፊነት የሚሠራ ስራ የሚያከናውን ሲሆን፣አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሌላቸው መሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2(1) ተደንግጓል፡፡

8. ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ ሙሉ በሙሉ በአመልካች መሪነትና ቁጥጥር ሣይሆን በአመልካች ድርጅት ውስጥ በቀን ለሁለት ሠዓት ያክል ከአመልካች ጋር የሆስፒታል ውል ለተዋዋሉ የአመልካች ደንበኞች የራድዮሎጅ የሙያ ግልጋሎት በራሱ የሙያ ኃላፊነት የሚሰጥ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ይህንን የሙያ ግልጋሎቱን ሌላ ቦታ የሚገኝ የህክምና ተቋም ወይም ከአመልካች ጋር ምንም አይነት የሆስፒታል ውል ግንኙነት ለሌላቸውና የአመልካች የህክምና ካርድ ላልያዙ ሰዎች እንዲሰጥናየሥራ ስምሪት መስጠትና አመልካችን ተቆጣጥሮ ማሠራት አይችልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 61 እና ተከታታይ ድንጋጌዎች መሠረት በቀን ሥምንት ሠዓት በሣምንት አርባ ሥምንት ሠዓት ከሥራ ቦታ እንዲገኝ ለማስገደድና ተቆጣጥሮ ማሰራት እንደማይችል የግራ ቀኙ ክርክርና ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ተረድተናል፡፡

9. የሥር ፍ/ቤት ተጠሪ በቀን ለሁለት ሠዓት ብቻ አገልግሎት መስጠቱ፤ ከአመልካች ጋር በአዋጅ ቁጥር 377/96 የሚሸፈን የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ከመመስረት አይገድበውም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ይህ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጉምና ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ከአንቀፅ 61 እስከ አንቀፅ 64 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘትና ውጤት ያገናዘበ ካለመሆኑም በላይ ፣በአዋጅ አንቀጽ 65 ልዩ ድንጋጌ ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 65 መሠረት በሥራ ውሉ ወይም በህብረት ስምምነት በሌላ አኳኃን ካልተወሰነ በስተቀር ፣የአዋጁ የስራ ሰዓት የሚመለከቱት ከአንቀጽ 61 እስከ አንቀጽ 64 የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የማይኖራቸው በንግድ መልዕክተኞች በንግድ ወኪሎች ላይ እንደሆነ በግልፅ ተደንግጎአል፡፡ ከዚህ አንፃር

የሥር ፍርድ ቤት የአዋጅ የሥራ ሠዓት ድንጋጌዎች ተጠሪ የአመልካች ቅጥር ሰራተኛ ነው ብሎ ለመወሰን ተፈፃሚነት እንደሌላቸው በመግለፅ የሰጠው ትርጓሜ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 65 ልዩ ድንጋጌ ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

10. ከላይ በዝርዝር የተገለፁት ምክንያቶች ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀፅ 2/1) መሠረት ከአመልካች ቁጥጥርና የሥራ አለመረዳት ሣይገደብ በራሱ የሙያ ኃላፊነት በቀን ለሁለት ሠዓት የራዲዮሎጅ የሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ እንጅ የአመልካች ሠራተኛ አይደለም፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የሚሰጠው የእውቀት ግልጋሎት እና ሥራ ውል በመሆኑ አመልካች በማናቸውም ጊዜ ውሉን ለማፍረስ የሚችል መሆኑን በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2638 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ ይህም በመሆኑ አመልካች አግባብነት ያለውንና ተፈፃነሚነት ያለውን የህግ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ አለኝ የሚለውን መብትና ጥቅም ከሚጠይቅ በስተቀር ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎች መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍለው የመጠየቅ መብት የለውም ፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከላይ በዝርዝር የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል ፡፡
2. ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 ንዑስ 2(1) መሠረት በራሱ የሙያ ኃላፊነት በቀን ለሁለት ሠዓት የሙያ አገልግሎት የሚሠጥ በመሆኑ የአመልካች ቅጥር ሠራተኛ ሣይሆን የዕውቀት ሥራና ግልጋሎት ለመስጠት የተዋዋለ ባለሙያ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሙያ (ዕውቀት)ሥራ ግልጋሎት ውል ያቋረጠው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2637 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. ይኽ ውሣኔ ተጠሪ የሙያ ግልጋሎት ውሉ በመቋረጡ ምክንያት አለኝ የሚለውን የመብት ጥያቄ ከማቅረብ የሚገድበው አይደለም ብለናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

የሰ/መ/ቁ.101913

የካቲት 17 ቀን 2007

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ መላከ ሙሉጌታ - ጠበቃ ሙሉጌታ ወንድምአገኘሁ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ አበበ አቡራ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 11115 ታህሳስ 21 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና ታህሳስ 28 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139436 ሰኔ 6 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠውየአፈፃፀም ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በአፈፃፀም ሂደት የቀዳሚነት መብት ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡

1. የፍርድ ባለዕዳ የሆነው ዲማክዶ መስማት የተሳናቸው የተባለ ድርጅት በመክሰስ አመልካችና ተጠሪ የፍርድ ባለመብት ሆነዋል፡፡ ተጠሪ የድርጅቱ የሥራ መሪ ስለነበረ በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት የፍትሐብሔር ክስ አቅርቦ የፍርድ ባለመብት ሆኗል፡፡ የፍርድ ባለዕዳውንም ንብረት አስቀድሞ በማስከበር በአፈፃፀም እንዲሸጥ አድርጓል፡፡ አመልካች በፍርድ ባለዕዳው ላይ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ክስ አቅርቦ የፍርድ ባለመብት ሆኗል፡፡ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 167 መሠረትየቀዳሚነት መብት ያለኝ ስለሆነ በቅድሚያ ለእኔ ሊከፈለኝ ይገባል የሚል ጥያቄ አንስቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካችም ሆነ ተጠሪ የፍርድ ባለዕዳው ሠራተኞች በመሆናቸው የቀዳሚነት መብት ያለው ንብረቱን ቀድሞ በአፈፃፀም የሸጠው /ተጠሪ/ ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ሁለቱም የፍርድ ባለመብቶች የፍርድ ባለዕዳ ሠራተኞች በመሆናቸው ከይግባኝ ባይ /አመልካች/ የቀዳሚነት መብት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡
2. አመልካች የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ተሸጦ ከተገኘው ገንዘብ በቀዳሚነት ሊፈፀምልኝ ሲገባ የበታች ፍርድ ቤቶች በሕግ የተሰጠኝን ልዩ የቀዳሚነት መብት አሳጥተውኛል በማለት የስር

አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ እኔም የፍርድ ባለዕዳው ተቀጣሪ ሠራተኛ በመሆኔ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን አፈፃፀም ትዕዛዝ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

3. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ የሕግ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
4. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ የፍርድ ባለዕዳውን ትምህርት ቤት ከስድስት ዓመት በላይ በወር 250 /ሁለት መቶ ሀምሳ የአሜሪካ ዶላር/ እየተከፈለው ያገለገለ መሆኑን፣ ተጠሪ የድርጅቱ የሥራ መሪ በመሆኑም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቂራ ምድብ 2ኛ ፍትሐ ብሔር ችሎት ክስ አቅርቦበመዝገብ ቁጥር 01892 ግንቦት 29 ቀን 2004 ዓ.ም የፍርድ ባለዕዳው 12,000 /አስራ ሁለት ሺ የአሜሪካን ዶላር/ እንዲከፍለው ውሣኔ የሰጡለት መሆኑን ተረድተናል፡፡ አመልካች በበኩሉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቂራ ምድብ የሥራ ክርክር ችሎት ክስአቅርቦ የፍርድ ባለዕዳው ብር 28,173.33 /ሃያ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሰባ ሦስት ብር ከሰላሳ ሦስት ሣንቲም / ለአመልካች እንዲከፍል በመዝገብ ቁጥር 09226 ሐምሌ 8 ቀን 2005 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡
5. ከላይ እንደተገለፀው በተጠሪና በፍርድ ባዕዳው መካከል የሥራ ቅጥር ውል መኖሩ ግልፅ ቢሆንም የፍርድ ባለዕዳው አመልካችን የቀጠረው በሥራ መሪነት በርዕሰ መምህርነት እንደሆነ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ በሌላ በኩል በአመልካችና በፍርድ ባለዕዳው መካከል የነበረው ግንኙነት በአዋጅ ቅጥር 377/1996 መሠረት የተመሠረተ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንድ የሥራ መሪ የሆነ ሰው በአሠሪው ድርጅት በፍትሐብሔር ሕጉ መሠረት ሊከፍለው የሚገባውን ክፍያ እንዲከፍለው ክስ አቅርቦ የፍርድ ባለመብት መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት አሠሪው የሚያስተዳድራቸው ሠራተኞች በፍርድ እንዲከፈላቸው ያስወሰኑት ክፍያ ከመክፈሉ በፊት ፍርድ ተፈፃሚ ሊሆንለት ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለው የህግ ጥያቄ መታየት ያለበት ነው፡፡
6. ይህም ጥያቄ በቅጥር ላይ ከተመሠረተ የሥራ ግንኙነት የሚመነጭ ማናቸውም የሠራተኛ ክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የዕዳ ጥያቄ ቅድሚያ ይኖረዋል በማለት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 167 ድንጋጌ አንፃር መታየት ያለበት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ሠራተኛ ማለት በአዋጅ አንቀጽ 4 በተመለከተው መሠረት ከአሠሪው ጋር በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ያለው እንደሆነ በአዋጅ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገ ሲሆን የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ በተገለፁት የሥራ መሪዎች ላይ ተፈሚነት የሌለው መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 167 የተደነገገው ልዩ የቀዳሚነት መብት የለውም፡፡ በመሆኑም ልዩ የቀዳሚነት መብት ያለው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ከፍርድ ባለዕዳው ጋር የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ያለው አመልካች እንጅ ተጠሪ አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ የቀዳሚነት መብት አለው በማለት የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀጽ 2፣ የአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 167 የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. በአፈፃፀም የቀዳሚነት መብት ያለው ተጠሪ ነው በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የውሣኔ ክፍል ተሸሯል፡፡
3. በአፈፃፀም የቀዳሚነት መብት ያለው አመልካች ነው በማለት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 167 መሠረት ወስነናል፡፡ የፍርድ ባለዕዳው ንብረት ተሸጦ ከተገኘው ገንዘብ፣ አመልካች በቅድሚያ ሊከፈለው ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ግ**

የሰ/መ/ቁ 103209

የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አትላስ 1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት - ጠበቃ መልካም ዓለማየሁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት መስታወት ስመኝ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የቀረበውን የግል የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስም፡- ከአመልካች ጋር በሕግ አግባብ ያደረጉት የስራ ቅጥር ውል ከሕግ ውጪ የተቋረጠባቸው መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መከላከያ መልስም፡- ተጠሪ ከስራ የተነሰናበቱት በአመልካች ንብረት ያላግባብ በመገልገላቸው ከስራ ባልደረባቸው ጋር በክፍል ውስጥ ግጭት በመፍጠራቸው ማስንጠቀቂያ እየተሰጣቸው ከስራ ገበታቸው ያለበቂ ምክንያት በመቅረታቸው እና ተጠሪ በሚያስተምሯቸው የክፍል ተማሪዎች ላይ የመግረፍና የማስደንገጥ ተግባር እየፈፀሙ በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የስነ ልቦና ችግር በማድረሳቸው ምክንያት ነው በማለት ስንብቱ ሕጋዊ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና የአመልካችን ምስክሮችን ከሰማ በኂላ ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ውጤቱን በተመለከተም የክፍያዎችን አይነትና መጠን በመዘርዘር በድምሩ ብር 14,988.33 (አስራ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከሰላሳ ሶስት ሳንቲም) አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከአስተማሪ ጋር በስራ ቦታ ተጣልተው በማስጠንቀቂያ የመታለፉቸውን ሁኔታ ለስንብት ምክንያት ሊሆን የሚችል

አይደለም በማለት ማለፉም ሆነ ተጠሪ ተማሪዎችን መደብደባቸውን በማስረጃ በአረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋቱ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት አይደለም በማለት ስንብቱን ሕገ ወጥ ሲል መወሰኑና ይህም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መጽናቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው በሰጡት መልስም ጥፋቶቹ ያለመረጋገጣቸውንና ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ሊያሰናብቱ የሚችሉበት አግባብ የሌለ መሆኑን ጠቅሰው በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡ይህም ችሎት ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤት የተከራከሩበትን መዝገብ እንዲቀርብ አድርጎ በአመልካች ምስክሮች የተነገረውንና የተረጋገጠውን የምስክርነት ቃል ይዘት ተመልክቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ ያገኘውን በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል ለማለት ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለው ጭብጥ ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት በዚህ ችሎት የሚከራከረው ተጠሪን ከስራ ባልደረባቸው በስራ ቦታ ጠብ ፈጥረው ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል በተማሪዎች ላይ ሕገ ወጥ የሆነ የድብደባ ተግባር ፈጽመዋል በማለት መሆኑን ነው፡፡ተጠሪ በበኩላቸው ጥፋቶቹን መፈፀሜ በማስረጃ አልተረጋገጠም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ መጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ስንብቱን ሕጋዊ ያደርጋሉ በማለት በመከላከያ መልሱ የጠቀሷቸውን ፍሬ ነገሮች ውድቅ ያደረጋቸው መሆኑን ሲሆን ለዚህም ያስቀመጣቸው ምክንያቶች ተጠሪ ከስራ ባልደረባቸው በስራ ቦታ ጠብ ፈጥረዋል ለተባለው አድራጎት በአመልካች በተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ከታለፉ በኂላ ይኼው በማስጠንቀቂያ የታለፈው ጥፋት ለስንብቱ ምክንያት ሊሆን እንደማይችል ተማሪዎችንመደብደባቸውም ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ጥፋት ስላለመሆኑ በሕጉ አልተመለከተም የሚሉ ናቸው፡፡

የአዋጅ ቁጥር 377/1996 የስራ ውል ስለሚቋረጥበት ምክንያቶችና ሁኔታዎችን በአንቀጽ 23 ከአንቀጽ 26 እስከ 30 ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ሕብረት ስምምነት መሰረት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ተደርጎ የተወሰደ ጉዳይም በአሰሪው ተነሳሽነት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል መሆኑ በአንቀጽ 27/1/ተ/ ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 24 እንደተመለከተው ውሉ በሕግ የሚቋረጥበት ምክንያቶች በአብዛኛው ከሁለቱም ወገን ቁጥጥር ውጭ ያሉ ሲሆን የስራ ውል በሁለቱም ፈቃደኝነት የሚገቡበት እንደመሆኑ ሁሉ ሁለቱም በፈቃደኝነት ከተስማሙ ውሉን ሊያቋርጡ የሚችሉበት ሁኔታም በአንቀጽ 25 ስር ሰፍሮ ይገኛል፡፡ስለዚህ ከላይ በተገለጹት ቁጥሮች በተደነገጉት ምክንያቶችና ሁኔታዎች የሚፈጸም የስራ ውል መቋረጥ ሕጋዊ የስራ ውል መቋረጥ ሲሆን ከነዚህ ውጭ የሚደረጉ የስራ ውል መቋረጥ በሕገ ወጥነት የሚፈረጁ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 42 ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህም ላይ በመመስረት የሚያስከተሉት ውጤቶች የሚለያዩ በመሆኑ በተናጥል የሚያስከትሉትን ውጤት ከሕጉ አግባብ በማየት ዳኝነትን መስጠት የሚጠይቅ መሆኑም ግልፅ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች ከተጠሪ ጋር በሕግ አግባብ የመሰረተው የስራ ውል መኖሩንና ስንብት ማድረጉን ሳይክድ አጥብቆ የሚከራከረው ስንብቱ ሕጋዊ ነው በሚል

ነው፡፡ለዚህም ተጠሪ በአመልካች ንብረት ያላግባብ መገልገላቸውን ከስራ ባልደረባቸው ጋር በክፍል ውስጥ ግጭት መፍጠራቸውን ተጠሪ ማስንጠቀቂያ እየተሰጣቸው ከስራ ገበታቸው ያለበቂ ምክንያት መቅረታቸውንና ተጠሪ በሚያስተምሯቸው የክፍል ተማሪዎች ላይ በመግረፍና በማስደንገጥ በተማሪዎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የስነ ልቦና ችግር ማድረሳቸውን የሚገልጹ ምክንያቶች ጠቅሶ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አስምቷል፡፡አመልካች ያቀረባቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ተጠሪ ከስራ ባልደረባቸው ጋር በስራ ቦታ ፈጠሩ ለተባለው ጸብ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው የታለፉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በስራ ቦታ ጠብ መፍጠር በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1(ረ) ድንጋጌ መሰረት እንደጥፋቱ ክብደት እየታየ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት ተግባር መሆኑ የተደነገገ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪ ለጥፋቱ በማስጠንቀቂያ የታለፉ መሆኑን በሚገባ ተረጋግጧል፡፡በመሆኑም በማስጠንቀቂያ የታለፉበት ጉዳይ የማስጠንቀቂያውን ተደጋጋሚነትን በመግለጽ ሌላ ጥፋት መፈጸሙ ሲረጋገጥ ለስንብት መሰረት ከሚሆን በስተቀር ራሱ በማስጠንቀቂያ ቀሪ የሆነ ጥፋቱ ግን ለስንብት መሰረት የሚደረግበት አግባብ የለም፡፡በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት የሚያገኝበትን አግባብ አላገኘንም፡፡

ሌላው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው ተጠሪ የሚያስተምሯቸውን ተማሪዎች መደብደባቸው በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጦ እያለ አድራጎቱ ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሰናብት አይደለም መባሉ ተገቢነት የለውም በሚል ነው፡፡በእርግጥ አንድ ተማሪ በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ ሕገ መንግስታዊ መብት ያለው መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 16 በግልጽ ያስቀመጠው ጉዳይ ሲሆን ይህን ህገ መንግስታዊ መብት መጣስ ሕገ ወጥ ድርጊት በመሆኑ በሕግ ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑም የሚታመን ነው፡፡በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1(ቀ)) ድንጋጌ ስር በተመለከተው አግባብም በአዋጁ አንቀጽ 14(2(ሀ)) ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲታይ ከስራ ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል ምክንያት ነው፡፡

በሌላ በኩል አንድ አስተማሪ የሚያስተምራቸውን ተማሪዎች በአግባቡ የመቆጣጠርና የመከተታል ህጋዊ ግዴታ ያለበት መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2124 እና 2125 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡በመሆኑም እነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች ተጣጥመው በአግባቡ ተግባራዊ መሆን ያለባቸው መሆኑ እሙን ነው፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ ተማሪዎችን ደብድበዋል የተባለው ከአስተማሪነታቸው ከሚጠበቀው ኃላፊነት በላይ ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ላይ የቀረቡትን የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን ይዘት በመመልከት ተገንዝበናል፡፡ ከሁሉም በላይ የአመልካች ሁለተኛ ምስክር በስር ፍርድ ቤት ቀርበው በሠጡት የምስክርነት ቃል ተማሪዎችን መግረፍ ክልክል መሆኑን ገልፀው እንደዚህ አይነት አድራጎት የፈፀመ አስተማሪ ለጥፋቱ ከምክር እስከ ማጠንቀቂያ የሚሰጥበት ሂደት መኖሩን መጨረሻ ላይም አስተማሪው ካልታረመ ጉዳዩን የበላይ አካል እንዲያውቀው ተደርጎ ተገቢው የሚወሰን መሆኑና ይህም በትምህርት ቤት መተዳደሪያ ደንብ ያለ መሆኑን ጭምር ዘርዝረው መግለጻቸው ሲታይ ትምህርት ቤቱ ሕገ ወጥ ተግባር ተጠያቂነትን የሚያስከትል መሆኑን ተገንዝቦ ይህንኑ ህገ ወጥ ተግባር ለመከላከልና ተፈጽሞ ሲገኝም አስተማሪው በዲሲፕሊን የሚጠይቅበትን ስርዓት ዘርግቶ እየሰራበት መሆኑ የሚያሳይ በመሆኑ አመልካች ተጠሪ ፈፀሙ የተባሉት አድራጎት ከአስተማሪነታቸው ኃላፊነት እና ግዴታ በላይ መሆኑንና ከትምህርት ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ውጪ መሆኑን ጭምር ያለማስረዳቱን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ መሆኑን የሚያስገነዝብ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ተማሪን መደብደብ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል አይደለም በማለት ያስቀመጠው ምክንያት ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 16 ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1(ቀ) እና 14(2(ሀ)

ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ውጪ ቢሆንም ተጠሪ ፈጸሙ የተባለው ድርጊት ከአስተማሪነት ኃላፊነት እና ግዴታቸው የወጣና ያልተገባ ስለመሆኑ ባለመረጋገጡ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሲል የደረሰበት ድምዳሜ ግን በውጤት ደረጃ ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አግኝተናል፡፡በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**_ው ሳ ኔ_**

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 36072 ሰኔ 19 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 140064 ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች እርምጃ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ ሲታይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ የሰበር ክርክር ወጪና ኪሳራን የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**_ት ዕ ዛ ዝ_**

**ሐምሌ 16 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡ይፃፍ፡፡**

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ይ

የሰ/መ/ቁ. 101040

መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካች፡- አቶ አየለ መንግሥቱ

ተጠሪ፡- የኢትዮጲያ እህል ንግድ ድርጅት

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሣሽ ሲሆን ተጠሪ ተከሣሽ ነበሩ አመልካች ባቀረበው ክስ ተጠሪ ያለምንም ምክንያት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ስላሰናበተኝ የአገልግሎት ካሣና ጉዳት ፣የስድስት ወር ደሞዝ፣ የአመት ዕረፍት ክፍያ እና የሥራ ልምድ ጨምሮ 51,778 ብር እንዲከፈለኝ በማለት ጠይቋል፡፡ ተጠሪም በሰጠው መልስ አመልካች የመጋዘን ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ 41.01 ኩንታል በቆሎ በጆንያ መሐከል ተደብቆ በፅዳት ሠራተኛ በኩል ተደረሶበት ይህንንም ያደረጉት ለራሳቸው ጥቅም ለማዋል በማሰብ ነው፣በድርጊቱም ተጠይቀው በቀን ሰራተኛ ሲጫን ተዛብቶ ይሆናል በማለት ተናግሯል፡፡ ይሁንና ይህ ተግባራቸው ያለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የሚያሰናብት ነው በማለት ተከራክሯል፡- ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም ተገኘ የተባለው በቆሎ ማን እንደደበቀው በግልፅ ባልተረጋገጠበት ያለማስጠንቀቂያ መሰናበቱ ህገ ወጥ ነው በመሆኑም በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 36፣37 ሣያሟላ እርምጃ መወሰዱ አግባብ ስላልሆነ በአዋጅ አንቀጽ 43(1) መሰረት ካሳና ደሞዝ ጋር ተያይዘው የሚመጡትን ክፍያዎች ጨምሮ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 40(1-3) ባጠቃላይ 49,998.50 ይከፈለው ሲል ወሰነ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የከፍተኛው ፍ/ቤት በፍ/ህ/ስ/ስ/ቁ.337 ሰርዞታል፡፡ የክልሉም የሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማየት ጠፋ የተባለው በቆሎ በመጋዘን ውስጥ ተደብቆ እና ቁልፉም ከተጠሪ ሌላ ማንም እንማይዘው ተረጋግጧል፣ በመሆኑም ተጠሪ የማጭበርበር ድርጊት የፈጸመ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(ሐ) መሰረት ያለማስጠንቀቂያ የሚያሰናብት ነው ሲል የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ ሽሮታል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታም ይህንን ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ በስር ፍ/ቤት ተጠሪ በሰጠው መልስ በመጋዘን ውስጥ የተደበቀ በቆሎ በመገኘቱ እንዳሰናበተኝ ቢገልጽም የደረሰ ጉዳት የለም በማለት አጣርቶ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያ እንዲከፈለኝ ቢወሰንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ፍ/ቤት የአመልካችን የመጋዘን ኃላፊ መሆኑን በመገልጽና ቁልፉም በእኔው እጅ እንደሚቀመጥ በመጥቀስ የማጭበርበር ድርጊት ተፈጸሟል

በማለት በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(ሐ) መሰረት ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የተወሰነልኝን የዓመት ዕረፍት ጭምር የሰረዘ ውሳኔን መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋዋል፡፡

በዚህ መሰረት ይህ ችሎትም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ስንብቱ ህጋዊ ነው ሲል ሲሽረው ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲከፈል የተወሰነውን የዓመት ዕረፍት ክፍያ ጭምር መሻሩን እንደ ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን አስቀርቦ መልስና የመልስ መልስ በማቀባበል እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ ለአመልካች የዓመት እረፍት ሊከፈል እንደሚገባ ሳይክድ በትርፍነት የተከፈላቸውን ገንዘብ እንዲከፍሉ (እንዲመልሱ) በማለት ሲከራከር አመልካች በበኩላቸው የሚፈለግባቸው ገንዘብ የሌለና አዲስ ክርክር ሊነሳ አይገባም ሲሉ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡

በመሆኑም የግራ ቀኙ ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው ህግ አኳያ አገናዝበን መርምረናል፡፡

በመሆኑም የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰውን ሲመስል እኛም ጉዳዩን እንዳየነው አመልካች በወረዳው ፍ/ቤት ከህግ ውጭ ተሰናበትኩ ሲል የዓመት ዕረፍትን ጨምሮ የተለያዩ ክፍያ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ግራ ቀኙን በማከራከር ስንብቱ ሕገ ወጥ በመሆኑ የስራ ከህግ ውጭ መሰናበት ውጤት የሆኑት ክፍያ እንዲከፈል ወስኗል፡፡በይግባኝ ሰሚውም ይኸው ውሳኔ ጸንቷል፡፡ በቀጣይነት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ውሳኔን በመሻር አመልካች የመጋዘን ኃላፊ ሆኖ በሚሰሩበት ወቅት ተደብቆየተገኘ በቆሎ መኖሩ የተረጋገጠ በመሆኑ ድርጊቱ በአዋጅ 377/96 አንቀፅ 27(1(ሐ) ስር የሚወድቅ የማጭበርበር ድርጊት በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ይህ ችሎትም የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ስንብቱ ህጋዊ ነው ሲል የደረሰበትን ድምዳሜ የሚቀበለው ሲሆን በስር ፍርድ ቤት የተጠየቀው የዓመት ዕረፍት ክፍያ ጥያቄን አስመልክቶ ሳይለይ በጠቅላላ መሻሩ ሊታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመሠረቱ የዓመት ዕረፍት ክፍያ ሠራተኛ በሥራ ዘመኑ ሊጠበቁለት ከሚገቡ መብቶች መሀከል አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ክፍያ የሠራተኛው ውል በህግ ወይም ከህግ ውጭ እንዲሁም ሠራተኛው በራሱ ጊዜ ሲያቋርጥየዓመት ዕረፍትክፍያ ሊታለፍበት (ሊነፈግ) የሚችል አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ጥያቄው ከሚቀጥለው ሁለት አመት በላይ ሊራዘም እንደማይችል በአዋጅ አንቀጽ 79(5) ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህም የሆነው ሰራተኛው ወደ ገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጠው ከሚጠይቅ ዕረፍቱን በአይነት ወስዶ በተሟላና አካሉን አሳርፎ በአዲስ ሀይል ሥራውን እንዲያከናውን ታስቦ እንደሚሆን ብዙ አያከራክርም፡፡ የህጉ አንቀጽ 76(1) ይህንኑ ሲያጠናክር በዚህ ረገድ ሰራተኛው የዕረፍት ጊዜውን ለመተው ሊስማማ የማይችል መሆኑን ክልከላ ያስቀመጠው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣም የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የአመት እረፍት ክፍያ ውድቅ ያደረገበት ምክንያት ግልፅነት የጐደለው ሲሆንአመልካችም ውሳኔው ቢሻርም በሥር ፍ/ቤትየታመነው የአመት እረፍት ክፍያ የ85 ቀን (5468.5) ብር ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ይከራከራሉ፡፡ ተጠሪም በበኩሉ ይህ ክፍያ ለአመልካች ሊከፈል እንደሚገባው በማመን መጠኑን አስመልክቶ የ48 ቀን ብቻ ነው ሊከፍለው የሚገባው ሲል መነሻው ግብር ተቀንሶ ሊከፍል ይገባዋል በማለት ይከራከራል፡፡ እንግዲህ የቀኑን ብዛት አስመልክቶ የተነሳው ክርክር በሥር ፍ/ቤት ጉልቶ መከራከሪያ ሆኖ ያልመጣ በመሆኑ አልተቀበልነውም ሌላው ተጠሪ የሚያነሣው ክርክር የዓመት ዕረፍት ክፍያው ግብር ተቀንሶ ሊከፈል ይገባል የሚል ነው፡፡ በዚሁ ውሳኔ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው የዓመት ዕረፍትን ለሰራተኛው መክፈል የማስፈለጉ አላማ ግልፅ ነው

በመርህ ደረጃ በዓይነት የእረፍት ቀናትን ወስዶ እንዲወጣ ነው፡፡ በዚህን ጊዜ በህግ የተፈቀደለትን የዓመት ዕረፍቱን ወስዶ ከመውጣት በቀር ሌላ ሊያሚላ የሚጠበቅበት ነገር የለም፡፡ በሌላበኩል በተለያዩ በህጉ በተቀመጡት ምክንያቶች የዓመት ዕረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ ሲከፈል እንደሌሎች ከአሰሪና ሰራተኛ ህጉ የሚመነጩ መብቶች (ክፍያ) የዓመት ዕረፍት ክፍያም የገቢ ግብር ከተቀነሰ በኋላ የሚከፈል ክፍያ መሆኑን ይህ ችሎት የሚቀበለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የገቢ ግብር የአዋጅ ቁ.286/94 እና ደንብ ቁ.78/94 አንቀፅ 3 የዓመት እረፍትን ያለማግለሉ ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች እንዲከፈላቸው የጠየቁትን የገንዘብ መጠን በሥር ውሳኔ በግልፅ ተጠቅሶ ባይቀመጥም ተጠሪ ለመጠንና ስሌት ክርክር ውጭ አመልካች የአመት ዕረፍት ክፍያ የላቸውም የሚል ክርክር አላቀረቡም በመሆኑም በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 77፣78 እና 79 በተደነገጉት መሠረት አመልካች ያቀረቡትን የገንዘብ መጠን በሌላ ማስረጃ አላስተባበለም፡፡

በአጠቃላይ የክልሉ ሠበር ሰሚ ችሎት የሥር ውሳኔን ሲሽር የአመልካችን የአመት ዕረፍት ክፍያ ጭምር መሻሩ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአርሲ ነገሌ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 20962 በቀን 20/12/05 የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 18732 በቀን 27/01/06 እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 74447 በቀን 01/07/06 በማሻሻል ፀንቷል፡፡
2. አመልካች የጠየቁትን የዓመት ዕረፍት ክፍያ በህጉ መሰረት አስፈላጊው የገቢ ግብር ተቀንሶ ይከፈላቸው ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ለአመልካች በትርፍነት ከወሰዱት ገንዘብ ሊመልሱልኝ ይገባል የሚለውን በህግ አግባብ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግድም፡፡
4. የወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ውሳኔ አግኝቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

እ/ኢ

የሰ/መ/ቁ. 101890

ጥቅምት 24 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ- ጠበቃ አውላቸው ደሣለኝ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ት ፍጹም ኃይሉ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ የቀረበው ክርክር የሥራ ውሉ ማቋረጡን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ አመልካች ከግንቦት 30 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ በዕቃ ግምጃ ቤት ተቆጣጣሪነት በቋሚ ደመወዝ ብር 2,639 የቀጠራቸው መሆኑና ያለማስጠንቀቂያ በ12/11/2005 የተፃፈ የቅጥር ውል ማቋረጫ ደብዳቤ በ15/11/2005 እንዲሰጣቸው በሕገወጥ መንገድ ከሥራ ስለአሰናበታቸው የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ እንዲወሰን የሚል ነበር፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ በትብብር በሚሰራ ድርጅት ተቀጥረው ሲሰሩ ስለነበር የተቀጠሩት በቋሚነት ነው በማለት ያቀረቡት ክርክር ከቀረበው ማስረጃ አንፃር ተገቢነት የለውም በማለት የታለፈ ሲሆን በግራ ቀኙ የነበረው የሥራ ውል ግንኙነት በ29/09/2005 ዓ.ም በተፃፈው ደብዳቤ ከግንቦት 7 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ለ45 ቀናት የሙከራ ቅጥር ተቀጥረው ሲሰሩ እንደነበር መሠረት በማድረግ ታልፏል፡፡

አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ተጠሪ ሊመደቡበት ላቀደው የዕቃ ግምጃ ቤት የስራ መደብ ተስማሚ መሆናቸውን ለመመዘን ለ45 ቀናት የሙከራ ግዜ ተቀጥረው ለታቀደው ሥራ ተስማሚ ያለመሆናቸውን በማረጋገጥ ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ የሥራ ውል ማቋረጡን ገልጿል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ በማገናዘብ በሰጠው ውሣኔ ተጠሪ በሰጡት የምስክርነት ቃል የሥራ ውል ማቋረጫ ደብዳቤ የተሰጣቸው እ.ኤ.አ ጁላይ 22/2013 ወይም ወደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ሲመለስ ሐምሌ 15/11/2005 መሆኑን ፤ የአመልካች ምስክርም ደብዳቤው የተሰጣቸው ጁላይ 19 ቀን 2013 ወይም ሐምሌ 15 ቀን 2005 ዓ.ም ነው በማለታቸው የተጠሪ የሥራ ውል ማቋረጫ ደብዳቤ የተሰጣቸው በ46ኛው ቀን ሐምሌ 15/11/2005 ዓ.ም በመሆኑ ስንብቱ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ለተጠሪ ያልከፈላቸው የ22 ቀናት ቀሪ ደመወዝ እንዲሁም የካሣ ክፍያ እንዲከፍላቸው የሥራ ልምድ ማስረጃም እንዲሰጣቸውበማለት ወስኗል፡፡ በይግባኝ ሥልጣኑየተመለከተው ከፍተኛ ፍ/ቤትም የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞታል፡፡

አመልካችም በሥር ፍ/ቤቶች ፍርድ ላይ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን የቅሬታ ነጥቡም ሲጠቃለል፡- በአመልካች እና ተጠሪ የነበረው የሥራ ግንኙነት ሕጉ በሚፈቅደው አግባብ ጁላይ 19 ቀን 2013 እ.ኤ.አ በተፃፈ ደብዳቤ መቋረጡ፤ ይህ ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር ሲመለስ ሐምሌ 12 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን እየታወቀ የውል መቋረጫ ደብዳቤ በ43ኛው ቀን

ተድፎ ሳለ ስንብቱ በ46ኛው ቀን የተደረገ በመሆኑ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ በሥር ፍርድ ቤት መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስ ከአሁን በፊት ለ5ወር ከ6 ቀን በማቴሪያል ኢንቨንተሪ ኮንትሮል ሥራ በአመልካች መስሪያ ቤት መሥራታቸው እየታወቀ ድጋሚ በዚያው ሥራ በሙከራ የቅጥር ውል መሥራታቸው ሕጋዊ አለመሆኑን ፤የሥር ፍ/ቤት ማስረጃዎች በመመዘን ውሣኔ መስጠቱ ፤የተጠሪ ምስክሮች የሥራ ውል ማቋረጫ ደብዳቤ እ.ኤ.አ ጁላይ 22 ቀን 2013 እንደተሰጣቸው ማስረዳታቸውአመልካች በሕግ የተቀመጠውን 45 ቀን አሳንሶ በ43ኛው ቀን የስንብት ደብዳቤ መስጠት እንደማይችል፤ ደብዳቤውም ከሥራ ሰዓት ውጭ የተሰጣቸው መሆኑንበመግለጽ የሥር ፍ/ቤት እንዲፀና አመልክቷል፡፡ አመልካችም ተጠሪ ላቀረቡት መልስ የመልስ መልስ በማቅረብ አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት እንደተቻለው በአመልካች እና ተጠሪ በሙከራ ጊዜ ላይ የተመሰረቱ የሥራ ቅጥር ውል መፈፀሙን ነው፡፡ ተጠሪ ከድርጅቱ ጋር ግንኙነት ባለው ሌላ ድርጅት በዚህ የሥራ መደብ ላይ ሲሰሩ እንደነበር በድጋሚ በተመሳሳይ የሥራ መደብ ለሙከራ መቀጠራቸው ሕጋዊ አለመሆኑን በመጥቀስ ቢከራከሩም የሥር ፍርድ ቤት ለሙከራ የተቀጠሩበት ደብዳቤ በማስረጃነት በመውሰድ ክርክራቸው አግባብነት የሌለው መሆኑን በውሣኔው አስፍሯል፡፡ ተጠሪ ይህንን ውሣኔ በመቃወም ያቀረቡት ይግባኝ ይሁን መስቀለኛ አቤቱታ የለም፡፡ በዚህ ረገድ በሰበር አቤቱታቸው በሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውድቅ የተደረገው ክርክር በሰበር ደረጃ ማቅረባቸው ሥነ-ስርዓታዊ አካሄድ የተከተለ አይደለም፡፡

አንድ ሠራተኛ ሊመደብበት ለታቀደው ቦታ ተስማሚ መሆኑና አለመሆኑን ለመመዘን ለሙከራ ጊዜ ሊቀጠር እንደሚችል፤ ይህ የግራ ቀኙ ስምምነትም በጽሑፍ መደረግ እንዳለበት፤ የሙከራ ጊዜውም ከ45 ተከታታይ ቀናት መብለጥ እንደሌለበት ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(1) ፣(2) እና (3) አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ አመልካች ተጠሪን ለሙከራ ጊዜ መቅጠሩ በሥር ፍ/ቤት የታመነበት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪን በግዜ ገደቡ ውስጥ ማሰናበቱን ሲከራከር ተጠሪ ደግሞ በ46ኛው ቀን የተሰናበቱ መሆናቸው በመግለፅ ስንብቱ ህገ ወጥ እንዲባልላቸው አመልክተዋል፡፡ በስር ፍ/ቤት የአመልካች ምስክሮች ስንብቱ እ.ኤ.አ. ጁላይ 19 ቀን 2013 መሆኑን ይህ ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር ሲመለስ ሐምሌ 15 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን በሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ሰፍሯል፡፡ ተጠሪ በሰጡት የምስክርነት ቃል የስንብት ደብዳቤው እ.ኤ.አ. ጁላይ 22 ቀን 2013 መሆኑ፤የጊዜ ስሌቱ ሲሰራ ከተቀጠሩበት ጊዜ ጀምሮ በ46ኛው ቀን መሆኑን ገልጿል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቱ የአመልካች ድርጊት ሕገወጥ ነው ለማለት እንደመነሻ የወሰደው ተጠሪን በ46ኛው ቀን ከሥራ አሰናብቷል በሚል ነው፡፡

አመልካች ተጠሪን ያሰናበታቸው በ43ኛ ቀን ነው?ወይስ በ46ኛው ቀን?በ46ኛው ቀን ሲሰናበቱ ሕጋዊ ውጤቱስ የተለየ ሊሆን ይችላል? የሚለው መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤት በአመልካች ተሰጠ የተባለው ደብዳቤ እ.ኤ.አ አቆጣጠር ጁላይ 19 ቀን 2013 ዓ.ም የተጻፈ መሆኑ ወደ ኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር ሲመለስ ደግሞ ሐምሌ 15 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑን በውሣኔው አስፍሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እ.ኤ.አ. ጁላይ 19 ቀን 2013 ወደ ኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር ሲመለስ ሐምሌ 15 ቀን 2005 ዓ.ም በማለት በውሣኔ የተጠቀሰው ተቀባይነት /conventional/ ካልሆነው የጊዜ አቆጣጠር ቀመር አኳያ ሲታይ አግባብነት ያለው አይደለም፡፡ ከላይ የተገለፀው ጁላይ 19 ቀን 2013 ወደ ኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር ሲመለስ ሐምሌ 12 ቀን

2005 ዓ.ም መሆኑን ተቀባይነት ካለው የጊዜ አቆጣጠር /ካላንደር/ አንፃር በማዛመድ በቀላሉ ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ጁላይ 19 ቀን 2013 እ.ኤ.አ ወደ ኢትዮጵያ የጊዜ አቆጣጠር ሲመለስ ሐምሌ 15 ቀን 2005 ዓ.ም ነው፡፡ በማለት ማስፈሩ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ አመልካች ተጠሪን ሐምሌ 12 ቀን 2005 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የሙከራ ግዜ ቅጥር ውል እንዲቋረጥ የተደረገ ከሆነ በ45 ቀን ጊዜ ገደብ ውስጥ የተፃፈ ደብዳቤ መሆኑ መረዳት ይቻላል ፡፡ አመልካች ተጠሪ ሊመደቡበት ለታቀደው ቦታ ተስማሚ መሆኑን አለመሆናቸው በ45 ቀን ውስጥ ውሣኔ ማስተላለፍ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር የሚቃረን ውሣኔ አይደለም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የአመልካች ድርጊት ሕገወጥ ነው በማለት ለመወሰን እንደ መነሻ የወሰደው ስንብቱ በ46ኛው ቀን ተከናውኗል በሚል ነው፡፡አንድ አሠሪ የሙከራ ጊዜ ውል ያለአግባብ በማሳጠር ይሁን ከሚገባው በላይ ጊዜው በማራዘም የሠራተኛው የተረጋጋ የሥራ ዋስትና እንዳይኖር ማድረግ እንደሌለበት ከአጠቃላይ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅቁ. 377/96 ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይሁንና አሠሪው በ45ኛው ቀን መጨረሻ ይሁን በ46ኛው ቀን መጀመሪያ ሠራተኛው ለተመደበበት የሥራ ቦታ ተስማሚ አይደለም በማለት ከወሰነ የፈጠነ ወይም በጣም የዘገየ ውሣኔ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የሙከራ ግዜው በ45ኛው ቀን መጨረሻ የሚጠናቀቅ ከሆነ በ46ኛው የመጀመሪያ ቀን የስንበት ደብዳቤ መፃፉ የሠራተኛው የሥራ ዋስትና አደጋ ውስጥ አስገብቷል ለማለት የሚያስችል አሳማኝ ምክንያት የለውም፡፡ በሥር ፍ/ቤት ተረጋግጧል የተባለው ፍሬ ነገር ተወስዶ ደብዳቤው በ46ኛው ቀን ነው የተፃፈው ቢባል እንኳ የአሠሪው የማሰናበት መብትና ሥልጣን ዘግይቶ ተግባራዊ የተደረገ ነው ሊባል አይችልም፡፡ የሙከራ ጊዜ ውል ለ 45 ተከታታይ ቀናት የሚቀጥል ከሆነ ግለሰቡ በመጨረሻው ቀን በመገምገም ለታቀደው ቦታ ተስማሚ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ውሣኔ ለማስተላለፍ የመጨረሻ ቀን የሥራ አፈፃፀም ውጤት ጭምር ታሳቢ መደረግ ያለበት በመሆኑ በ46ኛው ቀን የስንብት ደብዳቤ መፃፉ የሕጉን ይዘትና መንፈስ የሚቃረን አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለውን ጉዳይ በአግባቡ ሳያገናዝቡ የሙከራ ጊዜ ከ45 ቀናት መብለጥ የለበትም የሚለውን የሕጉ ይዘት ከአጠቃላይ የሕጉ ዓላማና ግብ ሳያገናዝቡ መወሰናቸው በአግባቡ አይደለም ብለናል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካች ድርጊት ሕገወጥ ነው በማለት መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ አተረጓጎም ስህተት ፈጽመዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## *ት ዕ ዛ ዝ*

1. የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ.85529 በ18/07/2006 ዓ.ም እንዲሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ. 139947 በ19/07/2006 የሰጡት ፍርድ እና ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪ ያለማስጠንቀቂያ ማሰናበቱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ለዚህ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ብ/ግ                                        የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 101795

መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካች፡-የኢትዮጵያ ምርጥ ዘር ድርጅት ነገረ ፈጅ ፈለቀ እንግዳሸት- ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ አድማሱ አበበ ከጠበቃ ጥላሁን ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ነው በሚል የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ በ08/02/2006 ዓ.ም አዘጋጅተው ያቀረቡት ክስ ይዘትም ባጭሩ፡-ተከሳሽ ድርጅት ለሕዝብ ግንኙነት ደጋፊ የስራ ሂደት ላወጣው ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ የድርጅቱ ደንብ፣መመሪያ እና የህብረት ስምምነት በሚፈቅደው መሰረት ከሳሽ መስፈርቶቹን አሟልተው ለውድድር መመዝገባቸውን፣ይሁን እንጂ ድርጅቱ በማስታወቂያ የወጣውን የመወዳደሪያ መስፈርት በመተው መስፈርቱን የማያሟሉትን አቶ አወቀ በለጠ የተባሉትን የድርጅቱ ባልደረባ ለውድድር አቅርቦ እንዲያልፉ ማድረጉን፣ከሳሽ ይህንን በመቃወም ለድርጅቱ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት አግኝቶ መስፈርቱን የማያሟሉት አቶ አወቀ በለጠ ለውድድር እንዲቀርቡም ሆነ እንዲያልፉ የተደረገው አላግባብ መሆኑን ገልጾ ኮሚቴው በ13/01/2006 ዓ.ም. የተጻፈ የውሳኔ ሀሳብ ያቀረበ ቢሆንም ድርጅቱ ለውድድር በቀረበው የስራ መደብ ላይ ከሳሽን ለመመደብ ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን በዝርዝር የሚገልጽ ሆኖ መስፈርቱን ላላሟሉ ሰራተኛ የተሰጠው ምደባ ተሰርዞ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት የስራ መደቡ መስፈርቶቹን ላሟሉት ለከሳሽ እንዲሰጥ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተከሳሽ ድርጅት በበኩሉ በ25/02/2006 ዓ.ም በሰጠው መልስ የመቃወሚያ እና የፍሬ ነገር የክርክር ነጥቦችን አቅርቧል፡፡የቀረቡት ሁለት የመቃወሚያ ነጥቦችም ክሱ የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት በመሆኑ እና ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያው የወጣበት የስራ መደብም የሚመለከተው የስራ መሪን እንጂ ሰራተኛን ባለመሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለውም የሚሉ ሲሆኑ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ የተሰጠው መልስ ይዘት ደግሞ ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂው የወጣው በስራ መሪዎች ምደባ መመሪያ መሰረት መሆኑን፣ጉዳዩም

የሚመለከተው ምደባን እንጂ የደረጃ ዕድገትን አለመሆኑን፣ የከሳሽ የምደባ ጥያቄ ተቀባይነት ያጣው የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የመንግስትን ፖሊሲ እና መመሪያ በማስፈጸም ረገድ በከሳሽ ላይ እምነት ባለመጣላቸው መሆኑንየሚገልጽ ነው፡፡ቦርዱም በቅድሚያ የመቃወሚያ ነጥቦቹን ከመረመረ በኃላ ከሳሽ ክሱን ያቀረቡት የዕድገት አሰጣጥ ስርዓት ተጥሶብኛል በማለት በመሆኑ እና የሰራተኛ አቀጣጠር እና ዕድገት አሰጣጥ ስርዓትን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮችን የማየት ስልጣን ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 142(1)(ሠ) ድንጋጌ መሰረት የተሰጠው ለቦርድ በመሆኑ ክሱ የግል የስራ ክርክርን የሚመለከት መሆኑን ጠቅሶ ተከሳሽ ያቀረበው የስልጣን መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን እና ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያው የወጣበት የስራ መደብየሚመለከተው የስራ መሪን እንጂ ሰራተኛን ባለመሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለውም በሚል የቀረበውን መቃወሚያ በተመለከተም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(2)(ሐ) ድንጋጌ መሰረት ለስራ መሪ የተሰጠው ትርጉም ቀድሞውንም ቢሆን የስራ መሪ ሆኖ በአንቀጹ ላይ የተዘረዘሩትን የስራ መሪ ተግባሮች ሲያከናውን የነበረን ሰው የሚመለከት እንጂ ሰራተኛ ሆኖ ለስራ መሪ በወጣ ክፍት የስራ መደብ ላይ ለውድድር የቀረበን እንደ ከሳሽ ዓይነት ሰውን የሚያጠቃልል ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው መቃወሚያም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ መቃወሚያዎቹን በ11/03/2006 ዓ.ም በብይን ካለፋቸው በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ጉዳዩን ለክፍት የስራ ቦታው በወጣው ማስታወቂያ ላይ ከተዘረዘሩት መስፈርቶች እና ከስራ መሪዎች ምደባ መመሪያ አንጻር መመርመሩን ገልጾ በውድድሩ 84.50% ውጤት አግኝተዋል የተባሉት አቶአወቀ በለጠ ወደ ውድድሩ የገቡት ተገቢ መመዘኛዎችን ሳያሟሉ በመሆኑ ለእርሳቸው የተሰጠው ምደባ ውድቅ ተደርጎ የስራ መደቡ እና የስራ መደቡ የሚያስገኘው ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም ተገቢ የመወዳደሪያ መስፈርቶቹን አሟልተው ወደ ውድድሩ ለገቡት እና በውድድሩ 71% ውጤት ላገኙት ለከሳሽ ሊሰጥ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ  በዚህ ጉዳይ ለስራ መሪ የስራ መደብ ብቁ ሆኜ ሳለ ቦታው ለሶስተኛ ወገን የተሰጠው አላግባብ ነው በማለት ተጠሪ ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ያቀረቡትን ክስ ቦርዱ የማየት ስልጣን የለውም በማለት አመልካች ያቀረበው መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት የማጣቱን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ላወጣው ክፍት የስራ መደብ ለውድደር በቀረቡበት ጊዜ ተጠሪ ይሰሩ የነበረው በሰራተኛነት መሆኑ፣ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያው የወጣው ለስራ መሪ የስራ መደብ መሆኑ፣በማስታወቂያው መሰረት በሰራተኞች እና በስራ መሪዎች መካከል ልዩነት ሳይደረግ ለውድድር የተጋበዙት በሁለቱም የስራ ዘርፍ የሚገኙ የድርጅቱ የሰው ኃይል አባላት መሆናቸው፣በመወዳደሪያ መስፈርቶቹ መሰረት ውድድሩ እና አሸናፊውን ተወዳዳሪ የመምረጡ ስርዓት የሚከናወነው በድርጅቱ የስራ መሪዎች ምደባ መመሪያ መሰረት መሆኑ እና በዚህ ረገድ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ም" ሆነ የድርጅቱ የህብረት ስምምነት ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መሆኑ በግራ ቀኙ ክርክር ያልቀረበበት እና ቦርዱም ቢሆን

የተቀበለው ጉዳይ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው ቦርዱ በስረ ነገር ስልጣን ረገድ ከአመልካች የቀረበለትን የመቃወሚያ ነጥብ ውድቅ ያደረገው ክሱ የቀረበው የዕድገት አሰጣጥ ስርዓት ተጥሶብኛል በማለት መሆኑን፣የሰራተኛ አቀጣጠር እና ዕድገት አሰጣጥ ስርዓትን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮችን የማየት ስልጣን ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 142(1)(ሠ) ድንጋጌ መሰረት የተሰጠው ለቦርድ መሆኑን እና የስራ መሪ የስራ መደብም ተጠሪው የሚወዳደሩበት እንጂ ይዘው የሚገኙት የስራ መደብ አለመሆኑን በመግለጽ ነው፡፡

እንደሚታወቀው አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሰረት አድርገው የሚነሱ የስራ ክርክር ጉዳዮች የሚታዩት እንደ ጉዳዩ ዓይነት በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ሲሆን በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሚታዩት በአዋጁ አንቀጽ 138(1) ስር ከፊደል (ሀ) እስከ (ረ) የተዘረዘሩ የግል የስራ ክርክር ጉዳዮች መሆናቸውን እና በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቋሚ ቦርድ የሚታዩት ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 142(1) ከፊደል (ለ) እስከ (ሸ) የተዘረዘሩ የወል የስራ ክርክር ጉዳዮች መሆናቸውን ከላይ የተጠቀሱት እንዲሁም የአዋጁ አንቀጽ 142(3) እና 147(1)(ሀ) እና (ለ) ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡ተጠሪ ክሳቸውን ለቦርዱ ያቀረቡትም የዕድገት አሰጣጥ ስርዓት ተጥሶብኛል በማለት ነው፡፡የዚህ ዓይነቱ የስራ ክርክር ደግሞ በባህርይው የወል እንጂ የግል የስራ ክርክር አይደለም፡፡በዚህም ሁኔታ ከላይ የተጠቀሱትን የአዋጁን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ ክሱ የቀረበው የዕድገት አሰጣጥ ስርዓት ተጥሶብኛል በማለት መሆኑን እና የሰራተኛ አቀጣጠር እና ዕድገት አሰጣጥ ስርዓትን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮችን የማየት ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 142(1)(ሠ) ድንጋጌ መሰረት የተሰጠው ለቦርድ መሆኑን በመግለጽ ቦርዱ የያዘው አቋም በራሱ የሚነቀፍ ባይሆንም ከጉዳዩ ልዩ ባህርይ አንጻር ለክርክር የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የሚሸፈን መሆን አለመሆኑ እና በዚህም ምክንያት በቦርዱ ስልጣን ስር የሚወድቅ መሆን አለመሆኑ በአግባቡ መጤን የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የተፈፃሚነት ወሰን በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ በተመሰረተ የስራ ግንኙነት ጉዳዮች የተገደበ ስለመሆኑ እና በተለይም ከስራ መሪ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 3(1) እና (2)(ሐ) ስር የተመለከተ ሲሆን ተጠሪ የስራ መሪ ባይሆኑም ለውድድር የቀረቡት በስራ መሪ በሚሸፈን የስራ መደብ ላይ ለመመደብ ነው፡፡ዋነኛ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የቀረበውም በአዋጁ መሰረት የተጠሪው ሰራተኛ የመሆን አለመሆን ጉዳይ ሳይሆን በስራ መሪ ለሚሸፈን የስራ መደብ የሚደረግ ውድድር የሚመራበት ስርዓት ነው፡፡በመወዳደሪያ መስፈርቶቹ መሰረት ውድድሩ እና አሸናፊውን ተወዳዳሪ የመምረጡ ስርዓት የሚከናወነው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ እና በህብረት ስምምነቱ መሰረት ሳይሆን በድርጅቱ የስራ መሪዎች ምደባ መመሪያ መሰረት መሆኑ አላከራከረም፡፡የስራ መሪዎችን የምደባ መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚነሱ ክርክሮችን የማየት ስልጣን ደግሞ በአዋጁ መሰረት ለፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎቶችም ሆነ ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አልተሰጠም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 142(1)(ሠ) ድንጋጌ ስር ***"...ስለሰራተኛ...ዕድገት አሰጣጥ ስርዓት"*** በሚል የተገለጸው ሐረግ ሊተረጎም የሚገባው ከአንድ የሰራተኛ የስራ መደብ ወደ ሌላ የሰራተኛ የስራ መደብ የሚፈጸም የዕድገት አሰጣጥ ስርዓት ተደርጎ እንጂ ከአንድ የሰራተኛ የስራ መደብ በስራ መሪ ወደሚሸፈን ሌላ የስራ መደብ የሚፈጸም የዕድገት አሰጣጥ ስርዓትን በሚያጠቃልል አግባብ አለመሆኑን

ከድንጋጌው አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 142(1)(ሠ) ድንጋጌ ስር "...ስለሰራተኛ...ዕድገት አሰጣጥ ስርዓት" በሚል የተገለጸውን ሐረግ ከአንድ የሰራተኛ የስራ መደብ በስራ መሪ ወደሚሸፈን ሌላ የስራ መደብ የሚፈጸም የዕድገት አሰጣጥ ስርዓትን እንደሚያጠቃልል አድርጎ በመተርጎም ቦርዱ በስረ ነገር ስልጣን ረገድ በአመልካች የቀረበውን መቃወሚያ በብይን አልፎ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ የሰጠው ውሳኔ በሕግ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ በመዝገብ ቁጥር 498/ቀወ2/06 በ12/06/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139704 በ22/09/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ክርክር ያስነሳው ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 የሚሸፈን ባለመሆኑ ቦርዱ ጉዳዩን ተቀብሎ በማስተናገድ ውሳኔ የሰጠው ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖረው ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. በዚህ መዝገብ በ12/10/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው የአፈጻጸም ዕግድ ተነስቷል፡፡
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ለአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እና ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

የሰ/መ/ቁ. 101579

ህዳር 24 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካቾች፡-

1. አቶ ገ/መድህን አስፋው
2. አቶ ተ/ፃዲቅ ደምሴ
3. አቶ ዳኜ አየለ
4. አቶ ወ/ሚካኤል ዋቄ
5. አቶ አምሃ ኃ/ስላሴ
6. አቶ አመሃ መላኩ ኃ/ማሪያም
7. አቶ ደምሴ ድጋፌ
8. አቶ ግዛው አስረስ
9. አቶ ታደሰ ገ/መድህን
10. አቶ ወረደወርቅ ጥላሁን
11. አቶ ከበደ አወቀ
12. አቶ ይልማ ጨርቆስ
13. አቶ ዓለማየሁ ተሾመ
14. አቶ ላቀው እርገጤ
15. አቶ ተሾመ አግዴ
16. አቶ አየለ ይግለጡ
17. አቶ ይትባረክ ሰሜ
18. ወ/ሮ ፀሐይ አእምሮ
19. ወ/ሮብዙነሽ ማሞ
20. ወ/ሮ በቀለች ጉዳና
21. አቶ ኃ/ማሪያም ገና
22. አቶ ገብረ ተ/ኃይማኖት
23. አቶ ፍቃደስላሴ ርዳው
24. አቶ ሞገስ ኃ/መስቀል

ከጠበቃ መስፍን አለማየሁ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ነ/ፈጅ ሳህለማሪያም ወዳጆ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 128430 ታህሳስ 7 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.96927 ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት ተሽሮ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡ ጉዳዩ የጡረታ ደመወዝ ማስተካከያ አስተዳደራዊ ውሳኔ ተግባራዊ ይሁንልን ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪ እና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጠቅላይ ቤተክህነት ጽ/ቤት ተከሳሾች ነበሩ፡፡

የአመልካቾች የክስ ይዘትም፡- መንግስት ለመንግስት ሰራተኞች እና ጡረተኞች ህዳር 23 ቀን 2003 ዓ/ም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባስተላለፈው ውሳኔ የደመወዝ ማስተካከያ ማድረጉን ተከትሎ የኢትዮጵያ ኦርተዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅድስ ሲኖዶስም በስሩ ላሉት ሰራተኞች የደመወዝ ማስተካከያ እንዲደረግ ወስኖ ባለበት ሁኔታ የአሁኑ ተጠሪ እምቢተኛ መሆኑን ዘርዝረው የጡረታ ደመወዝ ማስተካከያ እንዲከፈል ይወሰንልን የሚል ነው፡፡ የስር ተከሳሾች ጉዳዩ በፍርድ ሊታይ የማይችልበትን ምክንያትና አመልካቾች ክሱን ለማቅረብ መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን የሚያሳዩ ነጥቦችን በመጥቀስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተከራከሩ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃም ለአመልካቾች የጡረታ ደመወዝ እንዲስተካከል የሚደረግበት የህግ ወይም የህብረት ስምምነት የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካቾች ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከሰማ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ የአመልካቾች ጥያቄ በፍርድ ቤት ሊታይ እንደሚችል፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቋሚ ሲኖዶስ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ/ም ባደረገው ስብሰባ ማስተካከያውን ለሰራተኞችና ለጡረተኞች በወሰነው መሰረት የአሁኑ ተጠሪም ለአሁኑ አመልካቾች ማስተካከያው ሊከፍል ይገባል በማለት ደምድሞና ሊጨመር የሚገባውን ማስተካከያ በመቶኛ ገልጾና ይኼው ማስተካከያ የሚመለከተውን የጡረታ ደመወዝ መጠን ለይቶ ለአመልካቾች ተጠሪ የጡረታ ማስተካከያውን ሊከፍል ይገደዳል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኃላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስር የሚተዳደር ነገር ግን በራሱ ገቢ ራሱን የሚያስተዳድር ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ጉዳይ መሆኑን፣ ለአመልካቾች ክስም ሆነ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት የሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስለሠራተኞቹና ጡረተኞቹ የደሞዝ ማስተካከያ አስመልክቶ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም ያስተላለፈው ውሳኔ መሆኑን በዚህ ውሳኔ ጥናት ተደርጐ የቀረበውን ጉባኤው ያፀደቀላቸው ሲሆን ሌሎቹ ማለትም በትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤትና ጐፋ ጥበበ እድ ካህናት ማሰልጠኛ ለሚገኙት ሠራተኞችና ጡረተኞች እንደየገቢያቸው መጠን እየወሰኑ ለአስተዳደሩ አቅርበው እያስፀደቁ ተግባራዊ እንዲሆን ሲል ቋሚ ሲኖዶሱ መወሰኑን የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይዘት በግዴታ የማያመላክት መሆኑን ከዚህ መረዳት የሚቻለው የጉባኤው ውሳኔ የአሁኑን ተጠሪን በተመለከተ ቀጥተኛ ተፈጻሚነት እና አስገዳጅነት ያለው የደመወዝ ማስተካከያ ያለማድረጉ መሆኑን ይልቁንም ተጠሪ በራሱ ገቢ የሚተዳደር ከመሆኑ አንፃር እንደራሱ ገቢ መጠን ጥናት አድርጐ በአስተዳደሩ አፅድቆ ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል አቅጣጫ የተቀመጠለት መሆኑን እንጂ አስገዳጅ የሆነ ውሳኔ ያልተሰጠ መሆኑን የሚያስገነዝብ መሆኑን ደምድሞ አመልካቾች ባለው የቤተክርስቲያን መዋቅር መሰረት አቤቱታቸውን ከማቅረብ ውጪ በፍርድ ሃይል ተፈጻሚ የሚሆን ውሳኔ የላቸውም በማለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ በመቀበል አፅንቶታል ፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፦የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሲኖዶስ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ/ም ያሳለፈው ውሳኔ ተጠሪ ገቢውን መሰረት በአደረገ መልኩ ለሰራተኞቹም ሆነ ለጡረተኞቹ በተሰራው ስኬል መሰረት ማስተካከያውን እንዲያደርግ የሚል ሁኖ እያለ ተጠሪ ለሰራተኞቹ ብቻ ማስተካከያውን አድርጐ ለጡረተኞቹ ሳያደርግ ሲቀር የቀረበውን ክስ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያላግባብ ተርጐሞ ተጠሪ የሚገደድበት ውሳኔ የለም በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ነው የሚል ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል ።እንደመረመረውም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ በጭብጥነት የተያዘው ነጥብ ፦ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቋሚ ሲኖዶስ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ የአሁኑን ተጠሪ በስም ጠቅሶ ለሠራተኞቹና ጡረተኞቹ እንደየገቢያቸው መጠን እየወሰኑ ለአስተዳደሩ እያስፀደቁ ክፍያው እንዲፈፀም በማለት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ለሰራተኞቹ የጭማሪውን ክፍያ እንደአደረገ ተጠሪ ግንቦት 27 ቀን 2005 ዓ/ም በሰጠው መልስ ማመኑ ከተረጋገጠ የሲኖዶሱ ውሳኔ ለጡረተኞች ብቻ ተፈፃሚነት የለውም በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው። እኛም ጉዳዩን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር ብቻ መመርመሩን ተገቢነት ያለው ሆኖ አግኝተናል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሥር የሚተዳደር ነገር ግን በራሱ ገቢ ራሱን የሚያስተዳድር ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከ ጉዳይ መሆኑን፣ ለአመልካቾች ክስም ሆነ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት የሆነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስለሠራተኞቹና ጡረተኞቹ የደሞዝ ማስተካከያ አስመልክቶ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም ያስተላለፈው ውሳኔ መሆኑን፣ በዚህ ውሳኔ ጥናት ተደርጎ የቀረበውን ጉባኤው ያፀደቀላቸው ሲሆን ሌሎቹ ማለትም በትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤትና በጎፋ ጥበብ እድ ካህናት ማሰልጠኛ ለሚገኙት ሠራተኞችና ጡረተኞች እንደየገቢያቸው መጠን እየወሰኑ ለአስተዳደሩ አቅርበው እያፀደቁ ተግባራዊ እንዲሆን ሲል ቋሚ ሲኖዶሱ መወሰኑና ይህንኑ ተከትሎም ተጠሪ ለሠራተኞቹ የጭማሪውን አስተካክሎ ክፍያውን ሲፈፅም ለአሁኑ አመልካቾች፤ የድርጅቱ ጡረተኞች ግን ማስተካከያውን ሳያደርግ የቀረ መሆኑን አምኖ የሚከራከር መሆኑን ነው። የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ለክሱ ኃላፊነት የለበትም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው የሲኖዶሱ የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ይዘት ተጠሪ ለጡረተኞች ማስተካከያ እንዲያደርግ በግዴታየሚያመላክት አይደለም የሚለውን ምክንያት በመያዝ መሆኑን ከውሳኔው ይዘት ተረድተናል።

በመሰረቱ ተጠሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስር የሚተዳደር ከሆነ የቤተክርስቲያኗ የበላይ የሆነው አካል የሰጠውን ውሳኔ ያለምንም ልዩነት ተግባራዊ ማድረግ አለበት። ተጠሪ ለአመልካቾች የጡረታ ደመወዝ የሚከፍለው በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ሲሆን ይህ ክፍያ የሚፈፀመውም የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነቱ በጡረታ ምክንያት በመቋረጡ ምክንያት በመሆኑና ገንዘቡም ከአሰሪውና ከሠራተኞቹ ደመወዝ ተቆርጦ ሲጠራቀም ከነበረው መሆኑ ግልፅ ነው። የጡረታ ደመወዝ ሕጋዊ በሆነ የአስተዳደራዊ ውሳኔ መሰረት እንዲስተካከል ሲደረግ በሠራተኛው ስም የተቀመጠው ገንዘብ መኖሩን ብቻ በማረጋገጥ ነው ተብሎ አይታሰብም። ጡረታ አግባብነት ላላቸው የህብረተሰቡ ክፍሎች የኑሮ ዋስትና

ለመስጠት እንዲያስችል ተብሎ ተግባራዊ የሚደረግ ማህበራዊ መድህን መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የኑሮ ዋስትና የመስጠት መሰረታዊ አላማው የሚሳካው ደግሞ ተጨባጭነት ያለውን ወይም የሕብረተሰቡን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ማስተካከያው ሲደረግ መሆኑ የሚታመን ነው፡፡ በዚህ አግባብ የጡረታም ሆነ የደመወዝ ማስተካከያም ተግባራዊ እየተደረገ ያለበት ሁኔታ መኖሩም ግንዛቤ የሚወሰድበት ነው፡፡ የተጠሪ መስሪያ ቤት ባለቤት የሆነውና የበላይ የአስተዳደር አካሉ መንግስት ለሠራተኞቹና ለጡረተኞቹ ያደረገውን ማስተካከያ መነሻ በማድረግና በራሱ ፍላጎት ለተጠሪ ሠራተኞቹና ጡረተኞች ማስተካከያውን እንዲያደርግ፣ ማስተካከያው ደግሞ የተጠሪን ገቢ መሰረት አድርጎ ሊሰራእንደሚገባና በሚመለከተው አካል እየጸደቀ ተግባራዊ እንዲሆን የሚገልፅ ውሳኔ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ/ም መወሰኑም ይህንኑ የሚያሳይ ነው ፡፡ ተጠሪ የሲኖዶሱ ውሳኔ በተጠሪ ላይ አስገዳጅነት የለውም በማለት የሚያቀርበውና በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ያገኘው መከራከሪያ ነጥብ ሲታይም ተጠሪው ገቢውን መሰረት ያደረገ ጥናት አደርጎ ለቋሚ እና ለኮንትራት ሰራተኞቹ ማስተካከያውን አድርጎ ክፍያውን መፈጸሙን ያመነበትን አግባብ ክፍያውን ለጡረተኞቹ ላለማድረግ ህጋዊ ምክንያት የነበረው መሆን ያለመሆኑን አጣምሮ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ምክንያቱም የተጠሪ የበላይ አስተዳደር የሆነው አካል ለተጠሪ የሰጠው አስተዳደራዊ አቅጣጫ የማስተካከያው ክፍያ ተጠቃሚዎችን ሠራተኞች ወይም ጡረተኞች በሚል ጭምር ተለይቶ እንዲፈፀም የሚያሳይ ሳይሆን ለሠራተኞቹም ሆነ ለጡረተኞቹ ልዩነት ሳይደርግ የድርጅቱን ገቢ መሰረት አድረጎ ማስተካከያውን እንዲሰራና ተግባራዊ እንዲያደርግ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የበላይ አካልን ውሳኔ ተግባራዊ ላለማድረግ ሕጋዊ መከራከሪያ ሊሆነው የሚችለው የድርጅቱ የገቢ ሁኔታ ብቻ ነው፡፡ሆኖም ተጠሪ ለሰራተኞቹ ማስተካከያውን ያደረገው የድርጅቱን ገቢ መሰረት አድርጎ ስላለመሆኑ ያቀረበው ክርክርና ማስርጃ የለም፡፡የተጠሪ የበላይ አካል የሆነው ሲኖዶሱ ማስተካከያው ለተጠሪ ድርጅት ሰራተኞች ጡረተኞች እንዲደረግ ውሳኔ ከሰጠና ለሠራተኞቹ የተጠሪን ገቢ መሰረት ባደረግ መልኩ ማስተካከያው መደረጉ እስከተረጋገጠ ድረስ ደግሞ ተጠሪ ጡረተኞችን ብቻ በመለየት የማስተካከያው ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም የሚልበት አግባብ የለም፡፡ተጠሪ የበላይ አካሉን ውሳኔ ተቀብሎ ለሠራተኞቹ ብቻ ማስተካከያ አድርጎ ለጡረተኞቹ ብቻ ማስተካከያውን የተወበት አካሄድ ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ በውጤት የጡረታ መብት ለኑሮ ዋስትና ያለው ሕጋዊ ፋይዳ ዋጋ የሚያሳጣው ነው፡፡

አመልካቾች ተጠሪ ላይ በመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ የመሰረቱት ከተጠሪ ጋር መስርተው የነበሩት ሕጋዊ የአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ተቋርጦ የአመልካቾች የጡረታ መብት ተከብሮላቸው የጡረታ መብት ተካፋይ ሁነው ባሉበት ሁኔታ በአስተዳደራዊ ውሳኔ መሰረት የተከበረላቸው የጡረታ ማስተካከያ ክፍያ ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም በሚል በመሆኑ ጉዳዩ ኃይማኖታዊ ስርዓትን ተከትሎ ትርጉም የማያስፈልገው በመሆኑ ጉዳዩ በፍርድ ቤት መታየቱ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 11 ስር የተደነገገውን መርህ የማይነካ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ሕጋዊ የሆነ አስተዳደራዊ ውሳኔ ተግባሪዊ ሳይሆን ሲቀር በፍርድ ቤት ውሳኔ አስገዳጅነትእንዲኖረውማድረግም በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 37 እና 25 የተረጋገጡትን ፍትህ የማግኘት መብትና የእኩልት መብት ውጤታማ የሚያደረግ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪ የበላይ አካል የሆነው ሲኖዶስ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሰኔ የአሁኑን ተጠሪ በስም ጠቅሶ ለሠራተኞቹና ጠረተኞቹ እንደየገቢያቸው መጠን እየወሱነ ለአስተዳደሩ እያስፀደቁ ክፍያው እንዲፈፀም በማለት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ተጠሪ ለሰራተኞቹ የጭማሪው ክፍያ እንደ አደረገ ግንቦት 27 ቀን 2005 ዓ/ም በሰጠው መልስ ማመኑ

በተረጋገጠበት ሁኔታ የሲኖዶሱ ውሳኔ ለጡረተኞች ብቻ ተፈፃሚነት የለውም የሚል ትርጉም የሚያሰጥ ውሳኔ መስጠቱ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮችን ያላገናዘበ ሆኖ ስለአገኘነው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 96927 ግንቦት 05 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 128430 ታህሳስ 07 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ ለአመልካች ጥያቄ ኃላፊ ነው ተብሎ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ መጋቢት 20 ቀን 2003 ዓ/ም በወሰነው መሰረት ከጥር ወር 2003 ዓ/ም ጀምሮ የጡረታ ማስተካከያ አበል ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስነናል፡፡ ስሌቱን በተመለከተ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባስቀመጠው መሰረት ነው ብለናል፡፡
4. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማአለበት፡፡**

**እ/እ**

የሰ/መ/ቁጥር 102512

ታህሳስ 10 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካቾች፡-**

1.አቶ ብርሃኑ ቢኔ

2. አቶ ሞላ ደሴ

3. አቶ ተስፋዬ ሐበና

4. ወ/ሮ ጀማነሽ መንገሻ

5. አቶ ጉልትነህ ታደሰ

6. አቶ ወርቁ አይዴ

7. አቶ መኮንን ሙሉ

8. ወ/ሮ ክብነሽ ዋጤሮ

9. ወ/ሮ ታየች አሰፋ

10. አቶ አጫ አይሳሮ

11. ወ/ሮ ፀዳለ ቸችሮ

12. አቶ ሐይሌ አረጋዊ

13. አቶ ጠብቀው ሳንፎ

14. ወ/ሮ ለተብርሃን መኮንን

15. አቶ ዘሪሁን ደግፌ

16. አቶ በርሔ አሰፋ

17. ወ/ሮ አቦነሽ ሳካሎ

18. አቶ ዋህድ ካሳዬ

19. አቶ ግዛቸው ካሳ

20. አቶ አበራ ሐይሌ

21.አቶ ደምመላሽ ካሳዬ

22. ወ/ሮ መስከረም ካንኮ

23. አቶ ሙሉጌታ መቺሶ

24. አቶ ሱልጣን ሐሰን

25. አቶ ጌታሁን ሐይሌ

26. ወ/ሮ ዓለሚቱ ገብሬ

27. ወ/ሮ ባዩሽ በቀለ

28. አቶ ደሳለኝ ትንታግ

29. አቶ እንግዳ እሸቱ

30. ወ/ሮ ጀማነሽ መንገሻ

31. ወ/ሮ አየለች ባልቻ

32. አቶ መንበረ ጌታቸው

33. አቶ መተኪያ ፀጋዬ

34. አቶ አብዮት ጌታሁን

(19–34:) ደመነ ቱኔ የ34ቱም ጠበቃ

**ተጠሪ፡- የአርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካአ/ማ- ነ/ፈጅ ሹፋያን ሱልጣን ቀረቡ**

***መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡***

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 139151 ግንቦት 25 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የስራ ውል መቋረጥን የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በደቡብ ክልል የሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ነው፡፡ በክልሉ የሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. አመልካቾች በተጠሪ ድርጅት ከሃያ ዓመት በላይ በታማኝነት ያገለገሉ መሆኑን ገልፀው ተከሳሽ (ተጠሪ) አዲስ መዋቅር አስጠንቻለሁ በማለት የስራ መደባችሁ ታጥፏል በሚል ሰበብ በሕግ አግባብ የሰራተኛ ድልድልና ምደባ ሳያደርግ ቅነሳ በሚል ሀሰተኛ ምክንያት መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ/ም እና ሚያዝያ 10 ቀን 2005 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ የስራ ውላችንን ከሕግ ውጭ ያቋረጠ በመሆኑ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ይወሰንልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ጉዳዩ በመደበኛ ፍርድ ቤት የሚታይ ነው በማለት የመጀመሪያ የክስ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን፣ በአማራጭ ሰራተኞቹ የተቀነሱት የድርጅቱ መዋቅር በገለልተኛ ባለሙያ ከተጠና በኂላ ከሳሾች መዋቅሩ የሚጠይቀውን መስፈርት ባለማሟላታቸው ያልተደለደሉ በመሆኑና ድልድሉ የሰራተኞች ተወካይ ባለበት በግልጽ መስፈርት ሰራተኞች ተወዳድረው የተመደቡ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡
2. የክልሉ ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኂላ ተጠሪ አመልካችዎችን ከስራ ያሰናበተበት አግባብ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 29 የተደነገጉትን መስፈርቶች የማያሟላና ከሕግ ውጭ በመሆኑ ተጠሪ በሕጉ መሰረት ሁሉንም ሰራተኞች ባሳተፈ መልኩ እንደገና የሰራተኛ ድልደላ ይፈፅም፡፡ ተጠሪ እንደገና ለመደልደል ካልፈለገ ስንብቱ ሕግን ያልተከተለ በመሆኑ ከሳሾችን/ አመልካቾችን/ ወደ ስራ ይመልስ፡፡ ተጠሪ ከሳሾችን ወደ ስራ ካልመለሰ በሕግ አግባብ ካሳ በመክፈል እንዲያሰናብታቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ ይግባኝ ባይ (ተጠሪ) ሠራተኞችን የደለደለው በትምህርት ደረጃ፣ በስራ ልምድ፣ በማህደር ጥራትና የስራ አፈፃፀም ውጤት በመሆኑ ስንብቱ በህግ አግባብ የተፈፀመ ነው በማለት የክልሉ ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የሰጠውን ውሳኔ ሽሮታል፡፡
3. አመልካቾች ሰኔ 27 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ያስጠናው መዋቅር ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 20 የስራ መደብ ያለው ቢሆንም ሰራተኛ ድልድል የፈፀመው ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 12 ባለው የሥራ መደብ ላይ ብቻ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ ካሉት 674 ሠራተኞች አስር ፐርሰንት የሚሆኑ አልቀነሰም፡፡ መዋቅሩ ሠራተኞች ቁጥር እንዲጨምር የሚያደርግ ነው፡፡ ተጠሪ እኛን በሕግ አግባብ በማወዳደር ሠራተኞችን ያልደለደለ መሆኑን በማረጋገጥ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አላግባብ መሻሩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ጥቅምት 3 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ መልስ ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 12 ባለው የስራ መደብ

ሠራተኞች በአግባቡ ተወዳድረው ተመድበዋል፡፡ ከደረጃ 13 እስከ ደረጃ 20 ያለው የስራ መደብ የስራ መሪዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ከስራ የተሰናበቱት ሰራተኞች 10% በታች መሆኑ ስንብቱን ህገ ወጥ አያደርገውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲፀናልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች ጥቅምት 14 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ የመልስ መልስ ተጠሪ ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 12 ሰራተኞች ተወዳድረው ተመድበዋል ያለው ሀሰት ነው፡፡ ምክንያቱም በድርጅቱ ንብረትና ፋይናንስ ዘርፍ የሥራ መደቦች ላይ የተሰማሩ ሠራተኞች በድልድል አልተካተቱም፡፡ ተጠሪ ከደረጃ 13 እስከ ደረጃ 20 ያሉት የስራ መደቦች የስራ መሪ የስራ መደብ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር እውነትነት የሌለው ነው፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት ተከራክረዋል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ የአመልካቾችን የስራ ውል ያቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተገለፀውን ጭብጥ ለመወሰን፣ በመጀመሪያ ፍሬ ጉዳይ የማጥራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን በሕግ የተሰጠው የሠራተኞች ጉዳዮች ወሳኝ ቦርድ የግራ ቀኙን የሰውና የፅሁፍ ማስረጃ ሰምቶ፣ መርምሮና መዝኖ የደረሰባቸውን የፍሬ ጉዳይ መደምደሚያዎች ከሕጉ ድንጋጌ ጋር ማገናዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ የክልሉ ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪ ምርታማነትን ለማሳደግና አሰራር ለመለወጥ አዲስ መዋቅር ያስጠና መሆኑና በአዲሱ መዋቅር መነሻ በማድረግ አመልካቾችን ከስራ የቀነሰ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ካሉት 674 ሠራተኞች ቅነሳ በሚል ምክንያት ከስራ ያሰናበተው ከአስር ፐርሰንት የማይሆኑ ሠራተኞችን እንደሆነ አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስራ ምደባው ከተወዳደሩ በኋላ በውድድሩ ያላለፉ ሠራተኞችን ተጠሪ ከደረጃቸው ዝቅ አድርጎ የመደበና ያላሰናበተ መሆኑን በማስረጃ መረጋገጡንና የሥራ ድልድሉ ሁሉንም ሰራተኞች የማይመለከት በተለይ ንብረትና ፋይናንስ ክፍል የሚሰሩ ሰራተኞችን የማይመለከት መሆኑን በማስረጃ እንደተረጋገጠ ቦርዱ በግልጽ በውሳኔው ውስጥ አስፍሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከደረጃ 13 እስከ ደረጃ 20 ያሉ የስራ መደቦች ሰራተኞች በውድድር ያልተመደቡባቸው መሆኑን፣ በማስረጃ እንደተረጋገጠ በውሳኔው አስፍሯል፡፡ ይህም የሠራተኛ ቅነሳ ነው በማለት ተጠሪ ያከነወነው ተግባር የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት አያሟላም በማለት የሠራተኛ ውሳኝ ቦርዱ መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡
6. ከላይ የሰራተኛ ወሳኝ ቦርዱ በማስረጃ ያረጋገጣቸው ጉዳዮች አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አንጻር መርምረናል፡፡ በመጀመሪያ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) አሰሪው የድርጅቱን አቋም ወይም የስራ እንቅስቃሴ ምክንያት በማድረግ በተለይም የድርጅቱን ምርታማነት የማሳደግ አሰራር ዘዴዎች ለመለወጥ ወይም አዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ሲባል ሠራተኞችን የመቀነስ ውሳኔ ሊያስተላልፍ እንደሚችልና ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ሰራተኞችን ሊያሰናብት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህ መስረት የስራ መደብ መሰረዝ ሠራተኞችን የሚነካ ሲሆንና በአዋጁ አንቀጽ 29(1) መሰረት የሠራተኛ ቅነሳ የሚያስከትል ሲሆን የስራ ውሉ የሚቋረጠው በአዋጅ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 3 ሁኔታዎች በማሟላት መሆን እንዳለበት በአዋጁ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 3 ተደንግጓል፡፡
7. ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ባስጠናው አዲስ መዋቅር ምክንያት ካሉት ሠራተኞች አስር ፐርሰንት የሚሆኑትን የስራ ውል ያላቋረጠና ይህም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 29(1)

የተቀመጠውን መስፈርት የማያሟላ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች ካሉት ሠራተኞች አምስት ፐርሰንት የማይሆኑትን የስራ ውል ለማቋረጥ በአዋጅ አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገውን አስገዳጅ መስፈርት የመከተል ግዴታ አለበት፡፡ ሆኖም አመልካች በመጀመሪያ ደረጃ ከአመልካቾች ያነሰና ዝቅተኛ የሥራ አፈጻጸም ያላቸውን ሠራተኞች በተጠሪ ኃላፊዎች ትዕዛዝ በስራ እንዲቀጥሉ አድርጎ አመልካቾችን ያሰናበተ መሆኑ የሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ የግራ ቀኙን ምስክሮች የሰራተኛ ደልዳይ ኮሜቴ አባላት የምስክርነት ቃል በመስማትና በመመዘን አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የስራ ድልድልና ቅነሳው ተጠሪ ያሉትን ሁሉንም የስራ መደቦች የማያካትትና ሁሉንም የስራ ክፍሎች የማይመለከት መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡በአጠቃላይ ተጠሪ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 29/3/ የተደነገጉትን መስፈርቶች በመጠቀም የአመልካቾችን የስራ ውል ያላቋረጠ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባለው የሠራተኛ ጉዳይ ቦርድ ተረጋግጧል፡፡

8. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ያረጋገጣቸውን ፍሬ ጉዳዮች እና የደረሰበትን የፍሬ ጉዳይ እና የማስረጃ መደምደሚያ በመቀበል፤ሕጉን መሰረት ያደረገ መሆኑን ከመመዘን ያለፈ፣ የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና ስህተት በይግባኝ የማየትን የማረም ሥልጣን ከአዋጅ አንቀጽ 140 ንዑስ አንቀጽ 1 አልተሰጠውም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ተጠሪ ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 12 ሰራተኞች ለመደልደል በተጠቀማቸው አራት መስፈርት ከአመልካቾች ጋር ተወዳድረው ዝቅተኛ ነጥብ ያመጡ ሰዎች በስራ እንዲቀጥሉ ያደረገና የተሻለ ውጤት ያመጡትን አመልካቾች ያሰናበተ መሆኑን በማስረጃ እንዳረጋገጠ የገለጸውን የፍሬ ጉዳይ መደምደሚያ የሚያስከትለውን ሕጋዊ ውጤት ሳይመረምርና ሳይመዝን በማለፍ ተጠሪ ሠራተኞችን የደለደለው አራት መስፈርቶች ተጠቅሞ ነው በማለት ስንብቱ ህጋዊነው በማለት መወሰኑ በመዝገቡ የሠራተኛ ወሳኝ ቦርድ በማስረጃ ያረጋገጣቸውን ፍሬ ጉዳዮች በማለፍ የተሰጠና የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) እና ንዑስ አንቀጽ 3 እንዲሁም የአዋጁን አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 40(1) ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሠራተኞች ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የአርባ ምንጭ ቅርንጫፍ በመዝገብ ቁጥር 0002/05 መስከረም 24 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ. 104294

ቀን 29/07/2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ሐግቤስ ኃ/የተ/የግል/ማህበር - ነ/ፈጅ ፀጋዬ መካሻ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ በላይ ገ/ማሪያም - ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው በፌዴደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካች የስንብት እርምጃ ህገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጽናቱ በውሳኔው ላይ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሰረት ያደረገ የግል የስራ ክርክር ሁኖ አንድ ሰራተኛ ከአሰሪው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል ተብሎ ከስራ ያለማስጠንቀቂያ የሚሰናበትበትን የህግ አግባብ ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት የቀረበው የተጠሪ ክስ አመልካች ተጠሪን በጨረታ እንዳይሳተፍ የተደረገውን ጥፋት ሳይፈጽም ይህንኑ ጥፋት ፈጽመሃል በሚል ምክንያት የስራ ውል አላግባብ ያቋረጠ በመሆኑ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ የተጠሪ የስራ መዘርዝር በግልጽ የሚያሳየው የጨረታ ሰነድ አዘጋጅተው የጨረታውን ሂደት በመከታተል ሪፖርት ማቅረብ መሆኑን ፣ ተጠሪ ይህንኑ የስራ ግዴታ በመተላለፍ የጨረታ ሰነድ ሳያስገቡ በቀሩት የማሽን ጉልበት አመልካች ድርጅት ከጨረታ እንዲሰረዝ በመደረጉ ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ቢሆንም አመልካች ድርጅት ተሳታፊ እንዲሆን በወሰነበት የትግራይ የውሃስራዎች ኮንስትራክሽን መጋቢት 05 ቀን 2005 ዓ/ም ባወጣው ጨረታ ጨረታውን ሳይከታተሉ በመቅረታቸው ድርጅቱ በጨረታው እንዳይሳተፍ አድርገው የጥቅም ማጣት እንዲደርስበት ያደረጉ መሆኑን ዘርዝሮ ስንብቱ በህጉ አግባብ የተደረገ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤት ተጠሪ በፈጸሙት ከባድ ቸልተኝነት ምክንያት አመልካች ድርጅት በጨረታው ላይ ሳይሳተፍ የቀረ መሆኑ ቢረጋገጥም በዚህ ጥፋት ምክንያት በአመልካች ድርጅት ላይ የደረሰ ጉዳት መኖሩ አልተረጋገጠም የሚል ምክንያት አስፍሮ የአመልካች የስንብት እርምጃ ህገ ወጥ ነው በማለት አመልካች ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎችን ሊከፍል ይገባል በማለት የክፍያዎችን

አይነትና መጠን በመዘርዘር በድምሩ ብር 72,000.00 (ሰባ ሁለት ሺህ) እንዲከፍል፣ የስራ ልምድ የምስክር ወረቀት አዘጋጅቶ እንዲሰጠው ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ በስራ መዘርዝራቸው መሰረት ግዴታቸውን ያለመወጣታቸውና ከባድ ቸልተኝነት የነበረባቸው መሆኑን የስር ፍርድ ቤት አረጋግጦ ጉዳት ስለመድረሱ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት ብቻ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የወሰነው ከህጉ ይዘትና መንፈስ ውጪ ነው ፣ አመልካች በጨረታው ላይ ባለመሳተፉ ከብር ሃያ ሶስት ሚሊዮን በላይ የጥቅም ማጣት ደርሶበታል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ በፅሁፍ በሰጡት መልስም በአመልካች ድርጅት ላይ ጉዳት ያለመደረሱን ፣ በስራቸው የፈጸሙት ጥፋትም የሌለ መሆኑን ዘርዝረው ተከራክረዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው ከህግ ውጭ በመሆኑ ፣ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የተጠሪ የስራ መዝርዝር በግልጽ የሚያሳየው የጨረታ ሰነድ አዘጋጅተው የጨረታውን ሂደት በመከታተል ሪፖርት ማቅርብ መሆኑንና ይህንኑ የስራ ግዴታ ባለመወጣታቸው አመልካች ቀድሞ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው እንደነገና አመልካች ድርጅት ተሳታፊ እንዲሆን በወሰነበት የትግራይ የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን መጋቢት 05 ቀን 2005 ዓ/ም ባወጣው ጨረታ ጨረታውን ሳይከታተሉ በመቅረታቸው ድርጅቱ በጨረታው እንዳይሳተፍ ያደረጉ መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም ይህንን ጥፋት ያልፈጸሙ መሆኑን በማስረጃዎቹ ያላስረዱ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ይዘት ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ በዚህ የሰበር ክርክር ደረጃ ባቀረቡት መልስ በአመልካች ድርጅት ላይ በጨረታ ባለመሳተፉ የደረሰ ጉዳት የለም በማለት ከገለፁ በኂላ በአማራጭ ደግሞ ከባድ ቸልተኝነት እንዳልነበራቸውና ጥፋት እንዳልፈጸሙ ዘርዝረው በዚሁ በአማራጭ ባቀረቡት ክርክር መሰረት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሆኖም ተጠሪ ከባድ ቸልተኝነት እንዳልነበራቸው ፣ ጥፋት እንዳልፈጸሙ የሚያቀርቡት ክርክር በሰበር መልሳቸው የተገለፀ እንጂ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ ነው ሊባል የሚችል ካለመሆኑም በላይ የስር ፍርድ ቤት ፍሬ ነገሩን አጣርቶና ማስረጃን መዝኖ የደረሰበት ድምዳሜ በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊለወጥ የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በከባድ ቸልተኝነት አመልካች ድርጅት በጨረታው ላይ እንዳይሳተፍ ያደረጉ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ነው በሚል የምንቀበለው ነጥብ ነው፡፡

አመልካች ተጠሪን ለቀደመው ጥፋታቸው በማስጠንቀቂያ ያለፉቸው ቢሆንም መጋቢት 05 ቀን 2005 ዓ/ም በወጣው ጨረታ እንዳይሳተፍ የተደረገው በተጠሪ ጥፋት መሆኑ በመረጋገጡ ተጠሪን ከስራ ሊያስናብታቸው ችሏል፡፡ አመልካች በዚህ ጨረታ ያልተሳተፈው በተጠሪ ከባድ ቸልተኝነት መሆኑ በበታች ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ የሚሰሩበት የስራ ባህርይ የጨረታ ሰነድ አዘጋጅተው የጨረታውን ሂደት በመከታተል ሪፖርት ማቅረብ መሆኑንም በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪ አመልካች ድርጅትን ጥቅም ለማስጠበቅ ከፍተኛ ጥንቃቄና ትጋት በማድረግ ግዴታቸውን መወጣት የሚገባቸውና የድርጅቱ ኢኮኖሚ ጥቅም ጉዳት እንዳይደርስበት የማድረግ የስራ ግዴታ አለባቸው፡፡ ተጠሪ ይህንን የስራ ተግባሩን

በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመፈጸማቸው አመልካች ድርጅት ከጨረታ መሰረዙ በድርጅቱ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ ጉዳት አላደረሰም ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ተጠሪ ጉዳዩን ጨረታን መሰረት ያደረገና በውድድር ላይ የተመሰረት መሆኑን ግልጸው የአመልካች ድርጅት የጨረታ ሰነድ ከሌሎች ተጫራቾች ጋር ሲነጻጸር ጨረታውን ሊያሸነፍ ይችል ያልነበረ መሆኑን ጠቅሰው ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ በጨረታው ውደድር በአመልካች ድርጅት ጥቅም የሚገኝበት አግባብ መኖሩ ግልጽ ከሆነና አመልካች በተጠሪ የስራ ግዴታቸውን በአግባቡ ባለመወጣት ከውድድሩ ውጪ መሆኑ ከተረጋገጠ በአመልካች ድርጅት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ ጉዳት ያለመደረሱን የማስረዳት ግዴታ የተጠሪ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን ተጠሪ በአመልካች ላይ ጉዳት አልደረሰም ከማለት ውጪ ይህንኑ የሚያስረዳ ማስረጃ ያለማቅረባቸውን ከክርክሩ ሂደት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተጠሪ የፈጸሙት ጥፋት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1/ሸ/ የሚሸፈንና የተጠሪን የስራ ውል ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በተጠሪ ከባድ ቸልተኝነት ምክንያት በአመልካች ላይ የደረሰ ጉዳት የለም በማለት ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)ሸ እና አንቀጽ 12(2)(7) ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት ፣ መንፈስና አላማ ያላገናዘብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች የተጠሪን ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ በድጋሚ ጥፋት ሲፈጽሙ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሽ) እና 12(2)(7) ድንጋጌዎች መሰረት ህጋዊ እንጂ ህገ ወጥ ተግባር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው ከህግ ውጭ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለአገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 10206 ሚያዚያ 30 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 140042 ሐምሌ 25 ቀን 2006 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች እርምጃ ህጋዊ ነው፣ አመልካች ለተጠሪ ካሳም ሆነ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡ የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት ግን ይስጣቸው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሃ/ወ

የሰ.መ.ቁ. 105620

ሚያዝያ 13 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካቾች፡-1. አቶ ሀብቴ ብርሃኔ
2. አቶ በየነ ለሜቻ
3. አቶ ግርማ አንጉራ
4. አቶ ጌትነት ዘውዴ
5. አቶ ጥላሁን ተክለመድህን
6. አቶ ተመስገን ግርማ

} ጠበቃ አቶ ሣሙኤል ሽፈራው - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ሙሉነህ ቡና ላኪ ትራንስፖርትና ትሪንዚት አገልግሎት - ጠበቃ ፈጠነ ደረሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች መዝገብ ቁጥር 140043 ሐምሌ 3 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የሥራ ስንብት የሁለት ወር ደመወዝ ይከፈለን በማለት የቀረበ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሾች ተከሳሽ በሹፌርነት ተመድባችሁ የምታሽከረክሩት መኪና ተሸጧል በሚል ምክንያት የሁለት ወር ማስጠንቀቂያ ከሰጠን በኃላ የሥራ ውላችን አቋርጧል፡፡ ተከሳሽ የሥራ ውሉን በቅነሳ ምክንያት ማቋረጥ ሲገባው አላግባብ የሥራ መደብ ተሰርዟል በማለት ያቋረጠው በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ህግ መሠረት ሊከፍል የሚገባውን የሁለት ወር ደመወዝ የሥራ ስንብት ክፍያ ያልከፈለ በመሆኑ እንዲከፍል ውሣኔ ይስጥልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት ተከሳሽ

ሆኖ ቀርቦ ከሳሾች የሚያሽከረክሯቸው መኪኖች በመሸጣቸው የሥራ መደቡ ተሰርዟል፡፡ ስለዚህ ተከሳሾች የስራ ስንብት ክፍያ የምንከፍልበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

2. የሥር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተከሳሽ ኪሣራ አልደረሰበትም፡፡ ኪሳራ የደረሰበት ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የቡና ላኪ ድርጅት ላይ ነው፡፡ ከሳሾች የሚያሽከረክሯቸው መኪኖች የተሸጡትም የቡና ላኪ ድርጅት ዕዳ መክፈያነት ነው፡፡ ተከሳሽ የሥራ ውሉን ከሳሾች የሚያሽከረክሯቸው መኪኖች በቡና ላኪ ድርጅት ላይ በደረሰው ኪሣራ ምክንያት በዕዳ መክፈያነት በመሸጣቸው የሥራ ውሉን ያቋረጠ በመሆኑ፣የሥራ ውሉ የተቋረጠው በቅነሳ እንጂ የሥራ መደብ በመሠረዙ ምክንያት አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ ከሳሽ በተከሳሾች የሁለት ወር ደመወዝና አገልግሎት ጊዜአቸውን አስልቶ የሥራ ስንብት ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ መልስ ሰጭዎች ያሽከረከሯቸውየነበሩት መኪናዎች መሸጣቸው ተረጋግጧል፡፡ መልስሰጭዎች ያሽከረክሯቸው የነበሩ መኪናዎች መሸጣቸው ከተረጋገጠ ይግባኝ ባይ ሌላ መኪና ገዝቶ እስኪተካ ድረስ የሹፌርነት የሥራ መደብ ተሰርዟል ለማለት ይቻላል፡፡ ይግባኝ ባይ መልስ ሰጭዎችን የሥራ መደብ በመሰረዙ ምክንያት ከሥራ ያሰናበታቸው በመሆኑ የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል አይገባም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

4. አመልካቾች መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ካሉት ከመቶ በላይ ከሚሆኑ ሹፌሮች ዝቅተኛ አገልግሎትና የሥራ ልምድ በመምረጥ ቀንሶ ከሥራ አሰናብቶናል፡፡ ከዚህ አንፃር የተጠሪ አድራጎት ቅነሳ እንጂ የሥራ መደብ መሠረዝ ነው ሊባል አይገባውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሰሪው ሠራተኛውን ከሥራ ሲያሰናብት የአገልግሎት ክፍያ የመክፈል ሃላፊነት አለበት፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ስንብት ክፍያ አይገባችሁም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር እንዲታይልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ጥር 28 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች የተሰናበቱት የሥራ መደቡ የተሠረዘ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንን በማገናዘብ የሥራ ስንብት ክፍያ ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካችዎች የካቲት 14 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

5. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካቾች የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

6. አሠሪው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ውል ለማቋረጥ የሚችልባቸውን መሠረታዊ ምክንያቶች አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28 በሁለት ከፍሎ አስቀምጧቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ከሠራተኛው ችሎታ ማጣት ወይም ሁኔታ የሚመለከቱ ምክንያቶችም ሲሆኑ በአዋጅ አንቀፅ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ"ሀ" እስከ "መ" በዝርዝር ደንግጓል፡፡ ሁለተኛው ከአሠሪው ድርጅታዊ አቋም ወይም የሥራ እንቅስቃሴ የሚመለከቱ ምክንያቶች የሥራ ውል ሲቋረጥ መሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ አመልካቾች የሚያሽከረክሯቸው መኪኖች በዕዳ ምክንያት በመሸጣቸው የአመልካችዎች የሥራ መደብ በአዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 1 (መ) መሠረት ተሰርዟል በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተጠሪ ከፈፀመው ተግባር አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

7. አመልካችዎች የሚያሽከረክሯቸው መኪኖች የተሸጡት በተጠሪ ድርጅታዊ አቋምና የሥራ እንቅስቃሴ ምክንያት በመሆኑና በተለይም ቡና የሚልከው የንግድ ድርጅት ኪሣራ ስለደረሰበት መኪኖቹ ተሸጠው ዕዳ መክፈያነት የዋሉ መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ አንድ ድርጅት ሠራተኞች የተሰማሩባቸው ሥራዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ በቀጥታና በሌላ ቦታው የሚያስቆምና የሠራተኞች ቅነሳ የሚያስከትል ሁኔታ ሲያጋጥመው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ውሉን ሊያቋርጥ እንደሚችል በአዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) ተደንግጓል፡፡ የተጠሪም አድራጎት በዚህ ድንጋጌ ሥር የሚሸፈን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
8. ሰለ ሥራ ስንብት ክፍያ የሚደነግገው የአዋጅ ቁጥር 377/96 ምዕራፍ ሶስት በክፍል ሁለት የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ሰራተኛ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት ከሥራ ሲቀነስ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ያለው መሆኑ በአንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በተጠሪ ድርጅታዊ አቋምና የሥራ እንቅስቃሴ ምክንያት ከሥራ የተቀነሱት አመልካቾች በአዋጁ አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከቱትን የሥራ ስንብት ክፍያዎች የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መንፈስና ዓላማ የምንረዳው ጉዳይ ሆኖ እያለ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካችዎች የሚያሽከረክሯቸው መኪናዎች በዕዳ ምክንያት መሸጥ ከተጠሪ ድርጅታዊ አቋምና የሥራ እንቅስቃሴ ነጥሎ በማየት ተጠሪ ለአመልካችዎች የሥራ ስንብት ክፍያ የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) ና ንዑስ አንቀጽ 3 አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) እና የአዋጁን አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካችዎች የሥራ ስንብት ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
3. ተጠሪ ለአመልካችዎች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40 ንዑስ አንቀጽ 1 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በማስላት የሥራ ስንብት ክፍያ ይክፈላቸው በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የ/ማ

የሰበር መ/ቁ 105555

መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** 1.መፍትሃ ሙሜ
2. ናቶሊ መሃመድ ነጂብ } የቀረበ የለም
3. ሐናን መሃመድ ነጂብ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዑስማን ዓሊ - ጠበቃ ይማጅ ዮኒስ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሁኖ የጉዳት ካሣ ክፍያን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ የ1ኛ አመልካች ህጋዊ ባለቤት የሌሎች አመልካቾች ወላጅ አባት የሆኑት ሟች መሃመድ ነጂብ በተጠሪ በሠራተኛነት ተቀጥረው በማገልግል ላይ እያሉ የተጠሪ ንብረት የሆነውንና የሻንሲ ቁጥር JAAKP-34HbB7P5165፣የሞተር ቁጥሩ 4HG1-865627 የሆነና የሰሌዳ ቁጥር ያልወጣለትን አይሱዙ ተሽከርካሪ ከድሬዳዋ አዲስ አበባ ለማድረስ በማሽከርከር ላይ እንዳሉ ተጠሪ በእሩምታ ጥይት ተተኩሶባቸው ሕይወታቸው በማለፉየጉዳት ካሳ 903.000.00(ዘጠኝ መቶ ሰለሳ ሺ.ህ) ብር እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው:: የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነት ቀርበው ከሟች ጋር የስራ ቅጥር ውል የሌላቸው መሆኑንና ሟቹ በራሳቸው ኃላፊነትና መሪነት ለተለያዩ ሰዎች የሙያ አገልግሎት የሚሰጡ እንጂየተጠሪ ተቀጣሪ ያለመሆናቸውን፣ግንኙነቱ የሙያ አገልግሎት በመሆኑ ሊገዛ የሚገባው በፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ነው በማለት ክሱ ውድቅ እንዲሆንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር እና ማስረጃዎችን ከሠማ በኂላ በተጠሪ በኩል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረቡትን የክርክር ነጥቦች ውድቅ በማድረግ በሟችና በተጠሪ መካከል የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል የሚል ድምዳሜ ደርሶ የጉዳት ካሣውን መጠንን በተመለከተም የሟቹ የወር ደመወዝ ብር 12,000.00(አስራ ሁለት ሺ.ህ) መሆኑን መገንዘቡን ጠቅሶ በዚሁ ወርሃዊ የደመወዝ መጠን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(3) የሞት ጉዳት ካሳው ሲሳላ ብር 720,000.00 (ሰባት መቶ ሃያ ሺ.ህ) እንደሚሆንና

የቀብር ማስፈጸሚያም የሁለት ወር ደመወዝ ብር 24,000.00 ሊያዝ እንደሚገባ ገልፆ በድምሩ ብር 744,000.00(ሰባት መቶ አርባ አራት ሺህ ብር) ካሳ ለአመልካቾች ሊከፈል እንደሚገባ፣ አከፋፈሉን በተመለከተም ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ 50% የሟች ሚስት ለሆኑት ለአሁኗ 1ኛ አመልካች፣ ቀሪው 50% ደግሞ ለሟች ተወላጆች ለአሁኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ሊከፈል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡በጉዳት ካሳ መጠኑ ላይ 10% ደግሞ ለጠበቃ አበል እንዲከፈል ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በሟች እና በተጠሪ መካከል ያለው ግንኙነት የአሰሪና ሠራተኛ አይደለም፣ ሟች በራሳቸው ኃላፊነትና መሪነት ስራውን ሲሰሩ የነበሩ ናቸው በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም በፃፉት 4/አራት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡-ሟች ሹፌር ሁነው ለተጠሪ ሲሰሩ የነበሩ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ በራሳቸው ኃላፊነትና መሪነት የሙያ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ናቸው ተብሎ ግንኙነቱ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህግ አይገዛም ሲባል የተወሰነው ውሳኔ ስለሙያ አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተቀመጠውን መስፈርት ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ እና የቃል ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ጭብጦች፡-

1. በተጠሪ እና በሟች መካከል የነበረው ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች አግባብ የሚገዛ ነው? ወይስ አይደለም?
2. ከተባለስ የጉዳት ካሳ መጠኑ ምን ያህል ሊሆን ይገባል? የሚሉት ሁነው አግኝተናል፡፡

<u>**የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-**</u>

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች ህይወታቸው ያለፈው በሹፌነታቸው የተጠሪ ንብረት የሆነውን መኪና ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ በማሽከርከር ላይ እንዳሉ በተከፈተባቸው እሩምታ ተኩስ መሆኑን፣ሟች አንድ ጊዜ መኪና ሲያደርስ ብር 800.00 (ስምንት መቶ) ብር ለመከፈል ተጠሪ መስማማታቸውን ተጠሪ ባቀረቡት ክርክርም ሆነ የአመልካቾች ምስክሮች መረጋገጡን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው ላይ በግልጽ ያሰፈረው ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ በሟችና በተጠሪ መካከል እንደዚህ አይነት ስምምነት የተደረገው ከሚያዚያ ወር 2002 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑንና የሞት አደጋው የደረሰው ደግሞ የካቲት 08 ቀን 2003 ዓ/ም ስለመሆኑ በአመልካቾች ማስረጃዎች የተነገረ መሆኑንም ከስር ከበታች ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ይዘት ተመልክተናል፡፡

ይህንኑ ለመመለስም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አሰሪና ሰራተኛ ማን ነው የሚለውን ጉዳይ መመልከቱ የግድ ይላል፡፡ ይህ ጥያቄ ምላሽ ሊያገኝ የሚችለውም በአዋጁ የሚገዙት የትኞቹ አሰሪዎች እና ሰራተኞች ናቸው? የሚለው ጥያቄ መሰረት በማድረግ መሆኑ ይታመናል፡፡

በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 377/1996 በአንቀፅ 2/3/ ስር ሰራተኛ ማለት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 ስር በተመለከተው መሰረት ከአሰሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው በማለት በግልፅ ያስቀምጣል። በመሆኑም ይህ ሰራተኛ ለአሰሪው በአሰሪው ቁጥጥር ስር ሁኖ አሰሪው በሚከፍለው ደሞዝ በራሱ የጉልበት ወይም የእውቀት አገልግሎት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የሚሰጥ መሆኑን አዋጅ ያስገነዝባል። በሌላ በኩል አዋጁ በአንቀፅ 2/1/ ስር አሰሪ ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 በተመለከተው መሰረት ቀጥሮ የሚያሰራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ሊሆን እንደሚችል በመግለፅ ድርጅት የሆነውን አሰሪ በማየት አሰሪ ማን ነው? የሚለውን ጥያቄውን ለመፍታት የሚያስችል መሆኑ የሚያስረዳ ነው። ከዚህ አንፃር ጥያቄውን ስንመለከተውም አሰሪው ግለሰብ ወይም ድርጅት ሲሆን የስራ ውሉ ግንኙነት በአዋጅ የሚገዛ መሆኑን፣ አሰሪው ከነዚህ ውጭ ከሆነ እንደሁኔታው የሌሎች ህጎች ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው መሆኑን ሕጉ የሚያመለክት መሆኑን መረዳት የምንችለው ጉዳይ ይሆናል። በአዋጁ ስለሰራተኛ የተቀመጠው ትርጉም የሚያሳየው በአዋጁ አንቀጽ 4 በተመለከተው መሰረት ከአሰሪ ጋር በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ መሆኑን አንቀጽ 2(3) በግልጽ ያሳያል። በዚህ ድንጋጌ ይዘት አንድን ሰው ሰራተኛ ነው ለማለት በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነት መኖሩና በአዋጁ አንቀጽ 4 ድንጋጌ አግባብ መሰረት ሰራተኛው አገልግሎት ለመስጠት መስማማቱ፣ሰራተኛው አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑንና ሰራተኛው ሊሰጥ የሚገባውን አገልግሎት አይነት፣ የት አገልግሎቱን መስጠት እንደአለበት፣አገልግሎቱን መቼ ሊያከናውነው እንደሚገባና እንዴት ማከናወን እንደሚኖርበት አሰሪው የመቆጣጣር ስልጣን ያለው መሆኑ መረጋገጥ ያለባቸው መሆኑን ነው። አሰሪው ሰራተኛውን በዚሁ በህጉ በተቀመጠው አግባብ ተቆጣጥሮ ስራውን የሚያሰራ መሆኑ መረጋገጡ አንድ ተዋዋይ ወገን ዋጋ እየተከፈለው የንግድ ስራ ወይም በራሱ የሙያ ኃላፊነት የሚሰራ ስራ ከሚያከናውን ወገን በትክክል ለመለየት የሚረዳ መሆኑም ተቀባይነት ያለው መለኪያ ነው።በአዋጁ ለቅጥር ውሉ ከተሰጠው ትርጉም መካከል አንዱ የደመወዝ ጉዳይ ሲሆን ሰራተኛው ለአሰሪው በገባው ለአሰሪው ጥቅምና በአሰሪው ቁጥጥር ችሎታውንና ጊዜውን በመጠቀም ተገቢውን አገልግሎት ለአሰሪው ለመስጠት ግዴታ የሚገባው አሰሪው ለሰራተኛው ተገቢውን የድካም ዋጋ በደመወዝ መልክ የመክፈል ግዴታ ሲገባው። ደመወዝ ደግሞ በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት ሊሆን የሚችል ሁኖ የአከፋፈሉ ጊዜም እንደነገሩ ሁኔታ በየቀኑ፣በየሁለት ቀኑ፣ በየሁለት ሳምንቱ፣በየወሩ፣በተሰራው ስራ መጠን……ወዘተ ሊሆን እንደሚችል ከአዋጁ አንቀጽ 4 እና 58 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው።በመሆኑም በእነዚህ የአከፋፈል ጊዜያት ወይ ዘዴዎች ደመወዝ የመከፈሉ ሁኔታ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በተመሰረተው የቅጥር ሁኔታ ላይ በሕጉ ረገድ ለውጥ የማያስከትል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ሟች ተጠሪ ግለሰብ ከውጪ ከሚያስመጣቸው ተሽከርካሪዎች ውስጥ ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ በማመላለስ አገልግሎት ሲሰጡ እንደነበርና ስራውን የሚሰራው ጊዜና ቦታ መኖሩን፣ይህም በተጠሪው መሪነት ወይም ቁጥጥር ሲከናወን የነበረ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል።ተጠሪ ሟቹ ሲከፈላቸው የነበረው ደወመዝ በቁርጥ መሆኑን ጠቅሰው ከመከራከራቸው ውጪ ሟቹ የሚሰጡትን አገልግሎት በራሳቸው ቁጥጥር ስር ያልነበረ መሆኑን አላስረዱም። የደመወዝ አከፋፈል በቁርጥ መሆኑ ደግሞ የቅጥር ግንኙነት ከላይ በተመለከቱት የአዋጁ ድንጋጌ ስለ ሰራተኛ ማንነት የተቀመጠውን ትርጉም ላለመቀበል የሚያስችል አይደለም። ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ሟች በተጠሪ ቁጥጥር ስር ሁነው የሹፍርና አገልግሎት

ሲሰጡ የነበረ መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ሁኖ እያለ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሟች በራሱ የሙያ ኃላፊነት ሲሰሩ የነበሩ ናቸው በማለት ግንኙነቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 የሚገዛ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ መሻሩ በሕጉ ስለሰራተኛ ማንነት የተቀመጡ መለኪያዎችን በአግባቡ ባላገናዘበ መልኩ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ውሳኔው የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 2(1)(2)፣3(2(ረ))፣ 4 እና 58 ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ የጣሰ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

<u>ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ</u>፡-ሟች የተጠሪ ሠራተኛ ናቸው ከተባለ በስራ ላይ እያሉ ሕይወታቸው ማለፉ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ በስራ ምክንያት ለሚመጡ ጉዳቶች አሠሪው ሀላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ በስራ ምክንያት የሚመጣ ጉዳት ከሆነ አሠሪው ኃላፊነቱን እንዲወስድ የተደረገ ሲሆን በአዋጁም በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ መሆኑን በቁጥር 95(2) ደንግጓል በአዋጅ አንቀጽ 96(1) "አሠራው ጥፋት ባይኖረውም….." ተብሎ መመልከቱ የአሠሪው የኃላፊነት ዓይነት ጥፋት ሣይኖር ኃፊነት /Strict Liability or Liability in the absence of Fault/ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ አሠሪው ከዚህ ዓይነት ኃላፊነት የሚድነው ጉዳት የደረሠበት ሠራተኛ ሆነ ብሎ በራሡ ላይ ያደረሠው ጉዳት መሆኑን ማስረዳት ሲችል ስለመሆኑ አንቀጽ 98(2) ያስገነዝባል፡፡ሆነ ብሎ ያደረሠው ጉዳት የሚባሉት ሁኔታዎችም ሠራተኛው አስቀድሞ በግል የተሠጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎችን መጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን መተላለፍ ወይም አካሉን ወይም አእምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ እፅ ሠክሮ በሥራ ላይ መገኘት መሆናቸውን ህጉ በቁጥር 96(2(ሀ እና ለ)) ስር አመላክቷል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 97(1) ድንጋጌ ሲታይም አንድን አደጋ በስራ ላይ የደረሠ ነው ለማለት ሠራተኛው ስራውን በማከናወን ላይ እያለ ወይም ከስራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሡ ውጭ በሆነ ምክንያት ወይም ስራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ በማንኛውም ክፍል ተፈጥሯዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት የደረሠበት ጉዳት ስለመሆኑ መርሁን ያስቀመጠ ሲሆን ይኸው ድንጋጌ ከፊደል (ሀ) እስከ ፊደል (መ) በተመለከቱት ንዑስ ድንጋጌዎች የተመለከቱት ምክንያቶች በስራ ላይ የደረሠ አደጋ ተብለው የሚጨመሩ ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ ስለሆነም በመርሁ መሠረት ሠራተኛው የጉዳት ካሣ ለማግኘት ማሣየት የሚጠበቅበት አደጋው ስራውን በማከናወን ላይ እያለ የደረሠ መሆኑን፣ ወይም ደግሞ በራሡ ባልሆነ ምክንያት ግን ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው መልኩ የደረሠበት አደጋ መሆኑን ነው ፡፡ከላይ እንደተገለፀው ከስራ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ህጉ አስቀምጧል፡፡ ለዚህ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በአንቀጽ 97(1(ሐ)) ስር የተመለከተው ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት አሠሪው በመደበው የመጓጓዝ አገልግሎት ሠራተኛው ሲጠቀም ጉዳት ከደረሠ አደጋው በስራ ላይ እንደደረሠ ተቆጥሮ ኃፊነቱን ከአሠሪው ሊወሰድ የሚገባ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይኸው ድንጋጌ አሠሪው የመደበው የመጓጓዝ አገልግሎት አደጋው ከደረሠበት በአሰሪው ስር ባለው ሌላ ሠራተኛ ወይም 3ኛ ወገን ከሆነ አሰሪው ለተጐጂው ሠራተኛ የጉዳት ካሣ ኃፊነት የሌለበት ስለመሆኑ አያሣይም ይልቁንም ድንጋጌው በአዋጁ አንቀጽ 96(1) ስር ከተመለከተው የአሠሪ አላፊነት ዓይነት ጋር ተዳምሮ ሲታይ አሠሪው አላፊነት ያለበት መሆኑን የሚያጠናክር ነው በሌላ አገላለፅ በሠራተኛው ላይ ጉዳት ያደረሠው ሠራተኛው ወደ ስራ ሲሄድና ከስራ ወጥቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ አሠሪው በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ሲጠቀም አደጋ የደረሠበት መሆኑ ከተረጋገጠ 3ኛ ወገኖች ለአደጋው ያደረጉት አስተዋጽኦ ለአሰሪው መከላከያ

ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም ሟች የተጠሪን መኪና በወቅቱ ሲያሽከረክሩ የነበሩ መሆኑ መረጋገጡ ተጠሪን ነፃ ሊያደርገው የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት ስለሌለ ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊነት ያለባቸው ናቸው፡፡

ተጠሪ ለጉዳቱ ኃላፊ ናቸው ከተባለ የጉዳት ካሣ መጠኑ ምን ያህል ሊሆን ይገባል?፣ ካሳው መክፈል ያለበት ለየትኞቹ የተጐጂ ጥገኞች ነው? የሚለው ጥያቄም በህጉ አግባብ መታየት ያለበት ነው፡፡ ለዚህጥያቄ ምላሽ የሚሠጠው ድንጋጌም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 107(1(ሐ) ስር ተመልክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም በስራ ላይ የሚመጣ ጉዳት የደረሠበት ሠራተኛ የሞተ እንደሆነ ለጥገኞች የጡረታ አበል ወይም ዳረጐት ወይም ካሣ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡የአዋጁ አንቀጽ 110 ድንጋጌ ሲታይም ለሟች ሠራተኛ ጥገኞች የሚከፍሉትን የክፍያ ዓይነቶችንና ጥገኛ የሚባሉትን ወገኖች በንዑስ ቁጥር አንድና ሁለት በግልፅ ዘርዝሯል፡፡ በዚህም መሠረት ማንኛውም ሠራተኛ ወይም ለማጅ ሠራተኛ በስራ ምክንያት በደረሠበት ጉዳት የተነሣ የሞተ እንደሆነ የጉዳት ካሣ ለጥገኞች፣ የቀብር ሥነ ሥርዓት ወጪ እንደሚከፈልና ጥገኞች የሚባሉትም የሟች ህጋዊ ባል ወይም ሚስት፣ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ የሟች ልጆችና በሟች ሠራተኛ ድጋፍ ይረዱ የነበሩ የሟች ወላጆች ስለመሆናቸው ተመልክቷል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም 1ኛ አመልካች የሟች ሚስት፣ ሌሎች ተጠሪዎች ደግሞ ተወላጅ ናቸው፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በህጉ አግባብም የሟች ጥገኛ መሆናቸው ስለተረጋገጠ የጉዳት ካሣ የሚገባቸው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የጉዳት ካሳ መጠኑም በሰራተኛው በስራ ላይ እያለ የሞተ እንደሆነ የሰራተኛው የዓመት ደሞዝ በአምስት ተባዝቶ የሚከፈል እንደሆነ አንቀፅ 110(3) ተመልክቷል፡፡ይህንኑ ለመወሰን ደግሞ የሰራተኛው ደመወዝ መጠኑ በትክክል ሊታወቅ ይገባል፡፡በተያዘው ጉዳይ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሟችን ደመወዝ መጠን በወር 12,000.00 ያደረገው በወር ውስጥ አስራ አምስት ቀናትን ለተጠሪ አገልግሎት ለመስጠት ይችላሉ በሚል መነሻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ረገድ በግልጽ የቀረበ ማስረጃ የለም፡፡በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠው ሟች ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ ለሚያደርሱት አንድ ተሽከርካሪ ብር 800.00(ስምንት መቶ ) የሚከፈላቸው መሆኑ ነው፡፡ይህ ደግሞ ሟች በወር አስራ አምስት ቀናት ሙሉ ስራውን ይሰራሉ ተብሎ ስላልተረጋገጠ የወርሃዊ ደመወዝ መጠን በብር 800.00 ሊታሰብ የሚገባው ሁኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም ይህ ችሎት የሟች ወርሃዊ ደመወዝ ከብር 3200.00 ሊበልጥ የሚችልበትን አግባብ አላገኘም፡፡ ይኼው የደመወዝ መጠን መሰረት ተደርጎ አመታዊ ደመወዝ ሲሰላ ደግሞ ብር 38,400.00(ሰላሳ ስምንት ሺህ አራት መቶ ብር) ሁኖ በአዋጁ አንቀጽ 110(3) መሰረት የአምስት ዓመቱ ሲሰላ ብር 192,000.00(አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ ብር) የጉዳት ካሳ ሊሆን የሚገባው ሁኖ አግኝተናል፡፡

የቀብር ሥርዓት ማስፈፀሚያ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(1(ለ) መሠረት ሲሰላም የሁለት ወር ደመወዝ ብር 6,400.00(ስድስት ሺህ አራት መቶ ብር) መሆን ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

በአጠቃላይ 198,400.00 (አንድ መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አራት መቶ ብር) የሟች ጥገኛ ለሆኑት ለአሁኑ አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(3) እና (4) ስር በተመለከተው

አግባብ የሚከፈል የጉዳት ካሣ መጠን ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ፣ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ደግሞ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለባቸው በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. በፌዴራሉ ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 09770 ሐምሌ 23 ቀን 2006 ዓ/ም ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 38410 ጥር 26 ቀን 2006 ዓ.ም እና መጋቢት 29 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
3. በሟች እና በተጠሪ መካከል የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ውል አለ፣ ሟቹ የሞቱት በስራ ላይ እያሉ በመሆኑ ለሟቹ ጥገኞች የሞት ጉዳት ካሳ የሟቹ የአምስት አመት ደመወዝና የሁለት ወር ደመወዝ ለቀብር ስነ ስርዓት ማስፈፀሚያ ተጠሪ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው ብለናል፡፡
4. ተጠሪ ለአመልካቾች የሚከፍሉት የካሳ መጠንም ብር 198,400.00(አንድ መቶ ዘጠናስምንት ሺህ አራት መቶ) ሁኖ አከፋፈሉም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(3(ሀ) ((ለ)) በተመለከተው አግባብ 50% ለ1ኛ አመልካች (የሟች ሚስት) ቀሪው 50% ደግሞ ለሟች ልጆች (2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች) ሊሆን ይገባል ብለናል፡፡ የጠበቃ አበል በዚህ ችሎት በተወሰነው የገንዘብ መጠን 10% ተጠሪ ለአመልካቾች ሊተኩ ይገባል ብለናል፡፡
5. ሌሎች ወጪና ኪሳራዎች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰበር/መ/ቁ 101736

መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-**አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** ግዮን ኢንዱስትሪያልና ኮሜርሻል ኃ/የተ/የግል ማህበር ነገረ ፈጅ በዛዬ ሲያምረኝ

**ተጠሪ፡-** አቶ አዲስ አለም ሀ/ኪሮስ ጠበቃ ውቤ አለነ አልቀረቡም

**መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል።**

**ፍርድ**

ጉዳዩ ከአሠሪና ሰራተኛ የስራ ውል መቋረጥ ጋር የተያያዘ ሲሆን የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ነው። አመልካች በሥር የፌዴራል የመጀመሪያ እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጡ ውሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን የቀረበ ነው።

የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘት፡- በአመልካች ድርጅት ከመጋቢት 23/2005 ዓ/ም ጀምሮ በወር 2650 ብር እየተከፈላቸው በአሽከርካሪነት የስራ መደብ ሲሰሩ እንደ ነበር፣ አመልካች ያለ ምንም ጥፋትና ማስጠንቀቂያ የሥራ ውላቸውን ያቋረጡ በመሆኑ ስንበቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ በሕግ የተፈቀዱ ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲወስንላቸው ማመልከታቸውን የሚያሳይ ነው።

አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገሩም ተጠሪ በጡረታ የተገለሉ በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው እንዲባልለት፤ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ስለሆነ የሥራ ስንብት ክፍያ የመጠየቅ መብት እንደሌላቸው የካሳ እና ወደ ሥራ ልመለስ ጥያቄ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ተከራክሯል።

የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በተጠሪ የቀረበው ወደ ሥራ ልመለስ ካሳም ይከፈልኝ ጥያቄ በይርጋ የታገደ ስለመሆኑ፤ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ በመሆናቸው የሥራ ስንብት ክፍያ እንደ ማይገባቸው፤ የዘገየ ክፍያ ጥያቄ በተመለከተም በአመልካች የታመነው የፕሮፊደንት ፈንድ እና የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተቀይሮ የተከፈላቸው መሆኑ በመረጋገጡ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው፤

አመልካች ተጠሪን በጡረታ የተገለሉ ናቸው ይበል እንጂ ከግል ድርጅቶች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በተገኘው መረጃ መሰረት በጡረታ መገለላቸው አናውቅም በማለት መልስ በመስጠቱ እና ያለ ማስጠንቀቂያ ከሥራ በመሰናበታቸው ምክንያት የ3 ወር ደመወዝ ብር 7950 እንዲከፈለቸው ወስኗል፡፡

አመልካች እና ተጠሪ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ የስር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መነሻም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ የቀረበ ነው፡፡ ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት የጽሑፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው የጠቀሰው መሰረታዊ ነጥብ ተጠሪ በጡረታ የተገለሉ በመሆናቸው ሰንብቱ በሕግ አግባብ የተከናወነ መሆኑ እየታወቀ የማስጠንቀቂያ ጊዜ 3 ወር ደመወዝ እንዲከፈል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው 60 ዓመት ካለፈባቸው በኃላ በአመልካች ድርጅት ይሰሩ እንደነበር ለስንብቱ ምክንያት ጡረታ ሳይሆን በግብታዊ መንገድ የተወሰደ እርምጃ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና አመልክቷል፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም የሰበር አቤቱታው የሚያጠናክር ነው፡፡

የሥር የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክር ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ፤ ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር አግባብነት ከላቸው ድንጋጌዎች እና ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመረነውም አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የተጠሪ የቅጥር ውል በጡረታ በመገለላቸው ምክንያት በሕጉ አግባብ መቋረጡን መሠረት በማድረግ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ዕድሜያቸው 60 ዓመት ከሞላ በኂላም በሥራ መደባቸው ላይ መቀጠላቸውን እና ስንብቱ ግብታዊ መሆኑን ነው፡፡ የሥር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ አልተሰጣቸውም ለማለት እንደ መነሻ የወሰደው የግል ድርጅት ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ በጡረታ የተገለሉ ስለመሆኑ አናውቅም የሚል መልስ በመስጠቱ ምክንያት ነው ተጠሪ 60 ዓመት የሞላቸው ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የስራ ውል በሕግ ከሚቋረጥባቸው መንገዶች እንደ ሠራተኛው አግባብ ባለው ሕግ መሰረት በጡረታ ሲገለል እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር 377/ 1996 አንቀጽ 24 (3) በግልጽ ተደንጓል፡፡ የግል ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 17(1) የሠራተኛው የጡረታ መውጫ ዕድሜ 60 ዓመት መሆኑን ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ 60 ዓመት የሞላቸው ቢሆንም የቅጥር ውሉ እስከ ቀጠለ ድረስ ከሥር ለማሰናበት ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ እየተከራከሩ ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰራተኛ በሕግ የተቀመጠው የጡረታ መውጫ ዕድሜ ካለፈ በኃላ ሥራ ቢቀጥል ወይም እንደገና ተቀጥሮ ቢሰራ ያለው ሕጋዊ ውጤት ምንድነው? የሚለውን ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ አመልካች ለሰንብቱ መነሻ ያደረገው ተጠሪ 60 ዓመት የሞላቸው በመሆኑ በጡረታ ተገለዋል በሚል ነው፡፡ ክፍያ በተመለከተም በአመልካች የታመነው የፕሮፊደንት ፈንድ እና የአመት ዕረፍት በገንዘብ ተቀይሮ የተከፈላቸው ስለመሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ አንድ ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ከለፈበት በኂላ በሥራው ቢቀጥል አሰሪው በሕጉ አግባብ ሠራተኛውን ማስናበት እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 24(3) ተመልክቷል፡፡ አሰሪው ምርታማነቱ እና የገበያ ተዋዋዳሪነቱ ለማስቀጠል የሚችለው በጡረታ የተገለሉ ሠራተኞች በሕጉ አግባብ እያሰናበተ በአዲስ ኃይል እየተካ ሲሄድ መሆኑ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በጡረታ የተገለለ ሰው ስራ መስራት አይችልም የሚባል ባይሆንም አንድ አሰሪ በጡረታ

የተገለለን ሠራተኛ በድጋሚ ላልተወሰነ ጊዜ ቀጥሮ ያሰራል ለማለት እንደማይቻል የሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 18832 ህዳር 3 ቀን 2000 ዓ/ም አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል። ይህ አሰገዳጅ ውሳኔ ደግሞ በሁሉም ደረጃ ላይ በሚገኙ ፍርድ ቤቶች ተፈፃሚነት እንዳለው በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2(1) ስር ተደንግጓል።

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ዕድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ መሆኑ ተረጋግጧል። አመልካች ድርጅት ከተጠሪ ጋር የነበረው ግንኙነት በሕጉ አግባብ አቋርጠዋል። ይህ ከሆነ ደግሞ ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ መስጠት ይገባው ነበር ለማለት አይቻልም። ምክንያቱም አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረው የቅጥር ውል ሕጉ በደነገገው የጡረታ መውጫ ዕድሜ መሰረት የተቋረጠ በመሆኑ ነው። በሕጉ አግባብ የተቋረጠው የቅጥር ውል ደግሞ አሰሪ የማሰጠንቀቂያ ጊዜ አልሰጠሁም በሚል ምክንያት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈል አይገደድም። ተጠሪ 60 ዓመት ከሞላቸው በኃላ በሥራ ገበታቸው መቆየታቸው በአመልካች የተለየ ግዴታ የሚጥል አይደለም።

በዚህ መሠረት የስር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የ3 ወር ደመወዝ ብር 7950 እንዲከፈላቸው መወሰኑ እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

## ውሳኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 31577 በ27/10/2005 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 136076 በ18/09/2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ ተሽሯል።
2. አመልካች የተጠሪ የቅጥር ውል ያቋረጠው በሕጉ አግበብ ነው ብለናል። አመልካች ለተጠሪ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የ3 ወር ደመወዝ ብር 7950 ሊከፈል አይገባም በማለት ወስነናል።
3. ወጪና ኪሳራ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል።

## ትዕዛዝ

1. በዚህ ፍ/ቤት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል። ይፃፍ።
2. የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ። መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሩ/ለ

# ውል

ሰ/መ/ቁ.96858

ቀን 26/03/2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ አብቢልክሽ ገለታ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ዶ/ር ትግስት ቦርጋ - ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የኪራይ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄን መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው። የተጠሪ ክስ መጋቢት 10 ቀን 2004 ዓ/ም የተጻፈ ሆኖ ይዘቱም ህዳር 19 ቀን 2003 ዓ/ም በተደረገ የኪራይ ውል አመልካች /የስር ተከሳሽ/ የተጠሪ /የስር ከሳሽ/ የሆነውን ንብረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በንፋስ ስልክ ክፍለ ከተማ 522 የሆነ መኖሪያ ቤት በየወሩ ብር 2000.00 /ሁለት ሺህ ብር/ እየከፈሉ ለሶስት ወር ተጠቅመው ሊለቁና የተጠቀሙበትን የውሃና የመብራት ወጪ ከፍለው ቤቱን ለማስረከብ ግዴታ የገቡ መሆኑን ገልጸውና በግዴታው መሰረት ቤቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን፣ በዚህም ምክንያት ተጠሪ በህጋዊ ወኪላቸው በኩል ለአመልካች ታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ/ም ቤቱን አመልካች እንዲለቁ፣ የማይለቁ ከሆነ ደግሞ በየወሩ ብር 5000.00 /አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍሉ ማስጠንቀቂያ የሰጧቸው ቢሆንም ቤቱን ያልለቀቁላቸው መሆኑን ዘርዝረው አመልካች ያለባቸውን የሁለት ወር ከአስር ቀናት ውዝፍ ኪራይ ብር 13,499.00 እንዲከፍሉና ቤቱን እንዲያስረክቧቸው፣ ቤቱን እስከሚያስረክቡ ድረስ ያለውን ኪራይም እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል። የአሁኗ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ህዳር 19 ቀን 2003 ዓ/ም የተደረገው የኪራይ ውል መኖሩን ሳይክዱ የቤቱን የኪራይ መጠን ብር 5000.00 ስለመሆኑ ተሰጠ የተባለውን ማስጠንቀቂያ ግን ከተጠሪ ህጋዊ ወኪል ያልተሰጣቸውና አስገዳጅነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ለአመልካች ታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጠ የተባለው ማስጠንቀቂያ በተጠሪ ህጋዊ ወኪል የተሰጠ መሆን ያለመሆኑን ከአጣራ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ ማስጠንቀቂያ ለአመልካች ሲሰጥ የተጠሪ ጠበቃ ህጋዊ ውክልና ነበራቸው ባይባልም አመልካች የተጠሪ ፍላጎት መሆኑን ያወቁ መሆኑ መረጋገጡን ደምድሞ እና ከታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ያለው ግንኙነት ላልተወሰነ ጊዜ እንደታደሰ የሚቆጠር መሆኑን

በፍ/ብ/ህ/ቁ.2968(1) መደንገጉን ፣ በአከራይ ለተከራይ በፈለገው ጊዜ ቤቱን የማስለቀቅ ህጋዊ መብት ያለው መሆኑ በህጉ የተጠበቀለት መብት መሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2966 የተደነገገ መሆኑ በዋቢነት ጠቅሶ አመልካች ለተጠሪ ከታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን እስከሚያስረክቡበት ጊዜ ድረስ የሚታሰብ ወርሃዊ ኪራይ ብር 5000.00/አምስት ሺህ/ እንዲከፍሉ፣ የተጠቀሙበትን የውሃና የመብራት ወጪም እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ የተጠሪ መሆኑን በጊዜው ማወቃቸው በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ማስጠንቀቂያው ከተጠሪ ህጋዊ ወኪል አልተሰጠኝም የሚሉት ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ገልጾ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ለአመልካች በህጉ አግባብ ማስጠንቀቂያ ባልተሰጠበት ሁኔታ የቤቱ ኪራይ በወር 5000.00 /አምስት ሺህ ብር/ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ የኪራይ ገንዘቡ በወር ከብር 2000.00 ወደ ብር 5000.00 ብር ከፍ ማለቱ ተረጋግጧል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና ተጠሪ ህዳር 19 ቀን 2003 ዓ/ም ያደረጉት የኪራይ ውል የተወሰነ የኪራይ ዘመን የተቀመጠለትና ይህ ጊዜም ያለፈ መሆኑን፣ ጊዜው ካለፈ ስለ ኪራዩ መጨመር ማስጠንቀቂያ ከደረሳቸው በኃላም አመልካች የተጠሪን መኖሪያ ቤት መጠቀም መቀጠላቸውን፣ ተጠሪ አመልካች የኪራይ ጊዜው ከአለፈ በኃላ መኖሪያ ቤቱን ለተጠቀሙበት ጊዜ በአዲሱ የኪራይ ተመን መሰረት ኪራይ አልተከፈለኝም በማለት የሚከራከሩ መሆኑንና አመልካች አዲሱ የኪራይ ተመን ተጠሪ በወኪሉ በኩል አሳውቀአለሁ ቢሉም ወኪሉ ህጋዊ ውክልና ስላልነበራቸው አመልካች አዲሱን የኪራይ ተመን አውቀዋል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡

አመልካችና ተጠሪ ህዳር 19 ቀን 2003 ዓ/ም ለሶስት ወራት ያደረጉት የኪራይ ውል ዘመን ተጠናቆ አመልካች የተጠሪን ቤት መጠቀም የቀጠሉ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ግንኙነት የፍ/ብ/ህ/ቁ.2968/1/ ድንጋጌን የሚያሟላ የኪራይ ውል ግንኙነት መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በዚህ ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበትን ድምዳሜ ሲመለከተው የፍ/ብ/ህ/ቁ.2968/1/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ በመሆኑ እና አመልካችም በዚህ ረገድ ያቀረቡት ቅሬታ ስለሌለ የሚመለከተው ሆኖ አላገኘውም፡፡

በዚህ ችሎት መታየት ያለበት አቢይ ነጥብ አመልካች እና ተጠሪ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ግንኙነት ነበራቸው ተብሎ ድምዳሜ ከተያዘ አመልካች መኖሪያ ቤቱን ለተጠቀሙበት ጊዜ ሊከፍሉ የሚገባው የኪራይ ገንዘብ መጠን ምን ያህል ነው? የሚል ነው፡፡ አመልካች የኪራይ መጠኑንን ያሻሻለው የታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ/ም ማስጠንቀቂያ ከተጠሪ ህጋዊ ወኪል የተሰጠኝ አይደለም ቢሉም ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው አመልካች የኪራዩ መጠን እንዲጨመር የተደረገው በአከራዩ ፍላጎት መሆኑን ከማስጠንቀቂያው በኃላ ያወቁ መሆኑ በማስረጃ መረጋገጡን ደምድመዋል፡፡ ይህ ችሎት ደግሞ ይህን የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የያዙትን ድምዳሜ

እንዳለ የሚቀበለው መሆኑን ከኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የኪራይ ተመኑ ከብር 2000.00 ወደ ብር 5000.00/አምስት ሺህ/ ከፍ ስለማለቱ ተገቢው ማስጠንቀቂያ አልደረሰኝም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የሚሰጠው ሁኖ አልተገኘም፡፡

አመልካች ወርሃዊ የኪራይ ተመኑ ከፍ መደረጉን አከራይ ያሳወቃቸው መሆኑን በሚገባ ያውቁ ነበር፣ ቤቱንም መጠቀም ቀጥለዋል ከተባለ ደግሞ አዲሱን የኪራይ ተመን መቀበላቸውን ከፍ/ብ/ህ/ቁ.1684(1) ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች በዚህ አግባብ የኪራይ ተመን መሻሻሉን ከአወቁ በኃላ ቤቱን መጠቀም የቀጠሉ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2952 (2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት በአዲስ የቤት ኪራይ ተመን መሰረት ለቤቱ ባለቤት ኪራዩን ለመክፈል የማይገደዱበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በአጠቃላይ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.70432 ጥር 20 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.131903 ጥቅምት 19 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በግራ ቀኙ መካከል የህዳር 2003 ዓ/ም የኪራይ ውል ካበቃ በኃላ የኪራይ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ ተደርጓል ፣ የኪራይ ተመኑም ወደ ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ ከፍ ማለቱን አመልካች አውቀውታል ተብሎ ይህንኑ ገንዘብ ከታህሳስ 19 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ቤቱን እስከሚያስረክቡ ድረስ ለተጠሪ እንዲከፍሉ ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

ጥር 19 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁጥር. 95797

ጥር 20 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ደበበ ድርሪሳ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ -ስራ አስኪያጆች ባለቤት ደበበ ድሪርሣ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፈንታሌ ወረዳ ውሃ ማእድን ኢነርጂ ፅ/ቤት - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ከንጹህ ውሃ ግንባታ ጋር ተያይዞ የተነሳውን የወለድ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ እና በፈንታሌ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ጽ/ቤት ላይ በምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ጋር በ17/08/2002 ዓ/ም በተደረገ የውል ስምምነት መሰረት የንጽህ ውሃ ግንባታ በፈንታሌ ወረዳ ከኒፋ ቀበሌ ውስጥ ለማከናወን ግዴታ ገብቶ በውሉ መሰረት ስራው ተሰርቶና በባለሙያ ተለክቶ የ1ኛ የ2ኛ እና የ3ኛ ዙር የምስክር ወረቀት ተዘጋጅቶ ክፍያ የተፈፀመለት መሆኑን ከዚህ በኋላ የተሰራው ስራም ተለክቶ የ4ኛዙር ላይ ብር 239,828,88 የ5ኛ ዙር ሰርተፊኬት ላይ ብር 131,975,13 ለአመልካች ሊከፈል ይገባል በማለት በባለሙያ ሰርተፊኬት ተዘጋጅቶ ለሥር ከሳሾች ቢደርስም ክፍያውን ለመፈጸም ፈቃደኛ አልሆኑም በማለት የብር 371,803,88 ከተለያዩ የወጪና ኪሳራ ክፍያዎች እንዲሁም ከ20%ቅጣት ጋር ሊወሰንልኝ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቋል ፡፡ የአሁኑ ተጠሪም አመልካች ስራውን እንደውሉ ያለመፈጸሙንና ውሉን በጊዜ ገደቡ ያለማጠናቀቁን ጠቅሶ ለአመልካች ክፍያ ለመፈጸም የሚገደድበት አግባብ ያለመኖሩን ዘርዝሮ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካችን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ያደረገው ሲሆን የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአሁኑን አመልካች ለክሱ ኃላፊ አድርጎ ብር 412,668,41(አራት መቶ አስራ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ስምንት ብር ከአርባ አንድ ሳንቲም)ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ወጪና ኪሳራን በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ያለ ሲሆን ወለድና ቅጣትን በተመለከተ ግን የአሁን አመልካች ጠይቆ ውሉ የተደናቀፈው በተጠሪ ስላልሆነ መክፈል ያለበትን ገንዘብ አለመክፈሉ ቅጣትን ወለድን የሚያስከፍለው አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ወለድና ቅጣትን እንዲሁም ወጪና ኪሳራን በተመለከተ በተሰጠው የውሳኔ ክፍል የአሁኑ አመልካች ቅር

በመሰኘት የሰበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ወጪና ኪሳራን በተመለከተ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር ይግባኝ ሰሚው ችሎት ወጪና ኪሳራውን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 462 እና ተከታይ ድንጋጌዎች አግባብ ግራቀኙ አከራክሮ እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343(1)መሰረት መልሶለታል የአሁኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ወለድን በተመለከተ ዳኝነት ያለመስጠቱ ያላግባብ ነው በሚል ሲሆን ጉዳዩ ተመርምሮም የአመልካች የወለድ ይከፈልኝ ጥያቄ መታለፉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ተይዞ ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በገባው የውል ግዴታ መሰረት ከ1ኛ እስከ 3ኛ ዙር ያሉትን ክፍያዎችን በአግባቡ የከፈለ ሁኖ በ4ኛ እና 5ኛ ዙር ክፍያዎች ግን ከአመልካች ጋር በውል በተቀመጡ መሰረታዊ ጉደዮች ላይ ወደ ክርክር የተገባ በመሆኑና የሥራው ጊዜም ከ72 ቀናት ያለፈ በመሆኑ ሳይከፈል ለቀየው ገንዘብ ወለድ የሚከፍልበት የሕግ ምክንያት የለም ሲል ተከራክሯል አመልካችም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል ፡፡

አመልካች ለሰራው ስራ 4ኛ እና 5ኛ ዙር ክፍያ እንደሚገባው በባለሙያሰርቲፊኬት የተረጋገጠለት ቢሆንም ተጠሪ ጋር ውሉ በአግባቡ አልተከናወነም በሚል ወደ ክርክር የገቡ መሆኑ የክርክሩ ሂደት ያሳይል አመልካች በዚህ ሰበር ደረጃ የሚከራከረው ተጠሪ ሕጋዊ ወለድ የማይከፍልበት አግባብ የለም በሚል ሲሆን ለዚህም እንደ ሕጋዊ ምክንያት የሚያቀርበው ክርክር የተነሳበት ገንዘብ መጠን ከተሰራው ስራ ጋር በማመዛዘን የመስሪያ ቤቱ ባለሙያና ምድብ ሰራተኛ የክፍያ ሰርተፊኬት አዘጋጅቶ ካቀረበው ጊዜ ጀምሮ የሚታወቅ እዳ ነው የሚል ነው፡፡

ይሁን እንጂ በውሉ መሰረት ስራው መሰራት ያለመሰራቱ ላይ ግራ ቀኙ ሊተማመኑ ባለመቻሉ ወደ ክርክር የገቡ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል ፡፡ ይህ ደግሞ በአመልካች ላይ የጥቅም መቀነስን የሚያስከትል መሆኑ ግልፅ ቢሆንም ስራው በውሉ መሰረት መሰራት ያለመስራቱ አከራካሪ እስከሆነ ድረስ የታወቀ እዳ እያለ ተጠሪ ለአመልካች ሳይከፍል ዘግይቷል ሊባል የሚችል አይደለም ፡፡ አመልካች ላይ በተጠሪ ያልተገባ የውል ተግባር ቀጥተኛ የሆነ የገንዘብ ኪሳራ የደረሰባቸው መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡

ወለድ በሕጉ አግባብ የተዘረጋው ስርዓት እንደተጠበቀ ሁኖ በስምምነት ወይም ያለስምምነት ሊከፍል የሚችል ገንዘብ ነው፡፡ወለድ ተበዳሪ የወሰደውን ገንዘብ ወይም እቃ በወቅቱ ባለመመለሱ የተነሳ የሚከፈል የገንዘብ ካሳ ነው፡፡ በኮንስትራክሽን ስራ ውልም ወለድ ሊጠየቅበት የሚችል አግባብ ያለ ሲሆን አላማውም የገንዘብ ኪሳራን ማካካሻ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ምክንያቱም ከላይ ከተገለጸው የወለድ አይነት ሌላው አይነት ወለድ አንድ ሰው ግዴታውን ባለመፈፀሙ ወይም በማዘግየቱ የተነሳ የሚከፈለው ካሳ እኩያ መሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1803 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም ወለድ ለገንዘብ ብድር ብቻ እንዲከፈል የሚደረግ የካሳ የአይነት ሳይሆን ለግዴታ ባለመፈጸም ወይም ማዘገየት የተነሳ የሚከፈል ካሳ በመሆኑ ይህ ሲረጋገጥ ብቻ የሚከፈል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከት አመልካች የንጹህ ውሃ ግንባታ ውል ስምምነት ያደረገው ከአስተዳደር መስሪያ ቤት ጋር ነው፡፡

ከአስተዳደር ውሎች ያለመፈፀም ጋር ተያይዞ የወለድ ጥያቄ የሚቀርብበት አግባብ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3196 እና 3197 ድንጋጌዎች የሚታይ ነው ፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3196 ድንጋጌ ይዘት ሲታይ የወለድ ጥያቄ ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልግ ተገቢነት የሚኖረው የአስተዳደር መስሪያ ቤቱ በውሉ በተመለከተው መሰረት ከአስራ አምስት ቀን በኃላ ለተዋዋዩ ስለ ገንዘቡ አከፋፈል የሚያስፈልገውን የማረጋገጡ ስራ ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ወይም የአስተዳደር መ/ቤት የሚፈለግበትን ገንዘብ የማረጋገጡ ስራ በተፈፀመ በሶስት ወር ውስጥ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ስለመሆኑ ያስገነዝባል የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 3197 ድንጋጌ ደግሞ ተቃራኒ የውል ስምምነት ቢኖርም እንኳን ሳይከፈል የቆየበት ጊዜ ከስድስት ወር በላይ ሲሆን ወይም ውሉን ያደረገው የአስተዳደር መስሪያ ቤት ለመጉዳት ብሎ ያደረገው ወይም ከባድ በሆነ ቸልተኛነት ወይም ጥፋት ያደረገው የአስተዳደር መስሪያ ቤት ለመጉዳት ብሎ ያደረገው ወይም ከባድ በሆነ ቸልተኛነት ወይም ጥፋት ያደረገው ሲሆን ወለድ ሊጠየቅና ተቀባይነት ሊሰጠው እንደሚገባ አስቀምጧል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ እንዲሁም ከወለድ አላማ አንፃር አሁን የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከተው አመልካች ግዴታውን በውሉ በተቀመጠው አግባብ አልፈጸመም በሚል ምክንያት ተጠሪ ክፍያውን ሳይፈጽም የዘገዬ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የካሳ እኩያ የሆነውን ወለድ የሚያገኙበት የሕግ ምክንያት አላገኘንም ፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በተገለፁት ሕጋዊ ምክንያቶች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ፍርድ ቤት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስላላአገኘነው ተከታዩን ወስነናል ፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 159905 ጥቅምት 11 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የአመልካች የወለድ ክፍያ ጥያቄ በመታለፉ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ፤ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

የሰ/መ/ቁ. 103704

ጥር 20/ቀን 2007ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- -------ቀረቡ

ተጠሪ፡- ---------ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በአራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 2 ቤት.ቁ 1314 (ለ)የሆነውን የመንግስት ቤት አመልካች የተከራየውን ንግድ ቤት ለሶስት በመሸንሸን አንዱን በ8000 ብር አከራይቶኝ ሙዝ የመሸጥ ስራ እየሰራሁበት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በመመሪያ ቁ.3/2004 መሰረት የከተማው ግብረ ሀይል ተጠሪ አንዱን ክፍል በመያዝ ለአመልካች አንደኛውን ክፍል በመክፈል እንዲሰጠኝ ተወስኗል፤ ሆኖም የስር አንደኛ ተከሣሽ እኔ በሌለሁበት ዕቃዬን የታሸገውን ቤት በውስጡ ያለውን ንብረት ተጠሪ እንዲጠቀምበት አድርጓል ፤ንብረቴንም እየተጠቀመበት ነው፡፡ ቤቱንም ወደ መኖሪያ ቤት በመቀየር ይዟል ንብረቴን መረከብ እና የተቋረጠብኝ ገቢን ማስከፈል አልቻልኩም ስለዚህ የንብረት ግምት 4000 እና የተቋረጠ ገቢ ተከፍሎኝ የንግድ ቤቱን ያስረክቡኝ በማለት ጠይቋል፡፡ አመልካች ባቀረቡት መልስ ለተጠሪ ቤት ሸንሽኜ በ8000 አላከራየውም የሀሰት ክስ ነው፡፡ በመመሪያ ቁ.3/2004 መሰረት የኪራይ ውሉ ከእርሳቸው ጋር እንድቀጥል ጉዳዩን የሚመለከተው አካልም የተሳሳተ ግንዛቤ ውስጥ በመክተት ቢጠየቅም አመልካች ለማስፈጸም የተዋቀረውን ግብረሀይል ከቫይረሱ ጋራ መኖሬን የሚያስረዳ ማስረጃ በማቅረቤ የኪራይ ውሉን ከእኔ ጋርእንዲቀጥል ተደርጓል፤ በተጨማሪም ሌላ ገቢ የሌለኝና ወረዳው የወሰነልኝ በመሆኑ ቤቱን ለተጠሪ ላስረክብ አይገባም ፤ ቤት ውስጥ የነበረውን ንብረት ወይም ግምት እና ያጣሁትን ገቢ ይከፈለኝ ለተባለው ማስረጃ ያልቀረበበት በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል መልሱን ሰጥቷል ፡፡ ጉዳዩን ያየው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን በማከራከር አመልካች የኤች አይ ቪ ታማሚ በመሆናቸው ብቻ በመመሪያው ልዩ ድንጋጌ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም፤ በንግድ ቤቱ ቁጥር 1314 በአንደኛው ክፍል እየሰሩበት ገቢ በማግኘት ላይ መሆናቸውን በማረጋገጥ ተጠሪ የአከራካሪውን ቤት አንዱን ክፍል ሊያገኙ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ሌላውን የንብረት ግምትና የታጣ ገቢ ጥያቄ በማስረጃ አልተረጋገጠም ሲል ውድቅ አድርጎታል ፡፡ በቀጣይነት ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት ፍርድ ቤቶችም የስር ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት አጽንቶታል፡፡

የአመልካች አቤቱታም የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማሳረም ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልጹ ፡- በመመሪያ ቁ. 3/2004 መሰረት የኤች.አይ.ቪ. ታማሚ እና ሌላ

ገቢ የሌለኝ መሆኔን አረጋግጫለሁ፤1314(ሀ)(ለ) ሆኖ (ሀ) ለመኖሪያ እየተጠቀምኩበት የትኛውን እንደምካፈል እንኳ አልተለየም ፤በአጠቃላይ ሌላ የገቢ ምንጭ እንዳለኝ የቀረበ ማስረጃ ሳይኖር የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡

በዚህ መሰረት ችሎቱም አመልካች ኤች አይ ቪ ታማሚ እና የገቢ ምንጭ የለኝም ሲሉ ያነሱት ጥያቄ ውድቅ መሆኑን ከመመሪያ ቁ. 3/2004 እና 4/2002 አንቀጽ 6 መሰረት ለማጣራት በጭብጥነት በመያዝ የግራቀኙን መልስና የመልስ መልስ በጽሑፍ በማቀባበል ተከራክረዋል ፡፡

ተጠሪ በሰበር አቤቱታቸው የሚከራከሩት አመልካች የቤት ቁ.1314ን ለመኖሪያነት ከተከራዩ በኃላ ሀ፣ለ፣ሐ በማለት ለተጠሪ 1314(ለ)"ን" አከራይቶኝ ለራሳቸውም ሲሰሩ ነበር ስለዚህ በመመሪያው ቁ.6 አንፃር ጠቅላላውን ያከራዩ ሳይሆን በሌላኛው ቤት ሲነግዱና የገቢ ምንጫቸው ያደረጉት በመሆኑ ኤች አይ ቪ ታማሚ በመሆናቸው ብቻ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይገባም ተብሎ አመልካች የያዙትን እንዲሰሩበት ተደርጎ እኔም በተከራየሁት ተጠቃሚ እንድሆን መወሰኑ ሊጸና ይገባዋል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው በሽተኛ መሆኔ አልተካደም በይዞታዬ ስር አድርጌ ከምጠቀምበት ንግድ ቤት በቀር ሌላ የገቢ ምንጭ የለኝም ፣በመሆኑም ውሳኔው ሊሻር ይገባዋል በማለት ክርክራቸውን አጠናክረዋል ፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን እኛም የግራቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንጻር መርምረናል ፤ በዚህ መሰረት ከተያዘው ጭብጥ በመነሳት እንዳየነው ከተጠቃሾቹ መመሪያዎች አንጻር ልዩ ተጠቃሚ ለመሆን መመሪያ 3/2004 እና ቁ.4/2004 የኤች አይ ቪ ታማሚን አስመልክቶ የተለያየ ድንጋጌ አይታይባቸውም ፡፡ አንድነታቸው ጎልቶ ከመታየቱ በቀር የመመሪያ ቁ.3 አንቀፅ 6 እና መመሪያ ቁ. 4/2004 አንቀጽ 12 የሚሉት ከመንግስት የተከራየው ሰው የኤች አይ.ቪ. ታማሚ ሆኖ እና ሌላ የገቢ ምንጭ ሳይኖረው እና ሲጠቀምበት የነበረውን ቤት አከራይቶ ከተገኘ ይህንኑ አረጋግጦ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል በተያዘው ጉዳይ በተጠቃሹ ቤት ቁ.1314 "ን" አስመልክቶ አመልካች ሸንሽኖ ለተጠሪ አከራይቶና የቀረውን ክፋይ አመልካች ሲጠቀሙበት የነበረ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ እውነታ ነው፡፤ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች በአንደኛው ክፍል ቤት ላይ እየነገዱ መሆናቸውን ሳይክዱ ከዚህ የተለየ ሌላ የገቢ ምንጭ የለኝም ያለኝ ለመሆኑም አልተረጋገጠም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር መመሪያውን ያላገናዘበ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ይዘውት ባሉት ክፍል ተከራይነታቸው ሲቀጥል ተጠሪም የአንደኛውን ክፍል ሊያገኙ ይገባል መባሉን ይህ ችሎትም የሚቀበለው ይሆናል ፡፡

በመጨረሻም ጉዳዩን ያዩት የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እና የይግባኝ ሰሚው አመልካች ሌላ የገቢ ምንጭ ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ የመመሪያው ልዩ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይገባም በማለት የደረሱበት መደምደሚያ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት አልተቻለም ፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 06479 በ 03/7/06 ዓ.ም ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ.ቁ.21839 በቀን 29/8/06 እና በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.22278 በሀምሌ 11 ቀን /2006 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ ጸንቷል፡፡

2. አመልካች የገቢ ምንጭ ስላላቸው የኤች.አይ.ቪ.ታማሚ በመሆናቸው የመመሪያው ልዩ ተጠቃሚ ሊሆኑ አይገባም መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ግራቀኙ የወጪ ኪሳራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

በነሀሴ 08 ቀን 2006 ዓ.ም በዚህ ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 98358

ጥር 05 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡- አልማው ወሌ**

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ -ነገረ ፈጅ ኃይሉ ተሰማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዩጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ጠበቃ ማረን ወንዴ - ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የመድን ውልን መሠረት አድርጎ የቀረበውን የገንዘብ ይተካልኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- የአሁኑ አመልካች ለደንበኛው ለነፃ ኃላፊነቱ የተ.የግል ማህበር ከቱርክ ሀገር ለሚያስመጣቸው 246 ጥቅል ብረቶች ከተጫኑበት ሀገር ተጓጉዞ እስኪመጣ ድረስ ለሚያጋጥም ጉዳት በፖሊሲ ውል ቁጥር 01/ኤም አር ኦኤ/00001/07 የባህር ላይ የጉዞ መድን ሽፋን መስጠቱን፣ተጠሪ የመድን ሽፋን የተሰጣቸውን 246 ጥቅል ብረቶችን ተረክቦ ሆውማ ቤሊ ቪ.ኢኤስቲአር53 በሚባለው መርከብ ከሊአጋ ኢዝሚር ቱርክ አጓጉዞ ጅቡቲ ለማድረስ በባህር እቃ መጫኛ ሰነድ ቁጥር 305/ኤስሲ ግዴታ መግባቱን፣ተጠሪ ጅቡቲ ለማድረስ ግዴታ ከገባባቸው 246 ጥቅል ብረቶች ውስጥ እቃው ጅቡቲ ወደብ ደርሶ ሲራገፍ 11(አስራ አንድ) ጥቅል ብረቶች መጥፋታቸውን፣ ከተጓጓዘው 246 ጥቅል ብረቶች ውስጥ የአመልካች ደንበኛ በ11/04/2004 ዓ/ም 226 ጥቅል አዲስ አበባ ላይ በእቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 10431 መረከቡን፣ቀሪው 20 ጥቅል ብረት ውስጥ 9 ጥቅል ደግሞ ዘግይቶ በ05/06/2004 ዓ/ም በእቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 10999 መረከቡን፣ይህ የተጫነ እቃ መጥፋትና መጉደሉ በጅቡቲ የሰርቬየር ስራ በሚሰራው ገልፍ ኤጄንሲ አገልግሎት የሚባል ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ/ም ማረጋገጡን ገልጾ አመልካች ለደንበኛው የከፈለውን ካሳ ብር 289,527.23 ተጠሪ እንዲተካለት ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለክሱ በሰጠው መልስም፡-የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ያስቀደመ ሲሆን በዚህም መሰረት የአመልካች ክስ እቃው በጅቡቲ ወደብ ላይ መራገፉ ከተረጋገጠበት ከጳጉሜ 03 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ በሚታሰብ በአንድ አመት ይርጋ ጊዜ ውስጥ የሚታገድ መሆኑን የባህር ሕግ ቁጥር 203(1) ድንጋጌ እንደሚያሳይ እንዲሁም አመልካች ክስ ለማቅረብ መብት ወይም ጥቅም የሌለው መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲል ተከራክሯል፡፡

የስር ፍርድ ቤትም በዚህ መልክ የቀረበውን የይርጋ ክርክር በጭብጥነት ይዞ ጉዳዩን በመመርመር እቃው በጅቡቲ ወደብ የተራገፈው ጳጉሜ 03 ቀን 2003 ዓ/ም መሆኑን መነሻ አድርጎ ይርጋውን በመቁጠር የካቲት 05 ቀን 2005 ዓ/ም የቀረበው የአመልካች ክስ በባህር ሕግ ቁጥር 203(1) መሰረት በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ የታገደ ነው በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የመጨረሻ ርክክብ የተደረገው የካቲት 05 ቀን 2004 ዓ/ም ሁኖ እያለና የደንበኛው እቃ መጉደሉም የተገለጸው ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ/ም ሁኖ እያለ የእቃው ርክክብ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ይርጋው ሊቆጠር ይገባል ተብሎ የአመልካች ክስ ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው ነጥብ የአመልካች ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ሊመስርት የቻለው ለደንበኛው ለነፃ ኃላፊነቱ የተ.የግል ማህበር ከቱርክ ሀገር ለሚያስመጣቸው 246 ጥቅል ብረቶች ከተጫኑበት ሀገር ተጓጉዞ እስኪመጣ ድረስ ለሚያጋጥም ጉዳት በፖሊሲ ውል ቁጥር 01/ኤም አር ኦኤ/00001/07 የባህር ላይ የጉዞ መድን ሽፋን መስጠቱን መሰረት አድርጎ ሲሆን በዚህ ጉዞ ሂደት ጠፉ ለተባሉት 11 ጥቅል ብረቶች ለደንበኛው ከፈልኩ የሚለውን ገንዘብ እቃዎቹን የማጓጓዝ ግዴታ አለበት የሚለው ተጠሪ እንዲተካለት ነው፡፡ስለሆነም ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ሕግ የባህር ህግ ሲሆን ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚነት ያለውን የይርጋ ጊዜ የሚያስቀምጠው የህጉ ድንጋጌ ቁጥር 203 ሲሆን ድንጋጌው ሁለት ንዑስ ቁጥሮችን የያዘ ሁኖ የመጀመሪያው ንዑስ ቁጥር ከማመላለሻው ውል ውስጥ የተገኙ መብቶች በይርጋ የሚታገዱት የንግድ እቃውን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ ወይም የማስረከቡ ጉዳይ ሳይፈፀም ቀርቶ እንደሆነ እቃውን ማስረከብ ከሚገባበት ቀን አንስቶ የአንድ አመት ጊዜ ካለፈ በኂላ ነው በማለት አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ አስቀምጧል፡፡የተጠቃሹ ቁጥር ንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ደግሞ ከሂሳብ አከፋፋል ጋር ተያይዞ የሚነሳው ክርክር የሚታገድበትን አግባብ የሚያስቀምጥ ነው፡፡ የባህር ህግ ቁጥር 203 ድንጋጌ የሚገኘው በጭነት ማስታወቂያ የተረጋገጠ ደረሰኝ የማመላለሻ ውልን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች በሚገዛው ክፍል ሲሆን የድንጋጌዎችን ወሰን በተመለከተ በቁጥር 180 ስር ሕግ አውጪ አስቀምጧል፡፡ይህ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር አንድ ስር በክፍሉ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች የሚፀኑት በተለይ በመርከብ ላይ በተጫኑት የንግድ እቃዎች የጭነት ማስታወቂያ ደረሰኝ ወይም ይህን በመሰለ ሌላ አይነት ሰነድ በተረጋገጡ የጭነት ማመላለሻ ውሎች ላይ ብቻ መሆኑን ሲያስቀምጥ የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ሁለት እና ሶስት ደንጋጌዎች ደግሞ እንደቅደም ተከተላቸው የመርከብ መከራየት ውል ሰነድ ባለው ጉዳይ ላይ ተፈፃሚ ሊሆኑ እንደማይችሉና በዚህ ጊዜም ድንጋጌዎቹ ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉበትን ልዩ ሁኔታዎችን የሚያስቀምጡ ናቸው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ጅቡቲ ለማድረስ ግዴታ ከገባባቸው 246 ጥቅል ብረቶች ውስጥ እቃው ጅቡቲ ወደብ ደርሶ የተራገፈው ጳጉሜ 03 ቀን 2003 ዓ/ም ሁኖ በዚህ ጊዜ ከተጓጓዘው 246 ጥቅል ብረቶች ውስጥ የአመልካች ደንበኛ በ11/04/2004 ዓ/ም 226 ጥቅል አዲስ አበባ ላይ በእቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 10431 መረከቡን፣ቀሪው 20 ጥቅል ብረት ውስጥ 9 ጥቅል ደግሞ ዘግይቶ በ05/06/2004 ዓ/ም በእቃ መረከቢያ ሰነድ ቁጥር 10999 መረከቡን ፣ይህ የተጫነ እቃ መጥፋትና መጉደሉ በጅቢቲ የሰርቬየር ስራ በሚሰራው ገልፍ ኤጀንሲ አገልግሎት የሚባል ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ/ም ማረጋገጡንና አመልካች ክስ የመሰረተው የካቲት 05 ቀን 2005 መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡አሁን ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው ጉዳይ በባህር ህጉ ቁጥር 203(1) የተመለከተው የአንድ አመት የይርጋው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ከመቼ ጀምሮ ነው? የሚለው ነው፡፡አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር ስህተት ነው በማለት የሚከራከረው የእቃዎቹ ርክክብ ጊዜ በማስጫኛ ውሉ ላይ አልተገለፀም፣በመጀመሪያው ዙር 226፣ቀጥሎ ደግሞ 9 ጥቅል ብረቶች የተላኩ መሆኑንና ለክሱ መነሻ የሆኑት ቀሪዎቹ 11 ጥቅል ብረቶች መጥፋታቸው የተረጋገጠው ሰኔ 24 ቀን 2004 ዓ/ም ነው በሚል ነው፡፡እንግዲህ ከክርክሩ ይዘት በግልጽ መረዳት የሚቻለው እቃው በባህር ላይ ተጉዞ ጅቡቲ የተራገፈበት አግባብ በአንድ የማስጫኛ ሰነድ ያለመሆኑን ነው ፡፡በአንድ የማስጫኛ ሰነድ እቃዎቹን ተጠሪ ባልተረከበበት ሁኔታ የመጀመሪያው የማራገፊያ ቀን ማለትም ጳጉሜ 03 ቀን 2003 ዓ/ም ከይርጋው መቆጠር መነሻ ቀን የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የመጀመሪያ የርክክብ ቀን የሆነው ታህሳስ 11 ቀን 2004 ዓ/ም ለይርጋው መነሻ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል ማለቱ እቃው በሙሉ አንድ አይነት፣በአንድ የጭነት ሰነድ በአንድ የማጓጓዣ ውል የተጓጓዘ መሆኑን ከክሱ መረዳት ይቻላል በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ከዚሁ ከመጀመሪያው ርክክብ በኋላ 9 ጥቅል ብረትን የአመልካች ደንበኛ የካቲት 05 ቀን 2004 ዓ/ም መረከቡ ያልተካደ ፍሬ ነገር ነው፡፡ስለሆነም ርክክቡ የቆመው ከዚህ ከየካቲት 05 ቀን 2004 ዓ/ም በኋላ በመሆኑ የአመልካች ደንበኛ እቃዎቹ መጥፋታቸውን እርግጠኛ ሊሆኑ ይችላሉ ተብሎ የሚታሰበው ከዚህ ቀን በኋላ እንጂ የመጀመሪያው ርክክብ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ አይደለም፡፡ተጠሪ የባህር ህግ ቁጥር 180(2) ድንጋጌን መሰረት አድርጎ የሚያቀርበው ክርክርም እቃዎቹ ከመርከቡ ላይ ከተጫኑበት አንስቶ እስከሚራገፉበት ጊዜ ብቻ የበህር ህግ ቁጥር 203 ድንጋጌ ተፈፃሚ መሆኑን የሚያስቀምጥ ሲሆን ይህም እቃዎቹ ሙሉ በሙሉ ተጭነው ባልተቆራረጠ ሁኔታ ርክክቡ የሚፈፀምበትን አግባብ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተቀመጠ ድንጋጌ ነው ከሚባል በስተቀር በመርከብ ላይ የተጫኑት እቃዎች በተግባር በተለያዩ ጊዜያት እየተራገፉ ርክክቡም በተለያዩ ጊዜያት ሲደረግ የነበረበትን ሁኔታ ለመግዛት ታስቦ የተቀመጠ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡የአመልካች ደንበኛ እቃዎቹን በተለያዩ ጊዜያት ሲረከቡ የነበሩ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ከተረጋገጠ እቃዎቹ የተራገፉበትን ቀን ወይም የመጀመሪያ ርክክብ የተደረገበትን ቀን መነሻ አድርጎ ክሳቸው በይርጋ እንዲታገድ ማድረግ ከይርጋ ፅንሰ ሃሳብም ውጪ መሆኑ የሚታመን ነው፡፡

የይርጋ ህግ መሰረታዊ አላማ ተገቢውን ጥረት የሚያደርጉ ገንዘብ ጠያቂዎችን ወይም መብት አስከባሪዎችን መቅጣት ሳይሆን መብታቸውን በተገቢው ጊዜ ለመጠየቅ ጥረት የማያደርጉትን ሰዎች መቅጣት መሆኑ ይታመናል፡፡ስለሆነም የአመልካች ደንበኛ መብታቸውን ማስከበር ሲችሉ ያላግባብ የዘገዩበት ሁኔታ መኖሩን የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡በባህር ህግ ቁጥር 162 ድንጋጌ ስር የይርጋ አቆጣጠር ጊዜ የሚጀምርበትን አግባብ ያስቀመጠ ሲሆን ለተያዘው ጉዳይ ግን ድንጋጌው ሙሉ በሙሉ አግባብነት አለው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ምክንያቱም

ድንጋጌው በንኡስ ቁጥር አንድ ስር ለመጫን ወይም ለማራገፍ የተወሰነው ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ካፒቴኑ መርከቡን ሊጫን ወይም ሊራገፍ ተዘጋጅቷል ብሎ ካስታወቀበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ሲያስቀምጥ የድንጋጌው ንዑስ ቁጥር ሁለት ደግሞ ጊዜም የሚታሰበው ካፒቴኑ ማስታወቂያውን ሰጥቶ ስራው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ መሆኑን ያሳያል፡፡በሌላ አገላለፅ ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው የመጫኛና የማራገፊያ ጊዜ የሚጀምርበት ጊዜ በግልጽ በታወቀበት ሁኔታ ነው እንጂ እቃዎቹ በተለያዩ ጊዜያት በተጫኑበትና በተራገፉበት ግንኙነት ውስጥ አይደለም፡፡የአመልካች ደንበኛ እቃዎች ሙሉ በሙሉ የተጫኑበት ቀንም ሆነ የሚራገፉበት ቀን ያለመታወቁን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡

አመልካች በእርግጥም መብቱን ማስከበር የሚችልበት ጊዜ የካቲት 05 ቀን 2004 ዓ/ም ከተባለ ይኼው ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1848(1) ድንጋጌ መሰረት ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ በባህር ህጉ አንቀጽ 203(1) የተቀመጠው የአንድ አመት ጊዜ የሚያበቃው ከየካቲት 06 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ ሲሆን አመልካች ግን ይሄው ጊዜ ከማለፉ በፊት የካቲት 05 ቀን 2005 ዓ/ም ክሱን ያቀረበ በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ሁኖ አልተገኘም፡፡ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ክስ በአንድ አመት ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት የሰጡት ብይን ተገቢውን የይርጋ መቁጠሪያ ጊዜ መነሻ ያላደረገ ከመሆኑም በላይ የባህር ህግ ቁጥር 162 ድንጋጌን ይዘቱንና መንፈሱን ከተያዘው ጉዳይ ልዩ ባህርይ ጋር ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ብይኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ውሳኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 203024 ግንቦት 06 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 137802 ታህሳስ 08 ቀን 2006 ዓ/ም በትእዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ የታገደ አይደለም ብለናል፡፡
3. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 203024 ቀጥሎ በሌሎች የግራ ቀኙ የክርክር ነጥቦች ተገቢውን የክርክር አመራር ስርዓት ተከትሎ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

የሰ/መ/ቁ. 95072

ጥር 07 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-**አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-**ግሎሪየስ ኃ.የተ.የግል ማህበር - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሜሮን ታምራት - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታተ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የማቀዝቀዣ(ፊሪጅ) ሽያጭን መሰረት አድርጎ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ከተጠሪ በብር 16,750.00 የገዙት ፊሪጅ አስፈላጊውን አገልግሎት መስጠት እንደማይችል እንደተረዱ ወደአመልካች ድርጅት አድርስው ድርጅቱ እቃው እንደሚስተካከልላቸው ነግሯቸው እቃውን ተስተካክሏል በሚል ወደ ቤት ቢመልሱትም በተመሳሳይ ሁኔታ ለሁለተኛ ጊዜ ተበላሽቶ አገልግሎት መስጠት በማቆሙ እቃውን እንዲቀየርላቸው ድርጅቱን ቢጠየቁም ድርጅቱ ፈቃደኛ ያለመሆኑን ዘርዝረው አመልካች ድርጅት እቃውን እንዲቀይርላቸው ወይም የሽያጭ ገንዘቡን እንዲመልስላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ከተጠሪ ጋር የፊሪጅ ሽያጭ ውል መኖሩን ሳይክድ ማቀዝቀዣው ተጠግኖ እንዲሰራ ማድረጉን፣ ለአንድ አመት ደግሞ የጥገና ዋስትና ግዴታ ከመግባቱ ውጪ ፊሪጁን ለመቀየር ወይም የሽያጭ ገንዘቡን ለመመለስ ግዴታ ያለመግባቱንና ባለው የጥገና ዋስትና መሰረት ማቀዝቀዣውን ጠግኖ አመልካች ለመውሰድ ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆንይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤትም ፊሪጁ መስራት አለመስራቱን በቦታው ላይ ተገኝቶ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ፍሪጁ መስራቱን መመልከቱን ገልፆ አመልካች በውሉ ባለው የጥግና ዋስትና ውል ግዴታውን መወጣቱ መረጋገጡን በምክንያትነት ይዞ ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ፍሪጁ መስራት አለመስራቱ ከሁለት ድርጅቶች ባለሙያ ተመድቦ እንዲጣራ ትዕዛዝ ቢሰጥም አመልካች ድርጅት ከኦሜዳድ ድርጅት የተላከውን ባለሙያ ማቀዝቀዣውን እንዳይመለከት አድርጎ ሳልኔት ከተባለው ድርጅት የተላከው ባለሙያ ብቻ እንዲመለከት አድርጎ ይህ ድርጅት ያቀረበውን ሪፖርት በመመርመር የአመልካች አካሄድ ከቅን ልቦና የሆነ ነው በሚል ድምዳሜ አመልካች ለተጠሪ ተመሳሳይ ሞዴል ማቀዝቀዣ እንዲቀይርላቸው ወይም ዋጋውን ብር 16,750.00 እንዲመልስላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ እና

በኦሜዳድም ሆነ በሳልኔት ድርጅት ባለሙያዎች ማቀዝቀዣው መስራት ያለመስራቱ ተጣርቶ እንዲቀርብ አድርጎ ድርጅቶቹ ባቀረቡት ሪፖርት መሰረት ማቀዝቀዣ መስራቱ ቢረጋገጥም የባለሙያዎቹ አስተያየት እንደ አስገዳጅ ማስረጃ ሊወሰድ እንደማይችል፣እቃው ከሶስት ወራት በኋላ የማይበላሽ መሆኑን እርግጠኛ መሆን እንደማይቻል፣አዲስ የተገዛ እቃ ሁል ጊዜ እያስጠገኑ መጠቀም አለበት ሊባል እንደማይገባ በምክንያት ይዞ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ሙሉ በሙሉ አንጽንቶታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኝም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ለተጠሪ የተሸጠው ማቀዝቀዣ የተበላሸው በተጠሪ የአጠቃቀም ችግር የተከሰተ ሁኖ የሽያጭ ውሉም በአመልካች ላይ ለአንድ አመት የጥገና ግዴታ ከሚጥል በስተቀር እቃውን ለመቀየር ወይም የሽያጭ ገንዘቡን ለመመለስ የማያስገድድ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከውሉና ከሕጉ ውጪ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በአመልካችና በተጠሪ የተገባውን የሽያጭ ውል ስምምነት መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

አመልካችና ተጠሪ የማቀዝቀዣ ሽያጭ ውል ማድረጋቸው፣አመልካች ማቀዝቀዣውን ቢበላሽ ለአንድ አመት የጥገና ዋስትና ግዴታ መግባቱን፣አመልካች እቃውን ለተጠሪ አስረክቦ ተጠሪ እቃውን በመጠቀም ላይ እንዳሉ መጀመሪያ ሲበላሽ አመልካች ባለው የጥገና ግዴታ እቃውን ጠግኖ ሲመልስ እንደገና በመበላሸቱ ተጠሪ እቃውን ለአመልካች መልሰው አመልካች እንደገና ጠግኖ እቃው እንዲሰራ ቢያደርግም ተጠሪ እቃው ካልተቀየረ አልረከብም ማለታቸው በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ጉዳዮች ናቸው፡፡

በመሰረቱ ሽያጭ ማለት ሻጭ የሆነው አንዱ ወገን ገዥ ለሆነው ሌላ ወገን ዋጋው በገንዘብ የተወሰነውን አንድ ነገር ገዥው ሊከፍለው ግዴታ በገባበት መሰረት ሊያስረክብና ሀብትነቱን ሊያስተላልፍ የሚገደድበት ውል መሆኑ በፍ/ሕ/ቁ.2266 ተመልክቷል ፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ሻጭ የሆነ ወገን የሽያጩን ገንዘብ ከገዥ ወገን መጠየቅ መብት እንዳለው ሁሉ የተሸጠውን ነገር ደግሞ የማስረከብና ሀብትነቱን የማስተላለፍ ተነጻጻሪ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ ሻጭ ያስረከበው ነገር በውሉ መሰረት ትክክል ለመሆኑና ጉድለት ስላለመኖሩ ለገዢው ኃላፊ ነው፡፡ ዕቃው እንደ ውሉ አይደለም የሚባለው ዋቢነት የሚሰጥባቸው ጉድለቶች እና ጉድለት ስለመኖሩ ፣ ጉድለት ያለ ከሆነ ደግሞ ጉድለቱ መቼ መመርመር እንዳለበት ፣ ገዢው የገዛው እቃ ጉድለት ያለበት ስለመሆኑ መቼ ማስታወቅ እንዳለበት እንዲሁም ጉድለትን አለማስታወቅና የሚያስከትለው ውጤትን አስመልክቶ በፍትሐብሔር ህጉ ከቁጥር 2288-2293 ድንጋጌዎች ስር በግልጽ ተመልክቷል ፡፡

ገዢ ጉድለቱን ካወቀበት ወይም ጉድለት ያለበት መሆኑን ካስታወቀበት ግዜ አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ክስ ካላቀረበ መብቱ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁጥር 2298 የተመለከተ ሲሆን ይሁንና ሻጩ የደረሰውን ጉዳት የማስተካከል ወይም በአዲስ የመተካት መብቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2300 ድንጋጌ ተጠብቆለታል፡፡

የእቃውን ጉድለት መመርመርን በተመለከተ ህጉ ገዢው ግልፅ ጉድለትን በተመለከተ እቃውን በተረከበበት ግዜ የመመርመር ኃላፊነት እንዳለበት ሲያስቀምጥ ሻጩ ደግሞ ለድብቅ ጉድለቶች /በርክክብ ወቅት ሊታዩ ወይም ሊገለጽ የማይችሉ/ ሃላፊነት / let the seller be aware of latent / hidden/ defects/ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡
ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ያቀረቡት ጉድለት መኖሩን መሰረት አድርገው ሳይሆን ብልሽቱ እንዲጠገንላቸው ለአመልካች ጥያቄ አቅርበው አመልካች በግራ ቀኙ መካከለ ባለው ውል መሰረት ጠግኖ ከሰጠ በኂላ እቃው እንደገና በመበላሸቱ ምክንያት በድጋሚ ሲጠገን ለታሰበው አገልግሎት ሊውል አይችልም በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ ማቀዝቀዣው የሚሰራ መሆኑ በባለሙያ የተረጋገጠ ሲሆን የባለሙያዎች አስተያየት ማቀዝቀዣው እስከመቼ እንደሚሰራ ባይረጋግጥም አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለው ውል እቃው ቢበላሽ ጥገና ማድረግ መሆኑ ያልተካደ ጉዳይ ነው፤ስለሆነም አመልካች ለድብቅ ጉድለት ኃላፊነት አለበት ተብሎ ክስ ባልቀረበበትና በህጉ አግባብ የተቋቋመው ውል ደግሞ አድማሱ ለአንድ አመት ያህል አመልካች በነፃ የመጠገን ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ የሚገልጽ ሁኖ እያለ ከግራ ቀኙ የውል ስምምነት እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2300 ድንጋጌ ይዘት ውጪ አመልካች ማቀዝቀዣውን እንዲቀየር ወይም የሽያጭ ገንዘቡን እንዲመልስ ተብሎ የተወሰነው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731፣2298 እና 2300 ድንጋጌዎችን የጣሰ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ የግራ ቀኙን ስምምነት እና በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡትን ነጥቦችን ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 14450 መጋቢት 05 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 160863 ነሐሴ 28 ቀን 2005 ዓ/ም ፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት 174255 ህዳር 03 ቀን 2006 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.58788 ሰኔ 15 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. አመልካች በውሉ በገባው ግዴታ መሰረት ማቀዝቀዣውን ጠግኖ አግልግሎት እንዲሰጥ ከማድረግ ውጪ ማቀዝቀዣውን የመቀየር ወይም የሽያጭ ገንዘቡን የመመለስ ግዴታ የለበትም ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ.102711

ህዳር 10 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ፋንታዬ ፍሰሐ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ደጀኔ ማርዬ የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በግለሰቦች መካከል በተደረገ የብድር ገንዘብ ውልን መሰረት አድርጐ የቀረበውን የቤት ልረከብ ጥያቄን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው በሰሜን ወሎ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ ከአሁኑ አመልካች ጋር ጥር 15 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረጉት የብድር ውል በወር አምስት በመቶ ወለድ ሂሳብ የሚታሰብ ሁኖ ብር 8000.00 (ስምንት ሺህ ብር) ለአሁኑ አመልካች እንደአበደሯቸው፣ የብድሩ መመለሻ ጊዜም ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም መሆኑን፣ በዚህ ጊዜ አመልካች የብድር ገንዘቡን ካልመለሱ በላስታ ወረዳ ላሊበላ ከተማ 01 ቀበሌ ልዩ ስሙ ሽብጽ ከተባለው ቦታ የሚገኘውንና በ200 ካ/ሜትር ስፋት ባለው ቦታ ላይ የሰፈረውን ቆርቆሮ ቤትና ባህርዛፍ ተክል አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክቧቸው መስማማታቸውን በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብና ወለድ ስሌት መሰረት በድምሩ ብር 9600.00 (ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ብር) አመልካች ያለመመለሳቸውን ዘርዝረው አመልካች በውሉ መሰረት ንብረቱን እንዲያስረክቧቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ፍርድ ቤት ቀርቦ በሰጡት መልስም ከተጠሪ ጋር ለክሱ መሰረት የሆነውን ውል ማድረጋቸውን በማመን ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ውሉን አምነዋል በማለትና የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 242 ድንጋጌን በዋቢነት ጠቅሶ አመልካች ለክሱ መሰረት የሆነውን ቆርቆሮ ቤትና ባህርዛፍ ተክል ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የወሰነ ሲሆን በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ወሎ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ያጡ ሲሆን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የለም ተብሎ መዝገቡ ተዘግቶባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ከአመልካች ጋር በተደረገው ውል የገንዘብ ብድሩ የተደረገ መሆኑን ሳይክዱ የመያዣውን ንብረት በተመለከተ ግን የባህርዛፍ ተክል ብቻ መያዣ አድርገው የተስማሙ ሁኖ እያለ ተጠሪ የአመልካችን መሃይምነት በመጠቀም የአመልካች መኖሪያ ቤት ለመያዣነት እንደተሰጠ አድርገው በውሉ ላይ አስፍረው መገኘታቸውንና ለብር 9600.00 የብድር ገንዘብ ግምቱ ከብር 150.000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) በላይ የሆነውን መኖሪያ ቤታቸውን እንዲያስረክቡ መወሰኑ ጉዳዩ በአግባቡ ባልተጠራበትና ሕጉን መሰረት ሳያደርግ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ እንዲታረምላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጐላቸው ቀርበውም የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ያለመቅረቡን፣ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ክሱን ሳይክዱ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የንብረቱን ግምትና የመያዣውን አይነት መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክርክር ሥነ-ሥርዓቱን መሰረት አድርጐ ያልቀረበ መሆኑን ዘርዝረው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የለበትም ተብሎ ሊጸና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም በዚህ ችሎት እልባት ሊያገኙ የሚገባቸው ጭብጦች፡-

1. የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሕጉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ የቀረበ ነው ወይስ አይደለም?
2. አመልካች ለተጠሪ ቤቱንና የባህር ዛፍ ተክል ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ መወሰኑ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም የሚሉት ናቸው፡፡

**<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡-** አንድ የመጨረሻ ፍርድ ባገኘ ጉዳይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታውን ማቅረብ ያለበት በአዋጅ ቁጥር 25/1998 አንቀጽ 22(4) ባተመለከተው አግባብ በዘጠና ቀናት ውስጥ መሆኑን ሕጉ ያሳያል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት የመጨረሻ ፍርድ በመ/ቁጥር 03-08770 ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ/ም መሰጠቱን የሚያሳይ የትዕዛዝ ግልባጭ አያይዘው ያቀረቡ ሲሆን ለዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ደግሞ ሐምሌ 03 ቀን 2006 ዓ.ም ነው፡፡ ይህም የሰበር አቤቱታው በሕጉ የተመለከተው የዘጠና ቀናት የጊዜ ገደብ ከማለፉ በፊት የቀረበ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ተጠሪ በጉዳዩ ላይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 28950 መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ.ም ነው ውሳኔ የሰጠው በማለት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ለመቃወም ያቀረቡት ምክንያት የክርክሩን ሂደት ያላገናዘበ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

**<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ</u>፡-** ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች ከተጠሪ ገንዘብ ሲበደሩ ለገንዘቡም አመላለስ አመልካች ያላቸውን ቤትና ባህርዛፍ በመያዣ ለተጠሪ መስጠታቸውን ነው፡፡ ሆኖም መያዣ ውሉ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ አለመመዝገቡን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማናቸውም ዓይነት ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቢሆን ከተፃፈበት ቀን አንስቶ የማይነቀሳቀሰው ንብረት በሚገኝበት አገር ባለው በማይንቀሳቀስ ርስት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር በማንኛውንም ዓይነት ውጤት እንደማያስገኝ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3052 ስር በማያሻማ ሁኔታ ተደንግጐ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ህጉ

በግልጽ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚመሰረተው መያዣ መመዝገብ እንዳለበት የደነገገውን አለመከተል የመያዣው አመሰራረት ጉድለት ያለበት መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በመያዣ ውሉም አመልካች የተበደሩትን ገንዘብ እስከ ጥር 14 ቀን 2001 ዓ/ም ባይመልሱ ተጠሪ በመያዣነት የያዙትን ቤትና ባህርዛፍ እንደሚረከቡ በግልጽ ተዋውለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ውሉ በህጉ አግባብ የተደረገ ሆኖ አላገኘነም፡፡ ምክንያቱም በፍ/ህ/ቁ 3060/1/ በተደነገገው መሰረት ዕዳው እንዲከፈል በተወሰነበት ጊዜ ሳይከፈል የቀረ እንደሆነ ገንዘብ ጠያቂው የመያዣ መብት ያገኘበትን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይወስዳል በሚል የተደረገ ውል ፈራሽ ስለመሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የዚህ ድንጋጌ አይነተኛ አላማ ሰዎች ለጊዜው የገጠማቸውን የገንዘብ ወይም ኢኮኖሚያዊ ችግር ለማቃለል ሲሉ ተገቢውን መደራደር አድርገውና ነፃ የመዋዋል መብታቸውን ተጠቅመው ወደ ግዴታው በነፃ ፍላጎታቸው ይገባሉ ተብሎ ስለማይታሰብ በዚህ ሁኔታ ውሉ ተፈጽሞ ሲገኝ ሕጉ ለስምምነቱ ጥበቃ ባለማድረግ የተዋዋይ ወገኖችን የንብረት መብት ለመጠበቅ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን ከዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ አላማ በማየት የተጠሪን የአመልካች ቤትና ባህር ዛፍ ልረከብ ጥያቄን ውድቅ ማድረግ ሲገባቸው አመልካች አምነዋል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡

ቀጥሎ መታየት ያለበት የህግ ነጥብ ተጠሪ ያላቸው መፍትሔ ምንድነው? የሚለው ነው፡፡ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የገንዘብ ብድር ውል መደረጉ የተካደ ፍሬ ነገር አይደለም ፡፡ አመልካች ከተጠሪ ብር 8000,00 (ስምንት ሺህ) ተበድረው ወስደው በውሉ በተመለከተው የጊዜ ገደብ አልመለሱም፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1731፣በፍ/ብ/ህ/ቁ.2471 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት አመልካች ለተጠሪ የተበደሩትን ገንዘብ መመለስ ግዴታ አለባቸው፡፡አመልካች ይህንኑ ገንዘብ መመለስ ያለባቸው ከምን ያህል ወለድ ጋር ነው የሚለውን ስንመለከትም ወለድን በተመለከተ ገዥው መርህ በፍ/ብ/ህ/ቁ.2478 የተቀመጠው ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌው ተበዳሪው ወለድ እንዲከፍል የውሉ ቃል ካልሆነ በቀር ለተበዳሪው ወለድ መክፈል የለበትም ተብሎ አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ ወለድ የሚከፈለው በውሉ ወለድ ይከፈላል የሚል ቃል ሲኖር መሆኑን ድንጋጌው ያሳያል፡፡ ይሁን እንጂ ተዋዋዬች በወለድ የሚከፈለውን ገንዘብ በዓመት ከመቶ አስራ ሁለት በላይ እንዲሆን ለመዋዋል እንደማይችሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2479(1) ድንጋጌ በኃይለ ቃል አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም ተዋዋይ ወገኖች በገንዘብ ብድር ወለድን ገልጸው መስማማት እንደሚችሉና መጠኑ ግን በአመት ከመቶ አስራ ሁለት በላይ ሊሆን አይችሉም፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት የውል ስምምነት ወለድ ለመክፈል ስምምነት የተደረገ ቢሆኑም የወለዱ መጠን ግን በወር ከመቶ አምስት ሁኖ የሚታሰበውም በወር መሆኑን በግልጽ ስምምነቱ እንደሚያሳይ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው ህጉ ለብድር ገንዘብ ሊከፈል የሚችል የወለድ መጠን በአመት ከመቶ አስራ ሁለት ነው በማለት ከደነገገው ጣሪያ በላይ ስምምነት መደረጉን ነው፡፡ ህጉ ወለድ በአመት ጊዜ እንዲታሰብ እንጂ በወር ጊዜ እንዲታሰብ አልፈቀደም፡፡ ስለሆነም አመልካች በወር አምስት ከመቶ ወለድ እየከፈሉ የብድር ገንዘቡን ለመመለስ ያደረጉት ስምምነት ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711 እና 2479(1) ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ በህግ ጥበቃ ሊደረግለት የሚገባ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይም አመልካች ለተጠሪም በወር አምስት በመቶ እየታሰበ እንዲከፍሉ የሚገደዱበት የህግ አግባብ አላገኘንም ፡፡ ሆኖም አመልካች የብድር ገንዘቡን በጊዜ ገደቡ ያልመለሱ በመሆኑ በአመት የሚታሰበው ህጋዊ ወለድን (9%) ለተጠሪ የማይከፈሉበትን አግባብ ግን አላገኘንም፡፡ ሲጠቃለልም

የስር ፍርድ ቤቶች የመያዣ ውሉ ህጋዊ አድርገው በሰጡት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ ህግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ስላገኘን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00256 በ10/07/2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ፍርድ፣ የሰሜን ወሎ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12151 ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-08770 ሰኔ 30 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች እና ተጠሪ የመሰረቱት የማይንቀሳቀስ ንብረት የመያዣ ውል ሕጋዊ ስላልሆነ ተጠሪ ቤትና ባህርዛፍ ሊረከቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው ዋናውን የብድር ገንዘብ ብር 8000.00 (ስምንት ሺህ) ገንዘብ መመለስ ከነበረበት ከጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ (9%) ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**እ/ተ**

የሰ/መ/ቁ. 107990

መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች:-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች:-** እማሆይ ወ/ገብርኤል የቀረቡ የለም (ተወካይ)

**ተጠሪ:-** ደረጀ ደሳለኝ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ በጉራጌ ዞን አቤሽጌ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ በ1997 ዓ/ም የባለቤቴ ልጅ ባል የሆነው ቄስ ሀይሉም ተስፋዬ ይዞታዬን ወሮ ይዞብኝ ተጠሪ ረዳት መስሎ ቀርቦኝ ቦታውን በትክክል በማላውቀው ቦታ ወስዶኝ ልጄ ነው ብለሽ ፈርሚልኝ ብሎ ከ1999 ዓ/ም ጀምሮ በመሬቴ ላይ ያመረተውን ድርሻዬንና 1.65 ሄክታር ይዞታየን ነጥቆኛል በመሆኑም ይመልስልኝ በማለት ጠየቁ፡፡ ተጠሪም በሰጠው መልስ አመልካች በ23/07/98 ዓ/ም በተደረገ የስጦታ ውል በፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2443(1) እና በ881 መሠረት የተፈጸመ ስጦታ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን ያየው የወረዳ ፍርድ ቤት የግራቀኙን በማከራከር አመልካች የስጦታ ውሉ አልተመዘገበም በማለት ያቀረቡት ክርክር ውድቅ ነው፤ መሬቱን ወደውና ፈቅደው በስጦታ ውል ሰጡ እንጂ በማታለል መሆኑ አልተረጋገጠም፣ ስለዚህ ተጠሪ መሬቱን ሊለቁ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በመቀጠልም ጉዳዩን ያየው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ30/8/98 ለጉራጌ ዞን ፍትህ መምሪያ የቀረበው የስጦታ ውል እና የቀበሌ መስተዳደር የተጻጻፉት ደብደቤዎች ውሉ መመዝገቡን የሚይሳይ ካለመሆኑም በላይ በቀላጤ የሰው ንብረት ማስተላለፍ ስለማይቻል የስር ፍርድ ቤት አመልካች ወደውና ፈቅደው የሰጡት የስጦታ ውል ነው፤ በመሆኑም መሬቱን ተጠሪ ሊለቁ አይገባም በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የስጦታ ወሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2443 እና 881"ን" የተከተለ ባለመሆኑ ተንኮል ያለበት በመሆኑ ተጠሪ ሊለቁ ይገባል፤ የኪራይ ግምትም በአካባቢው ባህል መሠረት ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ በመጨረሻም ጉዳዩ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በመመርመር፤ በ23/7/98 የተደረገው የስጦታ ውል የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 እና 2443 ተከትሎ የተከናወነ፤ እንከን የማይወጣለት፣ የመመዝገብ ግዴታ የማይጥል በመሆኑ ተጠሪ ከ1998 ጀምሮ በስጦታው መሰረት ወደስሙ አዙሮ በጉልበቱ አለስልሶ፤ የሚጠቀምበትን

ይዞታ ግዴታህን አልተወጣህም ባልተባለበት ይልቀቅ መባሉ እንደማፈናቀል የሚቆጠር በመሆኑ ሊለቁ አይገባም በማለት የከፍተኛውን ውሳኔ በመሻር የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎትም ቅሬታውን ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡

የአመልካችም አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልጹ፡- የስር ፍርድ ከጠየቅኩት ዳኝነት ውጭ ጭብጥ በመያዝ በወረራ ተያዘብኝ ያልኩትን ይዞታ፣በስጦታ አስታኮ መወሰናቸው፣ እንዲጦረኝ ሰጥቸው ሲጦረኝ ቆይቶ አታሎኝ ስጦታ አስፈረመኝ እያልኩ ከዚህ ጭብጥ ወጥቶ መወሰኑ እና ለረጅም አመታት ሲጠቀምበት የነበረውን ይዞታዬን እንዲነጠቅ መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቋል፡፡ በዚህም መሰረት ችሎቱም አከራካሪውን መሬት ባለይዞታው ማነው? የሚለውን ለማስረዳት የቀረበው የስጦታ ውል በማስረጃነት ያለውን ተቀባይነት ለመመርመር በጭብጥነት በመያዝ የግራቀኙ በጽሁፍ መልስና የመልስ መልስ በማቀባበል አከራክሯል፡፡

ተጠሪም በሰበር መልሳቸው አመልካች የተገኘውን ምርት አላካፍል አለኝ አሉ እንጂ ስጦታ መስጠታቸውን አልካዱም፣ የቀበሌው አመራሮች ባሉበት በሰነዱ ላይ ወደው ፈቅደው ሰጥቶኛል፣ ግዴታህን አልተወጣህም ከተባልኩ እንድወጣ ማድረግ እንጅ ውሉን የማያፈርሰው ነው፡፡ በመሆኑም የወረዳውና የጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የይግባኝ ሰሚውና የሰበሩ ውሳኔዎች ሊጸና ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ከተጠሪ ጋር ዝምድና የሌላቸውና በቤተክርስቲያን ቀርበን አብረን ለመጠቀም ነበር የተስማማነው፣ የስጦታ ውሉ የማላውቀውና በተንኮል የተገኘነው፣ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/99 አንቀፅ 8/5,6 መሰረት ለቤተሰብ፣ ወይም ለወራሽ ካልሆነ በቀር ማስተላለፍ ስለማይቻል ሊሻር ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ባጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰው ሲመስል፡- እኛም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ አንፃር መዝገቡን መርመረናል፡፡

በመሆኑም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የስር የግራ ቀኙን ክርክር የተሰጠውን ዳኝነት እንዳየነው፣ የአመልካች ጥያቄ የነበረው ከሚች ባለቤታቸው የተላለፈላቸው የእርሻ መሬት ወሮ ይዞብኛል፣ በማላቀው ሰነድ አታሎም አስፈረመኝ ድርሻየን እና ምርቱን ያካፍለኝ በማለት በመጠየቃቸው ምክንያት መሆኑን ከተያዘው ክርክር የምንገነዘበው ሲሆን ተጠሪም፣ ይዞታውን አመልካች በ23/7/98 በተደረገ የስጦታ ውል መያዙን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡ እንግዲህ አመልካች እንዲመለስላቸው የሚጠይቁት 1.65 ሄ/ር ቦታን አስመልክቶ ይህ ተጠሪ ረዳት በመምሰልና ባልታወቀ ቦታ ወስዶአቸው አብረን እንበላለን ልጄ ነው ብለሽ ፈርሚ ብሎኝ ነው የፈረምኩት በማለት አሁን ተጠሪ የሚያቀርቡትን የስጦታ ሰነድ እየተቃወሙት ያሉት፣ በተጨማሪም ሲረዳኝ ቆይቶ አቅመ ደካማ መሆኔን አይቶ እርዳታውን በማቆሙ ረዳት አጥቼ ወደ ቤተክርስቲያን በመግባት በመጠለል እገኛለሁ በማለት ገልጸው በሰው ምስክርም አስረድቷል፡፡ ተጠሪ የሚለው አመራሮች ባሉበት ፈቅደው ሰጥተውኛል፣ ግዴታህን አልተወጣህም የሚባል ከሆነ ግዴታዬን ከመወጣት በቀር በፍ/ህ/ቁ 2442 መሰረት በይርጋ ይቀራል፣ ሊጠይቁኝ አይችሉም በስሜ አዙሬ እየተጠቀምኩበት ነው የሚል መከራከሪያ ነው የሚያቀርበው፣ ይሁን እንጁ ይህ የአመልካች ክርክር የሚያሳየው የተጠቀሰው ይዞታ በእጁ መሆኑን እና ከመሰረቱ የመጦር ግዴታ የለብኝም ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከአመልካች እድሜና አቅመደካማነትን፣ በአሁኑ ጊዜ ያለረዳት በረሀብ ላይ

እንዳሉ ከተገለፀው ፍሬ ነገር አንፃር ስንመለከተው ተአማኝነት የለውም፤ ላለመጦር ይዞታቸውን ይለቃሉ ተብሎም አይገመትም፤ ሌላው፤ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 2458/1/ ድንጋጌም እንደምንረዳው፤ በግልፅ የሰፈረ የዉል ቃል ባይኖርም ስጦታው ሰጪ በድህነት ላይ ወድቆ ሲገኝ፤ የመጦር ግዴታም እንደለበት ተደንግጎል፤ ይሁን እንጂ ተጠሪ ከዚህም አልፎ ይዞታውን ይዘው እንኳንስ መጦር በውለታ ቢስነት ይዞታውን ስመሃብቱን ወደስማቸው ያዞሩት መሆኑን ከክርክሩ የምንረዳው ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ያለመጦራቸውን ባረጋገጡበት ጊዜ ይዞታቸውን ማስመለስና ስጦታውንም እንዲሻር የመጠየቅ መብቱን ሊነፈጉ አይችሉም የፍ.ብ.ህ.ቁ. 2464(1) ይህንኑ ያመላክታል አመልካች ከይዞታቸው ያለመፈናቀል ሕገመንግስታዊ መብትም አላቸው፡፡ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ ሃዋሳ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚውና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አከራካሪውን ይዞታ ተጠሪ በስጦታ ያገኙትና ጉልበታቸውን አፍሰው አለስልሶ ወደስማቸው አዙሮ እየተጠቀሙበት በመሆኑ በስጦታ ያገኙትን ይዞታ ሊለቁ አይገባም ሊፈናቀሉ አይገባም በማለት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ማጽናታቸው ሊታረም የሚገባው ነው ብለናል፡፡

ባጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚውና የሰበር ሰሚው ችሎት ተጠሪው አከራካሪውን ይዞታ ሊለቁ አይገባም በማለት የከፍተኛው ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. የደ.ብ.ብ.ህ.ክ.መ. የአበሽጌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 06347 በቀን 15/05/06 የሰጠው የጉ/ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 08153 በቀን 28/06/06 የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ በመ.ቁ. 03248 በቀን 09/10/06 የስር ውሳኔን በመሻር የሰጠውና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 03727 በቀን 10/3/07 ቅሬታውን ባለመቀበል የሰጡት ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የጉ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 08153 በቀን 28/06/06 የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ በስጦታ ውል ያዝኩት የሚሉትን ይዞታ ለአመልካች ሊለቁ ይገባል ብለናል፡፡
4. የግራ ቀኙ የወጪ ኪሳራቸውን የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ውሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሩ/ለ**

# ወንጀል

የሰ/መ/ቁ.95440

ሰኔ 4 ቀን 2006 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ረታ ቶሎሳ

አዳነ ንጉሴ

ሙስጠፋ አህመድ

አመልካች፡- አቶ ሰሚር ኢብራሂም ሂቡ ጉዳይ ተከታታይ ነኝ በማለት አቶ ኢብራሂም ሂቡ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዐ/ሕግ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን ሁለት የወንጀል ክሶች የተመለከተው የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሰጠባቸው እና በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በውሳኔ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረባቸው ሁለት ክሶች ይዘት ባጭሩ፡- አመልካች የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ለመስጠት አስቦ በአንደኛ ክስ በ28/09/2005 ዓ.ምእና በሁለተኛ ክስ በ30/09/2005 ዓ.ምበየክሶቹ ላይ በተመለከተው ጊዜ እና ቦታ የግል ተበዳይ ለሆኑት አቶ አሩቅ ሙሐባ አባድር ቁጥሮቻቸው በየክሶቹ ላይ የተመለከቱትን በአጠቃላይ ብር 520,000 የያዙ ከሕብረት ባንክ የሚመነዘሩ ሁለት ቼኮችን በመስጠቱ እና ሁለቱም ቼኮች እንደቅደም ተከተላቸው በ06/10/2005 ዓ.ም.እና በ05/10/2005 ዓ.ም. ለክፍያ ለባንኩ ሲቀርቡ በቂ ስንቅ የላቸውም ተብሎ ክፍያ ሳይፈጸምባቸው በመቅረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 693(1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የሚያዝበት ገንዘብ ሳይኖር ቼክ የመስጠት ወንጀል አድርጓል የሚል ሲሆን አመልካች ተጠይቀው በሁለቱም ክሶች የተመለከተውን ወንጀል ማድረጋቸውን ሙሉ በሙሉ ማመናቸው በመረጋገጡ ፍ/ቤቱ ማስረጃ መስማት ሳያስፈልግ በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ.134 (1) መሰረት ላይ በሁለቱም ክሶች የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡

በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኃላ ለሁለቱም ክሶች በመመሪያው መሰረት የተሰላው መነሻ ቅጣት 11 ዓመት ጽኑ እስራት እና የብር 16,000 መቀጮ መሆኑን፣ ይህ የእስራት ቅጣት እና የመቀጮ መጠን በአባሪ አንድ እና ሁለት እንደቅደም ተከተሉ በእርከን 29 እና 7 ላይ የሚወድቅ

መሆኑን፣ ወንጀሎቹ ተደራራቢ በመሆናቸው ምክንያት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 85 መሰረት እርከኑ በአንድ ማክበጃ ምክንያት ወደ 30 ከፍ የሚል መሆኑን፣ በሌላ በኩል አመልካች የቀረበባቸው ሪከርድ አለመኖሩ፣ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው እና በችሎት ቀርበው ክሶቹን ማመናቸው በሶስት የማቅለያ ምክንያትነት ሲወሰዱ እርከኑን ከ30 ወደ 24 ዝቅ የሚያደርጉ መሆኑን፣ በአባሪ አንድ እርከን 24 ስር የተመለከተው ፍቅድ ስልጣን ከ6 ዓመት ከ6 ወር እስከ 7 ዓመት ከ8 ወር መሆኑን እና በአባሪ ሁለት በእርከን 2 የተመለከተው የመቀጮ መጠንም እስከ ብር 2000 መሆኑን በመግለጽ በመጨረሻ አመልካች በስድስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እና በብር 700(ሰባት መቶ) መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡት የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች የተከሰሱበትን ወንጀል አምነው የግል ተበዳይን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ መመለሳቸው፣ የወንጀል ሪከርድ ያልቀረበባቸው መሆኑን እና የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸውን የስር ፍ/ቤቶች በማቅለያ ምክንያትነት መያዛቸውን በገለጹበት ሁኔታ በአመልካቹ ላይ የጣሉት የቅጣት መጠን ተመዛዛኝ መሆን አለመሆኑን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ጉዳዩን መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ቀደም ሲል እንደተገለጸው አመልካች የቀረቡባቸውን ሁለት የወንጀል ክሶች ሙሉ በሙሉ በማመናቸው የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠባቸው በወ.መ.ሕ.ስ.ስ.ቁ. 134(1) መሰረት በሰጡት የእምነት ቃል መሰረት ነው፡፡ አንድ ተከሳሽ የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠበት የተከሰሰበትን ወንጀል ሙሉ በሙሉ በማመኑ በሆነ ጊዜ ስለቅጣቱ ልክ ወይም ስለቅጣቱ ሕጋዊነት ካልሆነ በስተቀር በጥፋኝነት ውሳኔው ላይ ይግባኝ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.185(1) ተደንግጓል፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች የተከሰስኩባቸውን ወንጀሎች በተመለከተ ክሱን በሰማው ፍ/ቤት የእምነት ቃል አልሰጠሁም ወይም ያስመዘገብኩት ቃል በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.134(1) መሰረት የእምነት ቃልን የሚያቋቁም አይደለም በማለት በሰበር አቤቱታቸው ላይ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ለሰበር ክርክሩ በጭብጥነት የተያዘውም የቅጣት ውሳኔው አግባብነት ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሊሻርልኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ሕጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የቅጣት ውሳኔውን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጃ ከወጣላቸው ውስጥ የሚካተት ሲሆን የፌ/ከ/ፍ/ቤት ቅጣቱን የወሰነው በቼኮቹ ላይ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን አንጻር በሁለቱም ክሶች የተመለከቱት ወንጀሎች በደረጃ 7 የሚወድቁ ሆኖ የእስራት ቅጣቱ እና መቀጮው እንደቅደም ተከተላቸው በአባሪ አንድ በእርከን 22 እና በአባሪ ሁለት በእርከን 6 ስር የሚወድቁ መሆኑን በመግለጽ፣ አንድ የማክበጃ ምክንያት እና ሶስት የማቅለያ ምክንያቶችን ተቀብሎ ቅጣቱን በመመሪያው መሰረት በማስላት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ፍ/ቤቱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 "ን" መሰረት በማድረግ የተከተለው ይህ የቅጣት አወሳሰን ስርዓት በመሰረቱ ተገቢ ቢሆንም በሌላ በኩል ግን አሁን በስራ ላይ ያለው የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ከወንጀል ደረጃው አመዳደብ አንፃር በቅጣት አወሳሰኑ ላይ የሚያስከትለው ለውጥ መኖር አለመኖሩ እና ካለም

ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው የትኛው መመሪያ እንደሆነ ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሰረቱ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያዎቹን ያወጣው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 88(4) ድንጋጌ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በመሆኑ ምክንያት መመሪያዎቹ እንደ ሕግ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸውን ወንጀሎች ያደረጉት መመሪያ ቁጥር 1/2002 ስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ሲሆን ይህ መመሪያ ከጥቅምት 1 ቀን 2006 ዓ.ም.ጀምሮ በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ተተክቷል፡፡ በሌላ በኩል አዲሱ የወንጀል ህግ እንዲጸና ከተደረገ በኃላ አድራጊው ህጉ ከመጽናቱ በፊት ላደረገው ወንጀል ሲፈረድበት ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ በስራ ላይ ከነበረው ሕግ ይልቅ አዲሱ ሕግ ቅጣትን የሚያቃልልለት ሲሆን ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው በአዲሱ የወንጀል ሕግ የተመለከተው ቅጣት ስለመሆኑ በወንጀለኛ ሕግ አንቀጽ 6 ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ከቀድሞው መመሪያ ይልቅ ለአመልካቹ የሚጠቅም መሆኑ ከተረጋገጠ በወ/ሕ/ አንቀጽ 6 የተመለከተው ድንጋጌ በዚህ ጉዳይ ተፈጻሚነት እንዲኖረው መደረግ ይኖርበታል፡፡

ለአመልካቹ ቅጣቱን የሚያቀለው የትኛው መመሪያ ነው? የሚለውን ነጥብ በተመለከተ ለ1ኛ ክስ ምክንያት በሆነው ቼክ ላይ የተመለከተው የገንዘብ መጠን ብር 120,000 በቀድሞው መመሪያ መሰረት በደረጃ 7 ስር ይሸፈን የነበረ ሲሆን በአዲሱ መመሪያ ግን በደረጃ 6 ስር እንዲሸፈን የተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ በፍቅድ ስልጣን አወሳሰን ረገድም አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ለተከሳሹ ቅጣትን የሚያቃልልለት በመሆኑ ለቅጣት አወሳሰኑ መሰረት ተደርጎ መያዝ የሚገባው አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በዚሁ በአዲሱ መመሪያ መሰረት በ1ኛ ክስ ስር የተመለከተው ወንጀል በደረጃ 6 ስር የሚወድቅ ሆኖ የእስራት ቅጣቱ እና መቀጮው እንደቅደም ተከተሉ በአባሪ አንድ በእርከን 15 እና በአባሪ ሁለት በእርከን 4 ስር የሚሸፈን መሆኑን፣በ2ኛ ክስ ስር የተመለከተው ወንጀል በደረጃ 7 ስር የሚወድቅ ሆኖ የእስራት ቅጣቱ እና መቀጮው እንደቅደም ተከተሉ በአባሪ አንድ በእርከን 17 እና በአባሪ ሁለት በእርከን 5 ስር የሚሸፈን መሆኑን፣ በአባሪ አንድ በእርከን 15 እና በአባሪ አንድ በእርከን 17 ስር ከተመለከተው ፍቅድ ስልጣን ውስጥ አነስተኛው የቅጣት መጠን ተወስዶ ሲደመር በሁለቱ ወንጀሎች የሚጣለው መነሻ ቅጣት 6 ዓመት መሆኑን፣ ይህ የቅጣት መጠንም በአባሪ አንድ በእርከን 21 ስር የሚወድቅ መሆኑን፣ ይህ እርከን በስር ፍ/ቤት ተቀባይነት ባገኙት አንድ የማክበጃ እና ሶስት የማቅለያ ምክንያቶች ሲሰላ ወደ እርከን 19 ዝቅ የሚል መሆኑን መሰረት በማድረግ ተፈጻሚ መደረግ የሚገባው የቅጣት መጠን በአባሪ አንድ በእርከን 19 ፍቅድ ስልጣን ስር የተመለከተው የቅጣት መጠን መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል በሁለቱም ክሶች በተመለከቱት ወንጀሎች በፌ/ከ/ፍ/ቤት ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፌ/ጠ/ፍ/ቤት በውሳኔ የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ እና በቅጣት ውሳኔው ላይ ግን ከላይ በተገለጸው ምክንያት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባ ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 136445 በ13/10/2005 ዓ.ም. እና በ25/10/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይ/ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 92629 በ20/01/2006 ዓ.ም. የጸናው ውሳኔ በወ.መ.ሕ.ስ.ቁ. 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተ.ቁ.1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በአመልካቹ ላይ በሁለቱም ክሶች የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በተ.ቁ. 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በአመልካቹ ላይ በሁለቱም ክሶችበድምሩ ተጥሎ የነበረውን የስድስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል አመልካቹ በዚህ ጉዳይ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሆኖ በአራት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
4. ይህንኑ ተገንዝቦ በተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም አመልካቹ ለሚገኙበት የአዲስ አበባ ማረሚያ ተቋም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ይላክ፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት እና በማረሚያ ቤት በኩል ለአመልካቹ ይላክ፡፡
6. በፌ/ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው የብር 700(ሰባት መቶ) የመቀጮ ውሳኔ አልተነካም፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ይ**

የሰ/መ/ቁ. 96607

መስከረም 29 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካቾች፡- 1ኛ.አቶ ኤርሚያስ ካጢሶ
2ኛ. አቶ ዮሐንስ ላምቤቦ } ጠበቃ ፀጋዬ አሰፋ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የከምባታ ጠምባሮ ዞን ገቢዎች ባለስልጣን ዋና ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ገቢን አሳንሶ የማስታወቅ ወንጀል መፈጸማቸው በማስረጃ ተረጋግጧል በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠብን የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ፍርድ ቤት ተጠሪ በአመልካቾቹ ላይ በ08/8/2005 ዓ.ም አዘጋጅቶ ባቀረበው ክስ ተከሳሾቹ በከምባታ ጠምባሮ ዞን በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ጊዜ ደበኦ በተባለ ቀበሌ አሸዋ እና ድንጋይ ለማምረት ከመንግስት ጋር ውል አድርገው ስራውን እያከናወኑ በነበረበት ከ2004 ዓ.ም እስከ ህዳር ወር 2005 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ትክክለኛ የገቢ ግብር ላለመክፈል ሆን ብለው በማሰብ በኤንትሬ ገልባጭ መኪና በቢያጆ ከብር 300 እስከ ብር 360 ይሸጡ የነበረውን ነጭ ድንጋይ ከብር 40 እስከ ብር 100 የሸጡ አስመስለው፣እንዲሁም በፊያት ገልባጭ መኪና በቢያጆ ከብር 140 እስከ ብር 250 ይሸጡ የነበረውን ነጭ ድንጋይ ከብር 30 እስከ ብር 60 የሸጡ አስመስለው በመመዝገብ እና ገቢያቸውን በማሳነስ የመንግስትን እና የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ አድራጎት የፈጸሙ በመሆኑ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 በአንቀጽ 97 የተደነገገውን በመተላለፍ ግብር አሳንሶ የማስታወቅ ወንጀል አድርገዋል በማለት ክስ የመሰረተ ሲሆን ተከሳሾቹ ድርጊቱን አልፈጸምንም በማለታቸው ተጠሪ ሁለት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ከመሆኑም በላይ የተለያዩ ሰነዶችን በማስረጃነት አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም የተጠሪን የሰው እና የጽሁፍ ማስረጃ መርምሮ በአመልካቾቹ ላይ በክሱ መሰረት ያስረዳ መሆኑን በመግለጽ ተከሳሾቹ መከላከያቸውን እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ ከሰጠ እና የተከሳሾቹን የሰው እና የጽሁፍ መከላከያ ማስረጃ

ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር በመመርመር  ዐቃቤ ሕግ በሰው እና በሰነድ ማስረጃ ያስረዳባቸውን ፍሬ ነገር ተከሳሾቹ በመከላከያቸው ያላስተባበሉ መሆኑን ገልጾ በክሱ በተመለከተው ድንጋጌ ስር በሁለቱም ተከሳሾች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በመቀጠልም የግራ ቀኙን የቅጣት አወሳሰን ክርክር ከሰማ በኃላ የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከአምስት ዓመት በማያንስ እስራት መሆኑን በመግለጽ፣ተከሳሾቹ ወንጀሉን የፈጸሙት ማስጠንቀቂያ እየተሰጣቸው መሆኑን በማክበጃ ምክንያትነት በመያዝ እና የቀረበባቸው የቀድሞ የወንጀል ሪከርድ አለመኖሩን ደግሞ በማቅለያ ምክንያትነት በመያዝ እንዲሁም የቤተሰብ ኃላፊዎች መሆናቸው በቅጣት ማቅለያ ምክንያትነት እንዲያዝላቸው ተከሳሾቹ ያቀረቡትን ጥያቄ ባለመቀበል እያንዳንዳቸው በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሳሾቹ በተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት፤ዐቃቤ ሕግ ደግሞ በተሰጠባቸው የቅጣት ውሳኔ መጠን ቅር በመሰኘት ሁለቱም ወገኖች ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን የከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከሳሾቹን ቅሬታ መሰረት አድርጎ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ዐቃቤ ሕግ ክሱን ያቀረበው በተሻረ ሕግ መሆኑን እና ተከሳሾቹ ለነጭ ድንጋይ የዋጋ ተመን ከወጣ በኃላ ከተመን በላይ ሽያጭ ስለማከናወናቸው ዐቃቤ ሕግ ያላስረዳባቸው መሆኑን በምክንያትነት በመጥቀስ የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔውን ሽሮ ተከሳሾቹን በነጻ በማሰናበት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ዐቃቤ ሕግ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በክሱ የተጠቀሰው የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 በአዋጅ ቁጥር 136/2003 በከፊል የተሻሻለ ከመሆኑ ውጪ ሙሉ በሙሉ ያልተሻረ እና ለክሱ መሰረት የሆኑት ድንጋጌዎችም በማሻሻያ አዋጁ ያልተነኩ ሆኖ እያለ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ክሱ የቀረበው በተሻረ ሕግ መሆኑን መግለጹ ተገቢነት የሌለው መሆኑን እና የተመን ጉዳይም  በክርክሩ ሂደት በግራ ቀኙ ምስክሮች እግረ መንገድ የተነገረ ከመሆኑ ውጪ ለክሱም ሆነ ለወንጀሉ የማቋቋሚያ ምክንያት ባልተደረገበት ሁኔታ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተመንን ጉዳይም በምክንያትነት የጠቀሰው አላግባብ መሆኑን ገልጾ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በመሻር እና የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካቾቹ ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ የተሰረዘ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ዐቃቤ ሕግ በተከሳሾቹ ላይ በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ አንሷል የሚለውን ቅሬታ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በማድረሱ ሰበር ችሎቱ በዚህ ረገድ በሌላ መዝገብ በቀረበለት አቤቱታ ሳቢያ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ በስር ፍርድ ቤቶች የተወሰነውን የቅጣት መጠን ከፍ በማድረግ ተከሳሾቹ እያንዳንዳቸው በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾቹ አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ተሻሽሎ እና ከፍ ተደርጎ የተሰጠባቸውን የቅጣት ውሳኔ ጨምሮ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ ገቢያችንን አሳንሰን ያሳወቅንበት የግብር መጠን በገቢ ማስታወቂው ላይ በሌለበት ሁኔታ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 በአንቀጽ 97 ስር ጥፋተኛ መባላችን የሕግ ስህተት ነው በማለት አመልካቾቹ ያቀረቡትን ቅሬታ ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ

በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካቾቹ ሲጠየቁ ወንጀሉን አላደረግንም በማለታቸው ተጠሪ አቅርቦ ያሰማቸው የውሃና ማዕድን ሀብት ጥናት የስራ ሂደት አስተባባሪ መሆናቸውን የገለጹት 1ኛ ምስክር እና የድንጋይ ግዥ ከአመልካቾቹ ሲፈጽሙ እንደነበረ የገለጹት 2ኛ ምስክር አመልካቾቹ በሽያጭ ደረሰኞች ላይ የሚጽፉት ዋጋ ድንጋዩን ከሚሸጡበት ዋጋ እጅግ ዝቅ ያለ መሆኑን፣ ግብር ይከፍሉ የነበረውም በደረሰኙ ላይ በተመለከተው መሰረት ከሽያጩ ዋጋ 3% መሆኑን፣ በደረሰኞቹ ላይ የሽያጩን ትክክለኛ ዋጋ እንዲሞሉ በተደጋጋሚ ሲነገራቸው የቆየ ቢሆንም ፈቃደኞች ሳይሆኑ መቅረታቸውን፣በኃላ ግን በተደረገ አጠቃላይ ውይይት ድንጋዩን የሚሸጡበት ተመን ወጥቶ ተግባራዊ መደረጉን፣ተመን ከወጣ በኃላ የተከሰተ ችግር ስለመኖሩ የቀረበ ሪፖርት አለመኖሩን እና መሰል ፍሬ ነገሮችን በመግለጽ በተመሳሳይ ሁኔታ የመሰከሩ መሆኑን እና ተጠሪ ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎችም የሽያጭ ደረሰኞችን ጨምሮ ይህንኑ ምስክርነት የሚያጠናክሩ መሆናቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡አመልካቾቹ እንዲከላከሉ በተሰጠው ብይን መሰረትም ድንጋዩን ለማምረት እና ለማስጫን ይወጣ የነበረውን ወጪ በአዋጁ አንቀጽ 20 በተመለከተው መሰረት ከአጠቃላይ የሽያጩ ገንዘቡ ላይ በመቀነስ በደረሰኙ ላይ ይጽፉ የነበረው የተጣራ ትርፋቸውን ወይም ገቢያቸውን ብቻ እንደነበረ ያውቁልናል በማለት እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ምስክሮችን ያሰሙ እና የተለያዩ ሰነዶችን በማስረጃነት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ አመልካቾቹ በተጠሪ ማስረጃ የተመሰከረባቸውን የወንጀል ፍሬ ነገር በመከላከያቸው አላስተባበሉም በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ያስተላለፈባቸውም ሕጋዊ ወጪዎችን ተቀናሽ የማድረግ መብት ተግባራዊ የሚደረገው ገቢያቸውን በስርዓቱ መሰረት እያስታወቁ ግብር ለሚከፍሉ ነጋዴዎች እንጂ ገቢያቸውን አሳንሰው ለሚያስታውቁ ነጋዴዎች ጭምር አይደለም የሚል ነጥብ በዓቢይ ምክንያትነት በመያዝ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በመሰረቱ በአመልካቾቹ ላይ የቀረበው ክስ መሰረታዊ ይዘት ግብር የሚከፈልበትን ገቢ አሳንሰው አስታውቀዋል የሚል ሲሆን"ግብር የሚከፈልበት ገቢ" ለሚለው ሐረግ ለክሱ በተጠቀሰው የክልሉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 የተሰጠ ትርጉም የለም፡፡በሌላ በኩል በአዋጁ ውስጥ የተለየ ትርጉም በግልጽ ካልተሰጣቸው በስተቀር በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት በተተረጎሙበት ሕግ የተሰጣቸውን ትርጉም የሚይዙ ስለመሆኑም በአዋጁ አንቀጽ 2 መግቢያ ላይ የተመለከተ ሲሆን ለጉዳዩ አግባብነት ባለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በአንቀጽ 2(11) ስር "ግብር የሚከፈልበት ገቢ" ማለት በአዋጁ እና በአዋጁ መሰረት በሚወጡ ደንቦች መሰረት ማናቸውም ወጪ እና ሌሎች ተቀናሽ ሂሳቦች ከተቀነሱ በኃላ የሚቀረው የገቢ መጠንስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች አጥብቀው የሚከራከሩት በእነዚህ የአዋጆቹ ድንጋጌዎች መሰረት ለምርት እና ለአገልግሎት ያወጣነውን ወጪ ከአጠቃላይ የሽያጭ ገንዘቡ ላይ ቀንሰን ግብር የሚከፈልበትን ገቢ በደረሰኝ ላይ ከማስፈር ውጪ ግብር የሚከፈልበትን ገቢያችንን አሳንሰን አላስታወቅንም በማለት ነው፡፡ በሽያጩ ዋጋ እና አመልካቾቹ በሽያጭ ደረሰኞቹ ላይ በሚሞሉት የዋጋ መጠን መካከል ልዩነት መኖሩን ከማስረዳት ውጪ አመልካቾቹ ወጪዎቻችን ናቸው የሚሏቸውን የተለያዩ ሂሳቦች በመቀናነስ በደረሰኞቹ ላይ ይሞሉት የነበረው የገቢ መጠን ከእውነተኛው ገቢያቸው መጠን በታች ስለመሆኑ

ተጠሪው ባለበት የማስረዳት ግዴታ መሰረት በማስረጃ ያረጋገጠው ፍሬ ነገር ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያረጋግጥም፡፡

አመልካቾቹ መግለጽ ይገባቸው የነበረው ከተቀናሽ ወጪዎች በኃላ የሚገኘው እውነተኛው የገቢ እና በገቢው ላይ መከፈል ይገባው የነበረው የግብር መጠን ምን ያህል እንደነበረ በመወሰን ተጠሪው በአዋጁ በተሰጠው ስልጣን እና በተዘረጋው የግብር አጣጣል ስርዓት መሰረት በአመልካቾቹ ላይ የጣለው ግብር ስለመኖሩም የቀረበ ክርክር እና ማስረጃ የለም፡፡ተጠሪው በሕግ በተጣለበት የማስረዳት ግዴታ መሰረት እነዚህን መሰረታዊ የወንጀሉን ፍሬ ነገሮች ማስረዳቱ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ደግሞ አመልካቾቹ በተከሰሱበት እና ጥፋተኛ በተባሉበት የወንጀል ሕግ አነጋገር መሰረት ግብር አሳንሶ የማስታወቅ ወንጀል አድርገዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱ ሕጋዊ መሰረት አለው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል አመልካቾቹ ለምርት እና ለአገልግሎት አውጥተናል የሚሏቸውን ወጪዎች የግብር አስገቢው መስሪያ ቤት በማያውቀው ሁኔታ በራሳቸው በመቀነስ በሽያጭ ደረሰኞቹ ላይ የተጣራ ነው የሚሉትን ገቢ ብቻ በመሙላት መፈጸማቸው የተረጋገጠው ድርጊት ራሱን ችሎ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ ቀጥሎ መታየት እና ምላሽ ማግኘት የሚገባው ጥያቄ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በዚህም መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ ግብር የሚከፈልበትን ከንግድ ስራ የሚገኝ ገቢ በሚመለከት በአዋጁ የተመለከቱት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ግብር ከፋዩ ወጪዎችን ማረጋገጥ እስከቻለ ድረስ ለንግድ ስራው ገቢ ለማግኘት፣ለንግድ ስራው ዋስትና ለመስጠት እና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች ተቀናሽ የሚደረጉ ስለመሆኑ ከላይ በተጠቀሰው የክልሉ መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ በአንቀጽ 20 ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ግብር የሚከፈልበት የንግድ ስራ ገቢ ተቀባይነት ያገኘውን የሂሳብ አያያዝ መርህ በመከተል የሚዘጋጀውን የትርፍና ኪሳራ ሂሳብ ወይም የገቢ መግለጫ ፣ አዋጁን እና የግብር ባለስልጣን የሚያወጣውን መመሪያ መሰረት በማድረግ በእያንዳንዱ የግብር ዘመን የሚወሰን ስለመሆኑ በዚሁ አዋጅ በአንቀጽ 18 ተመልክቷል፡፡

ከእነዚህ የአዋጁ ሁለት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መገንዘብ የሚቻለውም ግብር ከፋዩ ለንግድ ስራው ገቢ ለማግኘት፣ለንግድ ስራው ዋስትና ለመስጠት እና እንቅስቃሴውን ለማስቀጠል ተደርገዋል የሚባሉት ወጪዎች ተቀናሽ የሚደረጉት በራሱ በግብር ከፋዩ ውሳኔ ሳይሆን ሕጋዊ ወጪዎቹ ናቸው የሚላቸውን ወጪዎች ጨምሮ አጠቃላይ የሂሳብ መግለጫውን ለባለስልጣኑ ካቀረበ እና የወጪዎቹ ሕጋዊነትና ተገቢነት በግብር ባለስልጣኑ ተረጋግጦ ተቀባይነት ካገኘ በኃላ ብቻ መሆኑን ነው፡፡አንድ ግብር ከፋይ ለግብር ባለስልጣኑ በሚያቀርበው መግለጫ ውስጥ መካተት የሚገባቸውን ነጥቦች ያለበቂ ምክንያት ሳያካትት ያስቀረ በሆነ ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ድርጊት ራሱን ችሎ የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 98(1)(ለ) ስር የተደነገገ ሲሆን ለወንጀሉ የሚጣለው ቅጣትም ሳይካተት በቀረው ነጥብ ምክንያት ሳይከፈል የቀረውን የግብር መጠን መሰረት በማድረግ በአንቀጽ 98(2) በፊደል(ሀ) እና (ለ) ስር በተለያየ መጠን ተደንግጎ ይገኛል፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካቾቹ ሕጋዊ ናቸው የሚሏቸውን ወጪዎች ዝርዝር ለባለስልጣኑ ሳያቀርቡ በመቅረታቸው ምክንያት ሳይከፈል የቀረውን የግብር መጠን ተጠሪው ለይቶ ያላስረዳ በመሆኑ በአመልካቾቹ ድርጊት ምክንያት አንሶ እንዲከፈል የተደረገው የግብር መጠን በአንቀጽ 98(2)(ሀ) ስር የተመለከተው አነስተኛ መጠን ማለትም ከብር አንድ ሺህ የማይበልጥ ተደርጎ መወሰድ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም በአመልካቾቹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው በዚህ ድንጋጌ ስር ሲሆን ሊጣልባቸው የሚገባው የቅጣት

መጠንም በስር ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኙትን የቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች መሰረት በማድረግ  በድንጋጌው ስር የተመለከተው ከብር ሃያ ሺህ የማይበልጥ መቀጮ እና ከአንድ ዓመት የማያንስ እና ከሶስት ዓመት የማይበልጥ እስራት ነው፡፡በአመልካቾቹ የወንጀል ድርጊት ምክንያት ሳይከፈል የቀረው የግብር መጠን ቀደም ሲል እንደተገለጸው አነስተኛ ነው ተብሎ ግምት የሚወሰድበት በመሆኑ ውሳኔው በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 13(2) እና (3) መሰረት መፈጸሙ የተረጋገጠው ወንጀል በክብደቱ እና በአፈጻጸሙ ሊመደብ የሚገባው በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡ የጥፋተኝነት ውሳኔው በተሰጠበት ድንጋጌ ስር በዝቅተኛ ደረጃ ለተመደበ ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው የተቀመጠው ፍቃድ ስልጣን ከአንድ ዓመት እስከ አንድ ዓመት ከሶስት ወር የሚደርስ እስራት ሲሆን ይህም በመመሪያው አባሪ አንድ በእርከን ሰባት ስር የሚወድቅ ነው፡፡የገንዘብ መቀጮ መጠኑም በአባሪ ሁለት መሰረት እስከ ብር 20,000 (ሃያ ሺህ) የሚደርስ ነው፡፡

ሲጠቃለል በማስረጃ በተረጋገጠው የወንጀል ፍሬ ነገር መሰረት በአመልካቾቹ መፈጸሙ የተረጋገጠው ወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትለው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 አንቀጽ 98(2)(ሀ) ድንጋጌ ስር ሆኖ እያለ በአመልካቾቹ ላይ በክሱ በተጠቀሰው የአዋጁ በአንቀጽ 97 ስር የተሰጠው በጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊሻሻል የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥ~ል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06021 በ11/07/2005 ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ  በመዝገብ ቁጥር 01611 በ01/02/2006 ዓ.ም እና በመዝገብ ቁጥር 02314 በ29/02/2006 ዓ.ም በውሳኔ እና በትዕዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ እና በቀዲዳ ጋሜላ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 06021 በ11/07/2005 ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01612 በ29/02/2006 ዓ.ም. የተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካቾቹ የወንጀል ተጠያቂነት አለባቸው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በአመልካቾቹ ላይ በአዋጁ አንቀጽ 97 ድንጋጌ ስር ተሰጥቶ የነበረውን የጥፋኝነት ውሳኔ በማሻሻል የወንጀል ተጠያቂነታቸው የሚወድቀው በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ክልል መንግስት የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/1995 አንቀጽ 98(2)(ሀ) ድንጋጌ ስር ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በአመልካቾቹ ላይ በክልሉ ሰበር ችሎት ተሻሽሎ የተሰጠው የአምስት ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት ተሻሽሎ በዚህ በጉዳይ የታሰሩበት የሚታሰብላቸው ሆኖ አመልካቾቹ እያንዳንዳቸው በአንድ ዓመት እስራት እና በብር 1,000 (አንድ ሺህ) መቀጮ እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
5. በዚህ ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የውሳኔው ግልባጭ አመልካቾቹ ለሚገኙበት ማረሚያ ተቋም ይላክ፡፡ውሳኔው ዛሬ ጥቅምት 4 ቀን 2007 ዓ.ም ተነገረ፡፡
6. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍ/ቤቶች ይላክ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ እ/ተ

የሰ/መ/ቁ. 93234

መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኰንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካች፡- የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ኃይለኪሮስ ወልደብርሃን ካሕሳይ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች አቤቱታ ያቀረበው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በማዕከላዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪ ላይ አቅርቧቸው በነበሩት ሁለት የሙስና ወንጀል ክሶች ጉዳዩ የከሳሽን ምስክሮች ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት ምስክሮቹ እንዲሰሙ ከመደረጉ በፊት ተከሳሹ ከተከሰሱባቸው ሁለት የሙስና ወንጀሎች መካከል በሁለተኛው ክስ የተመለከተውን ወንጀል ያደረጉት ከሌላ ሰው ጋር በመተባበር ስለመሆኑ በሂደት የተደረሰበት መሆኑን ገልጾ የወንጀሉ ተካፋይ ነው የተባለውን ሌላኛውን ግለሰብ በክሱ በማካተት ክሱን አሻሽሎ ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ያቀረበውን ጥያቄ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምጽ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን እና በብይኑ ቅር በመሰኘት አመልካች ያቀረበውን ቅሬታ የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ባለመቀበል የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የክስ ማሻሻል ጥያቄውን በአብላጫ ድምጽ ሳይቀበል የቀረው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 118 እና 119 ድንጋጌዎች መሰረት ክስ እንዲሻሻል ሊደረግ የሚችለው ክሱ ተከሳሹን የሚያሳስት ወይም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያስቸግር በሆነ ጊዜ መሆኑን እና ተጨማሪ ተከሳሽን በክሱ የማካተት ጉዳይ ለክስ ማሻሻል ጥያቄ በምክንያትነት መቅረቡ ሕጋዊ መሰረት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ሲሆን አነስተኛው ድምጽ በበኩሉ ክስ እንዲሻሻል የሚደረገው ተከሳሹን የሚያሳስት ወይም ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያስቸግር በሆነ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በቁጥር 118 ድንጋጌ አነጋገር መሰረት በክሱ መገለጽ ይገባው የነበረ ነገር ግን ሳይገለጽ የቀረ መሰረታዊ ነገር መኖሩ ሲረጋገጥ ጭምር መሆኑን እና በወንጀሉ ተሳታፊ ነበረ የተባለ ሰው በማናቸውም ምክንያት በክሱ ውስጥ በተከሳሽነት ሳይካተት መቅረቱም ለክሱ መሰረታዊ የሚባል ነገር መሆኑን በመግለጽ ክሱ እንዲሻሻል ሊደረግ ይገባው ነበር በማለት የልዩነት ሀሳቡን አስፍሯል፡፡

በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት የማስረጃ ማሰማት ሂደቱን አቋርጦ አመልካች ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በስር ፍርድ ቤት የተያዘው ክርክር ለጊዜው ታግዶ እንዲቆይ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ይግባኝ ወደ ተባለበት ፍሬ ጉዳይ ሳይገባ በቅድሚያ ሊመረመር የሚገባው የይግባኝ አቀራረቡ ስነ ስርዓታዊ አግባብነት መሆኑን ገልጾ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 181(1) እና 184(መ) ድንጋጌዎች መሰረት ተከሳሹን ጥፋተኛ በማለት ወይም ነፃ በመልቀቅ ወይም ለጊዜው በመልቀቅ ውሳኔ ከተሰጠ በኂላ በዋናው ጉዳይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ከሚቀርበው ይግባኝ ጋር በአንድነት ካልሆነ በቀር በዋናው ጉዳይ ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት  በክስ ማሻሻል ክርክር ረገድ በሚሰጥ ብይን ወይም ትዕዛዝ ላይ ይግባኙን ነጥሎ ማቅረብ የሚቻልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ አለመኖሩን በምክንያትነት በመጥቀስ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበውም የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት አቤቱታውን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ክስ አቅርቦ ማስረጃ ከማሰማቱ በፊት ከተጠሪ ጋር አብሮ መከሰስ ያለበት ሌላ ግለሰብ መኖሩን ስለደረስኩበት ግለሰቡን ጨምሬ ክስ ላቅርብ በማለት ያቀረበውን ጥያቄ የስር ፍርድ ቤቶች ክስ ለማሻሻል የሚፈቀደው ክሱ ተከሳሹን የሚያሳስት ወይም ፍርድ ለመስጠት አስቸጋሪ ሲመስል ብቻ ነው በማለት ጥያቄውን ውድቅ የማድረጋቸውን አግባብነት ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 119 ድንጋጌ አንጻር ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ለክርክሩ ወደ ተያዘው የፍሬ ጉዳይ የክርክር ጭብጥ ከመገባቱ በፊት እልባት ማግኘት የሚገባው በዋናው ጉዳይ ላይ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት  በክስ ማሻሻል ክርክር ረገድ በሚሰጥ ብይን ወይም ትዕዛዝ ላይ ይግባኙን ነጥሎ ማቅረብ የሚቻልበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ አለመኖሩን በምክንያትነት ጠቅሶ ይግባኙን ባለመቀበል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው እና በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ መሆኑን በመገንዘብ  አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለውሳኔው መሰረት ካደረጋቸው የወንጀለኛ መቅጫ  ስነ ስርዓት ሕጉ ሁለት ድንጋጌዎች መካከል ከላይ ለተጠቀሰው ጭብጥ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ቁጥር 184 ድንጋጌ ሲሆን ይህ ድንጋጌም ተከሳሹን ጥፋተኛ በማለት ወይም ነፃ በመልቀቅ ወይም ለጊዜው በመልቀቅ ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ በዋናው ጉዳይ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ከሚቀርበው ይግባኝ ጋር በአንድነት ካልሆነ በቀር በቁጥር 94 መሰረት ቀጠሮ መስጠትን ወይም አለመስጠትን ወይም በቁጥር 131 መሰረት የሚቀርብ መቃወሚያን ወይም በቁጥር 146 መሰረት ማስረጃን መቀበልን ወይም አለመቀበልን አስመልክቶ በሚሰጡ ትዕዛዞች ላይ ይግባኙን ነጥሎ ማቅረብን የሚከለክል ነው፡፡

እንደሚታየው ይህ ድንጋጌ  ትዕዛዞቹ መሰረት የሚያደረጓቸውን ድንጋጌዎች ጭምር በመጥቀስ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት የትዕዛዝ ይግባኝ ክልከላ የተጣለባቸውን ጉዳዮች የሚዘረዝር ሲሆን ከዝርዝሩ ውስጥ የክስ ማሻሻል ጉዳይም ሆነ የክስ ማሻሻል ጉዳይ መሰረት የሚያደርጋቸውን ቁጥር 118 እና 119 ድንጋጌዎች አልተካተቱም፡፡ይህም ሕጉ የትዕዛዝ ይግባኝ ክልከላ በግልጽ ከጣለባቸው ውጪ በሆኑ የመጨረሻ ትዕዛዝ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ (የክስ ማሻሻል ጥያቄን

ውድቅ ከማድረግ ጉዳይ ጋር የተያያዙትን ጨምሮ) ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊትም ቢሆን ይግባኝ ማቅረብን አስመልክቶ የስነ ስርዓት ሕጉ ያስቀመጠው ክልከላ አለመኖሩን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ የክስ ማሻሻል ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ የተሰጠውን ትዕዛዝ በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ ፍርድ ቤት ቢሆን ከአሁኑ ተጠሪ ቀጣይ የወንጀል ክርክር ሂደት ጋር የሚያስተሳስረው ነገር ባለመኖሩ እና ትዕዛዙ የተሰጠበት ጉዳይ በድጋሚ ለክርክር ሊቀርብ የሚችልበት ዕድል የሌለ በመሆኑ ትዕዛዙ የመጨረሻ እንጂ ጊዜያዊ አገልግሎት እንዳለው ተቆጥሮ በስረ ነገሩ ከሚሰጠው ፍርድ ጋር ተጠቃሎ ይግባኝ የሚባልበት ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡በመሆኑም ይግባኙ የቀረበው በስነ ስርዓት ሕጉ የተመለከተውን የይግባኝ አቀራረብ ስርዓት መሰረት አድርጎ ባለመሆኑ ሊስተናገድ አይገባውም በማለት በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 184 ድንጋጌ የትዕዛዝ ይግባኝ ክልከላን የሚጥለው ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት በሚሰጡ ሁሉም ትዕዛዞች ላይ እንደሆነ አድርጎ በመተርጎም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው እና በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 57074 በ06/06/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 58589 በ12/10/2005 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 184 ድንጋጌ የትዕዛዝ ይግባኝ ክልከላ በግልጽ ከጣለባቸው ውጪ በሆኑ የመጨረሻ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊትም ቢሆን ይግባኝ ማቅረብን አስመልክቶ የስነ ስርዓት ሕጉ ያስቀመጠው ግልጽ ክልከላ ባለመኖሩ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር ምክንያት የሆነው የክስ ማሻሻል ጉዳይ ከስረ ነገሩ ፍርድ በፊት ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ይህንኑ በመገንዘብ የቀረበለትን የይግባኝ ክርክር መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲላክ ወስነናል፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ.92296

ህዳር 22 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካቾች፡- 1. አንዱዓለም አራጌ
2. ናትናኤል መኮንን
3. ክንፈሚካኤል ደበበ
} ጠበቆች አቶ ደርበው ተመስገንና አቶ አበበ ጉታ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌደራል ዓቃቤ ህግ አቶ ወንድምአገኝ ብርሃኑ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች በየግላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 112546 የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔና፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 83593 ጉዳዩን በይግባኝ ካየ በኋላ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ሥህተት ያለበት ሥለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ተጠሪ አመልካቾች የሽብርተኝነትና ከፍ ያለ የመክዳት ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ያቀረበውን የወንጀል ክስና ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በቀረበው የወንጀል መዝገብ ቁጥር 112546 ተጠሪ ከሳሽ፣አንደኛው አመልካች አንደኛ ከሳሽ፣ሁለተኛው አመልካች ሁለተኛ ተከሳሽ እና ሶስተኛው አመልካች አምስተኛ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. ከሥር የክርክሩን አመጣጥ ከመዝገቡ እንደተረዳነው፣ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾችና ሌሎች ተከሳሾች በአራት ወንጀል ክሶች የጠቀሳቸውን የወንጀል ሕግና የአዋጅ ቁጥር 652/2001 ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካቾችና በሌሎች ተከሳሾች ላይ ካቀረባቸው አራት ክሶች ውስጥ፣ አመልካቾች በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑት ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/፣ አንቀጽ 38 እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 252 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ በመተላለፍ ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ ሚስጥሮችን በመሰብሰብ ለኤርትራ መንግስት አሳልፈው በመስጠት የስለላ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት በአምስተኛው ተራ ቁጥር ያቀረበውን የወንጀል ክስ የሚያስረዳ በቂ ማስረጃ ባለማቅረቡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካቾችና ሌሎቹ ተከሳሾች

በነጻ እንዲሰናበቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪን ክስና ማስረጃ፣ የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃ በመስማት፣በመመርመርና በመመዘን በአመልካቾች ላይ ጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ የሰጠው ተጠሪ ባቀረበባቸው በሶስት የወንጀል ክሶች የተገለጹትን የወንጀል ድርጊቶች መፈጸማቸው በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦባቸዋል በማለት ነው፡፡

2. የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀፅ 4፣ የተመለከተውን በመተላለፍ፣የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣የተመለከተውን በመተላለፍና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ክሱ የዘረዘራቸውን የወንጀል ድርጊቶች ዋና ወንጀል አድራጊና ተካፋይ በመሆን የፈጸሙ መሆናቸው በበቂ ማስረጃ ተረጋግጦባቸዋል በማለት የጥፋኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002ን መሰረት በማድረግ አንደኛው አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘባቸው፣

ሀ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት፣

ለ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ ሰባት ዓመት ጽኑ እስራትና፤

ሐ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና አንቀጽ 248 (ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ሶስት ዓመት ጽኑ እስራት፣በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሰረት ሲደመር ሰላሳ ዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት እንደሚሆን በቅጣት ውሳኔው አመላክቷል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የጽኑ እስራት ቅጣት ከሃያ አምስት የማይበልጥ መሆኑን በመግለጽ፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2005 ከፍተኛው ጣሪያ ሃያ አምስት ዓመት እርከን 37 ላይ ይወድቃል፡፡ አንደኛ አመልካች ከዚህ በፊት በጽኑ እስራት ተቀጥቶ የነበረ በመሆኑ አንድ እርከን ከፍ ብሎ እርከን 38 ላይ እንደሚወድቅ በውሳኔው አስፍሯል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች ተቀባይነት ያለው የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያላቀረበ በመሆኑ በእርከን 38 ከተቀመጠው ቅጣት በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በውሳኔ ሰጥቷል፡፡

4. ሁለተኛው አመልካች በተመለከተ፣ የሥር ፍርድ ቤት ሁለተኛ አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘባቸው፤

ሀ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ4፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት፣

ለ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ ከፍተኛ ነው ብሎ  አስልቶ ያገኘውን ቅጣት ስምንት ዓመት ፅኑ እስራትና፣

ሐ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ሶስት ዓመት ጽኑ እስራት፣ መሆኑን  በቅጣት ውሳኔው አመላክቷል፡፡ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(1) መሰረት ሲደመር አርባ ዓመት እንደሆነ ነገር ግን የጽኑ እስራት ከሃያ አምስት የማይበልጥ መሆኑን በመግለጽ፤የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002 እርከን 37 ላይ የሚወድቅ መሆኑን፣ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቅጣት ማክበጃ ያልቀረበ መሆኑንና፤ሁለተኛ አመልካች ወንጀል ፈጽሞ የማያውቅ በመሆኑ አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያለው መሆኑን ገልጾ ሶስት እርከን ተቀንሶለት እርከን 34 ላይ ይወድቃል፡፡ በዚህ እርከን የተመለከተው የቅጣት ሬንጅ ከ 15 ዓመት እስከ 18 ዓመት የሚደርስ መሆኑን አስፍሮ ሁለተኛ አመልካች 18 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

5. ሶስተኛው አመልካች በተመለከተ፣ የሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛ አመልካች ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘባቸው፣

ሀ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ ከፍተኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ ሃያ ሁለት ዓመት ጽኑ እስራት፣

ለ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው  የቅጣት መነሻ ሥምንት ዓመት ጽኑ እስራትና፣

ሐ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ ከፍተኛ ነው ብሎ አስልቶ ያገኘው የቅጣት መነሻ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት መሆኑንና፣በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሰረት ሲደመር አርባ ዘጠኝ ዓመት መሆኑን ቅጣት ውሳኔው አመላክቷል፡፡ ነገር ግን የጽኑ እስራት ከሃያ አምስት ስለማይበልጥ፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት መመሪያ ቁጥር 1/2002 እርከን 37 ላይ ይወድቃል፡፡ ሶስተኛ አመልካች በችሎት መድፈር ስምንት ወር በመቀጣቱ የዘወትር ጸባዩ መልካም ነው ብሎ ለመያዝ የማይቻል መሆኑን ገልጾ በእርከን 37 የተቀመጠው የቅጣት ሬንጅ ከሃያ ዓመት እስከ ሃያ አምስት ዓመት ነው፡፡ ሶስተኛ አመልካች የፈጸማቸው የወንጀል ክብደቶችና ግላዊ ሁኔታ በማየት በሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

6. አመልካቾች የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካቾችን ይግባኝ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑት ሌሎች ይግባኝ ባዮች ጋር በማጣመር አይቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣የተመለከተውን በመተላለፍ

ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ስህተት ያለበት ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔውን ሽሮ አመልካቾች በነጻ እንዲሰናበቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

7. ይግባኝ ሰሚው ችሎት አንደኛ፣ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ እና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበራቸው ተሳትፎ መካከለኛ ነው በማለት ወስኗል፡፡

ሀ) አንደኛ አመልካች በሁለቱ ወንጀሎች መካከለኛ ደረጃ ላይ ተመድቦ በሥር ፍርድ ቤት የተወሰነበት 32 ዓመት ጽኑ እስራት መነሻ ቅጣት በወንጀል ሕጉ ከተመለከተው ከሃያ አምስት ዓመት በላይ በመሆኑ ቅጣቱ ከእርከን 37 እንደሚሆንና አንደኛ አመልካች ተቀባይነት ያለው የቅጣት ማቅለያ ያላቀረበና አንድ የቅጣት ማክበጃ ያለበት በመሆኑ በእርከን 38 መነሻ ተደርጎ ቅጣቱ ሲሰላ የሥር ፍርድ ቤት በአንደኛው አመልካች ላይ የሰጠውን የእድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የቅጣት ውሳኔ የሚያስለውጥ አይደለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ለ) ሁለተኛ አመልካችን በተመለከተም የሥር ፍርድ ቤት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ4፣ በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ደረጃ እንደሆነና የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ እና አንቀጽ 248(ለ) በመተላለፍ በተፈጸመው ወንጀል የነበረው ተሳትፎ መካከለኛ ደረጃ ነው በማለት ያስቀመጠውን የቅጣት መነሻ እንዳለ በመቀበል፣ በሁለቱ ወንጀሎች የስር ፍርድ ቤት የወሰነው መነሻ ቅጣት ሲደመር ሰላሳ ሁለት ዓመት በወንጀል ሕጉ ከተደነገገው 25 ዓመት በላይ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱ እርከን 37 መነሻ በማድረግ ሁለተኛው አመልካች ያቀረበውን አንድ ቅጣት ማቅለያ በመቀበል በእርከን 34 ከተቀመጠው የቅጣት ሬንጅ በ18 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የስር ፍርድ ቤት የወሰነውን የቅጣት ውሳኔ የሚያስለውጥ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

ሐ) ሶስተኛ አመልካች በተመለከተ በችሎት መድፈር መቀጣቱ አመልካች የወንጀል ሪኮርድ የሌለበብኝ በመሆኑ በቅጣት ማቅለያነት ሊያዝለት እንደሚገባ ያቀረበውን ጥያቄ፣ የሥር ፍርድ ቤት ሶስተኛው አመልካች በችሎት መድፈር ወንጀል ተቀጥቷል በማለት በቅጣት ማቅለያነት አለመያዙ ስህተት መሆኑን ገልጾ ይህ ማቅለያ ሲያዝ ደረጃው ከእርከን 37 ወደ እርከን 34 የሚቀንስ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት የወሰነውና ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት ተገቢ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ተሻሽሎ ሶስተኛው አመልካች በአሥራ ስድስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሌላ አነጋገር ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአንደኛና ሁለተኛ አመልካቾች ላይ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አጽንቶ፣ በሶስተኛው አመልካች ላይ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡

8. አመልካቾች ሐምሌ 22 ቀን 2005 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ዝርዝር ይዘት ከላይ የተገለጸው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ነው፡፡ አመልካቾች በጋራ ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ ጥፋተኛ ተብለን የተቀጣነው የግዙፍ ተግባር፣ ሃሳብና የህግ ሁኔታዎች ባልተሟሉበትና በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ነው፡፡

ወንጀሎቹን ለመፈጸማችን ከሳሽ በበቂ ማስረጃ ባላስረዳበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ተብሎ ሊሻር ይገባዋል፡፡አመልካቾች በይግባኝ ሰሚው ችሎት ጥፋተኛ የተባልንባቸው ሁለት የህግ ድንጋጌዎች በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሃሳብ የተፈጸሙ መሆኑን የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ የሚያሳይ በመሆኑ በሁለት ወንጀል ጥፋተኛ መባላችን የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ መርህና ይህ ሰበር ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሻረ በኂላ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካችዎች በስር ፍርድ ቤት በሶስት ወንጀሎች ጥፋተኛ ናቸው ተብለን የተወሰነብን የቅጣት ውሳኔ፣በይግባኝ ሰሚው ችሎት በአንደኛው ወንጀል ነጻ ተብለን በሁለት ወንጀሎች ብቻ ጥፋተኛ በተባልንበት ሁኔታ ሳይሻሻል እንዳለ የሚጸናበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

9. ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች ላቀረቡት የሰበር አቤቱታ የካቲት 16 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል መፈጸማቸው ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የግዙፍ ተግባር፣ ሀሳብና የህግ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ጥፋተኛ ተብለናል በማለት ያቀረቡት ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡ አመልካቾች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ስለ ጸረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4 የፈጸሙት ወንጀል፣ አመልካቾች ከሌሎቹ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ካልሆኑ ተከሳሾች ጋር በመሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ከፈጸሙት ከፍ ያለ የክዳት ወንጀል የተለያዩ ናቸው፡፡ ሁለቱም ወንጀሎች ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ወንጀሎች በመሆናቸው አመልካቾች በአንደኛው ወንጀል ብቻ ጥፋተኛ ልንባል ይገባል በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የህግ መሰረት የለውም፡፡ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች ለፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2፣ በመተላለፍ ጥፋተኛ መባል የለባቸውም በማለት ቢወስንም፣ይግባኝ ሰሚው ችሎት በአመልካቾች ላይ ባጸናቸው ሁለት የወንጀል ድርጊቶች በአንደኛና ሁለተኛ አመልካቾች ላይ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ የሚያስለውጥ አይደለም፡፡ ሶስተኛውን አመልካች በተመለከተ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ አሻሽሎታል፡፡ ስለዚህ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች መጋቢት 11 ቀን 2006 በተጻፈ የመልስ መልስ በሰበር አቤቱታቸው ያነሷቸውን ነጥቦች በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

10. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት፣የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾች ላይ ካስተላለፋቸው ሶስት የጥፋተኝነት ውሳኔዎች ውስጥ ለፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ

ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1፣ በመተላለፍ ወንጀል የፈጸሙ ጥፋተኞች ናቸው በማለት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ ሽሮ፤ አመልካቾች ጥፋተኛ መባል የሚገባቸው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ)፣ አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀጽ1 እና ስለ ፀረ ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ የተመለከተውን በመተላለፍ በማሴር፣ በማነሳሳት፣በማቀድና በማዘጋጀት ወንጀልና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀፅ 248(ለ) የተመለከተውን በመተላለፍ ከፍ ያለ የክዳት ወንጀል ነው በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠ በኂላ፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሶስተኛው አመልካች የሰጠውን ቅጣት ከማሻሻልና ከማስተካከል ውጭ በአመልካቾች ላይ የሥር ፍርድ ቤት በሰጠው የቅጣት ውሳኔ ላይ መሰረታዊ ለውጥ ሳያደርግ መወሰኑ ሕጋዊ መሰረት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

11. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካቾች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት በተፈረጀውና ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ የጦርነት፣የአመጽና ሌሎች የወንጀል ተግባራትን የሚፈጽመው የግንቦት 7 አሸባሪ ድርጅት ውስጥ አመራርና አባል በመሆን፣ በአገር ውስጥ ካሉት የድርጅቱ አመራሮች ጋር በሕቡዕ በመገናኘት፣ የሽብር ተልዕኮ በመቀበል ፣ለዚሁ የሽብር ተግባር አጋዥ የሚሆኑ ሰዎችን በመመልመል፣ ወደኤርትራ ለወታደራዊና ፖለቲካዊ ሥልጠና በመላክ እንደዚሁም ስለ ግንቦት 7 የፖለቲካ ዓላማ፣ጉዞ መመሪያና ወታደራዊ አደረጃጀት ለአባላት ገለጻ በመስጠት፣ የታቀደውን የሽብር ተግባር በቀጥታ በመምራት፣ በህቡዕ የሚተላለፈውን ገንዘብ ተቀብሎ የሽብር ወንጀል ፈጻሚዎች ያስተላለፉና የሽብር ዓላማ ያላቸውን ስብሰባዎችን በመጥራት፣ በመምራትና በተለያዩ የሽብር ተግባሮች ላይ ውሳኔዎችን በማስተላለፍ ዋና ወንጀል አድራጊና ሙሉ ተካፋይ በመሆን፣በማሴር፣ በማነሳሳት፣በማቀድና በማዘጋጀት ወንጀል የፈጸሙ ስለመሆናቸው ፍሬ ጉዳይ ማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጦባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካቾች ወሩና ቀኑ ተለይቶ ከማይታወቅበት ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ የጦርነት፣ የአመጽና ሌሎች የወንጀል ተግባራትን የሚፈጽመው የግንቦት 7 አሸባሪ ድርጅት ውስጥ አመራርና አባል በመሆን፣ ኢትዮጵያ ጋር በሰላማዊ ሁኔታ ሳይሆን በጦርነት ሁኔታ ከሚኖረውና በጠላትነት በመሰለፍ በማናቸውም መንገድ ኢትዮጲያን የማተራመስ አጀንዳ ካለው የኤርትራ መንግስት ጋር በህቡዕ በመገናኘት፣ለኤርትራ መንግስት የሚጠቅሙ የተለያዩ ተግባራትን ይፈጽሙ እንደነበር ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተረጋግጦባቸዋል፡፡

12. እኛም አመልካቾች ከላይ የተገለጹትን ሁለት ወንጀል ድርጊቶች የፈጸሙ ስለመሆናቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የደረሱበትን የፍሬ ጉዳይና የማስረጃ ምዘና መደምደሚያ ሙሉ በሙሉ እውነት ናቸው በማለት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረት በመቀበል እነዚህ አመልካቾች የፈጸሟቸው ሁለት ድርጊቶች ጥፋተኛ የሚያስብሉት በአንድ ወንጀል ነው ወይስ በሁለት ወንጀል የሚለውን ነጥብ መርምረናል፡፡ አመልካቾች በአሸባሪነት የተፈረጀው የግንቦት 7 ድርጅት ውስጥ አመራርና አባል በመሆን፣ በአገር ውስጥ ካሉት የድርጅቱ አመራሮች ጋር በሕቡዕ በመገናኘት፣የሽብር ተልዕኮ በመቀበል፣ለዚሁ የሽብር ተግባር አጋዥ የሚሆኑ ሰዎችን በመመልመል፣ ወደ ኤርትራ

ለወታደራዊና ፖለቲካዊ ሥልጠና በመላክ እንደዚሁም ስለ ግንቦት 7 የፖለቲካ ኣላማ፣ ጉዞ መመሪያና ወታደራዊ አደረጃጀት ለአባላት ገለጻ በመስጠት ፣ የታቀደውን የሽብር ተግባር በቀጥታ በመምራት፣ በህቡዕ የሚተላለፈውን ገንዘብ ተቀብሎ የሽብር ወንጀል ፈጻሚዎች ያስተላለፉና የሽብር ዓላማ ያላቸውን ስብሰባዎች በመጥራትና በመምራት በተለያዩ የሽብር ተግባሮች ውሳኔ በማሳለፍ የፈጸሙት የማሴር፣ የማነሳሳት፣የማቀድና የማዘጋጀት ድርጊት ራሱን የቻለ ወንጀል ድርጊት እንደሆነና ከአሥራ አምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት፣ በእድሜልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 4፣ ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

13. አመልካቾች ኢትዮጵያ ጋር በሰላማዊ ሁኔታ ሳይሆን በጦርነት ሁኔታ ከሚኖረውና በጠላትነት በመሰለፍ በማናቸውም መንገድ ኢትዮጵን የማተራመስ አጀንዳ ካለው የኤርትራ መንግስት ጋር በህቡዕ በመገናኘት፣ ለኤርትራ መንግስት የሚጠቅሙ የተለያዩ ተግባራትን መፈጸማቸው ራሱን የቻለ የወንጀል ድርጊትና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) መሰረት ከአምስት ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት፣ በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ አመልካችዎች ሁለቱም የወንጀል ድርጊቶች የተፈጸሙት በአንድ ወንጀል የመፈጸም ሃሳብ ማለትም ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል የመናድ ኃሳብ በመሆኑ በሁለቱ ወንጀሎች ጥፋተኛ መባላችንና የቅጣት ውሳኔ መሰጠቱ ሕጋዊ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካችዎች ጥፋተኛ ሆነው የተገኙባቸው ተደራራቢ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የመጣስ አድራጎት በወንጀል ህጉ አንቀጽ 61(ሀ) የተደነገገው መሰረታዊ መርህ ተፈጻሚ የሚሆንበት ሁኔታ የለም፡፡ በአንጻሩ ወንጀል አድራጊው በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ አደራርቦ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 187(1) መሰረት እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 65 በግልጽ ይደነግጋል፡፡

14. በወንጀል ሕግ አንቀጽ 187(1) ወንጀል አድራጊው በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ አደራርቦ የህግ ድንጋጌዎችን የጣሰ እንደሆነ (አንቀጽ 65 ) ፍርድ ቤቱ የአካባቢ ሁኔታዎችን ሲመረምር በተለይም ወንጀለኛው አስቦና አቅዶ ሕግ መጣሱን ወይም ግልጽ የሆነ መጥፎ ጸባይ ማሳየቱን ባመነ ጊዜ በአንቀጽ 184 መሰረት ቅጣቱን አክብዶ ለመወሰን እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ድንጋጌ ይዘት ስንመለከተው ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነጻነትን የሚያሳጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ እያንዳንዱ ተደራቢ ወንጀል ቅጣት ተወስኖ፣ ቅጣቱ እንደሚደመርና የቅጣቱ አይነት በሕጉ ከተመለከተው ከፍተኛ ቅጣት ሊበልጥ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንጻር አመልካቾች የወንጀል ህጉ አንቀጽ 61(ሀ) በመጥቀስ ያቀረቡት ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 65፣ አንቀጽ 187(1) እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተደነገገውን የቅጣት አወሳሰን መርሆች ያላገናዘበና የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

15. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ ህጋዊነት በተመለከተም አመልካቾች ጥፋተኛ በተባሉበት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 4፣ ሕጉ መነሻ ቅጣት አድርጎ በደነገገው አሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራትና በሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት መካከል ያለው ልዩነት አስር ዓመት ነው፡፡ ይህም በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ ከአስራ አምስት ዓመት እስከ አሥራ ሥምንት ዓመት ከአራት ወራት፣ በመካከለኛ ደራጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ አሥራ ሥምንት ዓመት ከአራት ወራት፣ እሰከ ሃያ አንድ አመት ከስምንት ወር፣ በከፍተኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ ሃያ

አንድ አመት ከስምንት ወር፣ እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ካወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ለመረዳት ይቻላል። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሶስቱም አመልካቾች በዚህ ወንጀል ያላቸው ተሳትፎ በመመካከለኛ ደረጃ የሚመደብ መሆኑን በውሳኔው አስፍሯል።

16. አመልካቾች ጥፋተኛ ሆነው በተገኙበት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና አንቀጽ 248(ለ) የቅጣት ዝቅተኛው መነሻ ሆኖ በተደነገገው አምስት ዓመት ጽኑ እስራትና እና ከፍተኛ በሆነው ሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት መካከል ያለው ልዩነት ሃያ ዓመት ነው።ይህም በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አንድ ዓመት ከሥምንት ወራት፣ በመካከለኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ አሥራ አንድ ዓመት ከስምንት ወራት እሰከ አሥራ ሥምንት ዓመት ከአራት ወር፣ በከፍተኛ ደረጃ የሚመደበው የቅጣት ሬንጅ አሥራ ሥምንት ዓመት ከአራት ወር፣ እስከ ሃያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ መሆኑን የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሰረት በማድረግ ለመገንዘብ ይቻላል። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሶስቱም አመልካቾች በዚህ ወንጀል ያላቸው ተሳትፎ በመመካከለኛ ደረጃ የሚመደብ መሆኑን በውሳኔው አስፍሯል።

17. የጽኑ እስራት ቅጣት ከሃያ አምስት አመት ሊበልጥ እንደማይችል በወንጀል ሕግ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የመጨረሻው ፓራግራፍ እና ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች ይዘት ለመረዳት ይቻላል። ይህ በመሆኑ የሶስቱም አመልካቾች ከፍተኛ የቅጣት ጣሪያ 25 ዓመት ጽኑ እስራት ሲሆን ይህም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት እርከን 37 ላይ የሚወድቅ ይሆናል።በይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሳኔ መሰረት ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ያላቸው መሆኑ ተመልክቷል። አንደኛ አመልካች የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የሌለው መሆኑንና አንድ የቅጣት ማክበጃ የቀረበበት በመሆኑ በእርከን 38 ላይ የሚወድቅ መሆኑን የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተስማምተዋል። በእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሶስት እርከን የሚቀንስ መሆኑን፣የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በውሳኔያቸው አስፍረዋል። የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ሶስት እርከን ተቀንሶላቸው እርከን 34 ላይ በማሳረፍ ፈቃደ ሥልጣናቸውን ተጠቅመዋል። ከዚህ በመነሳት የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በቅጣት አወሳሰን መመሪያው የተሰጣቸውን ፈቃደ ሥልጣንና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 88(2) የተደነገገውን መሰረት በማድረግ አንደኛ አመልካች በእድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣና ሁለተኛው አመልካች በአስራ ሥምንት ዓመት ጽኑ እስራት ያስተላለፉት የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም። ከዚህ በተጨማሪ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የስር ፍርድ ቤት በሶስተኛ አመልካች ላይ ያስተላለፈውን የሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 2(ለ)2 መሰረት በማሻሻል በአስራ ስድስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም።

18. የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የመጀመሪያው ፓራግራፍ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህን ተፈጻሚ ማድረግ እንዳለባቸው ይደነግጋል። ይህም አንድ ሰው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎችን ከፈጸመና ወንጀሎቹ ነጻነትን በሚያሳጣ ቅጣት የሚያስቀጡ ከሆነ ለእያንዳንዱ ወንጀል ሊቀጣ የሚገባውን ቅጣት በመወሰንና ቅጣቱን በመደመር በወንጀለኛው

ላይ የሚወሰነውን ቅጣት ለማስላት የሚያስችል ቅጣት አወሳሰን መርህ ነው፡፡ በሌላ በኩል ድንጋጌው ድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህ የሚገድብና ውጤት አልባ የሚያደርግ ደንብ የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በያዝነው ጉዳይ በጽኑ እስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሁለት ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመዋል፡፡ እደዚህ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ለሁለቱ ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰኑት ቅጣት የድምር ውጤት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፍተኛ የጽኑ እስራት ቅጣት ሆኖ ከተደነገገው ሃያ አምስት አመት ጽኑ እሰራት ሊበልጥ እንደማይችል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ ገደብ ያስቀምጣል፡፡ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ የተቀመጠው ገደብ ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቱ፣በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የመጀመሪያው ፓራግራፍ መሰረት በጥፋተኛው ላይ ሊወሰን የሚገባው ድምር የቅጣት ውጤት ከሃያ አምስት ዓመት በላይ በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የቅጣት ድምር ውጤቱን ወደ ሃያ አምስት ዓመት ዝቅ በማድረግ እንዲወስኑ የሚያስገድድና ሕግ አውጭው በአዲስ መልክ በወንጀል ሕጉ ያስገባውን የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህን ውጤት አልባ የሚያደርግ ገደብ ነው፡፡

19. ይህም ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህን እንዲተገብሩ በሚደነግገው የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ1(ለ) የመጀመሪያው ፓራግራፍና የቅጣቱ ድምር ውጤት በወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው ሃያ አምስት አመት ጽኑ እስራት ሊበልጥ እንደማይችል አስገዳጅ ገደብ በሚጥለው በወንጀል የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ መካከል በይዘትም ሆነ በተግባራዊ አፈጻጸማቸው ክፍተትና አለመጣጣም ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሆኖም ህጉ ባለው ክፍተትና አለመጣጣም አመልካቾች ተጠቃሚ እንጅ ተጎጅ አይደሉም፡፡ ስለሆነም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) በመጀመሪው ፓራግራፍ የደነገገውን የድምር ውጤት የቅጣት አወሳሰን መርህ ዋጋ በማያሳጣ ሁኔታ ለተደራራቢ ወንጀሎች ፍርድ ቤቱ የሚወስነው ድምር የቅጣት ውጤት የወንጀል ሕግ አንቀጽ 108 ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው ሃያ አምስት ዓመት መብለጥ የለበትም በማለት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184 ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) ሁለተኛው ፓራግራፍ የጣለውን አስገዳጅ ገደብ ማሻሻል ለህግ አውጭው የስራ ኃላፊነትና ተግባር ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ካላይ በገለጽናቸው ወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች የሚታየው ክፍተት አመልካቾችን መብት የሚያጣብብ ሳይሆን እነርሱን በሚጠቅም መልኩ የተተረጎመና ሥራ ላይ የዋለ በመሆኑ አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ የህግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች ላይ የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ማጽናቱና በሶስተኛው አመልካች ላይ የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ)2 መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 83593 በአመልካቾች ላይ የወሰነው የቅጣት ውሳኔ የጸና መሆኑን አውቆ ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይተላለፍ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ 97203

መስከረም 30 ቀን 2007

**ዳኞች፡-**አልማው ወሌ
ሡልጣን አባተማም
መኮንን ገ/ሕይወት
ሙስጠፋ አህመድ
ተኽሊት ይመሰል

***አመልካች፡-*** 1.አቶ ታምራት ደምሴ
2.አቶ በሪሁን ደምሴ
3.አቶ ታደለ ሽቱ
} የቀረበ የለም

***ተጠሪ፡-*** የቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በመተከል ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካቾች እና አቶ አለኸኝ ጋሻው በተባሉት ግለሰብ ላይ የመሰረተው ክስ፡- በ1996 ዓ.ም በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1)(ሀ) እና 539/1/ሀ/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ታህሳስ 29 ቀን 2002 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 3፡00 በሚሆንበት ጊዜ ግልገል በለስ ከተማ ከወ/ሮ አለምፀሐይ ጌታሁን ሻይ ቤት አረቂ እየጠጡ በፈጠሩት ፀብ ለምንድን ነው የሰደብከን? በማለት የአሁኑ 1ኛ፣2ኛ አመልካቾች እና የስር 3ኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ አለሸኝ ሟች ኤርሚያስ ኃይሉን ሊደበድቡት ሲሉ በገላጋይ ከቤት ከወጡ በኋላ ከስር ሶስተኛ ተከሳሽ ጋር በመሆን ተከታትለው በመሄድ ኤርሚያስ ኃይሉን በአንድ ላይ ተባብረው በዱላና በድንጋይ ግንባሩንና መላ ሰውነቱን ደብድበው በግፍ ገድለዋል የሚል ነው፡፡አመልካቾች ክሱ ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ በክሱ ላይ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገልፀው የድርጊቱ አፈጻጸሙን በተመለከተም ክደዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን ያሰማ ሲሆን የስር ፍ/ቤትም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን መርምሮ አመልካቾች ድርጊቱን መፈፀማቸው በበቂ ሁኔታ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የአሁኑ አመልካቾችን እንዲከላከሉ ብይን ሰጥቶ የስር 3ኛ ተከሳሽ የነበሩትን ግለሰብ ግን በነፃ አሰናብቷል፡፡በዚህ ብይን መሰረትም አመልካቾች የመከላከያ ማስረጃዎችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃነት ቃል ክብደት የማይሰጠው ነው በማለት ውድቅ ከአደረገ በኃላ አመልካቾችን በዓቃቤ ሕጉ በኩል ተጠቅሶ በቀረበው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ በማድረግ እያንዳንዳቸውን በ17 (አስራ ሰባት አመት) ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡ከዚህም በኃላ አመልካች በጥፋተኝነትና በቅጣት ውሣኔው ላይ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸውን፣የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካቾች ህዳር 23 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱንም ባጭሩ፡- የበታች ፍርድ ቤቶች በአመልካቾች ላይ የሰጡት የጥፋተኛነት ውሣኔ አግባብነት የሌለውን ማስረጃ መሰረት ያደረገ ከመሆኑም በላይ ማስረጃውም ተገቢውን የማስረጃ ምዘና ስርዓት ተከትሎ ያልተመዘነ መሆኑን፣አድራጎቱ በአመልካቾች ተፈፅሟል ከተባለም አግባብነት ያለው ድንጋጌ ተራ በሆነ የሰው መግደል ወንጀል የሚሸፍን ነው እንጂ በግፍ ሰው መግደልን በሚሸፍነው ድንጋጌ ስር የሚወድቅ ያለመሆኑን፣ እንዲሁም የቅጣት ውሳኔውም የአመልካቾችን የእድሜ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና የበዛ መሆኑን በመዘርዝር ውሣኔው ሊለወጥ ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም አመልካቾች ለወንጀል ድርጊቱ ተጠያቂ የመደረጋቸውን አግባብነት ከወ/ሕ/አንቀጽ 23(2) ድንጋጌ አንፃር ለመመርመር ሲባል ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጉት አበይት ነጥቦች፡-

1. ከአመልካቾች ውስጥ ለሟች ሕልፈት ተጠያቂነት ያለበት የትኛው ነው?፣

2. ተጠያቂነት አለበት ሊባል የሚችለው አመልካች አለ ከተባለ አድራጎቱ የሚሸፈነው በየትኛው አንቀፅ ስር ነው? እና ቅጣቱስ ስንት ሊሆን ይገባል የሚሉት ሁነው ተገኝተዋል፡፡

**<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>** ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በዓቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ ለህልፈት ተዳርገዋል የተባሉት ግለሰብ ለህልፈት የተዳረጉት በአመልካቾችና በስር 3ኛ ተከሳሽ በነበሩት ግለሰብ በግብረአበርነት በተፈፀመባቸው አድራጎት መሆኑን የተጠሪ ክስ የሚገልጸው ጉዳይ ሲሆን ተጠሪ በሟች ላይ ለህልፈተ ሕይወት መድረስ ምክንያት የሆነውን አድራጎት የፈፀሙት አመልካቾች መሆናቸውን ለማስረዳት አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን ማቅረቡን የውሳኔው ግልባጭ የሚያስገነዝብ መሆኑን ነው፡፡በዚህ ረገድ የተሰሙት ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ሲታይም፡-1ኛው ምስክር ድርጊቱ የተፈፀመው በአቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ መሆኑን ጠቅሰው አመልካቾችና ሟች የምስክሩ ጎረቤት በሆኑት በወ/ሮ አለምፀሐይ ጌታሁን ሻይ ቤት ሲጠጡ እንደቆዩና ጎረቤታቸው ወደ ምስክሩ ቤት እራት ሊበሉ ሂደው አመልካቾችና ሟቹ እንደተጣሉና ምስክሩ እንዲያገላግሏቸው ለምስክሩ ሲነግሯቸው ምስክሩም ወደ መጠጥ ቤት ሂደው ሲመለከቱ ሁሉም ቁጭ ብለው እንደአገኟቸው፣ከዚያ በኋላ ሟቹ ቀድሞ ከቤቱ ሲወጣ አለኽኝ ጋሻው የተባለው የስር 3ኛ ተከሳሽ ሟችን ተከታትሎ መውጣቱንና ከአምስት ደቂቃ ቆይታ በኋላም የአሁኑ አመልካቾች ተከታትለው እንደወጡ፣በወቅቱ በመጠጥ ቤት ውስጥ ሟቹና የስር ተከሳሾች ሲጨቃጨቁ ምስክሩ መስማታቸውን፣ተከሳሾች ከቤት ከወጡ በኋላ ምስክሩ ወደ ቤታቸው ተመልሰው ሂደው ከተኙ በኃላ ከምሽቱ 7፡00 አከባቢ ጩኸት እንደሰሙና በበነጋታውም 2፡00 አከባቢ ሟቹ ሞተ ሲባል መስማታቸውን መስክረዋል፡፡አለምጸሐይ ጌታሁን የተባሉት 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር በበኩላቸው ድርጊቱ የተፈፀመው በዐቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ መሆኑን ጠቅሰው በሻይ ቤታቸው ሶስት ሰዎች ቀድመው ገብተው በብርሌ አረቄ ገዝተዋቸው እየጠጡ እያለ

የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማውራት እንደጀመሩና ከቆይታ በኂላ ስድብ ሲጀምሩ ምስክሯ ነገሩ ጠብ መሆኑን በመረዳት ጎረቤታቸው ለሆኑት ለዓቃቤ ህግ አንደኛ ምስክር ከሻይ ቤታቸው ወጥተው በመሄድ ስለጉዳዩ እንደነገሯቸውና ጎረቤታቸውም ወደ ምስክሯ ቤት መጥተው በመጠጥ ቤት የነበሩትን አመልካቾችን "ሌላ ሰው ለምን ትረብሻላችሁ?" በማለት ሲናገሯቸው ከመጠጥ ቤት የነበሩት ሰዎች ተከታትለው እንደወጡና ምስክሯም ከዚህ በኂላ የመጠጥ ቤቱን በር ዘግተው የተኙ መሆናቸውን መስክረዋል፡፡ሦስተኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክርም የአቃቤ ሕግ 1ኛ ምስክር ባለቤት መሆናቸውን ጠቅሰው የሰጡት የምስክርነት ቃል በይዘቱ ከ1ኛው ምስክር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነው፡፡4ኛው የአቃቤ ሕግ ምስክር ደግሞ ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ጊዜ በግልገል በለስ ከተማ 02 ቀበሌ ግብርና ፅ/ቤት ወደታች ባላቸው የግል ሻይ ቤት የሥር 3ኛ ተከሳሽ አለኸኝ እና ኤርምያስ የተባሉት ሰዎች ሂደው የሚጠጣ ሻይ ከአዘዙ እና ሻሂውን ከጠጡ በኂላ ከምሽቱ 3፡00 አከባቢ ከቤት ወጥተው እንደሄዱ፣ከምሽቱ 4፡30 ሲሆን ደግሞ አለኸኝ የተባለው ተከሳሽ ተመልሶ ወደ ሻሂ ቤታቸው ገብቶ ጅን አረቂ እንዲሰጠው ሲጠይቃቸው ምስክሯ የለኝም የሚል ምላሽ ሲሰጡት ይሄው ግለሰብ ሻሂ ጠጥቶ ለብቻው ተመልሶ መሄዱን መስክረዋል፡፡5ኛው የአቃቤ ህግ ምስክር በሰጡት የምስክርነት ቃል፡-በዓቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ እንዳልነበሩ፣ድርጊቱ ከተፈፀመ በኃላ የወንጀል ክትትሉን እንደጀመሩ፣ከወንጀሉ መፈፀም በኃላ የደምሴ ልጆች መሰወራቸውን፣አባታቸውም ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ታስረው እንደነበር፣አቶ ደምሴ የተባሉት ግለሰብም "አይ እኔን ከእስር ቤት ፍቱኝና ሌሎች ልጆች ስላሉ አፈላልጌ ላምጣ!" ብለው ለፖሊስ አቤቱታ እንደአቀረቡ፣ከዚያም ሰውየው ፖሊስ ይሰጠኝ በማለታቸው ፖሊስና ልዩ ኃይል ተሰጥቷቸው ታምራት የተባለው ልጃቸው ከስራ ቦታ ተይዞ እንደመጣ፣በወቅቱ "ድርጊቱን ከወንድሜ በሪሁን ጋር የፈፀምኩት እኔ ነኝ፣ ታደለና አለኸኝም በድብደባው ላይ አሉ፤ድርጊቱን የፈፀምነው እኛ ነን!" በማለት ለፖሊስ መናገሩን፣ድርጊቱን አራት ሁነው የፈፀሙት መሆኑንና ሟቹ ይሞታል በሚል ሃሳብ እንዳልፈፀሙ፤ሟችን የመቱትም ታምራት በዱላ ግንባሩን፣ሌሎች በቡጢ እና በድንጋይየመቱት መሆኑን መግለፁንና ከዚያም እንደሸሹና እንደተበታተኑ እንዲሁም ጥዋት ወደ አዝመራ ቦታ ሂዶ ቆይቶ በልዩ ኃይል መያዙን ሲናገር መስማቱን የመሰከረ ነው፡፡6ኛው ምስክር በበኩሉ በወቅቱ በሟች ለቅሶ ላይ እያሉ "የእናተ ቤተሰብ ነው!" በሚል ምክንያት ተይዘው በፖሊስ ጣቢያ እንደነበሩ፣ምሽት ላይ ታምራት የተባለውን ተከሳሽ ፖሊሶች ይዘው ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እያለ አንድ የፖሊስ አባል ታምራትን "ለምንድነው እንዲህ አድርጋችሁ የምትማቱት?" በማለት ሲጠይቀው ታምራት ጭንቅላቱን አልመታሁትም፤እኔ ጀርባውን ነው የመታሁት፣ጭንቅላቱን የመታው ሰው ሌላ ነው ብሎ ሲመልስለት መስማቱን መስክሯል፡፡

እንግዲህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካቾችን ጥፋተኛ ለማድረግ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡት ምስክሮች ቃል ይዘት ከላይ የተጠቀሰው መሆኑን በውሳኔው ላይ የገለፁት ጉዳይ ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርድ ሐተታው በግልጽ ያስቀመጠው ድምዳሜውም ከዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል አመልካቾች ሟችን ሲመቱትና ሲገድሉት አየሁ በሚል ያልተገለጸ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካቾችን ለወንጀል ድርጊቱ ኃላፊ ያደረጋቸው በክሱ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ በሟቹና በአመልካቾች መካከል ጠብ ተፈጥሮ ሟቹ ከስር ሶስተኛ ተከሳሽ ጋር በአንድ በኩል፣አመልካቾቹ ደግሞ በሌላ በኩል ተቀምጠው ሟቹ ምራቅ ሲተፋ አመልካቾች "ይህች ምራቅ ዛሬ ደም ትሆናለች!" በማለት ተናገረው ወዲያውኑ ሟቹና የስር 3ኛ ተከሳሽ ከአረቂ ቤቱ ወጥተው ሲሄዱ ወዲያውኑ የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙን ተረጋግጧል በሚል ድምዳሜ ነው፡፡

አመልካቾች ከሚከራከርባቸው ነጥቦች ውስጥ የአመልካቾችን የድርጊት ፈፃሚነት በተገቢው መንገድ አቃቤ ሕግ በማስረጃ ያለማስደገፉንና የአቃቤ ሕግ የአይን ምስክሮች ድርጊት ፈፃሚዎችን በወቅቱ ስለመለየታቸው ሳይመሰክሩ ሰምተናል በማለታቸው ብቻ ጥፋተኛ መባላችን ያላግባብ ነው የሚለውን በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃ ከሚመዘንበት መርህ ጋር በማጣቀስ ነው፡፡

በመሰረቱ በአንድ የወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ ማስረጃ በቂና አሣማኝ በሆነ ሁኔታ የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙንና የወንጀል ድርጊቱን ፈፃሚውን ማንነት በትክክል ለይቶ ማሳየት ያለበት ስለመሆኑ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ድንጋጌ ይዘትንና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡አንድ ሰው ለወንጀል ድርጊት ኃላፊ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት የሚገባው ወንጀል መስራቱ ወይም መፈፀሙና ተሰራ ወይም ተፈፀመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በተከሳሹ መፈፀሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4)፤32፣40፤57፣ 58(1) እና ከወ/መሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141፣142 እና 149 ድንጋጌዎች አገላለፅና መንፈስ መመልከት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ የሚቆጠረው ወንጀሉን እርሱ ራሱ በቀጥታ ቢያደርግ ወይም በቀጥታ ባያደርግም እንኳን በመላ ሀሳቡና አድራጐቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተከፋይ በመሆን ወንጀሉን የራሱ ያደረገ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ለ/ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ከሳሽ የሆነው አቃቤ ሕጉም ይህንኑ በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ መወጣት አለበት፡፡

አመልካቾች ሟችን በቀጥታ መትተው ስለመግደላቸው አይተናል የሚል የአቃቤ ሕግ ምስክር ባይኖርም ሟች ጋር በእለቱ በአረቄ ቤት ሲጨቃጨቁ እንደነበር፣ሟች ምራቅ ሲተፉም ምራቁ ደም እንደሚሆን ተናግረው እንደነበር በአቃቤ ሕግ ምስክሮች ተገልፆአል፡፡ይሁን እንጂ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች በወቅቱ ከሟች ጋር ጠብ አስነስተው የነበሩትን ሰዎች ማንነት የገለፁ ቢሆንም ለሟቹ ህልፈተ ሕይወት እያንዳንዱ አመልካች የነበረውን ተሳትፎ ያልተናገሩ ከመሆኑም በላይ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል በሁሉም አመልካቾች ላይ እንደ አከባቢ ማስረጃ የሚወሰድ ነው ቢባልም ማስረጃው በ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ላይ ግን ጥንካሬ የሌለው ሁኖ ተግኝቷል፡፡በሌላ አነጋገር የተጠሪ ምስክሮች በወቅቱ ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ /Circumstantial Evidence/ የምስክርነት ቃል ሰጥተው የተመለሱ ቢሆንም ከጠቡ መነሻ ውጪ ከጠቡ በኋላ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የነበራቸውን ሚና በግልጽ የሚያሳዩ አይደሉም፡፡ በአገራችን የህግ ሥርዓት ምስክሩ ስለአጠቃላይ ሁኔታዎች በአይኑ የታዘበውን በጆሮው የሰማውንና የሚያውቀውን ፍሬ ጉዳይ ሊመሰክር እንደሚችልና የምስክሩም ቃል ህጋዊ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 137 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡ይሁን እንጂ በ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ላይ በአቃቤ ምስክሮች የተሰጠው የምስክርነት ቃል በአረቄ ቤት የነበረውን ጠብ እና ሟች ምራቅ ሲተፋ ይህ ምራቅ ደም ሊሆን እንደሚችል አመልካቾች ከመናገራቸው ውጪ በድርጊቱ ወቅት ወይም በኋላ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የፈፀሙትን አድራጎት የሚያሳይ አይደለም፡፡ስለሆነም በ2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ላይ የቀረበው የአቃቤ ሕግ ማስረጃ በወንጀል ሕግ የሚቀርብ ማስረጃ ስለጉዳዩ ለማስረዳት በቂና አሳማኝ ማስረጃ ነው ብሎ ለመደመድም የሚያስችል ሊሆን ይገባል የሚለውን መለኪያ ያሟላ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ስለሆነም በእነዚህ አመልካቾች የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

1ኛውን አመልካች ታምራት ደምሴን በተመለከተ ግን 1ኛ፣2ኛ እና 3ኛ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች አመልካቹ በወቅቱ ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ ከሰጡት የምስክርነት ቃል በተጨማሪ አመልካቹ ከወንጀል ድርጊቱ በኂላ በፖሊስ ተይዞ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተይዞ ከገባ በኂላ ወንጀሉን መፈፀሙንና እንዴት እንደፈጸመ ጭምር ሲገልፅ እንደነበር 5ኛ እና 6ኛ የአቃቤ ምስክሮች ከመሰከሩት ቃል መረዳት የሚቻል ሁኖ ስለተገኘ አመልካቹ በሟቹ ህልፈተ ሕይወት ተሳትፎ እንደነበረው በዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተደጋጋፊነትና ተመጋጋቢነት ባለው ጠንካራ የአከባቢ ማስረጃ የተረጋገጠ ሁኖ አግኝተናል፡፡በመሆኑም አመልካች ታምራት ደምሴ በቀጥታ የወንጀሉ ተሳታፊ ሁኖ በመላ ሀሳቡ የወንጀሉን ድርጊት እንዲሁም ውጤቱን የራሱ ያደረገ ስለሆነ አመልካቹ ለወንጀል ድርጊቱ ኃላፊ ልባል አይገባም በማለት ያቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሁኖ አልተገኘም፡፡

አንደኛውን ጭብጥ በተመለከተ ስናጠቃልለው 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ለወንጀሉ ድርጊት ኃላፊ የተባሉት ዓቃቤ ሕግ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 141 በሚያስቀምጠው የማስረጃ መለኪያ መሰረት የአመልካቾችን ተሳትፎ ባላስረዳበትና በሕጉ የተጣለበትን ግዴታ ባልተወጣበት ሁኔታ በመሆኑ በእነዚህ አመልካቾች ላይ የተሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሲሆን 1ኛ አመልካች ግን ሟች ከመሞቱ በፊትና ሲሞት የነበረው የወንጀሉ ተሳትፎ በሚገባ የተረጋገጠ በመሆኑ በሰው ግድያ ወንጀል ተጠያቂ መደረጉ የሚነቀፍ ሁኖ አይደለም ብለናል፡፡

<u>ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u> የስር ፍርድ ቤቶች 1ኛ አመልካችን ተጠያቂ ያደረጉት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539(1(ሀ)) ስር ነው፡፡

በመሰረቱ የሰው ግድያ ወንጀል በወንጀል ሕግ አንቀፅ 539(1(ሀ)) መሰረት ድርጊት ፈጻሚውን ሊያስጠይቅ የሚችለው ድርጊቱ ሆነ ተብሎ አስቀድሞ በማሰብና በመዘጋጀት ሲፈፀም ወይም በአንቀጽ 84 ወይም 86 ስር የተመለከቱት አክባጅ ሁኔታዎች በተገኙበት ሁኔታ የወንጀል አድራጊው በተለይ ጨካኝ፣ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን ሲያመለክቱ ስለመሆኑ ተጠቃሹ ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በድንጋጌው ስር የተመለከቱት የወንጀሉ ማቋቋሚያ ነጥቦች በየራሳቸው መቆም የሚችሉ ነጥቦች ስለመሆናቸው ነው፡፡

የወንጀል ህግ አንቀጽ 540 ድንጋጌ ሲታይ ደግሞ፡-

"ማንም ሰው አገዳደሉ በአንቀጽ 539 የተመለከተውን ያህል ከባድ ወይም በአንቀጽ 541 የተመለከተውን ያህል ቀላል ባልሆነ ሁኔታ አስቦ ሌላ ሰውን የገደለ እንደሆነ፤ ከአምስት ዓመት እስከ ሃያ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል በሚል አስቀምጧል፡፡

በመሠረቱ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 539 እና 540 መሠረት የሚፈፀሙ ግድያዎች ሆነ ተብሎ ወይም በማወቅ /አስቦ/ የሚሰሩ ናቸው፡፡ በዚህ ረገድ ሁለቱ አንቀፆች ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ነገር ግን ሁለቱን አንቀፆች የተለያዩ የሚያደርጓቸው መሰረታዊ ነጥቦች መኖራቸው የሚታወቅ ነው፡፡ አንድ ሰው በወ.ህ.አንቀጽ 539/1/ሀ/ መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ እንዲገኝ በዚሁ አንቀጽ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡እነዚህን ሁኔታዎች ደግሞ ሰውየው ድርጊቱን ለመፈፀም ካነሣሣው ሃሣብ እና ከድርጊቱ አፈፃፀም አንፃር በመመርመር የድንጋጌውን ትክክለኛ አፈጻጸም መለየት ይቻላል፡፡በድንጋጌው ስለሃሳብ ሁኔታ የሚገልጹትን ሁኔታዎች ስንመለከትም አስቀድሞ የማሰብ ሁኔታ፤ ቂም በቀል፣ጥላቻ፤ ቅናት ወዘተ----የሚሉ የሚገኙ ሲሆን ከባድ የድርጊት አፈፃፀም መኖርን የሚያመላክቱ ነጥቦች ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84

ስር የተመለከቱትና በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ በአንቀጽ 86 መሠረት ከባድ ምክንያቶች ናቸው ብሎ የሚቀበላቸውን ሁኔታዎች የሚያካትቱ ናቸው፡፡

አንድ ሰው ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት የሃሣብ ሁኔታዎች ወይም የድርጊት አፈፃፀም አንዱን እንኳ ፈጽሞ ቢገኝ እና ይህም ሁኔታ ሲታይ ገዳዩ "በተለይ" ጨካኝ፣ ነውረኛ ወይም አደገኛ የሚያሰኝ አይነት ሆኖ ከተገኘ በአንቀጽ 539/1/ሀ/ መሠረት ጥፋተኛ ሊሰኝ እና ለዚሁ አድራጎት በሕጉ የተመለከተው ቅጣት ውሳኔ ሊተላለፍበት ይገባል፡፡

አንቀጽ 539/1/ሀ/ በቅድሚያ እንዲሟላ የሚፈልገው መሰረታዊ ነጥብ የአገዳደሉ ሁኔታ አድራጊው በተለይ ጨካኝ፣ ነውረኛ ወይም አደገኛ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ መገኘትን ነው፡፡በድንጋጌው ስር "በተለይ" የሚለው ቃል የሚያስገነዝበው ከተራ አገዳደል ወይም የሃሣብ ሁኔታ ውጭ በሆነ አድራጐት ወይም ለጥቃት መገልገያ የተደረገው መሣሪያ በሟች ላይ ስቃይና መከራ ማሣደር እንዳለበት፣ ግድያውም ከተራው ሁኔታ የተለየ እንደነበር የሚያመለክት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡፡ በህጉ በተለይ ጨካኝ ነውረኛ ወይም አደገኛ መባሉ የአገዳደሉ ሁኔታና የመግደያው መሣሪያ አደገኛነት፣ ፍፁም ጨካኝነትን፣ ነውረኛነትን ወይም የተጋነነ አደገኛነትን ማሳየት እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው፡፡ስለሆነም የወ.ሕ.አንቀፅ 539(1(ሀ)) የማክበጃ ልዩ ሁኔታዎች በመኖራቸው ምክንያት ሆን ተብሎ የተፈፀመው ግድያ "ከባድ የሰው ግድያ" የሚባልበትን ምክንያቶች የያዘ ነው፡፡እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች በሌሉበት አንድን ተከሣሽ በዚህ አንቀጽ ስር ጥፋተኛ ሊባል የማይችል መሆኑን የሕጉ ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ ከእነዚህ እና በተጠቃሹ አንቀፅ በፊደል "ለ" እንዲሁም "ሐ" ስር ከተመለከቱት የድንጋጌዎቹ ማቋቋሚያዎች ውጪ ሆን ተብሎ የሚደረግ ሰው የመግደል ወንጀል የሚያስቀጣው በአንቀጽ 540 ስር ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣም አመልካች ሟችን ለመግደል አስቀድሞ ሐሳብ ያልነበረው መሆኑ ግልጽ ሲሆን አፈጻጸሙ ሲታይም በተለይ ጨካኝነት ያለበት ነው ለማለት የሚያስችል ስለመሆኑ የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል አያሳይም፡፡እንዲሁም የአገዳደሉ ሁኔታና የመግደያው መሣሪያ አደገኛነት ፍፁም ጨካኝነትን፣ ነውረኛነትን ወይም የተጋነነ አደገኛነትን አያሳይም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ አድራጎቱ በእለቱ በተፈጠረው ያለመግባባት በቀላሉ ለህልፈት የሚዳረግ የሰውነት ክፍል በዱላ በመምታት የሆነው ይሁን በማለት የፈፀመውና በተራ የሰው ግድያ ወንጀል ስር የሚሸፈን እንጂ በግፍ ሰው የመግደል ወንጀል በሚያስጠይቅበት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 539(1(ሀ)) ድንጋጌ መሰረት የሚጠየቅበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች 1ኛ አመልካችን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 539(1ሀ) ስር ጥፋተኛ ያሉት አጠቃላይ የድርጊቱን አፈፃጸም ከድንጋጌው ይዘትና መንፈስ ጋር ሳያገናዝቡ ሁኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ለ-2) ድንጋጌ መሰረት በመለወጥ 1ኛ አመልካች(ታምራት ደምሴ) የወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ድንጋጌን የተላለፈ ጥፈተኛ ነው በማለት ወስነናል፡፡

ቅጣትን በተመለከተ 1ኛ አመልካች ሊቀጣ የሚገባው በዚህ ችሎት ጥፋተኛ በተባለበት የሕግ ድንጋጌ መሰረት ነው፡፡አመልካች ተራ የሆነ የሠው ግድያ ወንጀል መፈፀሙ በሚገባ ተረጋግጧል፡፡በወንጀል ሕግ አንቀጽ 540 ስር ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ደግሞ ሊቀጣ የሚገባው ከአምስት አመት እስከ ሃያ አመት ጽኑ እስራት ነው፡፡

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ "የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል

እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሠብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሣሠንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሣዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን የቅጣት አወሳሳን ደንቡ በግልፅ ያሳያል፡፡ከላይ እንደተገለጸው የወንጀል ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2)ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ይህ ችሎትም እነዚህ ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤አመዛዝኗልም፡፡ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ ድርጊቱ በተፈጸመበትና ክርክሩ በስር ፍርድ ቤት ታይቶ ዳኝነት በተሰጠበት ጊዜ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ደረጃ ያልወጣለት የነበረ ሲሆን በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ደግሞ ደረጃ የወጣለት ነው፡፡እኛም ጉዳዩን ከዚሁ ከአዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንፃር ተመልክተናል፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች ከሟች ጋር ለጠብ የተዳረገው በሟቹ ስድብ ምክንያት ሲሆን ይህም ለወንጀል ድርጊቱ መንስኤው ሟቹ መሆናቸውን የሚያሳይ ሁኖ ለድርጊቱ አፈጻጸም አመልካች የተጠቀመበት መሳሪያም ዱላ የነበረ ሁኖ የዱላው አይነትና አደገኛነትም በማስረጃ ያልተረጋገጠ መሆኑ ሲታይ አፈፃፀሙ የራሱ የሆነ የተለየ ዘዴ የነበረው መሆኑን የማያሳይ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት የወንጀሉ ደረጃው 2 ሁኖ ይሄው ደረጃ በእርከን 23 ስር የሚወድቅ ነው፡፡በዚሁ እርከን ደግሞ የፍርድ ቤቱ የፍቃድ ስልጣን ከስድስት አመት እስከ ሰባት አመት ከሁለት ወር ነው፡፡ከዚሁ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ የመነሻ ቅጣቱን ይዘን የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶችን ባለመኖራቸው እርከኑን ከፍ ማድረግ ያለመቻሉን ተገንዝበናል፡፡በሌላ በኩል አመልካች ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያም ሆነ ልዩ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያሉት መሆኑን በስር ፍርድ ቤት በማስረጃ ተደግፎ የተመዘገበለት ያለመሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም በእርከን 23 ስር ካለው የፍርድ ቤቱ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ 1ኛ አመልካችን (ታምራት ደምሴን) ያርማል፣መሰል ወንጀለኞችን ያስጠንቅቃል ያልነው የቅጣት መጠን ሰባት አመት ሁኖ ስለአገኘን አመልካች በጉዳዩ ላይ የታሰረው ካለ የሚታሰብለት ሁኖ በዚሁ የቅጣት መጠን እንዲቀጣ በማለት ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በማሻሻል ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ውሣኔ**

1. በመተከል ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 04545 ሚያዚያ 5 እና 6 ቀን 2003 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 02856 ግንቦት 02 ቀን 2003 ዓ/ም፣በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03200 መስከረም 11 ቀን 2004 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 2ኛ አመልካች በሪሁን ደምሴ፣3ኛ አመልካች ታደለ ሽቱ ሟች ኤርሚያስ ሃይሉን ስለመግደላቸው በበቂና አሳማኝ ሁኔታ ስላልተመሰከረባቸው በእነዚህ አመልካቾች ላይ የተሰጠውን የጥፋተኛነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ለ-1) መሰረት ሙሉ በሙሉ በመሻር አመልካቾቹን በነጻ እንዲሰናበቱ በማለት ወስነናል፡፡አመልካቾቹ በሌላ ወንጀል የማይፈለጉ መሆኑ ከተረጋገጠ ወዲያውኑ ከእስር እንዲፈቱ ተገልፆ የመፍቻ ትዕዛዝ ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይድረሰው ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡
3. 1ኛ አመልካች ታምራት ደምሴ በሟች ኤርሚያስ ኃይሉ ህልፈት ተጠያቂ መደረጉ በአግባቡ ተመስክሮበት ሲሆን የአመልካቹ አድራጎት የሚሸፈነው ግን በወ/ሕ/አንቀጽ 539(1(ሀ) ሳይሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 540 ስር ነው በማለት በዚሁ የሕግ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ በማድረግ በጉዳዩ ላይ የታሰረው ማናቸውም ጊዜ የሚታሰብለት ሁኖ በሰባት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስነናል፡፡
4. በ1ኛ አመልካች በዚህ ችሎት ተሻሽሎ በተወሰነው የቅጣት ውሳኔ መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይድረስ ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ. 98283

መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

መኮንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ሐጐስ ገ/ሄር መኮንን

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል የስነ/ፀ/ሙ/ኮ - ዐ/ሕግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ፍርድ**

የአሁኑ አመልካች በወንጀል ህጉ አንቀጽ 407(2) የተመለከተውን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በትግራይ ክልል በደቡብ ዞን አሰላ ወረዳ ፍ/ቤት ዳኛ ሆኖ ሲሰራ ሥልጣኑን አላግባብ በመጠቀም የመንግስት የአበል አከፋፈል ሥርዓት በመጣስ ለራሱና ለሥራ ባልደረቦች ሊከፈል የማይገባውን ብር 7653.4 እንዲከፈል በማድረጉ በፈፀመው በሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም ወንጀል ተከሷል ሲል የአሁን ተጠሪ ክስ አቅርቦበታል፡፡

ጉዳዩን በቅድሚያ የተመለከተው የአላማጣ ማዕከላዊ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኂላ አመልካች በተዘዋዋሪ ችሎት ስም ከሥራ ቦታዬ ወደ ቀበሌዎች ሄጃለው በማለት በተሞክሮ ልውውጥ ስም፤ በመሀበራዊ ፍ/ቤትና የመሬት ዳኞች ሥልጠና ስም አበል አላግባብ መውሰዱ ፤ዳኞች ስልጠና ሰጥተዋል በማለት በፔሮል ወደ ቀበሌ እንደወጡ አስመስሎ አበል መክፈሉ ፤ የሂሳብ መደብ በማይፈቅድበት ሁኔታ በራሱ ስም አበል ወጪ በማድረግ የፅሕፈት መሣሪያ መግዛት እና ከፋይናንስ ደንብ እና መመሪያ ውጭ ስለመስራቱ በራሱ በዝርዝር የተመለከተውን እና የቀረበበትን የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ ማስተባበል ባለመቻሉ እንደ ክሱ አቀራረብ ጥፋተኛ ነው በማለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን ተቀብሎ በ1(አንድ) ዓመት ፅኑ እስራት እና በብር 2000 /ሁለት ሺህ /መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔው የሚነቀፍበት ምክንያት የለም በማለት ቅሬታውን ውድቅ አድርገዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍ/ቤት የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቹ የካቲት 24 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ 5 (አምስት) ገጽ ዝርዝር ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ተጠቃሎ ሲታይ የፍርድ ቤቱ ሥራ እንዳይጉዳ ብሎ የፈፀምኩት መሆኑ እየታወቀ፤በአግባቡም ሣይጣራ ተድበስብሶ የታለፈ በመሆኑ፤የቀረቡት ማስረጃዎች ከሚመለከታቸው ህጐች ሳይገናዘብ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑና ፤ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 33075 ባሳለፈው ውሳኔ የዳኝነት ሥራ በሚያከውኑበት ጊዜ የሚፈፅሙ ጥፋቶች እና ስህተቶች ዳኞች በስልጣን ያለ አግባብ መጠቀም በሚል ወንጀል ሊከሠሱ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሎ ተተርጉሞ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ በነፃ ልሰናበት ብለዋል፡፡

ቅሬታቸው ተመርምሮ ፈፀሙት የተባለው ድርጊት ጥፋተኛ በተባሉበት የህግ አንቀጽ ሥር የሚወድቅ መሆኑን ወይም ጉዳዩ ከዳኝነት ሥነ ምግባርና ዲሲፕሊን አኳያ የሚታይ መሆኑን ለማጣራት ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሠጡበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ሚያዚያ 9/2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ በወ/ህ/ቁ.407(2) መከሰሱ እና ጥፋተኛ መባሉ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ፤አስቀድሞ በሰ/መ/ቁ. 33075 የተሰጠው ውሳኔም የዳኝነት ሥራ በመከናወን ላይ እያለ የሚፈፀሙ ጥፋትና ሥህተትን እንጅ መሠል ተግባርን የሚመለከት ባለመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ያሳለፉት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡ አመልካቹም ግንቦት 2/2006 ዓ.ም የተፃፈ ክርክራቸውን የሚያጠናክር የመ/መልስ አቅርበዋል፡፡

ከላይ ባጭሩ ለመግለፅ የሞከርነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ ይዘን መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ፍሬ ነገሩን የማጣራት እና ማስረጃ ለመመዘን ሥልጣኑ የተሰጠው የሥር ፍ/ቤት አመልካቹ መንግስት የፋይናንስ ህጐች እና ደንቦች ከተፈቀደው ውጭ በአጠቃላይ ብር 7,650.40 እንዲወጣ በማድረግ ለራሱም ሆነ ለሥራ ባልደረቦቹ መጠቀሚያ በማድረግ በኃላፊነቱ አላግባብ መገልገሉን አረጋግጧል፡፡

ይኸው በማስረጃ ተረጋግጧል የተባለው አድራጐት በመንግስት ሥራ ላይ የተፈፀመ ከዳኝነት ሥራ ጋር ተቀላቅሎ ሊታይ የማይገባ የወንጀል ጥፋት ነው፡፡

አመልካቹ በዳኝነት ተሹመው በቋሚት የዳኝነት የመንግሰት ሥራን የሚሰሩ የመንግስት ሠራተኛ በመሆናቸው እና ይሠሩበት የነበረው የወረዳ ፍ/ቤትም በመንግስት በጀት ተመድቦለት የዳኝነት መንግስታዊ ሥራ የሚከናወንበት መስሪያ ቤት በመሆኑ በመንግስት ሥራ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የሚመለከቱ የወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች በመሠል ጥፋቶች ላይም በተመሳሳይ ተፈፃሚነት የሚሆኑ ናቸው፡፡ /የወ/ህ/ቁ. 402(1) እና (2) ይመለከታል፡፡

ሌላው መከራከሪያ እና የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ለመባሉ ምክንያት የሆነው ጉዳዩን ከዳኝነት ሥነ ምግባር እና ዲሲፕሊን አኳያ የሚታይ መሆኑን የተመለከተ ነው ፡፡

በትግራይ ክልል ዳኞች እና ሬጅስትራሮችን ለማስተዳደር ተሻሽሎ የወጣው ደንብ ቁጥር 1/2003 በመንግስት ገንዘብ ወይም ንብረት በዳኞች የሚፈፀምን ያላግባብ መጠቀም እና መውሰድ

የዲስፒሊን ጥፋት አድርጐ ይዟል፡፡ ነገር ግን የዲስፒሊን ደንቡ መሠል ድንጋጌ መያዙ በወንጀል ገረድ የሚኖረን ኃላፊነት የሚያስቀር አይደለም፡፡

የዲስፐሊን ጉዳዩች የሚቋቋሙበት፣ የሚመሩበት ሥርዓት እና ከሚሠጠው ውሳኔ የወንጀል ጥፋቶች ከሚቋቋሙበት፣ከሚመሩበት ሥርዓት እና ከሚሰጠው ውሣኔ ተለይቶ ሊታይ ይገባል፡፡ ስለሆነም የተፈፀመው ጥፋት የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆን አለመሆኑ ከዲስፒሊን ጉዳዩ ጋር ሊያታይ አይገባም፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 33075 ዳኛ ብርቁ ባላዬ እና የአማራ ክልል ስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በተከራከሩበት ጉዳይ ጥር 13/2001 ዓ.ም ባሳለፈው ውሳኔ የዳኝነት ሥራን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚፈፅሙ ስህተቶች እና ጥፋቶች ሁሉ ዳኛን በሥልጣን አላግባብ መገልገል ወንጀል ሊያስጠይቁ የማይችሉ ስለመሆናቸው መወሠኑ የዳኞችን ህገ መንግስታዊ የውሳኔ ነፃነት ለማጠናከር እንጅ በእጃችን እንዳለው ጉዳይ ከዳኝነት ሥራ ጋር ያልተያያዙ እና የአስተዳደር ስራ ሲያከናውኑ የሚፈፀሙ የወንጀል ጥፋቶች ሁሉ ተጠያቂነትን የሚያስቀር ትርጉም የሚሠጠው ባለመሆኑ አመልካቾች ይኸው ውሳኔ በማመሳሰል ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚ እንዲሆን ያቀረቡት ጥያቄ በህጉ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

በአጠቃላይ አመልካቾች በነበራቸው የሥራ ኃላፊነት ምክንያት ሊጠብቅ እና ሊከላከሉት የሚገባን የህዝብ እና የመንግስት ንብረት ከህግ ውጭ ሥልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም ለፈፀሙት ጥፋት በስር ፍ/ቤቶች የተላለፈባቸው ውሣኔ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል ተከታዩንም ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰጠው መ/ቁ. 6111/06 ታህሳስ 3 ቀን 2006 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ ፤የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.58434 ግንቦት 13 ቀን 2005 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ እና በደቡባዊ ዞን ማዕከላዊ ፍ/ቤት የአላማጣ ምድብ ችሎት በወ/መ/ቁ.02867/05 የካቲት 26/2005 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.195(2)(ለ)(2) መሠረት ፀንቷል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ግ**

የሰ/መ/ቁ.92826

ጥር 05 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች**፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች**፡- የደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት ዐቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ፀሐይ መጫሎ - ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍርድ**

ጉዳዩ የወንጀል ጉዳይ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች የክልሉን የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽንን በመወከል በአሁኗ ተጠሪና በሌሎች ሁለት ሰዎች ላይ በካፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡የአመልካች ክስ ይዘትም፡- ተጠሪና በስር ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ኢምቶ ወ/ማሪያም አቶ ዳዊት ደስታ የተባሉት ግለሰቦች ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሳቸው ለማግኘት በማሰብ በዬቻ ወረዳ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ውስጥ የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ኢምቶ ወ/ማሪያም ዋና ገንዘብ ያዥ፣የአሁኗ ተጠሪ ደግሞ የክፍያ ኦፊሰር፣ቼክ አዘጋጅና ፈራሚ፣የስር ሶስተኛ ተከሳሽ የነበሩትና በብይን በነፃ የተሰናበቱት አቶ ዳዊት ደስታ ደግሞ የክፍያ ሰራተኛ እና ቼክ ፈራሚ በመሆን እየሰሩ የአሁኗ ተጠሪ ከኢትዩጵያ ንግድ ባንክ ቦንጋ ቅርንጫፍ ከሂሳብ ቁጥር GOV 787 ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ) ብር ወጪ ተደርጎ ለስር አንደኛ ተከሳሽ እንዲከፈል ቁጥሩ 0741998 የሆነውን ቼክ ሰኔ 30 ቀን 2004 ዓ.ም አዘጋጅተው ከስር ሶስተኛ ተከሳሽ ጋር ፈርማ በኃላፊ ሳይታዘዙ በመስጠታቸውና የስር 1ኛ ተከሳሽም ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ) ከተጠቃሹ ባንክ አውጥቶ ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1(ሀ)) እና 676(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በግብረአበርነት ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈፅመዋል የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ክሱን ክደው የተከራከሩ ሲሆን አቃቤ ሕግ በበኩሉ አሉኝ ያላቸውን ማስረጃዎችን አቅርቦ ካሰማ በሁዋላ የተጠሪ የመከላከል መብታቸው ተጠብቆላቸው የመከላከያ ምስክሮችን አሰምተዋል፡፡የሥር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ በመከላከያ ምስክሮች የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን ሊያስተባብሉ አልቻሉም በሚል ምክንያት ክስ በቀረበባቸው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጓል፡፡ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበልና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት አስልቶ በአስራ አራት

አመት ፅኑ እስራት እና በብር 7000.00(ሰባት ሺህ) እንዲቀጡ ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛቸውን ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ተጠሪ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልል ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ግን ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ተደርጎ ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የወንጀል ድርጊት መፈፀማቸው መረጋገጡን ተቀብሎ አድራጎቱ የሚሸፈንበትን ድንጋጌ በተመለከተ አመልካች ተጠሪ ገንዘቡን ለግል ጥቅማቸው ስለማዋላቸው ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ስለማዋላቸው በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል ምክንያት በዓቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻ የተጠቀሰውን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 113 (2) መሰረት ወደ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 420(1) ለውጦ በዚሁ ድንጋጌ ስር የሙያ ግዴታ የመጣስ አድራጎት ፈጽመዋል በማለት ወስኗል፡፡ቅጣቱንም በተመለከተም በዚሁ በተለወጠው ድንጋጌ ስር በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ደረጃ ላልወጣላቸው የወንጀል ድንጋጌዎች ደረጃ የሚወጣበትን አግባብ ዘርዝሮና ከግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት ጋር በማገናዘብ መመርመሩን ገልፆ ተጠሪ በአንድ አመት ቀላል እስራት እና በብር 5000.00 (አምስት ሺህ) ብር እንዲቀጡ ወስኗል፡፡የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-የተጠሪ አድራጎት ከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል ሁኖ እያለ የስራ ኃላፊነትን ባለመወጣት የተፈፀመ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም የተጠሪ አድራጎት የሚሸፈነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 676(1) ሳይሆን በአንቀጽ 420(1) ስር ነው ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸውም ቀርበውም በፅሑፍ በሰጡት መልስ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ሕጋዊ ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው ውሳኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውን ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚያቋቁሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23 (2) በግልፅ ደንግጓል፡፡እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች የሚመለከት ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደምተከተላቸው ከድርጊት ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ አንቀፅ 24፣57 እና 58 ድንጋጌዎች ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን የሚመለከቱ መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉት በመንግስት መስሪያ ቤት በክፍያ ኦፊሰርነት፣ቼክ አዘጋጅነትና ፈራሚነት የስራ መደብ ላይ ተመድበው ሲሰሩ በቀን 30/10/2002 ዓ/ም ቁጥሩ 0741998 በሆነ ቼክ ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ) ለስር አንደኛ ተከሳሽ እንዲከፈል አዘጋጅተው በቼኩ ጉማጅና በባንክ ክፍያ ደረሰኝ ላይ ሳያስፈርሙ ሰጥተው የስር አንደኛ ተከሳሽ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቦንጋ ቅርንጫፍ ከሂሳብ ቁጥር GOV 787 ብር 100,000.00(አንድ መቶ ሺህ) ብር ወጪ አድርጎ ለግል ጥቅሙ እንዲያውል አድርገዋል፣ተጠሪ

ይህንኑ ያደርጉትም ያዘዛቸው ኃላፊ ሳይኖር መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተጋግጧል በሚሉ ምክንያቶች መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ከክርክሩ አመጣጥና ከስር ፍርድ ቤቶች የውሳኔ ይዘት አንጻር በዚህ ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የተጠሪ አድራጎት የሚሸፈነው በየትኛው ድንጋጌ ስር ነው? የሚለው ነው፡፡

ተጠሪ በአመልካች የተከሰሱትና በስር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባሉት የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 676/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከመንግስት የሂሳብ ቁጥር ብር 100,000.00 ለሌላ ሰው ጥቅም እንዲውል በማድረጋቸው ከባድ የእምነት ማጉደልና የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል ተብሎ ነው፡፡የወንጀል ሕጉ 676 በወንጀል ሕግ 675 የሚፈፀመውን የእምነት ማጉደል ወንጀል የሚከብ ድበትን ሁኔታ የሚዘረዝር ነው፡፡የድንጋጌው መሰረታዊ ማቋቋሚያ ነጥቦች በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675 ስር የተመለከቱት የእምነት ማጉደል ወንጀል ማቋቋሚያ ሁኔታዎች ስለመሆናቸው የሁለቱ ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባል፡፡ከባድ የእምነት ማጉደል የሙስና ወንጀል የሚሆነው ደግሞ የመንግስት ሰራተኛ ወይም የመንግስት ሰራተኛ ያልሆኑት ሰዎች በመንግስት ንብረት ላይ የእምነት ማጉደል ተግባሩን መፈፀማቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡በወንጀል ሕጉ 675 ንዑስ አንቀጽ 3 ተከሣሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም ባደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሀሳብ እንዳለው የሚቆጠር መሆኑን በግልፅ ደንግጓል፡፡ይህ የህግ ግምት የሚስተባበለው ደግሞ በተከሳሹ ነው፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪን ተጠያቂ ያደረጋቸው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 420(1) ስር ነው፡፡በዚህ ድንጋጌ የወንጀል ተጠያቂነት የሚመጣው ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የሥራ ግዴታ ተግባሩን በአግባቡ ሳይፈጽም በመቅረቱ በመንግስት፣በህብረተሰብ ወይም በግለሰብ ጥቅም ላይ ጉዳት አድርሶ የተገኘ እንደሆነ ነው፡፡የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 420 ድንጋጌ ተፈጻሚነት የሚኖረው የመወሰን ሥልጣን የሌላቸውና የሙያ ግልጋሎት የመስጠት ኃላፊነት ባለባቸው ሰዎች ነው፡፡ስለሆነም በአንቀጽ 420 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ መሰረት አንድን ሰው ተጠያቂ ለማድረግ የሙያ ተግባሩንና ሥራው በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመፈፀሙ ምክንያት በመንግስት ላይ ጉዳት መደረሱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

ወደተያዘው ጉደይ ስንመለስ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተጠሪ አድራጎት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 420(1) ስር የሚሸፈን ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ አድራጎቱን የፈፀሙት ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ለግል ጥቅሙ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም ለማዋል በማሰብ መሆኑን በማስረጃ አልተረጋገጠም በሚል አቢይ ምክንያት ነው፡፡በእርግጥ ተጠሪ የተከሰሱት በከባድ የእምነት ማጉደል ወንጀል መሆኑ ሲታይ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 676(1) የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675 መሰረታዊ የወንጀል ማቋቋሚያ የያዘ በመሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 675(3) በተመለከተው የሕግ ግምት መሰረት ተከሣሹ ሲጠየቅ በእምነት ወይም ባደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም የማዋል ሀሳብ እንዳለው የሚቆጠር መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ተጠሪ የክፍያ ኦፊሰር፣ቼክ አዘጋጅና ፈራሚ መሆናቸው እንጂ በመሰረታዊ የስራ ሂደት መሰረት በጉርዱ ላይ ለመመዝገብ የስራ ሂደቱን አስተባባሪ ትዕዛዝ መጠበቅ የግድ የሚላቸው መሆኑን የክርክሩ ሂደት ማስገንዘቡ ሲታይ ተጠሪ ብቻቸውን የመወሰን ሥልጣን የሌላቸውና የሙያ ግልጋሎት የመስጠት ኃላፊነት ብቻ የነበራቸው ናቸው ለማለት የሚያስችል ሁኖ አግኝተናል፡፡በስራ መደባቸው ተጠሪ ብቻቸውን የመወሰን

ስልጣን ሳይኖራቸው ባልተገባ መንገድ ቼኩን አዘጋጅተውና ፈርመው ለስር 1ኛ ተከሳሽ በመስጠት ከመንግስት የባንክ ሂሳብ ውስጥ ብር 100,000.00 ወጪ ሁኖ ለስር 1ኛ ተከሳሽ የግል ጥቅም እንዲውል ማድረጋቸው በመንግስት ሰራ ተመድበው በመስራት ላይ ባሉበት ሁኔታ በመንግስት ንብረት ላይ የስራ ኃላፊነት ወይም ግዴታቸውን ያለመወጣታቸውን የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 420(1) የተፈፃሚነት አድማሱን ከተጠሪ የስራ ኃላፊነት ዝርዝር ይዘት እና በወቅቱ ከነባራቸው ተሳትፎ ጋር በማዛመድ የተጠሪ አድራጎት የሥራ ኃላፊነትን ባለመወጣት የሚፈፀም ወንጀል ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስላላገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ውሣኔ</u>**

1. በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 00723 ሐምሌ 02 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2)(ለ-2)) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የተጠሪ አድራጎት የሚሸፈነው በወንጀል ሕግ አንቀጽ 420(1) ስር ነው መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ተ**

የሰ/መ/ቁ/89676

ጥር 4 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - ዐቃቤ ሕግ ምርምር ጥጋቡ ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ሣሙኤል ፈቃዱ ኃይሌ-ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረበው ተጠሪው በተከሰሰበት በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል ወንጀል ክስ ባሰማው የመከላከያ ማስረጃ የዐቃቤ ሕግን ክስ እና ማስረጃ ከጥርጣሬ ላይ የጣለ በመሆኑ በወንጀሉ ጥፋተኛ አይደለም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪው ላይ በ04/07/2004 ዓ.ም.አዘጋጅቶ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡-ተከሳሹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 627(1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በ08/06/2004 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት ከ10፡00 እስከ 11፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 03/09 ክልል ልዩ ቦታው ደጃች ውቤ ሰፈር ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ በሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ውስጥ ሣህሊት ብርሃን የተባለችውንየሁለት ዓመት ከስምንት ወር ዕድሜ ያላትን የግል ተበዳይ ሕጻን የለበሰችውን ልብስ ዝቅ በማድረግ እግሩ ላይ አስቀምጦ የግብረ ስጋ ግንኙነት በመፈጸም የክብረ ንጽህናዋ የታችኛው የቀኝ ክፍል እንዲቀደድ ያደረገ በመሆኑ በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል ወንጀል አድርጓል የሚል ሲሆን አመልካች ተጠይቆ መቃወሚያ እንደሌለው ገልጾ ወንጀሉን አላደረግሁም በማለቱ ፍርድ ቤቱ በተጠሪ በኩል የቀረቡ የግል ተበዳይ ሕጻንን ጨምሮ የአራት ምስክሮችን ምስክርነት ከሰማ እና በ09/06/2004 ዓ.ም. ከየካቲት 12 ሆስፒታል የተሰጠ የሕክምና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳበት መሆኑን ገልጾ አመልካች መከላከያውን ማሰማት እንዲጀምር በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚሁ መሰረት አመልካች በ08/06/2004 ዓ.ም. ከቀኑ 7፡00 ሰዓት ላይ ከእናቱ፣ከሕጻን ልጁ እና ከሰራተኞቹ ጋር ከእህቱ ቤት መጥተው ምሳ ከበሉ በኃላ ሰራተኛዋ ቡና አፍልታ እስከ 11፡00 ሰዓት ድረስ መቆየታቸውን፣ተከሳሽ በ11፡00 ሰዓት ወጥቶ ወደ ቤተክርስቲያን የሄደ መሆኑን፣በዚህ መሀል የግል ተበዳይ ሕጻን ወደ ቤቱ አለመምጣቷን፣በአካባቢው ሣሙኤል በሚባል ስም የሚጠራ ሌላ ሰው መኖሩን ያስረዱልኛል በማለት ሶስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የመከላከያ ምስክሮቹም እናውቃለን ስላሏቸው ፍሬ ነገሮች በጭብጡ ከተገለጸው በተጨማሪ በተከሳሽ እና በግል ተበዳይ ቤተሰቦች መካከል የቆየ ቂም በቀል መኖሩን እና የግል ተበዳይ ሰራተኛ አባት የግል ተበዳይ ቤተሰቦችን ልጇን በሀሰት አስመስክራችኃል በማለት ተከሳሽ ከተያዙ በኃላ መጥተው ልጃቸውን የወሰዱ መሆኑን ጭምር እና እነዚህኑ ፍሬ ነገሮች ሊያውቁ ስለቻሉበት ሁኔታ በዝርዝር በመግለጽ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡የግል ተበዳይ በጋንዲ ሆስፒታል በድጋሚ እንድትመረመር ተጠሪው በጠየቀው እና ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረትም ምርመራው ተከናውኖ የሕጻኗ የድንግልና አካል የሆነው ክፍል የተጎዳ እና ጉዳቱም የቆየ መሆኑን የሚገልጽ ከሆስፒታሉ በ11/10/2004 ዓ.ም. የተጻፈ ማስረጃ ቀርቦ ተያይዟል፡፡

ፍርድ ቤቱም በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተጠሪው ባሰማቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰረበትን ፍሬ ነገር ከጥርጣሬ ላይ በሚጥል ሁኔታ አስተባብሏል በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 149(2) ድንጋጌ መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው ይግባኙን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195(1) ድንጋጌ መሰረት ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪው የመድፈር ወንጀል አልፈጸመም ተብሎ በነጻ የመለቀቁን አግባብነት ከወንጀል ሕግ አንቀጽ 23 አንጻር ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች በክሱ መሰረት ያስረዱልኛል በማለት ያሰማቸው አራት ምስክሮች በተሰሙበት በቅደም ተከተል መሰረት የግል ተበዳይዋ ሕጻን፣የሕጻኗ እናት፣የሕጻኗ የእናት ወንድ አክስት እና የሕጻኗ ሞግዚት ሲሆኑ የምስክርነታቸው ይዘት ጠቅለል ተደርጎ ሲታይም የሕጻኗ ቤተሰቦች እና ተከሳሹ ጎረቤታሞች መሆናቸውን፣ሕጻኗ በ08/06/2004 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት ከ10፡00 እስከ 11፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ከተከሳሹ መኖሪያ ቤት ቆይታ ወደ ቤቷ የተመለሰች መሆኑን፣የተመለሰችውም እያለቀሰች መሆኑን፣ምን ሆና እንዳለቀሰች ሞግዚቷ የጠየቀቻት ቢሆንም ሕጻኗ አልናገርም ያለቻት መሆኑን፣በወቅቱ እናቷ ከቤት ያልነበረች መሆኑን፣ማታ ላይ አሞኛል በማለት ወደ ሀኪም ቤት እንድትወስዳት እናቷን የጠየቀቻት መሆኑን፣እናቷም ሕጻኗ እንደዚህ ያለቻት ቀደም ሲል ሀኪም ቤት ትወስዳት ስለነበረ እንደሆነ በመገመት ደህና ነሽ አላመመሽም ተኚ ያለቻት መሆኑን ሰውነቷን እንድትጠርግላት እና ተከሳሹ በጣቱ ወይም በሽንት መሽኛው ከሽንት መሽኛዋ ላይ የወጋት መሆኑን ሕጻኗ በነጋታው የጠየቀቻት እና የነገረቻት መሆኑን፣እናቷ ገልጣ ስትመለከት በሕጻኗ ብልት አካባቢ ቁስል እና የደረቀ የወንድ የዘር ፍሬ ያየችመሆኑን፣ወዲያውኑ ይዛት እህቷ ወደ ሆነችው 3ኛ ምስክር ወስዳ ያሳየቻት እና በመቀጠልም ወደ ሆስፒታል ወስደው ያስመረመሯት እና ውጤቱም መደፈሯን ያረጋገጠ መሆኑን፣ተከሳሹ የስድስት ወር ሕጻን ልጅ ያለው መሆኑን፣የግል ተበዳይ ሕጻን የተከሳሹን ልጅ ለማጫወት ሁሌም ወደተከሳሹ ቤት ትሄድ የነበረ መሆኑን፣ቤታቸው ቅርብ

ለቅርብ በመሆኑ የምትሄደው ብቻዋን መሆኑን፣ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ዕለትም ሕጻኗ የሄደችው በዚሁ ሁኔታ መሆኑን፣ሕጻኗ ወደ ተከሳሹ ቤት ሄዳ እዚያው በነበረችበት ጊዜ ሞግዚቷ የሆነችው 4ኛ ምስክር የሕጻኗን መኖር ለማረጋገጥ ወደ ተከሳሹ ቤት ሄዳ በሩን ስታንኳኳ ተከሳሹ እንደከፈተላት እና የሕጻኗን መኖር ስትጠይቀው መኖሯን የነገራት መሆኑን፣በወቅቱም ከተከሳሹ ቤት ውስጥ ከእርሱ እና ከግል ተበዳይዋ ህጻን በቀር ሌላ ሰው ያልነበረ መሆኑን እና መሰል ፍሬ ነገሮችን የሚገልጽ ነው፡፡ከየካቲት 12 ሆስፒታል በ09/06/2004 ዓ.ም. የተሰጠው የሕክምና ማስረጃም የሕጻኗ ድንግልና የታችኛው የቀኝ ክፍል ትኩስ መቀደድ የታየበት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሕጻኗ ድርጊቱ ተፈጽሞባታል በተባለበት ጊዜ የሁለት ዓመት ከስምንት ወር ዕድሜ የነበራት ሲሆን በፍርድ ቤት ቀርባ ምስክርነቷን የሰጠችውም ድርጊቱ ተፈጸመ ከተባለበት ቀን አንስቶ ሁለት ወር ባልሞላው ጊዜ ውስጥነው፡፡በማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ እርዳታ እና በተመሳሳይ ዕድሜ አካባቢ ለሚገኙ ሕጻናት በሚያመች ሁኔታ በተዘጋጀ የችሎት ፋሲሊቲ በመታገዝ ሕጻኗ የሰጠችው ምስክርነት በተለይ ሲታይ አዋቂ ሰዎች በሚጠቀሙበት ዓይነት አነጋገር እና አገላለጽ የተሰጠ ባይሆንም የተፈጸመባትን ድርጊት ዓይነት፣ድርጊቱን የፈጸመባትን ሰው ማንነት፣ፈጻሚው ድርጊቱን የፈጸመው በየትኛው የአካል ክፍሉ በመጠቀም እና በየትኛው የአካል ክፍሏ ላይ መሆኑን በግልጽ መገንዘብ በሚያስችል ሁኔታ የተሰጠ መሆኑን እና ድርጊቱን ፈጽሞብኛል ያለችውን ሰው ለይታ እንድታሳይ ተጠይቃም ወደ ችሎቱ አዳራሽ በመምጣት የአሁኑን ተጠሪ ለይታ ያሳየች መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት አጠቃላይ ይዘቱ ከላይ የተመለከተውን የግራ ቀኙን ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተጠሪው ባሰማቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰከረበትን ፍሬ ነገር ከጥርጣሬ ላይ በሚጥል ሁኔታ አስተባብሏል በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 149(2) ድንጋጌ መሰረት በነፃ እንዲሰናበት ለሰጠው ውሳኔ በመከላከያ ምስክሮች ከተሰጠው ምስክርነት ውስጥ መሰረታዊ ምክንያቶች አድርጎ የወሰደው፡-

1. የግል ተበዳይዋ ሕፃን ቤተሰቦች እና ተከሳሹ በሚኖሩበት አካባቢ ከተከሳሹ ጋር በተመሳሳይ ስም የሚጠራ በሃያ ዓመት ዕድሜ አካባቢ የሚገኝ ሌላ ሰው አለ መባሉን፣
2. በተከሳሽ ቤተሰቦች እና በግል ተበዳይ የእናት ወገን ቤተሰቦች መካከል የቆየ ቂም በቀል አለ መባሉን እና
3. የግል ተበዳይ ሰራተኛ (የሕጻኗ ሞግዚት) አባት የግል ተበዳይ ቤተሰቦችን ልጄን በሀሰት አስመስክራችኃል በማለት ተከሳሽ ከተያዘ በኃላ መጥተው ልጃቸውን ወስደዋል መባሉን እንደሆነ ከውሳኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡

የግል ተበዳይዋ ሕፃን ቤተሰቦች እና ተከሳሹ በሚኖሩበት አካባቢ ከተከሳሹ ጋር በተመሳሳይ ስም የሚጠራ በሃያ ዓመት ዕድሜ አካባቢ የሚገኝ ሌላ ሰው አለ መባሉን በተመለከተ በመሰረቱ የድርጊቱን ፈጻሚ ማንነት በተመለከተ በአመልካች ምስክሮች የተሰጠው ምስክርነት ድርጊቱን የፈጸመው ሣሙኤል የሚባል በሕጻኗ ቤተሰቦች መኖሪያ አካባቢ የሚኖር ሰው ነው ተብሎ በደፈናው እና የድርጊቱን ፈጻሚ ማንነት ለይቶ ለማረጋገጥ በማያስችል ወይም በሚያጠራጥር ሁኔታ የተሰጠ ሳይሆን ድርጊቱን የፈጸመው የአሁኑ ተጠሪ ስለመሆኑ በስም፣በመኖሪያ ቤቱ ማለትም ድርጊቱ በተፈጸመበት ቤት ልዩ አድራሻ እና በአካላዊ መለያው ጭምር ተለይቶ እና ተረጋግጦ የተሰጠ መሆኑን ይዘቱ ከላይ የሰፈረው የምስክርነቱ ይዘት በግልጽ የሚያመለክት በመሆኑ በአካባቢው ከተከሳሹ ጋር በተመሳሳይ ስም የሚጠራ ሌላ ሰው የመኖሩ ወይም ያለመኖሩ ጉዳይ ለክርክሩ አግባብነት ያለው የመከላከያ ፍሬ ነገር ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ

አግባብ የለም፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ለዚህ ዓይነቱ ለክርክሩ አግባብነት ለሌለው የመከላከያ ፍሬ ነገር ዋጋ ሰጥቶ ተጠሪው ባሰማው መካለከያ ማስረጃ በአመልካች ማስረጃ የተመሰከረበትን ፍሬ ነገር ከጥርጣሬ ላይ በሚጥል ሁኔታ አስተባብሏል ከሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱም ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡

በተከሳሽ ቤተሰቦች እና በግል ተበዳይ የእናት ወገን ቤተሰቦች መካከል የቆየ ቂም በቀል አለ መባሉን በተመለከተ የግል ተበዳይ እናት የሆኑት 2ኛ ምስክር ተጠይቀው በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል የቆየ ጥል ነበረ መባሉን እህታቸው ከሆኑት 3ኛ ምስክር የሰሙት ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ እንደሆነ፣ሌሎች የምስክሯ ቤተሰቦች በተለያየ ምክንያት አካባቢውን የለቀቁ መሆኑን እና አሁን በአካባቢው የቀሩት ምስክሯ ብቻ መሆናቸውን እና ድርጊቱ ከመፈጸሙ በፊት ነበረ ስለተባለው ጠብ የሚያውቁት ነገር ስላልነበረ ከከሳሹ ጋር በክፉ እና በደስታ ቀን ይደራረሱ እንደነበረ በመግለጽ የመሰከሩ ሲሆን 3ኛ ምስክር በበኩላቸው ጠቡ ተከስቶ የነበረው ከ35 ዓመታት በፊት መሆኑን እና የጠቡን መንስኤ ጭምር በመግለጽ መስክረዋል፡፡ተጠሪው እና የግል ተበዳይ ቤተሰቦች ጨርሰው የማይነጋገሩ እና 3ኛ ምስክር በገለጹት መሰረት በክፉ እና በደስታ ቀን የማይደራረሱ ስለመሆኑ በተጠሪው ምስክሮች የተነገረ ነገር የለም፡፡ምስክርነት በሰጡበት ጊዜ የ2ኛ እና የ3ኛ ምስክሮች ዕድሜ እንደቅደም ተከተሉ 30 እና 44 ዓመት መሆኑንም የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ተጠሪው በሁለቱ ቤተሰቦች መካከል የቆየ ቂም በቀል አለ በሚል ጭብጥ ዙሪያ መከላከያ ምስክሮችን ያሰማው የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የቆየውን ቂም በቀል መሰረት በማድረግ በሀሰት የመሰከሩበት መሆኑን ግምት ለማስወሰድ እንደሆነ የሚታመን ነው፡፡ይሁን እንጂ በተጠሪው ላይ ዋነኛ እና የዓይን ምስክር ሆና የቀረበችው የግል ተበዳይ ስለቂም በቀል ልታውቅ የማትችል የ2 ዓመት ከ8 ወር ሕጻን በመሆኗ እና  የአካባቢ ማስረጃ የሆነችው የሕጻኗ ሞግዚት 4ኛ ምስክርም የ14 ዓመት ዕድሜ ያላት እና በግል ተበዳይ እናት ቤት የቆየችው ለጥቂት ዓመታት ብቻ እንደሆነ መዝገቡ የሚያመለክት በመሆኑ እነዚህ ሁለቱ ምስክሮች ምስክርነት የሰጡት በቂም በቀል ሊሆን የሚችልበት ዕድል ፈጽሞ አለመኖሩን ከምስክርነታቸው አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ የሚያዳግት አይደለም፡፡ ምስክርነታቸውም በተጨባጭ የሀኪም ማስረጃ የተደገፈ ጭምር ነው፡፡በመሆኑም የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች የሰጡት ምስክርነት የተሰጠው በቂም በቀል ስለመሆኑ ምንም ዓይነት አመላካች ፍንጭ በሌለበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤቶች ለደረሱበት ድምዳሜ ይህንን ያልተረጋገጠ ፍሬ ነገር መሰረት ማድረጋቸው አጠቃላይ የማስረጃ ምዘና መርህን መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

የግል ተበዳይ ሰራተኛ አባት የግል ተበዳይ ቤተሰቦችን ልጄን በሀሰት አስመስክራችኃል በማለት ተከሳሽ ከተያዙ በኃላ መጥተው ልጃቸውን ወስደዋል መባሉን በተመለከተ በዚህ ረገድ ምስክርነት የሰጠችው 3ኛ የመከላከያ ምስክር ስትሆን የምስክርነቷ ይዘትም የሠራተኛዋ አባት ወደግል ተበዳይ እናት ስልክ ደውለው ልጃቸውን በሀሰት እንደዳስመሰከሯት ልጃቸው የነገረቻቸው መሆኑን እና የግል ተበዳይ እናትም የምትመሰክረው ነገር ስላለ መስክራ ትመጣልሃለች ብለው መመለሳቸውን የሚገልጽ ነው፡፡በመሰረቱ የመከላከያ ምስክሯ የመሰከረችው የስልክ ንግግሩን በቀጥታ ሰምቻለሁ በማለት ሳይሆን የስልክ ንግግሩን ከሰሙት የግል ተበዳይ ጎረቤቶች ሰማሁ በማለት ነው፡፡ተጠሪው ይህንን የስልክ ንግግር በቀጥታ ሰምተናል ያሉትን ጎረቤቶች አቅርቦ ማሰማት ያልቻለበት ምክንያትም ሆነ የጎረቤቶቹ ማንነት አልተገለጸም፡፡በሌላ በኩል ሠራተኛዋ በፍርድ ቤት ቀርባ ምስክርነቷን የሰጠችው የስልክ ንግግሩ ተደረገ ከተባለበት ጊዜ በኃላ ሲሆን በተጠሪው ጠበቃ ለቀረበላት መስቀልኛ ጥያቄ ምስክርነቷን እንድትሰጥ በግል ተበዳይ ቤተሰቦች በኩል የደረሰባት ምንም ዓይነት ተጽዕኖ አለመኖሩን በማረጋገጥ መመስከሯን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

ሲጠቃለል ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ከላይ በዝርዝር በተመለከተው አግባብ በከሳሽ የሰው እና የሰነድ ማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር ወደጎን ትቶ በመከላከያ ምስክሮች የተነገሩ ነገር ግን ለክርክሩ አግባብነት የሌላቸውን እና ያልተረጋገጡትን ፍሬ ነገሮች በዐቃቤ ሕግ የዓይን፣የአካባቢ እና የሀኪም ማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ጋር በመመዘን ተጠሪው ባሰማቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰከረበትን ፍሬ ነገር ከጥርጣሬ ላይ በሚጥል ሁኔታ አስተባብሏል በማለት የደረሰበት ድምዳሜም ሆነ ይህንን ድምዳሜ መሰረት አድርጎ ተጠሪን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 149(2) ድንጋጌ መሰረት በነፃ በማሰናበት የሰጠው እና በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ የማስረጃ ምዘና መሰረታዊ መርሆዎችን መሰረት ያላደረገ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 192326 በ30/11/2004 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 129168 በ28/05/2005 ዓ.ም. የጸናውን ውሳኔ በመሻር ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት በዓይን፣በአካባቢ እና በሀኪም ማስረጃ ያስረዳበትን የወንጀል ፍሬ ነገር በመካለከያው ያላስተባበለ በመሆኑ ተጠሪው በተከሰሰበት በሕጻናት ልጆች ላይ የሚፈጸም የግብረ ስጋ ድፍረት በደል ወንጀል ጥፋተኛ ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)(ሀ) መሰረት ወስነናል፡፡
2. ተጠሪው ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ በቁጥጥር ስር አቆይቶ እንዲያቀርበው ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ይጻፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየታቸውን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በቀጣይ ቀጠሮ በጽሁፍ ያቅርቡ፡፡
4. ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን የቅጣት አስተያየት ለመቀበል 20/05/07 ዓ.ም ተቀጠረ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ. 89676

ጥር 22 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ - ዐ/ሕግ ምርምር ጥጋቡ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ሳሙኤል ፍቃዱ ኃይሌ - ቀረቡ

መዝገቡን የተቀጠረው የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ነው፡፡ በዚህም መሰረት መዝገቡን መርምረን ተከታዩን የቅጣት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ቅ ጣ ት

1. አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሁኖ ከተገኘ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት ያለበት ሲሆን ቅጣቱ የሚወሰነው ደግሞ ስራ ላይ በዋለው በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ታይቶ ነው፡፡ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 627/1/ ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከአስራ አምስት አመት እስከ ሃያ አምስት ለሚደርስ በሚችል ጽኑ እስራት ነው፡፡
2. በመሰረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀፅ 1 ስር ሲደነግግ "የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው በማድረግ ነው" በማለት ያስቀምጣል ህጉ በአንቀፅ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሰረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ይኸው አንቀፅ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሰብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃወች አወሳሰን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀፅ ስር ያሉ ንዑስ አንቀፆች የሚያሳዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን

ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድጋጌዎች መሰረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ የነሳሱትን ምክንያቶችና የአሳቡን አላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነ ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን የቅጣት አወሳሰን ደንቡ በግልፅ ያሳያል፡፡ ከላይ እንደተገለፀዉ የወንጀል ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 88/2/ ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ይህ ችሎትም እነዚህ ሁኔታዎችን ሁሉ ተመልክቷል፤ አመዛዝኗልም፡፡

3. እንደ ቅጣት መመሪያው መወሰን እንዲቻል ደግሞ በተጠሪ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ከግራ ቀኙ ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ በዚህ አግባብ ቅጣቱ ከመሰላቱ በፊት ግን ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ክሱ ሲመረትም ሆነ በበታች ፍርድ ቤቶች ክርክር ሲካሄድ ደረጃ ያልወጣለት ቢሆንም በዚህ ችሎት ጉዳዩ በመታየት ላይ እያለና የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 በመሆኑ በዚሁ መመሪያ መሰረት የወንጀል ህጉ አንቀፅ 627 ደረጃ የወጣለት ድንጋጌ ነው፡፡ ተጠሪ ድርጊቱን የፈፀሙት እድሜዋ ዘጠኝ አመት ካልሞላት ሴት ህፃን ላይ በመሆኑ የወንጀሉ ደረጃ 2 ሁኖ የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን 35 ነው፡፡ በዚህ እርከን ለፍርድ ቤቱ የተተወው ፍቃደ ስልጣን ከአስራ ስድስት አመት ከስድስት ወር እስከ አስራ ዘጠኝ አመት ከስድስት ወር ነው፡፡ መነሻ ቅጣቱም በዚሁ ሬንጅ ውስጥ የሚያዝ ሲሆን በተጠሪ ላይ መጨረሻ ላይ የሚጣለው የቅጣት መጠን የሚታወቀው ግን የማክበጃ እና የማቅለያ ምክንያቶች ታይተው ስሌቱ ከተሰራ በኋላ ነው፡፡ በዚህም አግባብ የቅጣት መጠኑን ማስላት የግድ ሲሆን በተጠሪ ላይ በዓቃቤ ሕግ በኩል ቅጣቱን ሊያከብዱ ይገባል ተብለው የተጠቀሱት ምክንያቶች የድርጊቱ አፈፃፀም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84/1/ሀ/ የተጠቀሰው መጥፎ አመልንና ወራዳነትን ያሳያል እንዲሁም በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84/1/ሠ// መሰረት ድርጊቱ የተፈፀመው የተለዩ እንክብካቤ በሚያስፈልጋት ህፃን ልጅ ላይ ነው የሚሉት ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ ምክንያቶች ከወንጀል ሕጉ አንቀፅ 627 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ እንዲሁም የቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጀውን ሲያወጣ እድሜን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ከመሆኑ አንፃር የወንጀሉ ድርጊት ማቋቋሚያ ነጥቦች ሊባሉ የሚችሉ በመሆኑና በወንጀል ህጉ አንቀፅ 82/2/ ድንጋጌ አንፃር በቅጣት ማክበጃ ምክንያትነት መያዙ ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም አቃቤ ሕግ በቂ ጊዜ ተሰጥቶት ባቀረበው የቅጣት አስተያየት ተጠሪ የወንጀል ሪኮርድ አለባቸው የሚል ግልፅ አስተያየት አላቀረበም፡፡ ይህም ተጠሪ ሪኮርድ ያልቀረበባቸው መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ በመሆኑ ይኼው ምክንያት በማቅለያነት እንዲያዝላቸው የሚያደርግ ነው፡፡ ሌላም ተጠሪ ያቀረቡት የቅጣት ማቀለያ የቤተሰብ አስተዳዳሪነት ሲሆን ከራሳቸው ልጆች በተጨማሪ የዘመድ ልጅ የሆኑትን ሁለት ህፃናትን የሚያስተዳድሩ መሆናቸውን ገልፀው በቅጣት ማቅለያነት እንዲያዝላቸው የጠየቁ ሲሆን አቃቤ ሕግ በዚህ በኩል ክርክር ካለማቅረቡም በላይ ችሎቱም እነዚህ ምክንያቶች የቤተሰብ አስተዳዳሪነት በጠቅላላ ቅጣት ማቅለያነት፣ የዘመድ ልጆችን በመንከባከብ የማስተማር ሰብዓዊነት ተግባር መፈፀማቸው ደግሞ በልዩ

ቅጣት ማቅለያነት ሊያዝ የሚገባ ሁኖ አግኝቷል፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ተጠሪ ሶስት ህጋዊ የሆኑ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያሏቸው ሁኖ አግኝተናል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ድርጊቱን በተፈፀመበት የካቲት 08 ቀን 2004 እና ክሱ የካቲት 19 ቀን 2004 ዓ.ም ተመስርቶ ክርክሩ በስር ፍርድ ቤት ታይቶ ዳኝነት በተሰጠበት ጊዜ በነበረበት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ደረጃ ያልወጣለት የነበረ ሲሆን በተሻሻለውየቅጣት አወሳሳን መመሪያ ደግሞ ደረጃ የወጣለት ነው፡፡ እኛም የቅጣት ማቅለያ ዋጋ አያያዝን ከወንጀል ሕጉ አንቀን 6 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንፃር ለተጠሪ የተሻለ ሁኖ ያገኘነው ነባሩ የቅጣት አወሳሳን መመሪያ በመሆኑ የቅጣቱን መጠን ከዚህ አንፃር ተመልክተናል፡፡

ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ እንዲቀጡ በመነሻነት የሚያዘው እርከን 35 በመሆኑ በዚህ እርከን መነሻ ሲያዝ የቅጣት መጠኑ ከሰባት አመት በላይ በመሆኑ ተጠሪ ያላቸው ሶስት የቅጣት ማቅለያዎች በመመሪያው ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 13/8/ ድንጋጌ መሰረት እያንዳንዳቸው ሶስት እርከን የሚያስቀንሱ በመሆኑ ከእርከን 35 ወደ እርከን 26 መውረድን፣ በዚህ እርከን ውስጥ ተገቢውን ቅጣት መወሰን የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ቅጣቱን ስናሰላው ተጠሪ ሊቀጡ የሚገባው በእርከን 26 ስር ለፍርድ ቤቱ በተተወው የፍቅድ ስልጣን ማለትም ከሰባት አመት ከስምንት ወር እስከ ዘጠኝ አመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራት ውስጥ ነው፡፡ ከእነዚህ የእስራት ጊዜያት ተጠሪን ያርማል፣ ሌሎች መሰል አጥፊዎችን ከወዲሁ ያስጠነቅቃል ብለን ያመነው ሰባት አመት ከስምንት ወር ፅኑ እስራት ሁኖ አግኝተናል፡፡ ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች ተጠሪ በጉዳዩ ላይ የታሰሩት <u>**ማናቸውም ጊዜ ካለ**</u> የሚታሰብላቸው ሁኖ ተጠሪ <u>**በሰባት አመት ከስምንት ወር ጽኑ እስራት**</u> ሊቀጡ ይገባል በማለት በድምፅ ብልጫ ወስነናል፡፡

የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤትም በተጠሪ ላይ በዚህ ችሎት የተሰጠውን የቅጣት ውሳኔ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

<u>**የ ሃ ሳ ብ ል ዩ ነ ት**</u>

በአብላጫ ድምፅ በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ላይ የተጠሪው የዘወትር ፀባይ መልካምነት በማቅለያ ምክንያትነት ሊያዝ ይገባል የተባለው ዐ/ሕግ በቂ ጊዜ ተሰጥቶት እያለ ተጠሪ የወንጀል ሪኮርድ ያለባቸው ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር የለም በማለት ነው፡፡ በርግጥ አመልካች ባቀረበው የቅጣት አስተያየት ላይ ተጠሪ የወንጀል ሪኮርድ ያለባቸው ስለመሆኑ የቀረበው ክርክር የለም፡፡ ይሁን እንጅ ተጠሪው ከሌሉ ውጤቱ የታወቀ /የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠበት/፣ ከፊሉ ደግሞ የመጨረሻ ውጤቱ ያልታወቀ የኋላ የወንጀል ታሪክ የነበራቸው ስለመሆኑ የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት መዝገብ በግልፅ ያመላክታል፡፡ ተጠሪው በኋላ የወንጀል ታሪክ የነበራቸው ሲሆን ደግሞ ይህ የኋላ የወንጀል ታሪክ ሕጋዊውን ስርዓት ተከትሎ የተሰረዘ መሆኑ ሳይረጋገጥ የተጠሪው የዘወትር ፀባይ መልካም ነበር የሚል ግምት መያዙ ተገቢነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የተጠሪው የዘወትር ፀባይ መልካምነት በቅጣት ማቅለያነት እንዲያጣ ከመደረጉ በፊት የፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት መዝገብ የሚያረጋግጠው የተጠሪው የኋላ የወንጀል ታሪክ ሕጋዊውን ስርዓት ተከትሎ የተሰረዘ መሆን አለመሆኑ አስቀድሞ ሊጣራ ይገባው ነበር በማለት ስማችን በአራተኛ እና በአምስተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኞች ይህንን የልዩነት ሀሳብ አስፍረናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ 103452

ቀን ጥር 19/2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ጥዑም ተኬ ገብራይ ጠበቃ ሀብታሙ ንጉሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የዐቃቤ ሕግ የድሬደዋ ምድብ ዋልተንጉስ ፍቅሬ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድሬደዋ ምድብ ችሎት ነው ፡፡ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ያቀረበው ክስ የኢፌድሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 408(2) የተመለከተውን በመተላለፍ ከግል ተበዳይ አቶ ንጉሴ ለማ ብር ሁለት ሺህ (2,000.00) ጉቦ ሲቀበል እጅ ከፍንጅ ተይዟል የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

አመልካች በአሁኑ ተጠሪ የተመሰረተበት የወንጀል ክስ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ የተከራከረ ሲሆን ተጠሪም የበኩሉን መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሠረታዊ ይዘት በጉቦ መልክ ተቀብለው የተባለው የገንዘብ መጠን ትንሽ መሆኑ፤የሥልጣን ደረጃውም በአዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀፅ 2(5) እንደማይካተት በመግለፅ ክሱ በወ/ሕ/ቁ 408(1) ሥር እንዲቀርብ ዐቃቤ ሕግ ክሱን እንዲያሻሽል እንዲታዘዝለት አመልክቷል ፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ አመልካች ስራ አስኪያጅ መሆኑን ፤በአዋጅ ቁጥር 668/2002 መሠረት የመንግስት የልማት ድርጅት ስራ አስኪያጆች የመንግስት ባለ ስልጣን በሚል ሥር ያካተታቸው በመሆኑ መቃወሚያው ውድቅ እንዲሆን ጠይቋል፡፡

የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራቀኙ ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካች ከፍተኛ ባለ ስልጣን ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 433/97 አልተካተተም ፡፡ የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 2/2006 ለወንጀል ሕግ አንቀጽ 407(2) የወንጀል ደረጃ እና የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን ሲያወጣ ከፍተኛ ሥልጣን ማለት በተሻሻለው የፌዴራል ስነ ምግባር እና ፀረሙስና ኮሚሽን አዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2(5) ውስጥ የተካተቱ ባለሥልጣኖች ያላቸው ስልጣን ማለት እንደሆነ ተመልክቷል ፡፡ በወ/ህ/አ. 407(2) እና 408(2) ላይ የተቀመጡ ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች

ተመሳሳይ በመሆናቸው ለቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 408(2)መወሰዱ ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ ተከሳሽ የመንግስት የልማት ድርጅት ስራ አስኪያጅ መሆናቸው የስልጣን ደረጃቸው ከፍተኛ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል አይደለም፡፡ በጉቦ መልክ ተቀብለው የተባለው ገንዘብ ሁለት ሺህ ብር መሆኑ ሲታይ የተገኘው ጥቅም ዝቅተኛ ነው፡፡ ኃላፊነት ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ የከባድ የሙስና ወንጀል መለኪያ መስፈርቶችን የሚያሟላ ሆኖም አልተገኘም ፡፡ በመሆኑም ዓቃቤ ሕግ በወንጀል መቀጫ ሥነ ሥርዓት አንቀጽ 112 በሚያዘው መሠረት አሻሽሎ እንዲያቀርብ ብይን ሠጥቷል፡፡

ተጠሪ በሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይን ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታው ወደ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የግራቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ የዓቃቤ ሕግ ክስ ስለ ወንጀሉ የሚዘረዝረው ዝርዝር መግለጫ ከህጉ ጋር በእጅጉ የተራራቀ እስካልሆነ ድረስ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ስም ገና ከጅምሩ አንቀጽ ቀይሩ እያለ መዝገብ የሚዘጋ ከሆነ ገና ክሱ ሳይጀምር ወደ ማያባራ ውዝግብ እና ይግባኝ የሚደረግ ነው፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ከሰማ በኃላ ተጠሪ ተከላከል የሚል ከሆነ ሊከላከል የሚገባውም ከተከሰሰበት የህግ አንቀጽ ያነሰ የሚያስቀጣ ነው ብሎ ካመነ በዛን ግዜ አንቀጽን መቀየር የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ዓቃቤ ሕግ በከሰሰበት የወ/ህ/አንቀጽ 408(2) ክሱ ሊቀጥል እና ማስረጃ ሊሰማ ይገባል በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በሥር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተፈጽሟል ያሉትን የህግ አተረጓጐም ስህተት በዝርዝር ያቀረቡ ሲሆን ዋና ፍሬ ነገሩ ፈጸሙት የተባለው ድርጊት በተከሰሱበት የሕግ አንቀጽ ሥር የተቀመጡትን ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች የማያሟላ በመሆኑ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዓቃቤ ሕግ ክሱን እንዲያሻሽል የተሰጠ ትዕዛዝ ተገቢ ሆኖ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሻር የሚጠይቅ ነው ፡፡ ተጠሪ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና አመልክቷል ፡፡የአመልካች የመልስ መልስም የሰበር ቅሬታቸውን የሚያጠናክር ነው፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥ በሰበር ግራ ቀኙ በፅሑፍ ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የተነሱትን ክርክሮች ከተያዘው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የሥር ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይን በመሻር ዓቃቤ ሕግ በከሰሰበት የወ/ሕ/ቁ.408(2) ክሱ ሊቀጥል እና ማስረጃ ሊሰማ ይገባል በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ለተያዘው ጉዳይ ዕልባት መስጠት ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

በዚሁ መሰረት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቆ የሚከራከረው የተመደበበት የኃላፊነት ደረጃ ይሁን በወንጀል ድርጊቱ ተገኘ የተባለው ጥቅም አነስተኛ በመሆኑ ዓቃቤ ሕግ ክስ ማቅረብ የነበረበት በወ/ሕ/ቁ. 408 (1) ሥር መሆን ነበረበት በሚል ነው ፡፡ተጠሪ በበኩሉ የአመልካች ሥራ አስኪያጅ በመሆናቸው በከፍተኛ ሥልጣን ደረጃ የሚመደብ በመሆኑ የተገኘው ጥቅም አነስተኛ መሆን የተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ለመቀየር የሚያስችል አይደለም በማለት ተከራክረዋል ፡፡

የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ዓቃቤ ሕግ የሚያቀርበው ክስ ማሟላት ያለበት መሰረታዊ ነጥቦች ምን እንደሆኑ ደንግጓል። ተከሳሹ የቀረበበት ክስና ማስረጃ ዝርዝር አውቆና ለይቶ እንዲከላከል በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 111፣112 የተዘረዘሩት መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች በዓቃቤ ሕግ ክስ መገለጽ አለባቸው። ዓቃቤ ሕግ የሚያቀርበው ክስ የወንጀል ድርጊት መሆኑ ብቻ ሳይሆን የወንጀል ድርጊት መሆኑ የሚደነግጉ ፍሬ ነገሮች ተከሳሹ ፈጸመው ከተባለው ድርጊት የሚዛመድ መሆኑ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል ። በእንግሊዘኛው ("such description shall follow as closely as may be the words of the law creating the offence`) በማለት ተገልጿል ። በአግባቡ የቀረበ ክስ ደግሞ ተከሳሹ የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ዝርዝር ጉዳይ አውቆ የመከላከያ ማስረጃው እንዲያዘጋጅ ፍርድ ቤትም የጠራ ግንዛቤ በመያዝ ክርክሩን በሕጉ መሰረት ለመምራት የሚያስችለው እንደሆነ ከወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ111፣112 እና ከአጠቃላይ የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረታዊ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው።

አመልካች የኢትዮ ጅቡቲ ምድር ባቡር ዋና ሥራ አስኪያጅ ስለመሆናቸው በሙስና የተጠረጠሩትም ሁለት ሺህ ብር ጉቦ ሲቀበሉ እጅከፍንጅ የተያዙ እንደሆኑ መሰረት በማድረግ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 408(2) የተጠቀሰባቸው ስለመሆኑ ከሥር ፍርድ ቤት የክርክር ሂደት መገንዘብ ይቻላል ። የአመልካች የኃላፊነት ደረጃ በአዋጅ ቁጥር 433/97 አንቀጽ 2(5) ሥር በግልጽ የተጠቀሰ ባይሆንም በተመሳሳይ ደረጃ የሚታዩ ኃላፊዎች በዚህ ትርጓሜ ውስጥ ሊካተቱ እንደሚችሉ በአዋጅ የተጠቀሰ በመሆኑ ከወዲሁ የኃላፊነት ደረጃቸው ከፍተኛ ነው ወይስ ዝቅተኛ ? የሚለው በግልፅ የተወሰነ አይደለም ። የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጠሪ ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ምን እንደሚወሰን ስለማይታወቅ ከወዲሁ የአመልካች የኃላፊነት ደረጃ ወስኖ ወደ ክርክር መግባት ሥነሥርዓታዊ ነው ለማለት የሚቻል አይሆንም።በሌላ በኩል በወ/ሕ/ቁ/408(2) የተዘረዘሩት የማቋቋሚያ ነጥቦች ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ ፤የተገኘው ጥቅም ከፍተኛነት የኃላፊነት ወይም የስልጣን ደረጃ ወይም በግለሰብ ፣በህዝብ ወይም በመንግስት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ከፍተኛነት ናቸው ። ከላይ እንደተመለከተው ዋና ሥራ አስኪያጅ ከፍተኛ ኃላፊ ነው ወይስ አይደለም የሚለው በአዋጅ በግልጽ ባልተሸፈነበት ፍርድ ቤቱ ክርክሩ ሲመረምር ግለሰቡ ከተሰጣቸው ኃላፊነት አንፃር እንደየአግባብነቱ የሚወሰን እንጂ ከወዲሁ የሰበር ሰሚ ችሎቱ አቋም የሚወሰድበት አይሆንም ። ሌሎች የማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮችም መኖር አለመኖራቸው በክርክር ሂደት ነጥረው የሚወጡ እንጂ ከወዲሁ ድርጊቱ የተፈፀመው ለዚህ ዓላማ ነበር ተብሎ ድምዳሜ የሚያዝበት ሆኖ አልተገኘም።

ኃላፊነቱ ወይም ግዴታው እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ ምንድነው? የሚለው ምናልባት ለወደፊት ዓቃቤ ሕግ እንደክሱ የሚያስረዳ ከሆነ በሥር ፍርድ ቤት የሚታይ እንጂ ክርክሩ አሁን ባለበት ደረጃ ድምዳሜ ላይ መድረስ አይቻልም ።በተያያዘው ጉዳይ ተፈፀመ በተባለው ድርጊት በግለሰብ ወይም በህዝብ ወይም በመንግስት ጥቅም ላይ የደረሰው ጉዳት ምንድን ነው ? የሚለውም ዓቃቤ ሕግ እንደክሱ አቀራረብ የሚያስረዳ ከሆነ የሥር ፍርድ ቤት ከክርክር በኃላ የሚወሰነው እንጂ ከወዲሁ አቋም የሚያዝበት አይደለም ። እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ደምረን ስንመለከታቸው አቃቤ ሕግ ተፈፀመ ያለው የወንጀል ድርጊት በወ/ሕ/ቁ. 408(2) ሥር የሚወድቅ ነው ብሎ ካመነ እና ለዚሁም መነሻ የሆኑ ነጥቦች በክሱ መግለጹ ከተረጋገጠ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ከማስተናገድ ውጭ ክርክሩ አሁን ባለበት ደረጃ የወ.ሕ..ቁ 408(2) ማቋቋሚያ ፍሬነገሮች አያሟላም ብሎ ክሱን ውድቅ የሚያደርግበት ሥርዓታዊ ሂደት አይኖርም። በሌላ በኩል የሥር ፍርድ ቤት የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ በሚመረምርበት ወይም ዓቃቤ ሕግ እንደ ክሱ አስረድቷል

የሚል ድምዳሜ ላይ ከደረሰም የመከላከያ ማስረጃ በሚመረምረበት ጊዜ ሁሉ በአመልካች ላይ የተጠቀሰው የህግ አንቀጽ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ከመመርመር የሚገደበው ሥርዓት አይኖርም ። ይህ ከሆነ ደግሞ ክርክሩ አሁን ባለበት ደረጃ ዓቃቤ ሕግ በአመልካች ላይ ያቀረበው የወንጀል ክስ በወ/ህ/ቁ.408(1) የተዘረዘሩት የማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮችን አያሟሉም ተብሎ ወደ ወ/ህ/ቁ.408(1) እንዲቀየር የሚያስችል የህግ መሰረት የለውም ። በመሆኑም የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክሩ ዓቃቤ ሕግ ባቀረበው ክስ መሰረት እንዲቀጥል መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል።

ሲጠቃለል አመልካች የተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት በወ/ሕ/ቁ.408(2) እንዲቀጥል በፌዴራል የጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል ። የአመልካች የኃላፊነት ደረጃ ኃላፊነቱ እንዲጣስ የተፈለገበት ዓላማ ፤በግለሰብ በህዝብ ወይም በመንግስት የደረሰው ጉዳት ምንድነው የሚለው ዓቃቤ ሕግ በሚያቀርበው ማስረጃ ይዘት የሚመዘን ምናልባት የሥር ፍርድ ቤት ድርጊቱ የተፈጸመበት ሁኔታ ከለየ በኋላ ተጠያቂ የሚያደርጋቸው ከሆነ የሚያቀርቡት የመከላከያ ማስረጃ ተመዝኖ የሚወሰን እንጂ ክርክሩ አሁን ባለበት ደረጃ አቋም የሚወሰድበት ባለመሆኑ የአመልካች ክስ ይሻሻልኝ ጥያቄ አልተቀበልነውም ። በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.101820 ሐምሌ 10 ቀን 2006ዓ.ም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ብይን በመሻር የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል።

2. ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረበው የወ/ሕ/ቁ.408(2)ሥር ክርክሩ እንዲቀጥል መታዘዙ በአግባቡ ነው ብለናል ።

3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ የጸና ስለመሆኑ ለሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና አመልካች በሚገኝበት አድራሻ የፍ/ቤት ውሳኔ ግልባጭ ይድረሳቸው ። ይፃፍ፡፡መዝገቡ ተዘጋ፤ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

የሰ/መ/ቁ/103448

የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች:-**አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** አቶ አገኘሁ አስፋው የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** የፌዴራል አቃቤ ሕግ - ወይን ገ/እግኢአብሄር ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በሰው ሕይወትና አካል ላይ በቸልለተኝት ጉዳት ማድረስን የሚመለከት የወንጀል ክርክር ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ አመልካች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ የመሰረተው በአምስት ምድብ የተከፈለ ክስ ነው፡፡

1ኛክስ፡-በ1996 ዓ.ም የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(3) እና የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀጽ 13(ሀ) የተመለከተዉን በመተላለፍ አመልካቹ አሽከርካሪ በመሆኑ የሌላን ሰዉ የሕይወት ደህንነት የመጠበቅ የሙያ ግዴታ እያለባቸው በ03/06/2005 ዓ.ም ከቀኑ በግምት 9፡40 ሲሆን በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከ/ወረዳ 01 ልዩ ቦታዉ ቻይና ካምፕ መታጠፊያ አካባቢ የሠሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-15006 አ/ሮ የሆነ ተሽከርካሪ ይዞ ከአየር ጤና ወደ ሳሪስ አቦ አቅጣጫ እያሽከረከረ ሲንዝ ከተሽከርካሪ መንገድ ዉጭ በመዉጣት በእግረኛ መንገድ ላይ ስትንዝ የነበረችዉን ህጻን ሕይወት ዳዲ የተባለችዉን በሚያሽከረክረዉ መኪና የፊት አካል ገጭቶ በመግደሉ በቸልተኝነት ሰዉ መግደል ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነዉ፡፡

2ኛ፣ 3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ክሶች በተመሳሳይ የወ/ሕ/ አንቀጽ 559(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ በተጠቀሰዉ ጊዜ፣ ቦታና እንዲሁም በቸልተኝነት የድርጊት አፈፃጸም በ2ኛ ክስ የግል ተበዳይ በነበረችው ህጻን ብሩክታዊት ተስፋዬ የጆሮ ታምቡር መቀደድ ጉዳት አድርሷል፣በ3ኛ ክስ ተበዳይ በነበረችዉ ህጻን ሳምራዊት በቀለ ላይ የለስላሳ ጡንቻ ጉዳት አድርሷል፤ በ4ኛ ክስ ተበዳይ በነበረችዉ ህጻን ቅድስት አስማማዉ ላይ የለስላሳ ጡንቻ ጉዳት አድርሷል፤ እንዲሁም በ5ኛ ክስ ተበዳይ በነበረችዉ ህጻን ዋጋዬ ወቼሬ ላይ የለስላሳ ጡንቻ ጉዳት አድርሷ የሚል ነው፡፡

አመልካች የቀረበባቸዉ ክስ ደርሷቸዉ በግልጽ ችሎት ተነቦላቸው እንዲረዱት ከተደረገ በኃላ በሥር ፍርድ ቤት የእምነት ክህደት ቃል እንዲሰጡ ሲጠየቁ ጥፋተኛ አይደለሁም ሲሉ ክደው የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪም አሉኝ ያላቸውን የሠውና የሠነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል፡፡ ከዚህም በኃላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አቃቤ ሕግ እንደክሱ ማስረዳቱን በመገንዘብ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያስሙ መብታቸውን የጠበቀላቸው ሲሆን አመልካችም አሉኝ ያሏቸውን ማስረጃዎች አቅርበው አሰምተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም የዐቃቤ ሕግንና የአመልካችን የሰዉና የሰነድ ማስረጃዎች ሰምቶና መርምሮ አመልካችን የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን በመከላከያ ማስረጃዎቹ ያለማስተባበላቸውን ጠቅሶ የመከላከያ ማስረጃዎቹን ክብደት ሳይሰጥ ያለፈ ሲሆን አመልካችን በዐቃቤ ሕግ ተጠቅሶ በቀረበባቸው ክሶች በመሉ ጥፋተኛ አድርጎ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከተቀበለና ከወንጀል ሕጉ እንዲሁም ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር አገንዝቦ መመልከቱን ከጠቀሰ በኃላ አመልካችን በ6 ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 5,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ ከዚህም በኂላ አመልካች የይግባኝ አቤቱታቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ ችሎቱም ጉዳዩን መርምሮ 1ኛ ክስን በተመለከተ አመልካች ጥፋተኛ ሊባሉ የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(3) ድንጋጌ ሳይሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) መሆኑን፣በ3ኛ እና 5ኛ ክሶችም በአቃቤ ሕግ ክሱ የተነሳ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ጥፋተኛ ሊባሉ እንደማይችሉ፣በ2ኛ እና በ4ኛ ክሶች ጥፋተኛ የተባሉት ግን ተገቢ መሆኑን ገልፆ የጥፋተኝነት ውሳኔ በዚህ አግባብ ከአሻሻለ በኃላ ቅጣቱን በተመለከተም አመልካች የወንጀል ሪከርድ ያልቀረበባቸው መሆኑና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸው እንዲሁም ከግል ተበዳይ ህፃናት ወላጆች ጋር እርቅ መፈፀማቸውን በሶስት ቅጣት ማቅለያነት ሊያዝላቸው እንደሚገባ ጠቅሶ በአንደኛው ክስ በሶስት አመት እስራት፣በ2ኛ እና በ4ኛ ክሶች ደግሞ ለእያንዳንዳቸው አንድ አመት እስራት ይዞና እነዚህን ጊዜያት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84(1(ለ) ድንጋጌ ደምሮ መነሻ ቅጣቱን አምስት  አመት አድርጎ ይኼው መነሻ ቅጣት በእርከን ሃያ እንደሚያርፍና በሶስት ማቅለያ ምክንያቶች ደግሞ ወደ እርከን አስራ ሰባት እንደሚወርድ ጠቅሶ በዚሁ የቅጣት እርከን ውስጥ ካለው ሬንጅ ውስጥ አመልካች ሊቀጡ የሚገባው ሶስት አመት ከስድስት ወር እስራት ነው፣ የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተ ደግሞ ብር 2000.00 ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ በወንጀል ሕጉም ሆነ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ላይ የተቀመጠውን ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በአመልካች ላይ የተጣለው የቅጣት ውሳኔ ሕጉን የተከተለ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን  ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆኑትን የበታች ፍርድ ቤቶችን የውሳኔ ክፍሎችን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስልጉ ጭብጮች፡-

1. አመልካች ለ2ኛ እና 4ኛ ክሶች ጥፋተኛ ተብለው በመነሻ ቅጣትን የተያዘው ጊዜ ወደ ፅኑ እስራት ሳይቀር ከ1ኛው ክስ ጋር ተደምሮ መነሻ ቅጣቱ መያዙ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም?

2. እያንዳንዱ ቅጣት ማቅለያ የሚያስቀንሰው 1 እርከን ወይስ 2 እርከን ነው? የሚሉት ሁነው አግኝቷል፡፡

***የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-***

አመልካች በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባሉት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) እና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 559(2) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ተላልፈዋል ተብለው በሶስት ክሶች ነው፡፡እነዚህ ድንጋጌዎች የሚያስቀጡት በቀላል እስራት መሆኑን ድንጋጌዎች ያሳያሉ፡፡በመሆኑም የመነሻ ቅጣቱ ሲወሰን ለእያንዳንዱ የወንጀል ድንጋጌ ከተለየ በኋላ ተደምሮ የሚመጣው ውጤት ሲሆን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 84(1(ለ)) ድንጋጌ መሰረት እንደተመለከተው በቅጣት አደማመር ጊዜ በጽኑ እስራትና ቀላል እስራት በሚያስቀጡ ድንጋጌዎች አንድ ሰው ጥፋተኛ ከተባለ በቅድሚያ የቀላል እስራት ቅጣት ወደ ጽኑ እስራት መለወጥ አለበት፡፡ይህ ስሌት ተፈጻሚ መሆን እንደአለበትም ተሻሽሎ የወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያም በአንቀጽ 22 ስር ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡የወንጀል ሕጉም ሆነ የቅጣት መመሪያው አንድ ሰው በቀላል እስራት በሚያስቀጡ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ አድራጎቶች ጥፋተኛ ከተባለ ለእያንዳንዱ አድራጎት የሚጣለው ቅጣት ወደ ጽኑ እስራት መለወጥ ያለበት መሆኑን አይገልፁም፡፡በመሆኑም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543(2) እና 559(2) ድንጋጌ የሚያስቀጡት በቀላል አስራት በመሆኑ ለእያንዳንዱ ድንጋጌ መነሻ ቅጣቱ ተወስኖ ከሚደመሩ በስተቀር የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 559(2) ድንጋጌ ቅጣት ወደ ፅኑ እስራት ተቀይሮ ለወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) ለመነሻነት ከተያዘው ቅጣት ጋር የሚደመርበት የሕግ አግባብ የሌለ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

***ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ***፡-አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸው የህግ ድንጋጌዎች በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሻሽሎ በወጣው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 የወንጀሉ ደረጃ የወጣላቸው ሲሆን የስር ፍርድ ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ቅጣቱን በዚህ መመሪያ መሰረት ማስላቱን ተመልክተናል፡፡በክስ አንድ አመልካች የፈፀሙት አድራጎት የወንጀሉ ደረጃ አራት ሲሆን ይህም የቅጣት መነሻ እርከኑ 16 ስር የሚወድቅ ነው፡፡ለ2ኛ እና 4ኛ ክሶች ደግሞ ደረጃ 1 እርከን 7 የሚያርፍ ነው፡፡በእነዚህ እርከኖች ፍርድ ቤቶች ለእያንዳንዱ መነሻ ቅጣት ከለየ በኋላ ድምሩ አምስት አመት እስራት መሆኑን የገለፀ ይህም በእርከን ሃያ ስር የሚወድቅ ሁኖ በዚህ እርከን ስር ደግሞ ለፍርድ ቤቱ የተተወው ፍቅድ ስልጣን አራት አመት ከአምስት ወር እስከ አምስት አመት ከአራት ወራት እስራት ነው፡፡ይህንኑ ይዘን ወደ ቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ስንመጣ በተጠሪ በኩል የቀረበ ማክበጃ ምክንያት የሌለ ሲሆን አመልካች ሪከርድ የሌለባቸው መሆኑን፣ከግል ተበዳይ ህፃናት ወላጆች ጋር መታረቃቸውና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በቅጣት ማቅለያ ምክንያትነት ተይዞላቸዋል፡፡በመሆኑም አመልካች የሚኖራቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ብዛት ሶስት ይሆናሉ፡፡እነዚህ ማቅለያ ምክንያቶችም በመመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 23(4) ድንጋጌ መሰረት በጠቅላላው ሶስት እርከን የሚያስቀንሱ ይሆናል፡፡ ሆኖም አመልካች ጥፋተኛ የተባሉባቸው ድንጋጌዎች ድርጊቱ በተፈጸመበት የካቲት 13 ቀን 2005 ዓ/ም ተፈጻሚነት በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት የቅጣት ማቅለያ ዋጋ አያያዝ ከተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ የተለየ ነው፡፡በዚህም ምክንያት እኛም የቅጣት ማቅለያ ዋጋ አያያዝን ከወንጀል ሕጉ አንቀፅ 6 ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ አንጻር ለአመልካች የተሻለ ሁኖ ያገኘነው ነባሩ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በመሆኑ የቅጣቱን መጠን ከዚሁ አንፃር ተመልክተናል፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች እንዲቀጡ በመነሻነት የሚያዘው እርከን 20 በመሆኑ በዚህ እርከን መነሻ ሲያዝ የቅጣት መጠኑ ከአንድ አመት በላይ እና ከሰባት አመት በታች በመሆኑ አመልካች ያላቸው ሶስት የቅጣት ማቅለያዎች በመመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀጽ 16(6) ድንጋጌ መሰረት እያንዳንዳቸው ሶስት እርከን የሚያስቀንሱ በመሆኑ ከእርከን 20 ወደ እርከን 14 መውረድን፣ በዚህ እርከን ውስጥ ተገቢውን ቅጣት መወሰን የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ መሰረት ቅጣቱን ስናሰላው አመልካች ሊቀጡ የሚገባው በእርከን 14 ስር ለፍርድ ቤቱ በተተወው የፍቅድ ስልጣን ማለትም ከሁለት አመት ከስድስት ወር እስከ ሶስት አመት እስራት ውስጥ ነው፡፡ከእነዚህ የእስራት ጊዜያት አመልካችን ያርማል፣ሌሎች መሰል አጥፊዎችን ከወዲሁ ያስጠንቅቃል ብለን ያመነው ሶስት አመት ቀላል እስራት ሁኖ አግኝተናል፡፡ሲጠቃለልም ከላይ በዝርዝር በተመለከቱት ህጋዊ ምክንያቶች የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 133523 ጥር 21 እና 29 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 98818 ግንቦት 29 ቀን 2006 ዓ/ም ተሻሻሎ የተወሰነው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(2)(ለ-2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በ1ኛ፣ በ2ኛ እና 4ኛ ክሶች በተናጠል ጥፋተኛ መባላቸው ተገቢ ነው ብለናል፡፡ቅጣቱን በተመለከተም ለእያንዳንዳቸው መነሻ ቅጣቱ ከተለየ በኂላ ወደ ፅኑ እስራት ሳይቀየር መደመራቸው ተገቢ ነው ብለናል፡፡የቅጣት ማቅለያ ዋጋ አያያዝን በተመለከተ ግን ሶስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የሚያስቀንሱት ስድስት እርከን በመሆኑ ከእርከን 20 ወደ እርከን 14 በመውረድ በዚሁ እርከን ውስጥ በሶስት አመት እስራት እንዲቀጡ ብለናል፡፡የገንዘብ መቀጮውን በተመለከተ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
3. አመልካች በጉዳዩ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሁኖ በዚህ ችሎት በተወሰነው የእስራት ቅጣት መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይገለጽለት ብለናል፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

**ሩ/ለ**

የሰ/መ/ቁ/ 99883

ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ገ/ሥላሴ ገብሩ - ጠበቃ ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ ቀረቡ፣ ጠበቃ ሐና ዲግራንዲ ከመቀሌ በV.C. ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የትግራይ ብ/ክ/መንግስት ፍትሕ ቢሮ - ዐ/ሕግ ገ/እግዚአብሔር ተወልደብርሃን ከመቀለ በV.C. ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ እና ቁጥራቸው 98349 እና 98350 በሆኑት በዛሬው ዕለት በዚሁ ችሎት ውሳኔ በተሰጠባቸው ሌሎች ሁለት መዝገቦች ለቀረበው የሰበር ክርክር ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው ተጠሪ በ19/08/2003 ዓ.ም በተጻፈ የክስ ማመልከቻ በትግራይ ክልል በመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች እና 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በነበሩት ሌሎች ሁለት ተከሳሾች ላይ ስድስት የወንጀል ክሶችን በማቅረቡ ሲሆን ይዘታቸውም በአጭሩ፡-

1. በአንደኛ ክስ ሶስቱም ተከሳሾች በገቢ ግብር አዋጅቁጥር 286/1994 በአንቀጽ 96 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በተለያየ የንግድ ስራ ዘርፍ ተሰማርተው ይሰሩ በነበረበት ጊዜ

    - 1ኛ ተከሳሽ አቶ ገ/ሥላሴ ገብሩ ከ1997 ዓ.ም. እስከ 2002 ዓ.ም. ድረስ መክፈል ይገባቸው የነበረውን ግብር ብር 1,973,389.10 ባለመክፈላቸው፤
    - 2ኛ ተከሳሽ ወ/ት ብርኽቲ ተስፋይ ከ1999 ዓ.ም. እስከ 2000 ዓ.ም. ድረስ መክፈል ይገባቸው የነበረውን ግብር ብር 1,209,320.17 ባለመክፈላቸው፤
    - 3ኛ ተከሳሽ አቶ ፍጹም አብርሃ ከ2000 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ መክፈል ይገባቸው የነበረውን ግብር ብር 25,102.93 ባለመክፈላቸው ሕግን በመጣስ ግብር ያለመክፈል ወንጀል አድርገዋል፤

2. በሁለተኛ ክስ ሶስቱም ተከሳሾች በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 በአንቀጽ 49 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በተለያየ የንግድ ስራ ዘርፍ ተሰማርተው ይሰሩ በነበረበት ጊዜ፡-

- 1ኛ ተከሳሽ በገዛ ገብረስላሴ ባህላዊ ምግብ ቤት የወ/ሮ ከለላ ሃደራ ወኪል ሆነው በሰሩበት ጊዜ ከሚያዝያ እስከ የካቲት ወር 1999 ዓ.ም. ድረስ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ይገባቸው የነበረውን ብር 2,195,929.51 የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ባለማድረጋቸው፤
- 2ኛ ተከሳሽ ከሐምሌ 1999 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2002 ዓ.ም. ድረስ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ይገባቸው የነበረውን ብር 3,094,268.85 የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ባለማድረጋቸው፤እንዲሁም ከሐምሌ 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ሲገባቸው ባለመመዝገባቸው፤
- 3ኛ ተከሳሽ ከሐምሌ 2001 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2002 ዓ.ም. ድረስ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ይገባቸው የነበረውን ብር 199,334.17 የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ባለማድረጋቸው፤እንዲሁም ከሐምሌ 2001 ዓ.ም. ጀምሮ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ሲገባቸው ባለመመዝገባቸው፤ሕግን በመጣስ ታክስ ያለመክፈል ወንጀል አድርገዋል።

3 በሶስተኛ ክስ 1ኛ ተከሳሽ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 98(1)(ሀ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በመቀሌ ከተማ ለሚያሰሩት ባለ አምስት ኮከብ ሆቴል ከቀረጥ ነጻ ያስገቡት የተለያየ መጠን ያለው የቀረጥ መጠኑ ብር 8,741,024.44 የሆነ ቴንዲኖ በባለሙያዎች ተፈትሾ ባለመገኘቱ ከቀረጥ ነጻ ሆኖ ወይም በቅናሽ ቀረጥ የገባን ዕቃ ከቀረጥ ነጻ መብቱ ከተሰጠበት ዓላማ ውጪ ለሌላ አገልግሎት የማዋል ወንጀል አድረገዋል፤

4 በአራተኛ ክስ 1ኛ ተከሳሽ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 686/2002 በአንቀጽ 60(1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ መጀመርያ በሕንጻ ማከራየት የንግድ ዘርፍ ፈቃድ አውጥተው ከ2001 እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ ባለመክፈል እና ባለማደሳቸው፤በከብት ማድለብ የንግድ ዘርፍ ፈቃድ አውጥተው ከ2001 እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ ባለመክፈል እና ባለማደሳቸው፤ እንዲሁም በምግብ ቤት የንግድ ዘርፍ ፈቃድ አውጥተው ከ2001 እስከ 2003 ዓ.ም. ድረስ ሳይከፍሉ እና የጸና/የታደሰ/ የንግድ ፈቃድ ሳይዙ በንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው በመገኘታቸው የጸና የንግድ ፈቃድ ሳይዙ በንግድ ስራ ላይ የመሰማራት ወንጀል አድርገዋል፤

5 በአምስተኛ ክስ 1ኛ ተከሳሽ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 በአንቀጽ 50(3)(ለ) ስር የተደነገገውን ተላልፈው በክሱ ዝርዝር የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት በመፈጸማቸው የሐሰት ወይም አሳሳች መረጃ የማቅረብ ወንጀል አድርገዋል፤

6 በስድስተኛ ክስ1ኛ ተከሳሽ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 በአንቀጽ 97(3)(ለ) የተደነገገውን ተላልፈው በክሱ ዝርዝር የተመለከተውን የወንጀል ድርጊት በመፈጸማቸው የሐሰት ወይም አሳሳች መረጃ የማቅረብ ወንጀል አድርገዋል፤የሚሉ ናቸው።

1ኛ ተከሳሽ ያቀረቧቸው የመቃወሚያ ነጥቦች ውድቅ ከተደረጉ በኃላ ተጠይቀው ሶስቱም ተከሳሾች ወንጀሎቹን አላደረግንም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ በተጠሪ በኩል የቀረቡ በሁሉም ክሶች ኦዲተሮችን ጨምሮ በድምሩ የአስራ ሰባት ምስክሮችን ምስክርነት ከሰማ እና የኦዲት ሪፖርትን

ጨምሮ የተጠሪን የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተጠሪ በክሶቹ መሰረት አላስረዳባቸውም በማለት 1ኛ ተከሳሽን ከአምስተኛ እና ከስድስተኛ ክሶች በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 141 መሰረት በማሰናበት እና ቀሪዎቹን ክሶች በተመለከተ ግን ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ ሶስቱም ተከሳሾች  መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ ሶስቱም ተከሳሾች የተለያዩ የመከላከያ ጭብጦችን በማስያዝ በጋራ እና በተናጠል በመሆን በድምሩ አስራ አምስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ ከመሆኑም በላይ የተለያዩ ሰነዶችንም በመከላከያነት አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በአንደኛ ክስ በተጠሪ የቀረበባቸውን ክስ እና ማስረጃ በመከላከያቸው ያስተባበሉ መሆኑን ገልጾ በአንደኛ ክስ ከተመለከተው የወንጀል ክስ በነጻ ያሰናበታቸው ሲሆን ይከላከሉ በተባሉባቸው በቀሪዎቹ ክሶች ግን ሶስቱም ተከሳሾች ባሰሟቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰከረባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበልል አልቻሉም በማለት በየክሶቹ በተጠቀሱባቸው ድንጋጌዎች ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ በማስተላለፍ ግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡ በመቀጠልም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ካመዛዘነ በኃላ፡-

- 1ኛ ተከሳሽ በአንደኛ ክስ ስር በሁለት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት፤በሁለተኛ ክስ ስር በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት፤በሶስተኛ ክስ ስር በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት፤በአራተኛ ክስ ስር በአራት ዓመት ጽኑ እስራት በብር 200,000 መቀጮ በድምሩ በአስራ አንድ ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እና በብር 200,000 መቀጮ፤
- 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች እያንዳንዳቸው በሶስት ዓመት ጽኑ እስራት(የቅጣት መጠኑን በተመለከተ ብቻ በአብላጫ ድምጽ)፤እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሶስቱም ተከሳሾች በአንድነት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 54809 ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ከተሰጠው ውሳኔ መካከል በከፊሉ ቅር በመሰኘት በመዝገብ ቁጥር 54810 ይግባኝ አቅርቦአል፡፡ ፍርድ ቤቱም በከፍተኛ ፍርድ ቤት በሁለተኛ ክስ በተሰጠባቸው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሶስቱም ተከሳሾች ያቀረቡትን ይግባኝ በትዕዛዝ የዘጋ ሲሆን በ1ኛ ተከሳሽ እና በተጠሪ መካከል በሁለቱም መዝገቦች የቀረበለትን ክርክር በተመለከተ ግን ክርክሩን በአንድነት ከመረመረ በኃላ በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበውን ይግባኝ ውድቅ አድርጎ የ1ኛ ተከሳሽን የይግባኝ ክርክር በመቀበል በከፍተኛ ፍርድ ቤት በአንደኛ፣በሶስተኛ እና በአራተኛ የወንጀል ክሶች ተሰጥቶባቸው የነበረውን የጥፋተኛነት እና የቅጣት ውሳኔ ሽሮ በነጻ አሰናብቷቸዋል፡፡

ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ተጠሪ ባቀረበው አቤቱታ ሳቢያ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 98(1)(ሀ) ተጠቅሶበት የቀረበው ሶስተኛው ክስ ሁለተኛ ይግባኝ ያለው በመሆኑ ምክንያት በሰበር ሊያየው እንደማይችል ገልጾ በማለፍ በአንደኛ እና በአራተኛ የወንጀል ክሶች በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በማጽናት እና በ4ኛ ክስ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ የተሰጠው የቅጣት መጠን አንሷል በሚል የቀረበውን የዐቃቤ ሕግ አቤቱታ በመቀበል እና ለ4ኛ የወንጀል ክስ ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት በማስላት የመቀጮ ውሳኔውን ሳይነካ 1ኛ ተከሳሽ በሁለተኛ ክስ የተሰጠባቸውን የሶስት ዓመት ጽኑ እስራት ጨምሮ በድምሩ በአስራ አራት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ

የሰጠ ሲሆን 1ኛ ተከሳሽ በዚህ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 99883 አቤቱታ ያቀረቡትም ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ በስር የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጣምረው ከቀረቡት ክሶች መካከል አንዱ የተጨማሪ እሴት ታክስን የሚመለከት ከመሆኑ አንጻር ጉዳዩን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በአመልካቹ ላይ ከቀረቡት ስድስት የወንጀል ክሶች መካከል ሶስቱ ማለትም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 ተጠቅሶበት የቀረበው ሁለተኛ ክስ፣ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 98(1)(ሀ) ተጠቅሶበት የቀረበው ሶስተኛ ክስ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 50(3)(ለ) ተጠቅሶበት የቀረበው አምስተኛ ክስ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 4(4) እና 15(1) ድንጋጌዎች መሰረት የሚወድቁት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር መሆኑ፣እነዚህ ክሶች ለመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊቀርቡ የቻሉትም በሕገ መንግስቱ በተሰጠው የስልጣን ውክልና መሰረት መሆኑ፣ቀሪዎቹ ሶስት ክሶች በክልሉ የወረዳ ፍርድ የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ ሆነው ነገር ግን በስልጣን ውክልና መሰረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ከቀረቡት ክሶች ጋር ተጠቃለው ለከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ የተደረገው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 109(3) ድንጋጌ መሰረት መሆኑ እና ይህም ተገቢነት ያለው የክስ አቀራረብ ስርዓት መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ ይልቁንም አከራካሪ ሆኖ የቀረበው በአንድ ተከሳሽ ላይ ከቀረቡት ከአንድ በላይ ከሆኑ ክሶች መካከል ከፊሎቹ የሚወድቁት በፌዴራል ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር፣ከፊሎቹ ደግሞ በክልል ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር በሆነ ጊዜ እና ነገር ግን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 109(3) ድንጋጌ ስር በተመለከተው የክስ አቀራረብ መርህ መሰረት ተጠቃለው በቀጥታም ሆነ በውክልና በፌዴራል ፍርድ ቤት ቀርበው እንዲታዩ ተደርገው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔ ከተሰጠባቸው በኃላ ወደ ይግባኝ እና ወደ ሰበር የክርክር ደረጃ ሲደርሱ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ እንደተደረገው ሁሉ ተጠቃለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ስርዓት ተከትለው መጠናቀቅ አለባቸው ወይስ እንደየሚወድቁበት የስረ ነገር ስልጣን ሁኔታ ተነጣጥለው ከፊሎቹ የክልል ፍርድ ቤቶችን፣ከፊሎቹ ደግሞ በፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ስርዓት ተከትለው መጠናቀቅ አለባቸው? የሚለው ዓቢይ ነጥብ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በስራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ የወጣው በሀገሪቱ ውስጥ የፌዴራል የአስተዳደር ስርዓት እና ይህንኑ ተከትሎ አዲስ የፍርድ ቤቶች አወቃቀር ስርዓት ከመዘርጋቱ ከበርካታ ዓመታት በፊት በመሆኑ የስነ ስርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች በዚህ መዝገብ አከራካሪ ሆኖ ለቀረበው ነጥብ ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉ አይደሉም፡፡ በመሆኑም የሀገሪቱን አዳዲስ ሁኔታዎች ያገናዘበ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ተቀርጾ ተግባራዊ እስከሚደረግ ድረስ አከራካሪ ሆኖ ከቀረበው ነጥብ ጋር ግንኙነት ያላቸው አሁን በስራ ላይ ያለው የወንጀል የስነ ስርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ከፌዴራሊዝም ስርዓት እና ይህንኑ ተከትሎ ከተዘረጋው የፍርድ ቤቶች አወቃቀር ጋር በተቻለ መጠን ሁሉ ሊጣጣም በሚችል ሁኔታ እየተተረጎሙ ተግባራዊ እንዲሆኑ ከማድረግ ውጪ የተሻለ አማራጭ አይኖርም፡፡

በመሰረቱ በአንድ ተከሳሽ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ የወንጀል ክሶች በቀረቡ ጊዜ ክሶቹ በመርህ ደረጃ በአንድነት መታየት የሚገባቸው ስለመሆኑ በስነ ስርዓት ህጉ በቁጥር 116(2) ስር የተቀመጠው ድንጋጌ ዓይነተኛ ዓላማ በአንድ በኩል በተለያዩ ፍርድ ቤቶች እና መዝገቦች በአንድ ተከሳሽ ላይ ለየብቻ የቀረቡትን ከአንድ በላይ የሆኑ ክሶች በማስተናገድ ሊባክን ይችል የነበረውን ጊዜ እና ሀብት በማዳን ለተከራካሪ ወገኖችም ሆነ ለምስክሮች ምቹ በሆነ ሁኔታ የተቀላጠፈ ፍትሕ እንዲሰጥ ለማስቻል እና በሌላ በኩል ደግሞ በክሶቹ ተነጣጥሎ መታየት ሳቢያ በክሱ ክትትል ረገድም ሆነ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ በቅጣት አጣጣል ረገድ በተከሳሽ ወገን ላይ ሊደርስ የሚችለውን አላስፈላጊ ጉዳት በተቻለ መጠን ለማስወገድ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 109(3) ድንጋጌ ስር ከተመለከተው የክስ አቀራረብ መርህ አንጻር ከላይ የተጠቀሰው የቁጥር 116(2) ድንጋጌ ዓላማ ሊሳካ የሚችለው ደግሞ ተጠቃለው የታዩት ክሶች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔ ከተሰጠባቸው በኃላ ወደ ይግባኝ እና ወደ ሰበር የክርክር ደረጃ ሲደርሱ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ እንደተደረገው ሁሉ ተጠቃለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ስርዓት ተከትለው እልባት እንዲያገኙ ሲደረግ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የመቀሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሶቹን አጠቃሎ የተመለከተው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣኑ መሆኑን በመግለጽ የክልሉ ሰበር ችሎት በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ጉዳዮችን የማየት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ ከአመልካች የቀረበለትን መቃወሚያ ሰበር ችሎቱ ሳይቀበል የቀረው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ ናቸው ከተባሉት መካከል 2ኛውን ክስ አስመልክቶ የቀረበለት አቤቱታ አለመኖሩን እና 3ኛው ክስ ደግሞ የይግባኝ ስርዓቱ ያልተጠናቀቀ በመሆኑ ምክንያት በሰበር ሊታይ የማይችል መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡ ይህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቋም ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት ተጠቃለው እንዲታዩ የተደረጉት የወንጀል ጉዳዮች በይግባኝ እና በሰበር የክርክር ደረጃ ሲደርሱ እንደየሚወድቁበት የስረ ነገር ስልጣን ሁኔታ ከፊሎቹ የክልል ፍርድ ቤቶችን፣ ከፊሎቹ ደግሞ በፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ስርዓት ተከትለው እና ተነጣጥለው የሚታዩበትን አሰራር የሚፈጥር በመሆኑ እና የስነ ስርዓት ሕጉን ቁጥር 109(3) እና 116(2) ድንጋጌዎች ዓላማ የሚያሳካ ባለመሆኑ የተሻለ የክርክር አመራር አማራጭ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣኑ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 109(3) እና 116(2) ድንጋጌዎች መሰረት አጠቃሎ በማየት በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔ የሰጠባቸው ከፊሎቹ በክልል፣ከፊሎቹ ደግሞ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣኑ በይግባኝ አይቶ በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ ቀጥሎ ባለው የክርክር ሂደት መታየት የሚገባቸው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ እንደተደረገው ሁሉ ተጠቃለው የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ስርዓት ተከትለው መሆን ሲገባው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የቀረበለትን መቃወሚያ ባለመቀበል በክልሉ ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ ናቸው በማለት የቀረበለትን የሰበር አቤቱታ ተቀብሎ በከፊሎቹ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ውሳኔ መስጠቱ በክርክር አመራር ረገድ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 63092 በ12/07/2006 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ከላይ በተጠቀሰው ስነ ስርዓታዊ ምክንያት በአብላጫ ድምጽ ተሽሯል፡፡
2. የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ከፌዴራል ጉዳይ ጋር በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 109(3) ድንጋጌ መሰረት አጠቃሎ ያየውን የክልል ጉዳይ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር የማየት ስልጣን የለውም በማለት ወስነናል፡፡
3. በአንድ ተከሳሽ ላይ ከቀረቡት ከአንድ በላይ ከሆኑ ክሶች መካከል ከፊሎቹ የሚወድቁት በፌዴራል ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር፣ከፊሎቹ ደግሞ በክልል ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን ስር በሆነ ጊዜ እና ነገር ግን በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 109(3) ድንጋጌ ስር በተመለከተው የክስ አቀራረብ መርህ መሰረት ተጠቃለው በቀጥታም ሆነ በውክልና በፌዴራል ፍርድ ቤት ቀርበው እንዲታዩ ተደርጎ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት በአንድ ወይም በሌላ አግባብ ውሳኔ ከተሰጠባቸው በኃላ ወደ ይግባኝ እና ወደ ሰበር የክርክር ደረጃ ሲደርሱ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ እንደተደረገው ሁሉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የይግባኝ እና የሰበር ስርዓት ተከትለው እና ተጠቃለው መታየት አለባቸው በማለት ወስነናል፡፡
4. እንዲያውቀው የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. ውሳኔ ያገኝ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

**የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

## የሃሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር ሁለት የተገለጸው ዳኛከአብላጫው ድምጽ በተሰጠው የህግ ትርጉምና ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኔ በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡ የስራ ባልደረቦቼ ከሰጡት የህግ ትርጉምና ከደረሱበት መደምደሚያ የተለየሁባቸውምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ከአብላጫው ድምጽ በውሳኔ እንደተገለጸው፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ውክልና ያለው የክልሉ ዐቃቤ ህግ አመልካች በአዋጅ ቁጥር 622/2001 የተመለከተውን በመተላለፍ፣ ከግብር ነጻ ያስገባውን የግንባታ ማቴሪያል፣ ለሌሎች ሰዎች አሳልፎ በመስጠት ወይም በመሸጥ ወንጀል እንደፈጸመና፣ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 ድንጋጌዎች እንደተሻሻሉና አዋጅ ቁ.286/1994 የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመ መሆኑን፣የአዋጅ ቁጥር 686/2002 ድንጋጌ በመተላለፍ የጸና ንግድ ፍቃድ ሳይኖረው የንግድ ስራ በማከናወን ወንጀል የፈጸሙ መሆኑን የሚዘረዝር የወንጀል ክስ ለመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል የክልሉ አቃቤ ህግ በአመልካች ላይ ያቀረባቸው የወንጀል ክሶች

መካከል ክፊሎቹ በፌዴራል ፍ/ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቁና ክፊሎቹ ደግሞ በክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት /የወረዳ ፍ/ቤት/ የዳኝነት የስር ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁ መሆናቸው የሚያከራክር አይደለም፡፡

2. እያከራከረ ያለው፣ የክልሉ አቃቤ ህግ በክልል ፍ/ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ስልጣን ስር እና በወረዳው ፍ/ቤት የዳኝነት የስር ነገር ስልጣን ስር የሚወድቁትን የወንጀል ክሶች፣ የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 109 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 117 በሚደነገገው መሰረት በአንድ ላይ አጠቃልሎ ለመቀሌ ከተማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ማቅረብና የዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ያቀረበለትን የወንጀል ክሶች በመቀበል ፣የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ መስጠቱ፣ ጉዳዩ በይግባኝ እና በሰበር ታይቶ በሚወሰንበት ስርዓትና በክልል ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ላይ የሚኖረው ውጤት ምንድን ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡

3. ተጠሪ የፌዴራል ወንጀል የሆኑትንና የክልሉን ወንጀል የሆኑትን ጉዳዮች በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 109 ንዑስ አንቀጽ /3/ መሰረት በማጣመር ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 ንዑስአንቀጽ 4 ከክልል የዳኝነት ስልጣን በተጨማሪ የተሰጠው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስልጣኑ በመጠቀም የወንጀል ክሶቹን አይቶ እንዲወስንና ከዚህ ጎን ለጎን በኢፊዲሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 7 በክልሉ ህገ መንግስትና በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ በተሰጠው ክልልዊ የዳኝነት ሥልጣኑ መሠረት የፌዴራሉንና የክልሉን የወንጀል ጉዳዮች ጎን በጎን እውነት ፍርድ እንዲሰጥባቸው በማሰብ እንደሆነ ተጣምረው ከቀረቡለት የወንጀል ክሶች ይዘት ሙሉ መሠረታዊ ባህሪ፤ ከሕገ መንግስቱና ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

4. በእርግጥ የክልል ዐቃቤ ህግ የፌዴራል የክልል የወንጀል ጉዳዮች አጣምሮ ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለማቅረብ መሠረት አድርጎ የሚከራከረው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ በጠቅላላውና የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 109 ንዑስ አንቀፅ 3፣ አንቀፅ 117 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች አገሪቱ፣ አህዳዊ ቅርፀ መንግስት ትተዳደር በነበረበት ጊዜና የዳኝነት ሥልጣንም በአንድ ማዕከላዊ መንግስት ተጠቃሎ ተይዞ በነበረበት 1954 ዓ/ም የታወጁ ናቸው፡፡ እነዚህን እድሜ ጠገብ ድንጋጌዎች የመንግስት ስልጣን በፌዴራልና በክልል በተዋቀረበትና የዳኝነት ሥልጣንም በፌዴራልና በክልል ደረጃ ተከፍሎ ተግባራዊ በሆነበት ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ውስጥ ተፈፃሚ ሲያረጉ በሕገመንግስቱ አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 7 አንቀጽ 78 እንደዚሁም የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 3 (ለ) ንዑስ አንቀጽ 3 እና ንዑስ አንቀጽ 4 የተደነገጉትን መሠረታዊ መርሆች በማይጥስ ወይም በማይሸራርፍ መንገድ መተርጎምና ተግባራዊ ማድረግ ይጠይቃል የሚል እምነት አለኝ፡፡

5. ከዚህ አንፃር ሲታይ የመቀሌ ከተማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 ንዑስ አንቀፅ 3 እና የወ/መ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር 117 መሠረት አጣምሮ ካቀረበለት የወንጀል ክሶች መካከል፣ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን ስር የሚወድቁትን የወንጀል ክሶች በሕገመንግስት አንቀፅ 88 ንዑስ አንቀፅ 4 ካለው ክልልዊ የዳኝነት ሥልጣን በተጨማሪ ተደርቦ የተሰጠውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን በመጠቀም አይቶ አከራክሮና መርምሮ ፍርድ ሰጥቶበታል ተብሎ ሊያዝ የሚገባው ነው፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ሥር ከሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮች ጋር በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 ንዑስ

አንቀፅ 3 መሠረት ተጣምረው የቀረቡትን በክልል የዳኝነት ስልጣን ሥር የሚወድቁ የወንጀል ክሶች የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀጽ 7 በክልሉ ሕገ መንግስትና ሌሎች ክልላዊ የሕግ ማዕቀፎች የተሠጠውን ክልላዊ የዳኝነት ስልጣን በመጠቀም ጉዳዮችን አይቶ አከራክሮና በማስረጃ አጣርቶ ፍርድ ሰጥቶበታል የሚል ግንዛቤ ሊይዝ ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

6. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያለውን የፌዴራልና የክልል የዳኝነት ስልጣን መሰረት በማድረግ የሰጠው ፍርድ በይግባኝ አይቶ የወሰነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፤ ይግባኙን መርምሮ ውሳኔ የሰጠው በሕገ መንግስቱና ሌሎች ሕጎች የተሰጠውን ድርብ የዳኝነት ሥልጣን መሰረት በማድረግ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 4 እና በአዋጅ ቁጥር 25/1988 የተሰጠውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣኑ አይቶ በሰጠው ፍርድ ላይ ተጠሪ ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 2 በተጨማሪነት በተሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣኑንና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 5 የተሰጠውን የፌዴራል የይግባኝ የዳኝነት ስልጣን በመጠቀም ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ በሌላ በኩል የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከፌዴራል የወንጀል ክሶች ጋር ተጣምረው በቀረቡለት የክልል የወንጀል ክሶች ላይ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የቀረበለትን የይግባኝ ቅሬታ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 7፣ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 6 በክልሉ ሕገ መንግስትና በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ የሰጠውን ክልላዊ የይግባኝ የዳኝነት ስልጣኑን መሰረት በማድረግ መርምሮ ውሳኔ ሰጥቶባቸዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

7. ተጠሪ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ላይ የቀረበውን ጥቅል የይግባኝ ቅሬታ አይቶ ውሳኔ ሲሰጥ፣ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በፌዴራል የይግባኝ የዳኝነት ስልጣኑ አይቶ ውሳኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች ተፈፅሟል የሚለውን መሰረታዊ የሕግ ስህተትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በክልል የይግባኝ የዳኝነት ስልጣኑ አይቶ ውሳኔ በሰጠባቸው ክልላዊ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ፈፅሟል የሚለውን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት፣ በሰበር አይቶ እንዲያርምለት ጥያቄ ያቀረበ መሆኑን መዝገቡ ያሳያል፡፡ ሆኖም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በተጠሪ በኩል የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ይዘትና ከላይ የገለፅናቸውን የሕገመንግስቱን ድንጋጌዎች በማገናዘብ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ስልጣኑ አይቶ ውሳኔ የሰጠባቸውና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ይግባኝ የዳኝነት ስልጣኑ አይቶ ያሻሻላቸው ወይም በሻራቸው የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንዲታይለት ተጠሪ ማቅረቡ ህጋዊ መሰረት የሌለውና ተጠሪ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 5 በተደነገገው መሰረት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ እንዳለበት ገልፆ የተጠሪን የሰበር አቤቱታ ውድቅ ያደረገው መሆኑን ፣የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተደራቢ የዳኝነት ስልጣኑ አይቶ ውሳኔ በሰጠባቸው የፌዴራል ወንጀሎች ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በክልል የዳኝነት ሥልጣኑ በተጨማሪነት በተሰጠው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል የይግባኝ ሥልጣኑ መሠረት አይቶ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል ዳኝነት ሥልጣኑ የሰጠውን ውሳኔ ባፀናባቸው ጉዳዮች ፣ጉዳዩን በሰበር አይቶ የመወሰን ሥልጣን የሌለው መሆኑንና የሰበር አቤቱታው መቅረብ

የሚገባው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንደሆነ በመግልፅ የወሰነ መሆኑን መዝገቡ ያሣያል

8. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ፣ተጠሪ የሰበር አቤቱታ ካቀረበባቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፍርድ ከሰጡባቸው የወንጀል ጉዳዮች ውስጥ በሰበር አይቶው ውሣኔ የሰጠበት ተጠሪ ከፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች ጋር በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት አጣምሮ ክስ ያቀረበባቸውን በክልሉ ፍርድ ቤቶች የወንጀል የዳኝነት ስልጣን ሥር የሚወድቁ ክልላዊ የወንጀል ጉዳዮች ላይ የሆኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክልላዊ የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑን በመጠቀም ይግባኝ ሰሚው ችሎት ደግሞ ክልላዊ የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣኑን በመጠቀም በሰጡት ፍርድ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለመሆኑን በማጣራት ነው፡፡ ይህም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 2 የተሰጠውን በክልል ጉዳይ ላይ ያለውን የበላይና የመጨረሻ ሥልጣንና በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 3(ለ) የተሰጠውን የሰበር ሥልጣን መሠረት ያደረገና የሕግ ስህተት የሌለበት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

9. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነውን ውሳኔ የሰጠው በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 ተጣምረው ከቀረቡላቸው የፌዴራልና የክልል የወንጀል ክሶች፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በሕገ መንግስቱ ተደርቦ የተሰጣቸውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃና የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን መሠረት በማድረግ ፍርድ የሰጡባቸውን የፌዴራል የወንጀል ጉዳዮች በሰበር አይቶ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን የሌለው መሆኑን በግልፅ ለይቶ አውጥቶ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመወሰንና ከተጣመሩት የወንጀል ክሶች ውስጥ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት በክልል የዳኝነት ሥልጣናቸው አይተው ውሣኔ የሰጡባቸውን የወንጀል ጉዳዮች ላይ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ብቻ በመመርመር ነው፡፡ በእኔ እምነት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 ንዑስ አንቀፅ /3/ እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 117 መሰረት ተጣምረው ያቀረቡለትን የፌዴራልና የወንጀል ክሶችን በአንድ ላይ አይቶ የመወሰን ድርብ የዳኝነት ስልጣን ላለው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጣምረው መቅረባቸው፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል የወንጀል ክሶችን ከክልል የዳኝነት ስልጣኑ በተጨማሪ በሕገ መንግስቱ በተሰጠው የፌዴራል የዳኝነት ስልጣኑ፣ የክልል የወንጀል ክሶችን ደግሞ በክልል የወንጀል የዳኝነት ስልጣን አይቶ ውሳኔ ለመስጠት፣ በሁሉም የወንጀል ጉዳዮች የሚቀርበውን ክርክር አንድ ላይና በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመስማትና የመወሰን እድል ከመፍጠር ውጭ ከፌዴራል የወንጀል ክስ ጋር ተጣምሮ የወንጀል ክስ የቀረበበትን የክልል የወንጀል ጉዳይ ወደ ፌዴራል ወንጀልነት የመቀየር ውጤት አይኖረውም፡፡

10. የክልሉ ጉዳዮች ከፌዴራል የወንጀል ጉዳይ ጋር ተጣምሮ ክስ ያቀረበበት መሆኑ፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክልላዊ የዳኝነት ስልጣኑ አይቶ ውሳኔ በሰጠባቸው የክልል የወንጀል ክሶች ላይ የሰጠውን ፍርድ፣ ክልላዊ የሆነ የይግባኝና የሰበር የዳኝነት ስልጣን ያላቸው የክልሉ ፍርድ ቤቶች፣ ክልላዊ የሆነ በይግባኝና በሰበር አይተው ጉዳዩን ከመወሰን የሚገድባቸው አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ በዚህ ጉዳይ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3/ለ/ የተሰጠው ክልላዊ የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮች ላይ የሰጡት ውሳኔዎች በሰበር በማየትና ክልላዊ የዳኝነት ስልጣኑን በአግባቡ ከመጠቀም ውጭ የፈፀመው መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለ ብዬ ስለማላምን በሃሳብ ተለይቻለሁ፡፡

በዚህ ጉዳይ የቀረበው አከራካሪና መሰረታዊ የክልልና የፌዴራል የዳኝነት ስልጣን ጭብጥ፣ ይኸ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 91327 ውሳኔ ከሰጠበት ጉዳይ የሚለይባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፡፡ ይኸው የሰበር መዝገብ ቁጥር 91327 የቀረበውን ጉዳይ በመጀመሪያ አይቶ ውሳኔ የሰጠው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወ/መ/ሥ/ሕግ ቁጥር 109 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት ተጣምረው የቀረቡለትን ሁሉንም የፌዴራልና የክልል የወንጀል ጉዳዮች በዳኝነት አይቶ ለመወሰን የማያስችለው ድርብ የዳኝነት ስልጣንና የስረ ነገር ስልጣን የሌለው መሆኑ ነው፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ሕግ አንቀፅ 240 ተጠቅሶና ከክልል የወንጀል ጉዳይ ጋር ተጣምሮ የቀረበለትን የወንጀል ክስ፣ አይቶ የመወሰን ስልጣን በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀፅ 4 መሰረት ያልተሰጠው ቢሆንም፣ ከሌሎች የክልል ጉዳዮች ጋር አጣምሮ በማየት ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡ይህንን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕግ ከተሰጠው ስልጣን ውጭ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቅ የፌደራል ወንጀል የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አይቶ መወሰኑ ስህተት መሆኑን በመረዳት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ስህተቱንየማረምስራባለመሻራቸውናበፍርድ የፈፀመውን ስህተት ባለማረማቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ዉሣኔ የዚህ ሰበር ችሎት ሙሉ በሙሉ እንዲሻር ውሣኔ የተሰጠበት መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡

11. በያዝነው ጉዳይ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ተጣምሮ የቀረበውን የወንጀል ክስ በዳኝነት አይተው ውሣኔ የሰጡት ፣ጉዳዩን ለማየት ክልላዊ የዳኝነት ሥልጣንና በተደራቢ የሆነ የፌደራል የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎትም በሰበር አይቶ የወሰነው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በክልል የዳኝነት ሥልጣናቸው አይተው የወሰኗቸዉን የክልል የወንጀል ጉዳዬች ብቻ ለይቶና መርጦ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ የወንጀል ክሱንም ሆነ የይግባኝ ቅሬታውን እንደወንጀሎች መሠረታዊ ባህሪ በመለየት፣በሁለት የተለያዩ መዝገቦች አለማቅረቡና የወንጀል ክሶችን አጣምሮ በአንድ ላይ ማቅረቡ ጉዳዬቹን አይቶ የመወሰን ሥልጣን ያላቸው የፌደራል ፍርድ ቤቶች ናቸው ከሚለው መደምደሚያ ላይ ያደርሳል የሚል እምነት የሌለኝ በመሆኑ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የተሰጠው ውሣኔ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 7 የሕገ መንግሥቱን አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 (ለ) መሠረት ያደረገ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

**የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ግ**

የሰ/መ/ቁ. 104715

መጋቢት 02 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- መድሕን ኪሮስ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- እንደሻው ይልማ ዳዲ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ አቶ ያሬድ አየለ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ ጉዳዩ የወንጀል ክርክር የሚመለከት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ሁለት ክሶች አቅርበዋል፡፡ አንደኛው ክስ አመልካች የወ/ሕ/ቁ 692(1) የተመለከተውን በመተላለፍ ጉዳይ ፈፃሚ ነኝ የፍቺ የምስክር ወረቀት ላሰራልህ በማለት የግል ተበዳይ ወንድወሰን አራጋው እህት ለሆነችው ፍቅርተ አራጋው እና ባለቤቷ በማታለል በሁለት ጊዜ ክፍያ አርባ ሺህ ብር ከወሰደ በኃላ ለልደታ ክፍለ ከተማ ውልና ጋብቻ መዝገብ የተሰጠ በማስመሰል ሀሰተኛ የፍቺ የምስክር ወረቀት የሰጠመሆኑን፤ 2ኛ ክስ ደግሞ የወ/ሕ/ቁ 385(1)(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ በሀሰት የተዘጋጀ የፍቺ ምስክር ወረቀት በማዘጋጀት ለግል ተበዳይ የሰጠ በመሆኑ፤በምስክር ወረቀቶች ላይ በሚደረግ ወንጀል መከሰሱን የሚያሳይ ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤትም የአመልካች የእምነት ክህደት ቃል በሕጉ አግባብ ከመዘገበ በኃላ አመልካች ክዶ በመከራከሩ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል አዳምጧል፡፡ አመልካች በቀረቡ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ድርጊቱን የፈጸመ መሆኑን በመግለጽ በመመስከራቸው ምክንያት እንዲከላከል ታዞ የመከላከያ ምስክሮችን ቃል ሰምቷል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ ሁኔታ ከተጠናቀቀ በኃላ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቀረቡ ምስክሮች የአሁኑ አመልካች 40 ሺህ ብር ተቀብሎ በሀሰት የተዘጋጀ የፍቺ ምስክር ወረቀት መስጠቱን የቀረቡት የሰው ምስክሮች እንዲሁም አመልካች ለፖሊስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 27(2) በሰጠው ቃል ጭምር እንዳመነ፤በአመልካች በኩል የቀረቡ የመከላከያ ምስክሮች የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ አላስተባበሉም በማለት በተከሰሰባቸው ሁለቱም የህግ ድንጋጌዎች በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 149(1) መሰረት ጥፋተኛ ነው በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

ቅጣትን በተመለከተም የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት ከመዘገበ በኃላ አንደኛው ክስ የወ/ሕ/ቁ 692(1) የወንጀል ደረጃ፣ መነሻ የእስራት ቅጣት እና መቀጮ እርከን የወጣለት በመሆኑ የወንጀሉ ደረጃ 5 ተጓዳኝ የእስራት ቅጣት እርከን 14 መቀጮ ደግሞ 3 በመሆኑ ፍርድ ቤቱም መነሻ ቅጣቱ 2 ዓመት ከ 9 ወር እና 2,500.00 ብር መቀጮ እንዲሆን ወስኗል፡፡ 2ኛ ክስ የወንጀል

ደረጃ እና የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን ያልተዘጋጀለት በመሆኑ የወንጀሉ ደረጃ መካከለኛ ደረጃ በመመደብ አንድ ዓመት ቀላል እስራት በመነሻነት ይዟል፡፡ ሁለቱም መነሻ ቅጣቶችን በመደመር በእርከን 17 ሥር በመክተት ፍቅድ ሥልጣኑ 3 ዓመት ከ 3 ወር እስከ 3 ዓመት ከ 11 ወር ፅኑ እስራት እና 3000,00 ብር መሆኑን በመግለጽ በዓቃቤ ሕግ በኩል የቅጣት ማክበጃ ምክንያት አልቀረበም፡፡ በአመልካች በኩል ሦስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በመቀበል በእርከን 14 ሥር 2 ዓመት ከ 9 ወር እና ብር 600.00 እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ውድቅ ተደርጓል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል የተባለ በመሆኑ ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር ያደረጉ ሲሆን አመልካች በሰበር ቅሬታው የጠቀሰው መሠረታዊ ነጥብ የወንጀል ድርጊት በሁለት የህግ አንቀጾች የሚያስጠይቅ አይደለም፤ የቅጣት አወሳሰን ሥርዓቱም ቀላል እስራት ወደ ጽኑ እስራት ሳይለወጥ የተደመረ በመሆኑ የወ/ሕ/ቁ 184(1)(ለ) ያገናዘበ አይደለም የሚል ነው፡፡ ዓቃቤ ሕግ በሰጠው መልስ የማታለል እና የሀሰት ምስክር ወረቀት ማዘጋጀት ሁለቱም ድንጋጌዎች እራሳቸው የቻሉ እና አንደኛው ሌላኛውን የሳካተተ በመሆኑ በሁለቱም የህግ አንቀጾች ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነው፡፡ ቅጣት በተመለከተ የጽኑ እና ቀላል እስራት በወ/ሕ/ቁ 184 (1) (ለ) መሰረት ያልተሰራ በመሆኑ በህጉ አግባብ ተስተካክሎ በእርከን 12 ሥር ተሰልቶ ቢወሰን ተቃውሞ እንደሌለው አመልክቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም በዚህ ችሎት መታየት ያለባቸው መሰረታዊ ጭብጦች፡- አንደኛ አመልካች ተጠሪ በቀረበው ክስ የተጠቀሱ የህግ ድንጋጌዎች ሥር በሁለቱም ጥፋተኛ መባሉ በሕጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?ሁለተኛ የጥፋተኝነት ውሳኔው በአግባቡ ከሆነ የቅጣት አወሳሰን ሥርዓቱስ የወ/ህ/ቁ 184(1) (ለ) እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2005 ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም የሚሉ ናቸው፡፡

የመጀመርያው ጭብጥ በተመለከተ፡- በመሰረቱ አንድ ድርጊት አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የመነጨ መሆኑ በሕጉ አገላለጽ የተረጋገጠ ከሆነ በአንድ ድንጋጌ ሥር ጉዳይ የሚታይ ስለመሆኑ ከወ/ሕ/ቁ 61 መሰረታዊ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ በሌላ በኩል ተደራራቢ ወንጀሎች መፈጸማቸው ሲረጋገጥ ደግሞ ለሁለት እና ከሁለት በላይ ለሆኑ ድንጋጌዎች አጥፊው በሕጉ አግባብ የሚያስጠይቀው ስለመሆኑ በወ/ሕ/ቁ 60፣63 ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ወንጀል ከመሥራት ሐሳብ የሚመነጩ ድርጊቶች ሕግ አውጪው ራሳቸው ችለው ወንጀል እንደሚያቋቁሙ ለወንጀል ሕጉ ልዩ ክፍል የደነገገ ከሆነም ወንጀል ፈፃሚው በሁለቱም የሕግ አንቀጾች እንደሚቀጣ ግልጽ ነው፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች በአንደኛው ክስ የማታለል ወንጀል በ2ኛ ክስ ደግሞ ሐሰተኛ የምስክር ወረቀት ለግል ተበዳዮች መስጠቱን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ በማታለል ድርጊቱ መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሁኖ በ2ኛ ክስም በተደራቢነት ሊጠይቅ እንደሚገባ በወ/ሕ/ቁ 699 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም አመልካች ሁለቱም ድርጊቶች በአንድ ድንጋጌ ሥር የሚጠቃለሉ ናቸው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት የለውም፡፡

ሁለተኛው ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች በሁለት የህግ ድንጋጌዎች ጥፋተኛ ተብሏል፡፡ የሥር ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለመጀመሪያው ክስ የጽኑ እስራት አማራጭ የተወሰደ ሲሆን ለሁለተኛ ክስ ደግሞ የአንድ ዓመት ቀላል እስራት ወስደዋል፡፡ በጽኑ እስራት እና ቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ተደራርበው ሲገኙ የቀላል እስራት ወደ ጽኑ እስራት

እንደሚለወጥ፣ስሌቱም የሁለት ዓመት ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንደሚቆጠር በወ/ህ/ቁ 184 (1) (ለ) ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሁለተኛው ክስ (ወ/ሕ/ቁ 385) የአንድ ዓመት ቀላል እስራት የወሰነ ቢሆንም ወደ ጽኑ እስራት ሳይለወጥ የሁለቱም ድንጋጌዎች መነሻ ቅጣት በመደመር መወሰኑ የወንጀል ሕጉ እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ያላገናዘበ ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት የተፈፀመው የሕጉን አተገባበር ስህተት ሳያርም ማጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በእነዚህ ሁለቱ ምክንያቶች በሥር ፍርድ ቤቶች የተፈጸመው የሕግ አተገባበር ስህተት በከፊል መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸሙን የሚያሳይ በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ በመሆኑም ከላይ በተመለከተው የህግ ድንጋጌ መሰረት የሁለቱም ድንጋጌዎች መነሻ ቅጣት ሲደመር 3 ዓመት ከ 3 ወር ጽኑ እስራት እንደሚሆን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው የቅጣት ስሌት የምንረዳው ነው፡፡ በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀጽ 26(3) መሰረት መነሻ ቅጣቱ በመወሰንና በመደመር በቅጣት እርከኑ ሠንጠረዥ የሚያርፍበት የቅጣት እርከን መለየት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት መነሻ ቅጣቱ በእርከን 15 የሚካተት ሲሆን በአመልካች በኩል በሥር ፍ/ቤት ተቀባይነት ያገኙ ሦስት የቅጣት ማቅለያዎች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀጽ 23 (1) መሰረት በእያንዳንዱ ማቅለያ ምክንያት እርከን አንድ ወደታች ይቀንሳል፡፡ እንዲህ በመሆኑም ቅጣቱ በእርከን 12 ከተመለከተው ከ2 ዓመት እስከ 2 ዓመት ከ 6 ወር ባለው ፍቅድ ሥልጣን ፍርድ ቤት የመወሰን ሥልጣን አለው፡፡

ቅጣቱ ሲወሰን የወንጀል ሕጉ ዓላማ ግብ በአንድ በኩል በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል ፈፃሚው ግላዊ ሁኔታዎች፣ የወንጀል አፈፃፀም ሁኔታ እና ተዛማጅ ጉዳዮች ግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ላይ የሚወሰነው ቅጣት የሚያስጠነቅቀው፣ የሚያስተምረው፣ሌላ ወንጀል እንዳይፈፅም የሚያደርገው መሆን አለበት፡፡ በሌላ በኩል ማሕበረሰቡም በቂ ትምህርት በመውሰድ ከወንጀል ድርጊት እንዲርቅ የሚያደርገው መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም ከላይ የገለጽነው አጠቃላይ የቅጣት አወሳሰን መርሆዎች መሰረት በማድረግ አመልካች በዚህ ጉዳይ ከአሁን በፊት የታሰረበት ካለ በቅጣቱ የሚካተት ሆኖ በ 2 ዓመት ጽኑ እስራት እና 600.00 ብር መቀጮ እንዲቀጣ ወስነናል፡፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 143927 በ5/06/2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ 102208 በ 30-10-2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195(2) (ለ) (2) ተሻሽሏል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች በተከሰሰባቸው ሁለቱም ድንጋጌዎች ጥፋተኛ መባሉ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
3. የሥር ፍርድ ቤቶች በአመልካች ላይ የወሰኑት እስራት ቅጣት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ.ቁ 195 (2) (ለ) (2) በማሻሻል በሁለት ዓመት ጽኑ እስራት እና 600.00 ብር መቀጮ እንዲቀጣ ወስነናል፡፡ የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤትም በዚህ ችሎት በተሻሻለው ቅጣት መሰረት ተቆጣጥሮ እስራቱን እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ. 92141

መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- የደ/ብ/ብ/ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትፍትሕ ቢሮ አቃቤ ሕግ

ተጠሪ፡- አቶ አለማየሁ አስፋው

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ተጠሪ በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543/2/ ስር የተመለከተውን በመተላለፍ በሾፌርነት ሙያቸው የሌላውን ሰው ሕይወትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ እያለባቸው መጋቢት 02 ቀን 2004 ዓ.ም ከቀኑ 5፣30 ሲሆን ንብረትነቱ የድርባ ደፈርሻ የመንገድ ስራ ተቋራጭ የሆነውን፤ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-25709 ኦሮ የሆነውን ቶዮታ ሃይሉክስ መኪና ከአዲስ አበባ ከተማ ወደ አርባ ምንጭ መሰመር በከፍተኛ ፍጥነት እና የራሳቸውን መስመር በመልቀቅ በማሽከርከር ላይ እያሉ በምዕራብ አባያ ወረዳ ብርብር ከተማ የሰሌዳ ቁጥሩ 2-ደ/ሕ 11444 የሆነችውን ባለሁለት እግር ባጃጅ ሞተር ሲያሽከረክር የነበረውን ንጋቱ ሉቃስ የተባለውን ሰው በመግጨት የገደሉት በመሆኑ በፈፀሙት በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል ተከሰዋል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም የክስ ማመልከቻ ደርሷቸው ክሱን እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ ስለእምነት ክህደት ቃል ሲጠየቁ በክሱ ላይ ተቃውሞ እንደሌላቸው የገለፁ ሲሆን የድርጊቱን አፈፃፀም በተመለከተም ድርጊቱ መፈፀሙን አምነው አፈፃፀሙ ግን እንደ አቃቤ ህግ ክስ ያለመሆኑን ዘርዝረው የክህደት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ አቃቤ ህግ በበኩሉ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ ተጠሪ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈፀማቸው ሟች በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት ሕይወታቸው ያለፈ መሆኑን አቃቤ ህግ በማስረጃዎቹ ያስረዳባቸው መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ታምኖበት ይህንኑ እንዲያስተባብሉ የተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ ማሰማት መብታቸው ተጠብቆላቸው ተጠሪ አንድ የሰው መከላከያ ማስረጃዎችን አሰምቷል፡፡ ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ በሟች ላይ የሞት አደጋ የደረሰው በሟች ጥፋት መሆኑን ከማስረጃዎቹ መረዳቱን ገልፆና በአቃቤ ህግ ማስረጃዎችም ልዩነት መከሰቱን ዘርዝሮ ተጠሪ የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎቹን በመከላከያ ማስረጃቸው አስተባብለዋል በሚል ድምዳሜ ከክሱ በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙንና የሰበር አቤቱታውን እንደየቅደም ተከተላቸው ለክልሉ

ጠቅላይፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ቢያቀርብም ቅሬታው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 195(1) መሠረት ተሰርዞበታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚልባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- ተጠሪ ድርጊቱን የፈፀሙት ከጥንቃቄ ጉድለትና በከፍተኛ ፍጥነት ሲያሽከረክሩ ሆኖ እያለ በስር ፍርድ ቤቶች የሟች ጥፋት አለ ተብሎ የተጠሪ የወንጀል ተጠያቂነት የለባቸውም ሲባል መታለፉ ያላግባብ መሆኑን፣የትራፊክ ባለሙያዎች የሰጡት የትራፊክ ኘላንና የአደጋ መግለጫ የሰነድ ማስረጃዎች ውድቅ የተደረጉት ተገቢውን የማስረጃ ሚዛን ባለመከተል መሆኑን ዘርዝሮ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ በተጠሪው ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዲሰጥ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮ ተጠሪ በነጻ የመለቀቃቸውን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለው ወንጀሉን የሚቋቋሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 414/1996 የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 239(2) በግልጽ ደንግጓል፡፡እንግዲህ አንድን ድርጊት ወንጀል ነው ብሎ ለመወሰን ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች ተጣምረው መገኘት የግድ ይላል፡፡ሕጋዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት አለው ተብሎ የተጠቀሰውን ድንጋጌ ለማቋቋም ሙሉ በሙሉ መሟላት ያለባቸውን ነጥቦች ሲሆን ግዙፋዊና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች የሚባሉት ደግሞ እንደየቅደም ተከተላቸው ከድርጊቱ ማድረግ ወይም አለማድረግና ከሐሳብ ክፍል ጋር በሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚመለከቱ ናቸው፡፡በምክንያትነትና በውጤት መካከል ደግሞ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 24 በተመለከተው አግባብ ግንኙነት መኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ወንጀሉ በተከሳሹ የተፈፀመ መሆኑን ከሳሽ የሆነው ወገን አሳማኝ እና በቂ በሆነ ሁኔታ የማስረዳት ሽክም ያለበት መሆኑን ከወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141፣142 እና 194 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ ሲያሽከረክሩት የነበረው ተሽከርካሪ እና ሟች ሲያሽከረክር የነበረውን ተሽከርካሪ ተጋጭተው ሟች ላይ መጋቢት 02 ቀን 2004 ዓ.ም ጉዳት ደርሶ በዚሁ ጉዳት ምክንያት ሟቹ ለህልፈት የተዳረገ መሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ተጠሪ የሚከራከሩበት ነጥብ በወቅቱ ራሳቸው የሚያሽከረክሩትን መኪና በተገቢው ፍጥነትና ጥንቃቄ በተሞላበትሁኔታ ሲያሽከረክሩ እንደነበር ጠቅሰውና ይህንኑ አይተዋል ተመልክተዋል የሚሏቸውን አንድ የሠው መከላከያ ምስክራቸው አስረድተዋል ሟች የሞቱት በራሳቸው ጥፋት ምክንያት ነው የትራፊክፐላኑ አደጋው የደረሰው በተጠሪ ጥፋት ነው በሚል የቀረበው ተጠሪ ያልፈረሙበት በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም የሚሉ ነጥቦችን በማንሳት መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭና ከዋናው መዝገብ ከሰፈሩት የክርክር ሂደቶች ተገንዝበናል ፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም ይህንኑ የተጠሪን መከራከሪያ ነጥብ የተቀበለው ሲሆን የዐቃቤ ህግ ምስክሮች ቃል ልዩነት ያለበት መሆኑን፣የትራፊክ አደጋ ፐላኑና የአደጋው መግለጫ ሰነዶች የማይታመኑ መሆኑና የተጠሪ መከላከያ ማስረጃ ግን የሚታመኑ መሆኑን በውሳኔ ላይ ጠቅሷል

። ይሁን እንጂ የሥር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ ቀጥተኛና አግባብነት ያለውን የባለሙያ የምስክርነት አስተያየት በአደጋው ቦታ የተነሳውን ፕላንና የግራ ቀኙን ምስክሮች ቃል መዝኖ ተጠሪ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳያደርጉ ቀርተው አደጋው መድረሱን የዐቃቤ ህግ የሠውና የሰነድ ማስረጃዎች ያረጋገጡትን ፍሬ ነገር ውድቅ ያደረገው መሰረታዊ ነጥቦች ላይ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል ልዩነት ማሳየቱን ፣የባለሙያ ምስክርነት ቃልም በተገቢው ማስረጃ የተስተባበለ መሆኑን በግልጽ ጠቅሶ ያለመሆኑን ከውሳኔው ግልባጭና ከዋናው መዝገብ ላይ ከሰፈረው የአቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል እንዲሁም ከሰነድ ማስረጃዎች ይዘት ለመረዳት ችለናል። የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች የተከሰሰው ሲያሽከረክሩት የነበረውን መኪና በከፍተኛ ፍጥነት እና የራሳቸውን የቀኝ መስመር በመልቀቅ ወደ ግራ መስመር በመግባት በጥንቃቄ ጉድለት ሟችን ገጭተዋል በሚል ምክንያት ሲሆን አመልካች ይህንኑ የድርጊት አፈፃፀም በተመለከተ በጊዜው እና በቦታው የነበሩትን የሰው ምስክሮች ስለአደጋው ሙያዊ አስተያየት መስጠት የሚችሉትን የትራፊክ ፖሊሶች የሰጡትን ሙያዊ መግለጫ ለማስረጃነት አቅርቦ ለፍርድ ቤቱ ከመስማቱ በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ የትራፊክ ፖሊሶች ችሎት ቀርበው ስለጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጡበትም አድርጓል ። በአቃቤ ህግ በኩል የተሰሙት ሁለት ምስክሮች ተጠሪ ሲያሽከረክሩት የነበሩውን መኪና ፍጥነት ከሙያ አንፃር ሊመሰክሩ ይችላሉ ተብሎ የማይወሰዱ ቢሆንም ሟች በወቅቱ የነበረበትን ሁኔታና የደረሰበትን ጉዳት ከመመስከራቸውም በላይ ድርጊቱ ሲፈጸም የተጠሪ መኪና በከፍተኛ ፍጥነት ሁኖ ወደ ሟች ግራ መስመር አጥብቦ በመግባት ሟችን እንደገጨውና የተጠሪ መኪና የቆመበትን አጠቃላይ ሁኔታ እንደግንዛቤአቸው መጠን የገለጹ ሲሆኑ በምስክሮች ቃል ተከስቷል የተባለው ልዩነት ሟቹ ሲያሽከረክር የነበረው ባጃጅ ተሽከርካሪ ወደ ዋናው መንገድ የፊት ጎማው የገባ መሆን ያለመሆኑ እና የተጠሪ መኪና ከግጭቱ በኃላ የቆመበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፤ ስለጉዳዩ ሙያዊ አስተያየት በሰነድ ማስረጃዎቹ ላይ ያሰፈሩት የትራፊክ ፖሊሲዎች የተጠሪ የመኪና ማሽከርከር ሁኔታ የትራፊክ ደንቡን ተከትሎ የተከናወነ ያለመሆኑን ሟች ለግጭቱ መከሰት ያደረገው አስተዋጽኦ ያልነበረ መሆኑን በሚያስገነዝብ መልኩ የመሰከሩ ሲሆን የእነዚህ ምስክሮች ቃል በስር ፍርድ ቤት ክብደት ሳይሰጠው የታለፊው የአደጋ ቦታ ፕላኑ ረቂቁ የአደጋ መነሻ ቦታ ላይ ምልክት ያለበት ሁኖ ዋናው ግን ይኼው ምልክት የለውም የሚለውንና ለመርማሪ ከሳሽ ሲላኩ የሰነዶቹን የገጽ ብዛት ፍርድ ቤት ከቀረበው ጋር የተለያዩ መሆናቸውን የሚገልፁ ምክንያቶች በማስፈር ነው። ይሁን እንጂ ዋናው  የአደጋ ቦታ ፕላን የትራፊክ አደጋ የሚነሳበትን ደንብ መሰረት አድርጎ ያልተነሳ መሆኑን በተጠሪ ማስተባበያ ክርክርና ማስረጃ ያልቀረበበት ከመሆኑም በላይ ተጠሪ በወቅቱ ያሽከረክሩት የነበረውን መኪና ከተገቢው ፍጥነት በላይ እና ከተገቢው መስመር በመውጣት ሲያሽከረክሩ የነበሩ መሆኑን ሰነዶቹ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገልፁት መሆኑን የሰነዶቹ ይዘት በግልፅ ያሳያሉ። በመሆኑም በዚህ ረገድ በተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክር የተጠሪ መኪና ፍጥነት የለውም ብለው የሰጡት ምስክርነት የባለሙያዎችን የምስክርነት ቃል ሊያስተባብል የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል። አንድ የትራፊክ ባለሙያ የሚሰጠው ሙያዊ አስተያየት የማስረጃነት ዋጋ የማይሰጠው አስተያየቱ ተገቢውን የሙያ ደንብ ተከትሎ ያልተሰጠና ያልቀረበ፣ በጊዜውና በቦታው ከነበሩት የአይን ምስክሮች ቃል ጋር ተነጻፅሮ ሲታይ በመሰረታዊ ነጥቦች ላይ ልዩነት ያለበት መሆኑ ሲረጋጥ እንጂ በጭፍጫፊ ነጥቦች ላይ ልዩነት ተከስቷል ተብሎ ሊሆን አይገባም።

በመሰረቱ ፍርድ ቤቱ የልዩ አዋቂዎችን የምስክርነት ቃል ጉዳዩን ለማብራራት ወይም ለክርክሩ ውሣኔ አሰጣጥ ተገቢ ነው ካለ ወይም ተከራካሪ ወገኖች ክርክራቸውን ለማስረዳት በሕጉ አግባብ

ከቆጠሩ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸውን ልዩ አዋቂዎች ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ ሊያደርግ እንደሚችል ስለማስረጃ አቀራረብና አቀባበል ከተደነገጉት ድንጋጌዎች መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ የልዩ አዋቂዎች ምስክሮች ቃላቸውን ገለልተኛ ሆነው መስጠት እንደአለባቸውና ቃላቸው ያለበቂ ምክንያት ልዩ አዋቂ ያልሆኑ ሰዎች በሚሰጡት የምስክርነት ቃል ውድቅ መሆን የሌለበት መሆኑን ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ሕግ ደንቦች የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የልዩ አዋቂዎች የምስክርነት ቃል በገለልተኛነት ሊሰጥ እንደሚገባ አዋቂ ያልሆኑ ሰዎች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ከልዩ አዋቂዎች የምስክርነት ቃል የተሻለ ክብደት ሊሰጠው የሚገባው ፍርድ ቤቱ በቂ የሆነ ምክንያት ሲያገኝ በመሆኑ የልዩ አዋቂዎች የምስክርነት ቃል እንደ ማንኛውም ማስረጃ በጥንቃቄ ሊመዘን የሚገባው እንጅ ሁል ጊዜ ክብደት ሊሰጠው የሚገባ የማስረጃ አይነት አይደለም፡፡ የትራፊክ ፖሊስ የአደጋ ፕላን ሪፖርትም የባለሙያ ሙያዊ አስተያየትን በወረቀት ላይ ስዕላዊ በሆነ መንገድ የሚያስቀምጥ በመሆኑ በባለሙያ የሚረጋገጥ ሰነድ በመሆኑ እንደ ማንኛውም የልዩ አዋቂ የምስክርነት ቃል በተገቢው መንገድ ሊመዘን የሚገባው የማስረጃ አይነት እንጅ ሁልጊዜ ድምዳሜ ማስረጃ (Conclusive Evidence) ያለመሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይም የትራፊክ ሰነዱ ይዘትና የትራፊክ ባለሙያዎች አስተያየት ተገቢውን የትራፊክ ደንብ ተከትሎ ያልተሰራ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ልዩ አዋቂ ባልሆኑት በተጠሪ መከላከያ ምስክር ቃል ተስተባብሏል ተብሎ በበታች ፍርድ ቤቶች መወሰኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡትን መሰረታዊ ነጥቦችን ያላገናዘበና የማስረጃ አቀባበልና ምዘና ስርዓትን ያልተከተለ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በአንድ ጉዳይ የቀረበን የሰነድ ማስረጃ ይዘት ሙሉ በሙሉ ሳይመዘን በመተው በጭፍጫፊ ነጥቦች ላይ ብቻ በማተኮር ማስረጃን ክብደት ሳይሰጡ ማለፍ ደግሞ የማስረጃ ምዘና መርህና የዳኝነት አካሄዱ የማይፈቅዱት በመሆኑም የመሰረታዊ ህግ ስህተት መመዘኛን የሚያሟላ ነው፡፡ አንድ ፍ/ቤት በህግ በኩል የቀረቡትን ማስረጃዎቹን ውድቅ ሊያደርግ የሚገባው በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠውን ነገር ሙሉ በሙሉ ይዞ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የማስረጃ ምዘና መርህ ይዞ ማስረጃውን በመመዘን እንጂ ከማስረጃዎቹ ውስጥ ጭፍጫፊውን ወይም የተወሰነውን ፍሬ ነገር ብቻ በመያዝ ሊሆን እንደማይገባው ተቀባይነት ያላቸው የማስረጃ ህግ ጽንሰ ሀሳቦች የሚያስገነዝቡን ሐቅ ነውና፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የዐቃቤ ህግ ማስረጃዎች ተጠሪ ጥፋት የፈጸመው መሆኑን አላረጋገጡም ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው ተጠሪ እንዲከላከሉ ትዕዛዝ ከሰጠ በኃላ ሁሉም የዐቃቤ ህግ ምስክሮች የሰጡትን የምስክርነት ቃል እና በሰነድ ማስረጃዎች የሰፈረውን ይዘት አንድ ባንድ ባለማየትና የልዩ አዋቂዎች ሙያዊ አስተያየትን ውድቅ ለማድረግ ለሚያስችል በቂና ህጋዊ ምክንያት ሳይኖር ነው፡፡በመሆኑ ተጠሪ የሹፍርና ሙያ የሚጠይቀውን ጥንቃቄ ባለማድረግ የወንጀል ድርጊቱን በቸልተኝነት ያደረጉ መሆኑ በዓቃቤ ህግ የአይን ምስክሮች እና በትራፊክ ፖሊሶች ሙያዊ አስተያየት ተረጋግጦባቸው እያለ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር በመተው ተጠሪውን የስር ፍ/ቤት በነጻ ማሰናበቱም ሆነ በክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች አለመታረም መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡
በወንጀል ህጉ አንቀጽ 57 በግልጽ እንደሰፈረው "ለድርጊቱ ኃላፊ ሊሆን የሚገባው ሰው አስቦ ወይም በቸልኝተኝነት አንድ ወንጀል ካላደረገ በቀር በወንጀል ጥፋተኛ አይሆንም በአንጻሩ አንድ ሰው "የፈጸመው ድርጊት በህግ የሚያስቀጣ ቢሆንም ምንም ጥፋት ሳያደርግ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ ነገር የተፈጸመ ወይም የደረሰ ሁኖ ሲገኝ በወንጀል ህግ ሊፈረድበት አይገባም በማለት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 57/2/ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ የህጉ አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው በአንድ ድርጊት ምክንያት አንድን ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ነው ለማለት ከሳሽ የሆነው ዐ/ህግ ድርጊቱ የተፈጸመው ሆነ ተብሎ

ወይም በችልተኝነት መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት መሆኑን ነው፡፡ድርጊቱ ሆነ ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈጸመ መሆኑን ማስረጃ የሚጠበቅበት መሆኑን ነው፡፡ ድርጊቱ ሆን ተብሎ ወይም በቸልተኝነት የተፈጸመ መሆኑ ማስረጃ ካልቀረበ ወይም ድርጊቱ ከአቅም በላይ ወይም በድንገተኛ አጋጣሚ የተፈጸመ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በተከሳሽ በኩል ከቀረበ የተከሰሰውን ሰው በወንጀል ህግ ጥፋተኛ ብሎ መፍረድ ከህጉ መንፈስ ውጪ ነው፡፡ በወንጀል የተከሰሰ ሰው ቸልተኛ ነበር? ወይስ አልነበረም? የሚለው ጥያቄ በወንጀል ህግ በአንቀጽ 59 የሰፈረውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ የሚወሰን ነው፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ አሁን ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው በመሆኑም የህጉን ይዘት እንዳለ ማስቀመጡ ጠቃሚ ነው፡፡ ይኸው፡-ማንም ሰው በቸልተኝነት የወንጀል ተግባር አድርጓል የሚባለው ፡-

/ሀ/ ድርጊቱ በወንጀል ህግ የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል

እያወቀ አይደርስም የሚል ግምት ወይም ባለማመዛን፣ ወይም (ለ) ድርጊቱ በወንጀል የሚያስቀጣ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል ማወቅ አለበት ወይም እንዳለበት ባለመገመት ወይም ባለማሰብ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ነው፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው በቸልተኝነት ወንጀል ፈፅሟል የሚባለው ውጤቱን እያወቀ ውጤቱ አይደርስም ከሚል መነሻ ድርጊቱን የፈፀመ እንደሆነ ወይም ደግሞ የወንጀል ውጤት የሚያስከትል መሆኑን ባያውቅም ውጤቱን ማወቅ ነበረበት ወይም ጥረት ቢያደርግ ውጤቱን ማወቅ ይችል ነበር ማለት ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም ቸልተኝነት አለ ለማለት ሕጉ የሚጠቀምበት ዋነኛ መስፈርት የተከሰሰው ሰው በድርጊቱና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ ያለው ወይም ሊኖረው የሚገባው ግንዛቤ ነው፡፡ ድርጊቱን የፈፀመው ሰው የነበረው ዕውቀትና ግንዛቤ ወይም ሊኖረው የሚገባው ዕውቀትና ግንዛቤ የሚመዘነው የሰውዬው እድሜ ያለው የኑሮ ልምድ የትምህርት ደረጃው፣ ሥራውና የማህበራዊ ኑሮ ደረጃው ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነም የሕጉ አንቀጽ 59(1) ይደነግጋል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስመለስም ተጠሪ በሙያቸው አሽከርካሪ ሆነው እያለና በአሽከርካነት ሙያቸው ደግሞ የሌላውን ሕይወትና ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ እያለባቸው የሰሌዳ ቁጥሩ 3-25709 ኦሮ የሆነውን ቶዩታ ሃይሉክስ መኪና ከዲስ አበባ ከተማ ወደ አርባ ምንጭ ከተማ እያሽከረከሩ ተገቢውን ጥንቃቂ ከማድረግ ጉድለት መኪናው ሟች ሲያሽከረክር የነበረውን ባጃጅ በመግጨት ሟች የሞተ በመሆኑ ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) ስር የማይጠየቁበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ከወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23፣24፣57፣59(ለ) እና 543(2) ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ አንፃር ሲታይ ለወንጀሉ ኃላፊ ሊባሉ የሚገባ ሆኖ ስለአገኘነው ተጠሪ ላይ የተሰጠውን የነፃ መለቀቅ ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁጥር 195(2(ሀ)) መሰረት በመሻር ተጠሪ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 543(2) ሰር የተመለተውን ድንጋጌ በታወቀ ቸልተኝነት የተላለፈ ጥፋተኛ ነው ብለናል፡፡

ይህ ከተባለ በኂላ አመልካች ባለመቅረቡ የቅጣት አስተያየት መቀበል አልተቻለም፡፡

<u>**ትዕዛዝ**</u>

አመልካች የሚቀርብ ከሆነ አስተያየቱን ለመቀበልና ተገቢውን ለመከተል ለ11/02/07 ዓ.ም ተቀጠረ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ 92141

ጥቅምት 14 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች**፡-አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- የደቡብ ክልል ዐ/ህግ

ተጠሪ፡- ዓለማየሁ አስፋው

መዝገቡ የተቀጠረው የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ነው፡፡ በዚህም መሰረት መዝገቡን መርምረን ተከታዩን የቅጣት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ቅ ጣ ት

1. አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሁኖ ከተገኘ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት ያለበት ሲሆን ቅጣቱ የሚወሰነው ደግሞ ስራ ላይ በዋለው በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ታይቶ፡፡ ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ የሚያስቀጣው ከአንድ አመት እስከ አምስት አመት ሊደርስ በሚችል ቀላል እስራት ሁኖ የገንዘብ መቀጮ ደግሞ ከብር 3000.00 (ሶስት ሺህ ብር) እስከ 6000.00 ( ስድስት ሺህ) ብር ነው፡፡

   እንደ ቅጣት መመሪያው መወሰን እንዲቻል ደግሞ በተጠሪ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔከግራ ቀኙ ቅጣት ማክበጃ እና ማቅለያ ምክንያቶች ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ በዚህ አግባብ ቅጣቱ ከመሰላቱ በፊት ግን ተጠሪ ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ክሱ ሲመሰረትም ሆነ በበታች ፍርድ ቤቶች ክርክሩ ሲካሄድ ደረጃ ያልወጣለት ቢሆንም በዚህ ችሎት ጉዳዩ በመታየት ላይ እያለና የጥፋተኛነት ውሳኔ በተሰጠበት ጊዜ በስራ ላይ ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 በመሆኑ በዚሁ መመሪያ መሰረት የወንጀል ህጉ አንቀጽ 543 ደረጃ ድንጋጌ ነው፡፡ ተጠሪ ድርጊቱን የፈጸሙት በታወቀ ቸልተኝነት ከመሆኑም በላይ የሟች አስተዋጽኦ ስለሌለና ተጠሪም በሙያቸው ሹፌር በመሆናቸው የወንጀሉ ደረጃ አራት ሆኖ የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን 16 ነው፡፡ በዚህ እርከን የፍርድ ቤቱ የተተወው ፍቃደ ስልጣን ከሶስት አመት እስከ ሶስት አመት ከሰባት ወር ነው፡፡ መነሻ ቅጣቱም በዚሁ ሬንጅ ውስጥ የሚያዝ ሲሆን ተጠሪ ላይ መጨረሻ ላይ የሚጣለው የቅጣት መጠን የሚታወቀው ግን የማክበጃ እና የማቅለያ ምክንያቶች ታይተው ስሌቱ ከተሰራ በኃላ ነው፡፡ በዚህም አግባብ የቅጣት መጠኑን ማስላት የግድ ሲሆን በተጠሪ ላይ በዓቃቤ ህግ በኩል የቀረበ የቅጣት ማክበጃው ምክንያት የለም፡፡

አቃቤ ህግ ጥፋተኝነት ውሳኔ ሲሰጥም ሆነ የቅጣት አስተያየቱን የማቅረብ እድሉን ለመጠበቅ ቀጠሮ ሲያዝለት አልቀረበምና፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ሪኮርድ ያልቀረበባቸው መሆኑን የክርክሩ ሂደት ማሳየቱ ይኼው ምክንያት በማቅለያነት እንዲያዝላቸው የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ማቅለያ ምክንያት ደግሞ በመመሪያው አንቀጽ 23(4) ድንጋጌ መሰረት በተጠሪ ላይ የሚጣለውን ቅጣት ከእርከን 16 ወደ እርከን 15 ዝቅ የሚደረገው ነው፡፡ በዚሁ መጨረሻ እርከን ስር የተመለከተው የቅጣት ዓይነትና የእስራት መጠን ሬንጅ ከሁለት አመት ከዘጠኝ ወር እስከ ሶስት አመት ከስምንት ወር በመሆኑ በዚሁ ለፍ/ቤቱ በተሰጠው ፈቃድ ስልጣን መሰረት የአሁኑ ተጠሪ ለፈጸመው ጥፋት በሁለት አመት ከዘጠኝ ወር ቀላል እስራት ሊቀጣ የሚገባ ሆኖ ስለገኘነው ተጠሪ በጉዳዩ ላይ የታሰረው ካለ ማናቸውም ጊዜ የሚታሰብለት ሁኖ በሁለት አመት ከዘጠኝ ወር ቀላል እስራት ሊቀጣ ይገባል ብለናል፡፡

1. የገንዘብ መቀጮን በተመለከተ ደግሞ ተጠሪ ሊቀጡ የሚገባው ብር በእርከን 4 ሁኖ ስለአገኘነው በብር 3500.00 (ሶስት ሺህ አምስት መቶ ብር) ነው ብለናል፡፡
2. በአመልካች የሰበር አቤቱታ ላይ የተጠሪ መኖሪያ አድራሻ አዲስ አበባ መሆኑ ስለተጠቀሰ የፌዴራል ፖሊስ ከደቡብ ክልል ፖሊስ ጋር በመሆን ተጠሪን አፈላልጎ በመያዝ ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት እንዲያስረክብ ፣የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤትም ተጠሪን ተረክቦ በዚህ ችሎት ውሳኔ መሰረት ቅጣቱን ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ብለናል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ. 93577

ህዳር 22 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ዘውዴ ተስፋይ ስመኝ ጉዳይ ተከታታይ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበር፡፡ተጠሪ በአመልካች እና በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ በነበረው ካሳየ ጌጡ ያቀረበው ክስ ከባድ የሰው ግድያ ወንጀል ነው፡፡ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ መነሻ የሆነው የአሁኑ ተጠሪ ጉዳዩ የተሰማው በሌለበት በመሆኑ ከመጥሪያ አደራረስ ጋር የተያያዘ ክርክር በማቅረቡ ነው፡፡

ዓቃቤ ህግ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተጠሪ እና 1ኛ ተከሳሽ በነበረው ካሳየ ጌጡ ያቀረበው ክስ የወ/ሕ/ቁ.32(1)(ሀ) እና 539(1)(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ ሰው ለመግደል አስበው በ19/10/1997 ዓ.ም. ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት ትግራይ ክልል አላማጣ ወረዳ ቀበሌ ማረዋ ሚች ሰመሀኝ አረቂ በክላሽ ኮፐ መሳሪያ አንድ ጥይት በመተኮስ ገድለዋል የሚል ነው፡፡

አመልካች ጉዳዩ ሊሰማ በተያዘው ቀጠሮ ባለመቅረቡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.161(1) በሚያዘው መሰረት በመኖሪያ አካባቢው በተለጠፈ መጥሪያ ጥሪ ቢደረግለትም ባለመቅረቡ በሌለበት ክርክሩን ቀጥሎ የዓቃቤ ህግ ምስክሮች ከተሰሙ በኃላ የሥር ፍርድ ቤት ዐቃቤ ህግ እንደ ክሱ አቀራረብ አስረድቷል በማለት አመልካች ጥፋተኛ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ቅጣት በተመለከተም በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የወሰነ መሆኑ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት ይቻላል፡፡

አመልካች በፖሊስ ክትትል በቁጥጥር ስር ከዋለ በኃላ በማረሚያ ቤት በኩል በ15/09/2004 ዓ.ም. ውሳኔ ለሰጠው ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው አቤቱታ እና በፍርድ ቤት ባደረገው ክርክር ፈጽመው በተባለው የግድያ ወንጀል ክስ የተመሰረተበት መሆኑ አለማወቁን፤ በሚኖርበት አካባቢ ባህል በግድያ የተጠረጠረ ሰው ራሱ እና ቤተሰቡ ከአካባቢው ለቀው እንደሚሄድ፤ አመልካችም አካባቢው ለቆ በኦሮሚያ ክልል ሲኖር እንደነበር፤ ቀርቦ ቢከራከር እና ቢከላከል ከእሱ ጋር ተከሶ እንደነበረው ግለሰብ በነፃ ይለቀቅ እንደነበር በመግለጽ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ተነስቶለት ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ መጠየቁን፤ ዐቃቤ ህግ በበኩሉ አመልካች ወደ ህግ መቅረብ ሲገባው ሆነ ብሎ ከአካባቢው በመሸሹ

በአካባቢውም ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ በሌለበት የተሰጠው ፍርድ እና ቅጣት ሊጸና እንደሚገባ ተከራክረዋል፡፡

የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር በመመርመር በሰጠው ብይን አመልካች የአካባቢው ባህል መሰረት በማድረግ ከአካባቢው ለቆመሄዱ ያቀረበው ምክንያት ተቀባይነት እንደሌለው፤ በአንፃሩ ጉዳዩ ወደ ፍትህ አካል ቀርቦ መጨረስ ይገባው እንደነበር፤ አመልካች ወደ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በአካባቢው የአስተዳደር ክፍል ቤተዘመዶቹ በሚገኙበት አካባቢ መጥሪያ ተለጥፎ መቅረብ አልቻለም፡፡ ፖሊስ በቁጥጥር ስር ካደረገኝ በኃላ ነው ፍርደኛ መሆኔን ያወኩት የሚለው ተቀባይነት የለውም፡፡ መጥሪያው በአካባቢው መለጠፉን ያውቀዋል ተብሎ ይገመታል፡፡ በወ.ሕ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 197 ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስነዋል፡፡

አመልካች ቅጣት በተመለከተ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ ተቀባይነት በማግኘቱ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት በማሻሻል በ20 ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

አመልካች በሌለበት የተሰማው ጉዳይ ሊሻር ይገባል በማለት ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162(ሀ) እንደተመለከተው የጋዜጣ ጥሪ አስፈላጊ መሆኑ አስገዳጅ ድንጋጌ ቢሆንም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ለ) እንደተደነገገው ፍ/ቤቱ ለተከሳሽ ሊደርሰው ይችላል ብሎ በገመተው አግባብ ጥሪውን ማስተላለፍ እንደሚችል ስለሚገልጽ በአመልካች መኖሪያ አድራሻ መለጠፉ ስለተረጋገጠ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በማጽናት ወስነዋል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ከፍተኛ እና ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጸመዋል ያላቸውን ስህተቶች በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘቱ፡- የተጠረጠረበት ወንጀል ከተፈጸመ በኃላ ከአካባቢው ርቆ መሄዱ፤ በአካባቢው ባህልም የተለመደ መሆኑ፤ የተከሰሰ መሆኑ አለማወቁን፤ በአካባቢውም መከሰሱን ሊነግረው የሚችል ቤተሰብ አለመኖሩን፤ ሕጉም ጥሪ በጋዜጣ እንደሚደረግ እያዘዘ በአካባቢው በተለጠፈው ጥሪ ብቻ መጥሪያ ደርሶታል መባሉ በአግባቡ አለመሆኑን፤ ቀርቦ ባለመከራከሩ የመከላከል መብቱ መታለፉ በመግለጽ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሻር አመልክቷል፡፡

ዐቃቤ ህግ የበኩሉን መልስ አቅርበዋል፡፡ ዐቃቤ ህግ የሰጠው መልስ ዋና ፍሬ ነገሩ፡- የስር ፍርድ ቤት ህጉ በደነገገው አግባብ በተሰጠው አማራጭ ጥሪ ማስተላለፉ፤ አመልካች በአካባቢው በተደረገለት ጥሪ አለመቅረቡን፤ በገጠር አካባቢ በጋዜጣ የሚወጣ ጥሪ እንደማይነበብ የተሻለ የሚሆነው በአካባቢው መጥሪያው መለጠፍ መሆኑ፤ የስር ፍርድ ቤትም ይህንን አማራጭ በመውሰድ ለአመልካች የተላለፈው ጥሪ በአግባቡ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ጉዳዩን ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ጉዳዩ እንደመረመርነው በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ያለው መሰረታዊ የክርክር ጭብጥ በወንጀል ጉዳይ የተከሰሰ ሰው በሌለበት ነገሩ እንዲሰማ ሲታዘዝ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓቱ ምን መምሰል አለበት? የሚል ነው፡፡ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት መፍትሔ የሚሻው ጭብጥ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች የተከሰሰበት የግድያ ወንጀል በሌለበት እንዲታይ ሲወስኑ መጥሪያው ተከሳሹ ይኖርበት ነበር በተባለው ቀበሌ እና አካባቢ ብቻ መለጠፍ በወ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162 የተመለከተው ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት በአግባቡ ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚል ነው፡፡

ከስር ፍርድ ቤት የክርክር ሂደት መገንዘብ እንደተቻለው አመልካች በከባድ የግድያ ወንጀል ክስ ቀርቦበት ጉዳዩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ባለመቅረቡ በሌለበት ክርክሩን ተካሂዶ ጥፋተኛ ተብሎ በዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች እንዲቀርብ የሰጠው ትዕዛዝ ተፈፃሚ ባለመሆኑ መደበኛ መኖሪያው ነው በተባለው እና በአካባቢው አስተዳደር መጥሪያ በመለጠፍ በሌለበት ጉዳዩን እንዲሰማ አዟል፡፡ አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቆ የሚከራከረው የተከሰሰ ስለመሆኑ አለመሰማቱ፤ በአካባቢው ባህል በወንጀል የተጠረጠረ ሰው ቀየውን ለቆ የሚሄድ መሆኑ እና የስር ፍርድ ቤትም ህጉ ያስቀመጠውን በጋዜጣ የመጥራት አስገዳጅ ድንጋጌ በአግባቡ አለመተርጎሙን ነው፡፡

በመርህ ደረጃ የወንጀል የክርክር ሂደት ተከሳሾች ባሉበት እንደሚደረግ በልዩ ሁኔታ ደግሞ የፈጸሙት ወንጀል ቀርበው መከራከር የማይፈለጉና ከፍትህ ስርዓቱ የሸሹ ግለሰቦች በፍትህ ስርዓቱ መጠየቅ ያለባቸው በመሆኑ በሌሉበት ነገሩ ሊሰማ እንደሚችል ከወ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 161(1) እና (2(ሀ) ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት ንባብ የምንረዳው ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም አንድን ጉዳይ ተከሳሽ በሌለበት ለማየት እንዲችል ተከሳሹ በቀጠሮ ቀን ያለ በቂ ምክንያት መቅረቱን ሲረጋገጥ ብቻ መሆኑ የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ያመለክታል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በሌለበት ነገሩ ለመስማት ትዕዛዝ ከሰጠ ጥሪው ተደራሽ በሆነ አግባብ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል፡፡ በወ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162 እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ የሚያስተላለፈው ጥሪ ተከሳሹ ስለተጠረጠበት ጉዳይ ዝርዝር መግለጫ የያዘ እና ጥሪውም በጋዜጣ እንዲወጣ መታዘዝ እንዳለበት ከድንጋጌው ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ በሌላ በኩል ፍ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘም የመጥሪያ ማስታወቂያው በሌላ መንገድ ማስተላለፍ እንደሚችል የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ያሳያል፡፡

በስር ፍርድ ቤት የክርክር ሂደት እንደተገለጸው የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ አለማድረጉን ነው፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን እንዳሰፈረው አመልካች የአካባቢውን ባህል መሰረት በማድረግ መሸሹን ተቀባይነት የለውም በመኖርያ ቤቱ አካባቢ እና በአካባቢ አስተዳደር የተለጠፈው መመጥሪያ ጉዳዩ በሌለበት እንደሚታይ የሰማ መሆኑ ግምት ይወስዳል በማለት ከድምዳሜ ላይ መድረሱን በውሳኔው አስፍራው አምልካች የተጠረጠረበት ወንጀል ተፈጸመ ከተባለበት በኃላ ከአካባቢው ለቆመሄዱን በየትኛውም መልኩ መከሰሱን አለማወቁን እየተከራከረ ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አምልካች የተከሰሱበት ጉዳይ በሌለበት ለመስማት ትዕዛዝ ሲሰጥ  በጋዜጣ የጥሪ ማስታወቂያ ለማስተላለፍ ያልቻለበት ሁኔታ ምን እንደነበር በውሳኔው ግልጽ አላደረገም ፡፡በወንጀል የተከሰሱ ሰዎች የቀረበባቸው ክስና ማስረጃ ቀርበው የመከላከል መብት ያላቸው መሆኑ በሕገ መንግስቱ እና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች የተረጋገጠ ስለመሆኑ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 20 (1)እና(4)እና የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አካል የሆነው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች አለማቀፍ ቃልኪዳን አንቀጽ 14(3)(ለ) እና (መ)መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በሕገ መንግሥቱ እና ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች የተረጋገጠው ፍትሐዊ የዳኝነት መብት በየትኛውም መልኩ ሳይሸራረፍ በፍርድ ቤቶች ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡ በእጃችን ወደ አለው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች ጉዳዩን በሌለበት የታየው የጥሪ ማስታወቂያ በመደበኛ መኖርያ ቤት እና የአካባቢ አስተዳደር በመለጠፍ ብቻ ነው፡፡ በወ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ162(1) እንደተመለከተው ተከሳሽ በሌለበት የሚደረገው ክርክር የመጥሪያ ማስታወቂያ በቅድሚያ በጋዜጣ መደረጉ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የተከሰሰበት ጉዳይ ቀርቦ እንዲከራከር በጋዜጣ ጥሪ ለማድረግ ያልቻለበት ምክንያት ግልፅ

አላደረገም ። የወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ 161(ሀ) መሠረታዊ ይዘት እና አላማ እንደተመለከተው አንድ ተከሳሽ በሌለበት ነገሩ ሲሰማ በፍ/ቤት ትዕዛዝ የሚሰጥ ከሆነ የመጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ያለበት መሆኑ በአስገዳጅነት የተደነገገበት አግባብ ሰፊ ስርጭትና ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ የሚደረግ ጥሪ፤ጥሪ የሚደረግለት ተከሳሽ ፍርድ ቤት ቀርቦ ጉዳዩን ለመከታተል የሚያስችለው እንዲሆን ነው፡፡

የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካች ፍርድ ተሽሮ ጉዳዩ ድጋሜ ይታይልኝ ጥያቄ ውድቅ ሲያደርጉ ያሰፈሩት ምክንያት የወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.162(ለ) ፍርድ ቤቱ መጥሪያው ለተከሳሹ ሊደርስ ይችላል ብሎ በገመተው አግባብ ማስተላለፍ እንደሚችል ፤በዚህ የሕግ ድንጋጌ ትርጉም መሠረትም ተከሳሽ እንዲቀርብ በአካባቢው አስተዳደር እና መኖሪያ ቤቱ መጥሪያ እንዲለጠፍ አማራጭ መውሰዱን በመግለጽ ነው፡፡ በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162(ሀ) እንደተመለከተው ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ከታዘዘ የመጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ እንዲወጣ ማዘዝ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በወ.መሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162(ለ) የተመለከተው አገላለጽ ለተከሳሹ የሚደርሰ መስሎ ከታየው መጥሪያው የሚደርስበት ሌላ መንገድ ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል "የሚለውን ፍሬ ነገር በንኡስ አንቀጽ "ሀ"ላይ ከተመለከተው የጥሪ አደራረስ ሥርዓት በተሻለ አግባብ እንዲሆን ከማድረግ ውጭ ከዚህ ያነሰ መብት ለመስጠት ታስቦ የተደነገገ ስለመሆኑ ከአጠቃላይ የድንጋጌ ይዘትና ዓላማ የምንረዳው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት በፍርድ ቤቱ እይታ የጥሪ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከሚደረግ ጥሪ ለተሻለ አግባብ የሚደርስ ስለመሆኑ እርግጠኛ ከሆነ ነው እንጂ ሰፊ ስርጪት እና ተደራሽነት ካለው የጋዜጣ ጥሪ የጠበበ አማራጭ እንዲጠቀም የወ/መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 162(ለ) የሚፈቅድ አይደለም ፡፡

በአመልካች መኖሪያ አካባቢ ወይም በአስተዳደር አካባቢ የሚደረገው ጥሪ በወሰን ቋሚ አድራሻ የሚደረግ እንጂ እንደ ጋዜጣ አገራዊ /አካባቢያዊ ስርጭት እና ተደራሽነት ያለው አለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ተከሳሽ በሌለበት ነገሩ የሚታይበት የሙግት ሥርዓት ሕጉ ለይቶ በደነገጋቸው ጉዳዮች ብቻ የሚደረግ ሆኖ የአጠቃላይ መርሁን ልዩ ሁኔታ ነው፡፡ ከፍትሕ ሥርዓቱ ሽሽተው የሚደበቁ ተከሳሾች በሌሉበት ሁኔታም ጉዳያቸው የሚታይበት ሥርዓት መዘርጋት የወንጀል ሕጉ ዓላማና ግብ ለማሳካት ተገቢ ቢሆንም ተከሳሽ በሌለበት የሚደረገው ክርክር የተከሳሽ የመከላከል ሕገ መንግሥታዊ መብት የሚያጣብብ እንዳይሆን የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት ሕጉ የዘረጋውን ድንጋጌ በጥብቅ በመተግበር ነው፡፡ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 20(4) እና የሲብልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 14(3) (ለ) እና(መ) የተደነገጉት ቀርቦ የመከራከር እና የመከላከል መብት ማስከበር ፍትሐዊ የወንጀል ፍትህ ሂደት እንዲኖር የሚደረግ ነው፡፡

አመልካች ከሚኖርበት አካባቢ ከቤተሰብ ጋር ቀየውን ለቆ ስለመሄድ በሥር ፍርድ ቤት ከቀረበው ክርክር መረዳት ይቻላል፡፡ በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋለውም በኦሮሚያ ክልል መሆኑ እየተከራከረ ነው፡፡ አመልካች ራሱን ቤተሰቡን ከአካባቢው ለቆ መሄዱ በሚከራከሩበት በሚኖርበት ቀበሌ/አስተዳደር መጥሪያ መለጠፍ ለአመልካች በተሻለ አግባብ ጥሪ ተደርጎለታል ለማለት አይችልም፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የወንጀል ጉዳይ የሙግት ሥርዓት ፍትሐዊ የክርክር ሂደት ያከበረ መሆን ይገባል፡፡ ፍትሐዊ የወንጀል ሙግት ሥርዓት ደግሞ በወንጀል ለተጠረጠረው ግለሰብ ቀርቦ ጉዳዩ እንዲከላከል በአግባቡ ጥሪ ሊደረግለት ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች በአመልካች መደበኛ መኖሪያ ቤት እና ቀበሌ አስተዳደር ጥሪ መደረጉ በቂ ነው በማለት አቤቱታው ውድቅ ማድረጋቸው በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 162 የተመለከተውን አገላለፅ መሠረታዊ ይዘትና ዓላማ ያላገናዘበ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች እንዲቀርቡ ጥሪ የተደረገበት ሥርዓት ሕጉ ያስቀመጠው ጥብቅ መስፈርት ያልተከተለ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት

የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች የተከሰሰበት የወንጀል ጉዳይ ቀርቦ እንዲከራከሩ ሕጉ በዘረጋው ሥርዓት አግባብ የመጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ ሳያወጡ ተከሳሹ በሌለበት የክርክር ሂደቱን አጠናቅቀው አመልካች ጥፋተኛ ነው በማለት በ20 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ/መ/ቁ. 03870 በ24/09/2004 የሰጠው ብይን፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 58544 በ03/12/2005 ዓ.ም የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ሕጉ በዘረጋው የመጥሪያ አደራረስ ሥርዓት መጥሪያ ማስታወቂያ በጋዜጣ ሳይሰማ ክርክር ተካሄዶ መወሰኑ በአግባቡ አይደለም ብለናል፡፡
3. በአመልካች የቀረበው የወንጀል ክስ ግራ ቀኙ በተገኙበት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 202(1) በሚያዘው መሠረት በአካባቢው ባለው ሌላ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማለትም የደቡብዊ ምስራቅ ከፍተኛ ፍርድ ቤት/በተመሳሳይ ደረጃ ባለው ከፍተኛ ፍርድ ቤት/ ዐቃቤ ህግ ክሱን በማቅረብ ክርክሩን እንዲቀጥል አዘናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የስር ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ብይኖች የተሻሩ ስለመሆናቸው ለሁለቱም ፍ/ቤቶች ይድረሳቸው ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
5. ለአመልካችም የፍ/ቤቱ ውሳኔ ግልባጭ በትግራይ ክልል ማይጨው ማረሚያ ቤት በኩል ይድረሰው፡፡ ይፃፍ፡፡
6. ለተጠሪም የፍ/ቤቱ ውሳኔ በትግራይ ክልል ፍትህ ቢሮ በኩል ይድረሰው ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

ጉዳዩ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

እ/እ

የሰ/መ/ቁጥር 96310

ህዳር 26 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-አቶ ጉዲና ለማ ገዛኸኝ - አባት ነኝ በማለት አቶ ለማ ገዛኸኝ

ከጠበቃ ልዑል አያለው ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት የስ/ፀ/ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም የመውሰድና የመሰወር ከባድ የሙስና የወንጀል ክስ የተመለከተው በቤንች ማጂ ዞን የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠባቸው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች በትዕዛዝ የጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች እና በሌሎች አምስት ሰዎች ላይ ያቀረበው አንደኛ ክስ ይዘት ባጭሩ፡-ተከሳሾቹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) (ለ)፣33 እና413(2) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ በሚዛን አማን ሆስፒታል ውስጥ 1ኛ ተከሳሽ የዋናው መድኃኒት ቤት ጠባቂ፤2ኛ ተከሳሽ የመድኃኒት ማሰራጫ ክፍል ባለሙያ እንዲሁም 3ኛ ተከሳሽ የግዢና የፋይናንስ የስራ ሂደት ባለቤት ሆነው በመስራት ላይ በነበሩበት ጊዜ በወንጀሉ ስራና በሚሰጠው ውጤት በመስማማት 1ኛ ተከሳሽ ይሰራበት ወደነበረው የመድኃኒት መጋዘን በ13/03/2005 ዓ.ም. ገቢ የተደረጉትን ሁለት ዓይነት መድኃኒቶች 2ኛ ተከሳሽ ይሰራበት ወደነበረው የመድኃኒት ማሰራጫ እንዲገቡ ካደረጉ በኃላ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች እነዚህኑ መድኃኒቶች በ17/04/2005 ዓ.ም ከምሽቱ በግምት 1:00 ሰዓት ላይከአማን ከተማ በሆስፒታሉ ተሽከርካሪ ጭነው በማውጣት እና ወደ ሚዛን ከተማ በማጓጓዝ ወደ ባጃጅ አዛውረው በማጓጓዝ ከ4ኛ እስከ 6ኛ ለተጠቀሱት ተከሳሾች በብር 23,200 ከሸጡ በኃላ መድኃኒቱ ከ5ኛ ተከሳሽ እጅ፤የሽያጩ ገንዘብ ደግሞ ከ2ኛ ተከሳሽ እጅ የተያዘ በመሆኑ በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም የመውሰድ እና የመሰወር ከባድ የሙስና ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን ሁለተኛ ክስ የቀረበው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(1) (ሀ) (ለ)እና 420(1)ተጠቅሶ መድኃኒቶቹ ወጥተዋል በተባለበት ጊዜ በስራ ላይ በነበሩት የሆስፒታሉ የጥበቃ ሰራተኞች ላይ ነው፡፡አመልካች ተጠይቀው ወንጀሉን አላደረግሁም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ የሌሎቹንም ተከሳሾች የእምነት ክደት ቃል ጠይቆ ከመዘገበ በኃላ በተጠሪ በኩል የቀረቡ በአንደኛ ክስ አስራ ሁለት፤በሁለተኛ ክስ ደግሞ አንድ በሁለቱም ክሶች በድምሩ የአስራ ሶስት ምስክሮችን ምስክርነት ከሰማ እና የተጠሪን

የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በሁሉም ተከሳሾች ላይ የኮሚሽኑ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጸ መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ አመልካች ከዋናው የመድኃኒት ስቶር የመድኃኒቶችን የአወጣጥ ስርዓት ያስረዱልኛል ያሏቸውን ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡

ከዚህ በኃላ ፍርድ ቤቱ የቀሪዎቹንም ተከሳሾች የመከላከያ ማስረጃ ከሰማ በኃላ በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ አመልካቹ ባሰሟቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰረተባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበል አልቻሉም በማለት ከ1ኛ እስከ 3ኛ በተጠቀሱት ተከሳሾች ላይ በክሱ በተጠቀሰባቸው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ በማስተላለፍ ግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየታቸውን በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡በመቀጠልም በክሱ የተመለከተው ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጃ ያልወጣለት መሆኑን ገልጸ ከ1ኛ እስከ 3ኛ የተጠቀሱት ተከሳሾች የተሰጣቸውን መንግስታዊ አደራ ወደ ጎን በመተው ወንጀሉን የፈጸሙት ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ወደ ሆስፒታሉ በገባው መድኃኒት ላይ መሆኑን በምክንያትነት ጠቅሶ ወንጀሉን በክብደቱ እና በአፈጻጸሙ በከባድ ደረጃ በመመደብ ቅጣቱ በአባሪ አንድ በእርከን 29 ስር የሚወድቅ መሆኑን፣ተጠሪ በጠየቀው እና በወንጀል ሕግ አንቀጽ 84(1)(ሀ)(ለ)እና(መ) ስር በተመለከተው መሰረት በሶስት የማክበጃ ምክንያቶች እርከኑ ከ29 ወደ 32 ከፍ የሚል መሆኑን እና የአመልካች የቀድሞ ጠባይ መልካምነት በአንድ የማቅለያ ምክንያትነት ሲያዝ ቅጣቱ ከእርከን 32 ወደ 30 ዝቅ የሚል መሆኑን ገልጸ ቅጣቱን በመመሪያው መሰረት በማስላት በአባሪ አንድ በእርከን 30 ስር አመልካች በአስራ አንድ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች የቀረበላቸውን እንደቅደም ተከተሉ ይግባኝ እና አቤቱታ ዘግተው በማሰናበታቸው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የስር 2ኛ ተከሳሽ የሰጠውን የተከሳሽነት ቃል መሰረት በማድረግ አመልካቹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 413(2) ስር ጥፋተኛ የመባሉን እና የተጠቀሰበትን አንቀፅ አግባብነት ተጠሪው ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ተጠይቀው ወንጀሉን አላደረግሁም በማለታቸው ተጠሪው አቅርቦ ካሰማቸው አስራ ሶስት ምስክሮች መካከል፡-

- 1ኛ ምስክር የሆስፒታሉ ሾፌር መሆኑን፣በዕለቱ ምስክሩ ይዞት የነበረውን ሌላ ተሽከርካሪ አቁሞ አምቡላንሱን እንዲይዝ 3ኛ ተከሳሽ ወደ አመሻሽ አካባቢ እንደነገረው፣በኃላም ጊዜው ያለፈበት ስለሆነ ችግር የለበትም በማለት 3ኛ ተከሳሽ ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር ሆነው 2ኛ ተከሳሽ ከሚሰራበት የመድኃኒት ማሰራጫ መጋዘን ውስጥ በሶስት ካርቶን ያሉ መድኃኒቶችን በአምቡላንሱ ውስጥ እንደጫኑ፣2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ጥበቃዎቹ እንዳይጠረጥሩን በማለት በእግራቸው ወጥተው ውጪ እንደጠበቁት እና ከግቢው ውጪ እንደተሳፈሩ፣በመንገድ ላይ ሲደርሱ 2ኛ ተከሳሽ ከአምቡላንሱ ወርዶ በባጃጅ እንደተሳፈረ፣3ኛ ተከሳሽ ግን አብሮት መሄድ እንደቀጠለ፣ የተወሰነ ቦታ ሲደርሱ 3ኛ ተከሳሽ በጠየቀው መሰረት አምቡላንሱን

እንዳቆመው፣2ኛ ተከሳሽም በባጃጅ እንደደረሰባቸው፣ቀጥሎም መድኃኒቱን ሁለቱ ተከሳሾች ወደ ባጃጁ እንዳዛወሩት፣ምስክሩ በዚሁ እንደተለያቸው፣በሚዛን ከተማ ውስጥ ሲዘዋወር አደባባይ አካባቢ በዚያኑ ምሽት በፖሊሶች ተይዞ ስለጫናቸው መድኃኒቶች ሲጠየቅ ዝርዝሩን እንደነገራቸው በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤

- 7ኛ ምስክር የሆስፒታሉ የጥበቃ ሰራተኛ ሆኖ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ከስራ ሰዓት ውጪ ምሽት አካባቢ በግቢው ውስጥ 2ኛ ተከሳሽ ከሚሰራበት መድኃኒት ማሰራጫ አካባቢ መቆየታቸውን፣በወቅቱም 1ኛ ምስክር የሆስፒታሉን አምቡላንስ ይዞ እዚያው አካባቢ የነበረ መሆኑን እና በእለቱ 1ኛ ተከሳሽን በአካባቢው እንዳላየው በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤
- 2ኛ ምስክር በመንገድ ላይ 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በአምቡላንስ ውስጥ የነበረውን መድኃኒት 2ኛ ተከሳሽ ተሳፍሮ ወደመጣበት ባጃጅ ሲያዛውሩ አይቶ ለፖሊሶች ጥቆማ እንደሰጠ በመግለጽ ምስክርነት መስጠቱን፤
- 11ኛ እና 13ኛ ምስክሮችም 2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች በአምቡላንስ ውስጥ የነበረውን መድኃኒት ወደ ባጃጅ ሲያዛውሩ ማየታቸውን በመግለጽ ምስክርነት መስጠታቸውን፤
- 3ኛ፣4ኛ፣እና 12ኛ ምስክሮች ከ2ኛ ምስክር በተሰጠው ጥቆማ መሰረት ተገቢውን ክትትል አድርገው መድኃኒቶቹን ከ5ኛ ተከሳሽ እጅ፤የሽያጭ ገንዘቡን ደግሞ በነጋታው ከ2ኛ ተከሳሽ ቤት መያዛቸውን በመግለጽ ምስክርነት መስጠታቸውን፤
- 8ኛ ምስክር ቃላቸውን የሰጡት በ2ኛ ክስ በተከሰሱት የጥበቃ ሰራተኞች ላይ መሆኑን፤
- 1ኛ ተከሳሽ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከወንጀሉ ጋር ግንኙነት የነበረው ስለመሆኑ ወይም በዕለቱ የወንጀሉ አፈጻጸም ተጀምሮ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከ2ኛ እና ከ3ኛ ተከሳሾች ጋር ታይቶ የነበረ ስለመሆኑ ከላይ ከተዘረዘሩት ምስክሮች መካከል አንዳቸውም የጠቀሱት ነገር አለመኖሩን፤

የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት ሲሆን የስር ፍርድ ቤቶችም ከላይ በተጠቀሱት ምስክሮች በ1ኛ ተከሳሽ ላይ የተሰጠ ምስክርነት ስለመኖሩ በውሳኔአቸው ላይ አልገለጹም፡፡

ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር ግንኙነት ያለው ምስክርነት የሰጡት 5ኛ፣6ኛ፣9ኛ እና 10ኛ ምስክሮች ናቸው፡፡5ኛ እና 6ኛ ምስክሮች በሆስፒታሉ ውስጥ በቀን ሠራተኝነት የሚያገለግሉ ሲሆኑ እነዚህ ምስክሮች ወንጀሉ በተፈጸመበት ዕለት 1ኛ ተከሳሽ 5ኛ ምስክርን ጠርቶ መድኃኒቶቹን 2ኛ ተከሳሽ ወደሚሰራበት ማሰራጫ እንዲወስድ በነገረው መሰረት ሁለቱ ምስክሮች 1ኛ ተከሳሽ ወደሚሰራበት ዋና መጋዘን ሄደው በካርቶን የተደረጉ መድኃኒቶችን 2ኛ ተከሳሽ ወደሚሰራበት ማሰራጫ መውሰዳቸውን እና ይህ ስራ ሁል ጊዜም የሚያከናውኑት የተለመደ ስራ መሆኑን በመግለጽ የመሰከሩ ናቸው፡፡9ኛ ምስክር በሙያው ፋርማሲስት ሆኖ ቀድሞ የሆስፒታሉ ሰራተኛ የነበረ እና 10ኛ ተከሳሽ ደግሞ የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ሲሆን የሰጡት ምስክርነት ይዘትም በዕለቱ 1ኛ ተከሳሽ ከሚሰራበት መጋዘን ወጪ ተደርገው 2ኛ ተከሳሽ ወደሚሰራበት ማሰራጫ ከተወሰዱት መድኃኒቶች መካከል አንደኛው ዓይነት መድኃኒት ወጪ የተደረገው ማሰራጫ መቀመጥ ከሚገባው መጠን በላይ መሆኑን እና መድኃኒቶቹ ወጪ የተደረጉበት ሰነድም ስርዝ ድልዝ የሚታይበት መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡በተጠሪ በኩል የቀረበው አጠቃላይ የሰው ማስረጃ ከላይ የተመለከተው ሲሆን በማስረጃነት ከቀረቡት ሰነዶች መካከል 1ኛ ተከሳሽን የሚመለከተው መድኃኒቶቹ የተጠየቁበት እና ወጪ የተደረገበትሰነድ መሆኑንም ከመዝገቡ ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል፡፡በመሰረቱ 1ኛ ተከሳሽ የዋናው መድኃኒት ቤት መጋዘን ኃላፊ ሲሆኑ የስራ ድርሻቸውም በሆስፒታሉ የበላይ አመራር ተፈቅዶ፣ተፈርሞ እና ተረጋግጦ በሚደርሳቸው ሰነድ መሰረት መድኃኒቶችን ማስረከብ ከመሆኑ በቀር መድኃኒት ወጪ እንዲሆን የመፍቀድ

ወይም መጠኑን የመወሰን የስራ ድርሻ ያላቸው ስለመሆኑ፣ወንጀል ተፈጽሞባቸዋል የተባሉት መድኃኒቶች ከ1ኛ ተከሳሽ መጋዘን ወጪ የተደረጉት ይህንን የተለመደ አሰራር በሚጥስ ሁኔታ በሆስፒታሉ የበላይ አመራር በጽሁፍ የተሰጠ ትዕዛዝ ሳይኖር ስለመሆኑ እንዲሁም ወንጀል ተፈጽሞባቸዋል የተባሉት መድኃኒቶች 1ኛ ተከሳሽ ከተረከቧቸው መድኃኒቶች መካከል በጉድለት የተገኙ ስለመሆኑ በተጠሪ በኩል የቀረበ ክርክርና ማስረጃ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡

ይልቁንም ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ ክሱን እንዲከላከሉ ብይን የሰጠውም ሆነ ተከሳሹ የቀረበባቸውን ማስረጃ አላስተባበሉም በማለት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ያስተላለፈባቸው ወንጀሉን ስለማድረጋቸው በምስክሮች ወይም በሰነድ ማስረጃ ተመስክሮባቸዋል በሚል ሳይሆን 2ኛ ተከሳሽ ወንጀሉን ያደረገ ስለመሆኑ እና ያደረገውም በ1ኛ ተከሳሽ ጠንሳሽነት ወይም አነሳሽነት ስለመሆኑ በመግለጽ በምርመራ ጊዜ እንዲሁም ክሱ በተሰማበት ጊዜ የሰጠውን የእምነት ቃል ዋነኛ ማስረጃ አድርጎ በመቀበል ስለመሆኑ በውሳኔው ላይ በግልጽ ያሰፈረው ሲሆን በበኩላችን አንድ ተከሳሽ የሰጠው የእምነት ቃል በሌላኛው ተከሳሽ ላይ በማስረጃነት ሊወሰድ የሚችልበት የሕግ አግባብ መኖር አለመኖሩ እና በዚህ ዓይነቱ ማስረጃ ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት አስረድቷል ለማለት የሚቻል መሆን አለመሆኑ በአግባቡ መጤን የሚገባው ሆኑ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው ወንጀል አደረገ የሚባለው ሕገወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገን ድርጊት ፈጽሞ በተገኘ ጊዜ መሆኑ እና አንድ ወንጀል ተደረገ የሚባለውም ወንጀሉን የሚቋቁሙት ሕጋዊ፣ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮች በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ መሆኑ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23(1) እና (2) ስር ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ማንም ሰው በዋና ወንጀል አድራጊነት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በቀጥታ ወይም በእጅ አዙር ወንጀሉን ያደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን እርሱ በቀጥታ ባያደርገውም እንኳን በመላ አሳቡና አድራጎቱ በወንጀሉ ድርጊትና በሚሰጠው ውጤት ሙሉ ተካፋይ በመሆን ድርጊቱን የራሱ ያደረገ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑም በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 32(1) ስር ተደንግጓል፡፡ በወንጀል ጉዳይ የሚቀርብ የክስ ማመልከቻ ተከሳሹ የተከሰሰበትን ወንጀል እንዲሁም የወንጀሉ መሰረታዊ ነገርና ሁኔታዎች የተገለጹበት ሊሆን እንደሚገባ እና ስለ ወንጀሉና ስለሁኔታው የሚሰጠው ዝርዝር መግለጫ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 111 እና 112 ድንጋጌዎች ላይ የተደነገገውም ከሳሹን ወገን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 23(2) ስር የተመለከቱት የወንጀል ማቋቋሚያ ፍሬ ነገሮች ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለው መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡በሌላ አነጋገር ከሳሽ ወገን በክሱ መሰረት የማስረዳት ግዴታ ተወጥቷል ሊባል የሚችለው ቀደም ሲል በተጠቀሱት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 111 እና 112 ድንጋጌዎች መሰረት አዘጋጅቶ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ መሰረት ተከሳሹ ወንጀል መፈጸሙን ማስረዳት በቻለ ጊዜ ነው፡፡ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ተከሳሹ መከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ክሱን እንዲከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው ከሳሽ ወገን ያቀረበው ማስረጃ ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያደርገው መሆኑን ሲያረጋግጥ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 141 ስር በግልጽ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

እንደሚታወቀው አንድ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በምርመራ ሂደትም ሆነ ክስ ከቀረበበት በኃላ ክሱን ለሚሰማው ፍርድ ቤት የሚሰጠው የእምነት ቃል በሕግ ተቀባይነት ካላቸው የማስረጃ

ዓይነቶች ውስጥ የሚካተት መሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 27፣35 እና 134 ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የዚህ ዓይነቱን የእምነት ቃል የሚሰጠው የራሱን አጥፊነት አምኖ በመቀበል እንደሆነ የሚገመት በመሆኑ ሌሎች ተጠርጣሪዎች፣ተከሳሾች ወይም ማናቸውም ሌላ ሰው በወንጀሉ አደራረግ ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ በእምነት ቃሉ ውስጥ የሚገልጻቸው ፍሬ ነገሮች ምናልባት ለቀጣይ ምርመራ ፍንጭ ሊሰጡ ይችሉ ይሆናል ከሚባል በቀር በማናቸውም ሰው ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትሉ የሚችሉ ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፡፡በሌላ አነጋገር አንድ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ በምርመራ ሂደትም ሆነ ክሱን ለሚሰማው ፍርድ ቤት የሚሰጠው የእምነት ቃል ውጤት በራሱ በቃል ሰጪው ላይ ተወስኖ የሚቀር ከመሆኑ ውጪ ወደሌሎች ተጠርጣሪዎች ወይም ተከሳሾች ሊተላለፍ የሚችል አለመሆኑን ከላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች አነጋገር እና ይዘት መገንዘብ የሚቻል ከመሆኑም በላይ ወንጀሉን የፈጸሙት በጋራ ወይም በመተባበር መሆኑን በማመን አንደኛው ተከሳሽ የሚሰጠው የእምነት ቃል ወንጀሉን አልፈጸምኩም በማለት ክዶ በሚከራከረው ሌላኛው ተከሳሽ ላይ ሕጋዊ ውጤት ሊያስከትል የማይችል ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 94450 በ25/07/2006 ዓ.ም. የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በተያዘው ጉዳይ ላይ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል የክልሉ የስነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ በአመልካቹ ላይ ባቀረበው በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም የመውሰድና የመሰወር ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መሰረት ለማስረዳት በሕግ የተጣለበትን ግዴታ ባልወጣበት ሁኔታ ክሱን የተመለከተው በቤንች ማጂ ዞን የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 2ኛ ተከሳሽ ወንጀሉን ያደረገው በ1ኛ ተከሳሽ አነሳሽነት መሆኑን ገልጾ የሰጠውን የእምነት ቃል በሕግ ከተደነገገው ውጪ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ጭምር በማስረጃነት በመያዝ 1ኛ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ የሰጠው ትዕዛዝም ሆነ በመጨረሻ የሰጠውና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች በትዕዛዝ የፀናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በቤንጅ ማጂ ዞን የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 11935 በ21/09/2005 ዓ.ም. ከሰጠው እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 00918 በ28/10/2005 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 01110 በ22/02/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ ከጸናው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ውስጥ የስር 1ኛ ተከሳሽ (የአሁኑ አመልካች) አቶ ጉዲና ለማ ገዛኸኝን የሚመለከተው የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ክፍል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195(2)(ለ)(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ባቀረበው የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ አመልካች ወንጀሉን ማድረጋቸውን ያላስረዳ እና በሕግ የተጣለበትን የማስረዳት ግዴታ ያልተወጣ በመሆኑ አመልካች አቶ ጉዲና ለማ ገዛኸኝ ከተከሰሱበት በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም የመውሰድና የመሰወር ከባድ የሙስና የወንጀል ክስ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

3. በአመልካች ላይ ተጥሎ የነበረው የአስራ አንድ ዓመት ጽኑ እስራት ቅጣት የተሻረ በመሆኑ የሚፈለጉበት ሌላ ጉዳይ አለመኖሩን አረጋግጦ አመልካች አቶ ጉዲና ለማ ገዛኸኝን ወዲያውኑ ከእስር እንዲለቃቸው አመልካቹ ለሚገኙበት በኦሮሚያ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ለኢሉባቦር ዞን ማረሚያ ቤቶች ጽ/ቤት ትዕዛዝ ይተላለፍ፡፡ይፃፍ፡፡
4. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ በቤንጅ ማጂ ዞን ለቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍርድቤት፣ለደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ለኢሉባቦር ዞን ማረሚያ ቤቶች ጽ/ቤት ይላክ፡፡ለአመልካቹም በማረሚያ ቤት በኩል ይድረስ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**የ/ባ**

የሰ/መ/ቁ.96378

ህዳር 25 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ሀቢብ ጀማል

ተጠሪ፡- የደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ዐ/ሕግ -

አቤቱታ አቅራቢዎች፡- 1.ረዳት ሳጅን መሐመድ እንድሪስ
2. አብዱ ኡመር
3. ደግፌ አለሙ

ጉዳዩን ተከታታዮች ተስፋዬ አለሙ እና ወሰላ ከድር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የወንጀል ክርክርን የሚመለከት ሲሆን መዝገቡ የተከፈተው በሀቢብ ጀማል አመልካችነት ሁኖ ከተጠሪ ጋር ክርክሩ ተካሂዶ ይህ ችሎት ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በዚህ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በስር ፍርድ ቤት ከሀቢብ ጀማል ጋር ተከሳሽ የነበሩትን የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎችንም የሚጠቅም በመሆኑ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 196 ድንጋጌ መሰረት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል በማለት ህዳር 02 ቀን 2007 ዓ/ም ማመልከቻ ስለአቀረቡ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ይህንኑ የአቤቱታ አቅራቢዎችን ጥያቄ ለማስተናገድ ይቻለው ዘንድ ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደረገ ሲሆን ተጠሪ ህዳር 19 ቀን 2007 ዓ/ም ባቀረበው አስተያየት አቤቱታ አቅራቢዎቹ ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተጠቃሚ መሆን ያለባቸው መሆኑን የወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 196 ከአስቀመጠው ድንጋጌ የሚገነዘበው መሆኑን ዘርዝሮ አቤቱታ አቅራቢዎች አቶ ሀቢብ ጀማል ጥፋተኛ በተባሉበት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 422(1) ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ ተብለው በስር ፍርድ ቤት የቀረቡባቸው የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መሰረት ተደርገው ቅጣት ሊወሰንባቸው እንደሚገባ ገልፆ አስተያየቱን ሰጥቷል፡፡

እኛም ጉዳዩን ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

የጉዳዩ መነሻ በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክልላዊ መንግስት የስልጤ ዞን ዐ/ሕግ ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት የጥፋተኝነት እና ተገቢውን የቅጣት ውሳኔ በሰጣቸው አቶ ሃቢብ ጀማልና በአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ላይ አራቱም ተከሳሾች በወ/ህ/ቁ 32/1//ሀ/፣ 37፣ 27/1/ እና 671/1/ሀ/ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ የማይገባቸውን ብልፅግና ለማግኘትና ለሌላውም ለማስገኘት በማሰብ በስልጤ ወረዳ ውስጥ አሻኖ ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ከወራቤ ወደ ቡታጅራ በሚወስደው አስፋልት መንገድ ላይ ሚያዚያ 08 ቀን 2005 ዓ/ም ከምሽቱ 5:00 ሰአት እስከ 7:30 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ የውንብድና ወንጀል ተግባር ለመፈፀም አስቀድመው በማሰብ በቡድን /ህብረት/ ሁነውና ተደራጅተው የጦር መሳሪያና ለዚሁ ተግባር የሚያግዛቸውን ተሽከርካሪ ጭምር በማዘጋጀት  በመንገዱ ላይ ከአዲስ አበባ ወደ ወራቤ ምርጥ ዘር እና ሰዎችን ጭኖ ይጓዝ የነበረውንና በአቶ አብዱረዛቅ ዑመር አማካኝነት የሚሽከረከረውን ኤፍ.ኤስ.አር መኪና በማስቆም ከባድ የሆነ የውንብድና ወንጀል ለመፈፀም ሞክረዋል የሚል ሁኖ እያንዳንዱ ግብረ አበር በወቅቱ ፈፀመ የተባለውን ድርጊትም ክሱ ይዘረዝራል፡፡

የአሁን አቤቱታ አቅራቢዎች በተከሳሽነታቸው ቀርበው ድርጊቱን አልፈፀምነም፤ ጥፋተኛም አይደለንም በማለት ክደው ተከራክረዋል፡፡ በአቃቤ ሕግ በኩል በማስረጃነት የሰው ማስረጃና የሰነድ ማስረጃዎች ቀርበዋል፡፡ ከዚህም በኂላ ሁሉም ተከሳሾች እንዲከላከሉ ተደርጎ የመከላከያ ማስረጃዎቻቸውን አሰምተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ተካሳሾቹ የወንጀል ድርጊቱን ስለመፈጸማቸው በአቃቤ ሕግ ተነግሮባቸው በመከላከያ ማስረጃዎቻቸው አላስተባበሉም በሚል ምክንያት በአቃቤ ሕግ በተጠቀሰው ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎአል፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም የግራ ቀኙን አስተያየት ተቀብሎ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር አገናዝቦ መመርመሩን በማጣቀስ አቶ ሀቢብ ጀማልንና የአሁኑ አቤቱታአቅራቢ ከሆኑት 1ኛውን (የሥር 1ኛ ተከሳሽ) እና 2ኛውን (የሥር 2ኛ ተከሳሽን) እያንዳንዳቸውን በሰባት ዓመት፣ የስር 3ኛ ተከሳሽን (የአሁኑን ሶስተኛ አቤቱታ አቅራቢን) ደግሞ በስድስት አመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አቶ ሀቢብ ጀማል ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት፣ የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ግን በዚህ አግባብ የይግባኝና የሠበር አቤቱታቸውን ስለማቅረባቸው የክርክሩ ሂደት አያሳይም፡፡

ሆኖም ከአቤቱታ አቅራቢዎች ጋር በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ4ኛ ተከሳሽነት ተሰይሞ የነበረውና በበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠበት አቶ ሃቢብ ጀማል በሕጉ አግባብ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ለዚህ ችሎት የሠበር አቤቱታ አቅርቦ ጉዳዩ ተጠሪ ባለበት ከተጣራ በኂላ ተጠሪ አድራጎቱ የሚሸፈንበትን የሕግ ድንጋጌ በመለየትና የበታች ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጡበት ድንጋጌ ለስር ተከሳሾች አድራጎት አግባብነት የሌለው መሆኑን ዘርዝሮ በሰጠው መልስ መነሻ ይህ ችሎት ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ተከሳሾች አድራጎት የሚያቋቁመው በወ/መ/ሕግ አንቀጽ 32(1(ለ)፣ 33 እና 422(1) ድንጋጌ መሆኑን ገልፆ አቶ ሀቢብ ጀማልን በዚሁ ድንጋጌ ስር ጥፋተኛ አድርጎ የቅጣት ውሳኔውንም በዚሁ ድንጋጌ አግባብ ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ በሕግ አተገባበርና አተረጓጎም ረገድ የበታች ፍርድ ቤቶች የፈጸሙበትን ስህተት ከማረሙም በላይ በውጤቱ ደግሞ አቶ ሀቢብ ጀማልን የጠቀመ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከስር ተከሳሾች መካከል አንዱ ይግባኝ ጠይቆ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ለይግባኝ ባዩ የሚጠቅም በሆነ ጊዜና ከይግባኝ ባዩ ጋር

ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ ሰዎች ይግባኝ ቢያቀርቡ ኑሮ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ሊጠቀሙ ይችሉ የነበረ መሆኑ ከተረጋገጠ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ይግባኝ ላላቀረቡት ተከሳሾች ጭምር ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደሚገባ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 196(1(ሀ) እና(ለ) ድንጋጌዎች ስር በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ ለዚህ ችሎት የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓትም ተፈፃሚነት ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም ችሎቱ የሚመራበት የተለየ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ የለምና፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ከአቶ ሀቢብ ጀማል ጋር ለዚህ ችሎት አቤቱታ ቢያቀርቡ ኑሮ የፍርዱ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችሉ የነበረ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አቶ ሀቢብ ጀማልን በተመለከተ ይህ ችሎት ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 196(1))(ሀ) (ለ) መሰረት ለአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ላይም ተፈጻሚነት አለው ብለናል፡፡

ቅጣቱን በተመለከተ ግን አቶ ሀቢብ ጀማል ላይ የተሠጠው እንዳለ ተግባራዊ ይሁን የሚል ግልፅ ድንጋጌ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 196 ድንጋጌ ስር አለ ለማለት ስለማይቻልና በመርህ ደረጃም እያንዳንዱ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው በተሳትፎውና ግላዊ ሁኔታዎችን መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ ከወ/መ/ሕጉ አንቀጽ 40 ድንጋጌ እና ከወንጀል ቅጣት አወሳሰን መርሆዎች የምንገነዘበው በመሆኑ የአሁኑ አቤቱታ አቅራቢዎች ላይ የሚጣለው የቅጣት መጠንን መመልከቱ ተገቢ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለከተው ከአሁኑ ጥያቄ አቅራቢዎች ውስጥ 1ኛው ረዳት ሳጅን መሀመድ እንድሪስ፣ እና 2ኛው አብዲ አሙር ከሀቢብ ጀማል ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ የተቀጡ በመሆኑ በአቶ ሀቢብ ጀማል ላይ በዚህ ችሎት የተጣለው ቅጣት ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚነት ያለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ ዐቃቤ ሕግ በጥያቄ አቅራቢዎች ላይ በቅጣት ማክበጃነት በስር ፍርድ ቤት የተያዙት ምክንያቶች እንዲያዙ የጠየቀ ቢሆንም ይህ ችሎት በአቶ ሀቢብ ጀማል ላይ የቅጣት ውሳኔ ሲሰጥ በከፊል ውድቅ ያደረጋቸው በመሆኑ በአሁኑ ጥያቄ አቅራቢዎች ላይም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት የሚያገኙበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘም፡፡

3ኛውን ጥያቄ አቅራቢ አቶ ደግፌ አለሙን በተመለከተ በስር ፍርድ ቤት የተያዙለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ ይሄውም ሪኮርድ የሌለበት መሆኑና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ ናቸው፡፡ ይህንኑ ይዘን የቅጣት እርከኑን ስንመለከተው በአንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ከእርከን 11 ወደ እርከን 12 ከፍ የሚል ሲሆን ጥያቄ አቅራቢው አቶ ደግፌ አለሙ ሁለት የቅጣት ማቅላያ ምክንያት ስላላቸው በመመሪያው አንቀፅ 13(5) መሰረት በጥያቄ አቅራቢው ላይ ሊጣል ይችል የነበረው ቅጣት በአራት እርከን እንዲወርድ የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህ ስሌት መሰረትም ከእርከን 12 ወደ እርከን 8 የሚወርድ ሁኖ በዚሁ መጨረሻ እርከን ስር የተመለከተው የቅጣት አይነትና የመጠን ሬንጅ ከአንድ አመት ከሁለት ወር እስከ አንድ አመት ከስድስት ወርበመሆኑ ለፍ/ቤቱ በተሰጠው ፍቅድ ስልጣን መሰረት አቶ ደግፌ አለሙ ለፈፀሙት ጥፋት ተመጣጣኝ፣ ለመሰል አጥፊዎችን ደግሞ አስተማሪ ነው ብለን ያገኘነው አንድ አመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራት ነው፡፡ ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች በጥያቄ ባሁኑ ጥያቄ አቅራቢዎች ላይ የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በስልጤ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 09466 ሰኔ 28 ቀን 2005 ዓ/ም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 196/1/ /ሀ/ እና /ለ/ መሰረት ተሻሽሎ ጥያቄ አቅራቢ በሆኑት፡-

   ሀ/ ረዳት ሳጅን መሐመድ እንድሪስ

   ለ/ አብዱ ኡመር

   ሐ/ ደግፌ አለሙ ይህ ችሎት ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም በአቶ ሀቢብ ጀማል በሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ተፈፃሚነት አለው ብለናል፡፡ ስለሆነም ጥያቄ አቅራቢዎቹ ሊጠየቁ የሚገባው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 33፣ 32(1(ለ) እና 422(1) ድንጋጌ ስር ነው ብለናል፡፡

2. ቅጣቱን በተመለከተም ረዳት ሳጅን መሐመድ እና እንድሪስ አብዱ ኡመር እያንዳንዳቸው በጉዳዩ የታሰሩት ማናቸውም ጊዜ የሚታሰብላቸው ሁኖ ሊቀጡ የሚገባው በአንድ አመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራት ነው በማለት ወስነናል፡፡ ደግፌ አለሙን በተመለከተ ደግሞ የታሰሩት የሚታሰብላቸው ሁኖ በአንድ አመት ከሁለት ወር ፅኑ እስራት ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ውሳኔ መሰረት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለወራቤ ማረሚያ ተቋም ይገለጽለት ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**እ/ተ**

የሰ/መ/ቁ 100712

መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ሽብሩ ጌቱ ሴንጫ - ጠበቃ ወይሸት ከበደ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የፌዴራል አቃቤ ሕግ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ባሁኑ አመልካች ላይ በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ፡- በ1996 ዓ/ም የወጣውን የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 669(2)ን በመተላለፍ የማይገባውን ብልፅግና ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ በ18/02/06 ዓ/ም በግምት ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ሲሆን በኮ/ቀ/ክ/ከ/ወረዳ 02 ልዩ ቦታው ካራቆሬ ደጋማን የፕላስቲክ ውጤቶች ማምረቻ ድርጅት ውስጥ በስራ አስኪያጅነት ተቀጥሮ እየሰራ ባለበት የግል ተበዳይ አማረ አብርሃም የድርጅቱ ባለቤት የሆኑትን ንብረት አንድ መቶ ሃምሳ ከረጢት የጫማ ጥሬ እቃ ፕላስቲክ የአንድ ከረጢት ግምት ብር 1100.00 (አንድ ሺህ አንድ መቶ ብር) የጠቅላላው ግምት ብር 165,000.00 (አንድ መቶ ስልሳ አምስት ብር) የሚያወጣውን ወስዶ ለስር 2ኛ ተከሳሽ አቶ ደረጀ ፍቃዱ የሸጠና የተያዘ በመሆኑ ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽሟል የሚል ነው፡፡ አመልካችም ፍርድ ቤት ቀርቦ የአቃቤ ሕግ የክስ ቻርጅ ተነቦለት እንዲረዳው ከተደረገ በሁዋላ እምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ የወንጀል ድርጊቱን ያለመፈፀሙን በመግለጹ አቃቤ ሕግ አሉኝ የሚላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦ አሰምቷል፡፡

ከዚህም በኋላ ፍርድ ቤቱ አመልካች ድርጊቱን ስለመፈፀሙ በአቃቤ ማስረጃዎች የተነገረበት መሆኑን ተገንዝቦ የአመልካችን የመከላከያ ማስረጃ ማስማት መብቱን በአመልካች ፍላጎት ማለፉን ጠቅሶ አመልካችን በአቃቤ ሕግ በኩል ተጠቅሶ በቀረበበት አንቀጽ ስር ጥፋተኛ አድርጎ ቅጣቱንም ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ጋር አገናዝቦ ማየቱን ገልጾ በስምንት አመት ከአምስት ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማቱ ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ የጸና ሲሆን የቅጣት ውሳኔው ግን በማክበጃ እና በማቅለያ ምክንያቶች አያያዝ ላይ የስር ፍርድ ቤት ስህተት መፈፀሙ የተረጋገጠበት ነው በሚል ምክንያት ስህተቶቹን ለይቶና ማረሙን ገልፆ የስር ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ መጠን ዝቅ በማድረግ አመልካች በስድስት አመት ከስድስት ወራት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን የአቤቱታው መሰረታዊ ይዘትም፡- የስር ፍርድ ቤት የአመልካችን መከላከያ ማስረጃ ሳይሰማ ያለፈው

አመልካች የመከላከያ ማስረጃ አለኝ እያልኩ ነው፣የወንጀል ድርጊቱ መፈፀሙን አቃቤ ሕግ አላስረዳም፣ ተፈፀመ የተባለው የወንጀል ድርጊትና የተጠቀሰው ድንጋጌ አብረው የማይሄዱና የቅጣት ውሳኔ አሰጣጥም ተገቢነት የሌለው ነው የሚሉ ምክንያቶችን የያዘ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ ማሰማት መብት የታለፈው በአግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለማጣራት ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ሲታዘዝ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች ጥፋተኛ የተባለው ዐቃቤ ሕግ ያቀረባቸውን ማስረጃዎች የመከላከያ ማስረጃ የለኝም በማለት በቃልና በፅሑፍ ለስር ፍርድ ቤት አረጋግጧል ተብሎ ስለመሆኑ ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡ አሁን በዚህ የሰበር ክርክር ደረጃ ደግሞ አመልካች ይህ የሥር ፍርድ ቤት አገለላጽ ከፍላጎታቸው ውጪ መመዝገቡንና የመከላከያ ማስረጃ ላሰማ ጥያቄ አቅርበው የነበረ መሆኑን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ የተከሰሱ ሰዎች በሕግ ከተጠበቁላቸው መብቶች አንዱ የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸውን ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 20(4) የተደነገገ ሲሆን ይህ መብት በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9(4) ድንጋጌ አግባብ የአገሪቱ የሕግ አካል በሆኑት የአለም አቀፍ ስምምቶችም ጥበቃ ያገኘ ስለመሆኑ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን 14(3(ለ)) ድንጋጌን በመመልከት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በእነዚህ ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው የተከሳሽ መብት የሚያስገነዝበው አንድ ተከሳሽ ተገቢ ባልሆነ ማስረጃ ጥፋተኛ እንዳይባልና በከሳሹ ወገን ማስረጃ ቀርቦ ከሆነም በበኩሉ ምንም ጥፋት ያልፈፀመና ንፁህ መሆኑን የማስረዳት ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ለቀረበበት ክስ መከላከያ ለማዘጋጀት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮችንና በቂ ጊዜ ማግኘት እንደሚገባው ሕጉ ያስገነዝባል፡፡ ተከሳሹ ይህንኑ በሕገ መንግስቱ ጥበቃ ያገኘውን የመከላከል መብት በአግባቡ እንዲጠቀም ማድረግ የፍርድ ቤት ኃላፊነት መሆኑንም ከሕገ መንግስቱ አንቀጽ 13(1) እና (2) ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ የተከሳሽ ክስን የመከላከል መብት ሊታለፍ የሚገባው ተከሳሹ መብቱን የማይጠቀምበት መሆኑን በግልፅ ለፍርድ ቤቱ ሲያረጋግጥለት ብቻ መሆኑን ከድንጋጌዎች መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ ተከሳሹ መብቱን ስለመተው ባልተረጋገጠበት አግባብ ግን የተከሳሽን የመከላከል መብት ተከሳሹ ትቷል የሚል አገላለፅ በፍርድ ሐተታው ላይ በማስፈር ብቻ ዳኝነት መስጠት ተገቢነት የሌለው አካሄድ ነው፡፡

የጉዳዮችንመራዘምለማስቀረትየተቀየሰውየተፋጠነየወንጀልአሰጣጥ (RTD) መሰረታዊ ኣላምምበማስረጃደረጃውስብስብነትየሌላቸውንጉዳዮችበቀላሉለመወሰንአዲስአሠራር ለመዘርጋት ማስቻል ከሚሆን በስተቀር በሕገ መንግስቱና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች የተጠበቁትን የተከሳሽን መብቶች በሚጎዳ አኳኃን ለመተግበር አለመሆኑ ይታወቃል፡፡በመሆኑም በሕጉ የተጠበቁት መብቶችና የዳኝነት አካሄዶች በሕጉ አግባብ ተተግብረው ዳኝነት ከሚሰጥ በስተቀር አንድ ጉዳይ የተፋጠነየወንጀልአሰጣጥን (RTD) መሰረት አድርጎ በመቅረቡ ብቻ ቀሪ የሚሆኑ

አይደሉም፡፡ የተፋጠነየወንጀልአሰጣጥ (RTD) አሰራርን መሰረት አድርጎ የሚታይ ጉዳይ የተከሳሹን የመከላከል መብት ለመተው የሚያስችለው ተከሳሹን ይህንኑ መብቱን በማሻያማ አኳኃን የተወው መሆኑን ሲያረጋግጥ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉደይ ስንመለስ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ያየው የተፋጠነየወንጀልአሰጣጥ (RTD) አሰራርን ተከትሎ ሲሆን አመልካችን ጥፋተኛ ያደረገው ተከሳሽ ድርጊቱን መፈፀሙ በዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተነግሮበት የመከላከያ ምስክር እንዳለው ተጠይቆ የመከላከያ ማስረጃ "አለኝ በማለት በችሎት በፅሑፍ በቃል ያረጋገጠ" ስለሆነ ነው በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ከውሳኔው ይዘት ተመልክተናል፡፡ ይህ የስር ፍርድ ቤት አጻጻፍ በአንድ በኩል አመልካች በቃልም ሆነ በፅሑፍ የመከላከያ ማስረጃ "አለኝ" ያለ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ድምዳሜው አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌለው መሆኑን መግለፁን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ይህን ግልጽነት የጎደለውን የስር ፍርድ ቤትን አጻጻፍ ትክክለኛነቱን ለመረዳት ይቻል ዘንድም ዋና መዝገቡን አስቀርበን ተመልክተናል፡፡ የስር ፍርድ ቤትን መዝገብ እንደተመለከትነውም የሥር ፍርድ ቤት አመልካች እንዲከላከል ጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት ብይን ሲሰጥ ብይኑ ቀድሞ የተዘጋጀውን ቅጽ/ፎርም/ በመሙላት የተሰጠ ሲሆን በይዘቱም አመልካች መከላከያ ማስረጃ "የለኝም" በማለት መግለፁን፣ ይህንኑ የገለፀው ደግሞ በችሎት በፅሑፍና በቃል መሆኑን የሚጠቅስ ቢሆንም አመልካች በቃል የገለጸ ስለመሆኑ ከብይኑ ውጪ በእለቱ የችሎቱ የወረቀት ስራ ያልተመዘገበ፣ "በፅሑፍ አረጋግጧል" የሚለው አባባልም ከመዝገቡ ውስጥ ካሉት ሰነዶች ሲታይ ሰነዱ የሌለ መሆኑን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት ቀድሞ የተዘጋጀውን የብይንና የፍርድ ፎርም ሲሞላ በአማራጭ የተቀመጡትን ቃላትና ሐረጎችን በእስክርቢቶ እየሰረዘ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የለኝም ብሎ በቃልና በፅሑፍ አረጋግጧል በማለት የመከላከያ ማስረጃ መስማትን ያለፈ ቢሆንም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያለመኖሩን ከስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ተረድተናል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካች በሕጉ የተጠበቀላቸውን የመከላከያ ማስረጃ ማሰማት መብት የስር ፍርድ ቤት ያለፈው አመልካቹ በግልጽ በመብቱ የማይጠቀምበት መሆኑን ሳያረጋግጥ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 34797 ጥቅምት 28 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 144019 የካቲት 14 ቀን 2006 ዓ/ም ተሻሻሎ የፀናው ውሳኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 195(2(ለ-1)) መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ የማሰማት መብት የታለፈው ያላግባብ ነው ብለናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 34797 ቀጥሎ የአመልካችን የመከላከላያ ማስረጃ በሕጉ አግባብ ሰምቶ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. የስር ፍርድ ቤት አመልካችን የብር 10,000 (አስር ሺ.ህ) ዋስ እንዲጣራና ጉዳዩን በውጪ ሆኖ እንዲከታተል እንዲደረግም ብለናል፡፡ይጻፍ፡፡

## ትዕዛዝ

የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በአስቸኳይ ይመለስ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡** **የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

# ጉምሩክ/ታክስ/

የሰ/መ/ቁ.96168

ህዳር 9 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ አርአያ ኪዳነ ቤተሰብ ነኝ በማለት መምህር ፍሰሐ ገ/መስቀል ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዐ/ሕግ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ተጠሪ ያቀረበባቸውን የኮንትሮባንድ የወንጀል ክስ የተመለከተው የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠባቸው እና በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናው የጥፋተኝነት እና የተሻሻለው የቅጣት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽ በነበሩት የአሁኑ አመልካች እና የዕቃዎቹ ባለቤት ናቸው ተብለው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በብይን በተሰናበቱት 2ኛተከሳሽ ላይበ07/06/2005 ዓ.ም.አዘጋጅቶ ያቀረበው ክስ ይዘት ባጭሩ፡-ተከሳሾቹ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32(3) እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 በአንቀጽ 91(2) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈጸመባቸውን የቀረጥ እና የታክስ መጠናቸው ብር 136,657 የሆነ እና ንብረትነታቸው የ2ኛ ተከሳሽ የሆኑ የተለያዩ ዕቃዎችን 1ኛ ተከሳሽ ሲያሽከረክሩ በነበረው የሰሌዳ ቁጥሩ 2-A06860 አ.አ. በሆነ ተሽከርካሪ ለዕቃ መሸሸጊያ ተብሎ በተሰራ የመኪና አካል (ሻግ) ውስጥ ጭነው ከባሌ ሮቤ ወደ ሻሸመኔ በመጓዝ ላይ እያሉ በ15/05/2005 ዓ.ም. ከቀኑ በግምት 9:00 ሰዓት በአዳባ ኬላ ላይ የተያዙ በመሆኑ የኮንትሮባንድ ወንጀል አድርገዋል የሚል ሲሆን አመልካች ተጠይቀው ወንጀሉን አላደረግሁም በማለታቸው ፍርድ ቤቱ በተጠሪ በኩል የቀረቡ ሁለት የጉምሩክ ፖሊስ አባላትን ምስክርነት ከሰማ እና የተጠሪን የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኃላ 2ኛ ተከሳሽ የነበሩትን ግለሰብ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 መሰረት በነጻ በማሰናበት አመልካችን ግን ዐቃቤ ሕግ በክሱ መሰረት ያስረዳባቸው መሆኑን ገልጾ መከላከያቸውን ማሰማት እንዲጀምሩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት ትዕዛዝ በመስጠቱ አመልካች የተሳቢ መኪና ሾፌር መሆናቸውን እና የተከለከሉ ዕቃዎችን ጭኖአል የተባለውን ተሽከርካሪ በዕለቱ ሊይዙ የቻሉት ብር 500

ተከፍሎአቸው ተሽከርካሪውን ሻሸመኔ ድረስ እንዲያደርሱ ደላሎች በነገሯቸው መሰረት መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም በሁለቱ ወገኖች የቀረበውን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካቹ ባሰሟቸው የመከላከያ ምስክሮች በዐቃቤ ሕግ ማስረጃ የተመሰረባቸውን ፍሬ ነገር ለማስተባበለል አልቻሉም በማለት በክሱ በተጠቀሰባቸው ድንጋጌ ስር የጥፋተኝነት ውሳኔ ከሰጠባቸው በኃላ ግራ ቀኙ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርቡ አድርጓል፡፡በመቀጠልም በክሱ የተመለከተው ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ደረጃ ያልወጣለት መሆኑን ገልጾ በክብደቱ እና በአፈጻጸሙ በመካከለኛ ደረጃ መድቦ አመልካች የቀድሞ ፀባያቸው መልካምነት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸው በማቅለያ ምክንያትነት እንዲያዙላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በሚል ምክንያት ሳይቀበል ቀርቶ ቅጣቱን በመመሪያው መሰረት በማስላት በአባሪ አንድ በእርከን 27 ስር በአስር ዓመት ጽኑ እስራት እና በብር 15,000 መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካቹ የዘወትር ፀባይ መልካምነት በማቅለያ ምክንያትነት ሳይያዝ የቀረው አላግባብ መሆኑን ገልጾ የጽኑ እስራት ቅጣቱን በሶስት እርከን ዝቅ በማድረግ በእርከን 24 ስር ወደ ሰባት ዓመት አሻሽሎ ቀሪውን ውሳኔ በማጽናቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የጥፋተኝነት ውሳኔውን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመከለተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች በክሱ የተመለከተውን ወንጀል አላደረግሁም በማለት ክደው የተከራከሩ ቢሆንም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት በአመልካቹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠው ተጠሪ ባሰማቸው ሁለት ምስክሮች እና ባቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 141 ስር በተቀመጠው መስፈርት መሰረት አመልካቹን ጥፋተኛ በሚያደርግ ደረጃ በክሱ መሰረት ማስረዳቱን፣አመልካች መከላከያቸውን እንዲያሰሙ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 142 መሰረት በተሰጠው ትዕዛዝ አመልካች አቅርበው ያሰሟቸው ሁለት የመከላከያ ምስክሮች የምስክርነት ቃል በተጠሪ ምስክሮች እና ሰነዶች በአመልካቹ ላይ የተመለከተውን የወንጀል ፍሬ ነገሮች ማስተባበል ያልቻለ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ነው፡፡አመልካች ሲያሽከረክሩት በነበረው ተሽከርካሪ የተጫኑ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በጉምሩክ ኬላ መያዛቸውን ሳይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት ተሽከርካሪውን ከባሌ ሮቤ እስከ ሻሻመኔ ለማድረስ በብር 500 ተስማምቼ ከማሽከርከር በቀር ተሽከርካሪው የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈጸመባቸውን ዕቃዎች ጭኖ የነበረ ስለመሆኑም ሆነ የዕቃ መደበቂያ ሻግ የነበረው ስለመሆኑ የማውቀው ነገር ያልነበረ በመሆኑ በወንጀሉ ጥፋተኛ የተባልኩት አላግባብ ነው በማለት መሆኑን የአቤቱታው ይዘት ያመለክታል፡፡

ይሁን እንጂ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካቹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ያስተላለፈው አመልካች በክሱ የተመለከተውን ወንጀል ማድረጋቸው በተጠሪ ማስረጃ ተረጋግጦባቸው እያለ ይህንኑ በመከላለከያ ማስረጃ አለማስተባበላቸውን መሰረት በማድረግ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች በጥፋተኛነት ውሳኔው ላይ ያቀረቡትን ቅሬታ ሳይቀበል የቀረው ዕቃዎቹ ስለመጫናቸው የማውቀው ነገር የለም ይበሉ እንጂ 1ኛ የተጠሪ ምስክር በሰጡት ምስክርነት ቃል ውስጥ አመልካች በተሽከርካሪው ላይ የዕቃ መሸሸጊያ ቦታ (ሻግ) ካለ ተጠይቀው ሌላ ሻግ ከተሽከርካሪው ሳልቫቲዮ ውስጥ መኖሩን አሳይተውኛል የሚል ምስክርነት እንደሰጡ ከይግባኙ ግልባጭ መገንዘቡን ጭምር በመጥቀስ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ ተጠሪ ይህንኑ ሁኔታ በመጥቀስ በሰበር መልሱ ላቀረበው ክርክር የምስክሩ ቃል እርስ በርሱ የሚጋጭ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም ከማለት በቀር የዚህ ዓይነት ምስክርነት ስለመሰጠቱ አመልካች ያቀረቡት ማስተባበያ አለመኖሩን ከመልስ መልሳቸው ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገርን አጣርተው እና ማስረጃን መዝነው በአመልካች በኩል የቀረበውን መከላከያ ውድቅ በማድረግ የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚያስችል አሳማኝ ምክንያት ባለመገኘቱ አመልካች የጥፋተኝነት ውሳኔው የተሰጠብኝ አላግባብ በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ በነጻ እንድሰናበት ሊወሰንልኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የቅጣት ውሳኔውን በተመለከተ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክሱ የተመለከተው ወንጀል በወቅቱ በስራ ላይ በነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ደረጃ ያልወጣለት መሆኑን ገልጾ በክብደቱ እና በአፈጻጸሙ በመካከለኛ ደረጃ ለመመደብ ምክንያት ያደረገው ዕቃዎቹ በተሽከርካሪው ውስጥ ተደብቀው የተገኙት ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ልዩ የመሸሸጊያ ስፍራ መሆኑን ነው፡፡በመዝገቡ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት በማድረግ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ወንጀሉን በመካከለኛ ደረጃ መመደቡ የመሰረታዊ የሕግ ስህተት ጥያቄን የሚያስነሳ ባለመሆኑ ወንጀሉ ሊመደብ ይገባው የነበረው በዝቅተኛ ደረጃ ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በአመልካቹ ላይ የቀረበ የማክበጃ ምክንያት የሌለ ሲሆን የቀድሞ ፀባያቸው መልካምነት እና የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸው በማቅለያ ምክንያትነት እንዲያዙላቸው አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በሚል ምክንያት ሳይቀበል የቀረ ቢሆንም በዐቃቤ ሕግ በኩል የቀረበ ተቃራኒ ክርክር እና ማስረጃ እስከሌለ ድረስ የአመልካቹ የቀድሞ ጸባይ መልካምነት ግምት የሚወሰድበት መሆኑን ገልጾ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማቅለያ ምክንያትነት ተቀብሎ ቅጣቱን አሻሽሏል፡፡

ይሁን እንጂ የቤተሰብ አስተዳዳሪነታቸው በማቅለያነት ሊያዝላቸው እንደሚገባ አመልካች አሁንም ድረስ እየተከራከሩ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር ያለፈው በምን ምክንያት እንደሆነ ውሳኔው በግልጽ አያመለክትም፡፡ቀደም ሲል እንደተገለጸው በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡትን ጥያቄ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳይቀበል የቀረው የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረቡም በማለት ነው፡፡የጥፋተኛነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔው የተሰጠው በአንድ ቀን ስለመሆኑ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያመለክት በመሆኑ አመልካች አለኝ የሚሉትን የቅጣት ማቅለያ ምክንያት በማስረጃ ለማስደገፍ ጊዜ ወይም ቀጠሮ ተሰጥቷቸው የነበረ ስለመሆኑ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡

በመሰረቱ በወንጀል ጉዳይ የጥፋተኛነት ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ግራ ቀኙ አሉን የሚሏቸውን የማክበጃ እና የማቅለያ ምክንያቶች የማቅረብ እና አስፈላጊ ሲሆንም በማስረጃ የማስደገፍ መብት ያላቸው ስለመሆኑ ከወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 149 (3) እና (4) ድንጋጌ አጠቃላይ ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን ፍርድ ቤቶችም የእነዚህን መብቶች

ተግባራዊነት ለማረጋገጥ ያስችል ዘንድ ለተከራካሪ ወገኖች ጊዜ ወይም ተለዋጭ ቀጠሮ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡በመሆኑም ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቶ አመልካች የቤተሰብ አስተዳዳሪታቸውን በማስረጃ ማስደገፍ የሚችሉ መሆን አለመሆናቸውን ሳያረጋግጥ የማቅለያ ምክንያቱ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በማለት ወዲያውኑ የቅጣት ውሳኔ ወደ መስጠት ማምራቱ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ የተባለ ሰው በቅጣት ማቅለያነት እንዲያዝለት ያቀረበውን ምክንያት በማስረጃ ማስደገፍ እንዲችል በቂ ጊዜ ባላገኘበት ሁኔታ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በሚል የማቅለያ ምክንያቱን ውድቅ በማድረግ የሚሰጥ የቅጣት ውሳኔ ደግሞ በወንጀል ሕጉ እና በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ስለ ቅጣት አወሳሰን የተቀመጡትን ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል በቅጣት አወሳሰን ረገድ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17056 በ13/12/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 168474 በ12/03/2006 የተሻሻለው ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካቹ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካቹ ላይ የተጣለው የቅጣት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
4. የአመልካቹ የዘወትር ጸባይ መልካምነት በኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማቅለያ ምክንያትነት የተያዘው በአግባቡ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካች የቤተሰብ አስተዳዳሪ ስለመሆናቸው አለኝ የሚሉትን ማስረጃ እንዲያቀርቡ ካደረገ በኃላ ተገቢውን - የቅጣት ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
5. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ በውሳኔው መሰረት ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፤እንዲያውቁት ደግሞ ለኦሮሚያ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና በሚገኙበት ማረሚያ ተቋም በኩል ለአመልካቹ ይላክ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ 100079

መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** አቶ ዕቁባይ በርሀ ገ/እግዚአብሔር - ጠበቃ ደሳለኝ መስፍን ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** የኢትዮጵያ ገቢዎች ጉምሩክ ባለሥልጣን - ዐ/ህግ ወንድዬ ብርሃኑ ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 176025 ታህሳስ 19/2005 ዓ/ም የሰጠው ፍርድና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 131320 ጥር 21 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታርምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው ጉዳዩ ተጠሪ አመልካች የአንድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ ለግብር ስብሳቢው መሥሪያ ቤት አሳሳች ማስረጃ የማቅረብና ተጨማሪ እሴት ታክስ የማሳወቅና የመክፈል ኃላፊነቱን ባለመወጣት ወንጀል ፈፅሟል በማለት ያቀረበውን ክስና ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በሜጋ ኪነ ጥበብ ማዕከል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና በአመልካች ላይ የቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ
   - በሥር አንደኛ ተከሳሽ የሆነው ሜጋ ኪነ ጥበብ ማዕከል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 96 እና የወንጀል ህጉን አንቀፅ 34/1/ የተመለከተውን በመተላለፍ ከሀምሌ 1996 ዓ/ም እስከ 2002 ዓ/ም ባደረገው የንግድ እንቅስቃሴ ለመንግስት ገቢ ማድረግ የነበረበት ብር 39,801.32 /ሰላሣ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ አንድ ብር ከሰላሣ ሁለት ሳንቲም/ በማሣወቅ መክፈል ሲገባው ግብሩን ያላሳወቀ በመሆኑ ወንጀል ፈፅሟል ሁለተኛው ተከሳሽ (አመልካችም) የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 86 እና አንቀፅ 102(1) በመተላለፍ የንግድ ድርጅቱ ሥራ-አስኪያጅ ሆኖ የንግድ ድርጅቱን ገቢ ባለማሣወቁ ወንጀል ፈፅሟል፡፡
   - አንደኛ ተከሳሽ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286 /1994 አንቀፅ 97 ንዑስ አንቀፅ 3(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍ 1997 ዓ/ም ባከናወነው የንግድ እንቅስቃሴ ትርፍ አግኝቶ እያለ፤ ወጭውን ከፍ አድርጎ በማቅረብ ኪሣራ እንደደረሰበት አድርጎ በማሳወቁ፤ ለግብር

ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት አሳሳች ማስረጃ የማቅረብ ወንጀል ፈፅሟል ሁለተኛው ተከሳሽ (አመልካች) የአንደኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀፅ 96 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) አንቀፅ 102(1) የተመለከተውን በመተላለፍ አሳሳች ማስረጃ የማቅረብ ወንጀል ፈፅሟል፡፡

- አንደኛ ተከሳሽ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285 /94 አንቀፅ 49 እና በወንጀል ህግ አንቀፅ 34(ሀ) የተመለከተውን በመተለለፍ ከ1996 ዓ/ም እስከ 2002 ዓ.ም ባደረገው የንግድ እንቅስቃሴ የሰበሰበውን ብር 426.229.03 /አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ዘጠኝ ብር ከዜሮ ሶስት ሣንቲም) ተጨማሪ እሴት ታክስ ለመንግስት አሳውቆ ባለመክፈሉ ወንጀል ፈፅሟል፡፡ሁለተኛ ተከሳሽ (አመልካች) የአንደኛ ተከሳሽ ሥራ-አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ አንደኛ ተከሳሽ የሰብሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ለመንግስት አሳውቆ እንዲከፈል ባለማድረጉ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 ዓንቀፅ 49 እና 56(1) በመተላለፍ ወንጀል ፈፅሟል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

2 አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ ወንጀሉን አልፈፀምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት የቀረበበትን ክስ ክዶ ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ የአንደኛ ተከሳሽ የንግድ ፈቃድ፤ ሜጋ ኪነጥበብ ማዕከል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የመመሥረቻ ፅሑፍና መተዳደሪያ ደንብ የድርጅቱ ገቢ ኦዲት የተሰራበት ሪፖርትና የትርፍ ማስታወቂያ፣ ደረሰኝ የተተመበትን ሰነድና የሰው ምስክሮችን በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ያቀረባቸው ሁለት ምስክሮች አንደኛ ተከሳሽ የመፍረስ ጥያቄ በማቅረቡ ከሳሽ መሥሪያ ቤት የድርጅቱን ሒሳብ ኦዲት እንዲያደርጉ መድቧቸው ሒሳቡን ኦዲት ያደረጉ መሆኑን ሂሳቡን ኦዲት ያደረጉት የአንደኛ ተከሳሽ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ሁለተኛ ተከሳሽ ያቀረበውን የሂሳብ ሰነድና አንደኛ ተከሳሽ ለከሳሽ መሥሪያ ቤት ሲያቀርብ የነበረውን የሂሳብ ሪፖርት መሠረት በማድረግ እንደሆነ ገልፀው 1997 ዓ/ም አንደኛ ተከሳሽ ብር 15,748 /አስራ አምስት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ስምንት ብር/ ኪሳራ የደረሰበት መሆኑን ለከሳሽ አሳውቋል፡፡ ሆኖም 1997 ዓ/ም አንደኛ ተከሳሽ ብር 132,673.06/አንድ መቶ ስላሣ ሁለት ሺ ስድስት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከዜሮ ስድስት ሣንቲም/ አግኝቶ የነበረ መሆኑንና 1997 ዓ/ም አንደኛ ተከሳሽ 39.801 /ስላሳ ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ አንድ ብር) የንግድ ትርፍ ገቢ ግብር መክፈል የነበረበት መሆኑን በማረጋገጥ ወስነናል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ኪሣራ ደርሶብኛል በማለት ሪፖርት ያደረገው የድርጅቱ ሠራተኞች ባልሆኑ ሰዎች የከፈለው ደመወዝ የስልክ ወጭና የሌላ ድርጅት ንብረት የሆኑ መኪኖች የተሞላ ነዳጅ በወጭነት በማቅረብ ነው፡፡ ይህም የገቢ ግብር አዋጅንና አዋጁን ለማስፈፀም የወጣውን መመሪያ መሠረት ያላደረገ በመሆኑ በወጭነት አልያዝነውም፡፡ እኛ ሂሳብ ስንሠራ ወድቅ አድርገነዋል፡፡

3 ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ አንደኛ ተከሳሽ ለከሳሽ ባሣወቀውና አንደኛ ተከሳሽ ባከናወነው ግብይት ወይም የንግድ እንቅስቃሴ መካከል ልዩነት መኖሩን አንደኛ ተከሳሽ ብር 429,172 /አራት መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሰባ ሁለት ብር/ ተጨማሪ እሴት ታክስ ለመንግስት አሳውቆ መክፈል ሲገባው፤ ይህንን የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመንግስት ያልከፈለ መሆኑን ባከናወኑት የኦዲት ሥራ ማረጋገጣቸውን ለሥር ፍርድ ቤት ያስረዱ መሆኑን በውሣኔው አስፍሮታል፡፡ ሶስተኛው የተጠሪ ምስክር አንደኛ ተከሳሽ የሂሳብ ሠራተኛ መሆኑን ገልፆ ሁለተኛው ተከሳሽ የአንደኛ ተከሳሽ ሥራ አስኪያጂ በመሆን 1997 ዓ/ም እስከ 2002 ዓ/ም የሠራ መሆኑንና 1ኛ ተከሳሽ 1998

ዓ/ም ከሜጋ ማስታወቂያ ጋር ሲዋሀድም 2ኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ ሆኖ የሰራ መሆኑን እንደመሰከረ የሥር ፍርድ ቤት በውሳኔው ፅፎታል፡፡

4 ሁለተኛ ተከሳሽ /አመልካች/ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሂሳብ ሠራተኞች በየወሩ ለከሳሽ /ተጠሪ/ ሪፖርት ያደርጉ የነበረ መሆኑንና ገቢን አለማሳወቅና አሳሳች ማስረጃ ማቅረብ የተባለውም ገቢን አለማሣወቅና አሳሳች ማስረጃ የማቅረብ ወንጀል አልፈፀምኩም በኦዲት ተገኘ የተባለው የሂሳብ ልዩነት የተፈጠረው አንደኛ ተከሳሽና ሜጋ ማስታወቂያ 1998 ዓ/ም ጀምሮ በአንድ ሥራአስኪያጅ እየተመሩ አንድ ላይ ስራ ሲሳሩ የነበረ በመሆኑና በሜጋ ማስታወቂያ ሠረተኞች የስልክ ወጭና የሜጋ ማስታወቂያ መኪኖች ነዳጅ የወጣ ውጭ በመኖሩ ምክንያት ነው በማለት አምስት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡ አንደኛው የአመልካች የመከላከያ ምስክር የአንደኛ ተከሳሽ ጉዳይ አስፈፃሚ ሆኖ ሲሳራ ከፋይናንስ ክፍል ይሰጠው የነበረውን የተጨማሪ እሴት ተክስ ሪፖርት ለከሳሽ /ለተጠሪ/ ሲያደርስ እንደነበረና አንደኛ ተከሳሽ 1998 ጀምሮ ከሜጋ ማስታወቂያ ጋር ሲሰራ የሜጋ ማስታወቂያና መኪኖች በትውስት በመውሰድ ነዳጅ በመሙለት ሲጠቀም እንደነበረ የመሰከረ መሆኑን ሁለተኛ መከላከያ ምስክር የሒሳብ ባለሙያ መሆናቸውን ገልፀው ለአንደኛ ተከሳሽ የሂሳብ ሠራተኞች በ1996 ዓ/ም የሂሳብ አያያዝ ሥልጠና የሰጡ መሆኑን እንደመሰከረ፣ ሶስተኛ መከላከያ ምስክር የአንደኛ ተከሳሽ የሂሳብ ሠራተኛ እንደነበር 1997 ዓ/ም ጀምሮ የሽያጭ ወጭ ደረሰኞችን በመቀበል በየወሩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሪፖርት ያዘጋጅ እንደነበር እንደመሰከሩ፤ አራተኛ የመከላከያ ምስክር የአንደኛ ተከሳሽ ሹፌር የነበረ መሆኑን ገልጾ፣ 1ኛ ተከሳሽ ይጠቀምበት የነበረውን ላንድክሩዘር ኮድ ሁለት የሆነ መኪና ያሽከረክር እንደነበርና ወጭውንም የሚሸፍነው አንደኛ ተከሳሽ እንደነበር እንደመሰከረ፣ 5ኛ የመከላከያ ምስክር የፋሲል ኮንሰልት ኃ/የተ/የግል ማህበር የሂሳብ ሰራተኛ በመሆን የአንደኛ ተከሳሽ የሁለት አመት 1996ዓ.ም እና 1997ዓ.ም ሂሳብ የሰራ መሆኑንና የሂሳብ ሰነድ ወጭና ገቢ አያያዙ ጥሩ ሆኖ ማግኘታቸውንና ተከሳሽ ድርጅትም በኪሳራ ይንቀሳቀስ እንደነበር ያስረዱ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው አስፍሮታል፡፡

5 የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽና ሜጋ ማስታወቂያ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት ያልተቀላቀለ መሆኑ፣ አንደኛ ተከሳሽ በሜጋ ማስታወቂያ ሰራተኞች የከፈለው ደመወዝና የስልክ ወጭ የአንደኛ ተከሳሽ ሕጋዊ ወጭ ተደርጎ ሊያዝ የማይችል መሆኑን የተሽከርካሪ ትውስት የተባለውም ተቀባይነት ያለውን የሂሳብ አሰራር ያልተከተለ በመሆኑ ተጨማሪ እሴት ታክስን በተመለከተ፣ በየወሩ ሪፖርት ይደረግ የነበረ መሆኑን በመከላከያ ማስረጃ ከማስረዳት ውጭ አንደኛ ተከሳሽ የሰበሰበውን ብር 426,229.03 ተጨማሪ እሴት ታክስ ለከሳሽ መስሪያ ቤት ያላሳወቀና ገቢ ያላደረገ መሆኑን በማረጋገጥ በከሳሽ (ተጠሪ) በኩል ያቀረበውን ማስረጃ የሚያስተባብል ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ስለዚህ አንደኛ ተከሳሽ 1997ዓ.ም ትክክለኛ ገቢውን ባለማሳወቁና ኪሳራ እንደደረሰበት ሪፖርት በማድረጉ እንደዚሁም አንደኛ ተከሳሽ ከ1996ዓ.ም እስከ 2002ዓ.ም የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ሙሉ ለሙሉ ለተጠሪ (ለከሳሽ) ባለማሳቁና ገንዘቡንም ገቢ ባለማድረጉ ሁለተኛ ተከሳሽ በስራ አስኪያጅነቱ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 96 እና አንቀጽ 97 ንዑስ አንቀጽ 3(ሀ) የተመለከተውን በመተላለፍና በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነው በማለት የቅጣት ውሳኔ በመወሰንና በመገደብ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

6 በዚህ ውሳኔ አመልካችና ተጠሪ ቅር በመሰኘት አመልካች በመዝገብ ቁጥር 131320 ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 131160 ያቀረቡትን ይግባኝ ቅሬታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት

በመዝገብ ቁጥር 131320 በማጣመር፣ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል።

7 አመልካች የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነት ውሳኔ ለማስለወጥ ሚያዚያ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የወንጀል ክስ ከመመስረቱ በፊት የንግድ ድርጅት ስራ አስኪያጅነት መልቀቄን ሰነዶች ያረጋግጣሉ። እኔ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ በወንጀል ጥፋተኛ ልባል ከሚገባው በመጀመሪያ በስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው የንግድ ድርጅት ተጠርቶ፣ ቀርቦ ተከራክሮ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ነው። አንደኛ ተከሳሽ የሌለ መሆኑን ተጠሪ የወንጀል ክስ ሲመሰርት ያውቃል። አንደኛ ተከሳሽ የፈረሰና ህጋዊ ህልውና የሌለው በመሆኑ በወንጀል ሊከሰስና ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ አይችልም። አንደኛ ተከሳሽ በወንጀል ሊጠየቅ የማይችል ከሆነ ስራ አስኪያጅ በወንጀል ሊጠየቅ አይችልም ። የአንደኛ ተከሳሽ ሂሳብ ኦዲት የተደረገው በ2003 ዓ.ም ነው። ይህም አመልካች ድርጅቱን ከለቀቀ ከአስር ወር በኋላ ነው። ሜጋ ማስታወቂያና ሜጋ ኪነጥበባት፣ በኋላ የተቀላቀሉ መሆኑ ተረጋግጧል። ስለዚህ ስራ አስኪያጅ የነበረው አመልካች በተጨባጭ ለስራ ያወጣው ወጭ ውድቅ ተደርጎ አሳሳች ማስረጃ አቅርቧል፣ ተጨማሪ እሴት አሳውቆ ገቢ አላደረገም ተብሎ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል።

8 ሰኔ 27 ቀን 2006ዓ.ም በተጻፈ መልስ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት በራሱ ወንጀል የመፈጸም ሃሳብ የሚፈጥር ባለመሆኑ፣ ድርጅቱ ወንጀል የሚፈጽመው ከድርጅቱ ኃላፊዎች ወይም ሰራተኞች አንዱ የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ ባለመወጣት ወይም የድርጅቱን ጥቅም በህገ ወጥ መንገድ ለማራመድ ተንቀሳቅሰው በተገኙ ጊዜ ነው። ከስር ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት አመልካች አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ በነበሩበት ጊዜ ለተፈጸመው ወንጀል ተጠያቂ መሆናቸው በወንጀል ሕጉ የተቀመጠውን መርህ የተከተለ ነው። ከስር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት በህጋዊ መንገድ የፈረሰ ስለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ የለም። ተጠሪ የወንጀል ክሱንና መጥሪያውን ለማድረስ ጥረት አድርጎ ሊያገኘው አልቻለም። ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በጋዜጣ ጥሪ አድርጎለት አልቀረበም ከዚህ አንጻር የስር ፍርድ ቤት በጋዜጣ አለመጥራት እንደ ስነ-ስርዐት ስህተት ከሚታይ በስተቀር በአመልካች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ የሚያስለውጥ አይደለም። የድርጅቱም ሂሳብ በአግባቡ የተጣራና ወንጀሉ የተፈጸመ መሆኑ ተረጋግጦ የተሰጠ ውሳኔ በመሆኑ የአመልካች፣ የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል። አመልካች ነሐሴ 23 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ ሁለተኛ ተከሳሽ (አመልካች) በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑ የሚረጋገጠው አንደኛው ተከሳሽ በአግባቡ ተጠርቶ፣ ተከራክሮ ጥፋተኛ ነህ ተብሎ ሲፈረድበት ነው። ይህ ሳይደረግ ሁለተኛው ተከሳሽ ጥፋተኛ ተብሎ ሊፈረድበት አይችልም። የስር ፍርድ ቤት ድርጅቱንና ሁለተኛ ተከሳሽን ጥፋተኛ ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። ይህ ተገቢ ያልሆነና የወንጀል ህግን መሰረታዊ መርህ የሚጻረር ውሳኔ ነው። ምክንያቱም በስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት 1ኛ ተከሳሽን በመጥሪያም ይሁን በጋዜጣ አልተጠራም፣ አልቀረበም በሌለበት ይታያል ተብሎ አልተያዘም። 1ኛ ተከሳሽ ያፈረሰ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ሁለተኛ ተከሳሽ የለብኝም የሚልና ሌሎች በሰበር አቤቱታው ያነሳቸውን መከራከሪያዎች የሚያጠናክር ክርክር አቅርቧል።

9 ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የሜጋ ኪነጥበባት ኃላፊነቱ

የተወሰነ የግል ማሕበር ስራ አስኪያጅ ሆኖ ሲሰራ፣ የንግድ ትርፍ ገቢ በትክክል አለማሳወቅና የንግድ ትርፍ ገቢ ግብር አለመክፈል፣ አሳሳች ማስረጃ የማቅረብና የንግድ ድርጅቱ በፈጸማቸው ግብይቶች ወይም የንግድ እንቅስቃሴ የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ በተሟላ ሁኔታ አለማሳወቅና ገቢ ያለማድረግ ወንጀል ፈጽሟል በማለት የሰጡት የጥፋተኝነት ውሳኔ በሕግ አግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

10 ጉዳዩን እንደመረመርነው የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የሆነው ሜጋ ኪነጥበባት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር በንግድ ህግ አንቀጽ 542 እና አንቀጽ 543 መሰረት ያልፈረሰ ወይም የንግድ ህጉ ከአንቀጽ 544 እስከ አንቀጽ 554 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሰረት ከሌላ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር በተለይም ከሜጋ ማስታወቂያ ጋር በሕግ የተደነገገውን ስርዓት በማሟላት ያልተቀላቀለ መሆኑ የስር ፍርድ ቤት በውሳኔው በማረጋገጥ ውሳኔ ሰጥቷል የስር አንደኛ ተከሳሽ በህግ አግባብ ካልፈረሰ ወይም ከሌላ የንግድ ድርጅት ጋር አለመቀላቀሉ ካልተረጋገጠ፣ ህጋዊ ህልውና ያለው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፣ እንደሆነ ከህጉ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ የስር አንደኛ ተከሳሽ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመሆኑ ከመፍረሱ ወይም ከሌላ ድርጅት ጋር ከመቀላቀሉ በፊት ይከናወን ያላቸው ተግባራት አሉ፡፡ ከእነዚህ ተግባራት መካከል የማኃበሩ ሒሳብ የማጣራት ስራ ነው፡፡ ተጠሪ የአንደኛ ተከሳሽ ሂሳብ ኦዲት ያደረገው አንደኛ ተከሳሽ የመፍረስ ጥያቄ በማቅረቡ እንደሆነ፣ ተጠሪ ያቀረባቸው ምስክሮችና የአንደኛ ተከሳሽን ሒሳብ ያጣሩት ባለሙያዎች የገለጹ መሆኑን በስር ፍርድ ቤት በግልጽ ሰፍሯል፡፡ ይህም የአንደኛ ተከሳሽ ሒሳብ በተጣራበት ጊዜ አንደኛ ተከሳሽ የመፍረስ ጥያቄ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም በሕግ አግባብ ሒሳቡ ተጣርቶ የመፍረስ ውሳኔ ያልተሰጠና ህጋዊ ሕልውና ያለው ድርጅት የነበረ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣናቸው ያረጋገጡት በመሆኑ አመልካች አንደኛ ተከሳሽ ሕጋዊ ሕልውናው የከተመ ወይም የፈረሰ ድርጅት ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

11 .አንደኛ ተከሳሽ የሕግ ሰውነት ያለው የንግድ ድርጅት ነው፡፡ የሕግ ሰውነት ያለው የንግድ ድርጅት በሕግ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ በዋና ወንጀል አድራጊነት፣ በአነሳሽነት ወይም በአባሪነት ወንጀል ሊቀጣ የሚችል መሆኑ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች ሕጉ በወንጀል የሚጠየቁ እንደሆነ በልዩ ሁኔታና በግልጽ ባልደነገገባቸው ወንጀሎች የወንጀል ተጠያቂነት እንደማይኖርባቸው በወንጀል ህጉ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ማንኛውም የንግድ ድርጅት በዓመት ውስጥ ያገኘው ትክክለኛ ትርፍ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት የማሳወቅ ግብር የመክፈል ኃላፊነት እንዳለበትና ይህንን ኃላፊነቱን በመጣስ በተለይም አሳሳች የሆኑ ማስረጃዎችን በማቅረብ ግብር የማጭበርበር ተግባር ከፈጸመ በወንጀል ተጠያቂ እንደሚሆን ከአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 96 እና አንቀጽ 97(1) ድንጋጌዎች ተደንግጓል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ በ1997ዓ.ም ብር 132673.06 /አንድ መቶ ሰላሳ ሁለት ስድስት መቶ ሰባ ሶስት ብር ከዜሮ ስድስት ሳንቲም/ ከንግድ ስራ ትርፍ አግኝቶ እንደነበር ነገር ግን አንደኛ ተከሳሽ በሕግ አግባብ ላልተቀላቀለው ሜጋ ማስታወቂያ ሰራተኞች የከፈለውን ደመወዝ በስልክ ክፍያና የነዳጅ ወጭ አንደኛ ተከሳሽ ለእራሱ ስራ ያወጣው ህጋዊ ወጭ አስመስሎ በማቅረብና 1997ዓ.ም ከንግድ ስራ ትርፍ እንዳላገኘና ኪሳራ እንደደረሰበት ለተጠሪ ያሳወቀ መሆኑ ተጠሪ ባቀረበው የጽሑፍና የሰው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንደኛ ተከሳሽከ1996 እስከ 2002 ዓ.ም ባከናወነው

ግብይት ብር 426299.03 /አራት መቶ ሃያ ስድስት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ብር ከዜሮ ሶስት ሳንቲም/ ተጨማሪ እሴት ታክስ ሰብስቦ ለተጠሪ ይህንን ተጨማሪ እሴት ታክስ ገንዘብ የሰበሰበ መሆኑን እንዳላሳወቀና ገንዘቡንም ገቢ እንዳላደረገ ተጠሪ ባቀረባቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ሕግን በመጣስ የሰበሰበውን ታክስ ያላሳወቀ ወይም የሚፈለግበትን ታክስ ያልከፈለ እስከ አምስት አመት ሊቀጣ የሚችል መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 የተደነገገ ሲሆን የንግድ ድርጅት ይህንን አዋጅ በመተላለፍ ለሚፈጸመው ጥፋት የወንጀል ተጠያቂነት የሚኖርበት ስለመሆኑ ከአዋጁ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

12 .በስር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው የንግድ ድርጅት ለሌላ ድርጅት ሠራተኞች ሜጋ ማስታወቂያ ሠራተኞች የከፈለውን ደመወዝና የስልክ ወጭ የንግድ ተግባሩን ሲያከናውን ያወጣው ወጭ መሆኑን በሚገልጽ መንገድ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ሪፖርት በማቅረብ 1997ዓ.ም ትርፍ አግኝቶና ካገኘውም ትርፍ 39,801.32 የንግድ ስራ ትርፍ ገቢ ግብር መክፈል ሲገባው ኪሳራ እንደደረሰበት አድርጎ ሪፖርት ማቅረቡና ይህም ሪፖርት ለሌላ ንግድ ድርጅት ወጭ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ለመሸፈን የወጣ ወጭ እንደ ሕጋዊ ወጭ በማቅረብ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲት የተረጋገጠ መሆኑን እንደዚሁም አንደኛ ተከሳሽ ከ1996 እስከ 2002 ዓ.ም የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ለተጠሪ ያላሳወቀና ገንዘቡንም ገቢ ያላደገረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

13 .አመልካች 1997ዓ.ም አንደኛ ተከሳሽ ትርፍ አግኝቶ እያለ ትርፍ እንዳላገኘና ኪሳራ እንደደረሰበት ሪፖርት በማድረግ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 96 እና አንቀጽ 97 (1) (ሀ) የተመለከቱትን የወንጀል ድርጊቶች ሲፈጽም የአንደኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ የነበረ መሆኑ በተጣራ ማስረጃ ብቻ ሳይሆን አመልካች ባቀረባቸው የመከላከያ ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ያሳያል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ከላይ የጠቀስናቸውን ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመ መሆኑ ከተረጋገጠ ስራ አስኪያጁ በወንጀሉ ተጠያቂ እንደሚሆን በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 102 ንዑስ አንቀጽ 1 ተደንግጓል፡፡ እንደዚሁም አንደኛ ተከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 የተመለከተውን በመተላለፍ ከ1996 ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ባከናወነው ግብይት የሰበሰበውን ተጨማሪ እሴት ታክስ ለተጠሪ ያላሳወቀና ገንዘቡንም ገቢ ያላደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 ድንጋጌ የሚጥስ የወንጀል ተግባር በፈጸመበት ጊዜ አመልካች የአንደኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ እንደነበር በተጣራ ማስረጃ ብቻ ሳይሆን አመልካች ባቀረባቸው የመከላከያ ማስረጃዎች ተረጋግጧል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ወንጀሉን የፈጸመው ከ1996ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በመሆኑ አመልካች የአንደኛ ተከሳሽ ሂሳብ በተጠሪ በሚጣራበት 2003ዓ.ም እኔ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ አልነበርኩም በማለት የሚያቀርበው ክርክር አንደኛ ተከሳሽ በስራ አስኪያጅነት በሚሰራበት ወቅት ለተፈጸመው ወንጀል በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ተጠያቂ መሆኑን የሚያስቀር ባለመሆኑ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

14 .የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከክርክሩ ውጭ እንዲሆን አላደረገም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ በአንደኛ ተከሳሽ ላይ እና በአመልካች ላይ የቀረበውን የወንጀል ክስ እና ማስረጃ ከሰማና የአመልካችን መከላከያ ከመረመረ በኋላ "ስለሆነም ተከሳሹ የዐቃቤ ሕግን ማስረጃ የሚያስተባብል ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ በ1997ዓ.ም 1ኛ ተከሳሽ ባከናወነው የንግድ

እንቅስቃሴ ገቢን አሳውቆ ባለመክፈልና ተከሳሾች አሳሳች መረጃ በመስጠትና ኪሳራ ሪፖርት በማድረግና ከ1996ዓ.ም እስከ 2002 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውንየተጨማሪ እሴት ታክስ የሰበሰቡትን በሙሉ ሪፖርት ባለማድረጋቸው ሁለተኛው ተከሳሽ (አመልካች) በስራ አስኪያጅነታቸው አንደኛ ተከሳሽ ለፈጸመው ድርጊት ተጠያቂ በመሆናቸው ተከሳሾች በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 96 እና አንቀጽ 97 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 49 ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋተኛ ናቸው" በማለት ውሳኔ እንደሰጠ ከስር ፍርድ ቤት ከሰጠው ፍርድ በስምንተኛው ገጽ በአራተኛው ፓራግራፍ በግልጽ ሰፍሯል፡፡

15 ይህም የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ ከላይ በገለጽናቸው አዋጆች የተመለከቱትን የሕግ ድንጋጌዎችና በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመ መሆኑን በማረጋገጥ የጥፋተኛነት ውሳኔ የሰጠ መሆኑንና አንደኛ ተከሳሽ ወንጀሉን በሚፈጽምበት ጊዜ ሁለተኛ ተከሳሽ አመልካች የአንደኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 102 እና የአዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 56 ድንጋጌዎች መሰረት ሜጋ ኪነጥበባት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በስራ አስኪያጅነት ሲመራ በነበረበት ጊዜ በድርጅቱ ለተፈጸመው ወንጀል በኃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን በማረጋገጥ የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች የንግድ ድርጅቱ ወንጀሉን የፈጸመ መሆኑ ሳይረጋገጥ አና ለወንጀሉ ኃላፊ ተብያለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር በመዝገቡ ያለውን እውነታ የሚያንጸባርቅ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ከአመልካች ጋር ለተፈጸመው ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 176025 ታህሳስ 19 ቀን 2004ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በግልጽ የሚታይ ነው፡፡

16 አመልካች የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽን በአግባቡ ሳይጠራ አንደኛ ተከሳሽ በክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን ወይም ጉዳዩ አንደኛ ተከሳሽ በሌለበት እንዲታይ ትእዛዝ ሳይሰጥ የወንጀል ክሱን ሰምቶ የወሰነ መሆኑ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን መከራከሪያ አድርጎ አቅርቧል፡፡ አመልካች ከ 2003ዓ.ም ጀምሮ የአንደኛ ተከሳሽ ስራ አስኪያጅ እንዳልሆነና አንደኛ ተከሳሽንም ወክሎ ክርክር ለማቅረብ እንደማይችል በስር ፍርድ ቤት የገለጸ መሆኑን ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር ተገንዝበናል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ የወንጀል ጉዳይ የታየው የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ አንቀጽ 162 አንቀጽ 167 እና ሌሎች ድንጋጌዎች ከሚደነግጉት ውጭ ነው ብሎ ካለ የስር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ በሌለበት አይቶ የሰጠው ፍርድ እንዲነሳለት ከሚያመለክት በስተቀር አንደኛ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ መወሰኑን አመልካች መከራከሪያ አድርጎ ሊያቀርብ የሚችል አይደለም፡፡ አንደኛ ተከሳሽ በመወከልም አንደኛ ተከሳሽ በሌለበት ታይቶ የተሰጠው ፍርድ እንዲነሳ ለመከራከር የሚያስችለው ውክልና ወይም ስልጣን የለውም ስልጣንም ቢኖረው ክርክሩ መቅረብ የሚገባው በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ሕግ ከአንቀጽ 197 እስከ አንቀጽ 102 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ መሆን የሚገባው በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

17 አንደኛ ተከሳሽ አግባብነት ባላቸው የንግድ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት መፍረሱ ወይም ከሌላ ድርጅት ጋር መቀላቀሉን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ይህም አንደኛ ተከሳሽ ሕጋዊ ህልውና ያለው ድርጅት መሆኑን ያሳያል፡፡ አንደኛ ተከሳሽ በህግ አግባብ ሳይፈርስ ወይም ሌላ ድርጅት ጋር ተቀላቅሎ ህጋዊ ህልውናውን ሳያጣ አንደኛ ተከሳሽ በእውን እንዳይኖር የፈጸመበትን የንግድ ዓላማ የማይፈጽምና ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዳያደግ በማድረግ

በቁሙ ማክሰም የሚቻል መሆኑና አመልካችም አንደኛ ተከሳሽ በህግ አይን የፈረሰ ድርጅት ነው ባይባልም በእውኑ ዓለም የሌለና የከሰመ ድርጅት ነው የሚል መከራከሪያ ያቀረቡ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በመሰረቱ አንድን ድርጅት በቁሙ እንዲከስም በማድረግ ድርጅቱ ህጋዊ ህልውና ኖሮት ተግባራዊ የንግድ እንቅስቃሴ ሲያደርግ በነበረበት ጊዜ ለተፈጸመ ወንጀል የንግድ ድርጅቱንም ሆነ በወቅቱ ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ የነበረውን ሰውና የሌሎች ሰራተኞች የወንጀል ተጠያቂነት ለማስቀረት አይቻለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሕጋዊ ህልውና ያለው ድርጅት ወንጀል እንዳደረገ ተቆጥሮ የሚቀጣው በሃላፊዎቹ ወይም ከሰራተኞች አንዱ ከድርጅቱ ስራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የድርጅቱን ጥቅም በሕገ ወጥ መንገድ ለማራመድ በማሰብ ወይም የድርጅቱን ህጋዊ ግዴታ በመጣስ ወይም ድርጅቱን በመሳሪያነት አላግባብ በመጠቀም በዋና ወንጀል አድራጊነት በአነሳሽነትና በአባሪነት ወንጀል ሲያደርግ መሆኑ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 በግልጽ የተደነገገ መርህ ነው፡፡ አንድ የንግድ ድርጅት የወንጀል ተግባር ከፈጸመና ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ከተረጋገጠ በኂላ ድርጅቱ የወንጀሉን ፍርድ ሊፈጽም የማይችልበት ሁኔታ በቁም እንዲከስም መደረጉ ለወንጀሉ አድርጎት ኃላፊ የሚሆኑትን ሰራተኞችና ኃላፊዎች በወንጀል ከመጠየቅ ነጻ የማያወጣ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ በአመልካች ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) 2 መሰረት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴረል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ)2 መሰረት በድምጽ ብልጫ ጸንቷል፡፡
2. መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት**

## የልዩነት ሐሳብ

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር አምስት የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምጽ ከሰጠው ውሳኔ ባለመስማማት የሚከተለው የልዩነት ሐሳብ አስፍሬአለሁ፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ አንደኛ ተከሳሽ ሜጋ ኪነጥበብ ማዕካል ኃ/የተ/የግል ማህበር 2ኛ ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች በማድረግ ስድስት ክሶች ያቀረበ ሲሆን በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ ገቢን አለማሳወቅ፣ ትርፍ አሳውቆ አለመክፈል፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ አለመክፈል የሚሉ ናቸው፡፡ አመልካች ድርጊቱን ክደው በመከራከራቸው የግራ ቀኙ ማስረጃዎች ተሰምተው ጥፋተኛ ተብሎው የእስራት ቅጣት ተወስኖ የተገደበላቸው ስለመሆኑ ከሥር ፍርድ ቤት መዝገብ መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች በየደረጃው ጉዳዩን በተመለከቱት ፍርድ ቤቶች ያቀረቡት ቅሬታ መሠረታዊ ይዘት በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ጥፋተኛ ሳይባል መቀጣታቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑ የሚያስይ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ አንደኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ እንደተባለ እና ስለ መፍረሱ የቀረበ ማስረጃ አለመኖሩን አመልካች ድርጁቱን ወክለው ባይከራከሩም ለምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ በማቅረብ የተከራከሩ በመሆኑ የተጣበበ መብት የለም የሚል ነው፡፡

በሥር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ሜጋ ኪነጥበብ ማዕከል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ቀርቦ እንዲከራከር በሕጉ አግባብ ጥሪ የተደረገለት ስለመሆኑ ጉዳዩም በሌለበት እንዲታይ ግልጽ ትዕዛዝ የተሰጠ ስለመሆኑ የወሳኔው ይዘት አያሳይም ፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ ሥልጣኑ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው የሜጋ ኪነጥበባት ማዕከል በሕጉ አግባብ እንዳልተጠራ በዚህ ምክንያት መዝገቡ ወደ ሥር ፍርድ ቤት መመለሱ ውጤት እንደሌለው በመግለጹ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ድርጅቶች በሕግ በግልጽ በተመለከተ ጊዜ የወንጀል ተጠያቂነት ያለባቸው ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 34 ተመልክቷል፡፡ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 102 እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285 /1994 አንቀጽ 56(1) እንደተመለከተው ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት የወንጀል ጥፋት ከፈፀመ የድርጅቱ ስራአስኪያጅ ተጠያቂ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዝኛ ትርጉም ``subject to sub-Article (3) where an entity commits an offence every person who is manager of that entity at that time is treated as having committed the offence and is liable penalty under this proclamation`` የሚል ነው፡፡ ከዚህ የህግ ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘት ዓላማና መንፈስ መረዳት የሚቻለው የአንድ ድርጅት ሥራአስኪያጅ ኃላፊ የሚሆነው ድርጅቱ በሕግ አግባብ ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ሲንመጣ ድርጁቱ በህግ አግባብ መጥሪያ የደረሰው ስለመሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ የአሁኑ አመልካችም ድርጅቱ ከለቀቀ ከአንድ ዓመት በኃላ ክስ የተመሰረተባቸው ስለመሆኑ እየተከራከሩ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች የአሁኑ አመልካች ጥፋተኛ ከተባሉ ድርጅቱም ጥፋተኛ ነው በሚል ድምዳሜ ላይ መድረሳቸው ከውሳኔያቸው ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁንና የስር ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ የህግ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ ሕግ አውጪው ከላይ በጠቀሱኩዋቸው አዋጆች ላይ በግልጽ እንዳመለከተው ቅድሚያ መረጋገጥ ያለበት የድርጅት ጥፋት መኖር ያለመኖር ነው፡፡ አንድ ድርጅት ጥፋተኛ ነው ወይስ አይደለም ወደ ሚለው ድምዳሜ ለመድረስም በህጉ የተዘረጋው የሙግት አመራር ሥርዓት በጥብቅ ተግባራት መደረግ ነበረበት፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት ሕጋዊ ሰውነት ያለውና ያልከሰመ መሆን ያለመሆኑን በአግባቡ ሰያጣሩ ጥሪ ቢደረግለትም አይቀርብም በሚል ሰበብ እውነት የማፈለግ ግዴታቸው (truth finding) ወደ ጎን በመተው ሕጉን የዘረጋው የሙግት አመራር ሥርዓት ሳይከተሉ ከውሳኔ ላይ መደረሳቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈጸማቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ድርጅቱ ጥፋተኛ ሳይባል ስራአስኪያጅ ነበሩ የተባሉ የአሁኑ አመልካች በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ በአዋጅ ቁጥር 285 እና 286/1994 የተደነገገው የድርጅት እና ሥራአስኪያጅ የተጠያቂነት አወሳሰን ቅደም ተከተል ያዛባ ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶች ይሁን አብላጫው ድምጽ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የገቢ አዋጆች ስለ ድርጅት እና ሥራአስኪያጅ የወንጀል ተጠያቂነት አወሳሰን ማለትም የድርጅቱ ጥፋተኝነት በቅድሚያ የማረጋገጥ ሕጋዊ ግዴታ ታልፎ አመልካች ጥፋተኛ ናቸው በማለት የሰጡት ውሳኔ የአዋጆች ዓለማና ግብ ያላገነዘበ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት /ሜጋ ኪነጥበባት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በዚህ አገር በንግድ ህግ ተመዝግቦ የሚሰራ ድርጅት ከነበረ ስለ ድርጅቱ ሕጋዊ ሰውነት ያለው መሆን ያለመሆን ከከሰመም መቼና በማን ውሳኔ የሚሉ ነጥቦች ሊጣሩ የሚገባቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ ምክንያቱም አመልካች ድርጅቱ ከመስከረም 5/2002 ጀምሮ የፈረሰ ስለመሆኑ

ሲከራከሩ ተጠሪ በበኩሉ ድርጅቱ አልፈረሰም ተሰውሯል በማለት መልስ አቅርበዋል፡፡ ሕግና ሥርዓት ባለበት አገር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት በእርግጥ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ህያው ድርጅት ከሆነ ከሚመለከታቸው አካላት በማጣራት እውነት የማፈላለግ ሥራ መከናወን ነበረበት፡፡ በሌላ በኩል ድርጅቱ ሜጋ ማስታወቂያ ከተባለው ድርጅት የተዋሃደ/የተቀለቀለ / Amalgamation merge /ስለመሆኑ በክርክር ሂደት ተነስቷል፡፡ ይህ በተመለከተም ሁለቱም ድርጅቶች ተዋህደው ከሆነ መቼ እና በማን ውሳኔ ሰሚነት ተዋሀዱ የሚለው መጣራት ነበረበት፡፡ አመልካች እንደሚሉት በክርክር ጊዜ አግባብነት ያላቸው ሰነዶች ለማግኘት እንደተቸገሩ በተለይም ድርጅቱ ህያው ካልሆነ እና የድርጅቱ ሕጋዊ ሠራሽ የሆነው ድርጅት ወይም ግለሰብ በጉዳዩ ጣልቃ በመግባት ካልተከራከሩ ዞሮዞሮ የአመልካች የመከላከል ሕግ መንግስታዊ መብት ማጣበቡ የማይቀር ነው፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በተጠሪ ምስክሮች መሰቀለኛ ጥያቄ በማቅረብ ስለተከራከሩ የተጣበበ መብት የለም በማለት በውሳኔው ያሳፈረ ቢሆንም ክርክሩ ግለሰባዊ ጉዳይ ሳይሆን የአንድ ድርጅት ጥፋተኛ መሆን ያለመሆን ብሎም የድርጅቱ ሥራአስኪያጅ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትል ጉዳይ በመሆኑ ድርጅቱ እና የአሁኑ አመልካች ፈጸሙት የተባለው የወንጀል ድርጊት ለመከላከል መቅረብ ያለባቸው ሕጋዊ ሰነዶች እና የክርክር ነጥቦች ከድርጅቱ የተያያዙ አይደለም የሚለው ድምዳሜ የህጉን አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የሥር ፍርድ ቤት ይሁን ጉዳዩ በይግባኝ የተመለከተው ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት ህያው ድርጅት ነው ወይስ የከሰመ ድርጅት? የከሰመ ድርጅት ከሆነ መብትና ግዴታው ለማን ተላለፈ? የሚሉትና ተያያዥ ነጥቦች በማጣራት ድርጅቱ ጥፋተኛ ነበር ወይስ አልነበረም? የሚለው በቅድሚያ ውሳኔ መስጠት ይጠበቅባቸው ነበር፡፡

በማጠቃለል በሥር ፍርድ ቤት አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ሜጋ ኪነጥበበት ማዕከል ኃ/የተ የግል ማህበር በቅድሚያ በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎለት ራሱ ወይም ህልውናው የከሰመ ከሆነ መብትና ግዴታው የወረሰው ድርጅት/ተቋም/ ግለሰብ ሳይጣራ እና በአግባቡ ተጣርቶ ጥፋተኛ ሳይባል አመልካች ጥፋተኛ ናቸው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ አይደለም፡፡ በሥር አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ድርጅት ህልውና ካበቃ ወይም መብቱና ግዴታው የተላለፈለት ድርጅት/ግለሰብ ከሌለ በእርግጥ በሥራ አስኪያጅ የወንጀል ተጠያቂነት ያስከትላል ወይ የሚለውም ከወንጀል ቅጣት ዓላማና ግብ መታየት ነበረበት፡፡ ሜጋ ኪነጥበባት ማዕከል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ሜጋ ማስታወቂያ ድርጅት በሕጉ አግባብ ያልተዋሀዱ ከሆነ የወንጀል ተጠያቂነት የሚያስከትለው ውህዳቱን የወሰኑ እና ያስፈጸሙ የየድርጅቱ ባለቤቶች ናቸው ወይስ ሥራ አስኪያጅ ነው ተጠያቂ መሆን ያለበት? የሚለውን በአግባቡ የተጣራ ጉዳዩ አይደለም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባ ነበር በማለት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

**የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡**

**ሩ/ለ**

# ከውል ውጭ ኃላፊነት

የሰ/መ/ቁ. 95267

ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-ናይል ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር ነገረ ፈጅ ይነበብ ደርሰህ-ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ካሣሁን ወንድሙ- ቀረቡ
2. አቶ ግርማ ታጸኖ- ከክርክሩ ውጭ ተደርገዋል
3. ኒያላ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማህበር- ነገረ ፈጅ ዮሴፍ ገብሬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥ~ል፡፡

## ፍ ር ድ

ክርክሩ በተጀመረበት የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች በዚህ መዝገብ አቤቱታውን ያቀረበው በተሽከርካሪዎች ግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰበትን የደንበኛውን ተሽከርካሪ አስጠግኖ ወደ ነበረበት ለመመለስ ያወጣውን ወጪ ለማስተካት ያቀረበውን ክስ ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በ24/04/2004 ዓ.ም.አዘጋጅቶ ባቀረበው ክስ ንብረትነቱ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ሆኖ በአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በመሽከርከር ላይ የነበረ የሰሌዳ ቁጥሩ 3-02598 ደ/ሕ. የሆነ ተሽከርካሪ በሾፌሩ ጥፋት ንብረትነቱ የአድቫንስድ ኢንጂነርስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሆኖ በአመልካች የኢንሹራንስ ሽፋን የተሰጠውን የሰሌዳ ቁጥሩ 3-3277 የሆነ ተሽከርካሪ ገጭቶ ያደረሰበትን ጉዳት አስጠግኖ ወደ ነበረበት ለመመለስ አመልካች ያወጣውን ወጪ ብር 441,213.17 (አራት መቶ አርባ አንድ ሺህ ሁለት መቶ አስራ ሶስት ከአስራ ሰባት) 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንለት ዘንድ የጠየቀ መሆኑን፣1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እንዲሁም ለ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ የመድን ሽፋን የሰጠው እና በተጠሪው ጠያቂነት ወደ ክርክሩ የገባው 3ኛ ተጠሪ ከመቃወሚያ በተጨማሪ በኃላፊነት እና በመጠን ረገድ ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር ማቅረባቸውን፣ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ክስ የቀረበበትን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ውሳኔ መስጠቱን፣በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የተጠሪዎቹ ማስረጃ ሳይሰማ ውሳኔ መሰጠቱ እና የ3ኛ ተጠሪ ኃላፊነትም ተለይቶ አለመወሰኑ ተገቢ አለመሆኑን ገልጾ ውሳኔውን በመዝገብ ቁጥር 51395 በ30/11/2004 ዓ.ም. በመሻር ጉዳዩን በነጥብ የመለሰው መሆኑን፣ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በተመለሰለት መሰረት የተጠሪዎችን ማስረጃ ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን ማስረጃ መዝኖ የሁለቱ ተሽከርካሪዎች ግጭት የደረሰው

በአመልካች ደንበኛ ተሽከርካሪ ሾፌር ስህተት መሆኑ ተረጋግጧል ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረስ ተጠሪዎቹ ለክሱ ኃላፊነት የለባቸውም ሲል በነጻ ያሰናበታቸው መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናቱ ነው፡፡የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የስር ፍርድ ቤት እንደደረሰበት መደምደሚያ ለጉዳቱ መንስኤ ለሆነው ጉዳት የሁለቱም ወገኖች ጥፋት የለም፣የመኪኖች ግጭት ጉዳይ ነው ከተባለ የአሁኑ አመልካች ያቀረበው የጉዳት ካሳ ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2084(2) ድንጋጌ አንጻር ተጠሪዎች ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ ተደርጎ አመልካች ከ1ኛ እና ከ3ኛ ተጠሪዎች ጋር የጽሁፍ ክርክር የተለዋወጡ ሲሆን ለ2ኛ ተጠሪ መጥሪያውን ተከታትሎ ማድረስ ባለመቻሉ አቤቱታውን እንደተወው ተቆጥሮ 2ኛ ተጠሪ ከክርክሩ ውጪ እንዲሆን በ15/08/2006 ዓ.ም.ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የግጭት አደጋው የደረሰው በ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ ሾፌር ጥፋት ምክንያት አይደለም በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተደረሰበት ድምዳሜ እና ይህንን ድምዳሜ መሰረት በማድረግ የተሰጠው ውሳኔ በግራ ቀኙ የቀረበውን አጠቃላይ ክርክርና ማስረጃ ያገናዘበ አይደለም፤የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ ሾፌር ጥፋት አልነበረውም ቢባል እንኳ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2084(1) እና (2) ድንጋጌዎች መሰረት ተጠሪዎቹ ያወጣነውን ወጪ አጋማሽ የመክፈል ግዴታ አለባቸው በማለት መሆኑን የክርክሩ ይዘት ያመለክታል፡፡እንደተባለው ሁለት ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ሲጋጩ እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በየራሱ አንዱ በአንዱ ላይ አደጋ እንዳደረሰ የሚቆጠር ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ በቁጥር 2084 (1) ስር፣የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ባለሀብት ወይም ለአደጋው ኃላፊ የሆነው ሰው በአደጋው ምክንያት ከደረሰው ጠቅላላ ጉዳት ገሚሱን መክፈል የሚገባው ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 2084 (2) ስር እና አደጋው የደረሰው በተለይ ወይም በጠቅላላው በአንደኛው መኪና ነጂ ስህተት መሆኑ በማስረጃ በተገለጸ ጊዜ ግን ከዚህ በተጠቀሱት ሁለቱ ንዑሳን ቁጥሮች የተመለከተው ደንብ የማይጸና ስለመሆኑ በቁጥር 2084 (3) ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ ወገኖች የቀረቡትን የሙያ እና የዓይን ምስክሮች ቃል እንዲሁም የትራፊክ ፕላንን ጨምሮ የቀረቡለትን ሰነዶች አገናዝቦ ከመረመረ እና ከመዘነ በኃላ ተጠሪዎቹ ኃላፊነት የለባቸውም በማለት ውሳኔ የሰጠው አመልካች እንደሚከራከረው ጥፋቱ የ1ኛ ተጠሪ ተሽከርካሪ ሾፌር መሆኑ አልተረጋገጠም በማለት ሳይሆን ይልቁንም የግጭት አደጋው የደረሰው የአሁኑ አመልካች የመድን ሽፋን በሰጠው ተሽከርካሪ ሾፌር ስህተት ነው በማለት መሆኑን የውሳኔው ይዘት በግልጽ ያመለክታል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው ቁጥር 2084 (1) እና (2) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ጉዳቱን የመጋራት ደንብ ተፈጻሚነት የማይኖረው ስለመሆኑ በድንጋጌው ንዑስ ቁጥር (3) ስር በግልጽ የተመለከተ በመሆኑ አመልካች ያወጣውን ወጪ አጋማሽ ተጠሪዎቹ እንዲሸፍኑ መወሰን ነበረበት በማለት አመልካች የሚያቀርበው ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

በሌላ በኩል 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ለቀረበባቸው ክስ በሰጡት መልስ ለጉዳቱ መንስኤ ሁለቱም ተሽከርካሪዎች በመሆናቸው የየራሳችንን ጉዳት እንድንችል መደረግ ይገባዋል በማለት ተከራክረው እያለ አመልካች ያወጣውን ወጪ አጋማሽ እንዲጋሩ ሳይወሰን የቀረው አላግባብ ነው በማለት አመልካች ያቀረበውን የክርክር ነጥብ በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት መልስ ላይ ለጉዳቱ መንስኤ ሁለቱም ተሽከርካሪዎች በመሆናቸው የየራሳችንን ጉዳት እንድንችል መደረግ ይገባዋል በማለት የተከራከሩት በራሳቸው ተሽከርካሪ ላይም በተመሳሳይ ሁኔታ ጉዳት መድረሱን እና ለጥገና ወጪ ማውጣታቸውን ለመግለጽ እንጂ ጥፋቱ በራሳቸው ተሽከርካሪ አሽከርካሪ ነው በሚል  የቀረበባቸውን ክስ በማመን ካለመሆኑም በላይ በመልሳቸው መጨረሻ ላይ ለክሱ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ የተከራከሩ መሆኑን አመልካች አቅርቦ ያያዘው የ1ኛ ተጠሪ መልስ ይዘት የሚያመለክት በመሆኑ እና ቀደም ሲል እንደተገለጸው ግጭቱ የተከሰተው አመልካች የመድን ሽፋን በሰጠው ተሽከርካሪ ሾፌር ስህተት መሆኑ በማስረጃ የተረጋጠ እስከሆነ ድረስ በቁጥር 2084(1) እና (2) ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ጉዳቱን የመጋራት ደንብ ተፈጻሚነት የማይኖረው በመሆኑ አመልካች በዚህ ረገድ ያቀረበው የክርክር ነጥብም ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ከላይ ከተመለከተው አጠቃላይ የክርክሩ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ የሰጠው ፍሬ ነገርን በማጣራት እና ማስረጃን በመመዘን ረገድ በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት መሆኑን ሲሆን ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ማስረጃ የመዘነበት አግባብ ደግሞ በይግባኝ ሰሚው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(3)(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 በአንቀጽ 10 እንደተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ስልጣን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ መርምሮ በማረም የተገደበ በመሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን  የመመዘን ስልጣን የተሰጣቸው የመጀመሪያ ደረጃ እና ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች በዚህ  ረገድ የሰጡት ውሳኔ አግባብነት በዚህ ሰበር ችሎት ሊመረመር የሚችልበት ስርዓት የለም፡፡ በሕግ ረገድ ደግሞ ውሳኔው መሰረታዊ ስሕተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 24449 በ26/07/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 59437 በ23/12/2005 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. እንዲያውቁት የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡

የሰ/መ/ቁ 93772

የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ ሁሴን አመዴ - ጠበቃ ጌታቸው ቅጣው ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1.ኢትዩ ቴሌኮም - ነ/ፈጅ ዘለቀ ሰይፉ ቀረቡ

2 ድርባን ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግ/ማ…ጠበቃ ጋዲሳ ጉታ-ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የኮንስትራክሽን ስራ በኮንትራክተር ሲሰራ ደረሰ ለተባለ የቴሌኮሚኒኬሽን ኬብል መበጠስ ጉዳት የጉዳት ካሳ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽነት፣ በአሁኑ አመልካች ተከሳሽነት እና ለአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብነት በምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና ይዘትም ባጭሩ የሚከተለው ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ በስር ተከሳሽ ላይ ባቀረበው ክስ ተከሳሹ የአመልካች ንብረት በሆነው የአለም አቀፍ ግንኙነት በተሸከመ የኦፕቲካል ፋይበር ኬብል ላይ በሕግ የተጣለበትን ግዴታ በመጣስ ህዳር 30 ቀን 2002 ዓ/ም የብር 123,710.7234፣ ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ደግሞ የብር 374,754.2334 ጉዳት የ2ኛ ተጠሪን ፋብሪካ አጥር ግንባታ ሲያከናውን አድርሷል በሚል በድምሩ ብር 498,465.10(አራት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አራት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከአስር ሳንቲም) ከተለያዩ ወጪዎች ጋር እንዲከፍል ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡ የአሁኑ አመልካችም የሲሚንቶ ፋብሪካ አጥር ግንባታውን ያከናወኑት ከአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ጋር ባደረጉት የግንባታ ውል መሆኑን፣ አሰሪ የሆነው 2ኛ ተጠሪ በሰጣቸው ንድፍ መሰረት ስራውን በማከናውን ላይ እያሉ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳት እንደደረሰና ተገቢውን ጥንቃቄ አድርገው ሲሰሩ ለደረሰው ጉዳት በሕግም ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑን፣ ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ደረሰ ለተባለው ጉዳትም የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ሠራተኛ የሆኑት ከ23 ሜትር በኂላ ቆፍሩ ብለው ምልክት አድርገውላቸው 25.10 ሜትር ርቀት ላይ ሲቆፍሩ ጉዳቱ የደረሰ በመሆኑ ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ወድቅ እንዲሆን ከመከራከራቸው በተጨማሪ 2ኛ ተጠሪ ወደ ክርክሩ እንዲገባም ጥያቄ አቅርቧል፡፡

የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪ በጣልቃ ገብነት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ከተደረገ በኂላ በሰጠው መልስም ለክሱ ኃላፊነት የለብኝም የሚል ሁኖ ለዚሁ መልሱ መሰረት ያደረጋቸው ምክንያቶችም ከአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ጋር ያደረገው የግንባታ ውል ኃላፊነቱን ለ1ኛ ተጠሪ ማስተላለፉንና የግንባታ ፈቃድን ከሚመለከታቸው አካላት አግኝቶ ተገቢውን የፈፀመ መሆኑን የሚገልጹትን ነጥቦችን ነው፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አመልካችንና የአሁኑን 2ኛ ተጠሪ ለክሱ ኃላፊ አድርጎ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ብር 498,465.10(አራት መቶ ዘጠና ስንምት ሺህ አራት መቶ ስልሳ አምስት ብር ከአስር ሳንቲም) ከመስከረም 10 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲሁም ለክርክሩ የወጡትን ወጪና ኪሳራ በአንድነትና በነጠላ ሊከፍሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአሁኑ አመልካችየአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ለአሁኑ 1ኛ ተጠሪ የሚከፈላቸውን የጉዳት ካሳ ገንዘብም ሆነ ወጭና ኪሳራ በሙሉ የአሁኑ አመልካች ለጣልቃ ገብ ሊሸፍኑ እንደሚገባ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የአሁኑ ተጠሪዎች በመልስ ሰጪነት ከተከራከሩ በኂላ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በህዳር 30 ቀን 2002 ዓ/ም ከአመልካች ንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ መሆናቸው በአግባቡ ነው በማለት ሙሉ በሙሉ ያጸናው ሲሆን የታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ጉዳትን በተመለከተ ግን የአሁኑ አመልካች ሰራተኛ ቁፋሮው ከመንገዱ ከሃያ ሶስት ሜትር ርቀት በኂላ መቆፈር እንደሚችል ለአሁኑ አመልካች እስከቦታው ሂዶ በገለጸው መሰረት ቁፋሮው ከመንገዱ ከሃያ አምስት ሜትር ርቀት በላይ ሲከናወን የደረሰ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የ1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ ለጉዳቱ መድረስ አስተዋፅኦ ነበረው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ በዚህ ቀን ደረሰ ከተባለው የብር 374,754.3734 ጉዳት ውስጥ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ለግማሹ ብር 187,377.19(አንድ መቶ ሰማንያ ሰባት ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከአስራ ዘጠኝ ሳንቲም) ኃላፊነት አለበት በማለት ወስኗል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በሁለቱም ቀናት ደረሰ ለተባለው ጉዳት አመልካች ኃላፊነት የለብኝም በማለት በመቃወም ውሳኔውን ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ለደረሰው የንብረት ጉዳት ግማሽ ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ ለጉዳቱ መድረስ አስተዋጽኦ አደረገ የተባለው የ1ኛ ተጠሪ ሠራተኛው መሆኑን ተቀብሎ እያለ ሰራተኛው መስሪያ ቤቱን በመወከል በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ስራውን እንዲያከናውን ስምምነት መግለጽ የሚያስችል የስልጣን ውክልና የለውም ብሎ አመልካች በከፊል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ እንዲሁም አመልካችና 2ኛ ተጠሪ አደረጉ የተባሉት ስምምነት የተተረጎመበት አግባብም የግራ ቀኙን ውል፣እንዲሁም የኮንስትራክሽን መመሪያውን ይዘትና ተፈፃሚነትን ባግባቡ ያላገናዘበ መሆኑን ዘርዝረው አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊነትአለባቸው ተብሎ የወሰነው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሁኖ የተገኘው አመልካች በሁለቱም ቀናት በ1ኛ ተጠሪ ንብረት ላይ

ለደረሱት ጉዳቶች ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ በተሰጠው ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም የሚለው ጭብጥ ሁኖ አግኝቶታል፡፡

በዚህም መሰረት የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ ሁኖ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የብር 498,465.10 የንብረት ጉዳት ካሳ ክስ ያቀረበው ጉዳቱ በተለያዩ ቀናት መድረሱንና በእያንዳንዱ ቀን የደረሰውን የጉዳት መጠን ለይቶ ክስ ያቀረበ ሲሆን የስር ተከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በእያንዳንዱ ቀን ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊ የማይሆኑባቸውን ምክንያቶችን ጠቅሰው የተከራከሩ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ደግሞ ወደ ክርክሩ ጣልቃ እንዲገባ ተደርጎ ከአሁኑ አመልካች ጋር ባደረገው የግንባታ ውልም ሆነ ለጉዳዩ አግባብነት ካላው ሕግ አንጻር በ1ኛ ተጠሪ ንብረት ላይ ደረሰ ለተባለው ጉዳት ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ አመልካችንና 2ኛ ተጠሪን በሁለቱም ቀናት በአመልካች ንብረት ላይ ለደረሱት ጉዳቶች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ አድርጎ ለክሱ መሰረት የሆነውን ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ወስኖባቸዋል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኃላ የስር ፍርድ ቤት በሃላፊነት ላይ የሰጠውን የውሳኔ ክፍል አሻሽሎአል፡፡ ከዚህ ጋር አያይዞም የጉዳት ካሳ መጠኑን ቀንሶ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ለአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው የጉዳት ካሳ መጠን ብር 311,087.91 (ሶስት መቶ አስራ አንድ ሺህ ሰማንያ ሰባት ብር ከዘጠና አንድ ሳንቲም) ነው ሲል ወስኗል፡፡ ይህ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ይዘት የሚያስገነዝበው አመልካች የሕዳር 30 ቀን 2002 ዓ/ም ጉዳትን በ2ኛ ተጠሪ በተሠጣቸው ንድፍ መሰረት ስራውን ሲሰሩ ጉዳት ደርሷል ብለው ያቀርቡት ክርክር በማስረጃ ያለመደገፉን፣ ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ደረሰ ለተባለው ጉዳት ለአመልካች የስራ ትዕዛዝ አስተላለፉ የተባሉት ሰራተኛ ሕጋዊ ውክልና ሳይኖራቸው መሆኑ ተረጋግጦ የተወሰነ መሆኑን ነው፡፡ እንግዲህ ይህ የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ የተያዘው በሕጉ የተሰጣቸውን ስልጣን መሰረት በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና ፍሬ ነገሩን በማጣራት ስለመሆኑ የውሳኔው ይዘት ያሳያል፡፡ በመሆኑም ይኼው የበታች ፍርድ ቤቶች የፍሬ ነገር ማጣራትና የማስረጃ ምዘና ድምዳሜ በዚህ ችሎት የሚለወጥበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው በመሆኑ ይህንኑ የበታች ፍርድ ቤቶችን ድምዳሜ በመያዝ በበታች ፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ በሕጉ አተረጓጎም ወይም አተገባበር ረገድ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖር ያለመኖሩን ተመልክተናል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው አመልካች የግንባታው ባለቤት የሆነው የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ከሚመለከተው የመንግስት አካል በወሰደው የኢንቨስትመንት ቦታ ላይ አጥር ለማጠር ቁፋሮ ሲያካሂድ የ1ኛ ተጠሪ ንብረት የሆነው ፋይበር ኬብል መበጠሱን ነው፡፡ አመልካች በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አጥብቆ የሚከራከረው ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ደረሰ ለተባለ ጉዳት የ1ኛ ተጠሪ ኃላፊነት ነው፣ 2ኛ ተጠሪ ደግሞ የግንባታው ባለቤት ሁኖ በአዋጁ መሰረት ፈቃድ ባለማውጣቱ የደረሰ ጉዳት በመሆኑ አመልካች በውልም ሆነ በሕግ ለጉዳቱ ኃላፊ የሚሆኑበት አግባብ የለም በማለት ነው፡፡ እኛም እነዚህን በአመልካች የቀረቡትን ክርክሮች ሕጋዊ መሆን ያለመሆናቸውን ከቴሌኮሙኒኬሽንና የኤሌትሪክ ሐይል አውታሮችን ደህንነት ለመጠበቅ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 464/1997 እና አግባብነት ካላቸው የፍትሐ ብሔር ህግ ድንጋጌዎች አንጻር መመርመሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሰረቱ አዋጅ ቁጥር 464/1997 በአንቀጽ 3(3) ሥር የፌዴራልና የክልል ከተማ አስተዳደር አካላት የግንባታ ፈቃድ ከመስጠታቸው በፊት የቴሌኮሙኒኬሽን ወይም

የኤሌትሪክ ሀይል አውታር ስለመኖሩ እና ፈቃድ ጠያቂው አካልም ግንባታ ከማካሄዱ በፊት በቴሌኮሙኒኬሽን ወይም በኤሌትሪክ ሀይል አውታር ላይ ጉዳት የማይደርስ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ድንጋጌው በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌትሪክ ሀይል አውታሮች ላይ በግንባታ ወቅት ጉዳት እንዳይደርስ አስቀድሞ እንዲያረጋግጡ ግዴታ የጣለው በፌዴራልና በክልል አስተዳደር አካላት ብቻ ሳይሆን የግንባታ ፈቃድ ጠያቂ ላይ ጭምር ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪውም በዚህ የህግ ድንጋጌ መሰረት በቴሌኮሙኒኬሽን አውታር ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የማድረግና በሕግ የተጣለበትን ኃላፊነት አስቀድሞ የማረጋገጥ ግዴታ በመወጣት ቦታውን ላይ ተገቢው ስራ እንዲሰራ ማድረግ ያለበት መሆኑን የድንጋጌው ይዘት ያስገነዝባል፡፡

በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌትሪክ ሀይል አውታሮች ላይ እያወቀም ሆነ በቸልተኝነት ጉዳት ያደረሰ ሰው የሚቀጣ ስለመሆኑም ተደንግጓል ፡፡ ወደ ፍትሐብሄር ህጉ ስንመለስ አንድ ሰው በራሱ በኩል ምንም የገባው ግዴታ ሳይኖር በራሱ ጥፋት(አስቦ ወይም በቸልተኝነት) በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ኃላፊ እንደሆነ በቁጥር 2027(1) ከተደነገገው መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲሁም በህግ በትክክል ተገልጾ የተመለከተውን ልዩ ድንጋጌ፣ ልዩ ደንብና ሥርዓት የጣሰ ሰው ደግሞ ጥፋተኛ ሊሆን እንደሚገባ በፍ/ህ/ቁ 2035(1) ተመልክቷል፡፡ በአዋጁም ሆነ በፍትሐብሔር ህጉ የተዘረጋው ስርዓት ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን አመልካች በዚህ ችሎት በሕግ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር ሶስት አበይት ምክንያቶችን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይኼውም ታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ደረሰ የተባለው ጉዳት በ1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ስራው ሲከናወን ጉዳቱደርሷል፣ የሕዳር 30 ቀን 2002 ዓ/ም ጉዳትም 2ኛ ተጠሪ የግንባታ ፈቃድ ባላወጣበት ሁኔታ የተከናወነ በመሆኑ ጉዳቱ ሙሉ በሙሉ የሚመለከተው 2ኛውን ተጠሪ ነው፣2ኛ ተጠሪ ግዴታውን በውሉ ለአመልካች ማስተላለፍ አይችልም የሚሉ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ አመልካች ስለታህሳስ 30 ቀን 2002 ዓ/ም ጉዳት የሚያቀርቡት ክርክር የስር ፍርድ ቤቶች ከአረጋገጡት ፍሬ ነገር ውጪ የቀረበ በመሆኑ ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም ለአመልካች የስራ ትዕዛዝ ሰጠ የተባለው የ1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ በሕግ አግባብ ያከናወነው የሰራተኛ ግዴታ ስለመሆኑ ካለመረጋገጡም በላይ አመልካች ራሳቸው ሰራተኛው ሰጠ ካሉት ርቀት ውጪ ሄደው ቁፋሮውን ሊያከናውኑ የቻሉበት ሕጋዊ ምክንያትም በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ ስለመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በግልጽ ያሳያልና፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበው የአመልካች ክርክር የሕግ መሰረት የሌለው ሁኖ አግኝተናል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በአሰሪነቱ ሰራተኛው በሰራው ጥፋት ለሚደርስ ጉዳት ተጠያቂነት የሚኖርበት ሰራተኛው ስራውን በሚሰራበት ጊዜ ጥፋት የሰራ የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2130 ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡ አመልካች የ1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ የሆኑት ግለሰብ የሥራ ተግባሩን ሲያከናውን ጥፋቱ የተፈፀመ መሆኑን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2131/1/ እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2032/1/ መሰረት ሊያረጋገጥ የሚገባው መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2141 ድንጋጌ ይዘት የሚያስገነዝብ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ሰራተኛው የስራ ተግባሩን ሲያከናውን ያደረሰው ጥፋት የሌለ መሆኑን ማስረዳት እንደሚጠበቅበት የድንጋጌዎቹ ይዘት ያስገነዝባል፡፡ ከላይ እንደተገጸው የ1ኛ ተጠሪ ሰራተኛ የሆነው ግለሰብ ለአመልካች ሰጠ የተባለው የስራ መመሪያ ተገቢውን ስራ እንደደንቡ ለማከናወን ተብሎ ስራው ሲሰራ የደረሰ አለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም አመልካች የታህሳስ 20 ቀን 2002 ዓ/ም ጉዳት ኃላፊነቱ የ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የግንባታ ውል ያላቸው መሆኑን ሳይክዱ በውሉ በግንባታው ጊዜ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነቱ የአመልካች ተብሎ ስምምነት መደረጉ በ2ኛው ተጠሪ ላይ አዋጅ ቁጥር 464/97 አንቀጽ 3(3) ድንጋጌ የጣለውን ግዴታ በግለሰቦች ስምምነት እንደመለወጥ የሚቆጥር ነው በማለት ተራክረዋል፡፡ ሆኖም አዋጅ ቁጥር 464/97 አንቀጽ 3(3) ተጠሪ የግንባታው ባለቤት በመሆኑ ምክንያት ግንባታውን ከማከናወኑ በፊት በቴሌኮሚኒኬሽን ወይም በኤሌትሪክ ሀይል አውታር ላይ ጉዳት የማይደርስ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት የሚያሳይ ቢሆንም ግንባታው የተከናወነው በሕግ አግባብ በተቋቋመ የአመልካችና የ2ኛ ተጠሪ ስምምነት መሰረት በአመልካች ስራ ተቋራጭነት ነው፡፡ አመልካች በስራ ተቋራጭነቱ ግንባታውን የሚያከናውን ከሆነ ደግሞ ጉዳቱ እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡ በአመልካችና በ2ኛ ተጠሪ ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ/ም የተደረገው የግንባታ ውሉም በአንቀጽ 12.1.5. ሀ እና 12.1.6 ስር አመልካች ግንባታ ከማከናወኑ በፊት ከመብራት ኃይል ባለስልጣናትና ከ1ኛ ተጠሪ ፈቃድ መውጣት እንዳለበት ግራ ቀኙ መስማማታቸውን፣ በውሉ በግንባታው ጊዜ ተገቢውን ጥንቃቄ ለማድረግም አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የተስማማ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ አመልካች ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የሕዝብ መጠቀሚያ የሆነ ንብረት ኬብል እንደማይነካ፣ እንክብካቤ እንደሚደረግለት፣ ንብረቱ ያለባለቤቱ ፈቃድ በምንም ሁኔታ እንደማይነካ፣ በንብረቱ ላይ ምንም አይነት ጉዳት ቢደርስ ተጠያቂው ኮንትራክተሩ ስለመሆኑም ስምምነቱ ያስገነዝባል፡፡ እንዲሁም የቁፋሮ ስራ ሲካሄድ ኬብሉን ሊነካ ስለሚችል የ1ኛ ተጠሪን ፈቃድ አመልካች ማግኘት እንደአለበት፣ ኬብሉ ላይ ጉዳት እንዳይደረስ ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነትም የአመልካቹ መሆኑንና ማንኛውም ጉዳት ከደረሰ ተጠያቂ ኮንትራክሩ ስለመሆኑም የግራ ቀኙ የግንባታ ውል ስምምነት ያስረዳል፡፡

አመልካች ይህን የግራ ቀኙን የሥምምነት ይዘት መኖሩንና በነፃ ሐሳቡና ፈቃዱ መፈረሙን ሳይክድ ስምምነቱ ሕገ ወጥ ነው በሚል ያቀረበው ክርክር የአዋጅ ቁጥር 464/97 አንቀጽ 3(3) ድንጋጌን ሙሉ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ የግንባታው ባለቤት በቴሌኮሚኒኬሽን ወይም በኤሌትሪክ ሀይል አውታር ላይ ጉዳት የማይደርስ መሆኑን ማረጋገጥ እንዳለበት የሚያሳይ ከመሆኑ ውጪ ይኼው ግዴታ ግንባታውን ለሚያከውነው የሥራ ተቋራጭ በስምምነት እንዳይተላለፍ ግልፅ ክልከላ የሚያስቀምጥ አይደለም፡፡ የድንጋጌው መሰረታዊ አላማም የሕዝብ መጠቀሚያ የሆነ ንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደረስ ግንባታ ሲከናወን ሊወሰዱ የሚገባቸውን ቅድመ ጥንቃቄዎችንና ጥንቃቄውን ሊያደርጉ የሚገባቸው ወገኖች የትኞቹ እንደሆነ የሚያመላክትና ጥንቃቄ ባለመደረጉ በንብረቱ ላይ ለሚደረስ ጉዳት ደግሞ ካሳ ሊከፍል የሚችልበት አግባብ መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 464/97 የግንባታው ባለቤት ግንባታውን ለሚያከናውነው የስራ ተቋራጭ ግንባታው ሲከናወን በሕጉ የተጣሉበትን ፍትሐ ብሔራዊ ግዴታዎች ለስራ ተቋራጩ የሚያስተላልፍ ስምምነት አድርጎ ቢገኝ ሕጉ ስምምነቱን ጥበቃ የማያደርግበት ምክንያት የሌለ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1675፣ 1716 እና 1731 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ጋር አጣምረን በማየት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም 2ኛ ተጠሪ ግዴታውን ለአመልካች በስምምነት ማስተላለፉ ተቀባይነት ያለው ሲሆን ጉዳቱ በ2ኛ ተጠሪ ወይም ሰራተኛ ወይም ወኪሉ ስለመድረሱም እንዲሁም አመልካች ጉዳቱን ለመከላከል በማይችልበት ሁኔታ የደረሰ መሆኑም በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ ሐምሌ 09 ቀን 2001 ዓ/ም በአደረጉት የግንባታ ውል የውሉ አካል በሆነው በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በወጣው መመሪያ (Standard Conditions of

Contract for Construction of Civil Work Project) አንቀጽ 22 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መሰረት አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ የማይሆኑበት ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ያደረጓቸው በሕጉ አግባብ ነው ከሚባል በስተቀር ውሳኔያቸው የሚነቀፍበትን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ስላላገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. በምስራቅ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር1914 መስከረም 10 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 32796 ሰኔ 03 ቀን 2005 ዓ/ም ተሻሽሎ የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካችን ለጉዳቱ ኃላፊ አድርገው በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::***

***ት/ጌ***

የሰ/መ/ቁ. 95751

መስከረም 27 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

መኰንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ወ/ሮ እመቤት መኰንን - ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ መሰረት አስናቀ

2. ግሎባል ኢንሹራንስ ኩባንያ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ ሲሆኑ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪ ከሳሽ 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ ከሳሽ በቀረቡት ክስ ባለቤቴ ሟች ወንደሰን ከፍያለው በተከሳሽ መኪና የታርጋ ቁጥሩ 323459 በሆነው ላይ በአሽከርካሪነት ተቀጥሮ በወር 1000 እየተከፈለው ሲሰራ በደረሰው የመኪና አደጋ ህይወቱ አልፏል በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 110/1/ ለከሳሽ እና የሟች ልጅ ለሆነው (ዳግም ወንድወሰን) ጭምር በድርጅታችን 60,000 (ስልሣ ሺ) ይከፈለኝ በተጨማሪም የጠበቃ አበል 10% እና ውጪ ኪሣራ ይከፈለኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም በሰጡት መልስ ተጠቃሹ መኪና የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው መሆኑን በመግለፅ ግሎባል ኢንሹራንስ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር በጠየቁት መሠረት ይኸው አካል ወደ ክርክሩ በመግባት እስከ 60,000 ብር ድረስ ሽፋን መስጠቱን በመጥቀስ ከውላቸው ውጭ የመክፈል ኃላፊነት የሌለበት መሆኑን ገልፆ ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን ያየው የወረዳው ፍ/ቤት ግሎባል ኢንሹራንስ በሰጠው ሽፋን ልክ ይክፈል፡፡ በወቅቱ ባለመክፈሉ ምክንያት ለደረሰው ወጪና ኪሣራ እና የጠበቃ አበል ይክፈል በማለት ወሰነ፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ለደረሰው ጉዳት ይከፈል የተባለውን 60,000 በማጽናት የጠበቃ አበል፣ የወጪና ክሣራ አስመልክቶ ሊከፍል አይገባም በማለት አሻሽሎ አፀና በመጨረሻም 1ኛ ተጠሪ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ቅሬታዋን በማቅረብ የሰበር ሰሚውም ሽፋን ከተሰጠው በላይ የአሁን 2ኛ ተጠሪ /ግሎባል/ ሊከፍል አይገባም ከሽፋኑ በላይ የሆነውን የአሁን አመልካች ተተክተው ሊከፍሉ ይገባል ሲል አሻሽሎ አፅንቷል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታም ይህንኑ የሰበር ውሣኔ ለማሳረም ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ 2ኛ ተጠሪ (ግሎባል ኢንሹራንስ) ለደረሰ ጉዳት ተተክቶ ሊከፍልእና በውላችን መሠረት ግዴታውን ለመወጣት ተስማምቷል (ውል ገብቷል) ይሁን እንጂ 2ኛ ተጠሪ በፍርድ ካልተገደድኩ በማለት በወቅቱ ግዴታውን ባለመወጣቱ ለቀረበዉ ክስ ሽፋንከሰጠው በላይ ልገደድ አይገባውም ተብሎ አመልካች የወጪ ኪሣራና የጠበቃ አበል ትክፈል ተብሎ መወሰኑ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ጠይቀዋል፡፡

በመሆኑም የግራ ቀኙ ለአመልካች አቤቱታ መልስ በፅሑፍ በማቅረብ ክርክራቸውን አድርገዋል፡፡

በዚሁ መሠረት 2ኛ ተጠሪ ለአመልካች ከሰጠው ሽፋን በላይ የወጪ ኪሣራ እና የጠበቃ አበል ሊከፍል አይገባም ተብሎ አመልካች እንዲከፍሉ የመወሰኑን አግባብነት በጭብጥነት ተይዞ ቀርቧል፡፡

ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካለው ህግ አኳያ መርምረናል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰውን ይመስላል፡፡ እንግዲህ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው የሥር ከሳሽ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የሆኑት በባለቤታቸው ላይ በደረሰው የሞት አደጋ ምክንያት የአዋጅ 377/96 አንቀጽ 110(2) ሀ,ለ መሠረት 60,000 ብር እንድከፍላቸው በአሁኑ አመልካች ላይ ክስ በማቅረባቸው ምክንያት የአሁን 2ኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 43 መሠረት ወደ ክርክሩ እንድገባ ተደርጐ ለደንበኛው በሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን መሠረት 60,000 ብር እና የጠበቃ አበል 10% እና የወጪ ኪሣራ 1000 ብር እንዲከፍል በመወሰኑና በየደረጃው ባሉት የክልሉ ፍ/ቤቶች እያዩት የክልሉ ሰበር ሰሚ ደረሶ ግሎባል ኢንሹራንስ ከሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን በላይ የጠበቃ እና የወጪ ኪሣራ ልከፍል አይገባም የአሁን አመልካች ኢንሹራንስ ከከፈለው በላይ ያለውን 8000 ብር ይክፈሉ በመባሉ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የክልሉ ሰበር አመልካች ሊከፍሉ ይገባል ሲል የሠጠው የአሁን 2ኛ ተጠሪ (ግሎባል ኢንሹራንስ የንግድ ህጉን አንቀጽ 665(2) መሠረት ግዴታው ከውላችን ላይ ካለው የሽፋን መጠን ልበልጥ አይገባውም የሚለውን ክርክር በመቀበል መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ እንግዲህ የግራ ቀኙ መብትና ግዴታ የሚመነጨው በመሀከላቸው ከተቋቋመው ውል መሆኑ ይህ ችሎትም የሚቀበለው ጉዳይ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በተያዘው ጉዳይ የአመልካች ደንበኛ (ግሎባል ኢንሹራንስ) በአመልካች መኪና በደረሰው የሞት አደጋ በወቅቱ አግባብነት ያለውን ክፍያ ባለመፈፀሙ ምክንያት የአሁን 1ኛ ተጠሪ የመኪናውን ባለቤት የሆኑትን አመልካች ለመክሰስ ተገደዋል፡፡ ስለሆነም ለተለያዩ (ላልታሰበ) ወጪ መዳረጋቸው ያልተካደና የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ በመሆኑም ግሎባል ኢንሹራንስ ምንም እንኳ የሰጠው የኢንሹራንስ ሽፋን የተገለፀ ቢሆንም ከውል የመነጨውን ግዴታውን በወቅቱ ባለመወጣቱ ለተከሰተው ተጨማሪ ወጪ የአሁን አመልካች የሚቀጡበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የሞት ካሣውን የገንዘብ መጠን 60,000 ብር ላይ የጠበቃ እና የወጪ ኪሣራውን ግሎባል ኢንሹራንስ ሊከፍል የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ባጠቃላይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ውሳኔዎችን በማሻሻል ከ60,000 ብር በላይ የተጠየቀውን ተጨማሪ ወጪ አመልካች ሊከፍሉ ይገባል ማለቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ.63103 በቀን 27/3/05 የልዩ ዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.15437 በ29/08/05 እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሠበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 164154 በቀን 23/03/2006 የሰጡት ውሣኔዎች ተሻሽሎ ፀንቷል፡፡
2. የጠበቃ አበል እና የወጪ ኪሣራን ግሎባል ኢንሹራንስ /8000/ብር ለ 1ኛ ተጠሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡

የሰበሩን ክርክር አስመልክቶ ግራ ቀኙ የወጪ ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ. 97683

መጋቢት 18 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አክበር አሊ ካምሩዲን ኩባንያ

ተጠሪዎች ፡- 1) የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ

2) የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የቀጠና 4 ጽ/ቤት

3) በመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የአ/አ ቅ/ጽ ቤት

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ የቤት ቁ.868 እና 872 ሁከት በመፍጠር በመያዝ 2ኛ ተጠሪ በቤት ውስጥ የነበሩትን ልዩ ልዩ ዕቃዎች እና ሰነዶች በ3ኛ ተጠሪ መጋዘን የተቀመጠ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ዕቃውን እንዲመልስ ቢጠየቅ ለመመለስ ፍቃደኛ አልሆነም በተጨማሪም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የአመልካችን ቤት ለተለያዩ ግለሰቦች እያከራዩ ብር 149,294,00 (አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ ዘጠና አራት ብር) ተጠቅመውበታል፡፡ አመልካች ቤቱን ስረከብ 5000 ብር ወጪ አድርጌያለሁ ፡፡1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ቤቱን አከራይተው አለአግባብ የበለጸጉበትን እና ቤቱን ለማሳደስ ያወጣሁትን ወጪ በድምሩ 154,294,00 (አንድ መቶ ሀምሳ አራት ሺ ሁለት መቶ ዘጠና አራት ብር) የስር 4ኛ፣5ኛ ፣6ኛ ተከሳሾች ጭምር የአሁን ተጠሪዎች የአመልካችን ንብረት ይመልሱ ፣ካልሆነ ግምቱን ብር 124,786.(አንድ መቶ ሀያ አራት ሺ ሰባት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር) እንዲከፍሉኝ ባጠቃላይ ተጠሪዎች 279,080.00(ሁለት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺ ሰማንያ ብር) ከእነወለዱ እንዲከፍሉ፣ወጪና ኪሳራ እንዲተኩ ተብሎ ይወሰንልኝ ሲሉ ጠይቀዋል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በማየት የስር 4ኛ፣5ኛ እና 6ኛ ተከሳሾች ከክሱ በማሰናበት ከ1ኛ እስከ 3ኛ ያሉት ተጠሪዎች በሰጡት መልስ አመልካች ተጠሪዎች ያለአግባብ የበለጸጉበትን ኪራይ ገንዘብ ይከፈለኝ በማለት መጠየቅ አይችሉም መጠየቅ ቢችሉም በመንግስት እጅ የቆየን ንብረት የሚጠየቅ ጉዳትም ሆነ ኪራይ የለም ተጠሪ ንብረት ተረክቧል ቢባል እንኳ ንብረቶቹ ያልተመዘገቡና እርጅና ያልተቀነሰ እንዲሆን ቁሳቁሶቹን በመጋዘን ለማስቀመጥ የፈጀው ጊዜ ከቀረበው ዋጋ በላይ ነው ሌላው አመልካች 5000 ብር ወጪ አደረግኩ የሚሉት ቤቱን ለማበላሽታችን ባለ ማስረዳታቸው ጥያቄው

ባጠቃላይ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል ። ጉዳዩን የተመለከተው ፍርድ ቤትም ግራቀኙን በማከራከር አመልካች ያቀረቡትን የታጣ ገቢና የኪራይ ጥቅም አስመልክቶ በአዋጅ ቁ.192/92 በአንቀጽ 3 ላይ በመንግስት እጅ በቆየበት ጊዜ ለታጣ ጥቅም(ገቢ) ማናቸውም የጉዳት ካሳ መጠየቅ እንደማይቻል የሚደነግግ በመሆኑ የተጠየቀው የቤት ኪራይ ይከፈለኝ በማለት አመልካች የጠየቁትን ዳኝነት ውድቅ በማድረግ የንብረትን ጥያቄ በተመለከተ ተጠሪ እርጅናቸው አልተቀነሰም በማለት ተከራክረዋል። ይህ ደግሞ የአመልካችን የንብረት መጠየቅ መብት አያስቀረውም።ሌላው አመልካች ቤቱን ቀለም ለማስቀባት አወጣሁት የሚሉት 5000 ብር ተጠሪዎ በቤቱ ላይ ጉዳት ያድርሱ ወይም በራሱ ጊዜ ቀለም የፈለገ ስለመሆኑ የሚያሳይ አይደለም በማለት አልፎታል።

በአጠቃላይ ንብረትን በተመለከተ በተጠሪ ተዘርዝረው የቀረቡትን የንብረት በአይነቶች እነዲያስረክቡ ካልሆነ ግምቱን 124,786.000(አንድ መቶ ሀያ አራት ሺ ሰባት መቶ ሰማኒያ ስድስት ብር) ከነወለዱ ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ይክፈል በማለት ወስኗል። በቀጣይነት ጉዳዩን ያየው ከፍተኛው ፍርድ ቤትም መዝገቡን በመመርመር ክርክር የተነሳበት ቤት በተመለከተ የተወረሰ አይደለም ከህግ ውጭ ተይዟል በሚል ምክንያት ሁከት ይወገድ ተብሎ አመልካች ቤታቸውን የተረከቡ መሆኑን የበፊት መዝገብ ያመላክታል ይህ ከሆነ ደግሞ የአዋጅ ቁጥር 193/92 አንቀጽ 7/3 ከአዋጅ ውጭ በመንግስት እጅ የቆየ ንብረት ለታጣ ገቢ ወይም ለደረሰ ጉዳት ካሳ ክፍያ መጠየቅ አይችልም ስለሚል በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም ። ንብረትን አስመልክቶ ግምቱን ወይም በአይነት ያስረክቡ የሚለው የውሳኔ ክፍልም ስህተት የለበትም በማለት ባጠቃላይ አጽንቶታል።

የአመልካች አቤቱታም የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ ለማስለወጥ ነው በመሆኑም አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸውን ሲገልጹ፡- የአመልካች ጥያቄ ተጠሪዎች ቤቱን ሁከት በመፍጠር ይዘው አከራይተው የተቀበሉትን ገንዘብ ሊከፍሉኝ ይገባል የሚል ሆኖ ሳለ ለአዋጅ ቁጥር 193/92 የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት ሊከፈልህ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ሊታረም የሚገባው ነው። ተጠቃሹ አዋጅ ቁ.193/92 የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ለሚያስተናግደው ክርክር የወጣን ወጪን እንጂ በፍርድ ቤት ክስ ቀርቦበት ውሳኔያገኘ አይነት ባለመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል በአጠቃላይ መንግስት (ተጠሪ) ማከራየታቸውን ባልካዱበት የሰበሰቡትን ገንዘብ ሊመልሱ አይገባም መባሉና ብር 5000 ጥያቄ ውድቅ መደረጉም መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት አመልክቷል።

በዚህም መሰረት ችሎቱም የአዋጅ ቁጥር 193/92 ተጠቅሶ ተጠሪ የአመልካችን ቤት ሁከት በመፍጠር ይዞ አከራይቶ እየተጠቀመበት ሊመልሱ አይገባም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ የግራቀኙን በጹሁፍ በማከራከር መልስ እና የመልስ መልስ በማቀባበል አከራክሯል።

ተጠሪዎች በሰበር መልሱ የሚሉት በአዋጅ 47/67 የተወረሰ ቤት አይደለም ሁከት ፈጥራችው የያዛችሁት ነው ተብሎ ተወስኖ የነበረ መሆኑ የተረጋገጠ ነው። ስለዚህ መንግስት በእጁ ይዞ ሲያስተዳድር በነበረበት ጊዜ አመልካች ያጣውን ገቢ ወይም ጥቅም በአዋጁ ቁጥር 193/92 አንቀጽ 3 መሰረት ሊጠይቅ አይችልም ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ አይደለም ሌላው በስር ፍርድ ቤት ሁከት ፈጥሮ መያዝና ወርሶ መያዝ አንድ ናቸው አላለም ስለዚህ በዚህ ረገድ የተነሳው ክርክር ተቀባይነት የለውም። ባጠቃላይ ተጠቃሹ አዋጅ በአግባቡ የተተረጎመ በመሆኑ የአመልካች

ጥያቄዬ  አግባብነት የለውም፡፡ ሌላው አመልካች ለእድሳት አወጣሁ የሚሉት 5000 ብር(አምስት ሺ) ብር ውድቅ መደረጉ የሚነቀፍ ባለመሆኑ የስር ውሳኔ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊጸና የሚገባው ነው በማለት ተከራክረዋል አመልካች በበኩሉ የስር ክርክሩን በማጠናከር ተጠሪዎች ለ 11 አመታት ቤቶቹን አከራይተው የተጠቀሙበትን እና ያሳደስኩበትን ወጪ ነው የጠየቅኩት እንጂ የጉዳት ካሳ ከገንዘባቸው ክፈሉኝ የሚል ክስ የቀረበበት ሁኔታ የለም ስለዚህ ጉዳይ በማይመለከተው አዋጅ ቁ.193/92 ተጠቅሶ ገንዘብህን ሊከፈልህ አይገባም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡
በአጠቃላይ የክርክሩ አመጠጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰውን ይመስላል፡፡ እኛም የግራቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካለው የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል ፡፡ በመሆኑም ከተያዘው ጭብጥ አንጻር የክርክሩን አመጣጥ እንዳየነው የአመልካች ጥያቄ የነበረው ተጠሪዎች ሁከት ፈጥረው የያዙትን ቤት ለቀው ሁከት ይወገድ በመባሉ ለቀዋልና ያለአግባብ ይዘው በነበሩበት ወቅት ለግለሰቦች ቤቱን በማከራየት የሰበሰቡትን ገንዘብ ይመልሱልኝ በውስጡ የነበረውን ንብረት እና ያሳደስኩበትን ይተኩልኝ የሚል መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት የሚቻል ነው፡፡
እንግዲህ በተያዘው ጉዳይ ያከራከረው ተጠሪ አዋጅቁጥር 193/92 ጠቅሶ በመንግስት የቆየን ንብረት ጥቅም ወይም ጉዳት መጠየቅ ስለማይቻል ልንጠየቅ አይገባም በማለቱ እና የስር ፍርድ ቤቶችም በዚህ ረገድ የቀረበውን የተጠሪን መከራከሪያ በመቀበል በተጠቃሹ አዋጅ መሰረት አመልካች መጠየቅ አይገባውም በማለት በመወሰናቸው እና የእድሳት ገንዘቡን ውድቅ በማድረጋቸው ነው፤ይህ ችሎትም አመልካች በተጠቀሰው አዋጅ መሰረት በኪራይ ተጠሪዎች የሰበሰቡትን ገንዘብ ሊመልሱ ይገባል? ወይስ በተጠቃሹ አዋጅ መሰረት መክፈል የለበትም? የሚለው ነጥብ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ሆኖ አግኝቷል፡፡ በመሆኑምከስር ክርክር እንደተገነዘብነው ተጠሪ ያልተወረሰ ቤት በመያዙ ምክንያት በፍርድ ሀይል ሁከት መፍጠሩ ተረጋግጦ ቤቱን መልቀቁ የተረጋገጠና በግራቀኙ ያልተካደ ነው በተጨማሪም ተጠሪም ተጠቃሹን ቤት አላከራየሁም በማለት የተከራከረው ነገር የለም በስር ፍርድ ቤቶች የፍርድ ሀተታም ቢሆን ቤቱ አልተከራየም በሚል የተጠቀሰ ነገር የለም ፡፡ በመሆኑም መከራየቱ ያላከራከረ ፍሬ ነገር በመሆኑ በዚህ ረገድ ተጠሪም የዚህ ችሎት መከራከሪያው አላደረገም ፡፡ ይልቁንም የተጠየቀውን ገንዘብ ልንከፍል አንገደድም የሚል መሆኑን አጉልቶ የሚከራከረው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ከተጠቃሹ አዋጅ ቁ.193/92 ድንጋጌ በመንግስት እጅ በቆዬ ንብረት ለታጣ ገቢ ወይም ለደረሰ ማንኛውም ጉዳት ካሳ ክፍያ መጠየቅ አይቻልም የሚል ነው፡፡ እንግዲህ ከፍ ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው ቤቱ በተጠሪ በመያዙ ብቻ ሊያገኙ የነበሩትን ጥቅም በማጣታቸው የደረሰባቸውን ካሳ ከምንም ተነስቶ ተጠሪ እንዲከፈላቸው ሳይሆን በህገወጥ መንገድ ቤቱን ይዞ በእውነቱ ሲያከራየው የነበረውን እና ቤታቸው የፈጠረላቸውን የራሳቸውን ገንዘብ እንጂ ቤቱ ተወርሶ ተይዞ በመቆየቱ በካሳ መልክ ከመንግስት የሚከፈላቸው ማካካሻ አይደለም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ያልተወረሰ ቤት በህገወጥ መንገድ በመያዝ የበለጸገበትንና አላከራየሁም በሚል ያላስተባበለውን የኪራይ ገንዘብ ለመክፈል አልገደድም ማለቱ እና ፍርድ ቤቶቹም ተጠሪዎች ያቀረቡትን መቀበላቸው የአዋጁን አላማ እና ሊያሳካ የፈለገውን ግብ ያገናዘበ አይደለም አዋጅ ቁጥር 193/92 ለዚህ ጉዳይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የለም ፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች ቤቱን ይዘው ለሰበሰቡት ኪራይ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2162 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ኃላፊ ሊሆኑ ይገባል ብለናል ፡፡ ይህን ካልን በስር ፍርድቤት ተጠሪዎች በምን ያህል እንዳከራዩ፤ቤቱ ለስንት አመታት እንደተከራዬ ጭብጥ ተይዞና በማስረጃ ተለይቶ ክርክር

ያልተደረገበት በመሆኑ በዚህ ዙሪያ ያሉት ነጥቦች ተጣርተው ሊወሰኑ የሚገባቸው በመሆኑ ጉዳዩን ወደ ስር ፍርድ ቤት መመለሱ ስነ ስርዓታዊ ሁኖ አግኝተናል ፡፡

ሌላው የአመልካች ቅሬታ ቤቱ የታደሰበትን 5000 ብር አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ሊከፍል አይገባም ሲሉ የሰጡትን ውሳኔ ተገቢ አይደለም ብለው አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገሩን አጣርተውና ማስረጃውን መዝነው ውድቅ ያደረጉት ስለሆነ ይህ ችሎት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕግ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ከተሰጠው ስልጣን አንፃር የሚታይ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

በአጠቃላይ የፌዴራል የመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 193/92 መሰረት በማድረግ በመንግስት እጅ ለቆዬ ንብረት ተጠሪዎች የሰበሰቡትን ኪራይ ሊከፍሉ አይገባም በማለት የደረሱበት ድምዳሜ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል ፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥተዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 175802 በቀን 04/08/2004 ዓ/ም እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት በ125972 በቀን 25/03/2006 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
   - አመልካች ያቀረቡት የ 5000 ብር የእድሣት ክፍያ እና ንብረትን አስመልክቶ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪዎች ከአከራካሪው ቤት ላይ የሰበሰቡትን የኪራይ ገንዘብ የመመለስ ሀላፊነት አለባቸው ብለናል ፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አከራካሪው ቤት በምን ያህል የኪራይ ገንዘብ ሲከራይ እንደነበር ፤ እና ከመቼ ጀምሮ ሲከራይ እንደነበር በጭብጥነት ይዞ የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን በመስማትና እና አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነም ፍርድቤቱ በራሱ አነሳሽነት በሚያስቀርባቸው ማስረጃዎች አጣርቶ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.343(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል ፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የግራቀኙ የወጪኪሳራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ውሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

ት/ጌ                    የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

# ባንክና ኢንሹራንስ

ሰ/መ/ቁ 96309

መስከረም 27 ቀን 2006 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካች፡- ዳሽን ባንክ አ/ማ - ነ/ፈጅ ሠለሞን አያኖ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አበባየሁ ግርማ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታቸው የቀረበው የፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 189176 የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ በኮ/መ/ቁ/132422 ህዳር 23 ቀን 2006 ዓ.ም ማፅናቱን በመቃወም ነው፡፡ ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

በሥር ከሳሽ የነበሩት የአሁን ተጠሪ የሥር ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በባንኩ ደንበኛ ሆነው በማጠራቀሚያ ሂሳብ ቁጥር 50100055 02016 ገንዘብ በባንኩ ተቀማጭ አድርገው የቁጠባ ሂሳቡን በኤ.ቲ.ኤም ካርድ ሲያንቀሳቅሱ ከቆዩ በኃላ የኤቲ.ኤም ካርዱ ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም የጠፋ በመሆኑ ለባንኩ ጥር 25/2003 ዓ.ም በፅሑፍ ያሳወቁ ቢሆንም ባንኩ ሂሳቡን መዝጋት እያለበት ባለመዝጋቱ ሪፖርት ከተደረገበት ከ25/5/2003 ዓ.ም እስከ 09/6/2003 ዓ.ም ድረስ ለማይታወቁ 3ኛ ወገኖች 40,300.00 (አርባ ሺህ ሶስት መቶ) ወጪ ሆኖ የተከፈለ በመሆኑ ይህን ገንዘብ ከነወለዱ ወጪና ኪሣራ ጋር ይከፈለኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሳሽ በሠጠው መልስ ካርዱ የጠፋ መሆኑን ማሳወቃቸውን ሳይካድ ነገር ግን የጠፋ መሆኑን ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን በባንኩ አሠራር መሠረት ሂሳቡ እንዲዘጋ የመጠየቅ ግዴታ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ ግራ ቀኙ በገቡት ውል መሠረት የሚስጥር ቁጥሩን ለሌላ ወገን እንዳያሳውቁ ግዴታ ያለባቸው በመሆኑና የሚስጥር ቁጥሩ ካልታወቀ ደግሞ ገንዘቡ ወጭ ሊሆን የማይቻል በመሆኑ እንዲሁም የሂሳብ ይዘጋልኝ ጥያቄ ባልቀረበበት ሁኔታ ተከሳሽ ሂሳብ ሊዘጋ የማይችል በመሆኑ ላቀረበው ክስ ኃላፊነት እንደሌለበት በመግለፅ መልስ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩ በቅድሚያ የተመለከተው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ከሳሽ እና ተከሳሽ በገቡት የካርድ ክፍያ አገልግሎት ውል አንቀፅ 2(2) መሠረት ካርዱ መጥፋቱን በጽሁፍ ከማሳወቁ በፊት ለተደረገ ማንኛውም የክፍያ ትዕዛዝ ባለካርዱ ኃላፊነት እንዳለበት የሚያመለክት በመሆኑና የዚህ የውል ክፍል ተቃርኖ ትርጉም ባለካርዱ በፅሑፍ ካሳወቀ በኃላ በተደረገ የክፍያ ትዕዛዝ ባንኩ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ፤ የውሉ ድንጋጌዎች የመብት እና ግዴታ ዝርዝር ውስጥ ኃላፊነት ለመውሰድ ባለካርዱ ሂሳብ እንዲዘጋለት ማመልከት እንዳለበት ያልተካተተ በመሆኑ ከሳሽ ካርዱ መጥፋቱን ለባንኩ ባሳወቀበት እለት ባንኩ ባዘጋጀው ፎርም ላይ የሚስጥር ቁጥሩን መፃፉ የታመነ በመሆኑ የካርዱን የሚስጥር ቁጥር የተከሳሽ ሰራተኞች በቀላሉ የማያውቁበት ምክንያት ባለመኖሩ የተከሣሽ መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም ስለሆነም የክሱን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል በማለት ተወስኗል፡፡

የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ እና ተጨማሪ የሙያ ምስክሮችን ከሰማ በኃላ የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ አፅንቷል፡፡

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ታህሳስ 23 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ ክርክር የሰበር ቅሬታቸውን አቅርበዋል ቅሬታቸው ተመርምሮ ክርክር ያስነሳውን ገንዘብ አመልካች እንዲከፍል መወሰኑን አግባብ ለማጣራት ሲባል ለሠበር እንዲቀርብ ተደርጎ ተጠሪ በቅሬታው ላይ መልስ ሰጥተዋል ተጠሪ ጥር 27/2006 ዓ.ም የሰጡት መልስ የስር ክርክራቸውን የሚያጠናክር እና የሰበር ቅሬታው ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲጸና የሚጠይቅ ነው፡፡ አመልካችም የካቲት 21/2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከላይ በአጭሩ ለመግለፅ የሞከርነው የነገሩን አመጣጥ ሲሆን የሥር ፍ/ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔ የተፈፀመው የህግ ስህተት ቢኖር መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ካርዱ የጠፋ መሆኑን በፅሑፍ ለአመልካቾቹ ማሳወቁ፤ክርክር ያስነሳው ክፍያ የተፈፀመው ካርዱን መጥፋቱን ካሳወቀ በኃላ መሆኑ ግራቀኙ ባደረጉት ውል ካርዱ ከጠፋ በኃላ ለሚደረግ ክፍያ ባንኩ ኃላፊነት ይኖርበት ዘንድ ደንበኛው (ተጠሪ) ሂሳቡ በሙሉ እንዲዘጋለት የመጠየቅ ግዴታ እንደሌለበት፤ ተጠሪ ካርዱ መጥፋቱን በፅሑፍ ባሳወቀ ጊዜ በፎርሙ ላይ የሚስጢር ቁጥሩን መጻፉ ሁሉ ግራ ቀኙ የሚካካዱበት አይደለም፡፡

ከዚህም ሌላ ፍሬ ነገር ለማጣራትና ማስረጃ ለመመዘን ስልጣኑ የተሰጠው የስር ፍ/ቤት የሙያ ምስክሮችን በመስማት ተጠሪ በስህተት እንኳ የሚስጢር ቁጥሩን በፎርሙ ላይ ጽፎ ቢገኝ ይህ ቁጥር የተመዘገበበት ፎርም መቀመጥ እንደሌለበት ሙያዊ ምስክርነት እንዲሠጡ አረጋግጧል፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የሂሳብ ይዘጋልኝ ጥያቄ ባልቀረበበት ሁኔታ የተጠሪ ሂሳብ ሊዘጋ የማይችል መሆኑን እና ተጠሪ የሚስጥር ቁጥሩን በመግለፅ ግዴታውን መጣሱን በማንሳት ነው፡፡ነገር ግን ካርዱ መጥፋቱን ካሳወቀ በኂላ የሂሳብ ይዘጋልኝ ጥያቄ አልቀረበም በሚል ከኃላፊነት መዳን ስለመቻሉ በግራ ቀኙ ውል ካለመመልከቱም በላይ ተጠሪ በባንኩ ፎርም ላይ የሚስጥር ቁጥሩን ከሞላ በኂላ ሚስጥርነቱ ስለሚቀር ተገቢ ያልሆነ ተግባር እንዳይፈፀምበት በባንኩ በኩል ስለተደረገው ጥንቃቄ በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡

ከባንኩ የሚጠበቀው በተለመደው የባንክ ሥራ አካሄድ ጥንቃቄ ማድረጉን እና ጥፋት አለመስራቱን ማሳየት ነው፡፡ይህን ሳያሳይ ደንበኛው የሂሳብ ይዘጋልኝ ጥያቄ አላቀረበም በሚል

ከኃላፊነት የሚድንበት የህግም ሆነ የውል አግባብ ባለመኖሩ የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም ብለናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 189176 የካቲት 18 ቀን 2005 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 132422 ህዳር 13/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ስለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻሉ
3. የተጀመረው አፈፃፀም እንዲታገድ በዚህ ፍ/ቤት ታህሳስ 28/2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

# የዳኝነት ስልጣን

የሰ/መ/ቁ. 75560

ሐምሌ 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፊሳ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማሪያም - ጠበቃ ዮሴፍ አእምሮ ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ገብረ ስላሴ ሃይሌ- ወኪል ወርቅነሽ መንግስቱ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የባልነት ማስረጃን መሰረት ያደረገ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ባቀረቡት የመቃወም አቤቱታ መነሻ ነው፡፡አመልካች የመቃወም አቤቱታ ሊያቀርቡ የቻሉት የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የሟች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ባል ነኝ በማለት በሐሰት የወሰዱት ማስረጃ ያላግባብ ነው በማለት የተወሰደው ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረና የምስክሮች ቃል ከሰማ በኋላ በተጠሪና በሟች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ መካከል ጋብቻ ስለመፈፀሙ በትዳር ሁኔታ ተረጋግጧል በሚል ምክንያት የአመልካችን አቤቱታ ባለመቀበል ቀድሞ ተጠሪ የሟች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ናቸው በማለት የሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 360(2) መሰረት በማጽናት ወስኗል፡፡ከዚህም በኋላ አመልካች የይግባኝ ቅሬታቸውን ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ጉዳዩን ለከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበውም ተቀባይነት አላገኙም፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም የባልነት ጉዳይ አከራካሪ በሆነበት ሁኔታ ጉዳዩ በበታች ፍርድ ቤቶች የታየው ያለስልጣናቸው መሆኑንና የተጠሪ የባልነት ማስረጃ ከመጀመሪያውም የተሰጠው ተገቢ ያልሆነ አቤቱታ ቀርቦና በሕግ አግባብ መቅረብ ያለበት ማስረጃ ሳይቀርብ ነው የሚል ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮም ጉዳዩን የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ለማየት ስልጣን ያላቸው መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎቱ እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች በበኩላቸው የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ

ቤቶች ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ዳኝነት ሥልጣን አላቸው? ወይስ የላቸውም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥረ ነገር ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 361/1995 እና 408/1996 ስር ተመልክቷል፡፡በዚህም መሰረት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 እና አዋጅ ቁጥር 408/1996 ከተሰጧቸው ስልጣኖች መካከል የወራሽነት ምስክር ወረቀት መስጠት፣የባልና ሚስትነት፣የሞግዚትነት ማስረጃ መስጠት ይገኙበታል፡፡በዚህ ረገድ የተሻሻለውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀጽ 2 በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(ሸ) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ሰርዞ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የወራሽነት፣የባልና ሚስትነት እና የሞግዚትነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ ላይ የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው መሆኑ ተደንግጓል፡፡የድንጋጌው የእንግሊዝኛው ቅጂም "application for certification of succession,marriage and guardianship."በሚል የተቀመጠ ነው፡፡ከእነዚህ የድንጋጌዎች ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች ስለጋብቻ በሚሰጡት ማስረጃ ላይ በሚቀርብ ክርክር የሚኖራቸው የዳኝነት ሥልጣን አድማሱ እስከምን ድረስ መሄድ አለበት? የሚለው ጥያቄ የሚነሳ መሆኑን ነው፡፡በሌላ አገላለጽ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን የባልና ሚስትነት ማስረጃ ለመስጠት ነው ተብሎ የተቀመጠው የሕጉ አገላለፅ ፍርድ ቤቶቹ የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ ከሰጡ በኃላ በማስረጃው ተቃውሞ ቢቀርብ እና የተቃውሞው መሰረት የሚሆኑት ምክንያቶች የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃው የተሰጠው በቤተሰብ ሕጉ ስለጋብቻ መኖር ያለመኖር ሊቀርቡ የሚገባቸው የማስረጃ አይነቶች ሳይቀርቡ ነው፣ጋብቻ ሳይኖር ነው፣የቀረበው አቤቱታ ከሕጉ ስርዓት ውጪ ነው፣ሕጉን በሚጻረር መልኩ ነው የሚል ከሆነ ማስረጃዎች በማስረጃነቱ ከመስጠት ባለፈ በተጠቀሱት ነጥቦች ክርክር እንዲካሄድ በማድረግ ዳኝነት ሊሰጡ ይችላሉ? ወይስ አይችሉም? የሚል ነው፡፡ይህንኑ ጥያቄ ለመመለስ የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ ምንነት፣ማስረጃው የሚሰጥበትን ሁኔታ፣የማስረጃውን ይዘት፣አቤቱታው የሚስተናገድበትን ሥርዓት መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

የጋብቻ ምስክር ወረቀት ስለሚሰጥበት ሁኔታና ስለይዘቱ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግአዋጅ ቁጥር 213/1992 ይደነግጋል፡፡ ይሄው ህግ ለጋብቻ መኖር መቅረብ ያለባቸውን የማስረጃ አይነቶች ቅደም ተከተል እንዲሁም በማስረጃው ሊረጋገጡ ስለሚገባቸውሁኔታዎች አስፍሮ እናገኛለን፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ፍርድ ቤቱ በሕጉ በተመለከተው አግባብ መረጋገጡን በቂ ነው ብሎ የገመተውን ያህል ማስረጃ ተቀብሎና መዝኖ ጋብቻ መኖር ያለመኖሩን የሚያረጋገጥ መሆኑን፣ጋብቻው አለ ወይም የለም ተብሎ ሊሰጥ የሚችለውም በሕግ የተቀመጠውን መመዘኛ በማሟላታቸው በመለየት ስለሆነ ይህንኑ የሚገልፅ ወይም የሚያሳይ ምክንያት በመስጠት ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን ነው፡፡በአንፃሩ የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ መስጠት ግን ከላይ የተመለከቱት ሕጋዊ ክርክሮች በሌሉበት ሁኔታ የሚሰጥ ማስረጃ እንጂ ጋብቻ ስለመኖሩ ያለመኖሩ ክርክር ተደርጎ የግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃ በሕጉ አይን ተመዝኖ የሚሰጥ አይደለም፡፡ፍርድ ቤቱ ጥያቄው ሲቀርብ የሚሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ስለውሳኔ የተቀመጠውን ትርጉም የሚያሟላ ነው ሊባል የሚችል ሳይሆን የባልነት ወይም የሚስትነት የምስክር ወረቀቱን ስለሕጋዊ ማስረጃነቱ የሚያረጋገጥበት ነው፡፡ ይህን አይነት ውሳኔ ለመስጠት ፍርድ ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ስነ ሥርዓት ሲታይም ተከራካሪ ወገን የሌለበት፣አቤቱታ አቅራቢው ብቻ በማስረጃ በተደገፈ አቤቱታ መሰረት ይገባኛል የሚለውን መብት ወይም ጥቅም ትክክለኛነቱን፣ሕጋዊነቱን እንዲረጋገጥለት የሚያቀርብ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 305 መሰረት የተፋጠነ ሥርዓት ነው ሊባል የሚገባው ነው፡፡ ስለሆነም

የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ ይሰጠኝ አቤቱታ ይዘቱና ፍርድ ቤቱ ሊከተለው የሚገባው ስነ ሥርዓት ሲታይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የማስረጃ ይሰጠኝ ጥያቄውን ተገቢነቱን፣ ትክክለኛቱንና ሕጋዊነቱን ከማረጋገጥ ባለፈ ጋብቻ አለ ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘው በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመስማት፣ጉዳዩን በማጣራት እና ሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ክርክር ሲኖር አቤቱታውን ተቀብሎ ለማስተናገድ የዳኝነት ሥረ ነገር ሥልጣን የሌላቸው መሆኑን ያስገነዝባል፡፡በጉዳዩ ላይ ሚስትነት ወይም ባልነት የለም የሚልና ተቃውሞውን ለማቅረብ መብትና ጥቅም ያለው ወገን ጋብቻው ያለመኖሩንና እና ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ሕጋዊ ክርክሮችን መሰረት በማድረግ ተቃውሞ በማቅረብ ሕጋዊ መፍትሔ ሊያገኝ የሚገባው ጥያቄውን ወይም አቤቱታውን ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች ለማቅረብ እንጂ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በማቅረብ አይደለም፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ ወረቀት ላይ ውሳኔ ሰጥተዋል በሚል ምክንያት ብቻ ተቃውሞ ያለው ወገን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358"ን" መሰረት በማድረግ የተቃውሞ አቤቱታ ሲያቀርብና ፍርድ ቤቶቹም አቤቱታውን ተቀብለው የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ ትክክለኛነቱንና ሕጋዊነቱን ከማረጋገጥ ባለፈ ተከራካሪ ወገኖችን በማከራከር ስለጋብቻ መኖር ያለመኖር ላይ ማስረጃ ሳይሆን በጋብቻ ውጤት ላይ የራሱ የሆነ ትርጉም ያለውንና ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ ሲሰጡ በተግባር ይስተዋላል፡፡ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የተቃውሞ አቤቱታ የሚቀርበው በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተሰጠው የውሳኔ ትርጉም(አንቀፅ 3 ይመልከቷል) መሰረት ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ ከተሰጠ እና ውሳኔው የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገን መብትና ጥቅም የሚነካ መሆኑ ሲረጋገጥና አቤቱታው ውሳኔው ከመፈፀሙ በፊት ከቀረበ ነው፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አይነተኛ አላማ ማስረጃው ትክክለኛነቱና ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ በማስረጃነቱ (Declaratory Judgement) በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ሳይሆን ከላይ እንደተገለፀው ሊፈፀም በሚችል ውሳኔ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ወገን መብትና ጥቅምን ማስከበር ነው፡፡በአጠቃላይ የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ አቤቱታ ስለሚሰጥበት ሁኔታና ስለይዘቱ እንዲሁም በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ተቃውሞ የሚቀርብበት ሥርዓት በአንድነት ሲታዩ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የማስረጃው ይሰጠኝ ጥያቄ /አቤቱታ/ ትክክለኛነቱንና ሕጋዊነቱን በማረጋገጥ ለማስረጃነት ውሳኔ ከመስጠት ባለፈ ማስረጃውን ትክክለኛነቱንና ሕጋዊነቱን የሚቃወም ወገን አቤቱታ ሲያቀርብ ለተቃውሞው መሰረት ሊሆኑ በሚችሉት ጋብቻ የለም፣ተገቢው ማስረጃ አልቀረበም፣የቀረቡት ማስረጃዎችም ሐሰተኛ ናቸው በሚሉት ነጥቦች ላይ ክርክር በመስማት ዳኝነት ለመስጠት በአዋጅ ቁጥር 361/1995"ም" ሆነ የዚሁ አዋጅ ማሻሻያ በሆነው አዋጅ ቁጥር 408/1996 መሰረት ሥልጣን ያልተሰጣቸው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ሲያቀርቡ መሰረት ያደረጉት ከሟች ወ/ሮ ኪሮስ ጋር በጋብቻ ተሳስረው የነበሩ መሆኑን ጠቅሰው የባልነት ማስረጃ እንዲሰጣቸው ሲሆን ይህ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ሲያመለክቱም አቤቱታቸውን በቃለ መሃላ ያስደገፉ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ለተጠሪ በተጠየቁት አግባብ ማስረጃ ከሰጠ በሁዋላ የአሁኗ አመልካች ተጠሪና ሟች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ባልና ሚስት አይደሉም፣ጥያቄውና ማስረጃው የተሰጠበት አግባብ ሕጋዊ አይደለም የሚል ይዘት ያለው ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡ይህ በግልፅ የሚያሳየው የአመልካች የተቃውሞ አቤቱታ ተጠሪ ያገኙት የባልነት ማስረጃ ከማስረጃነቱ ባለፈ ሌሎች የቤተሰብ ሕግ ክርክሮችን የሚያስነሳ መሆኑን ሲሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የከተማው ፍርድ ቤትም የተሻሻለውን የፌዴራሉን የቤተሰብ ሕግ ሁሉ በመጥቀስ ውሳኔ መስጠቱን ከውሳኔው ተመልክተናል፡፡የአዲስ አበባ ከተማ

ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 361/1995 እና 408/1996 መሰረት ካገኟቸው ሥልጣኖች መካከል ከመሰረታቸው የፌዴራል ጉዳዮች የሆኑት የሚገኙት ሲሆን እነዚህ ጉዳዮች ለእነዚህ ፍርድ ቤቶች ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ተቆርሰው ሲሰጡ በሕግ አውጪው የታሰበው በባሕርያቸው ውስብስብ ያልሆኑ ናቸው በሚል ነው፡፡የጋብቻ መኖር ያለመኖር ውስብስብ ያልሆነ ክርክር የማይቀርብበት ሳይሆን ክርክር ተደርጎበት ውስብስብ የሕግ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥበት ነው፡፡በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የጋብቻ መኖር ያለመኖርን ለመወሰን ሥረ ነገር ስልጣን ያልተሰጣቸው በመሆኑ ጉዳዩ በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች መስተናገዱ ያላግባብ ነው፡፡ተጠሪ ያገኙትን ማስረጃ አመልካች ሊቃወሙት የሚገባቸው ስልጣን ባለው የፌዴራል ፍርድ ቤት ነው፡፡ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረቡት ምክንያቶችን በመመልከት ጉዳዩን ለማስተናገድ ስልጣን የሌለው መሆኑን ገልፆ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 እና 231(1(ለ)) መሰረት መዝገቡን መዝጋት ሲገባው ጉዳዩን ማስተናገዱም ሆነ የበላይ ፍርድ ቤቶች ይህንኑ ሳያረጋግጡ  የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በትእዛዝ ማፅናታቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 961/02 ጥቅምት 16 ቀን 2004 ዓ/ም ተሰጥቶ በከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 17036 ሕዳር 25 ቀን 2004 ዓ/ም፣በከተማው ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 17119ታህሳስ 13 ቀን 2004 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት በአብላጫ ድምፅ ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የባልነት ወይም የሚስትነት ማስረጃ በተመለከተ የቀረበው ጥያቄ ትክክለኛነቱንና ሕጋዊነቱን በማረጋገጥ በማስረጃነቱ ውሳኔ (Declaratory Judgement) ከመስጠት ውጪ ማስረጃው የተሰጠበትን ውሳኔ መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የተቃውሞ አቤቱታ መቀበልና ጋብቻ መኖር ያለመኖርን ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ክርክሮችን ለማስተናገድ የሥረ ነገር ሥልጣን የላቸውም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ አለኝ የሚሉትን ማስረጃ አመልካች በተጠሪና በሟች ወ/ሮ ኪሮስ ውቤ ጋር ጋብቻ የላቸውም የሚሉበትን ምክንያት መሰረት አድርገው ሊቃወሙ የሚችሉት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ሳይሆን በሌላ ክስ ሁኖ ስልጣን ባለው በፌዴራሉ ፍርድ ቤት ነው ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት**

## <u>የሃሳብ ልዩነት</u>

እኔ ስሜ በሶስተኛው ተራ ቁጥር የተጠቀሰው ዳኛ አብላጫው ድምፅ በሰጠው የሕግ ትርጉምና ከደረሰበት መደምደሚያ የማልስማማ በመሆኑ በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የወራሽነት፣ የባልና ሚስትነት የሞግዚትነትና የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ አከራክረው የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን ያላቸው

መሆኑ አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41/ሸ/ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀጽ 1 በግልፅ ተደንግጓል፡፡

የባልና ሚስትነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ፣ ባል ወይም ሚስት ነኝ በማለት አንድ ሰው የሚያቀርበውን ማመልከቻና መግለጫ ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ የባልና ሚስትነት ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ ማናቸውም ያገባኛል የሚል ሰው ባል ወይም ሚስት አይደለም በማለት የሚያቀርበውን ተቃውሞና ክርክርን የሚጨምር እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህጉ አንቀጽ 80 ንዑስ አንቀጽ 1 "የአቤቱታ ፅሁፍ ማለት ከሳሽ የሚጠይቀውን ሁሉ ዘርዝሮ የሚገልፅ ፅሁፍ፣ ተከሳሽ የሚሰጠው የመከላከያ ፅሁፍ፣ የተከሳሽ ከሳሽ የሚያቀርበው ፅሁፍ የይግባኝ ማቅረቢያ ፅሑፍ ወይም በሌላ አይነት ተፅፎ ለፍርድ ቤትና ክስ መነሻ ወይም ለዚሁ መልስ የሚመለከት ማናቸውም ፅሑፍ ነው በማለት የሰጠውን ሰፊ ትርጉም በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከአዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀጽ 1 የባልና ሚስትነት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ አቤቱታ የመዳኘት ሥልጣን የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች እንደሆነ ሲደነግግ፣ አንዲት ሴት የአንድ ሰው ሚስት መሆኔ ተጣርቶና በማስረጃ ተረጋግጦ ይወሰንልኝ በማለት የምትጠይቀውን የዳኝነት ጥያቄ ወይም አንድ ሰው የአንዲት ሴት ባል መሆኔ ተጣርቶና በማስረጃ ተረጋግጦ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት በሚያቀርበው የዳኝነት ጥያቄ ላይ ባል ነው የተባለው ሰው ወይም ሚስት ናት የተባለችው ሰው በህይወት ያለች ከሆነ የመከላከያ መልሷንና ማስረጃዋን እንድታቀርብ በማድረግ፣ ፍሬ ጉዳይ በማጣራት፣ ማስረጃ በመመርመርና በመመዘን በሁለቱ ተከራካሪዎች መካከል ህጋዊ ዕውቅና ያለው ጋብቻ መኖሩን ወይም አለመኖሩን የመወሰን ሙሉ ሥልጣን ያላቸው መሆኑን የሚያጠቃልል ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የባልነት ወይም ሚስትነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጥና አቤቱታ የቀረበው አንደኛው ወገን ላይ የመጥፋት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ወይም አንደኛው ወገን ከሞተ በኋላ እንደሆነ፣ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሰረት በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው የመከራከር መብት ያላቸው ሰዎች የሚያቀርቡትን ክርክርና የመከላከያ ማስረጃ በተሟላ ሁኔታ በመስማት ተገቢውን ውሳኔ የመስጠት ሥልጣንን የሚያካትት ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀጽ 1 ድንጋጌ ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 41 ድንጋጌ ጋር በማጣመር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ባል ወይም ሚስት መሆናቸውን የሚያረጋገጥ ማስረጃ ከመስጠታቸው በፊት፣ ተገቢውን የፍሬ ጉዳይ ማጣራት በማድረግ፣ አስፈላጊም በሆነ ጊዜ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 145/1/ እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 264 መሠረት ተጨማሪ የሰነድና የሰው ማስረጃ በማስቀረብ ፣ ውሣኔ የመስጠት ኃላፊነት ያለባቸው የከተማው ፍርድ ሰጭ ተቋማት መሆናቸውን በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀፅ 39 ተደንግጓል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ባል መሆኑ ወይም ሚስት መሆኗ ተጣርቶና ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው የቀረቡ የዳኝነት ጥያቄዎችን ፣ ለጉዳዩ መልስ መስጠት ያለበት - የትዳር አጋር /ካለ/ች/ መልስ እንዲሰጡና መከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድረግ፣ በራሳቸው አነሳሽነት ተጨማሪ የሰውና የፅሑፍ ማስረጃ በማስቀረብ ወይም በጉዳዩ ጣልቃ ገብ ተከራካሪ

ወገን ሊሆን የሚችል ሰው ሲቀርብ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 41 መሠረት የጣልቃገቡን ክርክርና ማስረጃ በመስማት በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል ጋብቻ መኖሩን ወይም በጋብቻ አለመኖሩን በማረጋገጥ የሰጡት ውሣኔ መብቴንና ጥቅሜን ይነካብኛል፤ በክርክሩ ተካፋይ መሆን ነበረብኝ የሚለው ሰው በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነ ሰው ቀደም ብሎ የተሰጠውን ውሣኔ ለማሰረዝ የፍርድ መቃወሚያ የሚያቀርበው ቀደም ብሎ ጋብቻ መኖሩን ወይም አለመኖሩን አከራክሮና አጣርቶ ለወሰነው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት እንደሆነ የአዋጅ ቁጥር 408/1996 አንቀፅ 1 ድንጋጌና የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 እና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 359 ንዑስ አንቀፅ 1 "መቃወሚያው የሚቀርበው በአቤቱታ አቀራረብ መልክ ሆኖ ተገቢው ዳኝነት ተከፍሎበት፣ መቃወሚያ ያቀረበለትን ለወሰነው ፍርድ ቤት ነው" በማለት በግልፅ የደነገገውን ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የባል ወይም ሚስት ስለመሆን የቀረበላቸውን አቤቱታ ተቀብለው አጣርተው በሰጡት ውሣኔ ላይ የሚቀርብን የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ተቀብሎ የማስተናገድ ሙሉ የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡ አብላጫው ድምፅ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች ጋብቻ አለ ወይም የለም በሚለው ጭብጥ ላይ መከራከር ያለባቸውን ሰዎች ክርክር በመስማት አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ውሣኔ እንደማይሰጡና ሥልጣን እንደሌላቸው በመቁጠር፣ የፍርድ መቃወሚያው መቅረብ ያለበት ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆን አለበት በማለት የሰጠው ትርጉም የአዋጅ ቁጥር 408/96 አንቀፅ 1፣ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር አንቀጽ 80/1/፣ አንቀጽ 41 እና አንቀጽ 358፣ አንቀጽ 359/1/፣ ድንጋጌዎች ይዘትና ተግባራዊ ተፈፃሚነት መሠረት ያደረገ ነው የሚል እምነት የሌለኝ በመሆኑ፣ በጉዳዩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የፍርድ መቃወሚያውን በመቀበል የማከራከርና የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ ጭብጥ በተያዘበት በዳኝነት ሥልጣንን መሠረት በማድረግ ሳይሆን የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች የተጠሪን የፍርድ መቃወሚያ በመቀበል የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ነጥብ ላይ ግራ ቀኙን በማከራከር ውሣኔ ሊሰጠው ይገባ ነበር በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

**የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ/ 98541

ህዳር 10 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

መስጠፉ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ አለማየሁ ኦላና - ቀረቡ

ተጠሪ፡-የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት (UNDP) ታልፏል ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው አመልካች በተጠሪ ላይ የአሠሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ድንጋጌዎችን መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክስ ተጠሪ በሌለበት ታይቶ በክርክሩ ከተረጋገጠበት የፍሬ ነገር ጉዳዮች በመነሳት የአሁኑ አመልካች የተለያዩ ክፍያዎች በተጠሪ እንዲከፍሏቸው በወረዳው ፍርድ ቤት በተወሰነው መሰረት የአፈጻጸም መዝገብ ከፍተው ክርክሩ በመታየት ላይ እያለ ተጠሪ የመከሰስ መብት የለውም ተብሎ የአፈጻጸም መዝገቡ በሁሉም የበታች ፍርድ ቤቶች መዘጋቱ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡

የአሁን አመልካች ተጠሪ ከህግ ውጪ ከስራ አሰናብቶኛል በማለት ካሳና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ በያበሎ ወረዳ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪ ላይ ክስ መስርተው የአሁኑ ተጠሪ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ተደርጎ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ስንብቱ ሕገ ወጥ መሆኑን በመደምደም ለአመልካች ካሳና የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሉ በማለት ወስኗል፡፡አመልካች ይህንኑ ውሳኔ ለማስፈፀም በወረዳው ፍርድ ቤት የአፈጻጸም ክስ ከፍተው ጉዳዩ መታየት ከጀመረ በኋላ የወረዳው ፍርድ ቤት ጉዳዩን መርምሮ የተባበሩት መንግስታት ኮንቬንሽንን አንቀፅ 2(3) በዋቢነት ጠቅሶ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት የአፈጻጸም መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ትዕዛዝ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለቦረና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታቸውን አቅርበውም ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል የሚል ትዕዛዝ ሰጥቶ

ተጠሪ ሊቀርብ ባለመቻሉ መልስ መስጠቱ የታለፈ ሲሆን ችሎቱ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ሁኖ አመልካች የሚከራከሩት የተባበሩት መንግስታት አካል ከሆነው ድርጅት ጋር መሆኑን፣ ከእንደዚህ አይነት ድርጅቶች ጋር የሚደረግ ግንኙነት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 የማይገዛ መሆኑ በተጠቃሹ አዋጅ አንቀጽ 3(ሀ) ስር መመልከቱን፣ተጠሪና መሠል አካላት በሕግ የተለየ ከለላ ያላቸው መሆኑ በተባበሩት መንግስታት ቻርተር አንቀጽ105፣በተባበሩት መንግስታት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ ለመንደንገግ በወጣው ስምምነት አንቀጽ 2(2) እና 3 ስር መደንገጉን፣ኢትዩጵያም ይህንኑ ስምምነት መፈረሟን በዋቢነት ጠቅሶ ከመነሻውም ተጠሪ በወረዳው ፍርድ ቤት መከሰሱ ተገቢነት እንደሌለው፣አመልካች ያላቸው መፍትሔም በ"United Nations Commission on International Trade Law (UNCITRAL)" ደንቦች መሰረት ከተጠሪ ጋር ባላቸው ስምምነት መሰረት በእርቅ መጨረስ መሆኑን፣በዋናው ጉዳይ ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ መወሰኑን ከተጠሪ ጥቅምና ከባለ መብቶች አንፃር ሲታይ ዋናውን ውሳኔ ሕጋዊ የማያደርገው መሆኑን ዘርዝሮ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለንም በማለት የአፈጻጸም መዝገብ መዝጋታቸውን በመቀበል የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በዋናው ጉዳይ ላይ ተጠሪ ቀርቦ ባልተከራከረበት ሁኔታ በአፈጻጸም መዝገብ የተጠሪን ያለመከሰስ ከለላ በመጥቀስ ዋናውን ውሳኔ ውድቅ ማድረግ ሥነ ሥርዓታዊና የሕግ የበላይነት እንዲሁም አመልካች እንደ ዜጋ ፍትህ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ በጽሑፍ መልስ መስጠቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎት ጉዳዩን ከበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሰረቱ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተነሳው ግንኙነት የቅጥር ውልን መሰረት ያደረገ ሲሆን ዋናው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አግባብ ታይቶ ዳኝነት ማግኘቱን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ የተለያዩ ዓይነት በቅጥር ላይ የተመሰረቱ የስራ ግንኙነቶች የሚኖሩ ሲሆን ግንኙነቶቹ የሚገዙበት የሕግ አግባብም ይለያያል፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ግንኙነቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ይህ አዋጅ በየትኞቹ ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው እንደሚችል በዋነኝነት የሚመራው የአዋጁን የተፈጻሚነት ወሰን የደነገገው አንቀጽ 3 ነው፡፡ለዚህ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የአንቀጹ ድንጋጌ በንዑስ ቁጥር ሶስት በፊደል "ሀ" ስር የተመለከተው ሲሆን በዚህ ንዑስ ድንጋጌ ስር የስራ ግንኙነቱ በንዑስ አንቀጽ ሁለት ስር የሚወድቁ ባለመሆናቸዉ በአዋጁ አንቀጽ 1 መሰረት በቀጥታ ሊፈጸምባቸው የሚችል ቢሆንም በንኡስ አንቀጽ 3 ስር በተገለጹት ሁኔታዎች መሰረት ከአዋጁ ሽፋን ውጭ ሊደረጉ የሚችሉ የስራ ግንኙነቶችን የሚመለከት ነው፡፡በዚሁ መሰረት ኢትዮጰያ ውስጥ የሚሰሩ የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ወይም አለም አቀፍ ድርጅቶች ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚመሰርቱት የስራግንኙነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ወይም ኢትዮጵያ በምትፈርማቸው አለምዓቀፍ ስምምነቶች መሰረት በአዋጁ ሊሸፈኑ እንደማይችሉ ተመልክቷል፡፡በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ሲታዩ አዋጁ በአጠቃላይ በአሰሪና ሰራተኛ መካካል በሚቋቋም በቅጥር ላይ በተመሰረተ የስራ ግንኙነት ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ቢሆንም በአዋጁ

በግልጽ በተደነገጉ ሌላ ህግ በሚገዛቸው ግንኙነቶች ላይ ተፈጻሚነት እንደማይኖረው ያስገነዝባሉ፡፡ በተጨማሪም አሁንም አዋጁ የሚሸፍናቸው የስራ ግንኙነቶች ሊሆኑ ቢችሉም ነገርግን የሚኒስትሮች ምክርቤት ወይም ኢትዮጵያ የምትፈርማቸው አለምአቀፍ ስምምነቶች በሚወስኑት መሰረት ከአዋጁ ሽፋን ውጭ ሊደረጉ የሚችሉ መሆኑን ተመልክቷል፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ሕግ አውጪው የዲፕሎማቲክ ግንኙነቶችን ስምምነትና ልምድን ለማክበር ሲባል የውጭ ዲፕሎማቲክ ሚስዮኖቹና ኢትዩጵያውን ሠራተኞቻቸው የሚያደርጉት የቅጥር ግኑነት ላይ የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ ተፈጻሚ እንዳይሆን ያደረገ መሆኑን ነው፡፡በመሆኑም በሕጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ወይም ኢትዩጵያ ከውጭ ድርጅቶች ጋር በምትፈራረምባቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት አዋጅ ቁጥር 377/1996 ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚደረግበት አግባብ መኖሩን ሕግ አውጪ በግልፅ ያስቀመጠው ጉዳይ ነው፡፡የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(3((ሀ)) መሰረታዊ አላማ የውጭ አገር መንግሥታት ተወካዮችን ሉአላዊነት እና አለምአቀፍ ስምምነቶችን ለማክበር ተብሎ ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን በተጨባጭ ባለው ሁኔታ ደግሞ የውጪ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችና አለም አቀፍ ድርጅቶች ከኢትዩጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መስሪያ ቤት ጋር ስምምነት ተፈራርመው ይኼው የመንግስት አካል በእነዚህ ተቋሞች ተቀጥረው የሚሰሩት ኢትዩጵያውንን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ በአለም አቀፍ ስምምነቶች በተካተተው አግባብ የተፈጠረው አለመግባብት ሰላማዊ በሆነ መንገድ በማግባባትና በድርድር እንዲፈታ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ የሚታወቅ ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ክርክር ያቀረቡት ግንኙነቱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(3(ሀ)) መሰረት ሊገዛ ከማይችል አካል ጋር ነው፡፡ተጠሪ የተባበሩት መንግስታት አካል ሲሆን የተባበሩት መንግስታት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ በተደነገገ ስምምነትም በማንኛውም መንግስት ፍርድ ቤቶች ተከሶ መቅረብ የሌለበት መሆኑን በተባበሩት መንግስታት ቻርተር አንቀፅ 105 እንዲሁም ከተባበሩት መንግስታት ጥቅምና የተለየ ከለላን በተመለከተ በተደነገገው ስምምነት አንቀጽ 2(2) እና 3 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር የሌለ ቢሆንም አሁን አጥብቀው የሚከራከሩት በዋናው ጉዳይ ውሳኔ ከአረፈ በውሳኔው መሰረት ከሚፈጸም በስተቀር የተጠሪ በሕግ ያለው የተለየ ከለላ እንደ አቢይ ምክንያት ተወስዶ አፈፃጸሙ ሊቆም የሚችልበት አግባብ የለም በሚል ነው፡፡በሕግ አግባብ የተሰጠ ፍርድ ዋጋ እንዳይኖረው የሚደረገው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተገቢነት እንደሌለው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 378 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡በሕግ አግባብ ታይቶ የተሰጠን ውሳኔ በሕጉ አግባብ ማስፈፀም በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 78(1) እና 79(1) እና (4) ስር የተረጋገጠውንና የተከበረውን የነጻ ፍርድ ቤት መኖርንና የዳኝነት ስልጣን በአግባቡ ተግባራዊ የሚያደርገው እና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ስር የተረጋገጠው የዜጎች ፍትህ የማግኘት መብትም ውጤት ባለው መልኩ ተግባራዊ የሚሆንበት መንገድ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡አፈጻጸም በፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ ትርጉም እንዲኖረው የማድረግ ውጤት ያለውና በተገቢው መንገድም መፈፀም ያለበት መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ይህ ግን ለማንኛውም ጉዳዮች ሁሉ ይሰራል ብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስ ተገቢ ያልሆነ ሕጋዊ ውጤት የሚያስከትል መሆኑ እሙን ነው፡፡በእርግጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 212 ድንጋጌ ስር በስነ ስርዓት ጉድለት አንድ ፍርድ ውድቅ ሊሆን እንደማይችል የተመለከተ ሲሆን ይህ ግን የሚሰራው የፍትሓ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ ተፈፃሚነት ወሰንን መሰረት በማድረግ በሌላ አኳኃን እንዲፈፀም በሕግ

ባልተደነገገበት ሁኔታ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡በመሆኑም ከመነሻውም ኢትዮጵያ በፈረመችው አለም አቀፍ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ላለመዳኘት ነገር ግን ከኢትዮጵያ ዜጎች ጋር ለመሰረተው ግንኙነት በሌላ አግባብ ጉዳዩን ለመጨረስ የሚያስችል ስርዓት ያለው ወገን በዋናው ክርክር ጊዜ ቀርቦ ባለመከራከሩና በይግባኝ ጉዳዩን ባለማሳረሙ ምክንያት ብቻ ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ እንዲፈጽም የሚገደድበት አግባብ የለም፡፡ስለዚህ ከዚህ ጉዳይ የተለየ ባሕርይ ስንነሳ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 212 እና 4 ድንጋጌዎች አንድ ላይ ተጣምረው ሲታዩ አፈፃጸሙ ዋጋ ያለውን ፍርድ መሰረት ያደረገ ነው፣ጉዳዩ ከስነ ስርዓት ጉድለት ጋር የተያያዘ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አላገኘነም፡፡ተጠሪ በሕግ የተጠበቀለት የከለላ መብትና ጥቅም እያለው ስልጣን የሌለው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ እንዲፈጽም ማድረግ ሕግ አውጪው የዲፕሎማቲክ ግንኙነቶችን ልምድን ለማክበር ሲባል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3(3(ሀ)) ስር ያስቀመጠውን ድንጋጌ ዋጋ የሚያሳጣው እና በዲፕሎማቲክ ግንኙነቱም አሉታዊ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ተመራጭ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ሲጠቃለልም የጉዳዩ ልዩ ባህርይ ሲታይ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 212 ድንጋጌን ጠቅሶ አፈፃጸሙን ማስቀጠል የሚቻልበት አግባብ ስለሌለና አመልካችም እንደዜጋ መንግስት በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በኩል በዘረጋው ስርዓት መሰረት መብትና ጥቅማቸውን የሚያስከበሩበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ የሕግ የበላይነት አልተከበረም፣ የዜጋ ፍትህ የማግኘት ሕገ መንግስታዊ መብት ተጥሷል ለማለት ስላልተቻለ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከታዩን ወስናል፡፡

**ውሣኔ**

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 163639 ታህሳስ 07 ቀን 2006 ዓ/ም የበታች ፍርድ ቤቶችን ትዕዛዝ በማፅናት የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የአፈጻጸም ክስ መዘጋቱ ተገቢ ነው ብለናል፡፡አመልካች አለኝ የሚሉትን መብትና ጥቅም በሌላ አግባብ ከመጠየቅ ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤተ ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::**

**መ/ብ**

የሰ/መ/ቁ. 99717

ጥር 20 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች**:- አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች** :- አቶ ሲሳይ ይማነ - ቀረቡ

**ተጠሪ**:- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ነገረ ፈጅ አቶ መስፍን ጌታቸው - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 41105 ህዳር 30 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 143053 ጥር 13 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የዳኝነት ስልጣን ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ አመልካች ያቀረበው ክስ ነው፡፡ አመልካች /ከሳሽ/ ከተከሳሽ ጋር የአካዳሚክ ሰራተኛ የነበረ መሆኑን ገልፆ፣ ግንቦት 9 ቀን 2001 ዓ/ም ከሳሽና ተከሳሽ ባደረጉት ስምምነት መሰረት በሌክቸረርነት አገልግያለሁ፣ ከሳሽ የማስተርስ ድግሪ ትምህርት በመማር ውጭ ሃገር ሄጄ ተመልሻለሁ፡፡ ከዚያም የዶክትሬት ድግሪ ትምህርት ለመከታተል ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ተከሳሽ ከነሀሴ 19 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ለሶስት ዓመታት የሚታሰብ ፍቃድ ሰጥቶኝ የዶክተሬት ትምህርቴን በመከታተል ላይ እገኛለሁ ትምህርት ፍቃድ የተሰጠኝ ሀምሌ 4 ቀን 2001 ዓ/ም ባወጣውና ህዳር 7 ቀን 2002 ዓ/ም በተሻሻለው መመሪያ መሰረት ነው፡፡ በመመሪያው መሰረት በሁለት የትምህርት ፈቃዶች መካከል አንድ አመት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ እንዳለ የተገለጸ ሲሆን ይህን የማያሟላ የአካዳሚክ ተቀጣሪ ፈቃዱን ማግኘት የሚችለው ፈቃድ በሚሆንበት ጊዜ ጥቅማ ጥቅሞቹን መብቶቹን /ደመወዙን ጨምሮ/ ላለመጠየቅ ሲስማማ

ነው ሆኖም የአካዳሚክ ሰራተኛው የተሰጠው ፈቃድ ከመጠናቀቁ በፊት ወደ ዩኒቨርስቲው ተመልሶ ያላሟላውን የአንድ አመት አገልግሎት ከሰጡ፣ ቀደም ሲል በስምምነት መነሻነት የተዋችው ጥቅማ ጥቅም የማግኘት መብት እንደሚኖረው በመመሪያው ተደንግጓል ፡፡ በዚህ መሰረት ከሳሽ የተሰጠኝ የትምህርት ፈቃድ ከማለቁ በፊት ተመልሼ የአንድ አመት አገልግሎት የሰጠሁት ግዴታን የተወጣሁ በመሆኑ ተከሳሽ በስምምነታችን መሰረት ሊከፍለኝ የሚገባውን ደመወዝ ጥቅማ ጥቅም የአየር መጓጓዧ ወጭ እንዲከፍል ብጠይቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ እነዚህን ክፍያዎች ከህጋዊው ወለድ ጋር እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል ፡፡

2. ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ ተከሳሽ በአዋጅ ቁጥር 515/99 እና በደንቡ ቁጥር 77/94 የሚተዳደር በመሆኑ ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሚያስችለው የስረ ነገር ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አቅርቧል ከሳሽ ተከሳሽ ባቀረበበት ጥያቄ መሰረት ከነሀሴ 19 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ የሶስት ዓመት ተሰጥቶ የስራ ውል ተቋርጧል፡፡ ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር ያለው ስምምነት ከጥር 6 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ የተቋረጠ በመሆኑ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው መብትና ጥቅም የለውም የሚልና ሌሎች መከራከሪያዎቹን አቅርቧል፡፡የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር የመነጨው በቅጥር ላይ ከተመሰረተ ግንኙነት ነው የስራ ውሉም የተደረገው የመንግስት ተቋም ከሆነው አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ጋር ነው፡፡ ተከሳሽ መንግስት በሚበጅትለት የሚተዳደር ነው፡፡ ከሳሽና ተከሳሽ ያደረጉት ውል፣ የውሉን አፈጻጸም አስመልክቶ ያለመግባባት ቢፈጠር በፍርድ ቤት ቀርቦ እንደሚታይ የሚገልጽ ቢሆንም ይህ አገላለጽ የግራ ቀኙ ክርክር የሚዳኘው በአስተዳደር ፍ/ቤት መሆኑን የሚያሳይ እንጂ ጉዳዩ ለመደበኛ ፍ/ቤት የሚቀርብ መሆኑን የሚያመላክት አይደለም ስለዚህ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡አመልካች ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካች ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

3. አመልካች አከራካሪው ጭብጥ የአካዳሚው ሰራተኛ የትምህርት ፈቃድ የሚያገኝበትንና የትምህርት እቅድ በተሰጠው ጊዜ መፈጸም የሚገባውን የአንድ ዓመት አገልግሎት የፈጸመ በሆነ ጊዜ ከዩኒቨርሲቲው ሊከፈለው ስለሚገባው ደመወዝ ፤ ጥቅማ ጥቅምና የትራንስፖርት ወጭ የሚመለከት በሌላ አነጋገር የውል አፈጻጸም የሚመለከት ሆኖ እያለ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ብይን መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ሚያዝያ 7 ቀን 2006 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ግንቦት 19 ቀን 2006 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያለው የስቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍ/ቤት እንደሆነ የሚገልጽ መከራከሪያ አቅርቧል፡፡አመልካች ሰኔ 2 ቀን 2006 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍ/ቤት ጉዳዩን በዳኝነት አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለንም በማለት የሰጡት ብይን የህግ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል ፡፡

5. ከላይ የተያዙት ጭብጥን ለመወሰን፣ በመጀመሪያ አመልካች ተጠሪ የሚያከራክራቸው መሰረታዊ ጉዳይ ባህሪና ይዘት የግራ ቀኙ ክርክር የሚፈታበትን መንገድ መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ለስር ፍ/ቤት ክስ ያቀረበው

ከተጠሪው ጋር በተዋዋልነው የመግባቢያ ስምምነት መሰረት የተሰጠኝ የትምህርት ፈቃድ ከማለቁ በፊት፣ ተመልሼ መጥቼ አንድ አመት አገልግሎት የመስጠት ግዴታዬን ተወጥቻለሁ፡፡ተጠሪም በውሉ የገባውንና ደመወዝ፣ጥቅማ ጥቅምና የአየር ትራንስፖርት ወጭ የመሸፈን ግዴታውን እንዲወጣ በፍርድ ተጣርቶ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ ይህም

/ሀ/በተጠሪ ፈቃድና ይሁንታ የዶክትሬት ድግሪ ትምህርቱን ለመከታተል የተፈቀደለት አመልካች፣ ደመወዝ ጥቅማ ጥቅምና የአየር ትራንስፖርት ወጭ ክፍያ ሳይጠይቅ የትምህርት ፈቃድ እንዲሰጠው ያቀረበው ጥያቄ በመቀበል ተጠሪ የሰጠው የትምህርት ፈቃድ መሰረታዊ ይዘትን ባህሪ እንደዚሁም ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው

/ለ/ አመልካች ተጠሪ የሰጠው የትምህርት ፍቃድ ከመጠናቀቁ በፊት ተመልሶ በመምጣት በመመሪያው የተገለጸውን አገልግሎት የሰጠ በሆነ ጊዜ ቀደም ብሎ ላለመጠየቅ ተስማምቶ የተወውን ደመወዝ ጥቅማ ጥቅም እና የአየር የትራንስፖርት ወጪ ክፍያ ለመጠየቅ የሚችልበት ሁኔታ አግባብነት ባለው መመሪያ አመልካችና ተጠሪ ባደረጉት የመግባቢያ ስምምነት ተደንግጓል ወይስ አልተደነገገም?

/ሐ/ ተጠሪ አመልካች የትምህርት ፈቃድ በነበረበት ጊዜ ደመወዝ ጥቅማ ጥቅም እና አየር ትራንስፖርት ወጭ ክፍያ የመክፈል ከውል ወይም ከህግ የመነጨ ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም? የሚሉትን ጭብጦች መርምሮና በማስረጃ አጣርቶ መወሰን የሚጠይቅ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር ለመረዳት ይቻላል፡፡

6. አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩባቸው በላይ የተገለጹበት መሰረታዊ የፍሬ ጉዳይ እና የህግ ጭብጦች አመልካችና ተጠሪ የትምህርት ፈቃድንና አመልካች በትምህርት ፈቃድ ባለበት ጊዜ ተጠሪ ለአመልካች የደመወዝ ጥቅማ ጥቅምና የአየር ትራንስፖርት ወጭ የሚከፍልባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ቅደመ ሁኔታዎቹ ባልተሟሉ ጊዜ ተጠሪ እነዚህን ክፍያዎች ከመክፈል ነፃ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ጉዳይ አመልካች በትምህርት ፈቃድ ለቆየበት ደመወዝ ጥቅማ ጥቅምና የአየር ትራንስፖርት ወጭ ክፍያ ለማግኘት የሚያስችሉትን ቅድመ ሁኔታዎች አመልክቷል፡፡ ወይስ አላመለከተም? አመልካች ቅድመ ሁኔታዎቹን አሟልቷል የሚባል ቢሆን ተጠሪ ለአመልካች መክፈል ያለበትም ምን ያህል ነው? የሚሉትን ጭብጦች የሚያካትት ነው፡፡ ጠቅለል ባለ አነጋገር አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት በመካከላቸው ስላለው የሥራ ቅጥር ውል፣እድገት ወይም ዝውውር ሳይሆን ተጠሪ ለአመልካች የትምህርት ፈቃድ ሲሰጠው በተዋዋሉት የመግባቢያ ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች ያላቸው መብትና ግዴታን ተዋዋይ ወገኖች በውል የገቡትን ግዴታ በአግባቡ የፈጸሙ መሆን አለመሆናቸውና ውል የሚተረጎምበትንና የሚፈጸምበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡

7. ከዚህ አንጻር የሲቪል ሰርቪስ የአስተዳደር ፍ/ቤት አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩባቸውን ከላይ የተገለጹትን የህግና የፍሬ ጉዳዩን ጭብጦች በመመስረት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማት በመመርመርና በመመዘንና በማጣራት ውሳኔ የመስጠት የዳኝነት ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ መመርመር ይጠይቃል፡፡ የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 75 የሚታዩ ጉዳዮችን በዝርዝር ደንግጓል በዚህ ድንጋጌ መሰረት በአስተዳደር ፍ/ቤት ታይተው ውሳኔ የሚያገኙት ከህግ ውጪ ከስራ መታገድ ወይም አገልግሎት መቁረጥ ጉዳይ ከባድ የዲስፒሊን ቅጣት

የተወሰነባቸው ጉዳዮች ሰራተኛው ከህግ ውጭ ደመወዝ ወይም ሌሎች ክፍያዎች የተያዘበት ወይም የተቆረጠበት የሚመለከት ሲሆን በእንግሊዘኛው "an illegal attach ment or deduction of his salary or other payment" ሰራተኛው በስራው ምክንያት በደረሰበት ጉዳት ጋር በተያያዘ መብቱ መጓደልን የሚመለከቱ ጉዳዮች እና ሌሎቹ በአዋጅ አንቀጽ 75 ንዑስ ከአንቀጽ 5 እና ንዑስ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን ጉዳዬች እንደሆነ ተደንግጓል፡፡

8. ይህም የአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 75 ድንጋጌዎች ይዘት ተጠሪ አካዳሚክ ሠራተኞች የትምህርት ፈቃድ የሚሰጥበት ሁኔታ፣በትምህርት ፈቃድ የወሰዱ የአካዳሚክ ሰራተኞች ጋር ባደረገው የመግቢያ ውልና ይህንን በሚመለከት በወጣው መመሪያ መሰረት ለአካዳሚክ ሰራተኞች ስለሚከፍለው ደመወዝ ጥቅማ ጥቅምና የትራንስፖርት ውጭ እና እነዚህን ክፍያዎች ለማግኘት የአካዳሚክ ሰራተኛው ማሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች የተሟሉ መሆናቸውን በማጣራት በአካዳሚክ ሰራተኛው የሚቀርበውን ክስ በቀጥታ ተቀብሎ ማስረጃ ሰምቶ መርምሮ፣ መዝኖና ፍሬ ጉዳይ አጣርቶና አግባብነት ያለውን የውል ስምምነትና የህግ ድንጋጌዎች በመተርጎም የአስተዳደር ፍ/ቤት ውሳኔ የሚሰጥ መሆንን የሚደነግግ አይደለም የክርክሩ ይዘት ባህሪ ክርክሩ የሚያቀርብበትና የሚወስንበት ስርዓት የአስተዳደር ፍ/ቤት የአመልካችና የተጠሪን ጉዳዩ ተቀብለው ለማየትና አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችለው አይደለም፡፡

9. ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበትን ጭብጥ በዳኝነት አይቶ የመወሰን ስልጣን ያላቸው በህግ መንግስቱ አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1 የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የበታች ፍርድ ቤቶች በተጠሪና በአመልካች መካከል የሚደረገውን ክርክር መሰረታዊ ይዘትና ባህሪ ሳይመረምሩ፣ ተጠሪ የመንግስት ተቋምና በመንግስትን በጀት የሚተዳደር መሆኑን በመመልከት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለንም በማለት የሰጡት ውሳኔ ከላይ የገለጽናቸው የህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል ፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል
2. የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር በዳኝነት አይተው የመወሰን ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችና የተጠሪ ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 341/1/ መሰረት መልስን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ያወጡትን ውጭና ኪሳራ በየራሳቸው ይቻሉ

**መዝገቡ ወደ መዝገቡ ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ 105962

ቀን የካቲት 19/2007 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- 1. ቢ.ኤም.ጂ ኃ.የተ.የግል ማህበር
2. ዜድ ኤ.ዲ.ኤስ ኃ.የተ.የግል ማህበር } ጠበቃ ሰለሞን እምሩ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ፕሮፌሰር ባደግ በቀለ - ወኪል ተካልኝ በቀለ ቀረቡ፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ከመንገድ ይከፈትልን ጥያቄ ጋር ተያይዞ በኦሮሚያ ክልል የተነሳን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የቀረበው በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል የተነሳውን ክርክር ለመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን ያለውን ፍርድ ቤትን ለመለየት እና ስልጣን ሳይኖር ዳኝነት ተሰጥቶ ሲገኝ ውሳኔው ሊኖረው ስለሚኖረው ዋጋ ለመወሰን ይቻል ዘንድ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ባሁኑ ተጠሪ ላይ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሚያ ልዩ ዞን ሰበታ አዋስ ወረዳ ፍርድ ቤት በመሰረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካቾች ክስ ይዘትም፡- ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰበታ ከተማ ወስጥ አንደኛው አመልካች 7939 ካ/ሜትር፣ ሁለተኛው አመልካች ደግሞ 8589 ካሬ ሜትር ቦታ ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዲስትሪ ልማት በኢንቨስትመንት መወሰዳቸውን፣ በዚህ ቦታ ላይ ለመውጫና መግቢያ የሚጠቀሙበትን መንገድ የአሁኑ ተጠሪ በመዝጋት መንገዱ እንዲከፈትላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ በሕግ አግባብ ለኢንቨስትመንት ቦታውን መውሰዳቸውንና የዘጉት መንገድ ያለመኖሩን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በዚህ መልክ ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ ከአጣራ በኋላ ተጠሪ አመልካቾች በኢንቨስትመንት በወሰዱት ቦታ ላይ ያለውን መውጫና መግቢያ መንገድ መዝጋታቸው ተረጋግጧል በሚል ድምዳሜ ተጠሪ ለመኪና ተቆፍሮ በተሰራው መንገድ ላይ የሰሩትን አጥር አንስተው መንገዱን እንዲከፍቱ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ጉዳዩን

ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ አቅርበው ግን ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ መንገድ ይከፈትልኝ የሚል በመሆኑ ይህንን አይነት ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን ያለው የወረዳው ፍርድ ቤት ሳይሆን የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በክልሉ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 128/1999 ተደንግጓል በሚል ምክንያት የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካቾች በፌዴራል መንግስት የተመዘገቡ የንግድ ድርጅቶች በመሆናቸው ክርክሩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፣ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ለክልሉ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት የሚቀርብበት አግባብ የሌለ ከመሆኑም በላይ ጉዳዩ ወረዳ ፍርድ ቤት መጀመሩ ስህተት ነው ቢባል እንኳን በይግባኝ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ታይቶ የጸና በመሆኑ ውሳኔው ሙሉ በሙሉ ዋጋ የለውም ተብሎ ውድቅ ሊሆን የሚችልበት የህግ አግባብ የለም በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች በፌዴራል መንግስት የተመዘገቡ የንግድ ድርጅቶች መሆናቸውን፣ ተጠሪም ከክልሉ መንግስት ለኢንቨስትመንት በወሰዱት ቦታ ላይ በሕግ አግባብ ስራቸውን ከማከናወናቸው ውጪ የዘጉት መንገድ የሌለ መሆኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን፣ ክርክሩ የመንገድ ይከፈትልን የዳኝነት ጥያቄን የሚመለከት ቢሆንም ከተከራካሪ ወገኖች መካከል በፌዴራል መንግስት የተመዘገቡ የንግድ ድርጅቶች ያሉበት መሆኑንና በክልሉ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 128/1999 መሰረት የመንገድ ይከፈትልኝ ጥያቄን በመጀመሪያ ደረጃ የስረ ነገር ስልጣን አይቶ ዳኝነት መስጠት የሚችሉት የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች መሆናቸው በግልጽ የተደነገገ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግስትና በክልሎች መዋቀሩን መሰረት በማድረግ የዳኝነቱም ስልጣን በፌዴራል መንግስቱ እና በክልል መንግስታት መካከል እንደተከፋፈለ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 50 እና 51 ስር ተመልክቷል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80 "የፍ/ቤቶች ጣምራነትና ስልጣን" በሚል ርእስ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፤ በክልል ጉዳዮች ላይ በክልሉ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ስልጣኑ የተደነገገ ሲሆን የክልል ፍ/ቤቶች በህገ-መንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና ስልጣን መሰረት ካልሆነ በቀር የፌዴራልን ጉዳይ ለማየት ፤ እንዲሁም የፌዴራል ፍ/ቤቶች የክልልን ጉዳይ ለማስተናገድ የሚያስችል ስልጣን የሌላቸውም መሆኑን በዚሁ ድንጋጌ ስር የተቀመጡት ንዑስ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ያሳያል፡፡ አንድ ጉዳይ የፌዴራል ነው? ወይስ የክልል? የሚለውን ለመለየትም መሰረቱ የአዋጅ ቁጥር 25/88 ሲሆን፣ በዚሁ ህግ አንቀጽ 5 ስር በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ብቸኛ ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የክልል ፍ/ቤቶች ስልጣን የሚኖራቸው በህገ-መንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና

ስልጣን አግባብ ብቻ ነው፡፡ ይህ በግልጽ የሚያሳየው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 መሰረት የፍርድ ቤቶች ስልጣን በጉዳዩ ባለቤትነት (subject matter) የስልጣን ክፍፍል እንደተጠበቀ ሆኖ ክሱም መቅረብ ያለበት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የስረ-ነገር ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ስለመሆኑ ነው፡፡ የፌዴራል ፍ/ቤቶችን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 8፣11፣14 እና 15 ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ ደግሞ አንዳንድ ጉዳዮች ሊያስነሱ በሚችሉት የክርክር ባህርይ ምክንያት ለተወሰኑ ፍ/ቤቶች እንዲቀርቡ በህግ ተለይተው ከተመለከቱት በቀር የስረ-ነገር ስልጣን የተደለደለው በክሱ በተመለከተው የገንዘብ ወይም የንብረት ግምት መነሻ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 14 እና 15 ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ እና የክልል መንግስታት ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ሕጎች ያስረዳሉ፡፡

አመልካቾች በፌዴራል መንግስት የተመዘገቡ የንግድ ማህበራት እንደመሆናቸው መጠን ጉዳዩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5(2) እና 5(6) መሰረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ሆኖ ክርክሩ የተነሳው በክልል ሲሆን የክርክሩ መሰረት ግምት በሌለው የመንገድ ይከፈትልኝ ጥያቄ ላይ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 14 መሰረት ጉዳዩን የማየት የመጀመሪያ ደረጃ የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የሆነውን ጉዳይ በውክልና ስልጣን በመጀመሪያ ደረጃ የስረ ነገር ስልጣን የሚመለከተው የክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(4) ድንጋጌ ተመልክቷል፡፡ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስት አንቀጽ 64(3) እንዲሁም በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 27(4) ድንጋጌዎችም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን የክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውክልና የማየት ስልጣን እንደአለው ተመልክቷል፡፡

የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሰረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(5) በግልጽ ያሳያል፡፡ የኦሮሚያ ክልል ህገ መንግስትም በአንቀጽ 64(4) ይህንኑ አስቀምጧል፡፡ ይህ በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሰረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ባልተቋቋሙባቸው ክልሎችም የሚሰራ ስርዓት ነው፡፡

ይህንኑ በህግ የተዘረጋውን ስርዓት መሰረት አድርገን ጉዳዩን ስንመለከተው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ስር የሚወድቁ ጉዳዮች በቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ወይም በወረዳ ፍርድ ቤት የሚታይበት አግባብ የለም፡፡ በክልሉ መንግስት ኢንቨስትመንት ፈቃድ ወስደው የመንገድ ይከፈትልኝ ክርክር ከሚያነሱ ወገኖች መካከል አንዱ በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ይኼው አካል/ተቋም/ የክርክሩ ተካፋይ መሆኑ ብቻውን ጉዳዩን የፌዴራል ጉዳይ የሚያደረገውበመሆኑ በክልሉ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት ጉዳዩ እንዲታይ የሚደረግበት የህግ አግባብ የለም፡፡ ጉዳዩ የፌዴራል መንግስት አወቃቀርን መሰረት አድርጎ ያልታየ መሆኑና በስርዓቱ መሰረት በክርክር ላይ ባለበት ሁኔታ የስረ ነገር ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሳኔ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ጉዳዩን በመጀመሪያ የስረ ነገር ስልጣን የሚመለከተው ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ አጽንቶታል በሚል ምክንያት ብቻም ውሳኔው ዋጋ እንዲኖረው ማድረግ ከይግባኝ መብት እንዲሁም የፍርድ ቤቶች የስልጣን ድልድል መነሻ ከሚያደርጋቸው ምክንያቶች አንጻር ሲታይም ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡

ስለሆነም አመልካቾች በፌዴራል መንግስት የተመዘገቡ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ እና ክርክሩን ያስነሳው ጉዳይም ግምት የሌለው ሁኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የመንገድ ይከፈትልኝ የሚል ነው በሚል ምክንያት ብቻ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ነው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ቢሆንም ከላይ እንደተመለከተው ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ ሁኖ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የሚወድቅ ሲሆን በህገ መንግስቱ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ መታየት ያለበት በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መሻሩ በውጤት ደረጃ የሚነቀፍ ሁኖ አላገኘነውም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 180394 ነሐሴ 12 ቀን 2006ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. ጉዳዩን በቀጥታ አይቶ የመዳኘት ስልጣን ያለው የክልሉ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት አይደለም ብለናል፡፡ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(4) ፣ አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 14፣ በኦሮሚያ ክልል ህገ መንግስት አንቀጽ 64(3) እንዲሁም በክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 27(4) ድንጋጌ መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው የክልሉ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል::**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

የሰ/መ/ቁ.99375

መጋቢት 15 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አምባቸዉ አለሙ - ጠበቃ ፋሲል ቀረበ

ተጠሪዎች፡-1ኛ የካ/ክ/ከ/ወ/01/አስተደር - የቀረበ የለም

2ኛ አቶ አሸናፊ መንገሻ

3ኛ አቶ አገስት አድነዉ

4ኛ አቶ አድማሱ አንጀሎ

*መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡*

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሾች ነበሩ፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ በተለምዶ ፈረንሳይ ለጋሲዩን ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ በግምት 5 ሄክታር የተጎዳ መሬት በ 1985 ዓ/ም ተረክቤ የተለያዩ የዉጭ እና የሀገር ዉስጥ ዛፎች አልምቼ ዙሪያዉን በግንብና በሽቦ አጥር በመከለል፤ በርካታ የንብ፤ እንስሳት እርባታ፤ የእንግዳ መቀበያ እና መዝናኛ ቤቶች የሚገኙበትን የተሟላ መናፈሻ አቋቁሜ እያለሁ ተጠሪዎች እኔ በማላዉቀዉ ሁኔታ በመምጣት መናፈሻዉን በዉስጡ የነበሩትን ንብረቶችን አዉድመውብኛል ፤ግምቱንና የተቋረጠ ገቢ ብር 30,822,160.00(ሰላሳ ሚሊዩን ስምንት መቶ ሃያ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ብር) ከፍለዉኝ ድርጅቱን እንዲያስረክቡኝ ሲል ጠይቋል፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰጠዉ መልስ አመልካች ይዞታዉን በህጋዊ መንገድ አልተረከበም፣ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1195 እና በደንብ ቁ.14/96 መሰረት ያቀረበዉ ማስረጃ የለም፣ ወደመ የተባለዉም ንብረት ስለመኖሩም አልተረጋገጠም፣ አመልካች ይዞታን አለቅም የሚል ሲሆን ተጠሪ በህግ በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ያከናወነው ተግባር በመሆኑ ሊከስ መብት የለዉም፣ ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም ከክርክሩና ከቀረበዉ ማስረጃ አመልካች ድርጅቱን በእጃቸዉ አድርገዉ የተለያዩ ስራዎችን እየሰሩበት የነበረ መሆኑ አልተካደም፣ ንብረት መዉደም ያለመዉደሙ በፍሬ ነገር ክርክር ወቅት የሚታይ በመሆኑ፣ ፍርድ ቤቱ የሰረ ነገር ስልጣን ያለዉ መሆኑን ስናይ በአዋጅ ቁ.361/1995 አንቀጽ 41(1) ((ረ))

መሰረት የአዲስ አበባ መስተዳድር አስፈጻሚ አካላት በህግ በተሰጣቸዉ ስልጣንና ተግባር ጋር በተያያዙ ለሚነሱ ክርክሮች ስልጣን ያላቸዉ የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች በመሆኑ የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት በፍ.ብሥ.ሥ.ህ.ቁ 244(2)((ሀ)) መሰረት ሳይቀበለዉ ቀርቷል፡፡የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎትም የአመልካችን ቅሬታ ባለመቀበል ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአመልካች አቤቱታም የቀረበዉ ይህንኑ ዉሳኔ ለማስቀየር ነዉ ፡፡በመሆኑም አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸዉን ሲገልጹ፡- ለደረሰብኝ ጉዳት ካሳ ገንዘቡን ገምቼ አቅርቤ እያለሁ ፍርድ ቤቱ የአዲስ አበባ አስተዳደር አስፈጻሚ አካል ጋር የዳኝነት ጥያቄዬን በማገናኘት በአዋጅ ቁ. 361/95 41(1)( ሀ) መሰረት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም ብለዋል ፤የአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 41 ስር ከተዘረዘሩት ዉስጥ አስተዳደሩ በግለሰቦች ላይ ለሚያደርሰው የንብረት ጉዳት ላይ የሚቀርብየካሳይከፈለኝ ጥያቄ አይቶ ለመወሰን ስልጣን እንዳላቸዉ አይገልጽም፤ በመሆኑም የደረሰብኝንጉዳት ገልጬ ያቀረብኩትን ክስ ተጠቃሹን አዋጅ መሰረት በማድረግ ስልጣን የለኝም ማለቱ አግባብነት የለዉም፤ ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን በአዋጅ 25/88 መሰረት የፌደራል ፍርድ ቤቶች በመሆኑ የቀረበዉ የዳኝነት ጥያቄን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የተሰጠዉ ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

በዚህም መሰረት ችሎቱም የቀረበዉን ካሳ ክፍያ ጥያቄ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማየት ስልጣን የለኝም ብለዉ የመወሰናቸዉን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ 1ኛ ተጠሪ እና አመልካችን በጽሁፍ መልስና የመልስ መልስ በማቀባበል አከራክሯል፡፡ከ2ኛእስከ 4ኛ ተራ ያሉትን ተጠሪዎችን አስመልክቶ ጥሪ ቢደረግላቸዉም ባለመቅረባቸዉ በጽሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፏል፡፡

ተጠሪ በሰበር በሰጠዉ መልስ የሚለዉ ጉዳዩ በቀጥታ ከተጠሪ ጋር ግንኙነት ያለዉና የክርክሩም መሰረት መሬት በመሆኑ ከአንድ ስረ ነገር የሚመነጩትን ጥያቄ በአንድ ቦታ መቅረቡ እና ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ብይኑ የሚነቀፍበት ምክንያት የለም፡፡ አመልካች መሬቱን የያዙት በህጋዊ መንገድ ባለመሆኑ በፍ.ብ.ህ.ቁ.1178 መሰረት ካሳ ሊጠይቁ አይገባም፣ በህግ ባልተፈቀደላቸዉ ቦታ ላይ ያሰፈሩትን መጠየቅ መብት የላቸዉም፡፡ የተሰጣቸዉን ማስጠንቀቂያ ወደጎን በማለት ሲጠቀሙበት የነበረ በመሆኑ የወሰድነዉ እርምጃ ሊነቀፍ አይገባም፤ ስለዚህ የተሰጠዉ ብይን ተገቢ ነዉ ይባልልን በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩላቸዉ ይዞታዉን እንድለቅ ሳልጠየቅ ደብዳቤ ሳይደርሰኝ ለ16 አመታት ስገብርበት የያዝኩትን ድርጅትና ንብረት አዉድሞብኛል ፤ጉዳዩ የቦታ ማስለቀቅ ጉዳይም አይደለም፤ ስለዚህ በስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዲስ አበባ ፍርድ ቤት ነዉ መባሉ ሊታረም ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመረምረው የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን በአዋጅ ቁ.361/95 በአንቀጽ 41 የተዘረዘረ ሲሆን ከከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት የመቆጣጠር ስልጣንና ተግባር ጋር በተያያዘ የሚነሱ ጉዳዮችን አይቶ የመወሰን ስልጣን እንዳለው በአዋጁ አንቀጽ 41/1/ለ/ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አኳያ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች ከሕግ ውጪ ተያዘ

የተባለውን ቦታ በሕግ በተሰጠው ስልጣን አግባብ መቆጣጠር፣ተገቢውን ክትትል ማድረግና አስፈላጊ ሁኖ ሲገኝም ተገቢውን እርምጃ መውሰድ የሚችሉ መሆኑ ግልጽ ነው። ሆኖም በዚህ ጉዳይ የቀረበውን ክርክር ይዘቱን እንዳየነዉ የአመልካች ጥያቄ የነበረዉ ተጠሪዎች ተረክቤ በይዞታዬ ስር የሚገኘዉን እና አልምቼ የምገለገልበትን መናፈሻ እና በዉስጡ የሚገኙትን የተለያዩ ንብረቶች እኔ በሌለሁበት ከሕግ ውጪ አዉድመውብኛል፣ በመሆኑም በግምት ብር 30,822,160 ያለው ንብረት የወደመብኝ በመሆኑ ገቢዬ ተቋርጧል፣ ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚገዙ ድንጋጌዎች አግባብ ካሳ ይክፈሉኝ የሚል መሆኑን ከመዝገቡ የምንረዳዉ ነው።ይሁንና ጉዳዩ የቀረበለት ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፤አዋጅ ቁ 361(41) ለ በመጥቀስ የአዲስ አበባ አሰተዳደር አስፈጻሚ አካላት በህግ በተሰጣቸዉ ስልጣንና ተግባር ስር የሚቀርቡትን ጉዳዮች የመዳኘት የስረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት በብይን መዝገቡን ዘግቶታል። ስለዚህ ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነዉ የአመልካች ዋና የዳኝነት ጥያቄ የነበረዉ በንብረታቸዉ ላይ ለደረሰዉ የጉዳት ካሳና የቀረ ጥቅም ይከፈለኝ የሚል ነው።በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ የአስተዳደር አካል የክርክሩ ተሳታፊ በመሆኑ ብቻ በተጠቃሹ አዋጅም ሆነ የአዋጁ ማሻሻያ በሆነው በአዋጅ ቁጥር 408/1996 ድንጋጌዎች ስር በግልጽ እንዲህ አይነት የካሳ ጥያቄ ለመዳኘት ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ስልጣን መሰጠቱ ሳይደነገግ የቀረበለትን ጉዳይ ተጠቃሹን አዋጅ በመጥቀስ ስልጣን የለኝም ሲል በብይን መዝገቡን መዝጋታቸው ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል።

ባጠቃላይ የከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በአዋጅ 25/88 መሰረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን መሆኑን አዉቆ በፍሬ ነገር ደረጃ መርምሮ አስፈላጊዉን ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ በብይን መዝጋቱና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎትም ሳይታረም መቅረቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ብለናል። በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል።

<u>ዉሳኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.108063 በቀን 08/05/2006 ዓ/ም የተሰጠዉና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት በመ.ቁ. 97764 በቀን 26/6/2006 ዓ/.ም የጸናው ውሳኔ ተሽሯል።
2. የፌዴራል ከፍተኛዉ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማከራከር (ማየት) ስልጣን እንዳለዉ አዉቆ አግባብነት ካላቸዉ ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል።ይጻፍ።
3. የግራቀኙ የዚህን ችሎት የወጪ ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል::

መዝገቡ ዉሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል።

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።**

የሰ/መ/ቁ 104511

መጋቢት 30 ቀን 2007

ዳኞች፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-1. ዳኜ ሀይሉ } ጠበቃ ታየ ቀረበ

2. በከልቻ መኮንን

ተጠሪዎች፡-1. አለምሰገድ ሀብታሙ - የቀረበ የለም

2. ታሪኩ ተክሌ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረዉ በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን ቡሌ ሆራ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካቾች ተከሳሽ ተጠሪዎች ከሳሾች ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ 1ኛ አመልካች የዕቁብ ሰብሳቢ 2ኛ ተጠሪ ዳኛ እና ጸሀፊ፤ ተጠሪዎች አባል በመሆን1ኛ ተጠሪን በ01/01/2005 ብር 50000 ደርሶአቸዉ 2ኛ ተጠሪን 08/07/2005 ዓም ብር 60,000 ደርሷቸዉ ከቡሌ ሆራ አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክእንዲወስዱ ቼክ ተሰጥቷቸዉ ወደ ባንክ ሄደዉ በቂ ገንዘብ የለም በመባላቸዉ አመልካቾች በጋራ እና በተናጥል ይክፈሉንበማለት ጠይቋል፡፡አመልካቾች ባለመቅረባቸዉ በሌሉበት በማየት ተጠሪዎች የእቁቡ አባል መሆናቸዉን በማረጋገጥ በተጠቃሹ ቼክ ባንክ ቤት ሄደዉ ገንዘቡን በማጣታቸዉና አመልካቾችም የዕቁቡ ሀላፊዎች በመሆናቸዉ 110,000.00 ብር ለተጠሪዎች የመክፈል ሀላፊነት አለባቸዉ በማለት ወስኗል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በማከራከር የስር ፍርድ ቤትን ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡በመጨረሻም ጉዳዩን ያየዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የቼክ ክርክር በመሆኑ በአዋጅ ቁ. 25/1988 መሰረት የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

የአመልካቾች አቤቱታም የቀረበዉ ይህንኑ ዉሳኔ ለማስቀየር ነዉ፡፡በመሆኑም አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ቅሬታቸዉን ሲገልጹ፡-በስር የቀረበዉ ክስ የነበረዉ ያልተከፈለኝ የእቁብ ገንዘብ እንዲከፈለን፤ የሚል ሆኖ ሳለ ክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ የቼክ ክርክር በመሆኑ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የአዋጅ ቁ.25/88 አንቀጽ 5(7) መሰረት መዝጋቱ ባግባቡ አይደለም፤ አመልካቾች የእቁብ ጸሀፊና ሰብሳቢ ናቸዉ በማለት፤ በምስክር ሳይጣራ ክፈሉ መባላችን ሊታረም ይገባል፤ ቼኩ የተፈረመዉ በስር ተከሳሽ በነበሩት

አቶ ቦጋለ ግዛዉ ስም ነዉ፤አመልካቾች ከቼኩ ጋር ግንኙነት የለንም፤ አልሰበሰብንም፤ የዕቁቡ ዳኛ መሆኑንና የሚመለከተዉ መሆኑን አዉቆ ጠፍቶ እያለ የአሁን አመልካቾችን ሀላፊ ናችሁ መባላችን ስህተት ነዉ፣ የዕቁብ ደንብ ለዕቁብተኞች ዉል ነዉ ፤እኛ ደግሞ ከዉልም ሆነ ከህግ የመነጨ ግዴታ የለብንም፣ ስለዚህ ገንዘቡን የመክፈል ሀላፊነት አለባችሁ ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ጠይቀዋል፡፡

በዚህም መሰረት የአመልካቾች እና ተጠሪዎች ክርክር በቼክ አማካኝነት የተሰጠን የዕቁብ ገንዘብ በቂ ስንቅ ባለመኖሩ ሊከፈለን ባለመቻሉ ይከፈለን በማለት የጠየቁት ዳኝነት የክልሉ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በአዋጅ ቁ.25/88 መሰረት ለማየት ስልጣን የለኝም ማለቱን አግባብነት በጭብጥነት በመያዝ ተጠሪዎች ባለመቅረባቸዉ መልስ መስጠት መብታቸዉ ታልፎ በአመልካቾች የቀረበዉን ቅሬታ እና የስር ክርክርን አይተናል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተጠቀሰዉን ይመስላል፡፡ በመሆኑም የግራቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የህግ ድንጋጌ አንጻር መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንግዲህ ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር የስር ክርክርን እንዳየነዉ ተጠሪዎችባቀረቡት ክስ በአመልካቾች ሰብሳቢነት፤ ጸሀፊነት እና የስር 2ኛ ተከሳሽ ዳኛ በሆኑበት የእቁብ አባል በመሆን እቁብ ደርሷቸዉ ተጠቃሹን ገንዘብ እንዲወስዱ ቼክ ተሰጥቷቸዉ ወደ ቡሌ ሆራ  አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በመሄድ በቂ ስንቅ ባለመኖሩ መዉሰድ ባለመቻላቸዉ  አመልካቾች በቼክ የተጠቀሰዉን ገንዘብ በአንድነትና ነጠላ እንዲከፍሏቸዉ በጠየቁት መሰረት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት  ጉዳዩን በማከራከር ዳኝነት ቢሰጡም በመጨረሻ ጉዳዩ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ችሎት ክርክሩ ከቼክ ጋር የተያያዘ በመሆኑ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት አዋጅ ቁ 25/88 5(7) በመጥቀስ ቅሬታዉን ሰርዞታል፡፡በዚህም ችሎት ሊታይ የሚገባዉ ነጥብ ሆኖ የተገኘዉ የሰበር ችሎቱ ጉዳዩን ያለማስተናገዱን አግባብነት ነዉ፤ በመሆኑም የግራቀኙ መሰረታዊ ክርክር ዕቁብን ተከትሎ ያዋጡት ገንዘብ የመከፈያ ቀኑ ደርሶ አመልካቾች የእቁቡ አመራር በመሆናቸዉ ተጠቃሹን ገንዘብ የመክፈል ሀላፊነት ስላላቸዉ ቼክ ቆርጠዉ በሰጧቸዉ መሰረት ወደ ባንክ ቤት በመሄድ ገንዘባቸዉን ባለማግኘታቸዉ የዕቁቡን ግንኙነታቸዉን መሰረት አድርጎ እንዲመለስላቸዉ የቀረበ ዳኝነት እንጂ የክርክሩ መሰረት ቼክ ነዉ በማለት አይደለም፡፡ ቼክ የዕቁብ ገንዘቡ ላለመከፈሉ ማረጋገጫ ሆኖ በተራ ሰነድ ማስረጃነት የቀረበ እንጂ በዋናነት ቼኩ ራሱ በንግድ ሕጉ የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን አተገባበር ለመመርመር የሚያስችል ክርክር በሚያስነሳ መልኩ የቀረበ ያለመሆኑን ከክርክሩ ይዘት ለመረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ የክርክሩ አጠቃላይ ይዘት የእቁብ ገንዘብን ይከፈለኝ ጥያቄ መሰረት አድርጎ ቼኩን በተራ የሰነድ ማስረጃነት የቀረበበት ሁኖ ሳለ የክልሉ ሰበር ችሎት የግራቀኙን የተጠየቀዉን ዳኝነት እና የክርክሩን አቅጣጫ ባላገናዘበ መልኩ ጉዳዩ በአዋጁ ቁ.25/88 ስር የሚታይ ነዉ ሲል የሰበር አቤቱታውን ሳይመለከተው መዝገቡን መዝጋቱ ስነ ስርዓታዊ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ባጠቃላይ ክልሉ ከፍተኛ እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በቀረበላቸዉ የዳኝነት ጥያቄ አከራክረዉ ዉሳኔ ላይ ቢደርሱም የክልሉ ሰበር ችሎት የቀረበለትን የዳኝነት ጥያቄ ከወዲሁ ስልጣኔ አይደለም ,በማለት መዝገቡን መዝጋቱ የክርክሩን ይዘት ያላገናዘበ

በመሆኑ ትዕዛዙ መሰረታዊ የሆነ ህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. በኦሮሚያ ክልል የቦረና ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 08843 በቀን 18/10/2005 ዓ/ም እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 168299 በቀን 26/9/2006 ዓ/ም የሰጡትን ዉሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 34(1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2. ጉዳዩ በክልሉ የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት በክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የታዬ በመሆኑ የክርክሩ ይዘትም የፌዴራል ጉዳይ ሊባል የማይችል፣የቼክ ጉዳይ ባለመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው ብለናል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ሰበር አጣሪ ችሎት በበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይፃፍ፡፡

3. የግራቀኙ የወጪ ኪሳራቸዉን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ዉሳኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

# ቤተሰብ

የሰ/መ/ቁ. 94952

መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

መኰንን ገ/ሕይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አመልካች፡- ወ/ሮ ዙሪያሽ ተገኝ - የቀረበ የለም፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ የሺ ውድዬ - ረ/ኢንስፔክተር ይመር ዮሴፍ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በሞት የተለየው ተጋቢ የግል ንብረት ነው የተባለን ቤት ከሌላኛዋ ተጋቢ ለማስለቀቅ ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበሩት በአሁኗ አመልካች ላይ በ08/02/2003 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የክሱይዘትም ባጭሩ፡-ከሳሽ የሟች ልጃቸው አቶታደሰ የሱፍ እናት እና ወራሽ መሆናቸውን፣ሟች እና ተከሳሽ በ17/09/1997 ዓ.ም. በባህላዊ ስርዓት ጋብቻ ፈጽመው አብረው ይኖሩ የነበረ መሆኑን፣በን/ስ/ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 09/14 የሚገኘው ቁጥሩ አዲስ የሆነው መኖሪያ ቤት ከጋብቻው በፊት የተፈራ የአቶ ታደሰ የሱፍ የግል ሀብት ስለመሆኑ ጋብቻውን በፈጸሙበት ጊዜ ባደረጉት የጋብቻ ውል ማረጋገጣቸውን፣ይሁን እንጂ ጋብቻው በልጃቸው ሞት ምክንያት መፍረሱን ተከትሎ ተከሳሽ ቤቱን እና በክሱ የተጠቀሱ የቤት ቁሳቁሶችን ለከሳሽ እንዲያስረክቡ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ መቅረታቸውን የሚገልጽ ሆኖ ተከሳሽ የዋጋ ግምቱ ብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ) የሆነውን ቤት እና የብር 10,000 (አስር ሺህ) የዋጋ ግምት ያላቸውን የቤት ቁሳቁሶች ለከሳሽ እንዲያስረክቡ እና ለስምንት ወራት ከቤቱ ኪራይ የሰበሰቡትን ገንዘብ ብር 8,000 (ስምንት ሺህ) ለከሳሽ እንዲከፍሉ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተከሳሽ በበኩላቸው በ09/07/2003 ዓ.ም. በሰጡት መልስ ከጋብቻው በፊት ሟች የሰሩት አንድ ሳሎን እና አንድ መኝታ ያለው ሁለት ክፍል ቤት ሆኖ ከጋብቻቸው በኃላ ሶስት ተጨማሪ ክፍሎችን ከሟች ጋር የሰሩ በመሆኑ ቤቱ በሙሉ የሟች የግል ሀብት እንደሆነ ተደርጎ የቀረበው ክስ ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣የቤት ቁሳቁሶቹ ግምት ከብር 1,000 የማይበልጥ መሆኑን እና ከቤቱ ኪራይ የተሰበሰበው የገንዘብ መጠንም ከቀለብ አልፎ ሊጠራቀም የማይችል መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ ውርሱ ተጣርቶ ሪፖርት እንዲቀርብለት ጉዳዩን ለውርስ አጣሪ የመራው ሲሆን አጣሪው ውርሱን ማጣራቱን ገልጾ ነገር ግን ቤቱ ሰነድ አልባ ስለመሆኑ ግራ ቀኙ የተማመኑ በመሆኑ የውርስ ሀብት ነው ለማለት ያልተቻለ መሆኑን በመግለጽ ሪፖርት አቅርቧል፡፡ፍርድ ቤቱ በበኩሉ ቤቱ ሰነድ አልባ መሆኑ ክርክሩን አይቶ ውሳኔ ከመስጠት የማይከለክል መሆኑን እና በመዝገቡ የሚሰጠው ውሳኔ ተፈጻሚነት የሚኖረው የቤቱን ሕጋዊነት በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ተመስርቶ መሆኑን ገልጾ ተጋቢዎቹ ከጋብቻቸው በኃላ የሰሩት ተጨማሪ ግንባታ መኖር አለመኖሩን ለማጣራት የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኂላ ቤቱ የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ስለመሆኑ ተከሳሽ በፈረሙት የጋብቻ ውል በማረጋገጣቸው ከቤቱ ድርሻ አላቸው ማለት ያልተቻለ መሆኑን፣ቤቱ በጋብቻ ውሉ ላይ የተገለጸው "ቤት" ተብሎ እንጂ የተከሳሽ ምስክሮች እንደገለጹት "የሸራ ወይም የላስቲክ ቤት" ተብሎ አለመሆኑን፣ስለቤት ቁሳቁሶች በከሳሽ ምስክሮች የተገለጸ ነገር አለመኖሩን እና ከቤቱ ኪራይ ይሰበሰብ የነበረው የገንዘብ መጠንም ከቀለብ አልፎ ሊጠራቀም የሚችል አለመሆኑን በዝርዝር በመግለጽ ተከሳሽ ክስ ያስነሳውን ቤት ለከሳሽ ለቀው እንዲያስረክቡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን አቤቱታው ተመርምሮ በጋብቻ ውሉ ላይ ቤቱ የአቶ ታደሰ የሱፍ የግል ንብረት ነው ተብሎ መጠቀሱን ብቻ መሰረት በማድረግ በጋብቻው ጊዜ በሁለቱ ተጋቢዎች በጋራ ከታደሰው ቤት እና በጋራ ከተሰሩት ተጨማሪ ክፍሎች ውስጥ አመልካች ድርሻ የላቸውም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዋ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ክርክሩ የታየበትን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መዝገብ በማስቀረብ ጭምር ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች አድራሻው በክሱ የተጠቀሰው ቤት ከጋብቻው በፊት የተፈራ የተጠሪ አውራሽ የግል ንብረት መሆኑን በማረጋገጥ ጋብቻው በተፈጸመበት ጊዜ የጋብቻ ውል የፈረሙ መሆኑ በአመልካች ያልተካደ እና የጋብቻ የውል ሰነዱን ጨምሮ በማስረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ የጋብቻ ውሉ በተፈረመበት ጊዜ የነበረው ከላስቲክ እና ከሸራ የተሰራ ዳስ ሆኖ እያለ ቤት እንደሆነ አድርገው ያስፈረሙኝ አላግባብ ነው በማለት አመልካች በሰበር ማመልከቻቸው ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል ግን በጋብቻው ወቅት ተጨማሪ ክፍሎች የተገነቡ ወይም የተሰሩ ስለመሆኑ በማስረጃ ተረጋግጦ እያለ ቤቱ ሙሉ በሙሉ የሟች የግል ሀብት እንደሆነ ተደርጎ ለተጠሪ እንድትለቅ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት አመልካች ያቀረቡት የአቤቱታ ነጥብ በክርክሩ ከተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች አንጻር በአግባቡ ሊጤን እና ሊመረመር የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በዚህም መሰረት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የሚያየው ፍርድ ቤት በፍትሐብሄር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 246፣247 እና 248 ድንጋጌዎች መሰረት ለጉዳዩ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችለውን ጭብጥ ይዞ ጉዳዩን በማስረጃ ካጣራ በኃላ ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ በክርክሩ የተያዘው ጭብጥ ምን እንደሆነ፣ጭብጡ እንዴት እንደተወሰነና በአንድ ወይም በሌላ አግባብ የተወሰነው በምን ምክንያት እንደሆነ በፍርድ ሀተታው ውስጥ መግለጽ እንዳለበት በቁጥር 182 (1) ስር በአስገዳጅነት ተደንግጎአል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት እና የተከራከሩት በጋብቻ ውሉ መሰረት ክርክር ያስነሳው ቤት የልጃቸው የግል ሀብት መሆኑን በመግለጽ ሲሆን አመልካች በበኩላቸው መልስ የሰጡት እና የተከራከሩት ከተጠሪ ልጅ ጋር በጋብቻ ውስጥ በኖሩባቸው ከ1997 ዓ.ም.እስከ 2002

ዓ.ም.ድረስ ባሉት ጊዜያት ቀደም ሲል ከነበሩት ሁለት ክፍል ቤቶች በተጨማሪ ሶስት ክፍል ቤቶችን በጋራ መስራታቸውን በመግለጽ ነው፡፡ከዚህ የግራ ቀኙ የክርክር አቋም በመነሳት በማስረጃ ሊጣራ የሚገባው ተጋቢዎቹ ከጋብቻቸው በኃላ የሰሩት ተጨማሪ ግንባታ አለ ወይስ የለም? የሚል ነጥብ መሆኑን በመግለጽ ፍርድ ቤቱ ለክርክሩ የያዘው ጭብጥ ተገቢነት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ ጭብጥ ላይ የተሰሙት የግራ ቀኙ ምስክሮች ቃል ሲታይም በአሁኗ አመልካች በኩል የተሰሙት ሁለት ምስክሮች ሟች ከቀድሞ ሚስታቸው ጋር የሰሩትን አንድ ክፍል ቤት አመልካች እና የተጠሪ ልጅ በጋብቻቸው ጊዜ አፍርሰው ቤቱን እንደ አዲስ ሶስት ክፍል አድርገው መስራታቸውን በተመሳሳይ ሁኔታ የገለጹ መሆኑን እንዲሁም በአሁኗ ተጠሪ በኩል ከተሰሙት ሁለት ምስክሮች መካከል 2ኛው ምስክር ቤቱ ጎርፍ የሚገባበት በመሆኑ አጥሩ ሲፈርስ የተጠጋገነ ከመሆኑ ውጪ ከጋብቻው በኃላ የተሰራ ቤት አለመኖሩን በመግለጽ የመሰከሩ ቢሆንም የተጠሪ 1ኛ ምስክር ግን ሟች ከቀድሞ ባለቤታቸው ጋር የሰሩት ዋናውን ቤት መሆኑን እና ከአመልካች ጋር ጋብቻ ከፈጸሙ በኃላ ደግሞ ሁለት ክፍል ቤት እና ኩሽና በጋራ መስራታቸውን በመግለጽ መመስከራቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ፍርድ ቤቱም ከላይ በተጠቀሰው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 182 (1) አስገዳጅ ድንጋጌ መሰረት ውሳኔውን በሚሰጥበት ጊዜ ይህንን የግራ ቀኙን ምስክሮች የምስክርነት ቃል መዝኖ የአንደኛውን ወይም የሌላኛውን ወገን ምስክሮች የምስክርነት ቃል የተቀበለበትን ወይም ያልተቀበለበትን ምክንያት በውሳኔው ላይ ማስፈር የሚጠበቅበት ሆኖ እያለ ቤቱ የሟች የግል ሀብት ነው በማለት ለደረሰበት ድምዳሜ እና ለሰጠው ውሳኔ መሰረት ያደረገው የጋብቻ ውሉን ብቻ መሆኑን የውሳኔው ይዘት ያመለክታል፡፡
ይህም በአንድ በኩል ተጋቢዎቹ ከጋብቻቸው በኃላ የሰሩት ተጨማሪ ግንባታ አለ ወይስ የለም? በሚል ፍርድ ቤቱ በጭብጥነት የያዘው ነጥብ ከግራ ቀኙ የክርክር አቋም አንጻር ተገቢነት ያለው ቢሆንም በሌላ በኩል ግን ቤቱ በጋብቻ ውሉ መሰረት የሟች የግል ሀብት ነው በማለት የደረሰበት ድማዳሜ እና የሰጠው ውሳኔ ከላይ የተጠቀሰውን ጭብጥ ለማጣራት በተሰሙት የግራ ቀኙ ምስክሮች ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡የዚህ ዓይነቱ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ደግሞ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 182 (1) አስገዳጅ ድንጋጌን እና በአንድ ክርክር በመዝገቡ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 36848 በ11/02/2001 ዓ.ም. እና በሌሎችም መዝገቦች የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚቃረን በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡

በክርክሩ በማስረጃ የተረጋገጠው ፍሬ ነገር ከጋብቻው በፊት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት መሆኑ በጋብቻ ውሉ ከተረጋገጠው አንድ ክፍል ዋናው ቤት በተጨማሪ ተጋቢዎቹ በጋብቻቸው ጊዜ ሶስት ተጨማሪ ክፍሎችን መስራታቸው ከሆነ ደግሞ ይህ ሁኔታ በግራ ቀኙ መብትና ግዴታ ላይ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት መታየት ይኖርበታል፡፡በመሰረቱ ተጋቢዎች ከጋብቻቸው በፊት በየግል የነበሯቸው ንብረቶች የየግላቸው ሆነው እንደሚቀሩ እና ከጋብቻቸው በኃላ ያፈሯቸው ንብረቶች ግን የጋራቸው እንደሚሆኑ በአዋጅ ቁጥር 213/1992 በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 57 እና 62 ድንጋጌዎች ተመልክቷል፡፡በተያዘው ጉዳይ ከጋብቻው በፊት የነበረው እና በጋብቻ ውሉ የአንደኛው ተጋቢ የግል ንብረት ነው ተብሎ የነበረው አንድ ክፍል ዋናው ቤትም ቢሆን በጋብቻው ውስጥ ፈርሶ እንደ አዲስ መሰራቱ እና ኩሽናውን ጨምሮ ሶስት ተጨማሪ ክፍሎች በጋብቻው ውስጥ መሰራታቸው በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ከጋብቻው በፊት የነበረው ቤት ፈርሶ እንደ አዲስ የተሰራ እና ሶስት ተጨማሪ ክፍሎች የተሰሩ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ እነዚህ ስራዎች የተከናወኑት በጋብቻው ውስጥ እስከሆነ እና እነዚህ ተጨማሪ ስራዎች

የተከናወኑት በሟች የግል ገንዘብ ነው በሚል የቀረበ ክርክር እና ማስረጃ እስከሌለ ድረስ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 63 (1) መሰረት ክርክር ያስነሳው ቤት የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ስለመሆኑ የሕግ ግምት የሚወሰድበት ነው፡፡

ሲጠቃለል ከጋብቻው በኃላ ስለተከናወኑት ተጨማሪ ስራዎች በግራ ቀኙ ምስክሮች የተመሰከረውን ፍሬ ነገር በዝምታ አልፎ በጋብቻ ውሉ ላይ ብቻ በማተኮር ክርክር ያስነሳው ቤት ከጋብቻው በፊት የተፈራ የሟች የግል ንብረት ነው በማለት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናው ውሳኔ በማስረጃ ከተረጋገጠው ፍሬ ነገር ውጪ የተሰጠ እና መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58686 በ02/07/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 135319 በ22/02/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ በን/ላ/ክፍለ ከተማ በቀበሌ 09/14 የሚገኘው ቁጥሩ አዲስ የሆነው መኖሪያ ቤት ከጋብቻው በፊት የተፈራ የአቶ ታደሰ የሱፍ የግል ንብረት በመሆኑ አመልካች ቤቱን ለቀው ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል በሚል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
3. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው በን/ላ/ክፍለ ከተማ በቀበሌ 09/14 የሚገኘው ቁጥሩ አዲስ የሆነው መኖሪያ ቤት ሟች አቶ ታደሰ የሱፍ እና አመልካች በጋብቻው ጊዜ ያፈሩት የጋራ ሀብት ነው በማለት ወስነናል፡፡
4. ከላይ ከተጠቀሰው ቤት ውስጥ ግማሹ የአመልካች በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ሀብት፣ቀሪው ግማሽ ደግሞ የተጠሪ የውርስ ሀብት በመሆኑ ግራ ቀኙ የሚቻል ከሆነ በዓይነት፣የማይቻል ከሆነ በስምምነት አንዳቸው ለሌላኛው የዋጋ ግምት ድርሻ ከፍሎ በማስቀረት፣በዚህ የማይስማሙ ከሆነም በሐራጅ እንዲሸጥ ተደርጎ የሽያጩን ገንዘብ እኩል እንዲካፈሉ በማድረግ ሊካፈሉት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
5. ከላይ በተራ ቁጥር 4 የተጠቀሰው የክፍፍል ውሳኔ አፈጻጸም ጉዳዩ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል የቤቱን ሕጋዊነት አስመልክቶ ሊያነሳ የሚችለውን ጥያቄ የሚያስቀር አይሆንም በማለት ወስነናል፡፡
6. በተራ ቁጥር 1 ከተጠቀሰው ውሳኔ ውስጥ የቤት ቁሳቁሶችን እና ከቤቱ ኪራይ የተገኘውን ገቢ አስመልክቶ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቷል፡፡
7. ጥያቄው ሲቀርብለት ከላይ በተራ ቁጥር 3፣4 እና 5 በተጠቀሰው ውሳኔ መሰረት እንዲያስፈጽም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
8. ቁጥሩ 58686 የሆነው መዝገብ ተመላሽ ይደረግ፡፡
9. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
10. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡** **ብ/ግ**

የሰ/መ/ቁ. 95680

መስከረም 26 ቀን 2007 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ የሺ ተሾመ

ተጠሪ፡- አቶ መስፍን ኃይሉ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥታል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል የሎሜ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሣሽ ሲሆኑ የአሁን ተጠሪ ተከሣሽ ነበሩ አመልካች ባቀረቡት ክስ፡- ከተጠሪ ጋር የነበረው ጋብቻ የፈረሰ መሆኑን በመግለፅ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ንብረት ያካፍለኝ በማለት በኤጀሬ ከተማ የሚገኝ በ198 ካ.ሜ.ላይ ያረፈ ቤትና ኩሺና፣ ዲናሞ ብቻውንና የወፍጮ ዲናሞ በንግድ ባንክ ያለ ገንዘብ በ369 ካ.ሜ. ላይ 90 ቆርቆሮ የተሠራ ቤት የሞተር ቤት 2 ክፍል በልማት የተከፈለ 80,000 ብር እና የተሸጠ የወፍጮ እና ጀኔሬተር ገንዘብ(13,000) ያካፍለኝ ብላለች በ198 ካ.ሜ.ላይ ያረፈው ቤት በ1982 ከጋብቻ በፊት (በ17/02/82) የገዛሁትን ነው፡፡በ369 ካ.ሜ. ላይ ያለው ቤት 85 ቆርቆሮ እንጂ 90 አይደለም በመንገድ ሥራ የመኖሪያ ቤት ፈርሶ የተከፈለኝ 54,000 ባገኘሁት ካሣ ከአቶ መለሰ ጫካ ከተባለ ሰው ገንዘብ ተበድሬ የሰራሁት የግል ንብረት ነው፡፡ የካሣ ገንዘቡም ብር 80,000 ሣይሆን ብር 54,000 ነው፡፡ በናፍጣ የሚሠራ ሁለት ወፍጮና ጀኔሬተር 13,000 የተገዛ ቢሆንም 11,495.55 ተጨምሮበት በ24,495.85 ወደ ኤሌክትሪክ ተቀይሮ በሥራ ላይ የሚገኝ እንጂ በጥሬ ገንዘብ የለም፡፡ በተጨማሪም የጋራችን የሆነ የላሜራ ሱቅ ሽቀጥ ግምቱ 60,000 በከሣሽ እጅ ይገኛል፡፡ የመብራት ሀይል ዕዳ (የወፍጮ) 21,000 የጋራችን ነው በመጨረሻም በ369 ካ.ሜ. ቦታ ላይ ያለውም ቤት የግሌ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤትም በግራ ቀኙ የተማመኑትን ንብረት በማለፍ አከራካሪ የሆኑትን ፍሬ ነገሮች በመለየት ንብረቶችን አስመልክቶ መስተዳደሩና የአካባቢ ሽማግሌዎች እንዲያጣሩ በማድረግ ተከሣሽ (ተጠሪ) ተበደርኩ የሚለውን 60,000 አመልካች የማታውቀውና ያልተረጋገጠ ነው፡፡ባንክ ቤት አለ የተባለው ገንዘብ በአመልካች በኩል እንዲያረጋግጡ አልተደረገም በማለት ውድቅ ካደረገው በኃላ የተቀሩትን ንብረቶች በቀረበው ማስረጃ በማረጋገጥ እኩል እንዲካፈሉ ሲል በተለይ በ198 ካ.ሜ. ቦታ ላይ ያለው ቤት የተጠሪ በግል ገንዘባቸው ገዝተው በ369 ቦታ ላይ ቤት መስራታቸውን የካሣ ገንዘብ 54,000 ይክፈሉ ሲል በ369 ላይ ያረፈውን ቤት እኩል ይካፈሉ

በማለት ወስኗል፡፡የይግባኙም ፍ/ቤት የግራ ቀኙን በማከራከር አጣርቶ ሲያፀናው በክልሉ ሰበርም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.337 ተሰርዟል፡፡

የአመልካች አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማሳረም ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በሥር ፍ/ቤት ከተጠሪ ጋር እንደባልና ሚስት ለ23 አመት ስንኖር ያፈራነውን ወፍጮ ከነ ቤቱ መኖሪያ ቤት አንድ ኩሽና አንድ ሽንት ቤት በ198 ካ.ሜ. ላይ ሰፍሮ የሚገኝ ጠጅ ቤት ፈርሶ መሬቱም ሲወሰድ የተከፈለውን ካሣ ገንዘብ 54,000 ብር በ369 ካ.ሜ ቦታ ላይ የተሰራውን ቤት አመልካች 54,000 ለተጠሪ ከፍላ ቤቱን በጋራ ትካፈል መባሉ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል ሲሉ አመልካች ጠይቀዋል፡፡

በዚህም መሠረት ይህ ችሎትም አመልካች 54,000 ብር ከፍላ በ369 ካ.ሜ.ቦታ ላይ ያረፈውን ቤት ትካፈል መባሉና በ198 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያለው ቤት በላዩ ላይ የተተከለው ወፍጮ ቤት በግል የተሰራነው?ወይስ በጋብቻ ውስጥ? የሚለው ወደ ድርጅትነት የተለወጠው መቼ ነው?የሚለው እና ለመብራት ሀይል የተከፈለው 24,000 መቼ ነው?የሚሉት ነጥቦች እንዲጣሩ በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኙ በቀረበው አቤቱታ ላይ መልስና የመልስ መልስ በመቀባበል እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡

በመሆኑም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰውን ይመስላል፡፡እኛም እንዳየነው አመልካች ጋብቻ መፍረሱን ጠቅሰው የጋራ ንብረታችን ነውና ልንካፈል ይገባል የሚሉትን የንብረት ዝርዝር በማቅረብ የጠየቁ ሲሆን የሥር ወረዳ ፍ/ቤትም በዝርዝር የቀረበለትንና የዳኝነት ጥያቄ የታመነውንና ተቃውሞ በተጠሪ የቀረበበትን ነጥብ በመለየት በማስረጃ አጣርቶ ውሣኔ አሳርፎበታል፡፡

እኛም በማስረጃ ረገድ ተጣርቶ ውሳኔ ያገኘውን በመቀበል በጭብጥነት በተያዙት ነጥቦችን ስናየው ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ ከአመልካች ጋር በነበረበት ጊዜ የነበረው ወፍጮ አብረው ሲጠቀሙበት የነበረ የመብራት ኃይል የአገልግሎት ዋጋ ብር 24.000.00 መክፈላቸውን አረጋግጠው የጋራ ዕዳቸው መሆኑንና በድርሻቸው አመልካች እንዲከፍሉ ጠይቋል፡፡ የሥር ፍ/ቤትም ግራ ቀኙ በጋብቻ ውስጥ እያሉ የተጠቀሙበት መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ቤት በነበሩበት ወቅት የቆጠረ የመብራት ዋጋ በመሆኑ ዕዳውን ሊከፈሉ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ እንግዲህ አመልካች ከወፍጮ ገቢ ተጠቃሚ አይደለሁም ሲሉ ባልተከራከሩበት የዕዳው ተጋሪ መሆን የለብኝም በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የለውም በመሆኑም ይኸኛውም የውሳኔ ክፍል ባግባቡ ተጣርቶ የተወሰነ በመሆኑ ተቀብለነዋል፡፡

ሁለተኛውን አከራካሪውን በ198 ካ.ሜ ይዞታ  አስመልክቶ ተጠሪ ከጋብቻ በፊት ገዝቼ እያለሁ በመንገድ ምክንያት ፈርሶ ያገኘሁትን ካሳ ገንዘብ 54.000 ብር በመያዝ ከአመልካች ጋር ተጋብተው በ369 ካ.ሜ ቦታ ላይ የሰፈረውን ቦታ ሰራን ፣ ስለዚህ ንብረቶቹ የግል ንብረት ነው በማለት ሲከራከሩ አመልካች በበኩላቸው ይዞታው የተገዛውና የተሰሩት አንድ ክፍል ቤት ብቻ መሆኑንና ይህ ፈርሶ ተስፋፍቶ በ369 ካ.ሜ ቤት ተሰርቶ የጠጅ ቤት ድርጅት ስንጠቀምበት የነበረና የፈረሰ በመሆኑ ከ23 አመት በኃላ ተጠሪ የግሌ ነው ሲል መከራከሪያ ሊያደርጉት አይገባም ይላሉና እኛም ተጠሪ ተቀበልኩ የሚሉትን ገንዘብ ከጋብቻ በፊት ያገኘሁት ነው ቢሉም ከአመልካች ጋር የ369 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ቤት በመስራት አስፋፍቶ ለረዥም ዓመታት መኖራቸው

ያላከራከረ ነው፡፡ እንግዲህ በእነዚህ ባለፉት አመታት በግራ ቀኙ አስተዋጽኦ ቤቱ ከተገነባ በቀጣይነት የሚገኙት ገቢዎች የሉም ማለት አይቻልም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ንብረቶች መቀላቀላቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ ተጠሪ ተጠቃሹ ገንዘብ የግሌ ነው የሚሉበት ምክንያት ከጋብቻ በፊት ያገኘሁትና በዚሁ ገንዘብ በ369 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ቤት ሰርተናል በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የኦሮሚያ የቤተሰብ ህግ ቁ.69/1995 አንቀፅ 74/1/ መሠረት ባልና ሚስቱ በየግል ያገኟቸውን ንብረትም ሆነ ገንዘብ በግል ይዘው መቀጠል እንደሚችሉ ሲደነገግ ይህ የግል የተባለው ንብረት የግል ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው በተጠቃሹ ህግ አንቀፅ 74/2/ ስር የግል ይባልልኝ ተብሎ በፍ/ቤት ሲፀድቅ መሆኑን በግልጽ ደንግጐታል፡፡ ይህ ደግሞ በህጉ እንደዋነኛ መስፈርት የተቀመጠ ጉዳይ ነዉ፡፡ በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ በዚህ መልኩ ተጠቃሹን ንብረት ወይም ገንዘብ አስመዝግቤያለሁ ሲሉ ያቀረቡት ክርክር አልነበረም፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ በስር ፍ/ቤቶች አመልካች 54,000 ብር በመክፈል ቤቱን ይካፈሉ የሚለውን የውሣኔ ክፍል ባለመቀበል፡፡ የተቀሩትን የውሣኔ ክፍሎች ባልነካ መልኩ በ369 ይዞታ ላይ ያረፈውን ቤት 54,000 አመልካች ይክፈሉና ቤቱን ይካፈሉ መባሉና በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች ያለመታረሙ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 34054 በቀን 23/07/05 የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ 33974 በቀን 06/12/2005 እና የክልሉ ሰበር ሰሚ በመ.ቁ 173245 በቀን 28/02/2006 የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሎ ፀንቷል፡፡

2. አመልካች አከራካሪውን ብር 54,000.00 ለተጠሪ ሣይከፍሉ የጋራ ነው የተባለውን ቤት ሊካፈሉ ይገባል ብለናል፡፡

3. የወጪ ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ውሣኔ በማግኘቱ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::**

**እ/ኢ**

የሰ/መ/ቁ.88275

ጥር 19 ቀን 2007.ዓ.ም

**ዳኞች**፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች**፡- አቶ ኃይለሚካኤል ልኬ ሎሶ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ** ፡- 1. አቶ መኮነን በለጠ - ጠበቃ መለሰ ጦና ቀረቡ

2. ወ/ሮ አምሳለች ዘበን - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የቅድሚያ ግዥ መብት ጥያቄ የሚስተናገድበትን የሕግ አግባብ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በሐዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአፈፃጸም ከሳሽ የሆኑት የአሁኗ 2ኛ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በዋናው ፍርድ መሰረት እንዲፈፅምላቸው ባቀረቡት የአፈጻም ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ ባልና ሚስት የነበሩ ሲሆን ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ ፈርሶ የጋብቻ ውጤት ከሆኑት ንብረቶች መካከል ለአሁኑ ክርክር መነሻ የሆነውን መኖሪያ ቤት በክልሉ የቤተሰብ ሕግ መሰረት የተቀመጡት የክፍፍል ስርዓቶችን መሰረት በማድረግ ቤቱ በግልጽ ጨረታ መሸጥ እንደአለበት ፍርድ ቤቱ ውሳኔ አሳርፎ የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶ የአሁኑ 1ኛ ተጠሪተወዳድረው የጨረታ አሸናፊ በመሆን የቤቱ ገዥነታቸው ከታወቀ በኂላ የአሁኑ አመልካች ቤቱን የመልሶ መግዛት መብት እንደአላቸው ጠቅሰው ቤቱን እንዲያስቀሩ እንዲወሰንላቸው ለፍርድ ቤቱ አመልክተው የአሁኑ ተጠሪዎች ይህንኑ የአመልካችን ጥያቄ ተቃውመው የመልሶ መግዛት መብት ለአመልካች ሊሰጣቸው አይገባም የሚለውን መከራከሪያ ሁለቱም ተጠሪዎች ከማቅረባቸውም በተጨማሪ የአሁኗ 2ኛ ተጠሪ አመልካች አዲስ አበባ ውስጥ መንግስት በሰጣቸው ደረጃውን በጠበቀ ቤት እንደሚኖሩና ራሳቸው ግን ሁለት ልጆችን ይዘው ቤት የሌላቸው መሆኑን ጠቅሰው የመልሶ መግዛት መብት ለራሳቸው እንዲጠበቅላቸው ጭምር ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የሀዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአመልካች ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ውደቅ አድርጎ የጨረታውን ውጤት እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡በዚህ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ ጉዳዩ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ የሚገዛ ቢሆንም የክልሉ የቤተሰብ ሕግ ስለመልሶ የመግዛት መብት የሚደነግገው ጉዳይ ያለመኖሩንና በዚህ ሁኔታ ደግሞ በፍትሐ ብሔር ሕጉ የጋራ ንብረትን መልሶ ስለመግዛት የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ተፈፃሚ ማድረግ በሕግ አተረጓጎም መርህ ተገቢ መሆኑን ጭምር ዘርዝሮ የአመልካች ቤቱን መልሶ የመግዛት መብታቸው ሊጠበቅ ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ትዕዛዝ ሽሮታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት

አቅርበው ተቀባይነት ያጡ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸውን በተናጠል ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ መዝገቦችን አጣምሮ በመመርመር የአሁኑ አመልካች የመልሶ መግዛት መብት አላቸው ተብሎ የተሰጠውን የከተማውን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ ያጸናውን የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ ሽሮ የከተማው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- የጋብቻ ውጤት የሆነውን ቤት መልሶ ለመግዛት በፍትሃ ብሔር ሕጉ በአንቀጽ 1261፣ከአንቀፅ 1386- 1409 ስር የተጠቀሱት ድንጋጌዎች መብት የሚሰጣቸው ሁኖ እያለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ መሰረት የሚዳኝ እንጂ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች የሚዳኝ አይደለም በማለት የሰጠው ውሳኔ ተገቢውን የሕግ አተረጓጎምና አተገባበር ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ በዚህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 37297 የተሠጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የሰበር አቤቱታቸው ተመርምሮም ከተጠቃሽ ድንጋጌዎችና ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንጻር የአመልካች ጥያቄ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የአሁኑ አመልካች የጋራ ንብረት ነው የሚለውን ቤት ከ1ኛ ተጠሪ መልሶ የመግዛት መብት ያለው መሆኑ አለመሆኑን፣ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1394፣ ከቁጥር 1405-1408 ከተመለከቱት ድንጋጌዎች እና የፍትሐብሔር ሕጉ ስለ ጋራ ባለሃብትነት በቁጥር 1257 እና የሚቀጥሉት አንቀጾች የደነገገውን ከክልሉ የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 103(2) እና 102 ድንጋጌዎች አኳያ ለመመርመር ተብሎ በመሆኑ ከዚሁ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለው ተመልክተናል፡፡

በክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ እኩል መብት ያላቸው መሆኑን፣የቤቱ የክፍፍል ስርዓት እንዲፈጸም የተደረገውም የክልሉን የቤተሰብ ሕግ መሰረት በማድረግ መሆኑን፣አመልካች አሁን አጥብቀው የሚከራከሩት የክልሉ የቤተሰብ ሕግ ስለመልሶ መግዛት የሚያስቀምጠው መፍትሄ ስለሌለ በፍትሐ ብሔር ሕጉ ያሉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ሊኖራቸው ይገባል በማለት መሆኑን፣2ኛ አመልካችም ቤቱን መልሶ የመግዛት መብት ሊጠበቅልኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት ጥያቄ እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ ተቀባይነት ያጣ መሆኑን የሰ/መ/ቁጥር 90586 የሚያሳይ መሆኑን፣1ኛ አመልካች አከራካሪውን ቤት የገዙት በግልጽ በተደረገው ጨረታ ተወዳድረው ጨረታው ሕጋዊነቱ ተረጋግጦ መሆኑን ከመሆኑም በላይ በዚህ የጨረታ ሂደት አመልካችም ሆነ የአሁኗ 2ኛ ተጠሪ እንዲሳተፉ ጨረታው እንዲከናወን ያዘዘው የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ያልሰጠበት ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ስርዓት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስትም ሆነ በክልል ሕግጋት መንግስታት የተረጋገጠውን የእኩልነት መብት መሰረት አድርጎ መከናወን ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ስርዓት የሚከናወንበትን መንገድ የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 በቅደም ተከተል ያስመቀጣቸው መንገዶች ከአንቀፅ 90 እስከ 93 ድረስ ባሉት የሰፈሩ ሲሆን ስራ ላይ ያሉት የክልል የቤተሰብ ሕግጋትም አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎችን ይዘው እናገኛለን፡፡ ለተያዘው ጉዳይ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለው የክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 75/1996 ሲታይም የባልና ሚስት ንብረት የሚከፋፈልበትን ሥርዓት ከአንቀፅ 101

እስከ 105 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች አካቶ ይዟል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለውም የጋብቻ ውጤት የሆነው የጋራ ንብረት ክፍፍል ሊከናወን የሚገባው የእኩልነት መርህን መሰረት አድርጎና የተጋቢዎችን ፈቃድ በመመርኮዝ መሆኑን ነው፡፡የተጋቢዎች ስምምነት ከሌለ ደግሞ ክፍፍሉ መፈፀም ያለበት በሕጉ የተመለከተውን ቅደም ተከተል መሰረት አድርጎ ሊሆን እንደሚገባ ሕጉ ያስገነዝባል፡፡በመሆኑም የጋብቻ ውጤት የሆነውን ንብረት ለማከፋፈል የበላይነት ያለው የቤተሰብ ህጉ ነው፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሕጉ አንቀጽ 1386 እና ተከታዩቹ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረው የጋራ ባለሐብቶች ለሆኑ ወገኖች እንዲሁም የጋራ ባለሐብት የሆኑ ወራሾች መካከል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕግ ድንጋጌ ቁጥር 1388 እና 1392 ይዘት ያመለክታል፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ የመግዛት መብት በሕግ ጥበቃ የተደረገለት መብት ሲሆን ሕጉ ሊያሳካ ያሰበው አላማም ከዘር የወረደ ንብረትን በተመለከተ ዘመዳሞች የሚኖራቸውን ስሜት ለመጠበቅና ከቤተሰቡ እጅ ወጥቶ ወደ ሌላ ወገን እንዳይተላለፍ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡በዘመዳሞች መካከል ይህ መርህ ተፈጻሚ የሚሆነው በውርስ ሀብት ላይ ሲሆን መብቱን ተግባራዊ የሚያደርጉትም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1391 ስር እንደተመለከተው በወራሽነት ቅደምተከተላቸው መሰረት ነው፡፡ ለቅድሚያ ግዥ መብት የሚወዳደሩት በእኩል የዝምድና ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች የሆኑ እንደሆነ በመሬቱ ላይ የሚኖረውና የሚጠቀምበት ሰው ቅድሚያ የሚሰጠው መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1392 ስር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህ ካልተቻለ ደግሞ መሬቱን በአንድነት እንደሚሰሩበት እኩል በሆነ ድርሻ የጋራ ባለሃብቶች እንደሚሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1393(1) ድንጋጌ ያሳያል፡፡በሌላ በኩል ሕጉ በባለጥቅሞቹ ላይ ያስቀመጠው ገደብም ያለ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1397 ድንጋጌ ያሳያል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት ባለጥቅሞቹ በቀዳሚነት የመግዛት መብትን ለሌላ ሰው ሊያስተላልፉ እንደማይችሉና እንዲሁም በእዳ ሊያዝ እንደማይችል አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ተቀምጧል፡፡ሌላው ስለቅድሚያ የመግዛት መብት በሕጉ የተቀመጠው ጉዳይ የመብቱ የተፈፃሚነት ጊዜ ነው፡፡በዚህም መሰረት በቅድሚያ የመግዛት መብት ተፈጻሚ የሚሆነው ባለሃብቱ ሀብቱን ወይም የሀብቱን አላባ በዋጋ በሚሸጥበት ጊዜ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1398 ድንጋጌ የሚያመላክት ሲሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1407(1) ድንጋጌም ንብረቱ የተላለፈው ያለ ዋጋም ቢሆንም ግምቱን በመክፈል ይገባኛል ባዩ ሊገለገልበት እንደሚችል ያስረዳል፡፡እንዲሁም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1400 ድንጋጌ ማንም ሰው በቀዳሚነት ይገባኛል በማለት መብት ሊገለገልበት የፈለገ እንደሆነ ንብረቱ በሀብትነት ወይም በአላባነት ለገዥ ወይም በሐራጅ ለሚገዛው ሰው የተላለፈ መሆኑ ለይገባኛል ባዩ ከተነገረበት ቀን አንስቶ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በመብቱ ሊገለገልበት የፈለገ መሆኑ ካስታወቀ መብቱ እንደሚቀርበት አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1401 ደግሞ በቀዳሚነት ይገባኛል በማለት መብት እንዲገለገልበት ለመጠየቅ የማስተላለፍያ ማስታወቂያ ሳይነገር የቀረ እንደሆነ የጋራ ባለሃብቶቹ በማያጠራጥር አኳኋን ንብረቱ ለሌላ ሰው የተላለፈ መሆኑን ካወቁበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በቀዳሚነት ይገባኛል በማለት በመብታቸው ሊገለገሉበት የፈለጉ መሆናቸውን ማስታወቅ እንደአለባቸውና የስጋ ዘመዳሞች ከሆኑ ደግሞ አዲሱ ባለሃብት ወይም የአላባ ጥቅም ተቀባዩ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት እጅ ካደረገበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር በስድስት ወር ጊዜ ውሰጥ በቀዳሚነት ይገባናል በማለት መብታቸውን ሊገለገሉበት የፈለጉ መሆናቸውን ማስታወቅ እንደአለባቸው እንደቅደምተከተሉ በተጠቃሹ ቁጥር ንዑስ አንቀጽ አንድ እና ንዑስ አንቀጽ ሁለት ድንጋጌዎች ስር በሕጉ የተመለከተውን ጊዜ ያለማስታወቅ እና ውጤቱን በተመለከተ ደንግገው እናገኛለን፡፡

እንግዲህ በቀዳሚነት የመግዛት መብትን አድማስ በተመለከተ በሕጉ የተቀመጡ ሁኔታዎች ከላይ የተቀመጡ ከሆኑ አሁን የተያዘው ጉዳይም እልባት ማግኘት ያለበት ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መሰረታዊ አላማ እንዲሁም ጉዳዩን በተለይ ለመግዛት የወጣው ህግ ድንጋጌዎች አንፃር ነው፡፡ከዚህ አኳያ ጉዳዩን ስንመለከተው አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በንብረቱ ላይ እኩል መብት ያላቸው ቢሆንም አንዱ ከሌላው በቅድሚያ ቤቱን መልሶ የመግዛት መብት የሚያገኝበት አግባብ የለም፡፡ የክልሉ የቤተሰብ ሕጉ በአንቀጽ 102 ስር ክፍፍሉ መሰረት ከሚያደርግባቸው ሁኔታዎች አንዱ ንብረቱ የተለየ ጥቅም የሚሰጠውን ተጋቢ መለየት እንደሆነ በተመለከተው አግባብም ለአመልካች ቤቱ እንዲሰጥ የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት መኖሩ አልተረጋገጠም፡፡ጉዳዩን የሚገዛው ልዩ ሕግ ስለ አንድ ክርክር መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችል ድንጋጌ ባልያዘበት ሁኔታ አግባብነት ያላቸው ሌሎች ሕጎች ስር ያሉትን ድንጋጌዎችን መሰረት አድርጎ ለአንድ የክርክር ጭብጥ መፍትሔ መስጠት ተገቢ መሆኑን ተቀባይነት ያላቸው የህግ አተረጓጎም ደንቦች የሚያስገነዝቡን ጉዳይ ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ግን በክልል የቤተሰብ ሕግ የጋብቻ ውጤት የሆነው ንብረት ክፍፍል የሚፈፀምበትን አግባብ በግልጽ የተቀመጠ በመሆኑና ተጋቢዎች ግራ ቀኙ በሚያደርጉት ስምምነት መሰረት ክፍፍሉ ሊፈጸም ያልቻለ ከመሆኑም በላይ 2ኛ ተጠሪም የመልሶ መግዛት ጥያቄ ያቀረቡ በመሆኑ የአሁኑ አመልካች ንብረቱን መልሰው የመግዛት መብት የሚያገኙበት አግባብ ከፍትሃ ብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች አንፃር የሚታይበት አግባብ የለም፡፡ጨረታው እንዲከናወን ያደረገው የሥር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ተጋቢዎች መብት አነጻጽሮ በጨረታው ላይ እንዲሳተፉና መልሶ የመግዛት መብት እንደሚኖራቸው ከመነሻውም ግልጽ ትዕዛዝ ያልሰጠበት መሆኑን ክርክሩ ያሳያል፡፡ በዚህ አግባብ በጨረታው ላይ ተወዳድሮ የጋብቻ ውጤት የሆነውን ንብረት የገዛ ተጫራች የጨረታው ውጤት ከታወቀ በኋላ ንብረቱን ለጋራ ባለሃብት መልሶ እንዲሸጥ ማድረግ የባልና ሚስት ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ በሚደረግበት ጊዜ ተወዳዳሪ እንዲቀርብ ያለማድረግ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑ ተቀባይነት አግኝቶ ሊተገበር የሚገባው አይደለም፡፡ስለሆነም ጉዳዩ ልዩ ሕግ በሆነው የክልሉ የቤተሰብ ሕግ የሚዳኝ እና በዚህ ሕግ የተቀመጡ የክፍፍል ስርዓቶች ደግሞ የጋራ ባለሃብት መብቱን እንዲጠቀም የሚያስችሉ ቅደም ተከተል ያላቸው በመሆኑ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በዚህ በህጉ በተቀመጡ ቅደም ተከተሎች መጠቀም ሳይችሉ ከቀሩ በኋላ በጨረታው ላይ የመልሶ መግዛት መብት እንዳላቸው ባልተቀመጠበትሁኔታ ሶስተኛ ወገኖች ተወዳድረው አሸናፊው ከተለየ በኋላ ንብረቱን መልሰን እንግዛ ሲሉ ጥያቄው በዚህ ረገድ በተደነገጉት የፍትሐ ብሔር ድንጋጌዎች የሚታይበት አግባብ የሌለ ሁኖ አግኝተናል፡፡ሲጠቃለለም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ እንጂ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 58418 መጋቢት 06 ቀን 2005 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች አከራካሪውን ቤት የመልሶ መግዛት መብት የላቸውም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

***<u>ትዕዛዝ</u>***

ነሐሴ 07 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይጻፍ፡፡

***መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡***

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ::**

***መ/ተ***

የሰ/መ/ቁ.90121

ቀን 28/01/2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

መኮንን ገ/ህይወት

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስስ

አመልካች፡- አቶ .........ጠበቃ ሀይልዬ ሰህለ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ............- ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል**

**ፍ ር ድ**

በዚህ በመዝገብ የቀረበው ክርክር የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ በመሆን በአመልካች ላይ ያቀረቡትን ክስ እናታቸው ወ/ሮ ..... ከአመልካች ጋር ከጥር ወር 1973 ዓ/ም እስከ ህዳር ወር 1974 ዓ/ም ድረስ ጋብቻ ሳይኖር እንደባልና ሚስት አብሮው በመቂ ከተማ ድግዳቦራ ወረዳ ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 190 ወስጥ ሲኖሩ መቆያታቸውን ገልጸው በዚህ ግንኙነታቸው መሰረት ተጠሪ በጋንዲ ሆስፒታል ሚያዝያ 02 ቀን 1974 ዓ/ም የተወለዱ መሆናቸውን በመግለጽ አመልካች የተጠሪ አባት ነው ተብሎ እንዲወሰን የሚጠይቅ ነው የአሁን አመልካች በስር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ ልጅነት የሚረጋገጠው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀፅ 154 እና 155 ላይ እንደተመለከተው የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ መሆኑን፣ተጠሪ ያቀረቡትማስረጃ አለመኖሩ አመልካች መቂ ከተማ ኑረው እንደማያወቁ ተጠሪም አንድም ቀን እራሳቸውም ሆነ በሰው የአመልካች ልጅ መሆናቸው ጠይቀው እንደማያውቁ በመጥቀስ ክሱ ውድቅ ተደርጐ እንዲሰናበቱ አመልክተዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት የተጠሪ ሁለት ምስክሮች በማዳመጥ በሰጠው ውሳኔ በአሁን አመልካች እና የተጠሪ እናት እንደ ባልና ሚስት አብረው ይኖሩ ነበር በሚል ስላልተረጋገጠ የአመልካች ምስክር መስማት አያስፈልግም፡፡ የአመልካች እና የተጠሪ እናት ግንኙነት በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 143 በሚያዘው አግባብ ሳይረጋገጥ የደም ምርመራ (የDNA ምርመራ) ማድረግ ተገቢ ስላልሆነ ፍ/ቤቱ የተጠሪ ጥያቄ ውድቅ ማድረጉን በመግልጽ አመልካች በነጻ ይሰናበቱ በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታውን ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ በማከራከር በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ በቃል ክርክር የድኤንኤ ምርመራ እንዲደረግለት ጠይቋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ምርመራውን ለማዘዝ የልጅ አባት ነው የሚያሰብል ግምት መያዝ አለበት በማለት መደምደሙ ከሰ/መ/ቁ.63195 አኳያ ተገቢነት የለውም፡፡ የአሁን ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በማስረጃነት

የጠቀሰውን የዲ.ኤን.ኤ ምርምራ ጥያቄ ሳይቀበለው አልፎ የሰጠው ውሳኔ የህግ አግባብ ባለመሆኑ ምርመራ ተደርጎ በምርምራው ውጤት የመስለውን እንዲወሰን ውሳኔውን በማሻር በነጥብ መልሶታል፡፡

የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሳኔ በመቃወም አመልካች ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ይግባኝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.337 መሰረት ተሰርዟል፡፡ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽሟል ያሉትን የህግ ስህተት እንዲታረም ግንቦት 13 ቀን 2005 ዓ/ም የተጻፈ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታ ዋና ፍሬ ነገሩ፡- የሰበር ውሳኔው ለዚህ ጉዳይ አግባብነት የለውም ፤ የስር ፍርድ ቤት የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ጥያቄ የተቀበለው ስርዓቱን ጠብቆ አይደለም ፤ ከአመልካች ስለመወለዱ አልተረጋገጠም በማለት ስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲሻር አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስ በአመልካች እና የተጠሪ እናት ግንኙነት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ የዲኤንኤ ምርመራ በመጀመሪያ ቀጠሮ መጠየቃቸው፤ ምርመራውም ጉዳዩን ግልጽ የሚያደረግ መሆኑ በመጥቀስ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና ጠይቋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ያቀረቡ ሲሆን አቤቱታቸውን የሚያጠናክር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ሰበር ሰሚ ችሎቱ ህዳር 05 ቀን 2006 ዓ/ም ግራ ቀኙ በችሎት በቃል አከራክሮ ውጤቱን መዝግበዋል፡፡

የክርክሩ አጭር ይዘትና  አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ነው፡፡ እኛም መዝገቡን በአጣሪ ችሎቱ ያስቀርባል ከተባለው ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አኳያ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን ተጠሪ በአመልካች እና እናቱ መካከል የነበረው ግንኙነት ለማስረዳት ምስክሮች በማቅረብ ያስማ መሆኑ ከመዝገቡ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የስር ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዲኤንኤ ምርምራ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በአመልካች እና የተጠሪ እናት ነበረ የተባለው ግንኙነት በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 143 መሰረት ከተመለከቱት ግምት የሚያሰጡ ምልክት ሰጪ ነገሮች በአንዱ አልተረጋገጠም የሚል ነው፡፡ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዲኤንኤ ምርምራ በተጠሪ በቃል ክርክር ወቅት የተጠየቀ በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.259(1) መሰረት እንዲሁም ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ. 63195 ከሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ አኳያ ዲኤንኤ ምርመራ ይደረግ ጥያቄ ተቀብሎታል፡፡ የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ በአንዱ በኩል አባት የማግኘት መብት ሲያረጋግጥ በሌላ በኩል ደግሞ አባት ያልሆኑ ግለሰቦች አባት ነህ ተብሎ እንዳይወሰን ለመከላከል የተበጀ ህጋዊ ስርዓት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ የዲኤንኤ ምርመራ ይደረግልኝ ጥያቄ በስር ፍርድ ቤት ማቅረቡ አልተካደም፡፡ የዲኤንኤ ምርመራ እንደ አንድ የማስረጃ ይዘት እንዲታይለት መጠየቁ እና ይህንን ጥያቄም ስርዓቱን ጠብቆ ማቅረቡ በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ጥያቄውን ውድቅ ለማድረግ መነሻ ያደረገው የደም ምርመራ ለማድረግ አመልካች የዲኤንኤ ምርምራ እንዲያደርጉ ለማስገደድ ተጠሪ እናትና አመልካች በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 143 መሰረት ግንኙነት የነበራቸው መሆኑ እና ተጠሪም በዚህ ግንኙነት የተወለደ መሆኑ በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት በሚል ምክንያት ነው፡፡ ይሁንና ይህ የስር ፍርድ ቤት ድምዳሜ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍሬ ነገር ማጣራትና ማስረጃ ምዘና ስርዓት ተገቢ አይደለም ተብሎ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቱ ከተሻረ በሰበር ችሎቱ የማስረጃ ምዘና ሂደቱ የሚታይበት ስርዓት አይኖርም፡፡

በአመልካች እና ተጠሪ እናት መካከል ግንኙነት ነበረ ወይስ አልነበረም የሚለው የፍሬ ነገር ክርክር የስር ፍርድ ቤቶች የየራሳቸው አቋም የወሰዱበት መሆኑ ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምሮ

ውሳኔ ከመስጠት ውጪ ፍሬ ነገርን በማጣራትና ማስረጃ ምዘና ረገድ የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ተገቢ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር የሚያስችል ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ ከኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ የቤተሰብ ህጉ የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ የሚቀርብበት የጊዜ ገደብ በግልጽ አልተገደበም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ከ30 ዓመት በኃላ የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ ማቅረቡ የጥያቄውን ህጋዊነት ከወዲሁ ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ሆኖ አልተገኘም፡፡ የሰበር ችሎቱ በመ/ቁ. 63195 የዲኤንኤ ምርመራ ወጪ ከመሸፈን ጋር በተያያዘ የሰጠው ትርጉም በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደ አስገዳጅ ውሳኔ መጠቀሱ የክርክር ምክንያት ቢሆኑም በዚህ ጉዳይ በዋናነት መታየት ያለበት ይህ ሰበር ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ የዲኤንኤ ምርመራ እንዳይደረግ የክልከላ ውጤት ያለው ውሳኔ ከመስጠቱ አንፃር ብቻ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሰበር ችሎቱ ከኤክሰፐርት ምርመራ ውጤትና የማሳረዳት ብቃቱ በተያያዘ የተሰጠ ትርጉም መኖሩ ግልጽ ቢሆንም በእጃችን ከተያዘው ጉዳይ ጋር በፍሬ ነገርና በጭብጥ ረገድ አንድና ተመሳሳይ የሆነ ምርምራ የሚከለክል ውሳኔ ያልተሰጠ ከመሆኑ አንፃር የስር ፍርድ ቤት ከላይ የተጠቀሰው መዝገብ በአስገዳጅ ውሳኔ መመዝቡ የውሳኔውን ህጋዊነት ጥያቄ ውስጥ የሚከተው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አባትነት የሚረጋገጥባቸውን መንገዶች አስቀምጧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የሚጠቀሱት አባትነት በህግ ግምት የሚወሰድባቸው ሲሆኑ በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ ልጆች እንዲሁም እንደባልና ሚስት ሆነው ከኖሩ ግለሰቦች የተወለደው ህፃን የሚመለከት መሆኑ ከቤተሰብ ህግ አንቀጽ 126 እና 130 ድንጋጌዎች መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ወጪ አባትነት እውቅና በመስጠት ሊረጋገጥ ይችላል፡፡ የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ ከላይ በተጠቀሱ ምክንያቶች ማረጋገጥ በማይቻልበት ሁኔታ በፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ እንደሚታይ ነው፡፡ በፍርድ ቤት አባትነት ለማረጋገጥ መነሻ ነጥቦች በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 143 የተዘረዘሩት ሲሆኑ በዚህ ረገድ የሚነሳው ክርክር ወይም ግምትና ምልክት ሰጪ ግምቶች ለማስተባበል የሚያስችሉ ምክንያቶች በዚህ ህግ አንቀጽ 144 በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረበው የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ በአመልካች ተክዷል፡፡ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት የዲኤንኤ ምርመራ እንዲታዘዝለት ጠይቋል፡፡ የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጥያቄውን ውድቅ ቢያደረገውም ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የጥያቄው ተገቢነት በመቀበል ምርመራው እንዲደረግ አዟል፡፡ የስር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተጠሪ የዲኤንኤ ምርመራ ይታዘዝልኝ ጥያቄ በወቅቱ የቀረበ መሆኑ በማረጋገጥ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንዲመለከተው መልሶ መላኩ በህግ አተረጓጎም ረገድ የፈጸመው ስህተት አለ ማለት አልተቻለም፡፡ የዲኤንኤ ምርመራ ውጤት በማንኛውም ሁኔታ እንዲደረግ የሚጠይቅ አለመሆኑ ችሎቱ የሚገነዘብ ቢሆንም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር የመጀመሪያ ደረጃ የፍሬ ነገር ድምዳሜና የማስረጃ ምዘና ባለመቀበል ምርምራ እንዲደረግ ማዘዙ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህግ የተደነገጉት የክርክር አመራር መሰረታዊ የስነ ስርዓት ድንጋጌዎች በአግባቡ አልተተረጎሙም ለማለት የሚያስችል ነገር አልቀረበም፡፡ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ያለው የአባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ የዲኤንኤ ምርመራ ተደረጎ የስር ፍርድ ቤት የመሰለውን እንዲወሰን መታዘዙ ፤ የምርመራ ወጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ከወዲሁ መተንበይ በማይቻልበት ሁኔታ አመልካች ለመጉዳት ታስቦ የተደረገ ነው የሚያስብል የህግ ምክንያት የለውም፡፡ በመሆኑም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ያለው አባትነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ ለመወሰን የዲኤንኤ ምርምራ አስፈላጊ መሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከታመነበት የፍ/ቤቱ ትእዛዝ

ተፈጻሚ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አንጻር የስር ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የዲኤንኤ ምርመራ እንዲደረግ ማዘዛቸው በአግባቡ ነው፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በስር ፍርድ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ እንደሚችሉ ግልጸዋል፡፡ የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክሱን ውድቅ በማድረግ የመከላከያ ማስረጃ አለማዳመጡን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም አመልካች የዲኤንኤ /DNA/ ምርምራ ቢደረግም አለኝ የሚሉትን የመከላከያ ማስረጃ የማስማት መብታቸው የሚከለክል አይሆንም፡፡

በማጠቃለል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር የዲኤንኤ ምርመራ እንዲደረግ ማዘዙ እና ውሳኔው በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህ መሰረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 57163 በ1/09/2004 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 126002 ጥር 30 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ.87769 የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. የስር ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የዲኤንኤ ምርመራ እንዲደረግ ማዘዙ በአግባብ ነው ብለናል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም በትእዛዙ መሰረት ይፈጸም ብለናል፡፡ አመልካችም አለኝ የሚሉትን መከለከያ ማስረጃ የማሰማት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡
4. በዚህ ጉዳይ ክርክሩ ለጊዜው እንዲቆም ግንቦት 28 ቀን 2006 ዓ/ም የተሰጠው ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
5. በዚህ የሰበር ጉዳይ ክርክር የተነሳ የግራ ቀኙ ላወጡት ወጪና ኪሳራ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::**

**ሃ/ወ**

የሰ/መ/ቁ. 96628

ህዳር 8 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- 1. አሳመነው ከበደ

2. ወ/ሮ ፍቅርተ ከበደ

3. አቶ ምንተስኖት ከበደ - ቀረቡ

4. ተማሪ ቀንአየሁ ከበደ

5. ተማሪ ብሩክ ከበደ

ጠበቃ አቶ ፍሰሀ አለማየሁ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ዳንኤል ከበደ- ጠበቃ አቶ በየነ ታደሰ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 38926 ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 137992 ጥር 14 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የውርስ ንብረት ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች አመልካችዎች ተጠሪ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ማመልከቻ ነው፡፡ ተጠሪ ወላጅ አባቴ አቶ ከበደ ሰለሞን ጥቅምት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በሞት ተለይቶ ወራሽነታችንን አረጋግጠናል፡፡ ስለዚህ ውርስ አጣሪ ተመድቦ ውርሱ እንዲጣራ ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ አመልካቾች ውርስ አጣሪ ቢመደብና የውርሱ ንብረት ተጣርቶ ቢቀርብ አንቃወምም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ውርስ አጣሪ ከመደበ በኋላ ውርሱ ሲጣራ ተጠሪ ሟች በ 24/11/1980 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል በ210 ካሬ ሜትር ላይ ያረፋ አንድ ክፍል ቆርቆሮ በቆርቆሮ ቤት ሰጥቶኝ አባታችን በህይወት እያለ ቆርቆሮ ቤቱን በማፍረስ ሁለት ክፍል የጭቃ ቤት ሠርቼ እየኖርኩበት እገኛለሁ፡፡ ቤቱ ዋናውን 568

ካሬ ሜትር ግቢው ውስጥ የሚገኝና ቦታውም ራሱን የቻለ ካርታ የሌለው በመሆኑ ሁለት ክፍል የጭቃ ቤት 210 ካሬ ሜትርይዞታ ከውርስ ንብረቱ ተለይቶ እንድያዝልኝ በማለት ለውርስ አጣሪው ጥያቄ አቅርቧል፡፡አመልካቾች የይርጋ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ስጦታው በፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 2443 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 መስፈርቶች የማያሟላ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ስጦታው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተደነገገውን መስፈረት ስለማያሟላ፣ ስጦታው ፈራሽ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ሆኖም ሁለት ክፍል ጭቃ ቤት የሥር አመልካቹ የአሁን ተጠሪ ያሰራው መሆኑን በሰውና በፅሑፍ ማሥረጃ የተረጋገጠ በመሆኑ በ201 ካሬ ሜትር ይዞታ ላይ የተሠራው ሁለት ክፍል ቤት የውርስ ንብረት ሣይሆን የአመልካች /የተጠሪ/ የግል ንብረት ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

2. አመልካቾች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡ አመልካቾች ጥር 8 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ በ210 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ አንድ ክፍል ቤት እንድሰራ በሰጦታ ተሰጥቶኝ ቤቱን አፍርሼ ሁለት ክፍል ቤት ሠርቻለሁ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ የስጦታ ውሉ የሕጉን ፎርም አያሟላም ተብሎ ውድቅ ተደርጓል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠሪ አማራጭ የዳኝነት ጥያቄ ያላቀረበበትን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179 ጠቅሶ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ ቤቱን መሥራቱን አመልካቾች አላመኑም፡፡ ቤቱን መስራቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ስለዚህ ቤቱን ያሠራው ተጠሪ ነው መባሉ ስህተት ነው፡፡ ተጠሪ ሠራሁ የሚለውን ቤት ከ30 ካሬ ሜትር በማይበልጥ ቦታ ላይ ያረፈ ሆኖ እያለ 210 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ የውርስ ንብረት ክፍል እንዳልሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

3. ተጠሪ የካቲት 21 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ አመልካቾች ቤቱንና ሽንት ቤቱን በግል የሠራሁት መሆኔን ገልጬ ያቀረብኩትን ክስ በግልፅ ክደው ክርክር አላቀረቡም፡፡ ተጠሪ 1179 ድንጋጌን በመጥቀስ በቃል ክርክርና በፅሑፍ ለሥር ፍርድ ቤት አማራጭ ክርክር አቅርቤያለሁ፡፡ አመልካቾች ቤት ያረፈበት በ30 ካሬ ሜትር የሚሆነው ይዞታ እንጅ 210 ካሬ ሜትር አይደለም በማለት ያቀረቡት ክርክር በሥር ፍርድ ቤት ያልቀረበ አዲስ የፍሬ ነገር ክርክር ነው፡፡ ስለዚህ የበታች ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ እንዲፀናልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 429 ግቢና ስፋቱ 568 ካሬ ሜትር ቦታ ውስጥ የሚገኘው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል ሽንት ቤትና ቤቶቹ የተሰሩት 210 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ የውርስ ንብረት ሣይሆን የተጠሪ የግል ቤትና ይዞታ ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሠረት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ መሠረታዊ ይዞታና በተጠሪና በአመልካቾች ክርክር ማስረጃ

የተረጋገጡትን መሠረታዊ ፍሬ ጉዳዩች መመርመር ያስፈልጋል፡፡ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤትና ለውርስ አጣሪው ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ሁለት መሠረታዊ መብቶች ተረጋግጠው በፍርድ እንዲወሰንለት የሚጠይቅ ነው፡፡ የመጀመሪያው ሟች ወላጅ አባቴ በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 429 ግቢ ውስጥ ሰርቶት የነበረውን አንድ ክፍል ቆርቆሮ በቆርቆሮ ቤት ሐምሌ 24 ቀን 1980 ዓ.ም ባደረገው የስጦታ ውል ሰጥቶኛል፡፡ ከዚህ በኂላ ሰጭው ወላጅ አባቴ በህይወት እያለ የሰጠኝን አንድ ክፍል ቆርቆሮ በቆርቆሮ ቤት በማፍረስ ፣ በራሴ ወጪ ሁለት ክፍል ሰርቪስ የጭቃ ቤትና አንድ ክፍል ሽንት ቤት ገንብቼ የኖርኩበት ስለሆነ ሁለቱ ክፍል ሰርቪስ ቤቶችና አንድ ክፍል ሽንት ቤት የሟች የውርስ ንብረት ክፍል አለመሆኑ ተረጋግጦ ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ ሁለተኛ የዳኝነት ጥያቄ ወላጅ አባቴ ሐምሌ 24 ቀን 1980 ዓ.ም ባደረገው የስጦታ ውል አንድ ክፍል ቆርቆር በቆርቆሮ የተሰራ ቤት ሣይሆን ሟች ከነበረው 568 ካሬ ሜትር የይዞታ መሬት210 ካሬ ሜትር ይዞታ በስጦታ ያስተላለፈልኝና ይህ የይዞታ መሬት ከጠቅላላው 568 ካሬሜትር ይዞታ ያልተለየ በመሆኑ ተለይቶና ተከልሎ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

6. ተጠሪ መብት አግኝበታለሁ የሚሉት የስጦታ ውል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተደነገጉትን መስፈርቶች የማያሟላ መሆኑ ፍሬ ነገር የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ በዚህ ምክንያት ተጠሪ የግል ንብረቴ ናቸው የሚላቸውን ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤቶችና አንድ ክፍል ሽንት ቤት ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የሥጦታ ውሉ መሠረት እንደማይሆንና የሥጦታ ውሉ ህጋዊ መብት እንደሌለው የበታች ፍርድ ቤቶች ወስነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የውርስ ንብረት ከሆነው የቤት ቁጥር 429 አጠቃላይ 568 ካሬ ሜትር ስኩየር የይዞታ ቦታ 210 ካሬ ሜትር ስኩዌር በስጦታ ይተላለፍልኝ የግል ይዞታዬ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የስጦታ ውሉ ፈራሽ ነው በመባሉ ምክንያት የሕግ መሠረት የሌለው መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ተጠሪ የስጦታ ውሉን መነሻ በማድረግ ሰርቪስና ሽንት ቤቱ በ 210 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ላይ ያቀረበው የመብት ጥያቄ፣የስጦታ ውሉ የሕጉን ፎርም ያላሟላ ፈራሽ ነው በመባሉ ምክንያት ውሉ በሙሉ ውድቅ የተደረገ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

7. የሥር ፍርድ ቤት በሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና በአንድ ክፍል ሽንት ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት መደምደሚያ ላይ የደረሰው፣ ተጠሪ ቤቶቹን የአመልካችዎች አውራሽና ወላጅ አባት ሣይቃወመው በራሱ ወጭና ገንዘብ የሠራቸው መሆኑ በማስረጃ ተረጋጋጧል በማለት ነው፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል ሽንት ቤት የአመልካቾችና የተጠሪ ወላጅ አባትና አውራሽ ፈቃድና ያለምንም ተቃውሞ ተጠሪ በራሱ ውጭ የገነባቸው መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች በማስረጃ አረጋገጠዋል፡፡ በአንድ ሰው የይዞታ መሬት ላይ ባለይዞታው ሣይቃወም ህንፃ የገነባ ሰው የህንፃው ባለቤት እንደሚሆን፣ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ሁለቱ ክፍል ሰርቪስ ቤቶችና አንድ ክፍል ሽንት ቤት ከጅምሩ የአመልካቾች አውራሽ የግል ሀብት ሣይሆኑ የተጠሪ የግል ንብረት መሆናቸውን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የደረሱበትን የፍሬ ጉዳይ መደምደሚያ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ በማጣመር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሟች ሲሞት ለሟች ወራሾች የሚተላለፈው በሟች መሞት ምክንያት የማይቋርጡ መብቶችና ግዴታዎች መሆናቸው በፍትሐበሔር

ሕግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር የአመልካችዎች አውራሽ ተጠሪ በራሱ ወጭ በሰራቸው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤቶች እና አንድ ክፍል ሽንት ቤት ላይ የባለሀብትነት መብት የሌለው በመሆኑ፣ አውራሻቸው የሌለው መብት ለአመልካች ወራሾች ሊተላለፍ የሚችልበት የሕግ መሠረት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ የሠራቸው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል ሰርቪስ ቤት የውርስ ንብረት ክፍል ሣይሆን የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት የሰጡት ውሣኔ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) ድንጋጌ መሠረት ያደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ ቤቶቹን የሠራኃቸው እኔ ነኝ የሚል ጥያቄ ያቀረበ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የሕግ ድንጋጌ ማለትም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) በመጥቀስ የሰጡት ውሳኔ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182(2) ድንጋጌ የሚጥስ ነው በማለት አመልካቾች ያቀረቡት ክርክር የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም ፡፡

8. ተጠሪ የውርስ ንብረት በሆነው የቤት ቁጥር 429 ግቢ ውስጥ የሠራቸው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል ሽንት ቤት የግል ባለሀብት ነው የተባለው በስጦታ ውሉ ሳይሆን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) መሠረት ባለይዞታው ሣይቃወመው በግል ገንዘቡ የሠራው ነው ተብሎ ነው፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) መሠረት ባለመብት የሚሆነው የአመልካቾች አውራሽ ሳይቃወመው በራሱ ወጭ በሠራቸው ቤቶችና ቤቶቹ በተሰሩበት ወይም ባረፉበት ቦታ ላይ እንጅ፤ ቤቶቹን ከሠራበት ቦታ ውጭ ባለው የይዞታ ቦታ ላይ ባለመብት የሚሆንበት ድንጋጌ አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር የበታቸ ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በግቢው ውስጥ በ 210 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ላይ መብት አግኝቼበታለሁ የሚለው የስጦታ ውል ፈራሽነው በማለት ከወሰኑ በኃላ ተጠሪ 210 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የይዞታ መብት እንዳለው ገልፀው የሰጡት ውሳኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826(2) ድንጋጌ መሠረት ያላደረገና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
9. ከዚህ አንፃር ቢታይ ተጠሪ ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል ሽንት ቤት ግንባታ ካከናወነበትና ቤቱ ካረፈበት ቦታ ውጭ በ210 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ባለይዞታ የሚሆንበት የሕግ መሠረት የሌለ በመሆኑ ፣የበታች ፍርድ ቤቶች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179 (1) ድንጋጌ ይዘት በአግባቡ ሣይገነዘቡ ተጠሪ በራሱ ወጭ የሰራቸው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤት፣ አንድ ክፍል ሽንት ቤትና 210 ካሬ ሜትር ይዞታ የውርስ ንብረት አይደለም በማለት የሰጡት ውሣኔ በከፊል መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ውሣኔ**

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. የበታች ፍርድ ቤቶች ተጠሪ በራሱ ውጭ የሠራቸው ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል ሽንት ቤት የውርስ ንብረት ክፍል ሣይሆኑ የተጠሪ የግል ንብረት ናቸው በማለት የሰጡት ውሣኔ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1179(1) መሠረት ያደረገ በመሆኑ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ በቤት ቁጥር 429 ግቢ ውስጥ 210 ካሬ ሜትር ቦታ ባለ ይዞታ ሆኜበታለሁ የሚለው የስጦታ ውል ፈራሽ የሆነ በመሆኑና ሁለት ክፍል ሰርቪስ ቤትና አንድ ክፍል

ሽንት ቤት ከገነባበትና ቤቱ ካረፈበት ውጭ ያለው 210 ካሬ ሜትር ቦታ የውርስ ንብረት ክፍል አይደለም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

4. ተጠሪ ሰርቪስ ቤቱና ሽንት ቤቱ ከገነባበትና ቤቱ ካረፈበት ቦታ ውጭ ባለው ይዞታ ቦታ ላይ የይዞታ መብት የለውም ብለናል፡፡ ተጠሪ ሰርቪስ ቤትና ሽንት ቤት ከገነባበትና ቤቱ ካረፈበት ቦታ ውጭ ያለው የቤት ቁጥር 429 ይዞታና ቤቱ ላይ አመልካችና ተጠሪ እኩል የወራሽነት መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡
6. ይህ ውሣኔ ተጠሪ በአፈፃፀም ወቅት የመውጭያና የመግቢያ መብት ይከበርልኝ የሚለበትን ጥያቄ ከማቅረብ አያግደውም፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ግ**

የሰ/መ/ቁ. 96364

ጥቅምት 10 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- እልፍነሽ ወርቁ ጠበቃ አሳምነው ቀረቡ

ተጠሪ፡- ኤልሳቤጥ አስራት ጠበቃ መስፍን ጌታቸው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የመ/አመልካች፣ተጠሪ ደግሞ የመ/ተጠሪ ነበሩ የመ/አመልካች የነበሩት የአሁን አመልካች ባቀረቡት የመቃወም አቤቱታ የመቃወም ተጠሪ ሟች ወ/ሮ አስረስ እሸቴ መስከረም 28/2000 ዓ.ም. ያደረጉትን ኑዛዜ ነሐሴ 23 ቀን 2003 ዓ.ም የሻሩት መሆኑን እያወቁ በተሻረው ኑዛዜ የወራሽነት ማስረጃ መውሰዳቸው ተገቢነት ስለሌለው ማስረጃው ይሻርልኝ በማለት ጠይቀዋል፤ተጠሪም በሰጡት መልስ ሟች መፃፍ እና መፈረም ይችላሉ መስከረም 28/2000 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜም ላይ ስማቸውን ጽፈው የፈረሙ ሲሆን አመልካች የኑዛዜ መሻሪያ ብለው ያቀረቡት ሰነድ ላይ ግን የሟች ፊርማ ተብሎ የተቀመጠው የጣት ምልክት ሲሆን ከምልክቱ በላይ ግን የሟች ስም ተፅፏል፡፡ በመሆኑም መሻሪያ የተባለው ሰነድና መስከረም 28/2000 ዓ.ም. ያደረጉት ኑዛዜ ከፍተኛ ልዩነት አለው፡፡ ሟችም ለረዥም አመት ታመው ፓራላይዝ ሆነው የሚያደርጉትን አያውቁም ባጠቃላይ መሻሪያ ተብሎ የቀረበው ሰነድ የኑዛዜን ፎርማሊቲ የማያሟላና ህጉን ተከትሎ የተፈፀመ አይደለም፣ንብረቱንም ቢሆን ተጠሪ ወደ ስሜ አዙሬዋለሁ፣ ተቃወሞዋቸው ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤትም፡- ሟች መስከረም 28/2000 ዓ.ም ያደረጉትን ኑዛዜ በግልፅ የሻሩት መሆኑን ነሐሴ 23/2003 ዓ.ም. ባስመዘገቡት መሻሪያ ሰነድ ገልጸዋል፤ፎርሙን አስመልክቶ አመልካች ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡ሟች ወ/ሮ አስረስ እሸቴ በፍ.ብ.ሕ.ቁ.898 ላይ በተቀመጠው መሰረት መስከረም 28/2000 ዓ.ም ያደረጉትን ኑዛዜ የሻሩት መሆኑን ስለገለፀ አመልካች በተሻረ የኑዛዜ ሰነድ የተሰጣቸው የወራሽነት ማስረጃ ተሰርዟል ሲል ወሰነ ፡፡የከተማው ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤትም የአመልካችን ይግባኝ ሳይቀበለው አፀንቶታል፡፡ በመጨረሻ ጉዳዩ የቀረበለት የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት የኑዛዜ መሻሪያ ሰነዱ ተናዛዥና በቦታው ለነበሩ ምስክሮች

የተነበበላቸው ስለመሆኑ የሚያመለክት ቃል በሰነዱ ላይ አይታይም።የፍ.ብ.ሕ.ቁ. 881 እና 898(1) ላይ የተጠቀሰውን የመሻሪያ ሰነዱ አያሟላም ሲል የሥር ውሣኔዎችን ሽሮታል፡፡
የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን ውሳኔ ለማሳረም ነው፡፡
አመልካች በሰበር አቤቱታው ቅሬታውን ሳያቀርብ በፍ.ሕ.ቁ. 898 መሠረት የግልፅ ኑዛዜ በሚያደርገው አይነት ኑዛዜን መሻር ይቻላል፡፡ በቀጣይ የፍ/ሕ/ቁጥር 899 መሠረት ደግሞ ተናዛዡ ያለውን የኑዛዜ መሻር ሀሳብ በቂ አድርጎ በመግለፅ አይነት የኑዛዜው አነጋገር በመሰረዝ ኑዛዜውን በማጥፋት በመቅደዱ ኑዛዜውን መሻር እንደሚቻል ህጉ እያመላከተ ፎርማሊት አላሟላም ተብሎ መወሰኑ እና ተናዛዥ ኑዛዜውን በፈለገው ጊዜ የመሻር መብቱን ያጣበበ በመሆኑ የፍ.ህ.ቁ. 881 አልተሟላም ተብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት አመልክተዋል፡፡
በዚህም መሰረት ይህ ችሎት ኑዛዜ ሲሻር ኑዛዜው በተሰጠበት አግባብ ብቻ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 898,899 እና 900 አኳያ ለመመርመር በጭብጥነት በመያዝ የግራ ቀኙን መልስና የመልስ መልስ በፅሑፍ እንዲቀባበሉ በማድረግ አከራክሯል፡፡
አመልካች ክርክራቸውን በማጠናከር የሟች የመሻሪያ ኑዛዜ ሰነድ በአግባቡ የተከናወነ እና የፍ.ህ.ቁ. 881 (ፎርማሊትን) ሊከተል የሚገባው አይደለም በመሆኑም የፍ.ሕ.ቁ. 898 መሰረት አድርጐ መሻሩበተረጋገጠበት የከተማው ሰበር ችሎት የሥር ውሳኔን መሻራቸው አግባብነት የለውም ሲሉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በተቃራኒው የሥር ውሳኔ መሻሩ በአግባቡ ነው ሲሉ ክርክራቸውን አጠናክረዋል፡፡
ባጠቃላይ የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰው ነው፡ በመሆኑም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረናል፡፡
በመሰረቱ የተያዘውን ጉዳይ ጠቅለል ባለመላኩ ስናየው እያከራከረ ያለው የህግ ጥያቄ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ ሲጤን ተጠሪ ከሟች መስከረም 28/2000 ዓ.ም አገኘሁት የሚሉት ኑዛዜ በድጋሚ ሟች በህይወት እያሉ ነሐሴ 23/2003 ዓ.ም. በውል አዋዋይ ጽ/ቤት ያደረጉት የመሻርያ ሰነድ በቀጥታ የመጀመሪያውን ኑዛዜ ዋጋ አልባ ያደረገዋል ወይስ የኋለኛው የመሻሪያ ሰነድ ሊከተለው የሚገባው ልዩ ስርዓት አለው የሚለውን አከራካሪ ነጥብ ከተጠቀሱት የፍ/ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ሆኗል።በመሠረቱ ኑዛዜ የሟች ጥብቅ የሆነ የግል ጠባይ ያለው እና ራሱ የሚተገብረው ነው በመሆኑም የተናዛዡ ሀሳብና ፍላጐት በጥንቃቄ ልንከተለው የሚገባው ነው፡፡ ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የፍ.ህ.ቁ. 898(1)ተናዛዡ ኑዛዜዎቹ ዋጋ ያላቸው እንዲሆኑ በሚያስፈልገው ፎርም ዓይነት ግልፅ አድርጎ በማስታወቅ ኑዛዜውን የሻረ እንደሆነ በጠቅላላው አኳኃን የሚሻር ይሆናል ይላል።በዚሁ ህግ አንቀፅ 899(1) ተናዛዥ የተናዘዘውን ለመሻር ወይም ለመለወጥ ያለውን ሀሳብ በቂ አድርጎ በመግለፅ ይህንንበኑዛዜው የተመለከተውን ቃል መሻር ይችላል በማለት ተደንግጓል፡፡
በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን ሁለቱንም ድንጋጌዎች ስናይ አንዱ ሌላኛውን በሚያጠናክር መልኩ የተቀመጠ እንጂ የሚቃረኑ አይደለም፡፡
ይህም ሲባል ሁለቱም አንቀፆች ተናዛዡ ያደረጋቸው ኑዛዜ መሻር ሲፈልግ ሀሳቡን በማያሻማ አኳኋን ግልፅ በሆነ መንገድ መሻር እንደሚችል የሚገልፅ ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ሟች (ተናዛዡ) ከዚህ ውጭ ሊከተላቸው የሚገባው ሥርዓት መኖሩን አይደለም፡፡ ይልቁንም ተናዛዡ ኑዛዜውን ለመሻር ሊከተላቸው የሚገባውን አማራጮች የሚያመለክት (የሚገልፅ) ነው፡፡ እንግዲህ በያዝነው ጉዳይም ሟች ነሐሴ 23/2003 ዓ.ም.ባደረጉት የመሻሪያ ሰነድ ተጠሪ (ተሻሪዋ) ከዚህ ቀደም እንደተገበሩት የተሰጣቸውን ሀላፊነት ባለመወጣታቸው እና ለግል ጥቅማቸው በማዋላቸው

ምክንያት በትክክለኛ አእምሯቸውና በፍላጐታቸው የመጀመሪያውን የኑዛዜ ሰነድ በግልፅ ቃልና አነጋገር የሻሩት መሆኑን ነው፡፡ ይህም የተፈፀመው በውል አዋዋይ ጽ/ቤት መሆኑም ተመልክቷል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው የግድ ሟች የመስከረም 28/01/2000 የፈፀሙትን ሥርዓት ሊከተሉ አይገባቸውም፡፡ ይህን ኑዛዜ ለመሻር በቁና ግልፅ ቃል መሻራቸውን መግለፃቸው የመጀመሪያውን ያስቀረዋል፡፡ የፍ/ህ/ቁ. 881ን አልተከተለም በማለት ብቻ የሟችን የግል ሀሳብና ፍላጎት መቃረን አይገባም፡፡

በመጨረሻም በሥር (ከተማው የሰበር ሰሚ ችሎት ሟች በመስከረም 28/01/2000 ዓ.ም.ያደረጉት ኑዛዜ በነሐሴ 23/2003 ዓ.ም. በተደረገው ሊሻር አይገባውም (ሊሽረው) አይችልም፤መባሉን ይህ ችሎት የሚቀበለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለዚህ የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት የከተማውን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና የይግባኝ ሰሚውን ውሣኔዎች መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

***ው ሣ ኔ***

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 927105 3/11/05 እና የከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 20673 በቀን 10/01/2006 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 21133 በቀን 27/3/2006 የተሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
3. ለተጠሪ በመስከረም 28/2003 ዓ.ም. የተሰጠው ኑዛዜ ነሐሴ 23/2003 ዓ.ም. በተደረገው የመሻሪያ ሰነድ ተሽሯል (ቀሪ) ሆኗል ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ በውሣኔ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**እ/ኢ**

የሰ/መ/ቁ. 97948

ታህሳስ 21 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች**፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች**፡-ወ/ሪት ሄለን ተክሌ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡-ወ/ሮ ዘይድ አብርሃ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ይጣራልኝ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች የሟች አባታቸው የአቶ ተክሌ ነጋሽ የውርስ ንብረት እንዲጣራላቸው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ የውርስ አጣሪው በፍርድ ቤቱ ተቋቁሞ የማጣራት ስራውን ከአጠናቀቀ በኋላ ሪፖርቱ ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ግራ ቀኙ አስተያየት ከሰጡበት በኋላ የውርስ አጣሪው ሪፖርት ተሻሽሎ በስር ፍርድ ቤት ፀድቋል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- አመልካች ሶፋውን ከእነ ሙሉ ጠረጴዛ የግል ንብረቴ ነው በማለት ጠይቀው እያለ በንብረቱ ላይ የግል ወይም የጋራ ነው ተብሎ ዳኝነት ሳይሰጥበት መታለፉ እና የቀበሌ ቤት የተከራይነት መብትን በተመለከተም አመልካች በወራሽነታቸው የሚገባቸው ስለመሆኑ በፍርድ ቤት መወሰን ሲገባው በቤቱ አካራይ የሚወሰን ነው ተብሎ መታለፉ ያላግባብ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታቸው ተመርምሮም በዚህ ችሎት ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ ተጠሪ እንዲቀርቡ ተደርጎ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ነጥቦች፡-

1. ሶፋውን ከእነ ሙሉ ጠረጴዛ ዳኝነት ሳይሰጥ መታለፉ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም?፣

2. በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ክልል ውስጥ በሚገኘውና በቁጥር 009 በሚታወቀው የቀበሌ ቤት የሟች አባት የነበራቸው የተከራይነት መብት ለአመልካች ሊተላለፍ የሚችል መሆን ያለመሆኑ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉ ሁነው ተገኝተዋል፡፡

<u>***የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ***</u>፡-አመልካች የሟች አቶ ተክሌ ነጋሽ ወራሽ መሆናቸውን ጠቅሰውና የሟቹ ንብረት እንዲጣራ የውርስ አጣሪ በፍርድ ቤት እንዲሾም ጠይቀው ፍርድ ቤቱም የውርስ አጣሪው እንዲቋቋም አድርጎ አመልካች ሊጣራ የሚገባቸውን የውርስ ንብረቶች ህዳር 05 ቀን 2005 ዓ/ም በፃፉት ማመልከቻ ዘርዝረው ያቀረቡ መሆናቸውን፣በዚህ የንብረት ዝርዝርም ከሟቹ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች ናቸው በሚል ወደ 48 የሚሆኑ የቤት መገልገለያ እቃዎችን መጥቀሳቸው የውርስ አጣሪው ከአቀረበው የውርስ ማጣራት ሪፖርት መጠቀሱን ከስር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ የተመለከተን ሲሆን በዚህ የንብረት ዝርዝር ውስጥ አመልካች በሟቹ መኖሪያ ቤት ሶፋ ከእነ ሙሉ ጠረጴዛ አለ በማለት የጠቀሱት ነገር እንደሌለ ግልባጩ የሚያሳይ ሁኖ አግኝተናል፡፡ከዚህም መረዳት የሚቻለው አመልካች ይህንኑ ንብረት የውርስ ንብረት ነው በማለት በዚህ ረገድ ተገቢው መጣራት እንዲደረግላቸው የማጣራት ስራውን እንዲያከናውን በፍርድ ቤት ለተሾመው የውርስ አጣሪ ጥያቄ ያላቀረቡ ከመሆኑም በላይ የማጣራት ስራውን ሲከታተል ለነበረው ፍርድ ቤትም በተገቢው ጊዜ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ጥያቄ ያለመኖሩን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡እንዲህ ከሆነ አመልካች ሶፋው ከእነ ሙሉ ጠረጴዛ ዳኝነት ተጠይቆበት የግል ወይም የጋራ ነው ተብሎ ውሳኔ ሳያርፍበት ቀርቷል በማለት የሚያቀርቡት ቅሬታ በስር ፍርድ ቤት የዳኝነት ጥያቄ ያልቀረበበት በመሆኑ እና የስር ፍርድ ቤት ደግሞ ባልተጠየቀ ጉዳይ ዳኝነት የሚሰጥበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182 (1) ድንጋጌ ስር የተመለከተ በመሆኑ ይህ ችሎት በዚህ ረገድ አመልካች የሚያቀርቡትን ቅሬታ የሚቀበለው ሁኖ አልተገኘም፡፡

<u>***ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ***</u>፡- አመልካች የሟች አቶ ተክሌ ነጋሽ ወራሽ መሆናቸውንና ሟቹ ከቀበሌ ተከራይተው ይኖሩበት የነበረ መኖሪያ ቤት እንዳላቸው ጠቅሰው የሟች አባታቸው የተከራይነት መብት እንዲተላለፍላቸው ዳኝነት እንዲያርፍበት ጥያቄ ማቅረባቸውን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡የበታች ፍርድ ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ያለፉት ጉዳዩ በቤቱ ባለቤት የሚወሰን እንጂ በፍርድ ቤት የሚወሰን አይደለም በሚል ነው፡፡ይሁን እንጂ የቀበሌ ቤት የተከራይነት መብት ተከራይ ሲሞት ለወራሾቹ ወይም ለቤተሰቦቹ የሚተላለፍ መሆን ያለመሆኑ በፍ/ብ/ሕጉ ስለማይንቀሳቀስ ንብረት የኪራይ ውል የተመለከቱትን ድንጋጌዎች፣የቀበሌ ቤትን የኪራይ መብትና ግዴታ ለመግዛት በሚመለከተው አካል በወጡት ደንብና መመሪያዎች አንጻር ታይቶ በፍርድ ቤት ዳኝነት የሚሰጥበት እንጂ የቤቱ አስተዳዳሪ የሆነ ቀበሌ ለፈለገው ሰው የሚያከራየው ነው ተብሎ በፍርድ እንዳያልቅ የሚደረግ ጉዳይ አይደለም፡፡የቀበሌ ቤት የተከራይነት መብት የሚሰጥበት አግባብ በሕግ ስርዓት የሚዘረጋለትና የራሱ የሆነ አሰራር ያለ መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡መብቱ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓትና አሰራር መሰረት መፈፀሙ ያለመፈፀሙ ላይ ክርክር ሲነሳ ደግሞ ነፃና ገለልተኛ በሆነ አካል፤በፍርድ ቤት ታይቶ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎችን፣ህጎችንና አሰራሮችን መሰረት በማድረግ ዳኝነት የሚሰጥበት እንጂ ጉዳዩ የቤቱ አስተዳዳሪ ለሆነው አካል የሚተው አይደለም፡፡የቀበሌ ቤት የተከራይነት መብት ላይ ክርክር ሲነሳ ጉዳዩ ለቤቱ አስተዳዳሪ ለሆነው ለቀበሌ የሚተው ነው ከተባለ የቀበሌ ቤት የተከራይነት መብት ማግኘት ያለባቸው ግለሰቦችም መብታቸውን በአግባቡ ለማስከበር የሚችሉበት አግባብ ይኖራል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም፡፡በመሆኑም የበታች ፍርድ

ቤቶች አንድ የቀበሌ ቤትን ተከራይቶ የነበረ ሰው ከዚህ አለም በሞት ሲለይ ወራሾቹ ወይም ቤተሰቦቹ የተከራይነት መብቱ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አግባብ ከኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 37፣ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 826(2) እና 2928 ድንጋጌዎች እንዲሁም በዚህ ረገድ የወጣውን መመሪያና ተቀባይነት ያለውን አሰራር በመመልከት የራሳቸው በቂ መተዳደሪያ የሌላቸው ዜጎች ከመንግስት ሊደረግላቸው ከሚገባው ድጋፍ ጭምር በመመርመር ዳኝነት መስጠት ሲገባቸው ጉዳዩ በፍርድ ቤት የሚያልቅ አይደለም በማለት የአመልካችን የቀበሌ ቤቱን የተከራይነት መብት የውርስ ጥያቄ ማለፋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 75418 መጋቢት 10 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 135521 ታህሳስ 22 ቀን 2006 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በየካ ክፍለ ከተማ በወረዳ 06 ክልል ውስጥ በሚገኘው ቁጥሩ 009 በሆነው የቀበሌ ቤት ላይ አመልካች ተከራይ የነበሩትን ሟች አባታቸውን አቶ ተክሌ ነጋሽ መብት ለመውረስ ያቀረቡት ጥያቄ በፍርድ ቤት የሚወሰን አይደለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡በቤቱ ላይ የቀረበው የተከራይነት መብት የውርስ ጥያቄ በፍርድ ቤት የሚያልቅ ነው በማለት በዚህ ነጥብ ላይ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን ቀጥሎ በፍርድ ሐተታው ላይ በተመለከተው አግባብ ጉዳዩን አጣርቶና ተገቢውን የክርክር አመራር ሁሉ በመከተል ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
3. ሶፋን ከእነ ሙሉ ጠረጴዛ በተመለከተ የበታች ፍርድ ቤቶች ማለፋቸውም ሆነ በሌሎች ንብረቶች ላይ የሰጡት የውሳኔ ክፍል ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውንወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

***መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡***

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::***

የሰ/መ/ቁ.102652

መጋቢት 16 ቀን 2007 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡-ወ/ሮ ሀቢባ መካ -ከጠበቃ ዘውዱ ተሾመ ጋር ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ደሊል ሁሴን - ቀረቡ
2. ኢትዮ የአሽከርካሪዎች እና መካኒኮች ማሰልጠኛ ማዕከል ኃ. የተወሰነ የግል ማህበር

- ጠበቃ ስንታየሁ ብርሃኑ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የአክሲዮን ድርሻ በተጋቢዎቹ መካከል የሚከፋልበትን ስርዓት አስመልክቶ የተነሳ የአፈጻጸም ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ በአመልካች እና በ1ኛ ተጠሪ መካከል በነበረው የንብረት ክፍፍል ክርክር በ2ኛ ተጠሪ ማህበር ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው 162 የአክሲዮን ድርሻ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ንብረት መሆኑ ተረጋግጦ እኩል እንዲካፈሉ በስረ ነገሩ ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፣ይህንኑ ውሳኔ ለማስፈጸም አመልካች ባቀረቡት የአፈጻጸም ክስ ላይ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 418 ድንጋጌን ጠቅሶ መቃወሚያ አቅርቦ የነበረ መሆኑን፣ፍርድ ቤቱም መቃወሚያው ወደፊት የሚታይ ነው በማለት የጋራ ናቸው የተባሉትን ሌሎች ንብረቶች በተመለከተ አፈጻጸሙን መቀጠሉን፣ከዚህ በኃላ የአክሲዮን ድርሻውን በተመለከተ እንደ ፍርዱ እንዲፈጸምላቸው አመልካች አቤቱታ ማቅረባቸውን፣ፍርድ ቤቱም የአክሲዮን ድርሻው የሚገኝበት ማህበር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ለአፈጻጸሙ ያመች ዘንድ በአፈጻጸም ጥያቄው ላይ ማህበሩ አስተያየት እንዲሰጥ ትዕዛዝ መስጠቱን ተከትሎ ከቀድሞ ተጋቢዎች መካከል አንዳቸው ለሌላኛው ድርሻውን ለቆ አንደኛው ወገን በማህበሩ አባልነት መቀጠል የሚችል ከመሆኑ ውጪ ሁለቱን ወገኖች በአንድነት በማህበሩ ውስጥ የማይፈልጋቸው መሆኑን ገልጾ አስተያየት ማቅረቡን፣ግራ ቀኙ የዋጋ ግምቱን ተቀብለው አንዳቸው ለሌላኛው ድርሻውን ለመልቀቅ መስማማት ያልቻሉ መሆኑን እና የማህበሩ አባላት ባልተስማሙበት ሁኔታ ደግሞ ፍርድ ቤቱ ሌላ ሰው በማህበሩ ውስጥ አባል እንዲሆን መወሰን የማይችል መሆኑን ገልጾ የአክሲዮን ድርሻው

ተሸጦ ገንዘቡን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ እኩል እንዲከፋፈሉ ትዕዛዝ መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ዘግቶ በማሰናበቱ ሲሆን የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት አክሲዮኖች በዓይነት መካፈል የሚችሉ ሆነው የ2ኛ ተጠሪ መተዳደሪያ ደንብም ሳይከለክል አክሲዮኖቹ በሐራጅ ተሸጠው ክፍፍሉ እንዲፈጸም የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት የስር ፍርድ ቤቶች የአፈጻጸም ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት በ2ኛ ተጠሪ ማህበር ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው 162 የአክሲዮን ድርሻ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት መሆኑ በስረ ነገሩ ፍርድ ተረጋግጧል፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት የአክሲዮን ድርሻው በሐራጅ ተሸጦ ክፍፍሉ በገንዘብ እንዲደረግ ውሳኔ ሊሰጥ የቻለው ከቀድሞ ተጋቢዎች መካከል አንዳቸው ለሌላኛው ድርሻውን ለቆ አንደኛው ወገን በማህበሩ አባልነት መቀጠል የሚችል ከመሆኑ ውጪ ሁለቱን ወገኖች በአንድነት በማህበሩ ውስጥ የማይፈልጋቸው መሆኑን ገልጾ 2ኛ ተጠሪ ማህበር አስተያየት አቅርቦአል በማለት ነው፡፡አመልካች ከስር ጀምረው የሚከራከሩት ደግሞ አክሲዮኖቹ በዓይነት ሊካፋፈሉ የሚችሉ በመሆኑ ሕጻናት ልጆቻቸውን ለማሳደግ ጭምር እንዲረዳቸው የአክሲዮኖቹ ክፍፍል በዓይነት እንዲደረግ በመጠየቅ ነው፡፡በመሰረቱ የጋብቻ መፍረስን ተከትሎ የጋራ ሀብት እንዲከፋፈል የሚደረገው እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሀብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰው በማድረግ ስለመሆኑ እና ክፍፍሉ በሽያጭ ሊደረግ የሚችለው ንብረቱ ለክፍፍል የማያመች ወይም ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ ንብረቱ ከሁለት ለአንዳቸው እንዲሰጥ ባልና ሚስቱ ሳይስማሙ በቀሩ ጊዜ ስለመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 91 እና 92 ስር በዝርዝር ተደንግጎ ይገኛል፡፡

በተያዘው ጉዳይ 2ኛ ተጠሪ ማህበር ከአመልካች እና ከ1ኛ ተጠሪ መካከል አንዳቸውን እንጂ ሁለቱን በማህበሩ ውስጥ አልፈልጋቸውም ከማለት በቀር አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ አክሲዮኖቹን በየድርሻቸው በዓይነት በመከፋፈልየማህበሩ አባላት መሆን የማይችሉበት ሕጋዊ ምክንያት ስለመኖሩ በስር ፍርድ ቤት ያቀረበው ክርክር እና ማስረጃ የለም፡፡በሰበር ደረጃም ቢሆን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ አክሲዮኖቹን በዓይነት ተከፋፍለው በአባልነት ይቀጥሉ መባሉ በማህበሩ ውስጥ ብርቱ ጭቅጭቅን እና አለመግባባትን የሚያስከትል ነው ከማለት ውጪ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሊከሰት ስለሚችልበት ምክንያት ያቀረበው አሳማኝ መከራከሪያ የለም፡፡ የአክሲዮኖቹ በዓይነት የመከፋፈል ጉዳይ የሚመለከተው በመሰረቱ አመልካችን እና 1ኛ ተጠሪን እንጂ 2ኛ ተጠሪን ባለመሆኑ አክሲዮኖቹ ሊከፋፈሉ የሚገባቸው በሽያጭ ነው በማለት 2ኛ ተጠሪ መቃወሚያ አቅርቦ ለመከራከር የሚያስችል መብት እና ጥቅም አለው ለማለትም የሚቻል አይደለም፡፡

ሲጠቃለል በ2ኛ ተጠሪ ማህበር ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው 162 የአክሲዮን ድርሻ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ የጋራ ንብረት መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ የአክሲዮን ድርሻውን አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በዓይነት እንዲከፋፈሉ ለመወሰን የሚከለክል ሕጋዊ ምክንያት ባልቀረበበት ሁኔታ 2ኛ ተጠሪ ማህበር የሰጠውን አስተያየት ብቻ

መሰረት በማድረግ የአክሲዮን ድርሻው ክፍፍል በሽያጭ አማካይነት እንዲፈጸም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በይግባኝ ሰሚው ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በትዕዛዝ የጸናው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 91 እና 92 ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ እና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በ2ኛ ተጠሪ ማህበር ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግበው የሚገኙት 162 የአክሲዮኖች ለአመልካች እና ለ1ኛ ተጠሪ ሊከፋፈል የሚገባው በሐራጅ ሽያጭ ነው በሚል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 206322 በ25/07/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 150907 በ30/08/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በ2ኛ ተጠሪ ማህበር ውስጥ በ1ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግበው የሚገኙት 162 አክሲዮኖች በዓይነት ሊከፋፈሉ የማይችሉበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ እነዚህን አክሲዮኖች አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 91(1) ድንጋጌ መሰረት እያንዳንዳቸው 81 አክሲዮኖችን በዓይነት ሊከፋፈሉ ይገባል በማለት ወስነናል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ በውሳኔው መሰረት እንዲያስፈጽም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ እንዲያውቀው ደግሞ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::**

የሰ/መ/ቁጥር 108539

መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ አበባው አጥናፉ - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ የካባ ግዛው - ወኪል ተሻገር ካሤ - ቀረበ

2. አቶ ጌቴ ግዛው - ቀረቡ

3. ወ/ሮ ምሳዬ ግዛው - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት መብት በውርስ የሚተላለፍበትን አግባብ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው በመቄት ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች የአሁኑ ተጠሪዎች የሟች እማሆይ እቴ አለማየሁ የገጠር መሬት ይዞታ ሕጋዊ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋገጥ ማስረጃ በወረዳው ፍርድ ቤት ሰኔ 21 ቀን 2004 ዓ/ም መውሰዳቸው ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ ውጪ ነው በማለት ተጠሪዎች የወሰዱት ማስረጃ እንዲሰረዝ መስከረም 20 ቀን 2006 ዓ/ም ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪዎች የገጠር መሬት ይዞታ ውርስ ማረጋገጫ ማስረጃ እንዲሰረዝ መሰረት ያደረጉት ምክንያት የሟች እማኊይ እቴ አለማየሁ የቤተሰብ አባልና የራሳቸው መሬት ይዞታ የሌላቸው ሁኖ እያለ ተጠሪዎች የሟቿ የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች በመሆናቸው ብቻ መሬቱን ሊወርሱ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም የሚል ሲሆን ተጠሪዎች ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርበው በሰጡት መልስ የሟች ልጆች ሁነው በሕጉ አግባብ የወራሽነት ማስረጃውን መውሰዳቸውን ፣ የአሁኑ አመልካች ደግሞ የሟቿ የቤተሰብ አባል ቢሆኑም እማሆይ እቴ አለማየሁ ከነበራቸው ሁለት ቃዳ መሬት ከመሞታቸው በፊት እኩሌታውን ከፍለው ለአሁኑ አመልካች የሰጧቸውና አመልካቹ የራሳቸው የሆነ ይዞታ እያላቸው የሟቿን ድርሻ ለመውሰድ ጥያቄ ማቅረባቸው ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡ በዚህ መልክ ክርክር የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳዳር አዋጅና ደንብ መሰረት ሳይናዘዝ የሞተ አርሶ አደር ይዞታ መብት የሚተላለፍበትን የሕግ አግባብ ዘርዝሮ ከአስቀመጠ በኋላ አመልካች መሬት ያላቸው የሟች የቤተሰብ አባል ሲሆኑ ተጠሪዎች ደግሞ መሬት ላቸው የሟች ልጆች ናቸው የሚል ምክንያት ይዞ ተጠሪዎች ይዞታውን ለመውረስ ማስረጃ መውሰዳቸው በአግባቡ ነው በማለት የአመልካችን ተቃውም ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሰሜን ወሎ

አስተዳዳር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው በፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ ጉዳዩን መርምሮይዞታውን የመውረስ መብት ያላቸው የአሁኑ አመልካች እንጂ የአሁኑ ተጠሪዎች አይደሉም በማለት የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኝቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች ያወጡት የወራሽነት ማስረጃ በደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11/7/ሐ// መሰረት መሬት ያላቸው የሟች ልጆች መሆናቸውን የሚገልጽ ነዉ ፣ የአሁኑ አመልካች ያወጣው የወራሽነት ማስረጃ በደንቡ አንቀጽ 11/7/ለ// መሰረት የሟች የቤተሰብ አባል መሆኑን የሚገልጽ ነው የሚል ምክንያት ጠቅሶና ማስረጃው የሟችን መሬት ለመውረስ ያላቸውን ደረጃ የሚገልጽ ገላጭ የሆነ ማስረጃ ነው ፣ በመሬቱ ላይ ያላቸውን የመውረስ ቅደም ተከተል ደግሞ በመሬቱ ላይ ክርክር በተደረገ ጊዜ የሚታይ እንጂ የማስረጃ ይሰረዝልኝ ጊዜ የሚታይ አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ውጤቱን አጽንቶታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት የሠበር አቤቱታውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ተጠሪዎች የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ በመሆናቸው ብቻ በመሬቱ ላይ ያገኙት የወራሽነት ማስረጃ ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ በመደረጉ 1ኛ እና 3ኛተጠሪዎች መጥሪያ ደርሷቸው ሊቀርቡ ባለመቻላቸው በጹሑፍ መልስ የመሰጠት መብታቸው የታለፈ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ግን ቀርበው ከአመልካች ጋር በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን በሥር በሚገኙት በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ያደረጉትን ክርክር እና በእነዚህ ፍርድ ቤቶች የተሰጡትን ዳኝነት አግባብነት ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ካላቸው ህጎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነው ክርክር ያስነሳው የእርሻ መሬት ይዞታ ሟች እማሆይ እቴ አለማየሁ ኑዛዜ ሳይተው ከዚህ አለም በመለየታቸው ምክንያት አመልካችና ተጠሪዎች የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ መሰረት አድርገው የውርስ ይገባናል ጥያቄ አቅርበው የወረዳው ፍርድ ቤትና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕጉ ያለውን የገጠር መሬት የውርስ ቅደም ተከተል መሰረት አድርገው ተገቢ ነው ያሉትን ዳኝነት የሰጡ ቢሆንም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን የቅደም ተከተሉን ጉዳይ እልባት ሳይሰጠው በመሬት ላይ ክርክር በተደረገ ጊዜ የሚታይ ነው በሚል ያለፈው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ይሄው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተገቢነት ነው፡፡

በአንድ ክርክር ዳኝነት ሊሰጥ የሚገባው የክርክሩን አርእስት በማየት ሳይሆን ዝርዝር ይዘቱን በአግባቡ በመለየትና ተገቢነት ያለውን ህግ መሰረት በማድረግ መሆኑን የክርክር አመራርና የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ ክርክር የሚመራው ደግሞ በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት ነው፡፡ የፍትሐብሔር ክርክር የሚመራው በ1958 ዓ/ም በወጣው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግና ተፈጻሚነት ባላቸው ሌሎች የክልል ሕግጋት መሆኑ ይታወቃል፡፡ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ መሰረታዊ ዓላማም ክርክሮች በአነስተኛ ወጪ፣ ጉልበት እና በአጭር ጊዜ ታይተው ፍትሓዊና ትክክለኛ ዳኝነት ለመስጠት ማስቻል መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ክርክር ይህንኑ የክርክር አመራር መሰረታዊ አላማ በሚያሳካ መልኩ ሊመራ ይገባዋል፡፡

ከዚህ አንፃር የተያዘውን ጉዳይ ስንመለከተውም አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት ያቀረቡት ጥያቄ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳዳር ሕግ ከተዘረጋው ስርዓት ውጪ ተጠሪዎች

የሚቿን ይዞታ ለመውረስ የሚያስችላቸው ማስረጃ መስጠቱን ገልጸውና ይዞታውን በህጉ አግባብ መውረስ የሚችሉት አመልካች መሆኑን ጠቅሰው ለተጠሪዎች የተሰጣቸው ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪዎች ደግሞ የአከራካሪው ይዞታ ህጋዊ ወራሾች መሆን የሚገባቸው ተጠሪዎች እንጂ አመልካች አለመሆናቸውን ገልጸው ማስረጃው ሊሰረዝ አይገባም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በጭብጥነት ይዞ እልባት የሚሰጥበት ጉዳይ ይዞታውን መውረስ የሚችለው ወገን የትኛው ነው የሚለው ነው፡፡ የዚህ ጭብጥ እልባት ማግኘት ደግሞ ይዞታው ላይ መብት ያለውን ሰው የሚለይ በመሆኑ መብቱ የተረጋገጠለት ሰው አዲስ የመሬትይዞታ ይገባኛል ክርክር የሚያቀርብበት አግባብ ሳይኖር ውሳኔውን መሰረት አድርጎ አፈጻጸሙን የሚቀጥልበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህም አላስፈላጊ ወጪና የጊዜ ብክነት በማስቀረት ለክርክር እልባት ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ተጠሪዎች ከገጠር መሬት ይዞታ ውጪ በሌሎች የሟች ንብረቶች ማስረጃውን የወሰዱ መሆኑን አመልካች ገልጸው የወራሽነት ማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ያለማቅረባቸውን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ በመሆኑም የወራሽነት ማስረጃውን መሰረት አድርጎ የሚቀርብ የክፍፍል ጥያቄ በሌለበት ሁኔታ ወይም የገጠር መሬት ይዞታ ላይ የተሰጠውን የወራሽነት ማስረጃ መሰረት አድርገው ግራቀኙ የድርሻ ወይም የክፍፍል ጥያቄ ሊያነሱ የሚችሉበት አግባብ ሳይኖር ከክርክሩ ባህርይና ከፍትሃብሄር ስነ ስርዓት ውጪ የማስረጃ ይሰረዝልኝ ጥያቄ ላይ የመሬት ይዞታ ወራሽነት ቅደም ተከተል የመሬት ክርክር ሲነሳ የሚታይ ነው ተብሎ መወሰኑ የሕግ መሰረት የሌለውና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ***<u>ው ሳ ኔ</u>***

1. የአማራ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 03-07895 ሐምሌ 29 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ 03-09360 ህዳር 03 ቀን 2007 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የሟች እሚኃይ እቴ አለማየሁ የገጠር እርሻ መሬት ሊወርስ የሚገባው ማን ነው? የሚለው ጥያቄ እልባት ማግኘት ያለበት በሌላ መዝገብ በሚከፈተው የመሬት ክርክር ሳይሆን አመልካች ባቀረቡት የክርክር አግባብ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ክርክሩን በመ/ቁጥር 03-07895 ቀጥሎ የወረዳው ፍርድ ቤት እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሕግ አዋጅ ቁጥር 133/98 እና በደንብ ቁጥር 51/99 የተደነገገውን አግባብ መሰረት ያደረገ መሆን ያለመሆኑን መርምሮ ተገቢውን ዳኝነት ሊሰጥበት ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ሰበር ደረጃ ግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር ምክንያት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል ፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

# ንብረት

የሰ/መ/ቁ 101079

ጥር 22 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች:-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-** የይልማና ዴንሳ ወረዳ አከባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ፅ/ቤት

ከክልል ፍትህ ቢሮ አይናዲስ አሰጋህኝ - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- አቶ ውበት ገ/መድህን - የቀረበ የለም

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው ጉዳይ የገጠር የእርሻ መሬት የሚመለከት ሆኖ የተጀመረው በይልማና ዴንሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁን ተጠሪ በአቶ ልንገርህ ውበት ላይ የእርሻ መሬት ይዞታዬን ያላግባብ ይዞብኛል በማለት ክስ መስርተው ፍርድ ቤቱን የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ አከራካሪውን መሬት አቶ ልንገርህ ውበት ለአሁኑ ተጠሪ እንዲያስረክቡ በማለት ውሳኔ ሰጥቶ የአሁኑ ተጠሪ በዚሁ ፍርድ መሰረት እንዲፈጸምላቸው የአፈጻጸም ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡በዚህ ሂደት የአሁኑ አመልካች አከራካሪውን ይዞታ ይዘው የነበሩት አቶ ልንገርህ ውበት የመንግስት ሰራተኛ ስለሆኑና አመልካችም የይዞታ ባለመብት ስላልሆኑ ይዞታውን ሊረከቡ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፣ ውሳኔው የህዝብንና የመንግስት ጥቅም የሚነካ በመሆኑ ሊነሳ ይገባል በማለት አቤቱታውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች የፍርድ መቃወሚያ ላይ መልስ እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡የአሁኑ ተጠሪ ለአመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ ላይ በሰጡት መልስም የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ አቀራረብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ስር የተመለከተውን አግባብ ያልተከተለ መሆኑን፣አቶ ልንገርህ ውበት የተባሉት ግለሰብ መሬቱን ከተጠሪ በስጦታ ስለመቀበሉ ምንም ማስረጃ ባልቀረበበትና ራሱ የፍርድ ተቃዋሚ ወገን ባለሙያ መድቦ ይህንኑ ባረጋገጠበት ሁኔታ ፍርዱን መቃወሙ ያላግባብ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የተጠሪን መከራከሪያ ነጥብ ውድቅ አድርጎና የቀድሞውን ውሳኔ በመሻር መሬቱ ለክፍሉ ቀበሌ የመሬት አስተዳደር ሊያስረክቡ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ

ጉዳዩን መርምሮ የአመልካች የፍርድ መቃወሚያ የቀረበው ተጠሪ የመሬት ይዞታውን ከተረከቡ በኂላ በመሆኑ መቃወሚያው ዋናው ፍርድ ከተፈጸመ በኃላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 መሰረት የሚቀርብበትና የሚስተናገድበት አግባብ የለም በማለት የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሳኔ ሽሮታል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡የሰበር አቤቱታ የቀረበለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካች የፍርድ መቃወሚያውን ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት ማቅረቡን፣ የአከራካሪው መሬት ይዞታ ስም በተጠሪ ሳይመዘገብ ርክክቡ ተፈፅሟል የሚባልበት አግባብ ያለመኖሩን ዘርዝሮ መቃወሚያው በሕግ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የቀረበ ሁኖ እያለ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ውድቅ መደረጉ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም፡- በሚያከራክረው የገጠር መሬት ይዞታ ላይ አመልካች ያቀረበው የፍርድ መቃወሚያ ስርዓቱን ጠብቆ የቀረበ አይደለም ተብሎ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ተጠሪ በልጃቸው ይዞታ ስር የነበረውን መሬት ልጃቸው ሕጋዊ መብት ሳይኖራቸው ይዘው እንደሚገኙ ገልፀው ባቀረቡት ክስ ከልጃቸው ጋር ተከራክረው መሬቱን እንዲለቀቅላቸው በተወሰነው መሰረት መሬቱን የተረከቡ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡አመልካች አሁን አጥብቆ የሚከራከረው የክርክሩ ምክንያት የሆነው የገጠር የእርሻ መሬት እንደመሆኑ መጠን አመልካች መሬቱን ተረክበዋል ሊባል የሚችለው የይዞታ ማረጋገጫ ሲያገኙ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡ተጠሪ በበኩላቸው ይህ አይነት አሰራር በተለያዩ የአስተዳደር አሰራሮች ሊዘገይ የሚችል በመሆኑ ተጠሪ መሬቱን አልተረከቡም ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመሰረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት የተዘረጋው ሥርዓት አስቀድሞ በተሰጠው ውሣኔ መብቱ የሚነካበት ወገን ባለበት ውሣኔ እንዳልተሰጠበት ተቆጥሮ እንደገና ክርክር የሚጀምርበት ሥርዓት ነው፡፡ መሰረታዊ አላማም ቅን ልቦና ያላቸው ወገኖች በመሰረታዊ ሕግ የተጠበቀላቸው መብት ባለመከራከር ዋጋ እንዳያጣ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ድንጋጌው በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ወገን አቤቱታውን ለማቅረብ መብት እንደአለው በመለኪያነት ያስቀመጠ ሲሆን ይኼው የድንጋጌ ይዘትም የተቃውሞ አቤቱታውን ለማቅረብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 39፣40 እና 41 አግባብ የክርክሩ ተካፋይ ሊሆን ይገባው የነበረውንና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33 አግባብ ደግሞ በጉዳዩ መብትና ጥቅም ያለው ወገን መሆን እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ የተቀመጠው የሕጉ ሐሳብ በተቃውሞ አቤቱታ አቀራረብ ስርዓት መብቱ ሊከበርለት የሚገባው ወገን ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ክፍል አንፃር ክርክር ባስነሳው ንብረት ላይ ያለው የመሚገት መብት የተጠበቀ ነው ለማለት እንጂ በማንኛውም ጉዳይ ቢሆን በአንድ ጉዳይ አፈፃጸሙ ማለቁ የተረጋገጠበት ወገን አፈጻፀሙ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ባገኘው ጊዜ

ከአፈፃጸሙ መዝገብ መዘጋት በኃላ የፍርድ መቃወሚያ በማቅረብ የመሚገት መብት አለው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 ሰፊና የፍትሃ ብሔር ስነ ስርዓት ሕጉ አላማ ውጤት አልባ የሚያደርግ ትርጉም ለመስጠት ተፈልጎ አይደለም፡፡ይህ ዓይነት አተረጓጎም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግን መሠረታዊ ዓላማ የተከተለ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሚያግኝበት አግባብ የለም፡፡አፈጻጸም የፍርድ ቤት ውሳኔ ትርጉም የሚያገኝበት ሂደት በመሆኑ አፈጸጸሙ በሕጉ አግባብ ከተጠናቀቀ በኂላ ይህንኑ ሂደት ወደ ኃላ መመለስ የአፈጻጸም ስርዓት የሚፈቅደው አይደለም፡፡በመሆኑም አንድ ፍርድ ከተፈፀመ በኃላ የፍርድ መቃወሚያ ማቅረብ የማይቻል መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ በቀላሉ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡አከራካሪው ጉዳይ አንድ ፍርድ ተፈፀመ የሚባለው መቼ ነው? የሚለውን ጥያቄ ነው፡፡ይህ ጥያቄ እንደ ለክርክሩ መነሻ እንደሆነው ንብረት ልዩ ባህርይ ታይቶ ሊመለስ የሚችል ነው፡፡ከዚህ አንፃር ጉዳዩን ስንመለሰው የፍርድ ባለመብት ፍርዱ ተፈጽሞለታል የሚባለው ጥሬ ገንዘብ ከሆነ ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ ሲመለስለት፣የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሆነ ደግሞ ንብረቶቹን ተረክቦ በይዞታው ላይ ሲያደርግ መሆኑ ይታመናል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ መሬቱን ከልጃቸው መረከባቸውን የበታች ፍርድ ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ይሁን እንጂ ተጠሪ በመሬቱ ላይ ያላቸው መብት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስትም ሆነ በክልሉ ህገ መንግስት እንዲሁም የገጠር የእርሻ መሬት አስተዳደርን አጠቃቀምን በተመለከተ በፌዴራሉ መንግስት በወጣው አዋጅ ቁጥር 456/1997 እንዲሁም ይህንኑ አዋጅ ተከትሎ በወጣው የክልሉ አዋጅ ቁጥር 133/1998 እና ደንብ ቁጥር 51/1999 አግባብ የይዞታ መብት ሲሆን ነው፡፡በመሆኑም መሬቱ ላይ ያላቸው የባለይዞታ መብት የሚረጋገጠው መሬቱን እንዲያስተዳደር በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል በሕጉ አግባብ ሲያስረክባቸውና በሕጉ በተዘረጋው ስርዓት መሰረት የባለይዞታ መብት ማረጋገጫ ደብተር ሲያገኙ ነው፡፡ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው ተጠሪ መሬቱን ከልጃቸው ተረክበዋል ከመባሉ ውጪ ርክክቡ መሬቱን የሚያስተዳድረው የመንግስት አካል እውቅና ሰጥቶ የተፈፀመ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ተጠሪ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲሰጣቸው በተገቢው ጊዜ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ጥያቄ አቅርበው በአስተዳዳራዊ አሰራር ችግር የዘገዬ ስለመሆኑም የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡ስለሆነም ተጠሪ በሕጉ የተጠበቀላቸውን የባለይዞታነት መብት ተረክበዋል ሊባል የሚችለው ይዞታውን ከግለሰብ እንዲረከቡ በመደረጉ ብቻ ሳይሆን ሕጋዊ ማረጋገጫ ሊሆን የሚችል ማስረጃ ሲያገኙ ነው፡፡የገጠር መሬትን በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮችን መሰረት አድርጎ የሚቀርብ የፍርድ መቃወሚያ አቤቱታ አቀራረብ፤ ፍርድ ከተፈጸመ በኃላ የቀረበ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 ድንጋጌ መለኪያ ሕገ መንግስቱን መሰረት አድርገው ጉዳዩን ለመግዛት የወጡ ሕጎችን፣ደንቦችንና መመሪያዎችን በሚያሳካ መልኩ ካልተተረጎመና ተግባር ላይ ካልዋለ ግለሰቦች ተገቢ ያልሆነ ክርክር በማቅረብ አንዱ ላንዱ ይዞታውን አስረክቤአለሁ በማለቱ ብቻ የገጠር መሬትን የሚያስተዳድረው የመንግስት አካል የሕዝብና የመንግስት ጥቅም ለማስከበር እንዳይችል የሚያደርግ ውጤትን የሚያስከትል በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የማይገባ ሁኖአግኝተናል፡፡ሲጠቃለልም አመልካች የፍርድ መቃወሚያውን ያቀረበው ፍርዱ ሙሉ በሙሉ ተፈጽሟል ሊባል በማይችልበት ሁኔታ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. በምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 52990 የካቲት 07 ቀን 2005 ዓ/ም ተሰጥቶ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 35349 ግንቦት 16 ቀን 2005 ዓ/ም ፣የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 32961 መጋቢት 18 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/348(1) መሰረት ሽረናል፡፡
2. በገጠር የእርሻ መሬት ላይ በተሰጠ ፍርድ የፍርድ መቃወሚያ ሲቀርብ ፍርዱ ተፈጽሟል ሊባል የሚችለው የፍርድ ባለመብቱ በይዞታው ላይ ሕጋዊ ማረጋገጫ ሲያገኝ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች በሚያከራክረው መሬት ላይ የፍርድ መቃወሚያው ያቀረበው ፍርዱ ከመፈጸሙ በፊት መሆኑን አውቆ በፍሬ ጉዳዩ ላይ የይልማና ዴንሳ ወረዳ ፍርድ ቤት ታህሳስ 11 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በሕግም ሆነ በፍሬ ነገሩ ተገቢ መሆን ያለመሆኑን መርምሮ ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን ለምዕራብ ጎጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

*መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡*

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**መ/ተ**

የሰ/መ/ቁ. 96495

ቀን 05/06/2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-አልማው ወሌ**

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ኢትዮ-ጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት - ነገረ ፈጅ ወይንሸት እንድሪስ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኃይሌ ብሩ - ተወካይ ዓመተ ኃይሌ ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 46873 በ30/08/2005 ዓ/ም የተሰጠው ፍርድ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በአመልካች ፈቃድ ተመስረተው ተጠሪ የገነቡት ቤት የሚኖረው ህጋዊ ውጤት የተመለከተ ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ ሲሆኑ የአሁኑ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ባጭሩ፡- በአመልካች ተቀጥረው ሲሰሩ በ1967 ዓ/ም አንድ ክፍል መኖሪያ ቤት እንደተሰጣቸው በሒደት የቤተሰባቸው አባላት ቁጥር በመጨመሩ በራሳቸው ወጪ ተጨማሪ ክፍል 2 መኝታ ፤ ሳሎን ፤ 2 ክፍል ኩሽና መስራታቸው በሰሩት ቤትም ከ1975 ዓ/ም ጀምሮ ለ 30 ዓመታት ሲጠቀሙ እንደነበር አሁን ግን አመልካች ቤቱን እንዲለቁ እያስገዳዳቸው በመሆኑ ድርጊቱ እንዲቆም ወይም ቤቱን የተሰራበት አርባ አምስት ሺህ ብር እንዲከፍላቸው ጠይቋል፡

የአሁኑ አመልካች በሰጠው መልስ ተጠሪ ቤቱን ያገኙት በስራ ምክንያት ነው ፤ ቤቱ የተገነባው ለህዝብ ጥቅም ሲባል የተቋቋመ በመሆኑ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በተቋቋመ ንብረት ላይ የይዞታ መብት ማቋቋም ስለማይቻል ክስ ማቅረብ አይችሉም፡፡ ቤቱም የገነቡት አመልካች እየተቃወመ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ማስረጃ እና ክርክር ከመረመረ በኃላ በአሰሪና ሰራተኞች ማህበር በተፈረመው የህብረት ስምምት መሰረት የተቋሙ ሰራተኛ በጡረታ ወይም በሌላ ምክንያት ከስራ ገበታው ሲገለል የተረከበው ቤት በነበረበት ሁኔታ ሊያስረክብ እንደሚያስገደድ በመጥቀስ ተጠሪ ቤቱን ለቀው ያስረክቡ፡፡ ቤቱን ለመስራት ያወጡት ወጪም አመልካች የመክፈል ግዴታ የለበትም በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታቸው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ቤቱን

የሰሩት በ1975 ዓ/ም ሲሆን የህብረት ስምምነቱ የተቋቋመው በ1989 ዓ/ም ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ቤቱን ሲሰሩ ምንም ተቃውሞ አላቀረቡም፡፡ ተጠሪ በተጨማሪነት ሁለት ክፍል ቤቶች መኝታ ቤት ሳሎን ኩሽና በቤት ቁጥር 420 ላይ ሲገነቡ አመልካች ምንም ያቀረበው መቃወሚያ የሌለ መሆኑን ፍርድ ቤቱ መገንዘቡን ፤ በዚሁም የተነሳ ተጠሪ ለእነዚህ ተጨማሪ መኖሪያ ቤቶች ባለሁበት ሆነዋል፡፡ አመልካች ለተጠሪ ግምቱን ሰጥቶ ማሰናበት አሊያም ደግሞ ተጠሪ ቤቱን አፍርሰው እንዲሄዱ መብት አላቸው በማለት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔውን ሽረዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 337 ተሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ግራ ቀኙ ከዚህ ችሎት የጽሁፍ ክርክር አድርገዋል፡፡ አመልካች በዋናነት የሚከራከረው አመልካች ድርጅት ለህዝብ ጥቅም የተቋቋመ በመሆኑ በነዚህ ይዞታዎች ላይ ግዙፍ መብት በማቋቋም ባለመብት ለመሆን እንደማይቻል በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1446፣1454 እና 1455 በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ የስር ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔዎች እንዲሻሩ የሚያመለክት ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው የሰጡት መልስ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በአመልካች ፈቃድ የገነቡት መሆኑን በድርጅቱ ለረጅም ዓመታት ሲያገለግሉ ቆይተው በጡረታ ተገለው እየኖርበት እንደነበር የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታው የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረነውም አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለው ለመኖሪያነት ተፈቅዶ በነበረው ይዞታ ላይ ተጨማሪ ቤቶች በመሰራታቸው ተጠሪ በቤቱ ላይ ያለቸው ህጋዊ መብትና ጥቅም በአመልካች ክርክር እንደተነሳው ለህዝብ ጥቅም በተቋቋመ ድርጅት መብት ማቋቋም አይችልም የሚለው የፍ/ህ/ቁ. 1454 እና 1455 መሰረታዊ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ከአጠቃላይ የህጉ ዓላማና መንፈስ ተገናዝቦ መታየት አለበት፡፡ በስር ፍርድ ቤት የክርክር ሂደት በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠው ነገር ቢኖር ተጠሪ የአመልካች ሠራተኛ በነበሩበት ጊዜ ለመኖሪያነት በተሰጣቸው ይዞታ ላይ ተጨማሪ ክፍሎች ሲገነቡ በአመልካች በኩል የቀረበ ተቃውሞ ስለመኖሩ አልተረጋገጠም፡፡ ተጠሪ ቤቱን ሰሩት የተባለው እና በአመልካች ድርጅት እና ሠራተኞች የተፈረመው የህብረት ስምምነት ቤቱ ከተገነባ በኃላ ስለመሆኑ በአመልካች የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡ ተጠሪ በሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት መልስ ቤቱን በአመልካች የጽሁፍ ፈቃድ የተገነባ ስለመሆኑ የገለጹ ሲሆን አመልካች ለተጠሪ ፈቃድ እንዳልተሰጠ የመልስ መልሱ ላይ አላሰተባበለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤት ላይ ጡረታ ከወጡ በኃላም እየኖሩበት እንደሆነ አልተካደም፡፡

አመልካች ከስር ፍርድ ቤት አንስቶ አጽንኦት በመስጠት የሚከራከረው ለህዝብ ጥቅም በተቋቋመ የመንግስት ይዞታ ላይ መብት ማቋቋም አይቻልም በሚል ነው፡፡ በእርግጥ ለህዝብ በተቋቋም መንግስት ይዞታ ላይ መብት ማቋቋም እንደማይቻል በፍ/ህ/ቁ. 1454 እና 1455 በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይሁንና የዚህ ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት ፣ ዓላማና ግብ መታየት ያለበት መብቱን ባቋቋመ ግለሰብ እና መንግስት የነበረው ህጋዊ ግንኙነት መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች እና ተጠሪ የስራ ውል ግንኙነት የነበራቸው ስለመሆኑ የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፤ አመልካች ለተጠሪ መኖሪያ ቤት የሰጣቸው መሆኑን ፤ በሂደት ቤተሰብ መስርተው የቤተሰብ አባላት ቁጥር በመጨመሩ ምክንያት ተጨማሪ ቤት እንዲገነቡ በአመልካች በጽሁፍ ፈቃድ መሰጠቱ በአመልካች አልተካደም፡፡ አመልካች እና ተጠሪ ህጋዊ ግንኙነት የነበራቸው በመሆኑ ተጠሪ

ቤቱን የገነቡት ከአመልካች ፈቃድና እውቅና ውጭ ነው ለማለት አልተቻለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ህጋዊ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች የተቋቋመው መብትና ግዴታ ምንም ህጋዊ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች እንደተገነባ ጥቅም መታየት የለበትም፡፡ ከላይ የተመለከትነው የህግ ድንጋጌም ህጋዊ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች የተገነባ ጥቅም /መብት/ ካለ የህግ ጥበቃ የሚሰጠው መብት ማቋቋም እንደማይችሉ የሚያስገነዝበን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል ግንኙነት መሰረት በማድረግ በአመልካች ፈቃድ ተጠሪ የግል ሀብታቸው በማውጣት የገነቡትን ቤት አፍርሰው ለመውሰድ አልያም የቤቱን ግምት የመጠየቅ መብት ሊነፈጉ አይገባም፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ተጠሪ አመልካች ሳይቃወም ለገነቧቸው ተጨማሪ ቤቶች ያወጡት ወጪ ብር 45,000 (አርባ አምስት ሺህ) ይክፈሉ ወይም ደግሞ ቤቱን አፍርሰው ይውሰዱ በማለት መወሰኑ እና በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፍትሐብሄር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔውን ማጽናቱ ህጉን በአግባቡ ተግባራዊ አድርገዋል ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 127167 በ12/11/2005 ዓ/ም የፌዴራል የመጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 46873 በ30/08/2005 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ በመሻር የሰጠው ፍርድ ፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/መ/ቁ. 93048 በ22/02/2006 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
2. ተጠሪ አመልከች ሳይቃወም ለገነቧቸው ተጨማሪ ቤቶች ያወጡትን ወጪ ብር አርባ አምስት ሺህ /45,000.00/ ይከፈላቸው ወይም ቤቱን አፍርሰው እንዲሄዱ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::**

**ሃ/ወ**

የሰ/መ/ቁ.97132

መጋቢት 30 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- አቶ መሀመድ ከማል ሀምዛ ቀረቡ

ተጠሪዎች ፡-1ኛ የከሚሴ ከተማ ወረዳ ፖሊስ
2ኛ የከሚሴ ከተማ ወረዳ ሚሊሻ ጽ/ቤት } ተወካይ አይኔ አዲስ አሰጋኸኝ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ በኢግዚቢት ተይዞ ነበር በተባለው እስታር ማክሮቭ ሽጉጥ አመላለስ ጋር በተያያዘ የቀረበ ሲሆን በሥር የደ/ሥ/ፊ/ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ ውድቅ የተደረገባቸው በመሆኑ በሰበር ተጣርቶ እንዲወሰን የቀረበ ነው፡፡ አመልካች በሥር ወረዳ ፍርድ ቤት በአሁኑ ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘት፡- ቁጥሩ 635 የሆነው እስታር ማክሮቭ ሽጉጥ ከ8 መሰል ጥይቶች ጋር ህገ ወጥ መሣሪያ ይዘሃል ተብሎ በፖሊስ ተጠይቀው መሣሪያውም በኢግዚቢት ተይዞ ምርመራ ከተጠናቀቀ በኋላ ሽጉጡ ፈቃድ ያለው የግላቸው መሆኑ ቢከራከሩም የሥር ፍርድ ቤት ሳይቀበል ጥፋተኛ ያላቸው መሆኑን፤ ለአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ በነፃ እንደተለቀቁ፣ በኢግዚቢት የተያዘው ሽጉጥ በፍትሐብሄር መጠየቅ እንደሚችሉ ሰበር ሰሚ ችሎቱ መብታቸው የጠበቀላቸው በመሆኑ፣ በኢግዚቪት ተያዘ የተባለውን ሽጉጥ ላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ አለመስጠቱን፤ ተጠሪዎች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊዎች በመሆናቸው ሽጉጡ ከመሰል ጥይቱ በዓይነት እንዲመልሱ፤ በዓይነት ማስረከብ የማይችሉ ከሆነም በድምር 33,400 ብር እንዲከፈሉ እንዲወሰንላቸው የሚጠይቅ ነዉ፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት በሰጡት መልስ ከአመልካች የተያዘው ሽጉጥ ቁጥር 635 ሳይሆን ቁጥር 165231 መሆኑን፤ ሽጉጥ የተያዘው መሃመድ ከማል የተባለው ግለሰብ ሲያስፈራሩበት የነበረ ስለመሆኑ በመግለጽ ከክሱ በነፃ እንዲሰናበቱ ማመልከታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም የግራቀኙ የቃል ክርክር እንዲሁም የተጠሪዎች የሰው ምስክሮች ካደመጠና የአመልካች የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ፖሊስ ከአመልካች የያዘው ሽጉጥ ቁጥሩ 635 የሆነ ማክሮቭ ሽጉጥ ሳይሆን ፈቃድ የሌለው ማክሮቭ ሽጉጥ ቁጥር 165231 ከሁለት መሰል ጥይቶች ጋር መሆኑን በወቅቱ ጉዳዩን ያጣራው መርማሪ ፖሊስ እና ሽጉጡን በኤግዚቢት ገቢ ያደረገው

የከሚሴ ከተማ ፖሊስ ጽ/ቤት የግምጃ ቤት ሠራተኛ አስረድቷል በማለት የአመልካች ክስ ውድቅ አድርጐታል፡፡ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ እና ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት ቅሬታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ የሰበር ቅሬታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመደረጉ ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር አድርጓል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው በመሰረታዊነት ያነሳቸው ዋና ዋና ነጥቦች፡- ድርጊቱ ተፈጸመ በተባለበት ቀን ይዘውት የነበረው ሽጉጥ ፈቃድ ያለው ነው፡፡ የንምራ ቁጥር 635 የነበረው በመፋቅ ሌላ ተለጣፊ ቁጥር ተደርጎበት በፎርጅድ ቁጥር ሌላ ባለሥልጣን የታጠቀው ስለመሆኑ፤ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ሽጉጥ ንምራ ቁጥሩ 635 ነው ወይስ 165231 የሚለው በፎረንሲክ የባለሙያ/expert/ ምርመራ ያልተደረገበት ስለመሆኑ፤ የሰበር ሰሚ ችሎት ንብረት የመጠየቅ መብታቸው መጠበቁ በመሆኑም በባለሙያ ምርመራ ተደርጎ ቁጥሩ መረጋገጥ እንደሚገባ ማመልከታቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ደግሞ  የተያዘው ሽጉጥ 635 ሳይሆን 165231 መሆኑን የሰው ምስክር በቂ እንደሆነ የፎረሲንክ ምርመራ አግባብነት እንደሌለው የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና መጠየቁን የሚያመለክት ነው፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም የሰበር አቤቱታቸው የሚያጠናክር ነው፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በአመልካች የቀረበው የጦር መሣሪያ ፈቃድ የመሣሪያው ዓይነት ስታር ሽጉጥ የወግ ቁጥር 635 መሆኑን የሚያመለክት፤ እንዲሁም የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ 24840 ህዳር 28 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ከአመልካች ተያዘ የተባለው ሽጉጥ የንምራ ቁጥር 165231 ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አለመቅረቡን፤ አመልካች የንምራ ቁጥር 635 የሆነ ማክሮቭ ሽጉጥ ፈቃድ እንዳለው ማስረጃ በማቅረባቸው ምክንያት ከወንጀል ድርጊቱ በነፃ እንዲሰናበቱ በኤግዝቢትነት የተወሰደባቸው ሽጉጥ በፍትሐብሔር ክስ አቅርበው የመጠየቅ መብታቸው መጠበቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ፤ ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

አመልካች ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ አጥብቀው የሚከራከሩት በኢግዚቢት ተያዘ የተባለው ሽጉጥ ንምራ ቁጥር 635 እንጂ 165231 አይደለም፡፡ የንምራ ቁጥር 165231 የተባለው ፎርጅድ ቁጥር ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሽጉጥ የንምራ ቁጥር 635 ይሁን 165231 በባለሙያ /expert/ ምርመራ ተደርጎበት ውጤቱ አልቀረበም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ በአንፃሩ ከአመልካች የተያዘው ሽጉጥ ንምራ ቁጥር 165231 ስለመሆኑ በሰው ምስክሮች ተረጋግጧል የፎረንሲክ ምርመራ ማድረግ አስፈላጊ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለክርክሩ መነሻ የሆነው ንምራ ቁጥር 165231 አመልካች ይዘው ስለመገኘታቸው አልተረጋገጠም በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች የጥፋተኝነት ውሳኔ ሽሯል፡፡ በአንፃሩ አመልካች ፈቃድ ያለው ንምራ ቁጥር 635 የሆነ ማክሮቭ ሽጉጥ እንደነበራቸው በውሳኔው አስፍሯል፡፡

የሥር ወረዳ እና ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከቱት ፍርድ ቤቶች አመልካች ይዘውት ተገኙ የተባለው ሽጉጥ ንምራ ቁጥር 165231 ስለመሆኑ በሰው ምስክር ተረጋግጧል የሚል ነው፡፡ ይሁንና ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት መገንዘብ እንደተቻለው ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ሽጉጥ ከተያዘ በኋላ በወ.መ.ሥ.ሕ.ቁ 33/4/ እና 97 መሰረት የተመዘገበ እና ከአመልካች የተያዘ ስለመሆኑም በሰነድ የተደገፈ ክርክር አልቀረበም፡፡ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቁጥር 635 እና 165231 በተለምዷዊ የዓይን ምልከታ መለየት የሚቻል ስለመሆኑ በሕጉ አግባብ የተረጋገጠ

ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች ንምራ ቁጥሩ ተፍቆ ፎርጅድ ቁጥር ተለጥፎበታል በማለት ይከራከራሉ፡፡ ይህ ጉዳይ በተጠሪዎች የተካደ ቢሆንም በኤግዝቢት ተያዘ በተባለው ሽጉጥ ንምራ ቁጥር 165231 ተብሎ የተመዘገበው ቁጥር በእርግጥ ኦርጅናል /ዋና/ ቁጥር ስለመሆኑ በልዩ ባለሙያ የተረጋገጠ ጉዳይ አይደለም፡፡ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ሽጉጥ ላይ የተፃፈው ቁጥር ኦርጂናል /ዋና/ መሆን ያለመሆን ደግሞ በቀላል የዓይን እይታ/ምልከታ/ የሚረጋገጥ ሳይሆን በሙያ እውቀት ባላቸው የፎርንሲክ ምርመራ ባለሙያዎች ሳይንሳዊ በሆነ አግባብ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የሥር ፍርድ ቤቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሽጉጥ ላይ የተፃፈው ቁጥር ሽጉጡ በሰራው ኩባንያ /ተቋም/ የተሰጠው ንምራ ቁጥር መሆን ያለመሆኑን በባለሙያ /expert/ ሳይረጋገጥ የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ግራቀኙ እያከራከረ ያለው ሽጉጥ ላይ የተፃፈው ንምራ ቁጥር 165231 በእርግጥ በእናት ኩባንያው የተሰጠው ቁጥር ነው ወይስ በጊዜ ሂደት የተተካ ቁጥር ነው? በአከራካሪው ሽጉጥ የተፃፈው ንምራ ቁጥር 635 ነው ወይስ 165231 ነው? የሚሉ መሰረታዊ ነጥቦች አግባብነት ካለው አካል በሚቀርበው ሙያዊ አስተያየት /expert opinion/ መሰረት ተደርጎ ሊወሰን የሚገባው በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔዎች ተሽሮ ጉዳዩ ደግሞ ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ሥር ፍ/ቤት ሊመለስ የሚገባው ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

1. በአብከመ የኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር የደዋ ጨፋ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 02932/05 በ04/10/2005 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤ የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳዳር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0101458 በ26/11/2005 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ፤ የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጠ/ፍ/የሰ/ይ/መ/ቁ 03-06689 በ 27/03/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የደዋ ጨፋ ወረዳ ፍርድ ቤት በፍርድ ይዘቱ እንደተገለጸው ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሽጉጥ ንምራ ቁጥር 635 ነው ወይስ 165231? ንምራ ቁጥሩ 165231 የተባለው ሽጉጥ ኦርጂናል ቁጥር ነው ወይስ በሂደት የተተካ ቁጥር ነው? የሚሉና ተዛማጅ ነጥቦች በፎረንሲክ ባለሙያዎች ተመርምሮ ውጤቱ ከታወቀ በኋላ ሕጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ይፃፍ፡፡
3. የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘጋ፡፡ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ት/ጌ**

# ንግድ

የሰ/መ/ቁ. 94278

ህዳር 11 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- አቶ ሐሰን መሐመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ማጂ አግሮ ፎረስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ ዶ/ር አሸናፊ ማሞ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

**ፍ ር ድ**

በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በዚህ መዝገብ አቤቱታ ያቀረቡት በተከሳሽነት ተሰይመው የነበሩት የማጂ አግሮ ፎረስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ስራ አስኪያጅ በማህበሩ የመመስረቻ ፅሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ሊወጡ ባለመቻላቸው ምክንያት የማህበሩ ሕልውና አደጋ ላይ የወደቀ መሆኑን በምክንያትነት በመጥቀስ በንግድ ሕግ ቁጥር 218 እና 542 መሰረት ማህበሩ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1835 መሰረት በአስር አመት ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት ክሱ  የቀረበለት በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት የማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የፀናው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡
ከመዝገቡ ግልባጭ መገንዘብ እንደተቻለው ክሱ የቀረበለት የማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከተከሳሽ የቀረበለትን የይርጋ መቃወሚያ በመቀበል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር. 1835 ድንጋጌን ጠቅሶ ክሱ በአስር ዓመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን የሰጠው የማህበሩ የመመስረቻ ፅሁፍ ከተፈረመበት ከ19/06/1991 ዓ.ም ጀምሮ ማህበሩ እንዲፈርስ ክስ እስከቀረበበት 03/10/2005 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር አስር ዓመት አልፎታል በማለት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች ማህበሩ የተመሰረተበትን ጊዜ መነሻ አድርጉ በማስላት አመልካች መስራች ሆነው አቋቁመውት ሲንቀሳቀስ የነበረው ማህበር ሒሳብ በኦዲት ተመርምሮ ድርሻቸው እንዲታወቅ እና ማህበሩ እንዲፈርስ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የመወሰናቸውን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርቡ በመደረጉ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው ነጥቦች፡-

1. ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ትዕዛዝ የፀናው ብይን ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. በከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ ተገቢውን የክስ አቀራረብ ስርዓት ተከትሎ የቀረበ አይደለም በማለት ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ያቀረቡት ክርክር ጉዳዩ አሁን ባለበት ደረጃ በዚህ ሰበር ችሎት ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ አለ ወይስ የለም? የሚሉ መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ጭብጦች አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህ መሰረት የመጀመሪያው ነጥብ በተመለከተ አመልካች ለማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘት የማህበሩ ስራ አስኪያጅ በማህበሩ የመመስረቻ ፁሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ሊወጡ ባለመቻላቸው ምክንያት የማህበሩ ሕልውና በአደጋ ላይ የወደቀ በመሆኑ ሂሳብ ተጣርቶ ማህበሩ እንዲፈርስ ይወሰንልኝ የሚል መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ እና የግራ ቀኙ የክርክር ይዘት ያመለክታል፡፡ አመልካች የማህበሩ መስራች አባል መሆናቸው እና በ1995 ዓ.ም ከማህበሩ የስራ አስኪያጅነት ስልጣን ተነስተዋል ከመባሉ በቀር ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ የማህበሩ አባልነታቸው ያልተቋረጠ ስለመሆኑ በተጠሪው አልተካደም፡፡ የማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክሱ በአስር ዓመት ይርጋ ይታገዳል ለማለት የቻለውም ጊዜውን የማህበሩ የመመስረቻ ፅሁፍ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ በመቁጠር ስለመሆኑ የብይኑ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በመሰረቱ አንድ የንግድ ማህበር በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፈርስ የሚደረገው ጥያቄ ስለቀረበ ብቻ ሳይሆን ማህበሩን ለማፍረስ የሚያስችሉ ትክክለኛ ምክንያቶች ስለመኖራቸው በማስረጃ ተረጋግጦ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በንግድ ሕጉ ዕውቅና የተሰጣቸው የንግድ ማህበራት ከአባላቱ በአንዱ የይፍረስልኝ ጥያቄ ሊቀርብባቸው የሚችል ስለመሆኑ በንግድ ሕግ ቁጥር. 218(1) ስር ተደንግጐ የሚገኝ ሲሆን የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበርን በተመለከተ በንግድ ሕግ ቁጥር 542(1) ስር የተመለከተው ድንጋጌም ተመሳሳይ ይዘት ያለው ነው፡፡ እንደሚታወቀው የንግድ ማህበር ይፍረስልኝ ጥያቄ በውል ከተቋቋመ የማህበርተኝነት መብት የሚመነጭ እና በማህበሩ እንቅስቃሴ ሂደት የሚፈጠሩ የተለያዩ ችግሮችን መሰረት አድርጐ የማህበሩ ህልውና እስካለ ድረስ በማንኛውም ጊዜ ሊቀርብ የሚችል ነው ከሚባል በቀር በታወቀ የይርጋ ጊዜ የሚታገድ ስለመሆኑ የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች አያመለክቱም፡፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለብይኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር. 1835 ድንጋጌን በምክንያትነት የጠቀሰው አለቦታው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በንግድ ሕጉ የተደነገገ የተለየ የይርጋ ዘመን በሌለ ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር. 1845 በተመለከተው ጠቅላላ የይርጋ ጊዜ ይታገዳል ሊባል ይችል የነበረውም የይፍረስልኝ ጥያቄው የቀረበው ተለይቶ በታወቀ ቀን የተፈጠረ ክስተትን ጠቅሶ ወይም መሰረት አድርጐ ቢሆን ኖሮ እና ክሱ የቀረበው ክስተቱ ከተፈጠረ አስር ዓመት ካለፈው በኋላ ቢሆን ኖሮ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክሱን ያቀረቡት በአንድ ተለይቶ በታወቀ ጊዜ ወይም ቀን የተፈጠረ ክስተትን መሰረት በማድረግ ሳይሆን ይልቁንም በማህበሩ እንቅስቃሴ ሂደት በተለያየ ጊዜ ተከስተዋል የተባሉ የተለያዩ ችግሮችን በምክንያትነት በመጥቀስ በመሆኑ ክስ የማቅረብ መብታቸው በይርጋ ይታገዳል የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የማህበሩ የመመስረቻ ፅሁፍ የተፈረመበት ቀንም በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን በማህበሩ እንቅስቃሴ ሂደት በተለያየ ጊዜ የተፈጠሩ የተለያዩ ችግሮችን መሰረት አድርጐ ለሚነሳ የማህበር ይፍረስልኝ ጥያቄ ለይርጋው አቆጣጠር የመነሻ ቀን ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር. 1835 ድንጋጌን አለቦታው በመጥቀስ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት

ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በትዕዛዝ የፀናው ብይን ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛው ነጥብ በተመለከተ ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ላይ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ ተገቢውን የክስ አቀራረብ ስርዓት ተከትሎ የቀረበ ባለመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው አይገባም በማለት የተከራከሩ ሲሆን አመልካች ክሱን ያቀረቡት በራሳቸው ስም ብቻ ነው ወይስ በሌሎች ሰዎች ስም ጭምር ነው? እንዲሁም ክሱን ያቀረቡት በማህበሩ ላይ ነው ወይም በማህበሩ ስራ አስኪያጅ ላይ ነው? በሚሉት ነጥቦች ላይ ግራ ቀኙ የአቋም ልዩነት ያላቸው መሆኑን በሰበር ደረጃ ከተለዋወጡት የፅሁፍ ክርክር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ጉዳዩ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በብይን የተዘጋው በይርጋ ምክንያት በመሆኑ በሰበር ክርክራቸው ላይ ግራ ቀኙ የተለያዩባቸውን ጨምሮ ቀሪዎቹ የክርክሩ ነጥቦች በስር ፍርድ ቤት ተጣርተው ውሳኔ የሚያርፍባቸው ከሚሆን በቀር ጉዳዩ አሁን ባለበት ደረጃ በዚህ ሰበር ችሎት ሊስተናገዱ የሚችሉበት የህግ አግባብ አይኖርም፡፡

ሲጠቃለል ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት በማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 19372 በ20/12/2005 ዓ.ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 01174 በ15/01/2006 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የማህበር ይፍረስልኝ ክስ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. በግራ ቀኙ የቀረበውን ቀሪ ክርክር መርምሮ እና አጣርቶ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር. 341(1) መሰረት ለማጂ አካባቢ ከፍተኛው ፍርድ ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ በዚህ ውሳኔ መሰረት ተገቢውን መፈፀም ያስችለው ዘንድ በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ለማጂ አካባቢ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፤ እንዲያውቀው ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይላክ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

**የማይበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት**

የሰ/መ/ቁ. 95069

ህዳር 23 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- 1. ሴፍሜት አግሪ ቢዝነስ ኃ.የተ.የግ.ማህበር
2. አቶ ወንድምአንተነህ መሸሻ } ጠበቃ ውቤ አለነ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ብሪቱ ሱኬሱ ጠበቃ ወንድአወክ አየለ ቀረቡ

**መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የገንዘብ ይመለስልኝ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የጀመረው የአሁኗ ተጠሪ የአሁኑ አመልካቾችን እንደቅደምተከተላቸው 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች፣ ወ/ሮ ትግስት ድረስ የተባሉትን ግለሰብ ደግሞ 3ኛ ተከሳሽ በማድረግ መጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የተጠሪ የክስ ይዘትም፡- 2ኛው ተከሳሽ 1ኛ ተከሳሽን በአሽሙር ማህበር በመመስረት የጥቁር ድንጋይ ማምረቻ እናቋቁም በማለት ተጠሪዋን ባግባቧቸው መሰረት በሚኖሩበት ከኬኒያ ናይሮቢ ከተማ ሆነው በተለያዩ ጊዜያት ማለትም ነሐሴ 06 ቀን 2001 ዓ.ም 10,000 የአሜሪካ ዶላር፣ ነሐሴ 07 ቀን 2001 ዓ/ም 70,000 የአሜሪካ ዶላር፣ ነሐሴ 11 ቀን 2001 ዓ.ም ደግሞ 67,000 የአሜሪካ ዶላር በ1ኛ አመልካች ስም ናይሮቢ ከተማ በሚገኘው ዲያመንድ ትረስት ባንክ አማካኝነት ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኘው በአቢሲኒያ ባንክ ቦሌ ቅርንጫፍ በኩል እንደላኩና ለእነዚህ በተለያዩ ጊዜያት ለተላኩት ገንዘቦች ደግሞ በተከታታይ 204 ዶላር፣ 1429 ዶላር፣ 1367 ዶላር ኮሚሽን እንደከፈሉባቸውና በአጠቃለይም 150,000 የአሜሪካን ዶላር ልከው 2ኛው አመልካችም ይህን ገንዘብ መቀበላቸውን በደረሰኝ ያረጋገጡላቸው መሆኑን እንዲሁም እርሳቸው ወደ አዲስ አበባ በመጡበት ወቅት የአሽሙር ማህበሩን ለማቋቋም ተጨማሪ ገንዘብ መስጠት አለብሽ በማለት 2ኛው አመልካች በጠየቋቸው መሰረት ጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ደረሰኝ አማካኝነት ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺህ የኢትዮጵያ ብር) የሰጧቸው መሆኑን፣ ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን 2ኛ አመልካችን ለማግኘት እንደተቸገሩና ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ አግኝተዋቸው ሲጠይቋቸው ገንዘቡን ለሌላ ፕሮጀክት እንዳዋሉት እንደገለፁላቸው፣ እርሳቸውን በደንብ የሚያውቋቸውን የ2ኛ አመልካች ባለቤት የሆኑትን የሥር 3ኛ ተከሳሽ የነበሩትን ግለሰብ ሲጠይቋቸውም "ገንዘብሽን አንከድሽም፤ ጊዜ ስጭንና ከባንክ ተበድረን እንሰጥሻለን" እንዳሏቸውና እርሳቸውም ባዶ እጃቸውን ወደ ኬኒያ እንደተመለሱ እና አመልካቾችም ሆነ የሥር 3ኛ ተከሳሽ ገንዘባቸውን ሊመልሱላቸው እንዳልቻሉ በመዘርዘር አመልካቾች የወሰዱትን 150,000 የአሜሪካ ዶላር ክስ በቀረበበት ከመጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ/ም በነበረው የአንድ ዶላር ምንዛሬ ብር

16.7293 ሂሳብ ብር 2,509,395 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ብር) እንዲሁም የዚህን ገንዘብ የመጨረሻ ክፍያ (67,000 ዶላር) ከተከፈለበት ከነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት እስከ መጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ 9% ወለድ ብር 368,159.20 ተጨምሮበት እንዲከፈላቸው፣ እንዲሁም ብር 800,000.00 (ስምንት መቶ ሺህ የኢትዮጵያ ብር) እና ይህ ገንዘብ ከተወሰደበት ከጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት እስከ መጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ 9% ወለድ ብር 112,636.60 (አንድ መቶ አስራ ሁለት ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ ስድስት ብር ከስልሳ ሳንቲም) እንዲከፈሏቸው ጠቅሰው በአጠቃላይም ከላይ የተዘረዘረውን ገንዘብ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ያለው ብር 3,790,189.82 (ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ዘጠና ሺ አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከሰማኒያ ሁለት ሳንቲም) ክሱ ከቀረበበት ከመጋቢት 27 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ከሚታሰብ ወለድ ጋር በውጭ ምንዛሬ የወሰዱትም በሚከፍሉበት ወቅት በሚኖረው ምንዛሬ ታስቦ እንዲከፍሏቸው፣ የጠበቃ አበል በውላቸው መሰረት፣ ሌሎች ወጪና ኪሳራዎች ደግሞ በሚያቀርቡት ዝርዝር መሰረት እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካቾች ለክሱ በሰጡት መልስም፡- ከሳሿ የክስ ምክንያት የሌላቸው መሆኑን፣ ከሳሿ ገንዘቡን ያዋጡት ለአሽሙር ማህበር መዋጮ በመሆኑ 1ኛ አመልካችን የሚመለከት ክስ ከሚሆን በስተቀር 2ኛ አመልካችን እና የሥር 3ኛ ተከሳሽን በሚመለከት የመክሰስ ጥቅም እንዳላቸው ያለማረጋገጣቸውን፣ ገንዘቡ ገቢ የተደረገውና በ2ኛ አመልካች ወጪ የሆነው በኢትዮጵያ ብር በመሆኑ እርሳቸው ባሉበት የዶላር ምንዛሬ ሊጠይቁ እንደማይገባ፣ ገንዘቡን የላኩት በመዋጮ መልክ በመሆኑ ወለድ ሊታሰብላቸው እንደማይገባ፣ ከሳሽ በአጠቃላይ ያዋጡት ገንዘብ ብር 2,634,089.73 ሁኖ ከዚህ ገንዘብ ውስጥም ብር 139,200.75 ከሳሿ መልሰው የወሰዱ በመሆናቸው ይህ ተቀንሶ የሚቀራቸው ብር 2,494,888.98 መሆኑንና ይህን ገንዘብ ብቻ ለመውሰድ ፈቃደኛ ባለመሆን በመሰረቱት ክስ ወጪና ኪሳራ ሊከፍሉ እንደማይገባ ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የሥር 3ኛ ተከሳሽም የአሁኑ 2ኛ አመልካች ባለቤት ከመሆናቸው ውጪ ለክሱ ኃላፊ የሚሆኑበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን ጠቅሰው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም አመልካቾች ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርጎ ፍሬ ነገሩን በተመለከተም ጉዳዩን መርምሮ ከሳሿ (ተጠሪ) በዶላር የላኩት ገንዘብ 2ኛ ተከሳሽ (የአሁኑ 2ኛ አመልካች) የተቀበሉት በብር ስለሆነ አሁን ባለው የብር ምንዛሬ እንዲከፈላቸው ያቀረቡት ክስ ውድቅ ነው፣ ከሳሿ ገንዘቡን የላኩት በራሳቸው ፈቃድ የአሽሙር ማህበር ለመመስረት አስበው ስለሆነ የወለድ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም፣ ተከሳሾቹ ባቀረቡት ክርክር ከሳሿ ብር 139,200.75 መልሰው ወስደዋል የሚለውም ተቀባይነት የለውም፣ 3ኛዋ ተከሳሽ ለከሳሿ ገንዘብሽን እንመልስልሻለን ከማለት ውጭ በክሱ ተጠያቂ የሚያደርጋቸው ነገር ስላልተገኘ ከክሱ በነፃ ሊሰናበቱ ይገባል፣ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ግን ከከሳሽ የተቀበሉትንና የወሰዱትን ብር 2,634,089.43 ዳኝነት ከፍለው መዝገቡን ካስከፈቱበት ከሚያዝያ 10/2003 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር በአንድነትና በነጠላ ለከሳሽ እንዲከፍሏቸው በማለት ወስኗል፣ እንዲሁም ከሳሿ በ1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ላይ 3ኛዋ ተከሳሽ ደግሞ በከሳሿ ላይ የወጪና ኪሳራ ዝርዝር የማቅረብ መብትም ጠብቋል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ በከፊል በመቃወም ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ይግባኛቸው መሰረታዊ ነጥብም፡- በኬኒያ አገር ናይሮቢ ከተማ ሆነው በዶላር የላኩላቸው ገንዘብ ለእኔ ጥቅም ባላገለገለበት ማለትም ለአሽሙር ማህበሩ በመዋጮ መልክ ባልዋለበትና እቃም ባልተገዛበት በወቅቱ በነበረው የብር ምንዛሬ ብቻ እንዲከፈላቸው ተብሎ መወሰኑ የደረሰባቸውን ጉዳት ያላገናዘበ ነው፤ የሥር ተከሳሾችም ገንዘቡን ከወሰዱበት ጊዜ ጀምሮ ወለድ ሊታሰብልኝ እየተገባ ክሱ ከቀረበበት ከሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ እንዲታሰብ መደረጉ ስህተት ነው፣ የስር 3ኛዋ ተከሳሽም ከሌሎች ተከሳሾች ጋር እኩል ኃላፊነት እንዳላቸው ሊወሰን ሲገባ መታለፉ ያላግባብ ነው የሚሉትን ነጥቦችን ዘርዝረው ይግባኙን ለማቅረብ የከፈሉትን ዳኝነት፣ የጠበቃና ሌሎች ልዩ ልዩ ወጪዎች የስር ተከሳሾች እንዲከፍሉ ሊወሰን ይገባል በማለት ዳኝነት መጠያቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ መልስ ሰጪዎች ለይ/ባይ ሊከፍሉት የሚገባው የዶላር ምንዛሬ መቼ በነበረው ነው? የሚለው ጭብጥ በተመለከተከፍ/ብ/ህ/ቁ 1750 ጋር አመሳስሎ በመተርጎም የአሁኑ አመልካቾች ለተጠሪ ሊከፍሏቸው የሚገባው የዶላር ምንዛሬ የስር ፍርድ ቤቱ ፍርድ በሰጠበት በታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም በነበረው የዶላር የብር ምንዛሬ ተመን መሆን ይገባዋል በማለት የወሰነ ሲሆን አመልካቾች ገንዘቡን ከወሰዱት ጊዜ ጀምሮ ተጠሪ ክስ እስከመሰረቱባቸው ድረስ ላለው ጊዜ ወለድ ሊከፍሉ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ ተጠሪ ገንዘባቸው ከእጃቸው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ ገንዘብ ያገኙት ምንም አይነት ጥቅም እንደሌለ፣ በአንፃሩ ደግሞ የገንዘቡ ተጠቃሚዎች አመልካቾች የነበሩ መሆኑን በምክንያትነት ይዞ ወለዱ የማይከፈልበት ምክንያት የለም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ተጠሪ በክሳቸው እንደጠየቁት 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ የአሜሪካን ዶላር) በሚመለከት ከነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ክስ ወደ ፍርድ ቤት እስከቀረበበት እስከ ሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ ላለው ጊዜም 9% ወለድ ሊከፈላቸው ይገባል፤ በተመሳሳይም አመልካቾቹ ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺህ ብር) ከተጠሪ ከወሰዱበት ከጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ተጠሪ ክሱን በሬጅስትራር እስካስከፈቱበት እስከ ሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ 9% ወለድ ሊከፍሏቸው ይገባል በማለት የስር ፍ/ቤቱ በዚህ ረገድ የሰጠውን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ እንዲሁም የሥር 3ኛ ተከሳሽን በተመለከተም በባለቤታቸው በሁለተኛው አመልካች በቤተሰብ ህጉ ድንጋጌዎች መሰረት ተጠያቂ ሊያደርጋቸው የሚችል ሁኔታ ካለ ከተጠያቂነት የማያመልጡበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ለተጠሪ ክስ ግን በቀጥታ ፍርዱ ሊያርፍባቸው የሚያስችል ነገር የለም፣ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቱ በዚህ ረገድ የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍ አይደለም በማለት በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ሲሆን የአመልካቾች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተገቢውን ጭብጥ ለጉዳዩ ሳይዝና አግባብነት የሌለውን ድንጋጌን መሰረት አድርጎ አመልካቾች ከኬንያ ናይሮቢ በአሜሪካን ዶላር ተልኮ በ2ኛ አመልካች ከአቢሲኒያ ባንክ በወቅቱ በነበረው የውጭ ምንዛሬ ተመን መሰረት ለተወሰደው ገንዘብ ለተጠሪ ገንዘቡን ሊመልሱ የሚገባው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በሰጠበት ጊዜ ባለው የውጭ ምንዛሬ ተመን ነው በማለት መወሰኑ አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ ተጠሪ ወለድ የሚያገኙበት ሕጋዊ ምክንያትም የሌለ መሆኑን ዘርዝረው በዚህ ረገድ የተሰጠው የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሽሮ በአንፃሩ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀናላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ነጥቦች፡-

1. አመልካቾች ለተጠሪ ሊከፍሉት የሚገባው ገንዘብ በውጪ ምንዛሬ ነው? ወይስ በኢትዩጵያ ብር ነው?፣
2. አመልካቾች ገንዘቡን ከወሰዱት ጊዜ ጀምሮ ተጠሪ ክስ እስከመሰረቱባቸው ድረስ ላለው ጊዜ ወለድ ሊከፍሉ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚሉት ሆነው ተገኝተዋል፡፡

***<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ</u>***፡- አመልካቾች ለተጠሪ የኢትዩጵያ ብር 800,000 እና 150,000 የአሜሪካን ዶላር በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ ሊከፍሏቸው እንደሚገባ ክርክር ያቀረቡበት ጉዳይ አይደለም፡፡ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው አመልካቾች ለተጠሪ መክፈል ያለባቸው 150,000 ዶላር ይኼው ገንዘብ በ2ኛ አመልካች ከአቢሲኒያ ባንክ ወጪ ሲሆን በኢትዩጵያ ብር ተመንዝሮ በተሠጠበት መጠን ነው? ወይስ በዶላር ነው? የሚል ሲሆን ይህ ጭብጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 246፣ 247 እና 248 ድንጋጌዎች አግባብ ሊመሰረት የሚገባው እና ተጠሪ በዶላሩ ነው ሊከፈላቸው የሚገባው የሚል ምላሽ ከተሰጠ ደግሞ ቀጥሎ የሚመጣው ጥያቄው የዶላሩ ምንዛሬ መሆን ያለበት አመልካቾች ገንዘቡን በወሰዱበት ጊዜ ባለው የውጪ ምንዛሬ ተመን ነው?፣ ተጠሪ ክስ በመሰረቱበት ጊዜ ባለው የውጭ ምንዛሬ ተመን ነው?፣ የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ በሰጠበት ጊዜ ባለው የውጭ ምንዛሬ ተመን? ወይስ አመልካቾች ገንዘቡን ለተጠሪ በሚከፈሉበት ጊዜ ባለው የውጭ ምንዛሬ ተመን ነው? የሚሉትና ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

ከክርክሩ መረዳት እንደተቻለው ተጠሪ ገንዘቡን ከኬኒያ ወደ ኢትዮጵያ ለአመልካቾቹ የላኩላቸው አብረው የንግድ ማህበር ለማቋቋም በመዋጮነት ቢሆንም ማህበሩም አልተመሰረተም፣ ገንዘቡም ለአመልካቾች ጥቅም የዋለ ነው ከሚባል በስተቀር ተጠሪ በዚህ ገንዘባቸው ያገኙት እንዳችም ጥቅም የሌለ መሆኑን፣ ተጠሪ በገንዘባቸው ምንም አይነት ጥቅም ሳያገኙ በአንፃሩ ግን አመልካቾች ይህንን ገንዘብ ከተጠሪ ከተቀበሉበት ጊዜ ጀምሮ ለራሳቸው ጥቅም በማዋል ከፍተኛ ገቢ እንዳገኙበት የሚገመት መሆኑን፣ ተጠሪ ገንዘቡ ለራሳቸው ንግዳዊ ስራ ወይም ለሌላ አገልግሎት አውለውት ቢሆን ኖሮ በወቅቱ ከፍተኛ ጥቅም ሊያገኙበት ይችሉ እንደነበር የሚገመት መሆኑን፣ ተጠሪ የገንዘባቸው ዋጋ ሳይወርድ አቻው የብር ምንዛሬ እስካላገኙበት ድረስ ገንዘባቸውን በተሟላ ሁኔታ አግኝተዋል ሊባሉ የሚችሉ ያለመሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በምክንያትነት ይዞ የስር ፍ/ቤቱ አመልካቾች ለተጠሪ የብር ምንዛሬው መክፈል ያለባቸው ገንዘቡን ሲወስዱ በነበረው የብር ምንዛሬ ነው ማለቱ የተጠሪን ጥቅም የሚያጓድል፣ አመልካቾችን ደግሞ አላግባብ ጥቅም እንዲያገኙ የሚያደርግ መሆኑን ደምድሞ እና ከፍ/ብ/ህ/ቁ 1750 ጋር አመሳስሎ በመተርጎም አመልካቾች ለተጠሪ ሊከፍሏቸው የሚገባው የዶላር ምንዛሬ የስር ፍርድ ቤቱ ፍርድ በሰጠበት በታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም በነበረው የዶላር የብር ምንዛሬ ተመን መሆን ይገባዋል በማለት መወሰኑን ነው፡፡

በመሰረቱ ተጠሪ እንዲመሰርት የፈለጉትና ጥቅም አገኝበታለሁ ብለው የነበሩት ድርጅት ባለመቋቋሙ አመልካቾች ገንዘቡን እንዲመልሱላቸው ዳኝነት መጠየቃቸው ግልጽ ሲሆን ዶላሩን

ከኬንያ አገር ወደ ኢትዩጵያ ቢልኩም 2ኛ አመልካች ገንዘቡን ከባንክ ወጪ አድርገው ሲወስዱ የተከፈላቸው በወቅቱ በነበረው የምንዛሬ ተመን ወደ ኢትዩጵያ ብር ተለውጦ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ከውጪ አገር የተላከ የውጭ ምንዛሬ ኢትዩጵያ ውስጥ በጊዜው በነበረው ተመን ታስቦ ክፍያ የተፈፀመበት ከሆነ ዶላሩ ለተላከበት አላማ አልዋለም በሚል ክርክር ሲነሳ ገንዘቡ ሊመለስ የሚገባው ዶላሩ ሲላክ በነበረበት የውጪ ምንዛሬ ተመን ሊሆን አይገባም የሚል የሕግ መሰረት የለም፡፡ ተጠሪ ከአመልካቾች ጋር ያለው ውል በመፍረሱ ምክንያት የደረሳባቸውን የጉዳት አይነትና መጠን በግልጽ ጠቅሰውም አልተከራከረም፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1750 ድንጋጌ ከገንዘብ እዳ ጋር ተይይዞ የሚነሳውን የውል አፈፃጸም ለመግዛት ታስቦ የወጣ ድንጋጌ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1749 ድንጋጌ ጋር ተጣምሮ ሲነበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1749(1) ድንጋጌ ገንዘብን የሚመለከት እዳ ሲሆን እዳው የሚከፈለው በአገሩ መገበያያ ገንዘብ መሆኑን በመርህ ደረጃ የደነገገ ሲሆን የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1750 ድንጋጌ ደግሞ እዳው በሚከፈልበት ቦታ ውሉ ሕጋዊ ዋጋ የሌለው ገንዘብ ጠቅሶ እንደሆነ ውሉ ቃል በቃል እውነተኛ ዋጋ ወይም ይህንኑ የመሰለ ቃል ከሌለበት በቀር እዳው በሚከፈልበት ቀን ዋጋ ልክ በአገሩ ገንዘብ ሊከፈል እንደሚችል የሚያስቀምጥ ነው፡፡ በመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1750 ድንጋጌ በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል ላለው ጉዳይ ቀጥታም ሆነ በማመሳሰል የትርጉም መርህ ተፈፃሚ የሚሆንበት አግባብ የለም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ የገንዘብ ክፍያ ውል መሰረት ያደረገ የገንዘብ እዳ ክፍያን የሚመለከት ካለመሆኑም በላይ አመልካቾች ከተጠሪ የተላከላቸውን የአሜሪካን ዶላር በቀጥታ የተቀበሉ ሳይሆን ዶላሩ በጊዜው በነበረው የአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ተመን መሰረት ተሰልቶ ወደ ኢትዩጵያ ብር ተመልሶ አመልካቾች መቀበላቸው የተረጋገጠ ጉዳይ ነውና፡፡ በአገሪቱ የገንዘብ ስርዓት መሰረት መንግስትና ሕዝብ በጊዜው በነበረው የውጪ ምንዛሬው ተመን ላገኙት ጥቅም ደግሞ ወደ ኢትዩጵያ ብር የተመነዘረ ዶላር ለተጠሪ ሊያስገኝ ይችል የነበረው ጥቅም ግምት ውስጥ ገብቶ ምንዛሬው ተመን የሚታሰብበት የሕግ አግባብም የለም፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አመልካቾች ያላግባብ ጥቅም ሊያገኙ የሚችሉበትን አጋጣሚ ግምት ውስጥ አስገብቶ ዶላሩ በተላከበት ጊዜ በኢትዩጵያ ብር ተመንዝሮ ለአመልካቾች መሰጠቱ በተረጋገጠበት ሁኔታ ለተጠሪ ዶላሩ ከተላከበት ጊዜ በኋላ ያለው የምንዛሬ ተመን በከፍተኛ ሁኔታ የተለዋወጠ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ሳያስገባ ተመኑ ለተጠሪም የሚያስገኘው ጥቅም ሕጋዊ አድርጎ መውሰዱ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይመሰርትና በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠው ፍሬ ነገር በመተው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1750 ድንጋጌን ያለቦታው ጠቅሶ አመልካቾች 150,000.0 የአሜሪካን ዶላር ለተጠሪ ሊመልሱ የሚገባው በታህሳስ 17 ቀን 2005 ዓ/ም ባለው የውጪ ምንዛሬ ነው በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካቾች ይህንኑ ዶላር ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው 2ኛው ተጠሪ ከአቢሲኒያ ባንክ ሲወስዱ በተከፈላቸው የውጪ ምንዛሬ ተመን ሊሆን የሚገባ ሁኖ አግኝተናል፡፡

<u>**ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-**</u> ተጠሪ ገንዘባቸው ከእጃቸው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በዚህ ገንዘብ ያገኙት ምንም አይነት ጥቅም ያለመኖሩ፣ በአንፃሩ ደግሞ የገንዘቡ ተጠቃሚዎች አመልካቾች በመሆናቸው ተጠሪ ይህ ገንዘብ ከእጃቸው አላግባብ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ያጡት ጥቅም በወለድ ክፍያ ሊካካስላቸው የሚገባ መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተቀበለው ጉዳይ ነው፡፡ አመልካቾች በዚህ ሰበር ደረጃ የሚከራከሩት ለተጠሪ ሕጋዊ ወለድ የሚታሰብበት አግባብ የለም በሚል ሲሆን ለዚህም እንደ ሕጋዊ ምክንያት የሚያቀርቡት ተጠሪ ለአመልካቾች ማስጠንቀቂያ ያልሰጡ መሆኑንና ጉዳዩ የገንዘብ ብድርን መሰረት ያላደረገ መሆኑን ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይመሰረታል የተባለው ድርጅት ሳይመሰረት መቅረቱን አመልካቾች የሚክዱት ፍሬ ነገር አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ በተጠሪ ቋሚ ሃብት ወይም ጥቅም ላይ መቀነስን የሚያስከትል መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በተጠሪ ላይ ቀጥተኛ የሆነ የገንዘብ ኪሳራ የደረሰባቸው መሆኑ በሚገባ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተጠሪ ለአመልካቾች ማስጠንቀቂያ የሚሰጡበት ምክንያት የለም፡፡ አመልካቾች ያመኑትን ገንዘብ ያህል ተጠሪ ለመውሰድ ፈቃደኛ ሊሆኑ ያለመቻላቸውንም በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጡት ጉዳይ አለመሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ይመሰረታል በማለት የጠበቁት ድርጅት ሳይመሰረት ከቀረ ለአመልካቾች በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1771 እና 1705 ድንጋጌዎች አግባብ ማስጠንቀቂያ ሊሰጡ ይገባ ነበር ለማለት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ እንዲሁም የወለድ ገንዘብ በብድር ጊዜ ብቻ ተፈፃሚነት የሚሆን ነው በሚል የቀረበው የአመልካቾች ክርክር ሲታይም የሕግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ ወለድ በሕጉ አግባብ የተዘረጋው ስርዓት እንደተጠበቀ ሁኖ በስምምነት ወይም ያለስምምነት ሊከፈል የሚችል ገንዘብ ነው፡፡ ወለድ ተበዳሪ የወሰደውን ገንዘብ ወይም እቃ በወቅቱ ባለመመለሱየተነሳ የሚከፈል የገንዘብ ካሳ ነው፡፡ ሌላው አይነት ወለድ አንድ ሰው ግዴታውን ባለመፈፀሙ ወይም በማዘገየቱ የተነሳ የሚከፈለው ካሳ እኩያ ነው፡፡ ስለሆነም ወለድ ለገንዘብ ብድር ብቻእንዲከፈል የሚደረግ የካሳ አይነት አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1803(3) ድንጋጌ አንፃር ሲታይም ተጠሪ አመልካቾች የውል ግዴታቸውን ባለመፈመፀማቸው የተነሳ የካሳ እኩያ የሆነው ወለድ የማያገኙበት የሕግ ምክንያት አላገኘንም፡፡

በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቱ ገንዘቡ ለተጠሪ ጥቅም ያለማዋሉን አረጋግጦ እያለ ገንዘቡን የላኩት ለንግድ ማህበር ማቋቋሚያ በመዋጮነት በመሆኑ ወለድ አይገባቸውም የሚል ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ባለመገኘቱ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያለመቀበሉ ተገቢ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በክሳቸው እንደጠየቁት 150,000 (አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ የአሜሪካን ዶላር) በሚመለከት 2ኛ ተጠሪ ከአቢሲኒያ ባንክ ወጪ አድርገው ከወሰዱበት ጊዜ ጀምሮ ክስ ወደ ፍርድ ቤት እስከቀረበበት እስከ ሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ ላለው ጊዜም 9% ወለድ ሊከፈላቸው ይገባል፤ በተመሳሳይም አመልካቾቹ ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺህ ብር) ከተጠሪ ከወሰዱበት ከጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተጠሪ ክሱን በሬጅስትራር እስካስከፈቱበት እስከ ሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ 9% ወለድ ሊከፍሏቸው ይገባል በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም ከላይ በተገለፁት ሕጋዊ ምክንያቶች የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻሻል የሚገባው ሁኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 88280 ጥቅምት 08 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች 150,000 የአሜሪካን ዶላር ለተጠሪ ሊከፍሉ የሚገባው ይኼው ዶላር ከኬንያ ናይሮቢ ወደ ኢትዩጵያ ተልኮ በአቢሲኒያ ባንክ በኩል በኢትዮጵያ ብር ተመንዝሮ በተሰጠው ተመን መሰረት ነው ብለናል፡፡

3. ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች ለተጠሪ በሚከፍሉት ገንዘብ ላይ ክሱ ከቀረበበት ከሚያዝያ 10 ቀን 2003 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ ከሚታሰብ 9% ወለድ አክለው እንዲከፍሉ የሚለውን የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል የሠጠውን ውሳኔ ይህ ችሎትም በማሻሻል አመልካቾች 150,000 ዶላሩን በሚመለከት ከላይ በተራ ቁጥር 2 መሰረት በሚገኘው የብር ስሌት ላይ ከነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ 9% ወለድ በማከል እንዲሁም ብር 800,000 (ስምንት መቶ ሺህ ብር) በሚመለከት ደግሞ አመልካቾች ገንዘቡን ከወሰዱበት ከጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ/ም ጀምሮ ገንዘቡ ተከፍሎ እስኪያልቅ ከሚታሰብ 9% ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍሏቸው ወስነናል፡፡
4. የሥር 3ኛ ተከሳሽን በሚመለከትይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ አልተነካም፡፡
5. በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ በሚመለከት አመልካቾች ለተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት በተወሰነው የገንዘብ መጠን መሰረት የዳኝነት ገንዘብ ይክፈሏቸው ብለናል፡፡ ሌሎች ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትና በዚህ ችሎት ክርክር የወጡትን ወጪና ኪሳራዎችን የያራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

*መዝገቡ ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡*

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::**

# አፈፃፀም

የሰ/መ/ቁ. 90722

ጥቅምት 11 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ወ/ሮ መዓዛ መዝገቡ - VC ሰላልሰራ መቅረባቸውን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ተጠሪ፡- አቶ መሰለ ገላነው - VC ሰላልሰራ መቅረባቸውን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በስር የፍርድ ባለመብት (በአሁኑ ተጠሪ) እና በስር የፍርድ ባለዕዳ (የአሁኗ አመልካች የቀድሞ ባለቤት በአቶ ሰመረ ኃይሉ) መካከል በነበረው የአፈጻጸም ክርክር የአማራ /ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በስር ሁለቱ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ በፍርድ ባለዕዳው ስም የሚታወቀው ቤት ካርታ እና ፕላን የሌለው መሆኑ እና የቀድሞ ተጋቢዎች የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ ቤቱን ለልጆቻችን ሰጥተናል በማለት በንብረት ክርክሩ መዝገብ ላይ ማስመዝገባቸው ቤቱ ለፍርድ አፈጻጸም እንዳይውል ሊያደርገው የሚችል ባለመሆኑ አፈጻጸሙ በቤቱ ላይ ሊቀጥል ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ በስረ ነገሩ ክርክር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በስረ ነገሩ 1ኛ ተከሳሽ እና የአሁኗ አመልካች ባለቤት ከነበሩት ከአቶ ሠመረ ኃይሉ ጋር በ22/06/2000 ዓ.ም. ጋር አቋቁመውት በነበረው ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው አቶ ሠመረ ኃይሉ ጉዳት አድርሰውብኛል በማለት ብር 270,926.50 እንዲከፍሏቸው በሁለቱ ተጋቢዎች ላይ በባህር ዳር ወረዳ ፍርድ ቤት ክስ መመስረታቸውን፣2ኛ ተከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አመልካች በሰጡት መልስ በውሉ ተዋዋይ ወገን ባለመሆናቸው በውሉ አለመፈጸም ሳቢያ በከሳሽ ላይ ደርሷል ለተባለው ጉዳት በኃላፊነት ሊጠየቁ የሚችሉበት የሕግ አግባብ አለመኖሩን በምክንያትነት በመጥቀስ ፍርድ ቤቱ ከክሱ እንዲያሰናብታቸው መጠየቃቸውን፣ፍርድ ቤቱም ጥያቄቸውን ተቀብሎ 1ኛ ተከሳሽ ለክሱ ኃላፊ የሚደረጉ ከሆነ 2ኛ ተከሳሽ ተጠያቂ ሊደረጉ የሚችሉበት ሁኔታ መኖር አለመኖሩ በአፈጻጸም ጊዜ ከሚታይ በስተቀር 2ኛ ተከሳሽ በስረ ነገሩ ሊከሰሱ የሚችሉበት አግባብ የለም ሲል 2ኛ ተከሳሽን አሰናብቶ 1ኛ ተከሳሽን ለክሱ ኃላፊ በማድረግ ብር 198,371.40 ለከሳሽ እንዲከፍሉ በመዝገብ ቁጥር 17174 በ30/04/2002 ዓ.ም. ውሳኔ መስጠቱን፣ከሳሽ በ1ኛ ተከሳሽ ላይ የተሰጠላቸውን ፍርድ ለማስፈጸም በዚያው የስረ ነገሩ መዝገብ የአፈጻጸም ማመልከቻ ባቀረቡበት ጊዜ ከስረ ነገሩ ክስ የተሰናበቱትን አመልካች በ2ኛ የፍ/ባለዕዳነት አካተው

ማቅረባቸውን፣አመልካቿ በስረ ነገሩ ኃላፊ ተደርጌ የተሰጠብኝ ፍርድ ሳይኖር የፍ/ባለመብቱ በፍ/ባለዕዳነት ሰይሞ ያቀረበኝ አላግባብ በመሆኑ ከአፈጻጸሙ ልሰናበት ይገባል የሚል ክርክር በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ ይህንኑ ተቀብሎ አመልካች ከአፈጻጸም ክስ ነፃ ናቸው በማለት በ05/05/2003 ዓ.ም. በተሰጠ ትዕዛዝ ያሰናበታቸው መሆኑን፣ከዚህ በኃላ የፍ/ባለመብቱ ለአፈጻጸሙ ይውል ዘንድ በባህር ዳር ከተማ በቀበሌ 16 የሚገኝ የፍ/ባለዕዳውን ቤት መምራታቸውን፣ቤቱ ተከብሮ እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ ለሰጠው ትዕዛዝም የክፍሉ ቀበሌ ቤቱ የሚታወቀው በፍርድ ባለዕዳው በአቶ ሰመረ ኃይሉ ስም ቢሆንም የተገነባው በጊዜያዊ ይዞታ ላይ በመሆኑ እና ካርታ እና ፕላን የሌለው በመሆኑ ምክንያት ለማስከበር እንደሚቸገር በ20/11/2002 በተጻፈ ደብዳቤ መግለጹን፣የቤቱ ሁኔታ ተጣርቶ እንዲቀርብለት እና ተከብሮ እንዲቆይ ፍርድ ቤቱ በድጋሚ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረትም የፍርድ ባለዕዳው እና ባለቤታቸው ፍቺ በፈጸሙበት ጊዜ ቤቱ ለልጆቻቸው እንዲሆን ለፍርድ ቤት አቅርበው ማስወሰናቸውን በመግለጽ የክፍሉ ቀበሌ በ15/06/2003 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ መስጠቱን፣ፍርድ ቤቱም ከቀበሌው የተገለጹለትን ሁለት ምክንያቶች መሰረት በማድረግ የፍርድ ባለመብቱ ሌላ ንብረት አፈላልገው ማቅረብ የሚችሉ ከመሆኑ ውጪ አፈጻጸሙ በቤቱ ላይ ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ አለመኖሩን ገልጾ በ21/06/2003 ዓ.ም.የአፈጻጸም መዝገቡን በብይን መዝጋቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

በብይኑ ቅር በመሰኘት የአሁኑ ተጠሪ ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የወረዳውን ፍርድ ቤት ብይን ያጸናው ሲሆን ጉዳዩን በመጨረሻ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ ቤቱ የሚታወቀው በፍርድ ባለዕዳው ስም መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ካርታ እና ፕላን የሌለው መሆኑ ለፍርድ አፈጻጸም እንዳይውል ከማድረግ የማይከለክል መሆኑን እና የቀድሞ ተጋቢዎች ቤቱን ለልጆቻቸው ሰጥተዋል መባሉን በተመለከተም ስጦታው ሕጉ እንደሚያዘው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2443 በተመለከተው ስርዓት መሰረት የተከናወነ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ተጋቢዎቹ በፍቺ ውሳኔ መዝገቡ ላይ ቤቱ ለልጆቻቸው እንዲሆን መስማማታቸው እና ስምምነታቸው የፍቺ እና የንብረት ውሳኔውን ባጸደቀው ፍርድ ቤት ተቀባይነት ማግኘቱ ቤቱ በሕጉ አግባብ በስጦታ ተላልፏል የሚያሰኝ አለመሆኑን እና ከፍቺ ጋር የተያያዘ ክርክር የቀረበለት ፍርድ ቤት ፍቺን እና የፍቺ ውጤቶችን ከመወሰን በቀር ስጦታን የማጽደቅ ስልጣን የሌለው መሆኑን ገልጾ የሁለቱን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር አፈጻጸሙ በቤቱ ላይ እንዲቀጥል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም ይዘቱ ከላይ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ የተደረገው በግራ ቀኙ መካከል ክርክር ሲካሄድበት ከነበረው ቁጥሩ 90723 ከሆነው መዝገብ ጋር ተጣምሮ እንዲታይ ተብሎ ቢሆንም በሁለቱ መዝገቦች ተከራካሪ ወገኖቹ ተመሳሳይ ቢሆኑም ለክርክር የቀረቡት ጭብጦች ግን የተለያዩ መሆናቸው በመረጋገጡ ቁጥሩ 90723 በሆነው መዝገብ የቀረበው ክርክር ተነጥሎ ውሳኔ የተሰጠበት ሲሆን በዚህ መዝገብ የቀረበውን አቤቱታ በተመለከተ ግን ለአፈጻጸሙ የተያዘው ቤት የተገነባው በጊዜያዊ ይዞታ ላይ መሆኑ እና በተጨማሪም በአመልካች እና በአቶ ሰመረ ኃይሉ መካከል የነበረው ጋብቻ ፈርሷል መባሉን ተከትሎ ቤቱ ለቀድሞ ተጋቢዎች ልጆች የተሰጠ መሆኑ በተገለጸበት ሁኔታ ቤቱ ለአፈጻጸሙ ሊውል ይገባል ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ የአቤቱታውን ግልባጭ ከመዝገቡ ወስደው መልስ

እንዲሰጡበት በቪዲዮ ኮንፈረንስ በችሎት ተነግሯቸው መልስ ሳይሰጡ በመቅረታቸው የመከራከር መብታቸው እንዲታለፍ ተደርጓል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ለአፈጻጸሙ የተያዘው ቤት በጊዜያዊ ይዞታ ላይ የተገነባ እና ካርታ እና ፕላን የሌለው ቢሆንም በሌላ በኩል ግን ተመዝግቦ የሚታወቀው በአቶ ሰመረ ኃይሉ ስም መሆኑን ጉዳዩ የሚመለከተው የአስተዳደር አካል ለወረዳው ፍርድ ቤት በጽሁፍ አረጋግጧል፡፡ በሌላ አነጋገር ቤቱ ከሚመለከተው የአስተዳደር አካል ዕውቅና ውጪ በሕገወጥ መንገድ የተገነባ ስለመሆኑ የተገለጸ ነገር የለም፡፡ይልቁንም አመልካች እና በፍቺ ተለያይተዋል የተባሉት የቀድሞ ባለቤታቸው አደረጉት በተባለው እና በፍርድ ቤት በተመዘገበው የፍቺ ስምምነት ቤቱ ለልጆቻቸው እንዲተላለፍ መስማማታቸው እና ጉዳዩ የሚመለከተው የአስተዳደር አካልም ቤቱ በቀድሞ ተጋቢዎች ስምምነት ለልጆቻቸው የተሰጠ በመሆኑ የፍርድ ቤቱን የማስከበሪያ ትዕዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚቸገር ገልጾ አፈጻጸሙን ለያዘው ፍርድ ቤት ምላሽ መስጠቱ ካርታ እና ፕላን የሌለው ከመሆኑ ውጪ የቤቱ ሕጋዊነት ጉዳይ በአስተዳደር አካሉ ዘንድ ጥያቄ ያላስነሳ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡

ቤቱ ለቀድሞ ተጋቢዎች ልጆች ተሰጥቷል በማለት የቀረበውን ክርክር በተመለከተም አመልካች እና ፍቺ ፈጽመዋል የተባሉት የቀድሞ ባለቤታቸው የፍቺ ክርክሩን በተመለከተው ፍርድ ቤት ቤቱን ለሕጻናት ልጆቻቸው መስጠታቸውን ገልጸው የፍቺ ስምምነት ከማስመዝገባቸው ውጪ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በውሳኔው ላይ እንደገለጸው ስጦታውበሕጉ በተደነገገው ስርዓት መሰረት የተደረገ ነው የሚባል ካለመሆኑም በላይ የፍቺ ስምምነቱ በፍርድ ቤት ተመዝግቧል የተባለውም ተጠሪው ክስ ከመመስረታቸው ከአምስት ቀናት በፊት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክርም ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል የሁለቱን የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በባህር ዳር ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17174 በ21/06/2003 ዓ.ም. ተሰጥቶ በምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 45472 በ29/05/2004 ዓ.ም. የጸናውን ብይን በመሻር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 20652 በ07/09/2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀን~ል፡፡
2. እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭለባህር ዳር ወረዳ ፍርድ ቤት፣ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 98263

ጥር 06 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- ወ/ሮ እናናይቱ ይሳ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ወራሽ መክያ ከንዙ - ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 34482 የካቲት 13 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35608 የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበችውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በአፈፃፀም ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ አፈፃፀሙ በመጀመሪያ የታየው በፎገራ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ የአፈፃፀም ከሳሽ አመልካች የአፈፃፀም ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ አመልካች በመዝገብ ቁጥር 11394 በተሰጠው ፍርድ መሰረት በመሬቱ ላይ የገነባቸውን ንብረት በማንሳት ቦታውን እንድታስረክብ ይወሰንልኝ የሚል የአፈፃፀም ክስ ለወረዳው ፍርድ ቤት በማቅረቧ ነው፡፡ አመልካች በተከሳሽነት ቀርባ፤ የፍርድ ባለመብት ከነበረችው ከሟች ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም የዕርቅ ውል ተዋውለናል፡፡ በዕርቁም የፍርድ ባለዕዳ ለፍርድ ባለ መብት ብር 6000 /ስድስት ሺ ብር/ ለመክፈልና ቦታውንና ቤቱን ባለበት ሁኔታ ይዥ ለመቆየት ተስማምተናል፡፡ የዕርቅ ውሉን ለማስመዝገብ መጋቢት 27 ቀን 2002 ዓ.ም ፍርድ ቤት ማመልከቻ ይዘን ቀርበን፣ በቀጠሮው ቀን ቅረቡ ተብሎ የተመለስን ሲሆን ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን የቀጠሮው ቀን ከመድረሱ በፊት በመሞታቸው ምክንያት የዕርቅ ውሉ፣ በፍርድ ቤት ሣይመዘገብ ቀርቷል፡፡ ጉዳዩ በዕርቅ ያለቀ ስለሆነ ቤቱን አፍርሼ ቦታውን እንዳስረክብ አልገደድም በማለት ተከራክራለች፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የፍርድ ባለዕዳ መከራከሪያ ያደረገችው የዕርቅ ውል በመዝገቡ ያልተያያዘና ያልተመዘገበ በመሆኑ ፍርድን ባለመፈፀም መከራከሪያ ሆኖ ሊቀርብ አይችልም በማለት አመልካች አዋሳኝ ምልክቱ በተገለፀው ቦታ

ላይ የሰራችውን ቤት አፍርሳ ለፍርድ ባለመብት ታስረክብ ማለት ጥቅምት 7 ቀን 2005 ዓ.ም የአፈፃፀም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

2. አመልካች በዚህ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለደቡብ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባለች፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የፍርድ ባለመብትና የፍርድ ባለዕዳ የካቲት 28 ቀን 2006 ዓ.ም በፍርድ ቤት የተሰጠዉን ፍርድ ቀሪ በማድረግ የተስማሙ በመሆኑ ተጠሪ እንደ ፍርዱ እንዲፈፀምላት ያቀረበችውን ጥያቄ በመቀበል የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢነት የለውም በማለት የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርባለች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የዕርቅ ውሉ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277 መሰረት በፍርድ ቤት ተመርምሮ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑ ያልተመዘገበና በዕርቅ ውሉ ሰበብ፣ የመሬት ሽያጭ የሚመስል ስምምነት የተደረገ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ተፈፃሚነት የሌለው ነው በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ አፅንቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርባለች፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

3. አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት የካቲት 17 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበችው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡትን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ቤት አፍርሽ ቦታ እንዳስረክብ በወረዳው ፍርድ ቤት ተወስኖብኝ ይግባኝ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቤ ጉዳዩ በቀጠሮ ላይ እያለ ከፍርድ ባለመብት ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም የዕርቅ ውል አድርገናል፡፡ ቦታው የከተማ ቦታ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዕርቅ ውሉ የመሬት ሽያጭ የሚመስል ነው በማለት የዕርቅ ውሉን ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የዕርቅ ውሉ ይፍረስልኝ የሚል ክስ ሣይቀርብ ዕርቅ ውሉን ማፍረስ ተገቢ አይደለም፡፡ አመልካች በርካታ ገንዘብ በማውጣት የገነባሁት 56 ዚንጎ ቆርቆሮ ቤት እንዳፈርስ የተሰጠው ውሳኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ተከራክራለች፡፡ ተጠሪ በበኩሏ፣ ሚያዝያ 13 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች ከአውራሽ ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ጋር ያደረገችው የዕርቅ ውል የለም፡፡ የቀረበው ሰነድ በሀሰት የተዘጋጀ የዕርቅ ሰነድ ነው፡፡ አውራሽ ወዳና ፈቅዳ የፈረመችው ሰነድ አይደለም፡፡ ዕርቁ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ያልተደረገና ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው በማለት መልስ ሰጥታለች፡፡ አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ለዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት የፅሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት አመልካች የአፈፃፀም ክስ የቀረበበትን ውሳኔ ገዥነትና አስገዳጅነት ለማስቀረት ከተጠሪ አውራሽ ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ጋር የዕርቅ ስምምነት አድርገናል በማለት ያቀረበችውን ክርክር ውድቅ ያደረጉት በሕግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው በወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪ አውራሽ ወ/ሮ ሀሲና ሁሴንና አመልካች ተከራክረው፣ አመልካች በአከራካሪው ቦታ ላይ የሰራችውን ቤት በማፍረስ ቦታውን እንድታስረክብ ፍርድ የተሰጠበት መሆኑን ግራ ቀኙ አይካካዱም፡፡ የወረዳው ፍርድ

ቤት በሰጠው ፍርድ የተጠሪ አውራሽ የፍርድ ባለመብት፣ አመልካች የፍርድ ባለዕዳ ሆነዋል፡፡ ተጠሪ ለፎገራ ወረዳ ፍርድ ቤት ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነውን የአፈፃፀም ክስ ያቀረበችው አውራሿ የፍርድ ባለመብት የሆነችበት ፍርድ እንዲፈፀምላት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ያቀረበችው የአፈፃፀም ክስ የማትፈፅምበት ምክንያት እንዳላት መከራከሪያ አድርጋ ያስቀረበችው፣ የወረዳው ፍርድ ቤት ቤቱን አፍርሽ ቦታውን እንዳስረክብ የሰጠውን ውሳኔ ተፈፃሚነትና አስገዳጅነት ለማስቀረት የፍርድ ባለመብት ከነበረቸው ሟች ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 የዕርቅ ስምምነት አድርገናል በማለት ነው፡፡

6. አመልካች ከተጠሪ አውራሽ ጋር አድርገነዋል በማለት ያቀረበችውን የዕርቅ ስምምነት ሰነድ በተጠሪ በኩል የታመነ አይደለም፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ የዕርቅ ስምምነት የተደረገ መሆኑን ያሳያል በማለት አመልካች ያቀረበችው ሰነድ፣ በሀሰት ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው፡፡ በሰነድ ላይ ያለው ፊርማ የአውራሽ የወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ፊርማ አይደለም፡፡ ሰነዱ በፍርድ ቤት ያልተመዘገበና ያልፀደቀ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት የተከራከረች መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔና ግራ ቀኙ ለዚህ በሰበር ችሎት ካቀረቡት ክርክር ተረድተናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ ሰነዱን ለመቃወም የአውራሽ ፊርማ አይደለም ብላ መከረከሯ በቂ እንደሚሆን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2007 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ከተጠሪ አውራሽ ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም ባደረገችው የዕርቅ ውል የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ ተፈፃሚ እንዳይሆን የዕርቅ ስምምነት አድርጋለች የሚል ውሳኔ የሰጠው፣ አመልካች የዕርቅ ውል ነው ካለ ባቀረበችው ሰነድ ላይ ተጠሪ ያቀረበችውን መቃወሚያ በመቀበል፣ ፊርማው ለምርመራ ወይም በሌላ መንገድ እንዲጣራ በማድረግና የሰነዱን ትክክለኛነት በማስረጃ በማረጋገጥ እንዳልሆነና የአመልካችን መከራከሪያ ዕውነት ነው ብሎ በመቀበል እንደሆነ ከውሳኔው ተረድተናል፡፡ ይህም ተጠሪ የዕርቅ ውል ነው ተብሎ የቀረበውን ሰነድና በሰነዱ ላይ ያለውን ፊርማ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2007 ንዑስ አንቀፅ 2 በተደነገገው መሰረት ክዳ ተከራክራ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰነዱን ትክክለኛነት በፍትሐብሔርሕግ ቁጥር 2008 በተደነገገው መሰረት ተገቢው ማጣራትና ምርመራ ሳያደርግ፣ ሰነዱን ትክክለኛ የዕርቅ ውል ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰ መሆኑን ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2007 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2008 ድንጋጌዎች መሰረት የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

7. ከላይ የገለፅነዉ ተጠሪ የሰነዱን ትክክለኛነትና ፊርማውን በመካድ ያቀረበችው ክርክር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሣያጣራና በማስረጃ ሳያረጋግጥ ማለፋ የመጀመሪያው የሕግ ስህተት ሆኖ፣ አመልካች ከተጠሪ ወራሽ ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም አድርጌዋለሁ በማለት ያቀረበችው የዕርቅ ውል፣ ትክክለኛና ሟች የፈረመችበት ሰነድ ነው ቢባል ተጠሪ ያቀረበችውን የአፈፃፀም ክስ ቀሪ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ ወይም አለመሆኑ መመርመር ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ከተጠሪ አውራሽ ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም የዕርቅ ስምምነት ፈፅመናል በማለት ያቀረበችው ሰነድ አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት የተፈረደባት ፍርድ አፈፃፀም ቀሪ ለማድረግና በምትኩ ብር 6000 /ስድስት ሺህ ብር/ ለተጠሪ አውራሽ ለመክፈል፣ የተስማሙ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ሰነዱ አመልካች የተጠሪ ወራሽ ተከራክረው የተሰጠን ፍርድ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት ለማስቀረት የተደረገ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የዕርቅ ስምምነት ሰነድ

የተፈረመው በወቅቱ አመልካች ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርባ በክርክር ላይ በነበረበት ወቅት እንደሆነ አመልካች ለስር ፍርድ ቤትና በዚህ ሰበር ችሎት ካቀረበችው የፅሁፍ ክርክር ተረድተናል፡፡

8. ይህም አመልካች ከተጠሪ አውራሽ ጋር አድርጌዋለሁ የምትለው የዕርቅ ውል በፍርድ የተሰጠ ውሳኔ ተፈፃሚነት ቀሪ የማድረግ ዓላማና ይዘት ያለው ከሆነ፣ በሕግ ፊት ውጤት እንዲኖረው ምን ምን መስፈርቶችን አሟልቶ መገኘት አለበት የሚለውን ነጥብ እንድንመረምር የሚያስገድድ ነው፡፡ የዕርቅ ውሉ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ ተፈፃሚ እንዳይሆን የማድረግ ይዘት እና አላማ ካለው፣ ከሌሎች የዕርቅ ስምምነቶች ለየት ባለ መንገድ የተደረገና ይዘቱ ተመርምሮ የፀደቀ መሆን እንዳለበት ከፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 274 እስከ ፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 279 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሰረታዊ ዓላማና ይዘት በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ በተለይም የዕርቅ ውሉ በፍርድ የተወሰነ ውሳኔ አፈፃፀም ቀሪ ለማድረግ የተደረገ በሆነ ጊዜ፣ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 276 እና በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 277 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ የተቀመጡ መስፈርቶች በጥብቅ የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በፍርድ የተወሰነ ጉዳይ ተፈፃሚነት ለማስቀረት የሚደረግ የዕርቅ ውል፣ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 276 መሰረት ተደርጉና በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277/1/ መሰረት ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ቀርቦ ካልፀደቀ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በፍርድ የተወሰነ ውሳኔ ተፈፃሚነት ለማስቀረት የፍርድ ባለመብትና የፍርድ ባለዕዳ ያደረጉት ስምምነት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 276 በሚደነግገው መሰረት ተዘጋጅቶ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277/1/ መሰረት ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ባልፀደቀበት ሁኔታ ፍርድ ቤቶች እየተቀበሉ የሚያከራክሩና ህጋዊ ውጤት የሚሰጡ ከሆነ፣ በዳኝነት አካሉ ክስ ቀርቦባቸው ተከራክረው በፍርድ ውሳኔ የተሰጠባቸው ሰዎች፣ የፍርዱን ውሳኔ ተፈፃሚነት ለማስቀረት ከፍርድ ቤት ዕውቅና ውጭ የዕርቅ ውል ተዋውለናል የሚል መከራከሪያ እያቀረቡ የፍርድ አፈፃፀም ስርዓቱን እንዲያጓትቱና እንዲያስተጓጉሉ ሰፊ ዕድል፣ የሚፈጥር አጠቃላይ የስነ ስርዓት ሕጉን አላማ የሚፃረርና ጉዳዮች በፍርድ ከተቋጩ በኋላ እንደገና ማቆሚያ የሌለው ክርክር እንዲቀርብላቸው የሚያደርግ ይሆናል፡፡

9. በመሆኑም በፍርድ ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ አፈፃፀም ለማስቀረት የፍርድ ባለመብት እና የፍርድ ባለዕዳ የሚያደርጉት የዕርቅ ውል፣ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 276 እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277/1/ የተደነገገውን ጥብቅ መስፈርት የሚያሟላ ባልሆነበት ጊዜ፣ ህጋዊ ውጤትና ተፈፃሚነት እንደማይኖረው የሚያረጋግጥ፣ ጥብቅ የሆነ የሕግ አተረጓጐም መርህ መከተል የፍርድ አፈፃፀም ስርዓቱን ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ ሁኔታ እንዲከናወን ለማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ከተጠሪ አውራሽ ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም አድርጌዋለሁ በማለት ያቀረበችው የዕርቅ ውል ሰነድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 276 እና በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277/1/ መሰረት ፍርድ ቤት ቀርቦ ያልፀደቀ በመሆኑ ከጅምሩ ተጠሪ ያቀረበችውን የአፈፃፀም ክስ ለማቋረጥ መከራከሪያ ሆኖ ሊቀርብ የሚችል አይደለም፡፡ ከዚህ አንፃር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ሰነድ በመቀበል አፈፃፀሙ እንዲቋረጥ የሰጠው የሕግ ትርጉምና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዕርቅ ሰነዱን አፈፃፀሙን ለማቋረጥ ሊቀርብ የሚችል ማስረጃ አድርጎ ከወሰደ በኋላ፣ የሰነዱን ይዘት መርምሮ ሰነዱ በይዘቱ የመሬት ሽያጭ የሚመስል በመሆኑ ለህግ ተቃራኒ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ ከላይ በዝርዝር የገለፅነውን የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 276 እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ

ቁጥር 277/1/ በፍርድ የተወሰነ ውሳኔ ተፈፃሚነት ቀሪ በማድረግ በሚደረጉ የእርቅ ስምምነት ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን ጥብቅ ተፈፃሚነት ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው፡፡

10. ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻራቸው ተገቢነት ያለው ቢሆንም፣ በፍርድ የተወሰነ ውሳኔ ተፈፃሚነት ለማስቀረት የፍርድ ባለመብትና የፍርድ ባለዕዳ ከፍተኛ ዕውቅና ማረጋገጫ ሣይሰጠው አድርገነዋል የሚሉት የዕርቅ ውል ህጋዊ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው አድርገው የሰጡት የሕግ ትርጉም፣ ስህተት ያለበት በመሆኑ፣ ምክንያቱን ለውጠንና አሻሽለን፣ በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ አውራሽ ወ/ሮ ሀሲና ሁሴን ጋር የካቲት 28 ቀን 2002 ዓ.ም ተዋውለናል በማለት ያቀረበችው የዕርቅ ስምምነት ሰነድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 276 እና የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 277/1/ መሰረት በፍርድ ቤት ያልፀደቀ በመሆኑ ተጠሪ ያቀረበችውን የአፈፃፀም ክስ ለማስቀረት ህጋዊ ተፈፃሚነትና ውጤት የለውም በማለት ወሰነናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት መጋቢት 24 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ የዕግድ ትዕዛዝ የተነሳ መሆኑ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡**

**ብ/ይ**

የ/ሰ/መ/ቁ 99743

መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ንብ ኢንሹራንስ (አ.ማ) - ነገረ ፈጅ ተስፋሁን ሽብሩ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- ራዲካል ኢንጅነሪንግ ኃላ/የተ/የግል ማህበር - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍርድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 147896 መጋቢት 22 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ትዕዛዝና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 99409 ሚያዝያ 3 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ ፍርድ አፈፃፀም የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የአፈፃፀም ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካች ወጪና ኪሣራን ጨምሮ አመልካች በፍርድ የተወሰነበትን ብር 589880/ አምስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሰማኒያ ብር / እንዲከፍል የአፈፃፀም ትዕዛዝ ይሰጥልኝ በማለት ለሥር ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ክስ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች በፍርዱ መሠረት የማይፈፀምበትን ምክንያት ቀርቦ እንዲያስረዳ ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች የፍርድ ባለመብት /ተጠሪ/ የሚከናወን ቅሪት ለመሸጥ የሚያስፈልግ ሊብሬና ውክልና እንዲሰጠን ብንጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆኑ በፍርድ የተወሰነብኝን ገንዘብ አልከፈልኩም የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበው መከራከሪያ በፍርድ የተወሰነበትን ገንዘብ ባለመክፈል በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም በማለት አመልካች እንደ ፍርዱ እንዲፈፅም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡
2. አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ሚያዝያ 6 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ አመልካች በመኪናው ላይ የደረሰውን ጠቅላላ ጉዳት ብር 450,000 በመክፈል ተሽከርካሪውን የማስቀረት መብት በመድን ውሉ ውስጥ ተሰጥቷል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ በፍርድ የተወሰነበትን ገንዘብ እንዲከፈለው ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ለአመልካች

እንዲያስረክብ፣ጉዳት የደረሰበትን ተሸከርካሪ አስጠግኖ ለመሸጥ፣ለመለወጥ የሚያስችል ውክልና የመኪና ሊብሬና ተሽከርካሪ ከዕዳና እገዳ እንዲሁም ከግብር ዕዳ ነፃ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃና ክሊራንስ ለአመልካች የመስጠት ግዴታውን መወጣት ይገባዋል፡፡ ተጠሪ ይህንን ሳይፈፅም ገንዘቡን ክፈል መባሉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

3. ተጠሪ ግንቦት 5 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ መልስ፣ፍርድ የሚፈፀመው የተሰጠው ፍርድ ይዘት መሠረት በማድረግ ነው፡፡ አመልካች በአፈፃፀም ወቅት ካነሳቸው መከራከሪያዎች በዋናው ጉዳይ ስንከራከር አንስቶ ፍርድ አላረፈበትም ይህ ከሆነ አመልካች በፍርድ የተወሰነበትን እንድፈጽም ስጠይቅ በፍርድ ተረጋግጦ ውሣኔ ያላረፈበትን ቅድመ ሁኔታ በመደርደር ፍርዱን ለመፈፀም እንቢተኛ መሆኑ የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ግንቦት 27 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡
4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በተጠሪ ብር 589,850 / አምስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ ብር/ ለተጠሪ እንድከፍል በፍርድ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑንና የፍርድ ባለመብቱ ተጠሪ በፍርድ የተወሰነለትን ገንዘብ አመልካች እንዲከፍለውና ፍርዱ እንዲፈጽምለት ጥያቄ ያቀረበ መሆኑን ግራቀኙ በሥርና በሰበር ደረጃ ካቀረቡት ክርክር ተረድተናል፡፡ አመልካች በፍርዱ መሠረት ፍርድ የማይፈፀምበትን ቀርቦ እንዲያስረዳ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 383 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት እንዲያቀርብ የተጠሪው አመልካች ከተጠሪ ጋር ባለው የመድን ውል መሠረት በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት ሰባ አምስት ፐርሰንት ከሆነ የመኪናውን በመድን ውሉ የተመለከተውን ሙሉ ዋጋ ከፍሎ የመረከብ መብት እንዳለው ገልፆ፣ገንዘቡን ለመክፈል በመጀመሪያ የመኪናውን ቅሪት፣ተጠሪ ሊያስረክበኝ ይገባል፡፡ የመኪናውን ሊብሬና ውክልና ሊሰጠኝ ይገባል የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ አመልካች በመድን ውሉና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት አለኝ የሚለው የመኪናውን ቅሪትና ሌሎች መኪናውን ለማስጠገንና ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች የመረከብ መብት፣የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 30 እና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 215(2) መሠረት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በማቅረብ በፍርድ ያስወሰነ ስለመሆኑ ያቀረበው የፍርድ ቤት ውሣኔ የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በአፈፃፀም ወቅት መከራከሪያ አድርጎ ያቀረባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች የክስ መከላከያ አድርጎ አቅርቦ፣ፍርዱን የሰጠው ፍርድ ቤት በጭብጥነት ይዞ፣ውሣኔ የሰጠባቸውና ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ የፍርድ ቤት ውሣኔ አላቀረበም፡፡
6. ፍርድ የሚፈፀመው በፍርድ ውስጥ በተገለፀው ውሳኔ መሰረት መሆኑን የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 378 ንዑስ አንቀጽ 1 ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፍርድ ባለመብት ፍርዱን እንዲፈፀምለት ሲጠይቅ፣የፍርድ ባለዕዳው፣የፍርድ ባለመብቱ ተነጻጻሪ የሆነ ግዴታውን እንዲወጣ ትዕዛዝ ይስጥልኝ በማለት ጥያቄ ለማቅረብ የሚችለው በአንድ ፍርድ ውስጥ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች የፍርድ ባለመብት መሆናቸው ተረጋግጦ ውሳኔ ተሰጥቶበት እንደሆነ መሆኑን ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 398 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አመልካች ከመድን ውሉና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች

ተጠሪ ሊፈፅምልኝ የሚገባው ግዴታ አለ በማለት በአፈፃፀም መከራከሪያ አድርጎ ያቀረባቸው ነጥቦች በዋናው ጉዳይ መከራከሪያ ሆነው ቀርበው ፍርድ የተሰጠባቸው አይደሉም ይህ ከሆነ አመልካች ከተጠሪ የሚጠይቀው መብት ካለ፣በሕግ አግባብ ክስ አቅርቦ በፍርድ ተረጋግጦ እንድንወስንለት ከሚጠይቅ በስተቀር፣ፍርድ ያላረፈበትን ቅድመ ሁኔታ በአፈፃፀም ክርክር በመደርደር ፍርዱን የመፈፀም ግዴታ የለብኝም በማለት ያቀረበው መቃወሚያ የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ፍርዱን የማይፈፅምበት በቂ አሳማኝና ህጋዊ ምክንያት አላቀረበም በማለት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት የአፈፃፀም ትዕዛዝ ከላይ የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 9 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጭ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**የ/ማ**

# ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁ.96833

ህዳር 08 ቀን 2007 ዓም

**ዳኞች**፡- አልማዉ ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- የመንግሥት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - ቀረቡ /ነ-ፈጅ/

ተጠሪ፡- አቶ አስፋዉ ደነቀ - የቀረበ የለም።

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ይህ ጉዳይ በማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጀመረው ተጠሪ አቶ አስፋዉ ደነቀ የተራዘመዉ አገልግሎት ለጡረታ ተግባር እንዲያዝላቸዉ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ነዉ፡፡ ተጠሪ የሚጠይቁት ተጠቃሹ መስሪያ ቤት በወቅቱ በነበረበት የሰዉ እጥረት የጡረታ ጊዜዬን ለ5 ዓመታት እንዲራዘም በጻፈዉ ደብዳቤ ለማ/ዋ/ቅ/ጽ/ቤት ሲጻፍ ለእኔም ግልባጩ ደርሶኝ በተከፈተዉ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት የውሃ ጽ/ቤት ተጠባባቂ ኃላፊነት ተመድቤ በ6 ወረዳዎች ሰራሁ፣በድጋሜ የጡረታ ግዜ ለ5 ዓመታት እንዲራዘም ለክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ተጽፎ የስምምነቱ ደብዳቤ ለመ/ቤቱ ሲደርስ ግልባጩ ለክልሉ ማ/ዋ/ኤ/ጽ/ቤት ደርሷል፣ የዉሃ ሀብት ቢሮ ባዘጋጀዉ አዲስ መዋቅር የተደረገዉ ስምምነት 2 ዓመት ሲቀረኝ እርምጃ ወስዷል፣ስለዚህ ከየካቲት 1995 እስከ ጥር 30 ቀን 2003 ዓ/ም ድረስ የተራዘመዉ የ8 ዓመታት አገልግሎቴ እንዲያዝልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም በሰጠዉ መልስም፡- አቶ አስናቀ ደነቀ የትዉልድ ዘመናቸዉ ጥር 13 ቀን 1940 ዓ.ም ሲሆን በጡረታ መገለል የሚገባቸዉ ከየካቲት 01 ቀን 1995 ዓም ጀምሮ ነዉ፣አሰሪዉ መ/ቤቱ መረጃ እንዲልክ በ2/9/95 ዓ.ም ቢጠየቅም የአገልግሎት ማራዘሚያ ጥያቄ ለሱማሌ ክልል መላኩ ስልጣኑ እንዳልሆነ በማሳወቅ የባለመብቱ መረጃ ተሟልቶ እንዲላክ በድጋሚ በ15/11/95 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የተጠየቀና የመጀመሪያ አምስት አመታት የጡረታ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ በሚመለከተዉ አካል ባልቀረበበት ሁኔታ በተጨማሪ ከ1/8/2000 እስከ 30/05/2005 ዓም እንዲራዘም የተደረገዉ የጡረታ መዉጫ ጊዜያቸዉ ካለፈና የጡረታ አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 11(ሀ) መሠረት የጡረታ መዉጫ ጊዜያቸዉ ካለፈ አገልግሎታቸዉ እንዲራዘም የተፈቀደበት መረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ከእድሜ ጣሪያ በላይ ላገለገሉበት የመዋጮ ተመላሽ ከሚከፈላቸዉ/ከሚጠይቁት በስተቀር የተራዘመዉ አገልግሎት ሊያዝላቸዉ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን ያየዉ ማህበራዊ ዋስትና ጉባኤም ከሱማሌ ክልል መንግስት የዉሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ በ12/10/1995 ዓም ለማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት በጻፈዉ ደብዳቤ የተጠሪ የአገልግሎት ጊዜ እንዲራዘም ጥያቄ ያቀረበ መሆኑ ከቀረበዉ መረጃ ለመረዳት

ተችሏል፣በተጨማሪም በ18/7/1995 ዓ.ም በቁጥር ሠአር ከሰ/2145/95 ከክልሉ የዉሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ የድሬዳዋ ጽ/ቤትን በመደበኛ ስራ ለማስጀመር የጽ/ቤቱ ጊዜያዊ ኃላፊ በመሆን የተሾሙ መሆኑን ከቀረበዉ ማስረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፣የሽንሌ ዞንም ከፍተኛ ድርቅ ተከስቶበት ስለነበር ችግሩን ለመቅረፍ ሲሰሩ እንደነበር እና ከፍተኛ ባለሙያ መሆናቸዉን ገልጾ በክልሉ የዉሃ ሀብት ኃላፊ ሆነዉ በሹመት ወደ ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ተዛዉረዉ በኃላፊነት ሲሰሩ እንደነበር ለጉባዔዉ ገልጸዋል የሚሉ ምክንያቶችን ይዞ በሹመት የቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን እንዲሰሩ የተመደቡ በመሆናቸዉ ከእድሜ ጣሪያ በላይ የፈጸሙት አገልግሎት ሊያዝላቸዉ እንደሚገባ በጉባኤዉ ታምኖበታል በማለት የኤጀንሲውን ዉሳኔ ሽሮ ተጠሪ ከዕድሜ ጣሪያ በላይ የፈጸሙት አገልግሎት ለጡረታ ተግባር እንዲያዝላቸዉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ኤጀንሲዉ ይግባኝ በማለቱ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎትም ቅሬታዉን በአዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 76 መሰረት ባለመቀበል ዘግቶታል፡፡

የአመልካች የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ዉሳኔ ለማስቀየር ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረበዉ የሰበር አቤቱታም ቅሬታዉን ሲገልጽ፡- ተጠሪ በክልሉ የዉሃ ሀብት ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ቢሮ ሥር ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ በመሆን ሲሰሩ የቆዩት በስራ ሀላፊነት እንጂ በሹመት አይደለም፣ ሃላፊ ተብለዉ መስራታቸዉ ሹመት ሊባል አይችልም፣ የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮ የፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁ. 515/99 ድንጋጌን በመጥቀስ የተጠሪ አገልግሎት ከተቋረጠ 5 ዓመታት በኊላ እንዲራዘም መፍቀዱ ህግን የተከተለ አይደለም፣ የጡረታ አዋጅ ቁ.710/2003 አንቀጽ 17(4)(ሀ) መሠረት ማንኛዉም የመንግስት ሰራተኛ በህጉ መሰረት አገልግሎቱ ካልተራዘመ የጡረታዉ መዉጫ እድሜዉ ከደረሰበት ከሚቀጥለዉ ወር አንስቶ የሚሰጠዉ አገልግሎት ለጡረታ ተግባርአይያዝም እያልንኤጀንሲዉና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት የተጠሪ አገልግሎት እንዲራዘምና እንዲያዝላቸዉ መወሰኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊሻር ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ በዚህም መሰረት ችሎቱም ተጠሪ ከጡረታ መዉጫ በኊላ የአገልግሎት ዘመኑ ለተጨማሪ 5 ዓመታት ተራዝሟል መባሉን ከአዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 89 ድንጋጌና ከዚሁ አዋጅ አንቀጽ 85/1 ድንጋጌ አንጻር ለማጣራት የግራ ቀኙ የመልስና መልስ መልስ በጽሑፍ ተቀብብለዉ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አኳያ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች የሚለዉ የአዋጅ ቁ.515/99 ተጠቅሶ ተጠሪ አገልግሎት ከተቋረጠ ከ 5 ዓመታት በኊላ እንዲራዘም መፈቀዱ ህግን የተከተለ አይደለም ፣በህጉ መሠረት ማንኛዉም የመንግስት ሰራተኛ አገልግሎት ካልተራዘመ በስተቀር የጡረታ መዉጫ ዕድሜዉ ከደረሰበት ከሚቀጥለዉ ወር አንስቶ የሚሰጠዉ አገልግሎት ለጡረታ ተግባር አይያዝም፣በመሆኑም ህጋዊነቱ ሳይረጋገጥ ተራዝሟል መባሉ ሊታረም ይገባዋል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በወቅቱ በነበረዉ የዉሃ አጥረት የተነሳ እንዳገለግል ፈቅዶ ሲያሰራኝ ቆይቶ መራዘሙን አላዉቅም ማለቱ የራሱን የመረጃ አያያዝ ድክመት መኖሩን የሚያሳይ ነዉ፣ አመልካች ማገልገሌን ሳይቃወም ዉሳኔዉን መንቀፉ አግባብ ባለመሆኑ የስር ዉሳኔ ስህተት የለበትም በማለትተከራክሯል፡፡

በመሰረቱ የአዋጅ ቁ.515/99 አንቀጽ 89 እና አንቀጽ 85(1) ድንጋጌዎች ከተያዘዉ ክርክር አንጻር ስንመለከታቸው አንቀጽ 89(2) ሠ እና 85(1) በመርህ ደረጃ የጡረታ ጊዜ አገልግሎት ሊራዘም የሚችለዉ ለኤጀንሲዉ ቀርቦ በህጋዊ መንገድ መፈቀድ እንዳለበት ይህ ካልሆነ

ያለተጨማሪ ስነ-ስርዓት አገልግሎት የሚቋረጥ መሆኑን እና የአገልግሎት መራዘም ከ10 ዓመት የማይበልጥ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት የህግ ድንጋጌዎች በመርህ ደረጃ ጡረታ መዉጫ ጊዜ ከደረሰ በኋላ አገልግሎት ዘመን ለማራዘም ሊከናወኑ የሚገባቸዉን ህጋዊ አካሄድን የሚያመላክቱ መሆናቸዉን መገንዘብ ተችሏል፡፡

በእጃችን ወዳለዉ ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ በክልሉ የዉሃ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ ሲያገለግሉ የነበሩና አስፈላጊ ባለሙያ በመሆናቸዉ ከጡረታ መዉጫ ጊዜያቸዉ በኋላ ተጨማሪ አገልግሎት እንዲሰጡ በመፈለጉ ምክንያት በ12/10/95 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ለማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን ማሳወቁን መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ላለፉት 8 ዓመታት የውሃ አጥረት በገጠማቸዉ አካባቢዎች ተዘዋውረው ሲሰሩ እንደነበሩና ለስራቸዉም ክፍያ ሲያገኙ እንደነበሩ የምንገነዘበዉና በስር ፍርድ ቤትም ተረጋግጦ እና በአመልካችም ያልተካደ ጉዳይ ነዉ፡፡ አከራካሪ የሆነዉ ጉዳይ ተጠሪ ይሁንታ ሳያገኙ የአዋጅ ቀ.714/2003"ን" መንፈስ ተከትሎ አስፈላጊውን ቅደመ ሁኔታ ሳያሟሉ (ጥያቄያቸዉ ተቀባይነት ሳያገኙ) በመስራታቸዉ ብቻ የተራዘመ አገልግሎት ለጡረታ አገልግሎት እንዲያዝላቸው መጠየቅ አይችሉም በማለት ነዉ፡፡ እንግዲህ ተጠሪ ለተጨማሪ ግዜ አገልግሎት መስጠታቸዉ ባልተካደበት አስፈላጊዉን አስተዳደራዊ መጻጻፍ በማድረግ ጉዳዩን ወደ ህጋዊነት የማምጣት ኃላፊነት እና ግዴታ ያለበት አመልካች እንጂ ተጠሪ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ምክንያቱም አሰሪዉ አካል እያወቀና ተቃዉሞ ከየትኛዉም አካል ሳይገጥማቸዉ ተጠሪ ስራቸውን መስራታቸዉን ማረጋገጣቸዉ በቂ ነዉ፡፡

በአጠቃለይ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በስር በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠዉን በመቀበል ተጠሪ ከዕድሜ ጣሪያ በላይ ያገለገሉት ጊዜ ለጡረታ አገልግሎት እንዲያዝላቸዉ መወሰኑ በአግባቡ ነዉ ብለናል፡፡

በመጨረሻም ማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚዉ ጉባዔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በመ.ቁ.ጤ/ይ/1/1/43/2006 በቀን 29/02/2006 ዓ/ም እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.95017 በቀን 30/04/2006 ዓ.ም የሰጡት ዉሳኔ ጸንቷል፡
2. ተጠሪ ከዕድሜ ጣሪያ በላይ የፈጸሙት አገልግሎት ለጡረታ ተግባር እንዲያዝላቸዉ መባሉ ባግባቡ ነዉ ብለናል፡፡
3. የግራቀኙ የወጪና ኪሳራቸዉን ይቻቻሉ፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ብ/ግ**

የሰ/መ/ቁ 99679
ታህሳስ 24 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ
ዓሊ መሐመድ
ሡልጣን አባተማም
ሙስጠፋ አህመድ
ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ኤርፓርቶች ድርጅት - ጠበቃ አቶ ሚካኤል ጉንታ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- አቶ በየነ ወልደገብርኤል - ጠበቃ ኃይሉ ብርሃኑ ጋር ቀረቡ፡፡

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 96130 ጥር 6 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የግልግል ጉባኤ ዳኛና ሰብሳቢ ሆኖ የተሰየመ ሰው ጉዳይን ከማየት ይነሳልኝ በሚል መንገድ በቀረበ ጥያቄ የተሰጠን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡

1. ጉዳዩ የተጀመረው ለአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤትና የዘርፍ ማህበራት የግልግል ተቋም አመልካች ባቀረበው ጥያቄ ነው፡፡ በግልግል ተቋሙ መልስ ሰጭ የሆነው አመልካችና የይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ የሆነው ጂኦሜትሪ ሉዊጅ ቫርኔሮ አምፐራስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በመካከላቸው የተፈጠረው አለመግባባት በግልግል ዳኞች እንዲቀርብ በመስማማታቸው የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤትና የማህበራት ዘርፍ የግልግል ዳኝነት ተቋም የግልግል ዳኞች ጉባኤ ተቋቁሟል፡፡ የግልግል ዳኞች ጉባኤ ሰብሳቢ ተጠሪ እንዲሆን ሰይሞታል፡፡ የግልግል ዳኞች የተከራካሪዎችን ክርክር በማየት ሂደት ላይ እያሉ አመልካች ታህሳስ 04 ቀን 2006 ዓም በተፃፈ ማመልከቻ የግልግል ዳኞች ጉባኤ ሰብሳቢ የሆኑት ተጠሪ ጉዳዩን ከማየት እንዲነሱለት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ የግልግል ተቁሙ የግልግል ዳኞች ጉባኤው በአመልካች ጥያቄ ላይ አስተያየት እንዲያቀርብ በማድረግ፣ የግልግል ዳኞች በአመልካች ማመልከቻ ላይ ዝርዝር አስተያየት ሰጥተዋል፡፡ የግልግል ተቋሙ፣ የግልግል የዳኝነት ጉባኤው ሰብሳቢ የሆኑት የአሁኑ ተጠሪ ጉዳዩን ከማየት እንዲነሳለት አመልካች ያቀረበውን ጥያቄ ያልተቀበለው መሆኑን በመግለጽ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡
2. አመልካች ግንቦት 15 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ ግልግል ዳኝነትና ከሰብሳቢነት ሊነሳ ይገባል የሚልባቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር የሰበር አቤቱታውን አቅርቧል፡፡ ከግልግል ዳኝነቱ እንዲነሳ የተጠየቀው ተጠሪ ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም

ከግልግል ዳኝነት አልነሳም የሚልበትን ዝርዝር ምክንያት በመግለፅ ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ሐምሌ 8 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

3. የሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ሂደት ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ተጠሪ ከዚህ በኋላ የግልግል ዳኛና ሰብሳቢ ሆኖ ለመቀጠል ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡
4. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከህዳር 16 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለው የአዲስ አበባ ንግድ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የግልግል ተቋም የተሻሻለ የግልግል ደንብ ስለዳኞች መነሳትና መተካት በአንቀፅ 15 የደነገገ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በግልግል ደንቡ አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ በአንደኛው ተከራካሪ ወገን አቤቱታ ወይም ጥቆማ መሠረት የግልግል ዳኛ እንዲነሳ ጥያቄ ሲቀርብ፣ ተዋዋዮችና ወይም የይነሳልን ጥያቄ ያልቀረበባቸው የግልግል ችሎት ሌሎች አባላት የፅሑፍ አስተያየት ከተቀበለ በኋላ ተቋሙ ውሣኔ እንደሚሰጥ ይገልፃል፡፡
5. አከራካሪው ጉዳይ ተቋሙ ከግልግል ችሎቱ እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት ዳኛ፣ ከግልግል ችሎቱ መነሳት የለበትም በማለት በሰጠው ውሣኔ ላይ የአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀፅ 9 እና አንቀፅ 10 መሠረት የይግባኝና የሰበር አቤቱታ ሲቀርብበት ወይም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3342 መሠረት መቃወሚያ ሲቀርብበት የተቋሙን ውሣኔ በመደገፍ ተከራካሪ ሆኖ መቅረብ ያለበት ማን ነው? ከጉዳዩ እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት ዳኛ፣ ጉዳዩን ከማየት እንዳልነሳ የተሰጠው ውሣኔ ተገቢነት ያለው ነው በማለት ጉዳዩን ለግልግል ዳኝነት ካቀረበውና ጥያቄውን ካነሳው ተከራካሪ ወገን ጋር መልስ ሰጭ ወይም ተጠሪ ሆኖ ቀርቦ ዝርዝር ክርክር ካቀረበ በኋላ፣ በፍርድ ቤት ተከራካሪ ሆኖ በቀረበበት ጉዳይና በተከራካሪነት ቀርቦ ሲሞግተው የነበረውን ተከራካሪ ወገን ለግልግል ዳኞች የሚያቀርበውን ክርክርና ማስረጃ በገለልተኝነት ስምቶ ሊወስን ይችላል ተብሎ በግልግል ዳኝነት እንዲሰየም ማድረግ የግልግል ዳኝነቱን ዓላማ የማያሳካ ነው ወይ? የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
6. የአዲስ አበባ ንግድ ዘርፍ ማህበራት የግልግል ተቋም የግልግል ደንብ፣ ተቋሙ ጉዳዩን ከማየት እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት የግልግል ዳኛ ጉዳዩን ከማየት አይነሳም በማለት በሰጠው ውሳኔ ላይ አንደኛው ተከራካሪ ወገን መቃወሚያ ፣ ይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ በሚያቀርብበትና አቤቱታው ተቀባይነት አግኝቶ መልስ እንዲቀርብ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ፣ የግልግል ተቋሙ ዳኛው ጉዳዩን ከማየት የሚነሳበት በቂ ምክንያት የለም በማለት የሰጠው ውሳኔ በዝርዝር ለማስረዳት ክርክሩን በማን በኩልና እንዴት እንደሚያቀርብ በግልፅ ያስቀመጠው ስርዓት የለም፡፡ ሆኖም በመርህ ደረጃ የግልግል ተቋሙ ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት (ሰብሳቢነት) ተሰይሞ ከማየት የሚከለክል በቂ ምክንያት የለም በማለት የሰጠውን ውሳኔ ለማስረዳት ከሚያቀርብ በስተቀር፣ጉዳዩን ከማየት እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት የግልግል ዳኛ በተከራካሪነት ቢቀርብና፣የግልግል ዳኛውን ከዳኝነት የሚያስነሳው በቂ ምክንያት አለ ወይስ የለም በሚለው ጭብጥ ዙሪያ ተከራካሪ ሆኖ መሰለፍና ዝርዝር ክርክር የሚያቀርብበት ሁኔታ መኖር የለበትም፡፡
7. ከዚህ አንጻር ስናየው ተጠሪ በጉዳዩ ተከራካሪ ሆነው መጠራታቸው ስህተት ነው፡፡ አመልካች ለግልግል ተቋሙ ተጠሪ ከግልግል ዳኛነትና ሰብሳቢነት እንዲነሳ ያቀረብኩት ምክንያት አላግባብ ውድቅ ተደርጎብኛል የሚል የሰበር አቤቱታ ሲደርሳቸው ተጠሪ

በጉዳዩ የተለየ ጥቅምና ፍላጎት የሌላቸው መሆኑንና ጉዳዩን በዳኝነት እንዲያይ ወይም ከግልግል ዳኝነት እንዲነሳ በህግ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ጉዳዩን አጣርተው የሚሰጡትን ውሳኔ በፀጋ እንደሚቀበሉ ከመግልጽ ማቆም ይገባዋል፡፡ ተጠሪም ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት ተሰይሜ ማየት አለብኝ የሚል አቋም በመያዝ ሰፊና ዝርዝር ክርክር እንዳቀረቡ ለዚህ ሰበር ችሎት ካቀረቡት ክርክር ተርድተናል፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ይዘት የቀረበውን ሙግት በመቃወም ፣ ተከራካሪ ሆነው ተሰልፈው ሰፊና ዝርዝር ክርክር ባቀረቡበት ሁኔታ የአመልካችንና በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆነውን "ቫርኔር" እየተባለ የሚጠራውን ድርጅት ጉዳይ ከዚህ በኋላ በግልግል ዳኝነት ተሰይመው እንዲያዩ መፍቀዱ ከመሰረታዊነትም ሆነ ከዕይታ አንጻር ሲመዘን ፣ የግልግል ዳኝነት ነጻነትና ገለልተኝነት መርህ የሚያስከበር ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ይህ ሁኔታ በራሱ በሶስተኛ ወገን የተመረጠ ዳኛ ባለማዳላቱ ወይም በነጻነቱ ላይ ጥርጣሬ ለማስገባት የሚችል አንድ አንድ የአካባቢ ሁኔታ ምክንያት በሚኖርበት ጊዜ ዳኛው ከግልግል ዳኛነቱ ሊነሳ እንደሚችል በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3340 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገውን የሚያሳይ ነው፡፡

8. ተጠሪ በጉዳዩ መልስ ሰጭ አድርጐ ሰይሞ በማቅረብ አመልካች በፈጸመውና ፍርድ ቤቱም ተጠሪን በተከራካሪነት በመጥራቱ ምክንያት በተፈጸመ ስህተት ፣ አመልካች ተጠሪ በአንድ አከራካሪ ጭብጥ ላይ በተከራካሪነት ተሰልፈው ሰፊ የሆነ ክርክር አቅርቧል፡፡ በሌላ አነጋገር በግልግል ዳኝነት አካሉ መልስ ሰጭ የሆነው አመልካችና የግልግል ዳኛ ሆኖ ጉዳዩን ከማየት የሚከለክለኝ ምክንያት የለም የሚል ክርክር ያቀረበው የግልግል ችሎቱ ሰብሳቢ ዳኛ የሆኑት ተጠሪ "ዳኛው ከግልግል ችሎቱ መነሳት አለበት ወይስ የለበትም" በሚለው ጭብጥ ላይ ሁለት ተቃራኒ አቋም በመያዝ ግራናቀኝ በተከራካሪነት ቆመው ተሟግተዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ተጠሪ የግልግል ጉባኤው ዳኛና ሰብሳቢ ሆኖ እንዲቀጥል ቢደረግ የግልግል ዳኛ ሁሉንም ተከራካሪ ወገኖች ጋር የነበረው ያለውና የሚኖረው ግንኙነት በገለልተኝነትና በነፃነት መርህ ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል የሚለውን የግልግል ተቋሙ የተሻሻለ ደንብ አንቀፅ 13 ድንጋጌና ሌሎች ሕጎች የተደነገገውን መርህ የሚጥስ በመሆኑ ተጠሪ የግልግል ዳኛና ሰብሳቢ ሆኖ መቀጠል አይገባውም በማለት በተሻሻለው የግልግል ደንብ ከአንቀፅ 13 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3340 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በማድረግ ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. ተጠሪ በግልግል ዳኝነትና ሰብሳቢነት መቀጠል እንደሌለበት የተወሰነ መሆኑን አውቆ ተገቢውን እንዲፈፅም ለአዲስ አበባ ንግድ ዘርፍ ማህበራት የግልግል ተቋም ውሣኔው ይተላለፍለት፡፡
2. ግራቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/

የሰ/መ/ቁ. 99689

ታህሳስ 24 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች**፡-አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች**፡-ዶ/ር መኮንን ንዋይ የአዲስ አበባ ዴንታል ሳይንስና ኮሌጅ ባለቤትና ዲን - ጠበቃ ግርማ ኃይሌ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- 1. መንግስቱ ጋሞ
2. አቶ እንዳለ አለማየሁ
3. አቶ ኢሳያስ አበራ
4. አቶካሊድ አባስ
5.ወ/ሮ መሰረት መላኩ
6. አቶ አዲስአለም አለማየሁ
(2–6) ሌሎች አልቀረቡም
7. አቶ ታዬ አዱኛ..........ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ ኦርጂናል ዲፕሎማ ይሰጠኝ ጥያቄ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡የተጠሪዎች የክስ ይዘትም፡-አመልካች በ1999 ዓ/ም አዲስ አበባ ዴንታል ሳይንስ ኮሌጅውስጥ ለማስተማር ተቀብሎ ለሶስት አመታት የጥርስ ህክምና ትምህርት አስተምሮ በ2002 ዓ/ም ካስመረቀ በኋላ ትራንስክርቢትና ጊዜያዊ ዲፕሎማ የሰጣቸው ቢሆንም ኦርጂናል ዲፕሎማውን ለመስጠት ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን ገልጸው ይህንኑ ማስረጃ እንዲሰጧቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ተጠሪዎች ትምህርቱን ጨርሰው ጊዜያዊ ዲፕሎማ መውሰዳቸውንአምነው ዋናውን ዲፕሎማ ለመስጠት ኮሌጁ ዝግጅት ላይ እንዳለ የመንግስት ክልከላና የፈቃድ ስረዛ በማጋጠሙ የተነሳ ማህተምም ሆነ ፊርማ የሚፈርም ባለስልጣን ባለመኖሩ ለተጠሪዎች ኦርጂናል ዲፕሎማ እንዳልተሰጠና በፍርድ ቤት ቢወሰንም ሊፈጸም የማይችል መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ተገቢ ነው ባለው መንገድ ሁሉ ከሚመለከተው አካል ስለ ጉዳዩ አጣርቶ የተጠሪዎችን ኦርጂናል ዲፕሎማ አመልካች ሊሰጥ የማይችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ማስረጃውን አመልካች ለተጠሪዎች ሊሰጥ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር

በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡የአመልካቸ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም በስር ፍርድ ቤት ያቀረባቸውን የክርክር ነጥቦችን የሚያሳይ ሁኖ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሻር ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያሳይ ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች ቀርበውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንጻር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡እንደመረመረውም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ለማለት ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች በአመልካች ባለቤትነትና በሚታወቀውና አመልካቹ በዲንነት ያስተዳድሩት ኮሌጅ ውስጥ ተመዝግበው በተገቢው መንገድ ትምህርታቸውን መከታተላቸውና መጨረሳቸው ተረጋግጦ ትራንስክርቢትና ጊዜያዊ ዲፕሎማ በአመልካቹ የተሰጣቸው መሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ከመሆኑም በላይ ኮሌጁ በመንግስት ክልከላና ፈቃድ ስርዛ ምክንያት ስራውን ያቆመ ቢሆንም ትምህርታቸውን በአግባቡ ተከታትለው ላጠናቀቁት ተማሪዎች ዋናውን ዲፕሎማ እንዳይሰጥ የሚከለክል መመሪያ የሌለ መሆኑና ኮሌጁ ዲፕሎማውን የመስጠት ግዴታ ያለበት መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ በቁጥር ኤ./4015/ተስጥመ/12/67 በቀን 17/10/2005 ዓ/ም ለስር ፍርድ ቤት በጻፈው ደብዳቤ መረጋገጡን ነው፡፡በመሆኑም ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካች ኮሌጅ በመንግስት ስልጠና ለመስጠት መከልከሉና ፈቃድ መሰረዝ ከዚህ የመንግስት እርምጃ በፊት ስልጠናውን በአግባቡ ተከታትለው የጨረሱ ተማሪዎች ኦርጂናል ዲፕሎማ እንዳያገኙ የማያደርግ መሆኑን ከሚመለከተው አካል ምላሽ ተሰጥቷቸው በሚገባ አረጋግጠዋል፡፡አመልካች ማህተም የሌለው ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ ካለመረጋገጡም በላይ ማህተም ያለመኖሩ ወይም ቀድሞ ለተጠናቀቀ የትምህርት ስልጠና በፊርማ አረጋግጦ ማስረጃ ለመስጠት በወቅቱ የነበረው ኃላፊ ያለመኖሩ ተፈፃሚነትባላቸው ሕጎች መሰረት ኦርጂናል ዲፕሎማውን ለተጠሪዎች ላለመስጠት የሚያስችለው መሆኑን አላስረዳም፡፡ይልቁንም አግባብነት ያለው አካል ኦርጂናል ዲፕሎማውን ማግኘት መብታቸው መሆኑን፣ማስረጃው መስጠት ደግሞ የአመልካች ግዴታ መሆኑን በሚያስገነዝብ መልኩ አረጋግጧል፡፡በመሆኑም አመልካች ከአዋጅ ቁጥር 650/2001፣ደንብ ቁጥር 199/2003 እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተጣለበትን ኃላፊነት ያልተወጣ መሆኑ በአንጻሩ ተጠሪዎች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ገብተው ለመማር የተቀመጡትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልተውና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ስርዓቱን በተከተለ አግባብ ስልጠናውን ተከታትለው የጨረሱ መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ይህንኑ የሚያረጋግጥላቸውን ማስረጃ ከአመልካች የማግኘት መብት ያላቸው ስለሆነ የበታች ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገሩን በአግባቡ አጣርተውና አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ተጠሪዎች ኦርጂናሉ ዲፕሎማ ሊሰጣቸው ይገባል በማለት መወሰናቸው ሕጋዊ ነው ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልተቻለም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ውሣኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 81505 ጥቅምት 18 ቀን 2006 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር143008 መጋቢት 23 ቀን 2006 ዓ/ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪዎች ኦርጂናል ዲፕሎማ የመስጠት ግዴታ አለበት ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

***መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡***

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች አለበት**

**የ/ባ**

የሰ/መ/ቁ. 102061

የካቲት 06 ቀን 2007 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሀመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

**አመልካች፡-** የከሰረው ሆላንድ ካር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ጠበቃ ግርማ አለሙ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ዘመን ባንክ /አ.ማ/ ነገረ ፈጅ አቶ አዳም ሰገድ በላይ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር 140316 ግንቦት 5 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101131 ግንቦት 28 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የእግድ ትእዛዝ መነሳትን የሚመለከት ነው፡፡

1. የክርክሩ መነሻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 200820 ተጠሪ የከሰረው የሆላንድ ካር ኃ/የተ/የግል ማህበር ንብረት ታግዶ እንዲቆይ የሰጠውን ትእዛዝ እንዲያነሳለት ጥያቄ አቅርቦ የስር ፍ/ቤት የእግድ ትእዛዝ የሚነሳበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ ነው፡፡ አመልካች የስር ፍ/ቤት የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ሲነሳና በመያዣነት የያዝኳቸውን ንብረቶች በአዋጅ ቁጥር 97/1990 እንደተሻሻለው በተሰጠኝ ስልጣን መሠረት ንብረቶቹን በሀራጅ ለመሸጥ ለብድሩ መክፈያነት ሳውል ይገባል በማለት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ፍ/ቤት የዕግድ ትእዛዝ ተነስቶ ተጠሪ በመያዣነት የያዘውን ንብረት በአዋጅ ቁጥር 97/1990 በአዋጅ ቁጥር 216/1992 እንደተሻሻለው በተደነገገው መሰረት ንብረቶቹን በሀራጅ ሸጦ ለዕዳው መክፈያ ሊያደርግ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡
2. አመልካች ሰኔ 9 ቀን 2006 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 97/1990 እና አዋጅ ቁጥር 216/1992 ስለመክሰር የሚደነግግ ድንጋጌዎች የሉትም፡፡ በመክሰር ጉዳይ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው የንግድ ህጉ ነው፡፡ የከሰረው ድርጅት ንብረት በንግድ ህጉ መሰረት እንዲጣራና እንዲሸጥ መደረጉ፣ የሁሉንም ገንዘብ ጠያቂዎች መብትና ጥቅም የሚያስከብርና ተጠሪም በመያዣው ላይ አለኝ የሚለውን መብት የማያሳጣው በመሆኑ በተናጠል ንብረት ለመሸጥ ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል፡፡ ባለዕዳው የተጠሪ

እዳ ከመክፈሉ በፊት ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ሊከፈሉ የሚገባ የሰራተኞች ደመወዝ ሌሎች ክፍያዎችና የመንግስት ግብር በአግባቡ ተጣርቶ ባልተለየበት ሁኔታ፣ ተጠሪ መያዥያ በተናጠል እንዲሸጥ ያቀረበውን ጥያቄ መፍቀድ የህጉን ዓላማ የማያሳካ በመያዥያ ያልተያዙ የባለ እዳውን ንብረቶች ለብክነት የሚዳርግና ጥበቃው ከፍተኛ ወጪ እንዲያስወጣ የሚያደርግ ነው፡፡ ስለዚህ እግዱ እንዲነሳ የተሰጠው ውሳኔ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

3. ተጠሪ ነሀሴ 27 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ መልስ አዋጅ ቁጥር 97/1990 እና አዋጅ ቁጥር 216/1990 አንድ የንግድ ድርጅት ሳይከስርም ሆነ መክሰሩ በፍርድ ከተረጋገጠ በኃላ ባንኮች ብድር ሲያበድሩ በመያዣነት የያዙትን ንብረት በሀራጅ ሸጠው የዕዳው መክፈያ እንዲያደርጉ ታስበው የታወጁ ህጎች ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ተጠሪ ለከሰረው ሆላንድ ካር ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ገንዘብ ሲያበድር በመያዣነት የያዘውን የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት በሀራጅ ለመሸጥ ያቀረበውን ጥያቄ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ትእዛዝ ስህተት የለበትም የሰራተኞች ደመወዝና የመንግስት ግብርን በተመለከተ ተጠሪ በሀራጅ ንብረቱን ሲሸጥ በራሱ የሚከፍላቸውና የሚፈጽማቸው ግዴታዎች በመሆናቸው አመልካች መከራከሪያ አድርጎ ማቅረቡ የህግ መሰረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ተጠሪ በመያዥያነት ይዥዋለሁ የሚለውን ፋብሪካ ህንጻና ማሽነሪዎች በተናጥል ከሸጠ፣ ያልተገጣጠሙ መኪናዎችን ገጣጥሞ ለመሸጥና ለእዳው መክፈያ ለማድረግ የማያስችል ነው፡፡ የሰራተኞቹን የቀዳሚነት መብትና የመንግስትን ግብር በቀዳሚነት የመክፈል ግዴታ ለመወጣት የማያስችል በመሆኑ የዕግድ ትእዛዝ ጸንቶ ሊቆይ ይገባል በማለት መስከረም 30 ቀን 2007 ዓ/ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከስር የክርክር አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጹሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የከሰረው ሆላንድ ካር መኪና መገጣጠሚያ ድርጅት የሚንቀሳቀስ ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥና ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የስር ፍ/ቤት የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቶ ተጠሪ በተናጥል በመያዥያ የያዘውን የፋብሪካ ህንፃና ማሽነሪ በሀራጅ እንዲሸጥ የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ባንኮች ያበደሩት የብድር ገንዘብ በወቅቱ ሳይከፈላቸው በሚቀርበት ጊዜ በመያዥነት የያዙትን ንብረት በሀራጅ በመሸጥ ብድራቸውን እንዲከፈል ለማድረግ የሚያስችላቸው ስልጣንና ስርዓት በአዋጅ ቁጥር 90/1997 በአዋጅ ቁጥር 216/1998 እንደተሻሻለ በአዋጅ ህግ አውጭው ደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል አንድ የንግድ ድርጅት መክሰሩ በፍርድ ተረጋግጦ ከተወሰነ በኃላ ከከሰረው የንግድ ድርጅት ገንዘብ የመጠየቅየቀዳሚነት መብት ያላቸው አበዳሪዎች እና ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችልበት ዝርዝር አሰራር በንግድ ህጉ በአምስተኛው መፅሐፍ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡

6. በያዝነው ጉዳይ አመልካችንና ተጠሪ የሚከራከሩበት በጉዳዩ ተፈፃሚነት ሊሰጠው የሚገባው አዋጅ ቁ.97/1990 እንደተሻሻለ መሆን ይገባል? ወይስ በንግድ ህጉ አምስተኛው መጽሐፍ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ሊሆን ይገባዋል የሚለውን መከራከሪያ በማንሳት ነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍ/ቤት የሰጠው የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ ውሳኔ የሰጠው አዋጅ ቁጥር 97/1990 እና አዋጅ ቁጥር 216/1992 ከንግድ ህጉ

አምስተኛ መጽሀፍ ከተደነገጉት ድንጋጌዎች በኃላ የወጡ ስለሆነ ተፈፃሚነትና ገዥነት አላቸው በማለት ነው፡፡ አመልካች የሚከራከረው ከአዋጅ ቁጥር 97/1990 እና አዋጅ ቁጥር 216/1992 ስለመክሰር የሚመለከት ድንጋጌ የላቸውም የከሰረ የንግድ ድርጅት ንብረት ስለሚሸጥበትና የቀዳሚነት መብት ላላቸው ለሌሎች የገንዘብ ጠያቂዎች የሚከፍልበትን ስርዓት የሚደነግጉ ልዩ ድንጋጌዎችን የያዘው የንግድህጉ አምስተኛው መጽሀፍ በመሆኑ፣ በዚህ ጉዳይ ተፈፃሚነት ሊኖራቸው የሚገባው የንግድ ህጉ ልዩ ድንጋጌዎች ናቸው በማለት ነው፡፡ ይህም ተጠሪ በኃላ የወጣው ህግ በፊት ከወጣው ህግ ላይ የበላይነትና ተፈፃሚነት አለው የሚለውን የህግ አተረጓጎም መርህ መሰረት በማድረግ የሚከራከር መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ልዩ የህግ ድንጋጌዎች በጠቅላላ የህግ ድንጋጌዎች ላይ የበላይነትና ተፈጻሚነት አላቸው የሚለውን የህግ አተረጓጎም መሰረት በማድረግ የሚከራከር መሆኑን ተረድተናል፡፡

7. በእኛ በኩል በዚህ መዝገብ አመልካችና ተጠሪ ለሚከራከሩበት ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው አዋጅ ቁጥር 97/1990 እንደተሻሻለ መሆን ይገባዋል ወይስ የንግድ ህጉ አምስተኛው መጽሀፍ የሚለው ምርጫ ከመምረጥና አመልካችና ተጠሪ ከጠቀሳቸው የአተረጓጎም መርሆች በላይ የሆኑ በርካታ ሁኔታዎቹን በመመርመር እና መመዘን የሚጠየቅ ሆኖ አግኝተነዋል ይኸውም ተጠሪ በተናጥል የከሰረውን የሆላንድ ካር የመኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ ህንጻና ማሽነሪዎች በሀራጅ እንድሸጥ ቢደረግ የከሰረው የሆላንድ ካር ንብረት ተሸጦ በሚገኘው ገንዘብ ላይ ከተጠሪ በፊት የቀዳሚነት መብት ያላቸውን የሰራተኞችና የመንግስት የግብር ዕዳ ለማጣራትና ለመክፈል የማያስችል መሆኑን አለመሆናቸውን የከሰረው ድርጅት ንብረት ጠባቂና መርማሪ ዳኛ ተጣርቶ እንዲሸጥ መደረጉ ተጠሪ በመያዣነት በያዘው ንብረት ላይ ያለውን ልዩና የቀዳሚነት መብት የሚያሳጣ መሆኑን ወይስ አለመሆኑን እንደዚሁም የከሰረው ድርጅት ንብረት በንብረት ጠባቂና መርማሪ ዳኛ በኩል ተጣርቶ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በፍርድ ቤት ፈቃድና ትዕዛዝ መሰረት እንዲሸጥ መደረጉ የቀዳሚነት መብት የሌላቸውን ገንዘብ ጠያቂዎች መብትና ጥቅም በተሻለ ሁኔታ ለማስከበርና ዕዳቸው እንዲከፈላቸው ለማድረግ የሚያስችል ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መንገድ ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

8. ከዚህ አንጻር ሲታይ፣ተጠሪ በመያዣነት የያዘውን የፋብሪካ ህንጻና የመኪና መገጣጠሚያ ማሽነሪ በተናጥል የሀራጅ ማስታወቂያ አውጥቶ እንዲሸጥ ቢደርግ የከሰረው ድርጅት ሰራተኞች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 167 የተሰጣቸውን የቀዳሚነት መብት በተሟላ ሁኔታ ለማጣራትና የሰራተኞች ጥያቄ ከተጠሪ በፊት ተከፋይ እንዲሆን በማድረግ የሚያስችል አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 በተናጠል የሚያከናውነው የሀራጅ ሽያጭ፣ መንግስት ከከሰረው ሆላንድ ካር መኪና መገጣጠሚያ ድርጅት የሚጠይቀውን ትክክለኛ የግብር ዕዳ በተሟላ ሁኔታ ለማጣራትና ለመወሰን እንደዚሁም ከድርጅቱ ሰራተኞች ቀጥሎ ከተጠሪ በፊት መንግስት ያለውን የቀዳሚነት የግብር እዳ የመጠየቅ መብት የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በተናጥል የሚያከናውነው የሀራጅ ሽያጭ ለሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች እዳ መክፈያ ሊሆኑ የሚችሉ ያልተገጣጠሙ መኪናዎች እና ሌሎች ንብረቶች ባለበት ሁኔታ በመጠበቅ ሸጦ የሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎቹን ዕዳ ለመክፈል የማያስችል መሆኑን ተጠሪ በመያዣነት ያልያዛቸውን የከሰረው ሆላንድ ካር ንብረቶች ለማጓጓዝና ለማስቀመጥ ተጨማሪ ወጪ የሚጠይቅና የሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች መብትና ጥቅም የሚጎዳ መሆኑን ግራ ቀኙ ካቀረቡት ክርክር ተረድተናል፡፡

9. በአንጻሩ ተጠሪ በመያዣነት የያዘው የፋብሪካ ህንጻና ማሽነሪዎች ከሌሎች የከሰረው ሆላንድ ካር ንብረት ጋር ተጣርተው እንዲሸጡ ቢደረግ አመልካች በመያዣነት ይዟቸው የነበሩት ንብረቶች ተሸጠው በሚገኘው ገንዘብ ላይ ያለውን የቀዳሚነት መብት የማያሳጣው መሆኑን ከንግድ ህጉ አንቀጽ 104 እና ሌሎች ተከታይ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሂደቱ ከንብረት ጠባቂና መርማሪ ዳኛ በላይ የሆኑ ጉዳዮች ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት እየታዩ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለማድረግ የሚያስችል አማራጭ እንደሆነ ከንግድ ህጉ አንቀጽ 989 እና አንቀጽ 990 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የማጣራትና የሽያጭ ሂደቱ፣ ተጠሪ በመያዣነት የያዘው የፋብሪካ ህንጻና የመኪና መገጣጠሚያ ማሽነሪ በተናጠል ይሆን ከሌሎች የከሰረው የሆላንድ ካር ንብረቶች ጋር በአንድ ላይ የሚጣራበት የሚከናወነበትንና በመጀመሪያ ከተጠሪ በፊት የቀዳሚነት መብት ያላቸው የድርጅቱ ሰራተኞች ጥያቄና የመንግስት የግብር ዕዳ ተከፍለው የተጠሪ ቀዳሚነት መብት ተጠብቆ መያዣው ተሸጦ የተገኘው ገንዘብ እንዲከፈለው መደረጉ ከተጠሪ በፊት የቀዳሚነት መብት ያላቸውን ገንዘብ ጠያቂዎች የተጠሪንና የሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች መብትና ጥቅም የሚያስከብርበመሆኑ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት አዋጅ ቁጥር 97/1990 በንግድ ህጉ አምስተኛ መጽሀፍ በኃላ የታወጀ ነው በሚል ምክንያት የዕግድ ትእዛዝ እንዲነሳ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ በመያዣነት በያዛቸው የፋብሪካ ህንፃና የመኪና መገጣጠሚያ ማሽነሪዎች በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ለመሸጥና ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ የስር ፍ/ቤት የሰጠው የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳለትያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ነው በማለት ወስነናል፡፡ ንብረቶቹ እንዲከበሩየስር ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ በመያዣው ላይ ያለው መብት እንዲከበር የከሰረው ሆላንድ ካር ሂሳብ ተጣርቶ ንብረቶቹ ተሸጠው በመያዣው ላይ ያለው የቀዳሚነት መብት እንዲከበርለንብረት ጠባቂ ለመርማሪ ዳኛና ስልጣን ላለው ፍ/ቤት በህግ አግባብ የማቅረብ መብቱን ይህ ውሳኔ የሚገድበው አይደለም ብለናል፡፡
4. ጉዳዩ የተጠሪ የመያዣ መብት ያለበት በመሆኑ በተቀላጠፈ መንገድና በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊፈጸም ይገባል ብለናል ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ውጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

የሰ/መ/ቁ 106286

መጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

አመልካች፡- ቦሮ ትራቪል የግንባታ ሥራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር ነገረ ፈጅ ም/ስ አስኪያጅ

ታከለ ንጉሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ኤፍሬም ሽብሩ - ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው የሥር ፍርድ ቤቶች ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው ጉዳይ በመጀመሪያ ወደ ፍርድ ቤት ከመሄዱ በፊት በሽምግልና ዳኞች መታየት ነበረበት የሚለውን የአመልካች ክርክር ነጥብ ውድቅ በማድረግ ጉዳዩ በፍርድ ቤት እንዲታይ ብይን የመስጠታቸው አግባብነት አመልካች ከመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41(1) አንፃር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ለመመርመር ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በቤንሻጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት ያቀረቡት ክስ ከማህበሩ መሥራች አባልነት ያለአግባብ መሰረዛቸው እና የቼክ ፈራሚነታቸው ያለአግባብ እንደተነቀሉ የሚገልጽ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካች ጉዳይ ከአሁኑ በፊት በፍርድ ያለቀ ነው፤ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሽምግልና ዳኞች መታየት አለበት የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኃላ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው የሚል ክርክር ውድቅ ያደረገ ሲሆን፤ ጉዳዩ በመጀመሪያ ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሽምግልና ዳኞች መታየት አለበት የሚለውን የአመልካች ክርክር በመቀበል በማህበራቸው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 መሰረት በሽምግልና ዳኞች መታየት እንዳለበት ብይን ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ግራቀኙ በማከራከር የግራ ቀኙ መተዳደሪያ ደንብ ሽምግልናን እንደ አንድ አማራጭ ማስቀመጡ ጉዳዩ በፍርድ ቤት እንዲታይ መስማማታቸውን አያሳይም በማለት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በስር

ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት አይደለም በማለት መወሰኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ትዕዛዝ በመስጠቱ ግራቀኙ የጽሑፍ ክርክር ያደረጉ ሲሆን አመልካች በሰበር አቤቱታው የጠቀሳቸው አንኳር ነጥቦች፡- መተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 41 በአባላት መካከል የሚፈጠር አለመግባባት በእርቅ፣በሽምግልና እንዲታይ የተደነገገው በሥር ፍርድ ቤቶች መታለፉ አለአግባብ መሆኑን፤የግራቀኙ ስምምነት ደግሞ ሕግ መሆኑን ለመግለጽ ውሳኔ እንዲሻር መጠየቃቸውን የሚያሳይ ሲሆን የተጠሪ መልስ መሠረታዊ ይዘትም፡- በማህበሩ እና አባላት መካከል የሚነሳው ክርክር በሽምግልና እንደሚፈታ የተገለጸ ቢሆንም ብቸኛ አማራጭ አለመሆኑን፤ በክልሉ መንገዶች ባለሥልጣን የበኩሉን ጥረት ማድረጉን፤አዋጅ ቁጥር 147/91 ተፈፃሚነት እንደሌለው፤ ማህበሩም ሕልውና እንደሌለው ጉዳዩም በሽምግልና እንደማይፈታ በመግለጽ ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረባቸው ተገቢ መሆኑን ተከራክሯል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ ያቀረቡ ሲሆን የሰበር አቤቱታቸው የሚጠናከር ነው፡፡

ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር፣ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ፤አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከሥር የክርክር ሂደት መረዳት እንደተቻለው አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የግራ ቀኙ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 ለክርክሩ መሰረት የሆነውን ጉዳይ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሽምግልና ዳኞች መታየት ነበረበት በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ጉዳዩ በቀጥታ ፍርድ ቤት እንዳይቀርብ የሚከለክል ስምምነት የሌለ መሆኑን ነው፡፡ የግራ ቀኙ መሰረታዊ የክርክር ነጥብ እልባት ለመስጠት የቦሮ ትራብል የግንባታ ሥራዎች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መተዳደርያ ደንብ አግባብነት ያለው ድንጋጌ መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ መመርመሩ ተገቢ ይሆናል፡፡ የአመልካች ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 በአባልነትና በማህበሩ መካከል የሚነሱ ክርክሮች የሚፈቱበትን አግባብ ደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንኡስ አንቀጽ 1 ሥር እንደተመለከተው አከራካሪ ጉዳዮች የሚነሱ ከሆነ የድርጅቱ ሥራ አመራር ኮሚቴ በሚያመቻቸው በአስታራቂ ሽማግሌዎች በዕርቅ እንዲያልቅ እንደሚደረግ ተመልክቷል፡፡ ክርክሩ በዕርቅ ያላለቀ እንደሆነ ጉዳዩ በሽምግልና ዳኞች ይታያል፡፡ ጉዳዩ በሽምግልና ዳኞች የማይፈታ ከሆነ በአገሪቱ በህግአግባብ እንደሚታይ በዚህ ደንብ አንቀጽ 42.2 ሥር በግልጽ ተጠቅሷል፡፡

ከአመልካች የመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 እና 42 ለመረዳት እንደተቻለው በአባልነትና በማህበሩ መካከል የሚነሱ ክርክሮች ለመፍታት ሦስት መንገዶች የሚከተል መሆኑን ነው፡፡ የመጀመሪያው እርቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሽምግልና ዳኞች አማካይነት ነው፡፡ ሦስተኛ እና የመጨረሻው አማራጭ በአገሪቱ በህግ አግባብ የሚል ሲሆን ይህ አማራጭ በቀጥታ ፍርድ ቤት የሚል ግልጽ መልስ የሚሰጥ ባይሆንም በሌሎች ሕጎች ጉዳዩ ለሌላ ተቋም ካልተሰጠ በስተቀር የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ከመሆኑ አኳያ ፍርድ ቤት የሚል ትርጉም ሊሰጠው የሚችል ስለመሆኑ ከአጠቃላይ የድንጋጌው መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ ተጠሪ ጉዳዩን በቀጥታ ፍርድ ቤት ማቅረቡ ደንቡን የሚቃረን አለመሆኑን እየተከራከረ ነው፡፡ አመልካች በአንፃሩ ጉዳዩ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሽምግልና መታየት ነበረበት የሚል ክርክር በአፅንኦት አቅርበዋል፡፡ በመሰረቱ ተዋዋዮች ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በሽምግልና ለማየት ከስምምነት ላይ ሊደርሱ ይችላሉ የተዋዋይ ወገኖች

ስምምነት በሕጉ አግባብ የተቋቋመ ከሆነ አስገዳጅ ስለመሆኑ በፍ/ህ/ቁ 1731(1) ተመልክቷል። በተዋዋይ ወገኖች የሚነሳው የውል አተረጓጎም ክርክርም የውሉ መሰረታዊ ይዘትና ዓላማ መሰረት በማድረግ መታየት እንዳለበት በፍ/ህ/ቁ 1732፣ 1736 እና 1738 በግልጽ ተደንግጓል ። በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 በማሕበሩ አባላት እና ድርጅቱ ሊነሱ የሚችሉ ክርክሮች በመጀመሪ በዕርቅ መፈታት እንዳለባቸው የተደነገገ ሲሆን የዕርቅ ስምምነቱ ውጤት ካላመጣ ደግሞ የሽምግልና ዳኞች እንደሚሰየሙ ተመልክቷል ። እነዚህ ሁሉ ጥረቶች ውጤት ካላስገኙ የመጨረሻው አማራጭ ጉዳዩ በአገሪቱ ሕግ የሚፈታ መሆኑ ተገልጸዋል።

የአሁኑ ተጠሪ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ጉዳዩ በዕርቅ ለመጨረስ ጥረት ስለማድረጋቸው የቀረበ ክርክር የለም። በእርግጥ የቤንሻንጉል ጉምዝ መንገዶች ባለሥልጣን በፃፈው ደብዳቤ ጉዳዩ በሕግ አግባብ እንዲታይ መግለጽን ተጠሪ ቢከራከሩም የተጠሪ ክርክሩ በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 መሰረት በዕርቅ ለመጨረስ የተደረገ ጥረት ስለመኖሩ የሚያሳይ አይደለም ። ተጠሪ ሌላ ያነሱት ነጥብ ማህበሩ ሕጋዊ ሰውነቱን አጥቷል የሚል ቢሆንም አመልካች ወክለው እየተከራከሩ ያሉት ምክትል ስራ አስኪያጅ እና ባለአክሲዮን መሆናቸው የተካደ ጉዳይ አይደለም ። የማህበሩ ሕልውና በሕግ አግባብ ስለመክሰሙም በሕግ የተደገፈ ክርክር አልቀረበም።ተጠሪ የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 የተዘረጋውን ሥርዓት በአግባቡ ሳይጠቀሙ እና አለመግባባቱን ለመፍታት ጥረት ሳያደርጉ ጉዳዩን በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት መውሰዳቸው ከላይ የተመለከተው መተዳደሪያ ደንብ ያላገናዘበ ነው።

የሥር ፍርድ ቤት ሽምግልናን እንደ አማራጭ የተወሰደ ነው በማለት በውሳኔው የገለጸ ቢሆንም የአመልካች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 እንደተመለከትነው በድርጅቱ እና በማህበሩ የሚከሰት አለመግባባት የሚፈታበት ሥርዓት ቅደም ተከተል ማስቀመጡን መገንዘብ ይቻላል። ተጠሪ በደንቡ የተዘረጋውን የክርክር አፈታት ሥርዓት ሳይከተል በቀጥታ በፍርድ ቤት ክስ ማቅረቡ የተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ያላገናዘበ ነው። በመሆኑም የግራቀኙ ክርክር በመጀመሪያ በእርቅ፣በሽምግልና ሳይታይ በቀጥታ በፍርድ ቤት መታየት ይችላል ተብሎ በሥር ጠቅላይ ፍርድ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት መወሰኑ እና በሰበር ሳይታረም መጽናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል።

በማጠቃለል የሥር ፍርድ ቤቶች ተጠሪ ጉዳዩን በዕርቅ እና በሽምግልና ሳይታይ በቀጥታ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል በማለት የሰጡት ብይን የአመልካች መተዳደርያ ደንብ አንቀጽ 41 እና 42 ያስቀመጣቸው የክርክር አፈታት ቅደም ተከተል ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ተከታዩን ወስነናል፡

<u>**ውሳኔ**</u>

1. የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 05440 በ 07-11-2006 ዓ.ም የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 08575 በ 21-09-2006 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በመሻር የሰጠው ፍርድ፤የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 05591 07/02/2007ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) ተሽሯል። ይፃፍ።
2. የአሶሳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 08575 በ 21/09/2006 የሰጠው ብይን ጸንቷል። ይፃፍ።

3. አመልካች እና ተጠሪ እያከራከረ ያለው ጉዳይ በአመልካች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 41 መሰረት በተዘረጋው ሥርዓት በዕርቅ፣ሽምግልና ሳይታይ በቀጥታ ፍርድ ቤት መቅረብ አይችልም በማለት ወስነናል፡፡
4. ግራ ቀኙ በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

**ትዕዛዝ**

- በዚህ ችሎት የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
- መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ተመለሰ፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**